አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ

በ

ተመስገን በየነ

ሐምሌ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ

ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በፎክሎር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ

ተመስገን በየነ

አማካሪዎች

ዓለሙ ካሣዬ (ዶ/ር)

ጥላሁን ተሊላ (ዶ/ር)

ሐምሌ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

### የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ትንተና

### በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ

ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ለፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በተመስገን በየነ

ሐምሌ 2012 ዓ.ም

<u>የፈተና ቦርድ አባላት</u>

| የአማካሪዎች ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| ዶ/ር ዓለሙ ካሣዬ | ፊርማ:- ___________ | ቀን:- ___________ |
| ዶ/ር ጥላሁን ተሊላ | ፊርማ:- ___________ | ቀን:- ___________ |

| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| [illegible] | ፊርማ:- ___________ | ቀን:- 3/2/13 |

| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| ___________ | ፊርማ:- ___________ | ቀን:- ___________ |

## ምስጋና

ይህ ጥናት ከታቀደበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ፤ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ረቂቁን አንብበው፤ የጎደለውን አሟልተው፣ የተዛባውን አስተካክለው እና የረሳሁትን አስታውሰው ሙያዊ ዕገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዎቼ ለዶ/ር ዓለሙ ካሣዬ እና ለዶ/ር ጥላሁን ተሊላ ልባዊ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የመስክ መረጃዎችን፤ በቅንነት፣ በይሁንታ እና በታዛዥነት በመስጠት እገዛ ላደረጉልኝ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ አባላት በሙሉ፤ በተለይ ለዐቢይ የባህል ሕክምና መረጃ ሰጪዎቼ ለመሪጌታ ዘላለም ባየህ፣ ለመሪጌታ ፋንታሁን ታዬ፣ ለአቶ ጌጡ ነጋሽ፣ ለመሪጌታ ባሕረጥበብ፣ ለአቶ ደሴ ገብሩ፣ ለመሪጌታ መኅሪ መስፍን፣ ለመሪጌታ አማረ አስፋው፣ ለመሪጌታ ፍሬስብሃት ወንድይራድ፣ ለሊቀጠበብት አብርሃም ዓለምነህ፣ ለአቶ ደርሶ ገዜ፣ ለመሪጌታ ስዩም ዓለሙ፣ ለመሪጌታ ስንታየሁ ሰሎሞን፣ ለመሪጌታ መንግስቱ ጫቅሌ እና ለቄስ አብርሃም አክሊሉ፤ እንዲሁም ለአጋዥ መረጃ ሰጪዎቼ ምስጋናዬ ባሉበት ይድረሳቸው።

የባህል ሕክምና ልማድን፣ ዕውቀትና ተግባርን እንዳጠና ላበረታታኝና አዎንታዊ ተፅእኖ ላሳደረብኝ የባህል ሐኪም አባቴ ደብተራ በየነ አበጋዝ፤ ነባር የባህል ሐኪሞችን በማስተዋወቅ እና የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ ከደቡብ ጎንደር ዞን (ወረዳዎች) የባህል ሕክምና ተጠሪዎች ጋር በማገናኘት እገዛ ላደረጉልኝ፤ የኢትዮጵያ ባህላዊ መድኃኒት ሕክምና አዋቂዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ሃጂ ሼህ አሊ ዓደም፤ በመስክ ቆይታዬ በየአካባቢው ስንቀሳቀስ የባህል ሐኪሞችን በማገናኘት፣ የአካባቢውን ባህልና እምነት ያውቃሉ የሚባሉ ግለሰቦችን በማስተዋወቅ አብረው/ኝ ለደከሙ፤ ለአቶ አበበ ጋሻዬ፣ ለአቶ አራጋው ዘውዴ፣ ለአቶ ደስታው አባይነህ፣ ለአቶ ሰሎሞን ካሳ፣ ለአቶ አዲሱ አዝመራው እና ለአቶ አባይነህ አድማስ፤ በአላችሁበት ቦታ እግዚአብሔር እድሜና ጤና ይስጥልኝ፤ ውለታችሁን ይክፈላችሁ።

በደረጃ ማበልፀጊያ ወቅት የጥናቱን ስድስት ምዕራፎች አንብባችሁ፤ ምሁራዊ አስተያየታችሁን ያለገደብ ለሰጣችሁኝ ዶ/ር የኔዓለም አረዶ እና ዶ/ር ሙሉጌታ ነጋሳ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የትምህርት እድል በመስጠት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የገንዘብ ድጎማ በማድረግ፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

መምህራንና አስተባባሪዎች ላደረጋችሁልኝ የሃሳብና የሞራል ድጋፍ አመሰግናለሁ። በተለይ የጥናት ፌር፣ አቅጣጫና አድማስን በማመላከት ዕውቀትን ከሥነ ምግባር ጋር ላካፈላችሁኝ ለዶ/ር ባይለየኝ ጣሰው እና ለዶ/ር መርሻ አለኸኝ፤ ፈጣሪ እድሜና ጤና ይስጥልኝ።

ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ ዲን ዶ/ር ዳዊት አሞኘ፤ ቢሮና መሰል ግብዓቶችን በመፍቀድ፤ በተከታታይ ዓመት (2011 እና 2012 ዓ.ም) የጥናት ሥራዬን በዩኒቨርሲቲው ዐውደ ጥናት ላይ እንዳቀርብ አስፈላጊውን ትብብር ማድረጉ፤ ዋቢ ፅሁፎችን በመጠቆምና በመስጠት የዘወትር ድጋፋችሁ ላልተለየኝ፤ ለፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል አባላት በሙሉ፤ በተለይ ለዶ/ር ዋልተ ንጉስ መኮንን (ሙያዊ ዕውቀትህን፤ የዕይታ አድማስህን፤ ጊዜህን በመስጠት አማክረህ፤ የጥናቱን ዐምድና ቅርፅ በማሲያዝ እገዛ በማድረግህ)፣ ለዶ/ር ዐቢዩ አስማማው (በባህል ሕክምና ላይ የተደረጉ ምርምሮችን በመስጠትህ)፣ ለአቶ ሞገስ ሚካኤል (ይህ ጥናት ሲታቀድና ሲተገበር ከጥንስሱ እስከ ውልደቱ ነበርክ፤ የተባ አንደበትህን! ሙያዊ ዕውቀትህን ሳትሰስት በመለገስህ)፤ ለአቶ ሃብታሙ አቃናው (በጭንቁ ሠዓት ደርሰህ፤ ሰዉ በጠፋበት ዋስ ሆነህ ተረጋግቼ እንድማር እድሉን ስላመቻቸህ፤ መጻሕፍትን በማዋስና ሙያዊ አስተያየት በመስጠትህ)፤ ለአቶ ሳምሶን አየለ (የምርምር ሥራዬን አጠናክሬ እንድቀጥል በሃሳብ፣ በገንዘብ እና በጉልበት እገዛ በማድረግህ)፤ በአላችሁበት ቦታ እድሜን ከጤና ጋር ይስጥልኝ።

ፀሐይ! እኔማ ያላንቺ ማን አለኝ? ይህ ውጤት ስኬት ከተባለ ያንቺ ነው (በሃሳብ፣ በጉልበትና ረቂቁን በማንበብ እገዛ ማድረግሽ)። ብቻሽን "ማሬን" ተንከባክበሽና አሳድገሽ፤ ቤታችንን መርተሽ፤ የቢሮ ሥራሽን ተወጥተሽ፤ "በርታ ውዴ!" ከማለት በስተቀር ቅር ሳይልሽ ጥንካሬን፣ ትዕግስትና ተስፋን ላስተማርሽኝ፤ የእናቴ አምሳል ባለቤቴ ለሁሉም ነገር ክብርና ፍቅር ይገባሻል። ልጄ ለማርያም! ከቤት ስውጣ ለቅሶሽ፤ ስመለስ ደስታሽ፤ እንደ ሰው ፊቴ ቆሞ ያናግረኛል። አጠገብሽ ተገኝቼ የአባትነቴን ድርሻ ባለመወጣቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ፤ ለትዕግስታችሁ በጣም አመሰግናለሁ።

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት “የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኀበረሰብ” በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፤ የጥናቱ ዐበይት ጥያቄዎች፤ የባህል ሕክምና ዕውቀትና ትግበራ በምን ዓይነት የሥነ ምህዳር ዐውድ ላይ ተመስርቶ ይከወናል? የዕውቀቱ ማሕቀፍ እስከ ምን ይደርሳል? የሚሉ ይዘቶችን በማንሳት ለመፈተሽ የታለመ ነው። የምርምሩ ዐቢይ ዓላማ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኀበረሰብ የሚካሄደውን፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን መመርመር ነው። ጥናቱ፤ የሕመም መንስኤ እሳቤን መግለጽ፤ የበሽታ መለያና መመርመሪያ ዘዴዎችን ማብራራት፤ የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔን መተንተን፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን አስተዋጽኦ መለየት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን አካቷል። እነዚህን ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የመስክ መረጃዎች፤ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታ፣ በቡድን ተኮር ውይይት እና በንጥል ጥናት ዘዴዎች ተሰብስበው፤ በማስታወሻ፣ በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ ተሰንደዋል። የመስክ መረጃ ሰጪዎች፤ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ብቻ ታላሚ በማድረግ (ከሶስት ወረዳዎች 76 ሰዎች) በዓላማ ተኮር እና በአጋዥ ጠቋሚ ናሙና ስልት ተመርጠዋል። ከዐብይና አጋዥ መረጃ ሰጪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች፤ በይዘትና በምድብ ተደራጅተው፤ ዓይነታዊ የምርምር ይዘትን በመከተል በሥነ ዕውቀት እና በማኀበራዊ ግንባታ፣ በዐውድ-ተኮር ክዋኔ እና ሕዝባዊ የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ፤ ከዐውድ-ተኮር ክዋኔ፣ ከተፈጥሮ ባሕርይ እና ከባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴሎች አንፃር በመፈተሽ፤ በገላጭ፣ በይዘት ትንተና እና ትርጓሜ (Interpretation) ስልት ተተንትነው ቀርበዋል። በትንታኔው መሰረት በደቡብ ጎንደር ዞን ማኀበረሰብ /በባህል ሐኪሞች/ እሳቤ፤ የሕመም መንስኤዎች ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ የመሬት እና የዐየር ጋኔል ተደርገው እንደሚታሰቡ፤ በጥናቱ ተረጋግጧል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች ዓለማዊና መንፈሳዊ የምርመራ ዘዴዎችን በመተግበር፤ የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ባሕርያትን (ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃና መሬት) በመከተል እና የበሽታ ባሕርይ ምድቦችን በማጤን ድንገተኛና አጣዳፊ፣ ቆንጣጭና ሰርሳሪ፣ አቃጣይና አስለፍላፊ፣ አብራጅና አድካሚ፣ አንቀጥቃጭና አርገብጋቢ፣ አደንዛዥ እና አወፋሪ በማለት፤ አካልን የሚያደቁ (ለቁስል) እና መንፈስን የሚያስጨንቁ የሕመም ዓይነቶችን እንደሚፈውሱ፤ ጥናቱ ጠቁሟል። የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ፤ ከባህል መድኃኒት ግብዓት አሰባሰብ እስከ መድኃኒት አሰጣጥ ድረስ ሲተገበር፤ በሥርዓተ ገቢር እና በፀሎት የሚመራ፣ በዐውድ (በቀን፣ በሠዓት፣ በጊዜ፣ በቦታና በሁነት) የተወሰነ፣ በድርጊት የታጀበና የተገደበ፣ ብላ/ አትብላ፣ አድርግ/ አታድርግ መመሪያና ገደቦችን በመከተል ይፈፀማል። የመድኃኒት ቅመማ ሂደቱም፤ በማጠብ፣ በማድረቅ፣ በመልቀም፣ በመከትከት፣ በመጨቅጨቅ፣ በመውቀጥ፣ በመፍጨት፣ በመንፋት፣ በመቀቀል፣ በማንጠርና በማሸግ ወደ መድኃኒት አሰጣጥ ይሸጋገራል። የመድኃኒት አሰጣጥ ሥርዓቱም፤ በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚታጠን፣ በሚጨስ፣ በሚቀባና በሚቀበር ይዘት እንደሚከወን፤ ጥናቱ አረጋግጧል። በመጨረሻም የባህል ሐኪሞች እምነት፣ ዕውቀትና ተግባር ለዕፅዋትና እንስሳት ጥበቃ በማድረግ፤ በአድባራት፣ በገዳማት፣ በፀበልና በደብር ቦታዎች የመትከል፣ የመዝራትና የማባዛት ልማድ መኖር ለአካባቢ ሥነ ምህዳር ጥበቃ አበርክቶ ሲያደርግ፤ የዕፅዋትና የእንስሳት ንግድ፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የከተማ መስፋፋት፤ ለዕፅዋትና እንስሳት መጥፋትና መሰደድ፣ ለሥነ ምህዳር ሚዛን መዛባት መንስኤ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል። ይህን ጉዳይ ታሳቢ በማድረግ፤ የባህል ሕክምና ዕውቀትን ከሥነ ምህዳር ይዘት ጋር በማስተሳሰር፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች፣ የአካባቢው ማኀበረሰብና አመራር አካላት፤ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ቢወያዩና የጋራ መፍትሔ ቢፈልጉ መልካም ነው።*

## ማውጫ


ምስጋና ........ i

አጠቃሎ.. ........ iii

ማውጫ ........ iv

የሠንጠረዥ ማውጫ ........ ix

የምስል ማውጫ ........ x

የፎቶ ግራፍ ማውጫ ........ xi

ሙዳዩ ቃላት ........ xii

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 9

1.3 የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች ........ 14

1.4 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ........ 15

1.5 የጥናቱ ፋይዳ ........ 15

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 17

1.7 የጥናቱ ውስንነት ........ 18

1.8 የጥናቱ አደረጃጀት እና የምዕራፎች ይዘት ........ 20

ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሣናት ........ 22

2.1 ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ ........ 22

2.1.1 የፎክሎር (ባህል)፣ ጤና እና ሕመም ምንነት ........ 22

2.1.2 የሥነ ምህዳር ምንነት ........ 25

2.1.3 የባህል መድኃኒት/ሕክምና ምንነት ........ 26

2.1.4 የባህል ሕክምና ዕውቀትና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ........ 28

2.1.5 የባህል ሐኪሞች ማንነት፣ የባህል ሕክምና ማሕቀፍ እና የባህል ሐኪሞች ምድብ ........ 33

2.1.6 በባህል ሕክምና የሕመም መንስኤ እሳቤ ........ 38

2.1.7 በባህል ሕክምና የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ........ 41

2.1.8 የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ እና ሥነ ምህዳር ........ 43

2.2 ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ........46
2.2.1 የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦች........46
2.2.2 የሥነ ዕውቀት ንድፈ ሃሳብ........48
2.2.3 ማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ........50
2.2.4. ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ........51
2.2.5 የንድፈ ሃሳቦች ትኩረትና ድክመት፤ ትስስር እና ማሕቀፍ ይዘት........55
2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት........57
2.3.1 የባህል ሕክምና ልማድን መሰረት ያደረጉ ጥናቶች........58
2.3.2 የባህልና የዘመናዊ ሕክምና ጥምረት፤ የማኅበረሰብ አመለካከትን መነሻ ያደረጉ ጥናቶች........73
2.3.3 የባህል ሕክምና ታሪክን ማዕከል ያደረጉ ጥናቶች........75
2.3.4 የባህል ሕክምና ግብዓትን በሣይንስ ቤተ ሙከራ የፈተሹ ጥናቶች........76
ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ሥነ ዘዴ........82
3.1 የምርምሩ ዕይታ መሰረት........82
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች........83
3.2.1 የካልዓይ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች........83
3.2.2 የቀዳማይ መረጃዎች አሰባሰብ ዘዴዎች........83
3.3 የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ ስልት........93
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃር........95
3.5 የጥናቱ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች........97
3.6 የመረጃ አደረጃጀት እና መተንተኛ ሞዴል........100
3.6.1 ባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል........104
3.6.2 ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ሞዴል........106
3.6.3 የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል........107
3.7 የመስክ ልምድና መረጃ መሰብሰቢያ ጊዜያት........110
3.8 የመስክ ተመክሮ........114
ምዕራፍ አራት፡- የደቡብ ጎንደር ዞን መልክዓ ምድራዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ዳራ........120
4.1 ለጥናት የተመረጡ ወረዳዎች መልክዓ ምድር፣ ሥነ ሕዝብ፣ የትምህርትና የጤና ሽፋን........122

4.2 የደቡብ ጎንደር ዞን ዋና ዋና ተፈጥሯዊና ሃይማኖታዊ መስሕቦች ........................... 124
4.2.1 የፀበል፣ ፍል ዉኃ እና "የማዕድን አምቦ" ዉኃ መገኛ ቦታና አገልግሎት ............ 124
4.2.2 የተፈጥሮ ጥብቅ ደን፣ ጥንታዊ ገዳማትና የሃይማኖት መገኛ ቦታ እና አገልግሎት ........................................................................ 127
4.3 የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እምነቶች ............................................ 128
4.4 በደቡብ ጎንደር ዞን በባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች ............ 137
ምዕራፍ አምስት፡- በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤ ይዘታዊ ትንተና ........ 140
5.1 የሕመም መንስኤ ........................................................................ 140
5.2 የአጋንንት ዓይነት እና መለያ ባሕርይ .................................................. 147
5.3 የተቃርኖ ኃይል ስበት እና የለውጥ ጥሪ ............................................... 154
5.4 መለከፊያ ዐውዶች .................................................................... 160
5.4.1 በሕሊና ተሰውረው፣ በዐየር ተበትነው የሚኖሩ አጋንንት ............................. 160
5.4.2 በዕፅዋት የሰፈሩ፣ በእንስሳት የሚበሩ አጋንንት ....................................... 165
5.4.3 በቆሻሻ የሚኖሩ፣ "በወንዝ" የሰፈሩ አጋንንት ......................................... 170
5.4.4 በደም፣ ምግብና መጠጥ የሚነሱ አጋንንት፤ .......................................... 173
5.4.5 የዓመትና ወቅት ዑደትን ጠብቀው የሚከሰቱ አጋንንት ................................ 178
5.4.6 የኮከብ ባሕርይ መግነንና መክሰም ..................................................... 182
5.5 የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች ማጠቃለያ ................................................... 189
ምዕራፍ ስድስት፡- በባህል ሕክምና ዕውቀት፣ የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ይዘታዊ ትንተና ........................................................................ 191
6.1 የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ...................................................... 191
6.1.1 ዓለማዊ የበሽታ መለያና ምርመራ ዘዴዎች አተገባበር ................................. 191
6.1.2 መንፈሳዊ የበሽታ መለያ ዘዴዎችና አተገባበር ........................................ 200
6.2 በምርመራ ሂደት የበሽታ ባሕርይ ምድብ ................................................ 205
6.2.1 ድንገተኛ እና አጣዳፊ ................................................................ 207
6.2.2 ቆንጣጭ እና ሰርሳሪ .................................................................. 210
6.2.3 አቃጣይ እና አስለፍላፊ ............................................................... 212
6.2.4 አብራጅ እና አድካሚ ................................................................. 212
6.2.5 አንቀጥቃጭ እና አርገብጋቢ .......................................................... 214

6.2.6 አደንዛዥ እና አወፋሪ ........ 215
6.3 የምርመራ ሂደት እና የተቃርኖ ሕክምና ........ 217
6.4 የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች ........ 221
6.5 የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች ማጠቃለያ ........ 232
ምዕራፍ ሰባት፡- የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ ትንተና ........ 234
7.1 የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ "ሥርዓተ ገቢር" ዐውድ ........ 234
7.2 የባህል መድኃኒት "ገቢር" ማስተካከያ ዐውዳዊ ስልቶች ........ 245
7.3 የባህል መድኃኒት ቅመማ ይዘት እና ቅድመ ተግባራት ........ 262
7.3.1. የዕፅዋት ግብዓት ባሕርያት ........ 263
7.3.2 የእንስሳት እና የነፍሳት ግብዓት ባሕርያት ........ 268
7.3.3 የማዕድናት ግብዓት ባሕርያት ........ 269
7.4 የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት ........ 273
7.5 የባህል መድኃኒት አሰጣጥ ሥርዓት ........ 282
7.6 የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች ማጠቃለያ ........ 293
ምዕራፍ ስምንት፡- የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው አስተዋፅኦ ይዘታዊ ትንተና ........ 295
8.1 የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው አስተዋፅኦ ........ 295
8.1.1 የባህል ሐኪሞች እምነትና ተግባር ለአካባቢ ሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው አበርክቶ ........ 296
8.1.2 የማኅበረሰብ ልማድ ለአካባቢ ሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው አበርክቶ ........ 303
8.2 የባህል ሕክምና ዕውቀት (የማኅበረሰብ ልማድ) ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው ተግዳሮት ........ 317
8.3 የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች ማጠቃለያ ........ 322
ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ማጠቃለያና ይሁንታ ........ 324
9.1 ማጠቃለያ (መደምደሚያ) ........ 324
9.2 ይሁንታ ........ 331
ማጣቀሻ ምንጮች ........ 334
አባሪዎች. ........ i
አባሪ አንድ፡- የምልከታ መከታተያ ቅፅ፤ ........ ii

አባሪ ሁለት፦ ለባህል  ሐኪሞች፤ ለዘመናዊ ሐኪሞች፣ ለአካባቢው ማኅበረሰብ፣ ለተፈጥሮ ሐብት፣ ለባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች የቀረቡ ቃለመጠይቆች፤ ............................iii
አባሪ ሶስት፦ የውል ስምምነት ...........................................................................viii
አባሪ አራት፦ የመስክ መረጃ ሰጪዎች ዳራ .................................................................. ix
አባሪ- አምስት:- በደቡብ ጎንደር ዞን፤ በባህላዊ እና በዘመናዊ ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች ...........................................................................xvi
አባሪ ስድስት፦ በባህል ሕክምና የበሽታ መለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት ናሙና ...........................................................................................................xxii
አባሪ ሰባት፦ የባህል ሐኪሞች እና የዕፀ መድኃኒት "ናሙና" ማሳያ ፎቶዎች .....................xxix

## የሠንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ አንድ፦ የሥጋ ባሕርያትና ግብሮች ይዘት ........................................ 109

ሰንጠዥ ሁለት፦ የወረዳዎች መገኛና አዋሳኝ ቦታዎች ........................................ 122

ሰንጠረዥ ሶስት፦ የወረዳዎች መልክዓ ምድራዊና የዐየር ንብረት ሁኔታ .................. 123

ሰንጠረዥ አራት፦ የወረዳዎች ሥነ ሕዝብ መረጃ ........................................ 123

ሰንጠረዥ አምስት፦ የወረዳዎች መሰረተ ልማት ........................................ 124

ሰንጠረዥ ስድስት፦ በባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ

ዓይነቶች፤ ለጥናት በተመረጡ ወረዳዎች ማሳያነት ........................................ 138

# የምስል ማውጫ

ምስል 1፡- ጥቅል የባህል ሕክምና ዕውቀት ይዘት....................................................33

ምስል 2፡- የባህል ሕክምና ፅንሰ ሃሳባዊ ማሕቀፍ....................................................35

ምስል 3፡- የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳብ ይዘት.......................................................47

ምስል 4፡- የንድፈ ሃሳቦች ትስስር እና የትንታኔ ይዘት ማሕቀፍ ..............................56

ምስል 5.፡- የሕመም፣ የሕይወት እና የጤና መስተጋብርና የስበት ኃይል ሚዛን.........144

ምስል 6፡- ለሕመም መንስኤ የሚባሉ ዋና ዋና የአጋንንት ምድብና የማኅበረሰብ ክፍፍል እሳቤ..........................................................................................148

ምስል 7፡- አራቱ የተፈጥሮ ባሕርያት (የነገር ሁሉ/የሕይወት ሥር) እና ሁለቱ የመንፈስ ባሕርያት ሥር መሰረትን የሚያሳይ ምስል.............................151

ምስል 8፡- የተቃርኖ ኃይል ስበት፣ ሕመም፣ መተላለፊያ መስመርና የለውጥ ጥሪ..........................................................................................................158

ምስል 9፡- የዕፅዋት ጣዕም ባሕርይ፣ ዓይነት እና ባህላዊ ምደባ ይዘት.......................168

ምስል 10፡- የሕመም መንስኤ የሚባሉ አጋንንት በዋናነት የሚያጠቁት የሰውነት አካል ..........................................................................................................177

ምስል11፡- ዐበይት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ምድብና ማሕቀፍ.................204

ምስል12፡- በባህል ሕክምና ምርመራ ሂደት የበሽታ ባሕርያት ምድብና ማሕቀፍ........207

ምስል 13፡- የምርመራ ሂደት እና የተቃርኖ ሕክምና ማሕቀፍ.................................218

ምስል 14፡- የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች ማሕቀፍ.................................224

ምስል 15፡- መሰረታዊ የዕፅዋት ጣዕም ዓይነቶች ይዘት ምደባ.................................264

ምስል 16፡- የዕፅዋት ባሕርያት ምድብ ማሕቀፍ በምግብ ሰብሎች ማሳያነት ..............266

ምስል 17፡- የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት ማሕቀፍ............................................274

ምስል 18፡- የባህል መድኃኒት አሰጣጥ ሂደት ማሕቀፍ............................................289

# የፎቶ ግራፍ ማውጫ


ፎቶ ግራፍ 1፡- ዓለምን (መሬትን) ከበውና አስረው የያዙ የ"ብሄሞትና ሌዋታን" እሳቤ ....156

ፎቶ ግራፍ 2፡- ባህላዊ የወፍ (የጉበት) በሽታ ምርመራ ሂደትና አተገባበር ....195

ፎቶ ግራፍ 3፡- በፋርጣ ወረዳ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሂደትና የመስክ ተግባራት ፎቶ....238

ፎቶ ግራፍ 4፡- በእብናት ወረዳ በአቋሽሞች ቀበሌ የኮመል (እሼ) ዛፍና ፍሬን የሚያሳይ ፎቶ....240

ፎቶ ግራፍ 5፡- ከመስክ የተሰበሰቡ የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች፣ አሞሌ ጨውና ካራ ....276

ፎቶ ግራፍ 6፡- ታጥቦ፣ ተለቅሞና ተጨቅጭቆ የተሰጣ የዕፀ መድኃኒት ቅጠል....277

ፎቶ ግራፍ 7፡- ዕፅዋትን ለቅሞ፣ ቀጥቅጦና አድርቆ የማስቀመጥ ሂደት....278

ፎቶ ግራፍ 8፡- በዱቄትና በፈሳሽ መልክ የታሸጉ ዕፀ መድኃኒቶች....279

ፎቶ ግራፍ 9፡- ከዕፅዋት ቅጠል የሚዘጋጁ የዕፀ መድኃኒቶች ግብዓት ዓይነቶች ....281

ፎቶ ግራፍ 10፡- የመድኃኒት ቅመማና ምጣኔ፤ ማባረዝና ማዋሃድ ይዘት ....288

ፎቶ ግራፍ 11፡- የዕርድ መስዋዕት የሚቀርብበት የዋርካ ዛፍ ፎቶ....307

ፎቶ ግራፍ 12፡- በባህል ሕክምና ቦታ የሚገኙ የጅብ፣ የአነር፣ የጥቁር ሙጨጭላና የገበሎ ቆዳዎችን የሚያሳይ ፎቶ ....319

## ሙዳዬ ቃላት

**ልቡሳነ ሥጋ** — በዚህ ጥናት ዐውድ ሥጋና አካል የሌላቸው የሰው አምሳልና ገቢር ያላቸው አጋንንት (ጅን ወይም ዛር) ማለት ነው፤

**ልክስክስ** — በቆሻሻ ቦታ ላይ የሚገኝ የምድር ጋኔል፣ የአጋንንት ጭፍራ ማለት ነው፤

**ልክፍት** — በወንዝና በኩሬ ውኃ በመታጠብ በሰውነት አካል ላይ የሚወጣ ቁስል፤ ክፍቱን ባደረ ውኃ፤ በምግብና መጠጥ ምክንያት የሚከሰት ሕመም ወይም ድንገት በመውደቅና በመደንገጥ አዕምሮን በመሳት የሚቀሰቀስ ሕመም፤

**ሕልመ ሌሊት** — በእንቅልፍ ልብ ተቃራኒ ጾታን ተመስሎ ሩካቤ ሥጋ መፈፀም፤

**መለኮት** — የፈጣሪ ባሕርይ፤ የማይለወጥ፣ የማያልፍ እና ፍጡር ያልሆነ፤ በአንድነቱ ፀንቶ የሚኖር ረቂት የአምላክነት ባሕርይ ነው፤

**መስተጋብር** — ሁለትና ከዛ በላይ በሆኑ አካላት መካከል የሚደረግ ተራክቦና ንክኪ፣ ተላውጦ እና ግንኙነት ማለት ነው፤

**መርበብተ ሰሎሞን** — የሰሎሞን ፀሎት፤ የአጋንንት ማባረሪያ፣ ማስለፍለፊያና ማስዎጫ ፀሎት፤

**መርከስ** — ኃጢዓት ሠራ ባሕርይውን ለቀቀ፣ አደፈ፣ ጎደፈ፤ ክብርና ሞገሱን አጣ፤

**መተሬ** — ዕድገቱ እንደ ሃረግ ያለ የዕፅዋት ዓይነት ሲሆን ፍሬው ለኮሶ መድኃኒት ተቀምሞ ይሰጣል፤

**መድፈንፈን** — በአንድ ቦታ ቁጭ ብሎ ከመቀመጫ ሳይንቀሳቀሱ ባሉበት ቦታ ወደቀኝ፣ ወደግራ፣ ወደፊትና ወደኋላ መንቀሳቀስ፤ አጎንብሶ መስራት፣ መሬት መጫርና መቆፈር፤

**መዋረስ** — ሰዎች በሚበሉት፣ በሚጠጡት፣ በሚያሸቱት፣ በሚነኩት፣ በሚያዩትና በሚያስቡት ነገር ውስጥ ተዛምዶ፣ ተዋርሶና ተመስሎ የሚገባና የሚዋሃድ መንፈስ ማለት ነው፡፡

**መጣባት** — ሥር የሰደደ ሕመም፤ ከልጅነት ጊዜ ጀምሮ የነበረና ያደገ፤ ከአካልና ከመንፈሱ ጋር አብሮ የቆየ፣ የተላመደ፣ የተዛመደ፤ በመቆየቱና በመሰንበቱ ምክንያት በቀላሉ የማይለቅ ሕመም፤

| | |
|---|---|
| ምስ | ግብር፣ ሥጦታ፣ መስዋዕት ማቅረብና መሰዋት፣ መመለሻ፣ ማቋደሻ፣ መፈወሻ ገቢር፤ |
| ቁመኛ | በቁም መንምኖ፣ ከስቶ፣ ደክሞ በአካሉ ላይ የሚገኘው ሥጋ አልቆ መታየት፤ |
| ቁራኛ | ከአካልና ከመንፈስ ተዋህዶ ያደገ፤ የተቆራኘ (የተሳሰር፣ የተዛመደና የተገናኘ) ሕመም፤ |
| ቅጥቃጤ | ሕልም፣ ቅዠት፣ በጥልቅ እንቅልፍና በውድቅት ሌሊት ወቅት የሚደረግ መቃዠት፣ መጮህ፣ መደንገጥ ማለት ነው፤ |
| ባሕርይ | የፍጥረት መሠረት፣ ሥር፣ ምንጭ፣ መውጫ፣ መፍለቂያ፣ መገኛ ማለት ነው፤ |
| አዷማ | መቆፈሪያ ዶማ |
| እዳሪ መሬት | ታርሶ የማያውቅ መሬት፤ እህል ያልተዘራበት ድንግል መሬት፤ |
| ደንቃራ | የዶሮ፣ የበግ፣ የፍየል እና መሰል እንስሳት በታረደበትና ደም በፈሰሰበት ቤት በድንገት ገብቶና ደም እርግጦ መለከፍ፤ |
| ደዌ | በሽታ/ ሕመም |
| የቀንድ ካራ | ከቀንድ እና ከብረት የተሰራ ቢለዋ፤ እጀታው ከቀንድ ሆኖ መቁረጫው ደግሞ ከብረት የተሰራ የዕፅ መቁረጫና መከትከቻ ካራ፤ |
| ገቢር | ድርጊት፣ ተግባር፣ ሥርዓት የአንድ ነገር ቅደም ተከተል ወይም ሂደት፤ የአደራረግና የአፈጻጸም ሥርዓት፤ |
| ጠባይ | ሰው ወዶና ፈቅዶ የሚያመጣው ዐመል፤ ከባሕርይ ሲወጣ የሚከተለው አዲስ ነገር፤ |
| ጥላ | የሕመምተኛን በሽታ የሚያባብስ፣ ተመልሶ እንዲቀሰቀስ፣ እንዲያገረሽ ምክንያት የሚሆን፤ |
| ዛር | ውቃቢ፣ የሚያስለፈልፍ፣ የሚያስጮህ፣ የሚያንቀጠቅጥ፣ የሚያስጎራ ከመንፈስ ጋር የሚያናግር ፤ |

# ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ የሚካሄደውን የባህል ሕክምና ዕውቀት[1] እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን በመመርመር፤ የሕመም መንስኤ እሳቤ፤ የምርመራ ዘዴ፤ የዕፀ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ክዋኔ፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን አስተዋፅኦ ትንትኗል፡፡ በዚህ ምዕራፍ፤ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ፋይዳ፣ የጥናቱ ገደብ፣ የጥናቱ ውስንነት እና የጥናቱ አደረጃጀት ተካተዋል፡፡ የጥናቱ ዳራና ማዕከላዊ ትኩረት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ አካላዊ፣ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ በሽታን ለመከላከል፣ ከሕመም ለመፈወስ፣ በሕይወት ለመኖር ሲል፤ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ማኅበራዊ የጤና አጠባበቅ ሥርዓት፣ ዕውቀት፤ በሽታን የመከላከልና የመፈወስ ስልት፣ ልምድ፣ ልማድ፣ አተገባበር እና ደንብ እንዳለው ምሁራን ጠቁመዋል (አሰፋ፣ 2008፤ Molvaer, 1987; P.11)[2] ፡፡ ይህን ልማድ ለመተግበር፤ የሥነ ምህዳር ሥርዓትን (Ecological System) ባሕርይ፣ ይዘት እና ዓይነት፣ ለመለየት፤ ራሱን ከአካባቢው ዐውድ ጋር ለማላመድ፣ ለማስማማት፣ ለማግባባት፣... የተለያዩ ልማዳዊ ወይም እምነታዊ ሥርዓቶችን ይፈፅማል (Brady, 2001: McElroy and Townsend, 2009)፡፡

የኢትዮጵያ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ሥብጥርና ሁነት፣ የዐየር ንብረት፣ የሥነ ምህዳር ዓይነትና ብዝኀነት ለባህል ሕክምና[3] ዕውቀት (ሥርዓትና አተገባበር) ልማድ፤ የዕውቀት ምንጭ እና መሰረት በመሆን ዘመናትን አስቆጥሯል (Alemayehu, 1984; PP.124-125: Assefa, 1992; PP.88-89: Pankhurst, 2005; P.27)፡፡

---

[1]በዚህ ይዘት "የባህል ሕክምና ዕውቀት" ሲባል የባህል ሕክምና ሥርዓትና አተገባበር ይዘትን፤ የዕፀ መድኃኒት ባለሙያዎችን ይመለከታል፡፡ "ሥርዓትና አተገባበር" በአማራጭነት/ በመተካካት የቀረቡ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[2]የፀሃፊው/ዋ ስም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከተፃፈ የአውሮፓውያንን የዘመን አቆጣጠር የሚያሳይ ሲሆን በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈው ደግሞ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር የሚያመለክት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[3]ባህላዊ መድኃኒት (Traditional Medicine) በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራል፡፡ ለአብነት ያህል፤ ባህላዊ ዕፀ መድኃኒት (Traditional Herbal Medicine)፣ ሃገረሰባዊ መድኃኒት (Folk medicine)፣ አማራጭ መድኃኒት (Alternative Medicine)፣ አገር በቀል መድኃኒት (Indigenous Medicine) አጋዥ መድኃኒት (Complementary Medicine)፣ ነገድ መድኃኒት (Ethno Medicine) የሚሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ (Sofowora, 1982; PP.3-5)፡፡ ይህን የስያሜ ልዩነት ለማስወገድ ሲባል፤ በዚህ ጥናት ይዘት ባህላዊ መድኃኒት የሚለውን ስያሜ በወጥነት ተጠቅሜያለሁ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ “የባህል ሕክምና” የሚለውንም ፍቺ ያጠቃልላል፡፡

ከባህል፣ ጤና እና ሕመም ጋር የተገናኙ ቀደምት ጥናቶች፤ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ልማድና ሥርዓት መቼ ተጀመረ? እነማን ጀመሩት? ለምን ዓይነት ሕክምና? ለሚሉ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ እና ማስረጃ ማግኘት እንደማይቻል ጠቁመው፤ ስለዕውቀትና ታሪኩ አመጣጥ ሁለት ዓይነት አተያይ እንዳለ ገልፀዋል (አሰፋ፣ 2008፤ Pankhurst, 2005: Alemayehu, 1984)፡፡ Alemayehu (1984; P.124) የቀደምት ጥናታዊ ሥራዎችን ዋቢ በማድረግ "የሰው ልጅ በሽታን መከላከል፣ መድኃኒት መጠቀምና መፈወስ የጀመረው ከጥንተ-ክርስቶስ ልደት 25,000 ዓ.ዓ በፊት ነው" ይላሉ፡፡

Pankhurst (1976; P.10) ደግሞ፤ ኢትዮጵያውያን የባህል መድኃኒት ከ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት የመጠቀም ልማድ እንዳላቸው ጠቁመው፤ "Matsahafe Fews" በ17ኛው መ/ክ/ዘ አጋማሽ፤ "Mastahafe Medhanit" ደግሞ በ18ኛው መ/ክ/ዘ መጀመሪያ ታዋቂ የመድኃኒት መቀመሚያ ዐውደ ጥበብ (Pharmacopoeia) እንደነበሩ ገልፀዋል፡፡ እነዚህ ሰነዶች የባህል መድኃኒት መቀመሚያ ትዕዛዝ እና መመሪያን በመያዝ፤ ከሥነ ምህዳር (Ecology) የሚገኙ የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የአዕዋፍ እና የማዕድናት ግብዓቶችን፤ አስማታዊ እና መለኮታዊ ተግባራትን እንዳካተቱ አስረድተዋል (Desta, 2004; P.2: Pankhurst, 2005; P.31)፡፡ አሰፋ (2008፤ ገ.5) የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ዳራ "ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር ተያያዥነት ያለው የሕክምና ጥበብ እስከ አሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የሚደርስ መረጃም በጽሑፍ የሰፈረ ታሪክ..." እንዳለ ጠቁመዋል፡፡

ሁለተኛው መከራከሪያ ጉዳይ፤ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ዕውቀት ምንጭ፤ በአንድ በኩል "የውጭ አገር ተፅዕኖ አለበት" (Assefa, 1992) ሲባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱን የሥነ ምህዳር ሥብጥር (Ecological diversity) መነሻ በማድረግ ዕውቀቱ አገር በቀል እንደሆነ ይታሰባል (Alemayehu, 1984)፡፡

Assefa (1992; P.4)፤ "የኢትዮጵያ ሃይማኖትና አምልኮ የውጭ አገር ተፅዕኖ አለበት" ይላሉ፡፡ የባህል ሕክምና ዕውቀት ከሃይማኖት፣ ከእምነትና ከአምልኮ ሥርዓትና ተግባር ጋር እንደሚገናኝ ጠቁመው፤ የኢትዮጵያ ሃይማኖት፣ አምልኮና እምነት ከጎረቤት አገሮች ጋር የተወራረሰ በመሆኑ፤ የውጭ አገር ሃይማኖትና ልማድ ተፅዕኖ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ በተለይ ከግብፅ፣ ከዐረብና ከሱዳን በነበረን፤ የንግድና የሃይማኖት ግንኙነት የባህል ሕክምና ዕውቀትና ሥርዓት፣ አምልኮና ጥበብ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ (እንደተዛመተ) አትተዋል፡፡

Fekadu (2001; P.15)፤ የ"Assefa"ን ሃሳብ በመደገፍ፤ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ዕውቀትና እድገት የውጭ አገሮች አሻራ እንዳለበት ይገልፃሉ። ይህ የባህል ሕክምና ዕውቀት ከጎረቤት አገሮች፣ በንግድና በሃይማኖት ግንኙነት ወደ አገር ቤት መግባትና መስፋፋቱን ያትታሉ። የሕክምና ዕውቀቱ ቀይ ባሕርን አቋርጦ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ የ"ሴማውያን" ሃይማኖት መጀመር እና መተዋወቅ፤ እንደ "ጁዲዝም፣ ክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት" በአገር በቀሉ የባህል ሕክምና ዕውቀት ላይ ተፅእኖ እንዳሳደሩ፤ ያስረዳሉ።

Kloos (1973; P.133) ደግሞ፤ የአንድ አገር ማኅበረሰብ ባህል ሙሉ በሙሉ የሌላውን አገር ባህል ሊወክል አይችልም። ይህም በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ዕውቀት የግሪክ፣ የዐረብ እና የግብፅ አገሮች አሻራ ያለበት ቢሆንም፤ የባህል ብዝኀነት፣ አገሪቱ የምትገኝበት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፤ የሥነ ምህዳር ሥብጥር (የዐየር ንብረት፣ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ መልክዓ ምድር፣...) እና መሰል ልዩነቶች የባህል ሕክምና ዕውቀትና ተግባሩን የተለየ ዐውድ እንደሚያሲዙት፤ አትተዋል።

Alemayehu (1984; P.124) ደግሞ፤ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ዕውቀትና ሥርዓት ምንጩ "አገር በቀል ነው" ይላሉ። ኢትዮጵያ በምድር ወገብ አካባቢ መገኘቷ፤ ለዕፅዋትና ለእንስሳት ዓይነት፣ ለተለያዩ በሽታዎች መንስኤ መሆን፣ ለዐየር ንብረት ለውጥ፣ ለመልክዓ ምድራዊ ገፅታ (ሥነ ምህዳር) መለያየት ምክንያት መሆኗን ይገልፃሉ። እነዚህን ሁነቶች ታሳቢ በማድረግ፤ የበሽታ፣ የመልክ ዓምድር እና የዐየር ንብረት ለውጥን በማስተናገድ፤ በዓይነትና በይዘት የተሰባጠሩ የዕፅዋት፣ የእንስሳትና ማዕድናት ውጤቶችን በማግኘት፤ የተለያዩ የመድኃኒት ግብዓቶችን ቀምመው ሕሙማንን በመፈወስ፤ የዕውቀት ምንጩ፣ ሥርዓትና ተግባሩ እንዲቀጥል አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን ይመክራሉ።

Assefa (1992; P.5)፤ ዐረቦች የግሪክን ባህል በመጠበቅና ዕውቀቱን ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ ጉልህ አስተዋፅዖ እንደነበራቸው ገልጸዋል። ግሪኮች አራቱን ተፈጥሯዊ ንጥረ ነገሮች (Elements) ውኃ፣ እሳት፣ መሬትና ዐየርን በመለየት በታዋቂ ግሪካውያንና ሮማውያን ባለሙያዎች የሕክምና አገልግሎት ይሰጡ እንደነበር ጠቁመዋል። በተለይ የ"Hippocrates and Galen Medicine" የሕክምና ዕውቀት ዐረቢያን እንደ መሸጋገሪያ አድርገው ከግሪክ ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ አስረድተዋል። የግሪክ አራቱ ንጥረ ነገሮች በሰው አካላዊም ሆነ አዕምሯዊ ጠባይ ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደሩ ይታሰባል። ዐረቦች፤ ከግሪኮች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስለነበራቸው ከግሪክ የወረሱትን ዕውቀት ለሌላም አገር አዛምተዋል። ኢትዮጵያም

ከዐረብ አገሮች በነበራት የንግድ፣ የሃይማኖትና ማኅበራዊ ግንኙነት፤ የባህል ሕክምና ዕውቀቱም ከዐረቢያ ወደ ኢትዮጵያ እንደተሸጋገረ አትተዋል፡፡

እንደ Alemayehu (1984; PP.24-25) ገለፃ፤ የሰው ልጅ ታላቁን ስልጣኔ የጀመረው በናይልና በሞሶፖታሚያ ወንዞች አካባቢ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ የታላቁ ጥቁር ዐባይ ምንጭ፣ የሰው ልጅ መገኛ በመሆኗ በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች የዕፅዋት መድኃኒትን በመጠቀም ከዓለም የመጀመሪያዎቹ እንደሚሆኑ፤ ይጠቁማሉ፡፡

Alemayehu ከ"Assefa" እና ከ"Fekadu" በተቃራኒ ኢትዮጵያ የተለያየ ሥነ ምህዳር፣ መልክዓ ምድር፣ የዕፅዋትና የእንስሳት ዓይነት መገኛ መሆኗን ታሳቢ በማድረግ፤ የባህል ሕክምና ዕውቀቱም ሆነ ሥርዓቱ አገር በቀል እንደሆነ አትተዋል፡፡ Assefa እና Fekadu ደግሞ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ሥርዓት፣ ልማድና አምልኮ የጎረቤትና የውጭ አገሮች ተፅዕኖ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ በተለይ በንግድና በሃይማኖት በነበረው ግንኙነት የግብፅ፣ የሱዳን፣ የዐረብና የግሪክ የባህል ሕክምና ሥርዓቶች ዕውቀትና አምልኮዎች በኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ሥርዓት ላይ አሻራቸውን እንዳሳረፉ ጠቁመዋል፡፡ ከነዚህ መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው፤ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ይዘት አገር በቀል ዕውቀትን፣ የጎረቤት አገሮችን ልማድ እና ተግባርን "በማዳቀል"፣ በማላመድ እና አካባቢያዊ በማድረግ፤ እምነታዊ ሥርዓትና ተግባራትን በማላበስ፤ "ቤተኛ" እንደሆነ፤ ይታመናል፡፡ ከዚህ በላይ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ዳራና የሥነ ምህዳር ጥቁምታ የቀረበ ሲሆን፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት በፎክሎር መስክ እንዴት ይታያል/ ይተገበራል?

Hurreize (2006; P.120)፤ የባህል ሕክምና በአንድ በኩል ፎክሎር በሌላ መልኩ ደግሞ የሕክምና ዘርፍ መሆኑን ጠቁመው፤ መስኩ የባህልና የሣይንስ ትስስር፣ መስተጋብርና መሰል ጉዳዮችን አጣምሮ በመያዝ፤ የሁለቱን ግንኙነት በውል የሚያሳይ ሙያ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ Yoder (1972; P.192) ደግሞ፤ የማኅበረሰብን የባህል ሕክምና ዕውቀትና ልማድ ማጥናት አንዱ የፎክሎር ትኩረትና አቅጣጫ ሲሆን፤ በልማድ ዘውግ ሥር እንደሚመደብ አስረድተዋል፡፡ ጥናቱ፤ የባህል ሕክምና ልማድን ከፎክሎር ሙያና ተግባር አንፃር የመረመረ ሲሆን ሣይናሳዊ/ዘመናዊ የሕክምና ዘርፍን አይመለከትም፡፡

Hufford (1986; P.307)፤ የባህል ሕክምና ዘርፍ፤ ከፎክሎር ጥናት መስኮች መካከል "በሃገረሰባዊ ልማድ" (Social Folk Customs) ሥር የሚመደብ ሲሆን፤ በዚህ ንዑስ ክፍል "ሃገረሰባዊ

መድኃኒት" (Folk Medicine) አንዱ ይዘት እንደሆነ ገልፀዋል። የባህል ሕክምና ደግሞ ተፈጥሯዊ መድኃኒት «Natural/ Secular Folk Medicine» እና መለኮታዊ "Magico-religious/ Spirituals)" ኃይልና ተግባራትን በማካተት እንደሚፈፀም ምሁራን (Yoder, 1972; P.192: Murdock, 1980; P.6: ፈቃደ፣ 1991፣ገ.13) አስረድተዋል።

ተፈጥሯዊ ሕክምና ሲባል ከሥነ ምህዳር (Ecology) የሚገኙ የተፈጥሮ መድኃኒት ግብዓቶችን (ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ አዕዋፍ፣ ማዕድናት፣ ነፍሳት) እና በዘርፉ የሚሰጠውን የሕክምና ተግባር እንደሚያጠቃልል ገልፀዋል (Konadu, 2007: Winkelman, 2009)። ይህን ታሳቢ በማድረግ የባህል ሕክምና እና የሥነ ምህዳር ምንነት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የባህል ሕክምና ማለት ምን ማለት ነው? ሲባል Sofowora (1982; P.2)፤ የባህል ሕክምና ማለት የዕውቀት እና የተግባር አጠቃላይ ድምር (sum total) የሆነ፤ አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ጠንቆችንና ተውሳኮችን ለመከላከል፣ ለማስወገድና ለመመርመር ሲባል የሚተገበር፤ በተግባራዊ ልምምድ እና ምልከታ የሚከወን፤ ዕውቀቱና ጥበቡም በአብዛኛው ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ወይም በጽሑፍ እንደሚተላለፍ ገልጸዋል። በተመሳሳይ መልኩ Steiner (1986; P.66) እና Kannon (2004; P.32) "የባህል መድኃኒት" ማለት የተለያዩ ብያኔዎች፣ ጽንሰ ሐሳቦች፣ የሥነ ምህዳር ዕውቀት፣ የማኅበረሰብ ልማድና ተመክሮዎች አጠቃላይ ድምር ውጤት ሲሆን፤ ከሥነ ምህዳር የሚገኙ ግብዓቶችን መሰረት በማድረግ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድን ውጤቶች እንደሚዘጋጅ አስረድተዋል።

ሥነ ምህዳር (Ecology) ሲባል፤ ሕይወት ያላቸውና የሌላቸው ረቂቅ፣ ግዙፍና ግዑዝ አካል መገኛ፤ የዐየር ንብረትን (ሙቀት፣ ቅዝቃዜ)፣ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥን (ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ቆላ.../ዉኃማና ደረቅ መሬትን)፣ የበሽታ መከሰት እና ዐውዳዊ ሁነትን እንደሚያጠቃልል (Steward, 2006: Sutton and Anderson, 2010; PP.8-9) ገልፀዋል። የባህል ሕክምና ዕውቀት ደግሞ፤ ከሥነ ምህዳር የሚገኙ ግብዓቶችን በመሰብሰብ፤ የሥነ ምህዳር ዐውድን በመለየት፤ ለበሽታና ለበሽታ መንስኤ ያለን እሳቤ፣ እምነት፣ አምልኳዊ ሥርዓት፣ የሥነ ከዋክብት ዕውቀት (Astrology[4] Knowledge)፣ ተግባር (Heindel and Heindel, 2011; PP.4-6)፣ ሥነ-ቃል፣ ሚታዊ "ተረኮችን" እና ባህላዊ ዕውቀትን አካቶ በመያዝ እንደሚከወን እና እንደሚጠና ምሁራን

[4] ይህ ጥናት ለበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴ ተብሎ ተግባራዊ የሚደረገውን የኮከብ ቆጠራ (Astrology) ሥርዓት ብቻ ነጥሎ ተመልክቷል። የኮከብ ቆጠራ ዕውቀት ውስብስብና ሰፊ ርዕሰ ጉዳዮችን፣ እሳቤዎችን፣ ተግባርና ይዘትን የሚያካትት መስክ ነው (Heindel and Heindel, 2011)። ጥናቱ ከምርመራ ዘዴ ጋር በተያያዘ የኮከብ ቆጠራ ሥርዓትና ልማድን ከመዳሰስ ባለፈ የዚህ ጥናት ማዕከላዊ ይዘትና ትኩረት አለመሆኑን ልብ ይሏል።

ገልፀዋል (Hurreize, 2006: ፌቃደ፣ 1991)፡፡ የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ዘርፍ ለሁለተኛ እና ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ በተለያየ መስክ ያጠኑ፤ የሂዩማኒቲስ፣ የማኅበራዊ እና የሥነ ሕይወት ሣይንስ ፋኩሊቲ ምርምሮች ትኩረት እንደሚከተለው ተዳሰዋል፡፡

በሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች ማዕከላዊ ትኩረት የባህል ሕክምና ተግባር፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ይዘትን፤ ማኅበራዊ ልማድና አመለካከትን፤ ሃይማኖታዊ እና እምነታዊ ተግባራትን፣ የባህል ሕክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶችን ዳሰዋል (ዓለማየሁ፣ 2000፤ ምህረት፣ 2000፤ መስፍን፣ 2002፤ ተመስገን፣ 2003፤ ደነቁ፣ 2003፤ ፍቅርተ፣2009፤ ዐቢዩ፣ 2010)፡፡

እንደ ዓለማየሁ (2000) ጥናት ግኝት የኑዌር ማኅበረሰብ ለበሽታ ያላቸው አመለካከት በዋናነት ከፈጣሪ እና ከሃገረሰባዊ እምነቶች ጋር የተያያዘ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ምህረት (2000) ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ የባህል ሕክምና አገልግሎት በስፋት እንደሚሰጥ ጠቁመው፤ የባህል መድኃኒት ባለሙያዎች ዕውቀቱን በዋናነት ከሃይማኖታዊ ተቋማት እንደተማሩት ይገልጻሉ፡፡ መስፍንም (2002)፤ በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የባህል መድኃኒት ባለሙያዎች ለመድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶችን ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት ቀምመው እና እምነታዊ ሥርዓቶችን ፈፅመው መድኃኒት እንደሚሰጡ፤ ተመስገን (2003)፤ በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የባህል መድኃኒት ሲቀምሙ እምነታዊ ሥርዓቶችን እንደሚፈፅሙ፤ ደነቁም (2003)፤ በወላይታ ሶዶ ከተማና አካባቢዋ የዕፀ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ልማድ አካባቢ ተኮር ይዘትና ተግባር እንዳለው፤ ፍቅርተ (2009)፤ በከምባታ ብሔረሰብ ከዕፅዋት የሚገኙ ሃገረሰባዊ መድኃኒቶች አዘገጃጀትና አሰጣጥ አካባቢያዊ እምነትንና ግብዓትን ታሳቢ በማድረግ እንደሚከወን፤ ዐቢዩ (2010)፤ የቦሮ ሽናሻ ሃገረሰባዊ መድኃኒት ምንጩ፣ ተስተላልፎ እና ገቢር እየተዳከመ መምጣቱን፤ ማኅሌት (2011) ደግሞ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ የሚተገበረው የሃገረሰባዊ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ልማድ በጥቂት አዋቂዎች እጅ መገኘቱ፤ ከመንግስት አካላት ተገቢው ትኩረትና ዕውቅና አለማግኘቱ ሙያውን እያዳከመው እንደሄደ ገልፀዋል፡፡ ከአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ውጪ የተካሄዱ ቀደምት የጥናት ሥራዎች እንደየሙያ መስካቸው ቢለያዩም፤ የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ታሪክ፣ ልማድ እና ተግባር እንደሚከተለው ዳሰዋል፡፡

በታሪክ ትምህርት ክፍል (Assefa, 1992: አሰፋ፣ 2008)[5] የቀረቡ ጥናቶች፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰቱ የበሽታ ዓይነቶችንና የባህል ሕክምና ታሪክን ይዳስሳሉ:: እንደ Assefa (1992) ጥናት ጥቁምታ፤ ቀደምት የባህል ሕክምና ተግባርና ምርምር በአባላዘር በሽታና ፈውስ ሥርዓት ላይ የተመሰረተ እንደነበር ጠቁመዋል። በተለይ በደሴ ከተማ አካባቢ የሚኖሩ መድኃኒት አዋቂዎች ለቁምጥና፣ ለቂጥኝ፣ ለኩፍኝ፣ ለጨብጥ፣ ለሳንባ ነቀርሳ ፈውስ፤ ከልማዳዊ ተግባር እና ከመንፈሳዊ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ሕክምና ይሰጡ እንደነበር ገልጸዋል:: ሁለተኛ ጥናታቸው "የኢትዮጵያ ባሕላዊ መድኃኒትና ሕክምና የምዕተ ዓመት ጉዞ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የምርምራቸው ማዕከላዊ ይዘት የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ታሪክ፣ የመስኩን ባለሙያዎች ሕይወትና ልምድ፣ የዘመን ክስተት፣ የመንግሥት አዋጅና መመሪያን ይዘግባል (አሰፋ፣ 2008)። ከታሪክ ትምህርት ክፍል ባለፈ፤ በሥነ ሰብዕ ትምህርት ክፍል የባህል ሕክምና ልማድና ሥርዓትን የሚመለከቱ ይዘቶች እንደሚከተለው ተቃኝተዋል።

በሥነ ሰብዕ ትምህርት ክፍል በባህል ሕክምና ዘርፍ ከተካሄዱ ጥናቶች መካከል በዋናነት Young (1970)[6]፣ Mirgissa (1993)፣ Abraraw (1998)፣ Zerihun (2001) እና Wondwosen (2006)፣ Tebaber (2015) ይጠቀሳሉ:: የጥናቶቹ ትኩረት አካባቢያዊ ባህልን መሰረት በማድረግ በዘርፉ የሚሰጠውን ሕክምና፣ ተግባርና ሥርዓት ይገልፃሉ:: Young (1970) የጥናታቸው ማዕከላዊ ጉዳይ በቤጌምድር የሚካሄደውን የባህል ሕክምና አምልኮና ተግባር በመዳሰስ፤ ውስጣዊና ውጫዊ የሕክምና (Internal and External) ዓይነቶችን፤ ተፈጥሯዊና መለኮታዊ የበሽታ መንስኤዎችን ለመከላከል፤ ማኅበረሰቡ በአስማትና በዕፀ መድኃኒት የሚፈውሱ የባህል ሐኪሞችን እንደሚጠቀም አስረድተዋል:: Mirgissa (1993) በኢሉባቦር የሚገኙ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች መንፈሳዊና ዓለማዊ በመባል በሁለት እንደሚከፈሉ ጠቁመው፤ በመንፈሳዊ ኃይል በመታገዝ ሕሙማንን ለመፈወስ የጫት መቃም ሥርዓት፣ ልመና፣ ጸሎትና ዱአ (Duai) እንደሚያካሄድ ጠቁመዋል። Abraraw (1998) ደግሞ በደሴ ከተማ ሰዎች የጤና እክል ሲገጥማቸው ሁለቱንም (መንፈሳዊ እና ዓለማዊ) የባህል ሕክምና ዓይነቶች በአማራጭነት እንደሚጠቀሙ፤ በአካባቢው ዘመናዊ ሕክምና የሚገኝ ቢሆንም አብዛኛው ማኅበረሰብ የባህል ሕክምና ዘርፍን እንደሚመርጥ፤ በጥናታቸው ገልፀዋል። Zerihun (2001) በዛይ ደሴት በሚገኙ የአዕምሮ ሕሙማን ላይ ጥናት አካሂደዋል።

---

[5]Assefa፣1992 (MA)፤ አሰፋ፣2008 (PhD)፤ እነዚህ ጥናቶች በታሪክ ትምህርት ክፍል መስክ በአሰፋ ባልቻ (ዶ/ር) የቀረቡ ናቸው:: በአማርኛና በእንግሊዝኛ የተፃፉበት ምክንያት የምርምር ሥራዎቹ መገኛ ቋንቋን ታሳቢ ያደረገ ነው::

[6]Young (1970) የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ያጠኑ የውጭ አገር የሥነ ሰብ ባለሙያ ናቸው::

የአዕምሮ ሕመም መነሻ ከመንፈስ ጭንቀት፣ ከማኅበራዊ፣ ከኢኮኖሚ ቀውስ እና ከፖለቲካ አንጻር እንደሚከሰት አስረድተዋል። በጥናታቸው ግኝት ለአዕምሮ ሕሙማን የሚደረገው እንክብካቤና በማኅበረሰቡ ያለው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል። Wondwosen (2006)፤ በአዲስ አበባ የሚካሄደውን የባህልና የዘመናዊ ሕክምና ጥምረትና ሥርዓትን መርምረዋል። በጥናታቸው ይዘት የባህል ሕክምና ዘርፍ ውስብስብና እና የተለያዩ ተግባራትን ያካተተ መስክ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዘመናዊ ሕክምና ጋር በመጣመርና በመተጋገዝ የማኅበረሰብን ጤና ማሻሻል እንደሚቻል አመላክተዋል።

በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ትምህርት ክፍል በባህል ሕክምና ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ Mekonen W.(2008) እና Mekonen M.(2010) ይጠቀሳሉ። እንደ Mekonen W.(2008) ጥናት፤ የምዕራብ ጎጃም ዞን ማኅበረሰብ ለእብድ ዉሻ በሽታ ፈውስ ከዘመናዊ ሕክምና ይልቅ፤ የባህል ሕክምናን ምርጫቸው እንደሚያደርጉ አስረድተዋል። Mekonen M.(2010) ደግሞ፤ የኩናማ ማኅበረሰብን የባህል ሕክምና ሥርዓት እና ተግባር አጥንተዋል። አብዛኛው የኩናማ ማኅበረሰብ በሽታን ለመከላከል፤ ከሕመም ለመፈወስ የባህል መድኃኒቶችን በብዛት እንደሚጠቀሙ፤ በጥናታቸው አረጋግጠዋል።

የባህል ሕክምናን ከሣይንስና ከማኅበረሰብ ልማድ ጋር በማገናኘት፤ ከአጠኑ የሥነ ሕይወት ሣይንስ ትምህርት ክፍል Fekadu (2001) ይጠቀሳሉ። በጥናታቸው ሂደት፤ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት በዘመናዊና በባህላዊ ሕክምና ዘርፍ ያላቸውን ሚና በመለየት፣ የዕፅዋቱን የመድኃኒት አቅምና የፈውስ ኃይል በቤተ ሙከራ በማረጋገጥ፣ በባህልና በዘመናዊ ሕክምና የሚሰጡትን ጠቀሜታዎች መጠቆማቸው፤ በዚህ ይዘት ከተጠቀሱ ጥናቶች የተለዩ ያደርጋቸዋል።

ይህ ጥናት፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን መርምሯል። በጥናቱ ይዘት የሕመም መንስኤ እሳቤን፤ የምርመራ ዘዴን፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ክዋኔን፣ የሕክምና ዕውቀቱ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አስተዋፅኦ እንዳለው መተንተኑ፤ ከዚህ በላይ ከተዳሰሱ ምርምሮች የተለየ ያደርገዋል። በጥናቱ፤ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብና መልክዓ ምድርን መሰረት በማድረግ ከሶስት ወረዳዎች (ፋርጣ፣ ሊቦ ከምከም እና እብናት) የመስክ መረጃዎች ተሰብስበው፣ በይዘትና በመልክ ተደራጅተው ተተንትነው ቀርበዋል። ከዚህ በታች የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት ዐበይት አነሳሽ ምክንያቶች:-

### 1ኛ. ከባህል ሕክምና እና ከሥነ ምህዳር ባሕርይ አንጻር

እንደ Messeret ገልፃ፤ "...አብዛኛው የገጠሩ ሕዝብ በባህል መድኃኒትና በባህል ሐኪሞች ላይ ጥገኛ ነው፤ በከተማም ቢሆን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ የባህል መድኃኒት ተጠቃሚ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በዘርፉ አጠቃቀምና አተገባበር ዙሪያ ሰፊ ምርምር አልተካሄደም" (1996; P.5) ይላሉ፡፡ Agonafer (2004; P.49) ደግሞ፤ "... 90% የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የባህል መድኃኒት ተጠቃሚ ነው"፤ የባህል ሕክምና ዕውቀቱም በሥነ ምህዳር ዓይነት፣ ግብዓትና ሁነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፤ Fekadu (2001) እና Alemayehu (1984) የባህል ሕክምና (የዕፀ መድኃኒት) ባለሙያዎች ዕውቀት በአካባቢያዊ ልማድና በሥነ ምህዳር ግብዓቶች ላይ የተወሰነ እንደሆነ ጠቁመው፤ በየአካባቢው ተጨማሪ ምርምሮች መካሄድ እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡

Mekonen (1988)፤ ለባህላዊ መድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት በሰው ሰራሽ (Human made) እና በተፈጥሮ አደጋ (Natural disasters) ከዕለት ወደ ዕለት እየተመናመኑ እና እየጠፉ መሄዳቸውን ጠቁመዋል፤ በዕፅዋት ሕክምና የሚሰጡ የባህል ሐኪሞች ዕፀ መድኃኒት ፈልገው ለማግኘት እንደሚቸገሩ ገልፀዋል፡፡ Fekadu (2001; P.3) እና Mekonen (2008; P.5) ደግሞ፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት (ዕፀ መድኃኒት) ከተፈጥሮ ሐብት (Natural resource) እና ብዝሀ ሕይወት (Bio-diversity) ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳለው በማስረዳት፤ የሥነ ምህዳር ለውጥና ጥፋት በሕክምና ዕውቀቱ ላይ ቀጥተኛ ተፅእኖ እንዳለው አስረድተዋል[7]፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ ለዕፀ መድኃኒት የሚውሉ ዕፅዋት ባህላዊ እሳቤያቸውና ተግባራዊ ዕውቀታቸው ሳይጠፉ በሥርዓት ተለይተው፣ ክትትል፣ ቁጥጥርና እንክብካቤ ቢደረግላቸው፤ በየአካባቢው የሚካሄዱ የባህል ሕክምና ሥርዓቶች

---

[7]Pankhurst (2005; PP.38-39) ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና እና ጤና በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶች የተካሄዱ ቢሆንም በተለይ ከዕፅዋት ሣይንስ ወይም ከክሊኒካዊ ምርመራ አንፃር (Botanical or Clinical point of View) የምርምር ክፍተት እንዳለ አስረድተው፤ ወደፊት የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና በአራት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንዳለበት አመላክተዋል፡፡ እነርሱም በግዕዝና በአማርኛ የተፃፉ የባህል ሕክምና መጻሕፍትን ማሰባሰብ፤ ሣይንሳዊ ጥናት በማካሄድ የዕፀ መድኃኒት መገኛ የሥነ ምህዳር ዓይነቶችን መለየትና ለህትመት ማብቃት፤ ባህላዊ የሕክምና ልማዶችን፣ በጽሑፍ የማይገኙ ቃላዊ የፈውስ ተግባራትን መሰነድና ሣይንሳዊ ምርምር ማካሄድ፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን ልማድ፣ ተግባርና የሕይወት ታሪክ መፃፍ፤ ከምስጢራዊነቱ ባሻገር እንዴት ለፈውስ አገልግሎት እንደሚውሉ እና ለትውልድም ዕውቀቱ፣ ተግባሩ እና ሥርዓቱ እንዲተላለፍ የምርምር ሥራ መካሄድ እንዳለበት መክረዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ የምርምር ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የበኩላቸውን እምነትና አስተያየት "I believe, do much to encourage research on traditional medicines and practitioners alike" በማለት (2005; P.39) ጠቁመዋል፡፡

በውል ተጠንተው የማኅበረሰቡን ጤና ማሻሻል እና ተግባራዊ ዕውቀታቸው ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ማዕከላዊ ጉዳይ መሆኑን (Kokawaro, 1976: Fekadu, 2001: Konadu, 2007) መክረዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች የባህል ሕክምና እና ሥነ ምህዳር ዝምድና እንዳላቸው ቢመክሩም፤ በፎክሎር መስክ የባህል ሕክምናን መነሻ አድርጎ ሥነ ምህዳርን የመረመረ፤ የሁለቱን ዐውዳዊ መስተጋብር የፈተሸ ጥናት አልተገኘም (በዚህ ጥናት የተዳሰሱ ሥራዎችን ልብ ይሏል)፡፡ ይህን ክፍተት ለመሙላት፤ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ የሚካሄደውን፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን በመመርመር፤ በዘርፉ ያለውን ዕውቀት ለመፈተሽ፣ ክፍተቱን ለማጥበብ እና የመፍትሔ ሃሳብ ለመስጠት አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ታሳቢ አድርጓል፤

Trostle (2005) እና Sutton and Anderson (2010) የሥነ ምህዳር መለያየት ለበሽታ፣ ለዕፀ መድኃኒት ግብዓት፣ ለአኗኗር ልማድ ልዩነት ምክንያት እንደሚሆን አስረድተዋል፡፡ ይህን ርዕሰ ጉዳይ መነሻ በማድረግ፤ የደቡብ ጎንደር ዞን መልክዓ ምድር (ሥነ ምህዳር) ይዘትን እና የባህል ሐኪሞች መገኛ መሆኑን በቅድመ ዳሰሳ[8] (Primary Survey) ወቅት መለየት ተችሏል፡፡ ጥናቱ ከቆላ እስከ ደጋ (ከእብናት/ኒቋራ እስከ ፋርጣ/ጉና ተራራ) ያለውን የመልክዓ ምድር ልዩነት በመቃኘት፤ ከዞኑ ወረዳዎች መካከል ፋርጣ 44% ደጋ፣ ሊቦ ከምከም 95.9% ወይና ደጋ እና እብናት 50% ቆላማ የዐየር ንብረትን መሸፈናቸው፤ በዞኑ ከሚገኙ ወረዳዎች በተለየ ተመራጭ አድርጓቸዋል (የደ.ጎ.ዞ.ባ.ቱ.ቢ[9]፣ 2007፣ገ.150፣ 30፣ 110፤ በቅደም ተከተል)፡፡ በሶስቱም ወረዳዎች የባህል ሕክምና ዕውቀትና ሥርዓት እንዴት ይተገበራል? ምን ዓይነት በሽታዎች በየትኛው ሥነ ምህዳር በተደጋጋሚ ይከሰታሉ? መልክዓ ምድር፣ ወቅትና የዐየር ንብረት ዐውድን ታሳቢ አድርገው የሚከሰቱ በሽታዎች፤ የመድኃኒት ግብዓቶች ምን ምን ናቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ርዕሰ ጉዳዩ ተመርጧል፡፡

---

[8]በደቡብ ጎንደር ዞን፤ በሊቦ ከምከም፣ በፋርጣ፣ በፎገራ፣ በእስቴ ወረዳዎች "ባህላዊ የልጆች አስተዳደግ ዕውቀትና አተገባበር በጎንደር" (ከ2006-2009 ዓ.ም) በሚል ርዕስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለተካሄደ ፕሮጀክት አስተባባሪ በመሆን፤ "የባህል ሕክምና ሥርዓትና አተገባበር ከሥነ ምህዳር አንፃር" እና "በአውራ አምባና አካባቢው ማኅበረሰብ የባህልና ልማት እሳቤና አተገባበር በደቡብ ጎንደር ዞን" በሚሉ ርዕሶች፣ ለፒ.ኤች.ዲ (2009) ትምህርት ኮርሶች ማሟያ ጥናት ለማቅረብ ወደ አካባቢው መሄዴን ታሳቢ ያደርጋል፡፡ የዞኑ የዐየር ንብረት ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላማ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 55.34 % ደጋ፣ 46 % ወይና ደጋ፣ 21.89% ቆላ እና 1.97% ዉርጫማ የዐየር ንብረቶችን አካቶ እንደያዘ የዞኑ መረጃዎች ጠቁመዋል (የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ 2007፡18)፡፡ ዉርጫማው የዐየር ንብረት ክፍል የሰው ልጆች መኖሪያ አካባቢ አለመሆኑን ታሳቢ በማድረግ፤ ከዚህ ጥናት ይዘት ውጪ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[9] የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ (የደ.ጎ.ዞ.ባ.ቱ.ቢ)፤ የሚለውን አፅኅሮተ ቃል ይወክላል፡፡

## 2ኛ. ከቅድመ ዳሰሳ ቅኝት እና ተግባር አንፃር

አንደኛ፡- በ2009 ዓ.ም በደቡብ ጎንደር ዞን በፎገራ ወረዳ ማኅበረሰብ "የባህል ሕክምና ሥርዓትና አተገባበር ከሥነ ምህዳር አንፃር"[10] በሚል ርዕስ ለኮርስ ማሟያ በአዘጋጀሁት ጽሁፍ እና ቅኝት በአደረኩባቸው ወረዳዎች (በፋርጣ፣ በሊቦ ከምከም፣ በፎገራ) የሚገኙ የማኅበረሰብ አባላት፤ ለሕመም መንስኤ "ቡዳ፣ ዛር፣ ጅን፤...ናቸው" ብለው በማመን፤ ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸውን ግንኙነትና መስተጋብር ሲገድቡና ሲፈቅዱ ይታያል፡፡ ሰው ሲታመም "ቡዳ በልቶት ነው፤ አጋንንት አርፎበት ነው" እየተባለ ከሕመሙ ለመፈወስ የተለያዩ ልማዳዊ ሥርዓቶችን ይፈፅማሉ፡፡ እንደ ማኅበረሰቡ እሳቤ "የቆሌ ማረፊያ፤ የአጋንንት ማደሪያ፣ የሰይጣን መደበቂያ" የሚባሉ ዕፅዋትን (ዋርካ፣ ሾላ፣ ዋንዛ) ከአካባቢያቸው ሲያርቁ፤ በአንፃሩ "ለአጋንንት ማስወጫና ማስለፍለፊያ፤ ለክፉ መንፈስ ማባረሪያ እና ለፈውስ ይበጃሉ" የሚሏቸውን ዕፅዋት (ብሳና፣ ጠመናይ፣ ቀበርቾ፣ ስሚዛ፣ ግራዋን) በማቅረብ፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ ከሥነ ምህዳር ጋር ያለውን ዐውዳዊ መስተጋብር ድንበር፣ ገደብና ዐውድ ለይቶ ዕለታዊ ሕይወቱን ሲከውን ይታያል፡፡ ለምን ያርቃሉ/ያቀርባሉ? የእሳቤው ማዕከላዊ ጉዳይ ምንድን ነው? የሕመም መንስኤ እና ሥነ ምህዳር ምን ዓይነት መስተጋብር አላቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቶ ምላሽ ለመስጠት የታለመ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ሁለተኛ፡- ይህ ጥናት በሚካሄድበት አካባቢ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የሕሙማንን አካላዊ አቋም፣ ንግግር፣ ስሜት፣ ግንባር፣ አንገት፣ እጅ፣ ደረት፣ በእጃቸው እየዳሰሱ፤ ሽንት እና ዓይነ ምድራቸውን በማየትና በመጠየቅ እንደ ሕመማቸው "ጠባይ" መድኃኒት አዘጋጅተውና ቀምመው ሲሰጡ ይታያል፡፡ በአግባቡ ምርመራ አድርገውና የበሽታውን ዓይነት ለይተው መድኃኒት ሲሰጡ የፈውስ መንገድ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በአንፃሩ "በምርመራ ስህተት እና አተገባበር ሕሙማን ለከፋ ስቃይና ሞት ይዳረጋሉ" ተብሎ የሕክምና መስኩ ይታማል፡፡ ይህን ተግባር ታሳቢ በማድረግ፤

[10] በ2009 ዓ.ም፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች የሚሰጠውን "Issues in Popular Culture and Environmentalism" ኮርስ ስከታተል፤ የባህል ሕክምና ሙያ እና የሥነ ምህዳር መስክን አጣምሮ ለማጥናት መንገድ ከፍቶልኛል፡፡ ለዚህ ምርምር መነሻ በመሆን፣ የመስክ መረጃዎችን ለመቃኘት እና ይዘታቸውን ለመለየት፤ የምርምር ክፍተቶችን ለማጤን እና ዝግጅት ለማድረግ፤ አግዟል፡፡ ጥናቱን በደቡብ ጎንደር ዞን ለማካሄድ፣ አካባቢውን ለመተዋወቅ፣ የመረጃ ዓይነቶችን ለመለየት እና ርዕሰ ጉዳዩን ለመወሰን በር ከፋች ሥራ ነበር፡፡ ጠቅለል በአለመልኩ የባህል እና የሥነ ምህዳር መስተጋብር የሚዳስስ ኮርስ መማሬ፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን ለመመርመርና ለመፈተሽ አዎንታዊ ተፅእኖ ያሳደረብኝ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው? የሕክምና ዕውቀቱ ማሕቀፍ ምንድን ነው? የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች ምንድን ናቸው? እንዴት ይከወናሉ? የምርመራ ዘዴና ሥነ ምህዳር ምን ዓይነት መስተጋብር አላቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የታለመ መሆኑ፤

3ኛ. የማኅበረሰብ ልማድ፣ የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ በሥነ ምህዳር ዐውድ ይወሰናል (Huffored, 1986; P. 307: Alemayehu, 1984; PP.122-126: Kapchan, 1995; PP481-485)፡፡ ቅኝት በአደረኩባቸው ወረዳዎች የሚገኙ የባህል ሐኪሞች፤ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ ከሥነ ምህዳር ዐውድ ጋር በእጅጉ የተገናኘ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በተለይ የሥነ ምህዳር ሚዛን መዛባት፣ የዕፅዋትና እንስሳት መጥፋት ለባህል ሕክምና ዕውቀትና ተግባር መዳከም ጉልህ ሚና እንዳላቸው ይታሰባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፤ የዕፀ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት "በልማድ የተንጠለጠለ፤ መመሪያና ማሕቀፍ የሌለው፤ በግለሰብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው" ተብሎ በዘመናዊ ሐኪሞች ይታማል፡፡ ከዚህ አንጻር፤ የባህል ሕክምና ልማድ  እና ሥነ ምህዳር ምን ዓይነት ዐውዳዊ መስተጋብር አላቸው? የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ክዋኔ እንዴት ይተገበራል? የዕውቀቱ መሰረትና ማሕቀፍ ምን ይመስላል? የባህል ሕክምና ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አስተዋፅኦ አለው? የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮችን አንስቶ ለመተንተን፤ የታለመ መሆኑን ልብ ይሏል፤

3ኛ. ከአጥኚው ልምድ እና ተመክሮ አንጻር

አንደኛ፡- የሕይወት ልምድን ይመለከታል፡-

> በጠራራ ፀሐይ በወንዝ ዳር አትቀመጡ ጅን ይመታችኋል፤ ቆሻሻ በተደፋበት፣ አመድና አተላ በፈሰሰበት ቦታ አትሂዱ አጋንንት ይጣላችኋል፡፡... ለሆድ ቁርጠት አቱች አኘካችሁ ምጠጡበት፤ ለራስ ፎረፎር የባድማ ጠባቂ ቅጠል ጨቅጭቃችሁ ለጥፉበት፤ ለሽረሪት ቁስል ምስር አኝካችሁ ትፉበት፤ የሕጻን ልጅ ዕንጥል ሲወርድ በአናቱ (በመሃል እርግብግቢቱ) የሎሚ ዉኃ አፍሳችሁ፣ አመድ ነስንሱበት፤...

ይባላል፡፡ አባቴ ሰውም ሆነ እንስሳት ሲታመሙ መድኃኒት አዘጋጅቶ ይሰጣል፡፡ ...በወቅቱ ለምን ይህን አድርግ/አታድርግ እንደሚለኝ አይገባኝም ነበር፡፡ ከመስክ ቆርጦና ሰብስቦ የሚያመጣቸውን የመድኃኒት ግብዓት፤ ለሰው ብናገር፣ ባመለክትና ባስተምር "መድኃኒቱ ይረክሳል፤ አጋንንት ልሳንህን (አንደበትህን) ይዘጉታል፤ ዓይንህን ያጠፉታል፤ እዚህ ቦታ አትሂድ" በማለት ይመክረኝ

ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር፤ ሰው እና አካባቢው (ሥነ ምህዳር) ምን ዓይነት ዐውዳዊ መስተጋብር አላቸው? እንዴት የሕመም መንስኤ ይሆናሉ? የበሽታ መለያ ስልቶች ምንድን ናቸው? ሰው ለአካላዊ ሕመሙና ለንፈሳዊ ጭንቀቱ ፈውስ ለማግኘት፤ በአካባቢው የሚገኙ ዕፅዋት፣ እንስሳትና ማዕድናትን ይጠቀማል (Yoder, 1972: Hurreize, 2006: Sutton and Anderson 2010)፡፡ ይህ ተግባር እና መስተጋብር በምን ዓይነት ዕውቀት ላይ የተመሰረተ ነው? እንዴት ይከወናል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የታሰበ መሆኑ፤

ሁለተኛ፡- በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በዐባይ ምርምር ማዕከል "በአገር በቀል ዕውቀት ዘርፍ/ ክፍል" አስተባባሪ በነበርኩበት ጊዜ፤ ከአማራ ክልል የባህል ሕክምና አዋቂዎች ማኅበር እና ከአማራ ክልል ጤና ቢሮ ባለሙያዎች ጋር ስለባህል ሕክምና እድገትና ተግዳሮት ተከታታይ ውይይቶችን አካሂጃለሁ[11]፡፡ ይህን መልካም አጋጣሚ ታሳቢ በማድረግ የባህል ሕክምና ዘርፉን ለማጥናት አመቺ ሁኔታን ፈጥሮልኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፤ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች፤ "ሃገረሰባዊ መድኃኒት" (Folk medicine) የሚል ኮርስ ማስተማሬ እና ከተማሪዎች ጋር በነበረኝ ቆይታና ውይይት፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር እንደማኅበረሰቡ ልማድ፣ ተመክሮ እና መልክዓ ምድራዊ ሁነት የሚለያይ ቢሆንም፤ በሕመም መንስኤ፣ በምርመራ ዘዴ፣ በዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ክዋኔ፤ በባህል ሕክምና እና በሥነ ምርዳር መስተጋብር ላይ የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች አለማግኘቴ (በዚህ ጥናት የተዳሰሱትን ቅኝቶች ልብ ይሏል)፤ ርዕሰ ጉዳዩን በትኩረት እንዳጠናው አነሳስቶኛል፤

4ኛ. በቀደምት ጥናቶች ያልተዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ፤

ቀደምት በዘርፉ የተካሄዱ[12] የፎክሎር፣ የታሪክ፣ የሥነ ሰብ፣... ጥናቶች ትኩረት፤ ማኅበረሰቡ ለባህል ሕክምና ባለሙያዎች ያለውን አመለካከት፤ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ፣ ለዘመናዊ ሕክምና ያለውን አስተዋፅኦ፣ ጥምር የሕክምና አሰጣጥ ሥርዓት ጠቀሜታን፣ ፈትሸዋል

[11] በባሕር ዳር ዩኒበርሲቲ የዐባይ ጥናትና ምርምር ማዕከል በአዘጋጀው ዐውደ ጥናት፤ በአማራ ክልል ከሚገኙ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች (ተወካዮች) ጋር በመነጋገር ከ2008-2010 ዓ.ም የባህል መድኃኒት ዐውደ ርዕይ ቀርቧል/ተካሂዷል፡፡ ይህን ንዑስ ዘርፍ ሳስተባብር ከባህል ሕክምና ባለሙያዎች ጋር እንድተዋወቅ መልካም አጋጣሚ ፈጥሮልኛል፡፡

[12] ዓለማየሁ (2000)፣ ምህረት (2000)፣ መስፍን (2002)፣ ተመስገን (2003)፣ ደነቁ (2003)፣ ፍቅርተ (2009)፣ ዐቢዩ (2010)፣ ማኅሌት (2011)፤ Young (1970), Assefa (1992), Mirgissa (1993), Abraraw (1998), Zerihun (2001), Fekadu (2001), Wondwosen (2006), Mekonen W.(2008), Mekonen M.(2010), Tebaber (2015) እና አሰፋ (2008) ናቸው፡፡

(Mekonen, W. 2008: Wondwosen, 2006)፤ የማኅበረሰብን ጤና በማስጠበቅ ረገድ የባህል ሕክምና አስተዋጽኦና ሚናን ዳሰዋል። የሕክምና ዘርፉ አካባቢያዊ ዕውቀትን፣ ልማዳዊ እና እምነታዊ ሥርዓትና ተግባርን መሰረት ያደረገ መሆኑን ገልፀዋል (ዓለማየሁ፣ 2000፤ መስፍን፣ 2002፤ ተመስገን፣ 2003)። የባህል ሕክምና ጥበብ መተላለፊያ ስልት፣ መንገድና ታሪክን ቃኝተዋል (Mekonen M. 2010; አሰፋ፣ 2008)። ይህን የጥናት ክፍተት ታሳቢ በማድረግ የባህል ሕክምና እና የሥነ ምህዳር መስተጋብርን መርምሯል። ጥናቱ የሚከተሉትን የምርምር ክፍተቶች በመለየት፤ ተግባራዊ አድርጓል፦

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን በመመርመር፤ ማኅበረሰቡ ለበሽታና ለሕመም መንስኤ ምን ዓይነት እሳቤና አተገባበር አለው? የባህል ሕክምና ባለሙያዎች የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው? የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ክዋኔ እንዴት ይተገበራል? የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አስተዋፅኦ አለው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል። እነዚህን ጥያቄዎች ከግብ ለማድረስ የጥናቱ ዐቢይና ንዑስ ዓላማዎች ይዘት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 1.3 የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ የሚካሄደውን፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን መተንተን ነው። ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አካቷል፦

- ✓ በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤን መግለፅ፤
- ✓ በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎችን ማብራራት፤
- ✓ በባህል ሕክምና የመድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔን መተንተን፤
- ✓ የባህል ሕክምና ዕውቀት (የማኅበረሰብ ልማድ) ለሥነ ምህዳር ጥበቃ (ደህንነት) ያለውን አስተዋፅኦ መለየት፤ የሚሉ ናቸው።

### 1.4 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በምርምሩ ሂደትና አተገባበር ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል ፡-

1ኛ. በባህል ሕክምና/በማኅበረሰቡ እሳቤ የሕመም መንስኤ ምንድን ነው?

2ኛ. በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው? የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች እንዴት ይከወናሉ?

3ኛ. በባህል ሕክምና ልማድ፤ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ እንዴት ይተገበራል?

4ኛ. የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አስተዋፅኦ አለው? የማኅበረሰብ ልማድ ሥነ ምህዳርን እንዴት አስጠበቀ/አራቆተ? ለምን? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

### 1.5 የጥናቱ ፋይዳ

ይህ ጥናት፤ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብን የባህል ሕክምና ዕውቀትና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን ፈትሾ፣ ዕውቀትና ተግባሩን መተንተኑ፤ ለአካባቢው ማኅበረሰብና ለባህል ሕክምና ምርምር ዘርፍ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይታሰባል፡፡

1ኛ. ይህ ጥናት ባህል፣ ጤና እና ሥነ ምህዳርን በማገናኘት፤ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እና የባህል ሐኪሞች ለጤና፣ ለበሽታ/ለሕመም መንስኤ ያላቸውን እሳቤና አተያይ፣ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ፤ ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸውን መስተጋብር መርምሯል፡፡ የጥናቱ ውጤትም የዞኑን ማኅበረሰብ የሕመም መነሻ እሳቤን ያስረዳል፡፡ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ የሚሰጡ የጤና መጠበቂያ፣ ማስተማሪያና ግንዛቤ መፍጠሪያ "ማኑዋሎች" ዝግጅት የአካባቢውን እሳቤና ዐውድ መነሻ በማድረግ ለማዘጋጀት ይጠቅማል፡፡ ከባህል፣ ከጤና፣ ከሥነ ምህዳር የተገናኙ የማኅበረሰብ ጤና ፖሊሲ አውጪዎች፣ ለባህላዊ መድኃኒት አስተዳደር ቢሮ፣ ለብሔራዊ ዕፅዋት ምርምር ማዕከል፣ ለዘመናዊ ሕክምና፣ ለባህላዊ መድኃኒት ጥናት፣ ለቅድመ በሽታ ክትትልና ቁጥጥር ለሚያደርጉ ጤና ቢሮዎች፣ ለሥነ

ምህዳር ጥበቃ (ለተፈጥሮ ሐብት፤ ለዱርና እንስሳት ባለሙያዎች)፣ ለሕግና ደንብ አውጪ አካላት፤ መረጃዎችን በመጠቀም ያገለግላል[13]፡፡

2ኛ. የባህል ሕክምና ዕውቀትን ለማሳደግ እና የአካባቢ ሥነ ምህዳርን ለመጠበቅ ዓላማና ግብ ለአላቸው፤ የባህል (ዕፀ) መድኃኒት አሰባሰብ፣ አዘገጃጀት፣ አያያዝ፣ አጠቃቀም፣ አሰጣጥና መመሪያ ይዘትን ለመጠቆምና ዕውቀቱም እንዲሰነድ፤ እንዲሻሻል ፍንጭ ለመስጠት፤ በባህል ሕክምና ዘርፍ ቁጥጥር፣ ክትትል፣ ድጋፍና ስልጠና ለሚሰጡ የጤና ተቋማት፤ በዘርፉ ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ ባለሙያዎች፤ መንግስታዊ በሆኑና ባልሆኑ ድርጅቶች፣ ለክልሉ ወረዳና ጤና ቢሮዎች፣... እንደመረጃ ምንጭ ያገለግላል፡፡

3ኛ. የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብን፤ የባህላዊ ሕክምና አገልግሎት፣ ሥርዓት፣ የዕፀ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን ፋይዳና ተግዳሮት ለይቶ የመፍትሔ ሐሳቦችን መጠቆሙ፤ ሃገረሰባዊ ልማዶችን «Social Folk Customs» ለሚያስተምሩ እና ሃገረሰባዊ መድኃኒትን «Folk Medicine» ለሚያጠኑ የፎክሎር፣ የማኅበረሰብ፣ የሥነ ሰብ፣ የታሪክ፣ የሥነ ሕይወትና የሕክምና ተመራማሪዎች እና ባለሙያዎች የመረጃ ምንጭ በመሆን ይጠቅማል፡፡

---

[13]የጤና ማስተማሪያና መከታተያ ቅፅና ሰነዶችን ይዘት አይተሃል? ይዘታቸውን ገምግመሃል? ምን ዓይነት ክፍተት አለባቸው? የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የማኅበረሰብ ጤና መከታተያ ቅፅና ሰነዶች በየጤና ቢሮው ይገኛሉ፡፡ ቅጾቹ፤ በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ የተዘጋጁ ሰነዶች ናቸው፡፡ እነዚህን ቅጾች ተቀብሎ ከመተግበር ባለፈ የአካባቢውን ተጨባጭ ዐውድና የማኅበረሰብ እሳቤ፣ የአኗኗር ልማድ፣ የሕይወት ፍልስፍናን መሰረትና መነሻ አያደርጉም፡፡ ለዚህ ትዝብት አጭሩ ማስረጃ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በየቀበሌው "ጎጥ" /ሰፈር ይገኛሉ፡፡ ከማኅበረሰቡ ጋር ያላቸው መስተጋብርና ከጤና ባለሙያዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ሁለት ዓይነት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

"አኗኗራችን ማኅበረሰቡን፤... ሣይንሳዊ ዕውቀታችን የጤና ባለሙያውን ይመስላል፤ ከማኅበረሰቡ ጋር ስንኖር አብረን እንበላለን እንጠጣለን፤... ከዞንና ከወረዳ የሚሰጠንን መመሪያ ይዘን ማኅበረሰቡን እናስተምራለን፡፡ ...አንዳንዱ እቅድ ተግባራዊ ይሆናል፤ ሌላው ደግሞ በጅምር ይቀራል፤ ...አፈጻጸምና ግምገማ እየተባለ በወር፣ በሶስት ወር፣ በስድስት ወር ሪፖርት ይቀርባል፡፡ የምንሰጠው ትምህርትና የማኅበረሰቡ ተቀባይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ቢመጣም አጉል ባህል፣ እምነት፣ ዛር፣ ቡዳ፣ የሚባሉ ተግባራትን ሙሉ በሙሉ ማቆም አልተቻለም፤ "የእናት አባት ጣጣ ነው" ይሉሃል፤... ቡዳ እንዳለ እኔም አምናለሁ፤ እርድ ይፈጸማል፤ ጽዳት የለም፤ ሽንት ቤት አስቆፍረህ ዘወር ስትል፤ ስድስት ውር ሳይሞላው "ተደረመሰ" ይልሃል፤... አንዳንድ ጊዜ ለመግባባት ይከብደናል፡፡... መድኃኒት ለየወረዳው በኮታ ይከፋፈላል፤ አንዱ ወረዳ ቶሎ ያልቃል ሌላው ወረዳ ሳይጠቀሙት ይበላሻል፡፡ በመድኃኒት ስርጭት ላይ ክፍተት አለ፡፡ አንተ እንደምትለኝ ደጋ፣ ቆላ ብለው መድኃኒት አያድሉም፤ የቀበሌውን ሕዝብ ቁጥር ነው የሚያዩት፤... ከክልል ተዘጋጅቶ የመጣውን መመሪያ ተከትለን በዘመቻ መስራትና ማስተማር ነው ያለው" (አቶ ዐባይ፤ ቃለመጠይቅ፣ 30/05/2011) በማለት ያስረዳሉ፡፡ ለማኅበረሰብ ጤና ማስተማሪያ የሚዘጋጁ መጻሕፍት ከማኅበረሰቡ የዕለት ሕይወትና አኗኗር ፍልስፍና ጋር ቢገናኙ፤ በዞን፣ በወረዳ፣ በቀበሌ የተዘጋጁ ማስተማሪያ ሞጁሎች፤ የአካባቢያቸውን ተጨባጭ ዐውድ መነሻ ቢያደርጉ፤ የመማር ማስተማሩን ሂደትና ግንኙነት ከማጠናከሩም ባለፈ የጤና እቅዶች ተፈጻሚና ቀጣይነት እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡

4ኛ. በባህል ሕክምና ዘርፉ የሚታዩ የምርምር ክፍተቶችን በመቃኘትና በመለየት፤ ከሥነ ምህዳር ጋር ያለውን ዐውዳዊ መስተጋብር በመመርመር፤ ለባህል ሕክምና ዘርፍ ጥናት መዳበር እና ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን ፋይዳና ተግዳሮት መጠቆሙ፤ የማኅበረሰቡን እሳቤ፣ ዕውቀትና ተግባር ከባህል፣ ከሥነ ምህዳር፣ ከሕመም እና ከጤና አንጻር መሰነዱ ወቅታዊ ሁነትና አስተሳሰብን ለመጠቆም፤ ይጠቅማል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት፤ ከርዕሰ ጉዳይ፣ ከቦታ፣ ከጊዜና ከተጠኚ አካላት አንፃር ትኩረትና ገደቡን ወስኖ ተነስቷል። ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር፤ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ በተመረጡ ወረዳዎች የሚካሄደውን የባህል ሕክምና[14]ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን በመፈተሽ፤ የሕመም መንስኤ፣ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ክዋኔን ታሳቢ በማድረግ፤ የባህል ሕክምና ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን አስተዋፅኦ መርምሯል።
ምርምሩ ከባህል ሕክምና ዘርፍ፤ በተፈጥሯዊ (ዓለማዊ) የባህል ሕክምና ምድብ ሥር ይካተታል። በዚህ ምድብ ውስጥ ከሚጠቀሱ ንዑስ ይዘቶች (የዕፀ መድኃኒት አዋቂ፣ ወጌሻ፣ አዋላጅ፣ እንጥል ቆራጭ) መካከል፤ የዕፀ መድኃኒት አዋቂዎችን[15] (የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የማዕድናት፣ የነፍሳት እና የዉኃማ አካላት ግብዓቶችን የሚጠቀሙ ባለሙያዎችን) ነጥሎ ዕውቀትና ተግባራቸውን አጥንቷል። ጥናቱ፤ የመድኃኒትን ንጥረ ነገር፣ ይዘት፣ በሽታን የማዳን ኃይልና ጊዜን አይፈትሽም። ለምን? ሲባል፤ ለመድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶች የንጥረ ነገር (የኬሚካል) ልኬት፣ መጠንና ደረጃቸው በቤተ ሙከራ ተፈትሸው፤ የጥቅምና የጉዳት መጠናቸው፤ ኃይልና ጉልበታቸው በዕፅዋት ሣይንስና በጤና መስክ በተሰማሩ ባለሙያዎች የሚለዩና የሚጠኑ መሆናቸው፤ ከዚህ ጥናት ዓላማና አድማስ ውጪ መሆናቸውን ልብ ይሏል።

ጥናቱ ከቦታ አንጻር ሲቃኝ፤ በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ የሚገኙ ሶስት (ፋርጣ፣ ሊቦ ከምከም እና እብናት) ወረዳዎችን መርጧል። እነዚህ ወረዳዎች በምን ስሌት? ለምን ዓይነት ዓላማና ተግባር

[14]በኢትዮጵያ ከ80 ሺህ በላይ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች እንደሚኖሩ (ፈቃዱ 2002፤ገ.31) ይገመታል። በአማራ ክልል በባህል ሕክምናው ዘርፍ የተሰማሩ ከሁለት ሺህ (2000) በላይ የባህል ሐኪሞች እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ (Wondosen: 2006,44; Fekadu: 2001):: የአማራ ክልል የባህል ሐኪሞች ማኅበር ፀሐፊ መሪጌታ ብሩህ ዘላለም በደቡብ ጎንደር ዞን በአማካይ 450 የባህል ሐኪሞች እንደሚገኙ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤18/02/2011 ፋርጣ)።
[15]በዚህ ጥናት የዕፀ መድኃኒት አዎቂዎች (ባለሙያዎች) ሲባል፤ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት፣ ከአዕዋፍ፣ ከማዕድናት፣ ከነፍሳት እና ከዉኃማ አካላት የሚገኙ የመድኃኒት ግብዓትን በማሰባሰብ፤ በሽታን ለመፈወስ እና ለመከላከል ጥረት የሚያደርጉ የባህል ሐኪሞችን ይመለከታል።

ተመረጡ? ሲባል አንድም የወረዳዎቹን የዐየር ንብረት እና መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥን ታሳቢ በማድረግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የበሽታ እና የዕፀ መድኃኒት ዓይነቶች፣ መገኛ ቦታዎች ልዩነትን እንደ መነሻ ምክንያት በመውሰድ በሶስት ወረዳዎች ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በሶስቱም ወረዳዎች 114 (43፣ 34፣ 37 በወረዳዎቹ ቅደም ተከተል) ቀበሌዎች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ቀበሌዎች መካከል፤ ቦታን፣ ጊዜን፣ ዓላማና ወጪን፤ የአካባቢውን መልክዓ ምድር (ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ ቦታዎችን)፤ የባህል ሐኪም መገኛ ቦታዎችን እና ለጥናቱ አንጻራዊ በሆነ መልኩ አመቺ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት በ16 (በፋርጣ 5፤ በሊቦ ከምከም 6 እና በእብናት 5) ቀበሌዎች ምርምሩ ተካሂዷል:: በጥናቱ ሂደት 76 የመስክ መረጃ ሰጪዎች የተሳተፉ ሲሆን የአካባቢውን ማኅበረሰብ ሃይማኖት፣ ብዛትና ተደራሽነትን እንደ መነሻ ምክንያትና አስገዳጅ ሁነት በመውሰድ፤ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮችን ብቻ የጥናቱ ትኩረትና ገደብ አድርጓል፡፡

የጥናቱ ገለፃ፣ ውይይት እና ትንተና፤ ዕይታዊ መሰረት (Philosophical Foundation) "ተርጓሚ የዕይታ መንገድን" (Interpretive Paradigm) በመከተል እና ኢትኖግራፊያዊ (Ethnography) ስልትን በመተግበር የመስክ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ የትንታኔ ማሕቀፉ (Analytical Framework) አንፃር ሰው፣ ባህል፣ ሕመም እና ሥነ ምኅዳር ሲሆኑ፤ አላባውያን ደግሞ የአካባቢው የባህል ሐኪሞች፣ ታካሚዎች፣ አዛውንት አባትና እናቶች፣ የጤና፣ የተፈጥሮ ኃብት፣ የባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎችን ይመለከታል (ለተጨማሪ መረጃ፤ የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ ንዑስ ክፍል 3.3 ይመልከቱ)፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት፤ ከርዕሰ ጉዳይ ገደብና ይዘት፣ ከምርምሩ ዓይነትና ባሕርይ፣ ከመረጃ ሰጪዎች ዕውቀት (ባህል/ልማድ፤ የግለሰብ፣ የቡድን እና የማኅበረሰብ አካባቢያዊ ዕውቀት፣ እምነት እና ተግባር ውጤት ነው)፤ ከንድፈ ሃሳብ ገደብና አንፃር፤ ውስንነት እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

1ኛ. ጥናቱ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብን መሰረት በማድረግ፤ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተካታዮችን ብቻ፤ ነጥሎ በማውጣት የጥናቱ ትኩረትና ወሰን አድርጓል፡፡ ለምን? ሲባል፤ በአካባቢው ጎልቶ የሚታየው እና 98% (ዘጠና ስምንት ፐርሰንት) የሚሸፍነው ማኅበረሰብ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ቀሪ 2% (ሁለት ፐርሰንት) የእስልምና እና ሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችን ይወክላል (በአካባቢው ይኖራሉ)፡፡ የእነዚህን ማኅበረሰብ አባላት እሳቤ፣ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ጥበብ፣ ልማድና ክዋኔ ባለማካተቱ እና የደቡብ ጎንደር ዞን ሕዝብን

ሙሉ በሙሉ ወካይ ባለመሆኑ፤ ውስንነት ይታይበታል፡፡ ለምን ቀሪዎቹን የማኅበረሰብ አባላት (ሃይማኖት ተከታዮች) አላካተተም? ሲባል፤ ውስንነቱ ከጥናቱ ዓይነትና ባሕርይ ይመነጫል፡፡

ምርምሩ በልማድና በክዋኔ የሚቀርቡና የሚተገበሩ እሳቤዎችን፣ ዕውቀትና ክህሎትን መሰረት አድርጓል፡፡ እነዚህን ተግባራት ለማጥናት በአካባቢው ጎልቶ የሚታየውን ሃይማኖት (ቡድን) በዓላማ ተኮር ናሙና መርጦና ነጥሎ አጥንቷል፡፡ የመስክ መረጃዎችን የጋራ ባሕርይ፣ ክዋኔ፣ ሥርዓት፣ ድግግሞሽና ማሕቀፍን በመለየት፤ የክዋኔ እና የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴሎችን እንደ ጥናት መተንተኛ ስልት ተጠቅሟል፡፡ በተለይ የክዋኔ ንድፈ ሃሳብና ሞዴል የአንድ ቡድን ክዋኔ፣ ሥርዓት፣ ተግባር፣ እሳቤ፣ ዕውቀትና ክህሎትን ለመተንተን፣ ለማስረዳትና ለመተርጎም አመቺና ተመራጭ እንደሆነ ምሁራን ገልፀዋል (Bauman, 1977; 1986; 1992: Ben-Amos,1993; 1997: Sims and Stephens, 2005)፡፡ የተጠኚው ቡድን ዓይነት እና አላባውያን ሲቀየሩ እሳቤው፣ ክዋኔው፣ ሥርዓትና ተግባሩ፤ በመጠኑ፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ይለወጣል፤ ቀጣዩ ቡድን በሃይማኖት፣ በሥርዓትና ተግባር፣ በሙያ… ይለያል፤ በዚህ ሂደት በተለያየ ቡድን ውስጥ ተመሳሳይ ይዘትና ተግባር ማግኘት ይከብዳል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፤ ጥናቱ ተተኳሪ ያደረገውን ማኅበረሰብ/ቡድን ወካይ ሲሆን፤ የሌሎች ሃይማኖት ተከታይ ማኅበረሰብ አባላትን ዕውቀትና ተግባር ባለማካተቱ፤ ውስንነት ይታይበታል፡፡

ቀጣይ ምርምሮች ቀሪ የማኅበረሰብ ቡድኖችን (የሃይማኖት ተከታዮችን) በትኩረት አጥንተው ሲጨርሱ፤ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ወካይ የሆነ የወልና የጋራ ዕውቀት፣ ክዋኔ፣ ልማድ፣ ሥርዓትና ተግባርን በተሟላ ደረጃ ለማውጣት ንፅፅራዊ ጥናት ማካሄድን ይጠይቃል፡፡ በሂደትም የምርምሮቹን አንድነትና ልዩነት በማነጻፀር፣ በማመሳከርና በማወዳደር፤ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብን የባህል ሕክምና ዕውቀትና ተግባር ሙሉ በሙሉ ወካይ የሚሆን ጥናት ማግኘት እንደሚቻል ይታመናል፡፡

2ኛ. ጥናቱ፤ የሕመም መንስኤ፣ ሥነ ዕውቀት፣ የማኅበረሰብ ግንባታ፣ ዐውድ ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት አድርጓል፡፡ ከተጠቀሱት ንድፈ ሃሳቦች በተጓዳኝ የመስክ መረጃዎች፤ የሥነ ልቡና፣ የተግባራዊ፣ የሥነ መዋቅር፣ "የሴሚዮቲክስ" ንድፈ ሃሳቦችን እና እሳቤዎችን የሚጠሩ ቢሆንም በጥናቱ ይዘት አልተካተቱም፡፡ ከነዚህ አተያዮች፣ ተግባርና ይዘት አንጻር ሲቃኝና ሲታይ፤ ጥናቱ ውስንነት እና ገደብ እንዳለው ይታሰባል፡፡

## 1.8 የጥናቱ አደረጃጀት እና የምዕራፎች ይዘት

ይህ ጥናት፤ መግቢያና ማጠቃለያን ጨምሮ ዘጠኝ ምዕራፎችን አካቷል፡፡ እነዚህ ምዕራፎች በሶስት ጥቅል ማሕቀፍ ተደራጅተው የቀረቡ ሲሆን ከምዕራፍ አንድ እስከ አራት የቀረቡ ይዘቶች፤ የምርምሩን ዳራ፣ ዓላማ፣ ተግባር፣ ሂደት እና ማዕከላዊ ጉዳይ የሚያስተዋውቁ ናቸው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ከምዕራፍ አምስት እስከ ስምንት የቀረቡ ይዘቶች ደግሞ የምርምሩን ትንታኔ ክፍል ይሸፍናሉ፡፡ ትንታኔዎቹ፤ የጥናቱን ዓላማዎች መነሻ በማድረግ ተደራጅተው የቀረቡ ሲሆን፤ የመስክ መረጃዎች ተሰብስበው፣ በዓይነት እና በይዘት ተለይተው፤ ከጽንሰ ሃሳብ፣ ከንድፈ ሃሳብና ከመተንተኛ ሞዴሎች ጋር ተገናዝበው፤ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ ይሁንታ እና ዋቢዎችን የሚመለከቱ ይዘቶች ተካተዋል፡፡ እነዚህ ይዘቶች የጥናቱን ማጠቃለያ፣ ግኝት እና ጭምቅ ሃሳብ በመጠቆም፤ ይሁንታና ዋቢዎችን አጠቃለው ይዘዋል፡፡ ከዚህ በታች የምዕራፎቹ ርዕስ ጉዳይ እና ትኩረት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የመጀመሪያው ምዕራፍ፤ የጥናቱ መግቢያ እና ማስተዋወቂያ ክፍል ሲሆን፤ የጥናቱን አጠቃላይ መልክ፣ ትኩረት፣ መዋቅር እና ሂደት ይገልፃል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሥር፤ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ ፋይዳ፣ ወሰን፣ የጥናቱ ውስንነት እና አደረጃጀት ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት የጥናቱ ክለሳ ድርሣናት የተካሄደበት ክፍል ሲሆን፤ ለምርምሩ መነሻ፣ ደጋፊና መሰረት የሆኑ ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራዎች፣ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተካተውበታል። ምዕራፍ ሶስት የጥናቱን "ሥነ ዘዴ" በማስተዋወቅ፤ የመስክ መረጃዎች አሰባሰብ እና አተገባበር፣ አደረጃጀት እና አተናተን ሂደቶችን ያስረዳል፡፡ በዚህ ምዕራፍ፤ የምርምሩ ዕይታ መሰረት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻሮች፣ ሙያዊ ሥነ ምግባር፣ የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ሞዴሎች፣ የመስክ ልምድና ተመክሮ ቀርበዋል። ምዕራፍ አራት የደቡብ ጎንደር ዞን መልክዓ ምድራዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ዳራን ይመለከታል፡፡ በዚህ ይዘት፤ የዞኑ መልክዓ ምድራዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና መሰል ሁነቶች የተዋወቁበት ክፍል ሲሆን በሥሩ፤ ለጥናት የተመረጡ ወረዳዎች መልክዓ ምድር፣ ሥነ ሕዝብ፣ የትምህርትና የጤና ሽፋን፤ በዞኑ የሚገኙ ዋና ዋና የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሐብቶች፣ የሃይማኖት መስሕብ መገኛ ቦታዎች እና አገልግሎት፤ የማኅበረሰብ እምነቶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡ ከምዕራፍ አምስት እስከ ስምንት የሚገኙ ተከታታይ አራት ምዕራፎች የመስክ መረጃ ትንታኔ ይዘትን ተመልክተዋል፡፡

በምዕራፍ አምስት፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤን ርዕሰ ጉዳይ በማድረግ ትንታኔ ቀርቧል፡፡ በትንታኔው መሰረት፤ የሕመም መንስኤ እሳቤዎች፣ መለከፊያ ዐውዶች፣ መገለጫ ባሕርያት፣ አጋላጭ ሁነቶች፤ የኮከብ ባሕርይ መግነንና መክሰም፣ የወቅቶች ዑደትና መፈራረቅ፤ ለሕመም መንስኤ ምን ዓይነት ተግባርና ይዘት እንዳላቸው፤ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በምዕራፍ ስድስት በባህል ሕክምና የበሽታ የመለያ እና የምርመራ ዘዴዎችን ዓላማ በማድረግ ትንተና ተካሂዷል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች፣ ሂደት፣ ባሕርያት፣ የተቃርኖ ሕክምና፣ የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች ምን ምን ናቸው? እንዴት ይከወናሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ምላሽ ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ ሰባት፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔን የሚመለከቱ ተግባራት ተገልፀዋል፡፡ በገለፃ ሂደቱም፤ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ "ሥርዓተ ገቢር" ዐውዳዊ ክዋኔ፣ የባህል መድኃኒት "ገቢር" ማስተካከያ ዐውዶች፣ የግብዓት ዓይነትና ባሕርያት፣ የቅመማ ሂደትና አሰጣጥ ሥርዓት በዓይነትና በይዘት ተለይተው ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡ በምዕራፍ ስምንት የባህል ሕክምና ዕውቀት (የማኅበረሰብ ልማድ) ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አስተዋፅኦ እንዳለው፤ የመስክ መረጃዎችን ዋቢ በማድረግ ምላሽ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም፤ (በምዕራፍ ዘጠኝ) የጥናቱ ማጠቃለያ፣ ይሁንታ፣ ዋቢዎችና አባሪዎችን በማካተት፤ ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

-

# ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሣናት

በዚህ ምዕራፍ ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ፣ ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 2.1 ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ፎክሎር (ባህል)፣ ጤና እና ሕመም፤ ሥነ ምህዳር፤ የባህል መድኃኒት/ሕክምና፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር፤ የባህል ሐኪም ማንነት፣ የባህል ሕክምና ማሕቀፍ እና ምድብ፤ በባህል ሕክምና የበሽታ መንስኤ እሳቤ፤ በባህል ሕክምና የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች፤ የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ እና ሥነ ምህዳር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1 የፎክሎር (ባህል)፣ ጤና እና ሕመም ምንነት

ፎክሎር[16]፤ ውስብስብ ባሕርይ፣ ተግባር፣ መገለጫ እና ይዘት ያለው፤ የማኅበረሰብ ልማድን፣ ማኅበራዊ መስተጋብር እና እሳቤን መሰረት ያደረገ፤ አካባቢያዊ ዕውቀትን፣ ክህሎትና ተግባርን በማስተባበር የሚከወን፤ ለጤና መጠበቅ/መንደል እና ለሕመም ፈውስ/መንስኤ በመሆን፤ ጉልህ ሚና እንዳለው ምሁራን ያስረዳሉ (Yoder, 1972; PP.194-198: Helman, 1984; PP.7-12: Brady,

---

[16]ፎክሎር ማለት "ፎክ" እና "ሎር" ከሚሉ ሁለት ቃላት ጥምረት የተገኘ ቃል ሲሆን "ፎክ" ማለት የማንኛውም ቡድን፣ ጎሳ፣ ማኅበረሰብ ወይም አካል መጠሪያ ስያሜን ይመለከታል፡፡ እነዚህ ቡድኖች በአንድ የጋራ ጉዳይ የተገናኙ፤ የተሳሰሩ፤ የራሳቸው መለያና የጋራ እሴት ያላቸው…፤ ቡድኖችን ይመለከታል፡፡ ይህ የጋራ እሴት ደግሞ "ሎር" ወይም ዕውቀት/ ጥበብ ይባላል፡፡ ምሁራን ‹‹ሎር›› ለሚለው ጽንሰ-ሃሳብ፤ የሰው ልጅ በማኅበር፣ በጋራና በቡድን ሲኖር በየትኛውም፣ ዐውድና አጋጣሚ፣ ቦታና ጊዜ የሚፈጠር፤ በተግባር፣ በዘመንና በሂደት የሚዳብርና የሚለወጥ፤ ማንኛውም ዓይነት አገር በቀል ዕውቀትን ይመለከታል፡፡ "ሎር" ማለት ጥበባዊ አገላለፅ እና መግባቢያ መንገዶችን (ቋንቋና አካላዊ እንቅስቃሴ) መሰረት በማድረግ የቡድን፣ የማኅበረሰብ እና የሕዝብ የሆኑ በቃል፣ በትውን ጥበብ፣ በልማድ፣ በቁሳዊ ባህል፣ በጽሑፍ፣ በድርጊት አማካይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ፤ የአንድ ማኅበረሰብ እሳቤ፣ ግንዛቤ፣ ፍልስፍና፣ ተመክሮ፣ ገጠመኝ፣ ድርጊት፣ እምነት፣… መለያና መገለጫ የሆነ ዕውቀት እና/ወይም "ጥበባዊ እሴት ነው"፤ በማለት አስረድተዋል (Ben-Amos, 1971: Dorson, 1972: Dundes, 1980: Schoemaker, 1990):: በአጠቃላይ "ሎር" ማለት አንድ ቡድን፣ ጎሳ ወይም ማኅበረሰብ በጋራ ሲኖሩ የሚፈጥሩት፤ የሚከውኑት፤ የሚኖሩት፣ የሚሰሩት፣ የሚናገሩት፣ የሚያስቡት፤...ይዘት፤ ጤናቸውን ለመጠበቅ፤ በሽታን ለመከላከል፤ ከሕመም ለመፈወስ፤ ከሥነ ምህዳር ዐውዶች ጋር ለመግባባት፣ ለመላመድ የሚተገብሩትን ዘዴዎች፣ ስልቶች፣ ጥበቦች፣ አመለካከቶች፣ እምነቶች፣ አምልኮዎች፣ ፍልስፍናዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ የእርስ በርስ ግንኙነቶች፣ ገጠመኞችን፤… አጠቃሎ የያዘ ጽንሰ-ሃሳብ (ዕውቀት/ ጥበብ) ሲሆን እንደማኅበረሰቡ/ ቡድኑ እሳቤ፤ መስተጋብር፤ ዐውድ፤ የኑሮ ደረጃና መልክዓ ምድራዊ ሁነት… ዕውቀቱና ጥበቡ እየተሻሻለ፣ እየተለወጠ፣ እየተተካ፣ እየተወራረሰ፤… ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ፤ የጋራ ዕውቀትን፣ ጥበብና የወል እሴትን እንደሚወክል፤ ምሁራን አስረድተዋል (Dundes, 1980: Oring, 1986: Bauman, 1992: Shoemaker, 1990: Kapchan, 1995)::

2001; P.14)። በአጭሩ ፎክሎር (ባህል)[17] ማለት ምን ማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ ምሁራን እንደሚከተለው ምላሽ ሰጥተዋል፡-

ፈቃደ (1996፣ገ.15)፤ ፎክሎር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ፤ የሰው ልጆችን ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ሕይወት፣ ልማድና ሁለንተናዊ መስተጋብርን የሚያጠቃልል፤ ሰፊና ዘርፈ ብዙ ማሕቀፍ እንዳለው ገልፀው፤ ፎክሎር (ባህል) ማለት "የአኗኗር ዘዴ ወይም ስርዓት ነው" ይላሉ ። Ferraro and Andreatta (2010; P.28) ደግሞ "the way of life of a people" በማለት፤ የአንድ ሕዝብ የአኗኗር ዘዴ መሆኑን ይገልፃሉ። ፎክሎር፤ የሰው ልጆች በሕይወት ሲኖሩ የሚፈጥሩት፣ የሚተገብሩት፣ የሚኖሩት፣ የሚጋሩት፣ የሚዛመዱት፤ የጋራ እና የተለመደ ሕይወት፣ ትውፊት፣ ኢ-መደበኛ፣ ጥበባዊ እና ቀጥተኛ ተግባቦት፣ እሴት፣ ሥርዓት፣ ባሕርይን መሰረት ያደረገ እንደሆነ ምሁራን ይመክራሉ (ፈቃደ፣ 1991፣ ገ.16፤ Oring, 1986; PP.17-18: Schoemaker, 1990; P.2)።

Ferraro and Andreatta (2010; P. 28) "ባህል" ማለት "Culture is that complex whole which includes knowledge, belief, art, morals, law, custom, and any other capabilities and habits acquired by man as a member of society" ዕውቀትን፣ እምነትን፣ ኪነ ጥበብን፣ ሞራልን፣ ሕግን፣ ወግን እና ሌሎች ተግባራትን የሚያጠቃልል ሲሆን ሰው የኅብረተሰቡ አባል በመሆን የቀሰማቸውን ክህሎቶችና ልምዶች ጭምር የሚያካትት ውስብስብ የሆነ ውህድ እንደሆነ፤ አስረድተዋል።

ፎክሎር፤ አካባቢዊና ማኅበረሰብ ተኮር በመሆኑ፤ ክዋኔውና መገለጫዎቹ ከቦታ፣ ከቡድን፣ ከጎሳ፣ ከማኅበረሰብ፣ ከቋንቋ፣ ከመኖሪያ አካባቢ፤... አንጻር ይለያያል። ይህም ሰው ከአካባቢው (ሥነ ምህዳር) ጋር ያለው መስተጋብራዊ ዕውቀት፤ ልማዳዊ ሥርዓት (ከአካባቢው ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ መልክዓ ምድራዊ ሁነት፣ የእንስሳት እርባታ፣ የንብ ማነብ፣ የግብርና ሥርዓት፣ የባህል መድኃኒት/ሕክምና ክህሎት፤...) አካባቢያዊ ዕውቀት (አገር በቀል) እና ተመክሮን መሰረት ያደርጋል (ፈቃደ፣ 2004፣ ገፅ.108-109፤ Oring, 1986; PP.3-5: Schoemaker, 1990; PP.2-4)።

---

[17]በዚህ ጥናት ዐውድ "ፎክሎር" እና "ባህል" የብያኔና የይዘት ልዩነት ሳይኖራቸው፤ እንደ አስፈላጊነቱ እያፈራረቅሁ የተጠቀምኩ መሆኑን ልብ ይሏል። በአጥኚው ዕሳቤ፤ ለባህል ምንጩና ገባር ወንዙ ፎክሎር ሲሆን ግንዱና መዳረሻው ባህል ነው፤ ተብሎ ይታሰባል። ፈቃደ (2004፣96) "ቁዘማ፦ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ፎክሎርና ባህልን በተጓዳኝ ተጠቅመዋል፤ ወደፊት መላ እስከሚበጅለት በዚሁ መጠቀምን መርጠዋል። ፎክሎር አውዳዊና ጥበባዊ አገላለጽን በመጠቀም ትርጉምና ስሜት በሚሰጥ ቋንቋ የሚቀርብ፤ በምልክት፣ በትዕምርት፣ በእንቅስቃሴ እና በተግባር ላይ የተመሰረተ የጋራ ዕውቀትና እሴት ሲሆን በአነስተኛ ቡድን ውስጥ የሚገኝ ጥበባዊ ተግባቦት ነው፤ ይላሉ (Ben-Amos, 1971; P.13):: Schoemakere (1990; P.3) ፎክሎር የአንድ ማኅበረሰብ፤ ወግ፣ ልማድ፣ ሥርዓት፣ እሴት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ አኗኗር ወዘተ. የሚያጠና ሰፊና ጥልቅ የሆነ የማኅበረሰብ ሳይንስ ዘርፍ ነው። ፎክሎር ጥበባዊ ተግባቦት ሲሆን በሦስት ዘርፍ ከፍለው ሰዎች የሚሉትን (ሥነ ቃል)፣ የሚያደርጉትን (ልማዳዊ ባህል) እና የሚያበጁትን (ቁሳዊ ባህል) በማለት መድበዋል።

Winkelman፤ ባህል ለማንኛውም የጤና ርዕሰ ጉዳይና ተግባር መሰረት እንደሆነ ጠቁመው፤ የጤና ጥበቃን ለማሻሻል ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል ባህል ይጠቀሳል። ባህል በጤና ላይ ከሚያሳድረው ተፅዕኖ፣ ሁነት፣ እምነት እና ተግባር አንጻር መጤን እንዳለበት፤ የማኅበረሰብ ጤና የባህል ሥርዓትን መሰረት ያደረገ ሰፊ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚያካትት በየሙያ መስኩ የተለያየ ተግባር፣ ትኩረትና ይዘት እንዳለው Winkelman (2009;P.2) እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> Culture is the foundation of every one's health concerns and practices. Improving health care requires attention to cultural influences on health concerns, conditions, beliefs, and practices. People's health occurs within cultural systems that are concerned with broader issues of well-being than addressed by physicians' concerns with disease and injury; [Medical Anthropology, Folk medicine, Epidemiology…][18] concerned with psychological, social, emotional, mental, and spiritual well-being. As biomedicine turns from a disease-focused approach to concepts with health and well-being, cultural perspectives and cultural competency emerge as central frameworks for improving care.

ይህን ይዘት ታሳቢ በማድረግ፤ ጤና ማለት ምን ማለት ነው? ሲባል፤ አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ደህንነትን (ይሁኔ፣ 2010፤ ገ.5፤ WHO, 1972; P.9 ጠቅሰው) ይመለከታል። ይሁኔ (2010፣ ገፅ 5-29) ጤና ማለት "የበሽታ አለመኖር ሳይሆን የተሟላ አካላዊ፣ አዕምሯዊና ማኅበራዊ ደህንነት ነው" በሚል የዓለም ድርጅት ያቀረበውን ብያኔ በመተቸት፤ ጤና ማለት ውስብስብ፣ ሰፊና ፈርጀ ብዙ መገለጫዎች እንዳሉት ያስረዳሉ። ሰው፤ የአዕምሮ፣ የአካል፣ የሥሜት፣ የአካባቢና የማኅበራዊ ውስብስብ መስተጋብሮች፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊ ግንኙነት ያለው፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከግለሰቡ ጤንነት እና ደህንነት ጋር እንደሚያያዝ ይገልጻሉ። በተመሳሳይ መልኩ Winkelman፤ "…health involves not only physical, mental, and social well-being but also the ability to participate in every day activities in family, community, and work, commanding the personal and social resources necessary to adapt to changing circumstances." (2009; P.14) እንደሆነ ያስረዳሉ። Helman (1984; P.12) ደግሞ በተለያየ ሁነት የጤና ሚዛን (Balance) ሲጠበቅ ደህንነትን፤ የጤና ሚዛን ሲዛባ (Imbalance) የሕመም መንስኤ መሆኑን ይጠቁማሉ። በአጠቃላይ ባህል ከጤና እና ከሕመም ሥርዓትና እሳቤ ጋር ዝምድና እንዳለው የቀረቡ ምንጮች ይመክራሉ። ከዚህ ይዘት በመቀጠል የሥነ ምህዳር ምንነት፤ እንደሚከተለው ቀርቧል።

---

[18] በአራት ማዕዘን ሣጥን ውስጥ( [ ] ) የቀረቡ ቃላት፣ ፍቺና ይዘት የጥናት አቅራቢው ሃሳብ፣ ትርጉምና ማብራሪያ መሆናቸውን ታሳቢ ያደርጋል።

## 2.1.2 የሥነ ምህዳር ምንነት

ሥነ ምህዳር (Ecology)[19] ማለት፤ የተፈጥሮና "የፍጡራን" ግንኙነት፣ መስተጋብር እና ትስስር የሚጠናበት ሰፊ የምርምር መስክ ሲሆን የሥነ ሕይወታዊ ሁነት (ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ ነፍሳትና ረቂቅ አካላት...) መልክዓ ምድራዊ ይዘት (ዐየር፣ ዉኃ፣ ዐፈር፣ ሙቀት፣ ቀዝቃዛ፣ ከፍታ ዝቅታ...)፣ ባህላዊ ዐውድ (Cultural context)፤ የተፈጥሮ አካላት እና በእነዚህም አካላት መካከል የሚኖር ግንኙነትን ይመረምራል (Benally, 2010; PP.8-13: Sutton and Anderson, 2010; PP.3, 8, 91-96)። ይህንን ሃሳብ Sutton and Anderson "Ecology is the study of the relationships between organisms and their environment, the 'economics' (or livelihood) of the earth and its totality of forms." (2010; P.35) በማለት በይነዋል።

ፊቃዱ (2002፣ ገ.69) ደግሞ፤ ሥነ ምህዳር ሲባል የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የአዕዋፍ፣... ስብስብ እና የእነሱ መኖሪያ ስፍራ፤ የአዕዋፍና እንስሳት ዝርያ፣ የመሬት አቀማመጥ፣ ከፍታ፣ የአካባቢው ሙቀትና እርጥበት፣ የዐፈርና የሥነ ምህዳር ባሕርይና ዓይነትን እንደሚያካትት ያስረዳሉ።

Sutton and Anderson (2010; PP.3-4) የሥነ ምህዳር ጥናት በሁለት ዘርፍ እንደሚከፈል ጠቁመዋል። እነርሱም የሰው ልጅ ሥነ ሕይወታዊ ሥነ ምህዳር (Human life Ecology) እና ባህላዊ ሥነ ምህዳር (Cultural Ecology) ይባላሉ። የሰው ልጅ ሥነ ሕይወታዊ ሥነ ምህዳር ጥናት ትኩረት፤ የሰው ልጆችን ቋንቋ፣ ቅድመ ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ የማኅበረሰብ አደረጃጀትና መዋቅር፣ ኢኮኖሚ እና አዝግሞተ ለውጥ ሂደትን ይመለከታል። ባህላዊ ሥነ ምህዳር ደግሞ የባህሉን መሰረት፣ ምንጭ፣ መንስኤና ምክንያት፤ ማኅበረሰቡ የሚተዳደርበትና የሚኖርበት ሥርዓት፤ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ መዋቅሮችና ደንቦች፣ ባህላዊና አካባቢያዊ መስተጋብርና ኢኮኖሚያዊ ገደቦች፣ መተዳደሪያ ልማዶችን... በዋናነት (Milton, 1996; PP.37-38: Steward, 2006; P.5: Sutton and Anderson, 2010; P.9) ይመረምራል። በዚህ ጥናት ባህል፣ ጤና፣ ሕመምና የሥነ ምህዳር መስተጋብር ማዕከላዊ ይዘት ናቸው፤ እነዚህን ታሳሚ በማድረግ ባህላዊ ሥነ ምህዳር (Cultural Ecology/ Folk Ecology) የዚህ ጥናት ትኩረት መሆኑን ልብ ይሏል።

---

[19] ሥነ ምህዳር "Ecology" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የመጣው "oikos" እና "logos" ከሚሉ የግሪክ ቃላት ሲሆን "oikos" የሚለው ፍቺ፤ መጠለያ "house" ወይም መኖሪያ "habitat" ማለት ነው። "logos" ደግሞ የጥናት መስክ "word/ academic discipline" ወይም ዘርፍ ማለት ነው (Sutton and Anderson, 2010; p.35)።

ፈቃዱ (2006፣ ገ.69፤ ጌታቸው ተስፋዬ እና በሪሁን ገብረመድህን 1996ን ጠቅሰው) በኢትዮጵያ ውስጥ ዐስር ዓይነት የሥነ ምህዳር ቦታዎች እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡ እነርሱም፡-

የተራራማ የሳር መሬት ሥርዓተ ምህዳር፤ የደረቅ ተራሮች ደንና ቅጠላቸው የማይረግፍ ቁጥቋጦ ሥርዓተ ምህዳር፤ የውርጭና ውርጭ ቀመስ ሥርዓተ ምህዳር፤ የግራር ከርቤ ሥርዓተ ምህዳር፤ የእርጥባማ ተራሮች ደን ሥርዓተ ምህዳር፤ የቆላማው ክፍል ሥርዓተ ምህዳር፤ የበርሃማ ክፍል በርሃማ ሥርዓተ ምህዳር፤ የእርጥባማ መሬቶች ሥርዓተ ምህዳር፤ የዉኃ አካላት ሥርዓተ ምህዳር ዓይነቶች በኢትዮጵያ እንደሚገኙ ዘርዝረዋል፡፡

በአጠቃላይ ሥነ ምህዳር ሲባል በተፈጥሮ አካባቢ ውስጥ የሚገኙ ሕይወት ያላቸውና የሌላቸው (ግዑዛን) አካላትን ይመለከታል፡፡ ሥነ ምህዳር፤ ሰው፣ ዕፅዋት እና እንስሳት፣ መልክዓ ምድር፣ የዐየር ንብረት ወዘተ. ጉዳዮችን አካቶ የያዘ፤ የነዚህን አካላት ግንኙነት፣ ትስስር እና መስተጋብርን የሚያጠና ሰፊና ውስብስብ ባሕርይ እንዳለው መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ ይህ ጥናት ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ አዕዋፍና ማዕድናት ከባህል ሕክምና እና ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸውን ትስስር እና አበርክቶ ፈትሿል፡፡ በቀጥይ ይዘት የባህል መድኃኒት/ሕክምና ምንነት ቀርቧል፡፡

### 2.1.3 የባህል መድኃኒት/ሕክምና ምንነት

የባህል መድኃኒት (Folk Medicine) ማለት ምን ማለት ነው? ሲባል፤ እንደየሙያ መስኩ የተለያየ ዕይታና ፅንሰ ሃሳባዊ ይዘት እንዳለው ምሁራን ገልፀዋል (Yoder, 1972; PP.193-196: Kannon, 2004; PP.31-32: Brady, 2001; P.14)፡፡ እንደ WHO (2002; P.7) መረጃ፤ ለባህል ሕክምና የሚሠጡ ብያኔዎችና ፅንሰ ሃሳቦች የዓለምን ማኅበረሰብ በወጥነት እንደማያግባቡ ይጠቁማል፡፡ እንደ ድርጅቱ ብያኔ፤ ባህላዊ መድኃኒት ማለት የተለያዩ የጤና ሕክምናዎችን፣ ዘዴዎችን፣ ዕውቀቶችንና እምነቶችን የሚያጠቃልል፡፡ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚዘጋጁ መድኃኒቶችን ከመጠቀም ባለፈ መንፈሳዊ እና የእጅ ሕክምና ስልቶችን (ብልሃቶችን) ይመለከታል፡፡ ጤናን ለመጠበቅ፣ በሽታን ለመከላከል፣ ሕመምተኛን ለመፈወስ ሲባል በተናጠልም ሆነ በቡድን የሚደረጉ ተግባራትን እንደሚያካትት ያስረዳል፡፡

Yoder (1972; PP.191-193) እና Steiner (1986; P.67) ደግሞ፤ የባህል መድኃኒት ሁሉን አቀፍ የሆነ የቃልም ሆነ የጽሑፍ ዕውቀትና ልምድን አካቶ በመያዝ አጠቃላይ ጤናን ለመጠበቅ፤ በሽታን ለመከላከል እና ሕመምን ለማስወገድ፣ ለመመርመር እና ለመፈወስ የሚተገበር ክህሎትን ይመለከታል፡፡ ይህም አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ጤንነትን በመገንባቱ ሂደት

ሁሉን አቀፍ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ የባህል መድኃኒት እንደ ከዋኙ ማኅበረሰብ ባህል፣ ሥነ ምህዳር፣ ልምድና ዕውቀት የተለያዩ ብያኔዎችና ስያሜዎችን የሚያካትት ሲሆን መተላለፊያ መንገዱ በቃል የሆነ፣ አካላዊ፣ አዕምሯዊና ማኅበራዊ የጤና ቀውሶችን በአገር በቀል ጥበብና ዕውቀት ለመከላከል፣ ለማከምና ለመፈወስ ሲባል የሚከወን አጠቃላይ ድምር ውጤት እንደሆነ፤ የጥናት ምንጮች ገልፀዋል (Yoder, 1972; P.192: Fekadu, 2001; PP.1-2)፡፡

Brady (2001; PP.14-15) ደግሞ፤ የባህል መድኃኒትን (Folk Medicine) ከማኅበረሰብ ማንነት እና ከአካባቢያዊ ሁነት ጋር በማዛመድ ይበይኑታል፡፡ የባህል መድኃኒት፤ አካባያዊ ዐውድን፣ ማኅበረሰባዊ መስተጋብርን፣ መልክዓ ምድራዊ ሁነትን መሰረት ያደረገ፤ መተላለፊያ መንገዱ በዋናነት ቃላዊ የሆነ፤ በግለሰቦች ተግባቦት እና በቀጥተኛ ግንኙነት የሚለመድ ዕውቀትና ክህሎት ሲሆን ምላሹም ቀጥተኛና ወዳው የሆነ፤ በጋራ እሴትና ልማድ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የሕክምና ልምድና ዕውቀቱም ከቦታ ቦታ የሚለያይ፤ ለውስን አካባቢና ማኅበረሰብ ፍላጎት አገልግሎት የሚውል፤ ከማኅበረሰቡ አባላት ወይም ቡድን ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው፤ የጋራ ማንነትና መገለጫዎችን፣ ባህላዊ ዳራና ቅርስን የሚጋራ (መሰረት ያደረገ) እንደሆነ መክረዋል፡፡ "Folk medical traditions tend to show regional variation and to accommodate specific local conditions, as well as to be closely tied to groups or populations who share important identity-defining features such as a particular ethnicity… a broadly shared cultural heritage." (Brady, 2001; P.15).

ከዚህ በላይ የቀረቡ ምንጮችን ዋቢ በማድረግ የጥናቱ መስሪያ ብያኔ (Operational definition) እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ጥናት ዐውድ የባህል መድኃኒት ማለት፤ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የማኅበረሰብ አባላት (ቡድኖች) ጤናቸውን ለመጠበቅና ከሕመም ለመፈወስ ሲሉ፤ ለበሽታ፣ ለአካባቢና ለዓለም ያላቸውን እሳቤ፣ የምርመራ ዘዴና ተግባርን በማስተባበር፤ አገር በቀል ዕውቀትን፣ እምነትን፣ እሴትን፣ የአኗኗር ስልትና ሥርዓትን መነሻ በማድረግ የሚከውኑት፤ ከአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር የሚገኙ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን፣ አዕዋፍን፣ ነፍሳትን እና ማዕድናትን በማሰባሰብ፣ በመለየትና በመቀመም የሚዘጋጅ መድኃኒትን እና የሕክምና ልማድን ይመለከታል፡፡ የሕክምና ልማዱም፤ በባህልና በትውፊት እሳቤ ላይ የተመሰረተ፤ የባህል መድኃኒት አጠቃቀምና አተገባበሩም በአካባቢው ማኅበረሰብ (ቡድን) ልማድና ስምምነት ላይ የተወሰነ፤ ዕውቀቱም ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል፣ በፅሁፍ ሆነ በተግባር እየተላለፈ የመጣ ክህሎት እና ጥበብን ታሳቢ ያደርጋል፡፡

ከዚህ ብያኔ በመነሳት የባህል ሕክምና ዕውቀት እና ሥነ ምህዳር ምን ዓይነት ዐውዳዊ መስተጋብር አላቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል፡፡

### 2.1.4 የባህል ሕክምና ዕውቀትና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር

የባህል ሕክምና ዕውቀት ከሥነ ምህዳር ሥርዓት ጋር ጥብቅ ትስስር፣ ዐውዳዊ መስተጋብር፣ ዘርፈ ብዙ አንጻር (Multi-dimension)፣ ግንኙነት እና ይዘት እንዳለው የጥናት ዋቢዎች ጠቁመዋል (Maclachlan, 2006: UNDEP, 2008; PP.91-98: Winkelman, 2009)፡፡ ሰው ከሥነ ምህዳር (ከአካባቢው) ጋር በሚያደርገው፣ ግንኙነትና ተራክቦ ይማራል፤ አካባቢውን በማሰስና በመፈተሽ የማወቅ፣ የመመርመርና "የመፈላሰፍ" ችሎታውን ያዳብራል፡፡ በሂደትም፤ በአካባቢው የሚገኙ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ መልክዓ ምድራዊ…፤ ሁነቶችን እንዴት መቅረብ፣ መራቅና መጠቀም እንዳለበት በምልከታና በተግባራዊ ልምምድ ዕውቀት ያገኛል (ጠና፣ 2009፣ ገ.9፤ Sutton and Anderson, 2010)፡፡

የባህል ሕክምና ዕውቀት[20] እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ሲባል የሁለቱ መስኮች ተራክቦ በመቼት (በቦታና በጊዜ)፣ በወቅት፣ በሁነት፣ በድርጊት በዐውድ-ተኮር ክዋኔ ይዘት ላይ የተመሰረተ መሆኑን (Brady, 2001: Maclachlan, 2006: Winkelman, 2009) ልብ ይሏል፡፡ በፎክሎር ጥናት ዐውድ (context)[21] ማለት አንድ ድርጊት (ክዋኔ) የሚቀርብበት ድባብ፣ አጋጣሚ፣ ወቅት፣ ሁነትን እና የሚከወንበትን ጊዜና ቦታ (መቼት) ያጠቃልላል (Ben-Amos, 1971; 1993: Bauman, 1983; 1986: Dundes, 1980; PP.21-32)፡፡ Sims and Stephens (2005; PP.137) ዐውድን "…context refers to anything and everything that surrounds a text and performance" በማለት በየትኛውም ቦታና አጋጣሚ በአሃድና በክዋኔ የታጀበ ድርጊት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

---

[20]በዚህ ጥናት ዐውድ፤ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብና የባህል ሐኪሞች በአካባቢያቸው (ሥነ ምህዳር) የሚገኙ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ አዕዋፍና መልክዓ ምድራዊ ግብዓቶችን በመለየት፣ በመጠቀምና በማራቅ ከሰው፣ ከባህል (ከጤና፣ ከሕመምና ፈውስ) እና ከአካባቢ አንፃር ያላቸውን ዐውዳዊ መስተጋብር ፈትሿል፡፡ ለዓብነት ያህል፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች አካባቢያዊና ልማዳዊ ዕውቀት፣ ክህሎትና ጥበባቸውን በመጠቀም፤ የአካባቢውን ዐውድ በማጤን፤ ዕፅዋትን መቼ መቅረብና መጠቀም እንዳለባቸው፤ እንዴት ቆርጠው፣ ለክተው፣ ቀምመውና መጥነው ለሕሙማን እንደሚሰጡ የሚተገብሩትን ዕውቀት ይመለከታል፡፡

[21]የዐውድ (የዐውድ-ተኮር ክዋኔ) ምንነት፣ ይዘትና ማብራሪያን ለመገንዘብ፤ ተጨባጭና ማኅበራዊ ዐውድ ትኩረትን (Dundes, 1980; PP.21-32: Sims and Stephens, 2005; PP.134-139) ለመለየት፤ ባህላዊና ማኅበራዊ ዐውድ ምድብ ይዘት ለማጤን (Bauman, 1983; PP.363-365)፤ የፎክ እና የሎር (ዕውቀት) መስተጋብርን ለመረዳት (Dundes,1980; PP.1-17) ዋቢዎችን ይመልከቱ፡፡

ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ደግሞ የመከወኛ አጋጣሚና ዐውድን ተከትለው የሚመጡ እና የሚከሰቱ ተግባራት፣ በድርጊት እና በጥበባዊ ተራክቦ (ክዋኔ) የሚገለጹ ይዘቶች፣ በሥርዓት እና በቅደም ተከተል ተሰድረው የሚቀርቡ ድርጊቶች፣ በማሕቀፍ ተለይተው፣ አካባቢያዊ ድባብን መሰረት አድርገው፣ "ሥጋ፣ ደም እና አጥንት ለብሰው፣ ነፍስ ዘርተው፣ ሕልው/ሕያው" ወይም ተጨባጭ ሆነው የሚቀርቡበትን ይዘት ይመለከታል፣ ዐውድ ሲቀየር ሥርዓትና ተግባሩ የራሱን ቅርፅ፣ ቀለምና ይዘት ይለውጣል/ ይቀየራል (Dundes, 1980; PP.24-32: Bauman, 1983; PP.363-365: Sims and Stephens, 2005; PP.134-136: ፈቃደ፣ 1991)። ይህ ጽንሰ ሃሳብ በዐውድ ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ንዑስ ይዘት (2.2.3) እና በመተንተኛ ሞዴል ክፍል (3.6.2) ተብራርቶ የቀረበ መሆኑን ታሳቢ ያደርጋል።

በዚህ ጥናት የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዐውድ ተኮር ክዋኔ ሲባል፣ የባህል (የዕፀ) መድኃኒት አሰባሰብ ሥርዓተ ገቢር ዐውዳዊ ክዋኔ፣ የቅመማ ሂደትና የመድኃኒት አሰጣጥ ሥርዓትን ይመለከታል። ዕፀ መድኃኒት መቼ፣ እንዴት፣ የት፣ በማን፣ በምን እንደሚቀረጡ እና እንደሚቀምሙ፣ በምን ተመጥነው እንደሚሰጡ፣ የቁጥር ቀመር፣ የቦታና አቅጣጫ ይዘት፣ የቁስና የቀናት ትዕምርት፣ በዐውድ ተኮር ክዋኔ ሥርዓትና ገቢር ምን ዓይነት ተግባር እና ይዘት እንዳላቸው በምዕራፍ ሰባት ትንታኔ ቀርቧል።

የባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ከሕመም መንስኤ እስከ ፈውስ (ሕክምና) ድረስ ያለውን ዐውዳዊ ክዋኔ (የድርጊቶች ትዕምርት፣ ፍቺና ትርጓሜ...)፣ ሂደትና ማሕቀፍን ያካትታል (Brady, 2001)። የሥነ ምህዳር ዐውድ (Ecological Context) ሲባል የመልክዓ ምድር ዓይነት (ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ቆላ...፣ ከፍታ/ዝቅታ)፣ የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የአዕዋፍ... መገኛ ቦታና ሥርጭት፣ የዐየር ንብረት መለዋወጥ (ሞቃት/ ቀዝቃዛ) እና የወቅት መፈራረቅ (ክረምት/ በጋ፣ ፀደይ/ መኸር)፣ ይዘትን (Kapchan,1995; PP.150-155: winkelman, 2009) ያጠቃልላል።

የሥነ ምህዳር ዐውድ መለዋወጥ ለበሽታ መንስኤ ወይም ፈውስ፣ ለሕክምና ዐውድ መለያየት፣ ለበሽታ ሥርጭት፣ ለዕፀ መድኃኒት ግብዓት ልዩነት ምክንያት ይሆናል። የባህል ሕክምና ባለሙያዎች የሥነ ምህዳር ሥርዓት፣ ሁነት እና ዐውድን በማንበብ (Ecological Pattern Reader's) ለሕመም መንስኤ የሚባሉ እሳቤዎችን በመለየት፣ የጤና ሚዛንን ለመጠበቅና ለመመለስ ይበጃል የሚሉትን ዕውቀትና ተግባር በመፈፀም የሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ መረጃዎች (Maclachlan, 2006: Payyappallimana, 2009; PP.74-78: Sutton and Anderson, 2010) አመላክተዋል።

Maclachlan ደግሞ የ"ሜዲካል ኢኮሎጂ" ይዘት እና አንጻርን በማጤን፤ የሁለቱ መስተጋብር ዐቢይ ትኩረት የሥነ ሕይወታዊ መሰረት እና የባህል ዐውድን ይመለከታል። በይዘቱም የሥነ ምህዳር ሥርዓት፣ የሰው ልጅ አዝግሞተ ለውጥ፣ ጤና እና ሕመም፤ ከአካባቢ ተላምዷዊ (Environmental Adaptation) ሁነት አንጻር ያላቸውን ዝምድና እና መስተጋብር በትኩረት ይመረምራል። ቀጥተኛ ይዘቱ (ምንጩ) እንደሚከተለው ቀርቧል (Maclachlan, 2006; P.3)፡-

> The medical ecology perspective is concerned more explicitly with the interaction of biological conditions and cultural contexts. It thus considers the inter relationships of ecological systems, human evolution, health and illness, where health may be seen as a measure of environmental adaptation.

የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር መስተጋብር፤ አዎንታዊ ትስስር ካላቸው ለሥነ ምህዳር ሥርዓት እና ለተፈጥሮ ሚዛን፤ ለጤናማ ሥነ ሕይወታዊ ሥርዓት መካሄድ፤ ለዐየር ንብረት እና ለመልክዓ ምድር ይዘት መጠበቅ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ይታመናል። የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የአዕዋፍ እና የነፍሳት ትስስር፤... የምግብ ሰንሰለት ሥርዓት (Food Chain System)፣ የሥነ ምህዳር ሁነት፣ የማኅበረሰብ እምነት እና ዕውቀት ከሥነ ምህዳር ጋር ያለው መስተጋብር በአዎንታዊ መልኩ ከተገናኘ የአካባቢ ሚዛን ይጠበቃል። በአንጻሩ፤ የሥነ ምህዳር ሥርዓት ሚዛን ሲዛባ የዐየር ንብረት መለወጥ፣ የዉኃ ብክለት፣ የበሽታ ወረርሽኝ መከሰት፣ የዕፅዋትና የእንስሳት መጥፋት፣ የሥነ ሕይወታዊ ሥርዓት መረበሽ፣ የመልክዓ ምድር "መራቆት" እና የዐፈር መሸርሸር፤... ይከሰታል (Chokevivat, 2005; PP.6-11: UNEP, 2008; PP.94-96: Payyappallimana, 2009; P.74: Sutton and Anderson, 2010)።

የሰው ልጅ ከአካባቢው ጋር ባለው መስተጋበር የጤና ሚዛኑ ተፅዕኖ ሊደርስበት ይችላል። የ"ሜዲካል ኢኮሎጂ" (Medical Ecology) ትኩረት የሰው ልጆችን ጤና ከአካላዊ ይዘት፣ ከሥነ ሕይወታዊ መስተጋብር፣ ከማኅበረ-አካባቢያዊ ሁነት ጋር ያላቸውን ዝምድና እና ግንኙነት ይመረምራል። በሂደትም፤ የዐየሩን ሁኔታ፣ የዕፅዋት እና የእንስሳት መኖሪያ አካባቢን፣ የሕዝብ ብዛትና ተለዋዋጭ ዐውድን ይመለከታል። ሥነ ምህዳራዊ ሥርዓት ሶስት ዐበይት ፅንሰ ሃሳባዊ አንጻሮችን ያካትታል። እነርሱም አካላዊ፣ ሥነ ሕይወታዊና ባህላዊ ሁነት ሲሆኑ የሶስቱን መስተጋብራዊ ዐውድ በማጤን፤ የሕዝቡን ብዛት፣ መልክዓ ምድራዊ ሁነት፣ የዐየር ንብረት ስብጥር፤ ለበሽታ ስርጭት፣ መንስኤ፣ መገኛ ቦታና አካባቢያዊ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ ምሁራን ገልፀዋል (Brady, 2001: Bodeker and Burford, 2007; PP.11-14: Winkelman, 2009;

PP.250-252)። ጤና፤ ከሥነ ምህዳር ጋር በአለው መስተጋብር የተለያዩ ተፅእኖዎች እንደሚደርሱበት Winkelman (2009; P.250) እንደሚከተለው አስረድተዋል፡-

> Health is affected by many interactions with the environment. Medical ecology examines the relationships of health to physical, biological, and social environments, such as climatic conditions, plants and animals, and population dynamics. ...Ecological systems are conceptualized as having three major aspects—abiotic (physical), biotic (biological), and cultural—that interact with each other and the human population in the determination of disease.

የባህል ሕክምና ዕውቀት በሥነ ምህዳር ዓይነት፣ ግብዓት፣ ይዘት እና መስተጋብር ይወሰናል (Helman,1984: Maclachlan, 2006)። የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ለመድኃኒት የሚያገለግሏቸውን ግብዓቶች ከተለያዩ የሥነ ምህዳር ቦታዎች በመሰብሰብ ለሕክምና አገልግሎት የሚጠቀሙ ሲሆን የሥነ ምህዳር ሥርዓት ሚዛን ሲዛባ ለሕክምና የሚያገለግሉ ግብዓቶች (ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ አዕዋፍ፣ ነፍሳት፣ ማዕድናት እና በዉኃ ውስጥ የሚገኙ..) በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ምክንያት እንደሚጠፉ፤ ምሁራን ጠቁመዋል (Sutton and Anderson, 2010: Benally, 2010)። በሂደትም የባህል ሕክምና ዕውቀት እየተዳከመ፤ ተግባር እና ጥበቡ እየጠፋ ይሄዳል። ማንኛውም ማኅበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ ባህላዊ እሳቤውን ከሥነ ምህዳር ዕውቀቱ ጋር በማስተሳሰር፤ እምነታዊ፣ አምልኳዊ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓት እና አተገባበርን በመፈጸም የአካባቢውን መልክዓ ምድር፣ እንስሳት፣ ዕፅዋት፤ ባሕርይ በማጤን እንዴት መቅረብ እና መራቅ እንዳለበት፤ ይወስናል።

ማኅበረሰቡ፤ ለዓለም እና ለተፈጥሮ ሥርዓት ያለው እሳቤ፤ የሥነ ሕዋ እና የሥነ ከዋክብት ቆጠራ እና እምነት፤ የአደን፣ የግብርና፣ የባህል ሕክምና ዕውቀት፤ የዕፅዋት እና የእንስሳት መራቢያ ወቅትን... መመዝገብና መሰነድ አስፈላጊ እንደሆነ፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት ለሚኖሩበት ሥነ ምህዳር ምን እሳቤ አላቸው? እንዴት ይመድቡታል/ ይለዩታል? እንዴት ይጠቀሙታል? የአካባቢያቸውን ሥነ ምህዳር መመርመሪያ እና መገንዘቢያ የነገድ ወይም የጎሳ ሣይንስ "Ethnoscience" አተገባበርን መረዳት፣ ማጥናትና መመርመር፤ የዘመኑ እሳቤና አዲስ የምርምር መስክ (የባህል እና የሥነ ምህዳር መስተጋብርን) መሆኑን፤ ምሁራን ጠቁመዋል (Maclachlan, 2006: Sutton and Anderson, 2010; P.96,105)። የሥነ ምህዳር ሥርዓት ሚዛን ለመጠበቅ እና አካባቢያዊ ዐውድን ለመገንዘብ፤ ለዓለምና ለተፈጥሮ ያለ አተያይ...፤ እምነታዊ፣

ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ተግባራት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው Sutton and Anderson (2010; PP.104-105) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡-

> World view, cosmology, astronomic beliefs, hunting theories, agricultural lore, and other ecological knowledge were recorded in wonderful detail. Most cultures code much of their ecological knowledge as part of religion (… a source of considerable information regarding plants and animals of its time). A new component of cultural ecology had been invented: the study of what local people know about their environment, how they classify that information, and how they use it, an approach called ethno science and later ethnoecology.

በአጠቃላይ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር (በወቅት፣ በዕለት፣ በዘመን፣ በወር፣ በመልክዓ ምድርና በዐየር ንብረት ለውጥ) ጥብቅ ትስስር እና ግንኙነት እንዳላቸው፤ የወቅት መቀያየር የበሽታ ዓይነትን እና የሕክምና ዐውድን እንደሚለውጥ ምሁራን (Winkelman, 2009: Sutton and Anderson, 2010) ገልጸዋል። የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ለሕክምና የሚያገለግሏቸውን ግብዓቶች ከተለያየ መልክዓ ምድር በመሰብሰብ የሚጠቀሙ ሲሆን የሥነ ምህዳር ሥርዓት እና ሚዛን መዛባት በባህል ሕክምና፣ በማኅበረሰብ ጤና እና መስተጋብር ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር መገንዘብ ተችሏል (ትንታኔ ይዘት፤ ምዕራፍ ስምንትን ይመልከቱ)። ማኅበረሰቡ ከአካባቢው ሥነ ምህዳር ሥርዓት ጋር ለመግባባት፣ ለመላመድና ለመስማማት የነገድ ሣይንስ እሳቤን (እምነታዊ፣ አምላኪዊ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓትና ተግባራትን) በመተግበር ተግባብቶ እና ተስማምቶ እንደሚኖር ከዚህ በላይ የቀረቡ ዋቢዎች ጠቁመዋል። ይህ ጥናት፤ ጥቅል የባህል ሕክምና ዕውቀት (Holistic Traditional medicine Knowledge) ይዘትን መነሻ አድርጓል። ጥቅል የባህል ሕክምና ይዘት ሲባል የአካባቢውን ማኅበረሰብ፣ ሥነ ምህዳር፣ ባህል፣ በሽታ እና የሕክምና ዕውቀትን ይመለከታል። ለዝርዝር መረጃ የሚከተለውን ይዘትና ማሕቀፍ ይመልከቱ፡-

**ምስል 1፡- ጥቅል የባህል ሕክምና ዕውቀት ይዘት**




**ምንጭ፡-** Helman, 1984፡ Maclachlan, 2006; P.11፡ Winkelman, 2009

ከዚህ በላይ የቀረበው ምስል እንደሚያስረዳው፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት ጥቅል ይዘትን መነሻ በማድረግ የአካባቢው ማኅበረሰብ ባህል (እምነት)፣ አካባቢ (ማኅበረሰብ፣ ሥነ ምህዳር)፣ በሽታ እና የፈውስ መስተጋብራዊ ሁነቶችን ማዕቀፉ ይገልፃል፡፡ ይህ ጥናት በማዕቀፉ ከተጠቀሱ ይዘቶች መካከል ባህልን ማዕከልና አንፃር በማድረግ ማኅበረሰቡ ከሥነ ምህዳር (አካባቢን)፣ ከበሽታና ከፈውስ ሥርዓት ጋር ያለውን መስተጋብራዊ ይዘት ፈትሿል፡፡ በቀጣይ ይዘት የባህል ሐኪሞች ማንነት፣ ምድብና ማሕቀፍ ይዘት፤ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

## 2.1.5 የባህል ሐኪሞች ማንነት፣ የባህል ሕክምና ማሕቀፍ እና የባህል ሐኪሞች ምድብ

የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን[22] ማንነት፣ ተግባር እና ሚናን በተመለከተ በመስኩ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን፤ ተቀራራቢ ገለፃና ብያኔዎችን ሰጥተዋል (Yoder, 1972: Hurreize, 2006: Sindiga, 1995: Wondwosen, 2006: Winkelman, 2009)፡፡ Sindiga (1995; P.19) እና Brady (2001; P.26)፤ የባህል ሕክምና ባለሙያ ማለት የዕፅዋት፣ የእንስሳት እና የማዕድናት ንጥረ ነገሮችን በመጠቀም፤

---

[22]ከዚህ በፊት የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት (ዓለማየሁ 2000፤ መስፍን 2002፤ ተመስገን 2003፤ Mekonen 1988: Young 1970: Wondwosen. 2006) ከሆነ የባህል ሐኪሞች በሚኖሩበት ማኅበረሰብ የተለያዩ ስያሜዎች ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ይዘት ማኅበረሰቡ ለባህል ሐኪሞች የሚሰጠውን ከበሬታ፣ ተቀባይነትና መጠሪያ መሰረት በማድረግ የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን፤ የባህል ሐኪም፣ የባህል ሕክምና ባለሙያ፣ ባለመድኃኒተኛ፣ የዕፀ መድኃኒት አዋቂ የሚሉ ስያሜዎችን እንደአመቺነታቸው በማፈራረቅ ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡

በማኅበራዊ፣ በባህላዊና በሃይማኖታዊ መስተጋብር እና በማኅበረሰቡ ውስጥ በሰፊው ተለምዶ ባለው ዕውቀት፣ ዝንባሌና እምነት ላይ በመመስረት የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያን ይመለከታል። ይህ ሰው በሚኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ የጤና እንክብካቤን ወይም ሕክምና ለመስጠት "ብቃት አለው" ተብሎ ተቀባይነት ያገኘውን ይመለከታል። በሽታዎችን እና የአካል ጉዳቶችን ለመከላከል እና መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት አካላዊ፣ አዕምሯዊ እና ማኅበራዊ ጤናን በማስገኘት ወይም በማስጠበቅ ረገድ በማኅበረሰቡ ዕውቅና ያገኘ፤ መሆን እንዳለበት አስረድተዋል።

ከዚህ ሃሳብ ጋር በተቀራረበ መልኩ Kannon (2004;P.32)፤ የባህል ሕክምና ባለሙያ ሲባል በሚኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የማዕድናት ንጥረ ነገሮችን እንዲሁም ሌሎች በማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ልምዶች ላይ የተመሰረቱ ዘዴዎችን በመጠቀም፤ "ሕመምን የመፈወስ ብቃት አለው" ተብሎ ተቀባይነትን ያገኘ ሰው "የባህል ሐኪም" እንደሚባል ገልፀዋል። የባህል ሐኪም መረጌታ ፍሬስብሃት ደግሞ፤ "ዱሮ፤ ሥር ማሽ፣ ቁጢት በጣሽ፤ ዐባይ፣ ጠንቋይ፤..." እየተባለ በማኅበረሰቡና በመንግስት አሉታዊ ስም ይሰጣቸው እንደነበር ጠቁመው፤ "አሁን... የሙያ ፈቃድ አውጥቶ፣ የሥራ ግብር ከፍሎ፤ የዕፅዋት፣ የእንስሳትና የማዕድናት መድኃኒቶችን አዘጋጅቶና ቀምሞ የሚሰጥ ሰው፤ የባህል ሐኪም" እንደሚባል አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም)[23]።

በአጠቃላይ የባህል ሕክምና ባለሙያ የበሽታ መንስኤዎችን ለመለየት፤ አካባቢያዊ ዕውቀትን፣ የሥነ ምህዳር ዐውድን፣ ልማድን፣ እምነትና ሃይማኖትን፣ ማኅበራዊ ሁኔታን መሰረት በማድረግ የሚተገበሩትን ሕክምና ይመለከታል። የባህል ሐኪም ሲባል ከሥነ ምህዳር የሚገኙ ግብዓቶችን (ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናት፣ ከአዕዋፍ፣ ከነፍሳት እና ከዉኃማ አካላት የሚገኙ የመድኃኒት ግብዓትን) በመጠቀም እና በመቀመም ለሕሙማን የሚሰጡ፤ የማኅበረሰብ ጤናን በማስጠበቅ ረገድ ጉልህ ሚና ያላቸው፤ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዕውቅና ያገኙ ባለሙያዎች "የባህል ሐኪም" እንደሚባሉ፤ ከዚህ በላይ የቀረቡ ምንጮች ጠቁመዋል። ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ የባህል ሐኪሞች ምድብና ማሕቀፍ በስንት ይከፈላል? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል።

[23]በዚህ ጥናት ቃለመጠይቅ (ቃ.መ)፤ ተተኳሪ ቡድን ውይይት (ተቡው/ከተቡው/የተቡው) በሚሉ ፊደላት የተወከሉ መሆኑን ልብ ይሏል።

ምሁራን፤ የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ዓይነት በሁለት ዐበይት የሕክምና ዘርፍ ስር ይመደባሉ፤ (Mekonen,1988; P.82: Young, 1970; PP.27-29: Wondwosen, 2006; PP.32-34):: እነርሱም ተፈጥሯዊ[24] (Secular) እና መለኮታዊ (spiritual) በማለት ይከፈላሉ:: የአመዳደብ ሥርዓታቸው ጊዜያዊ የሕክምና ዕውቀታቸውን፣ ዘዴያቸውን፣ ቴክኒካዊና መንፈሳዊ ክህሎታቸውን መሰረት ያደርጋሉ:: በተፈጥሯዊ (Secular) ይዘት ስር የዕፀ መድኃኒት አዋቂ፣ አዋላጅ፣ ወጌሻና ዕንጥል ቆራጮችን ይጠቅሳሉ:: በመለኮታዊ (spiritual) ይዘት ደግሞ "አስማት፣ ጠንቋይ፣ አጥማቂና ሼክ" ይካተታሉ:: ከዚህ በታች የባህል ሕክምና ማሕቀፍ እና የባህል ሐኪሞች ምድብ[25] እንደሚከተለው ቀርቧል:-

ምስል 2:- የባህል ሕክምና ፅንሰ ሃሳባዊ ማሕቀፍ




**ምንጭ:-**(Young,1970; PP.34-36: Sofowora,1982; PP.29-30: Mekonen,1988; PP. 81-82: Wondwosen, 2006; PP. 32: Konadu, 2007; P.67)

---

[24]በዚህ ይዘት ተፈጥሯዊ፣ ምክንያታዊ፣ ተጨባጭና ዓለማዊ የሚሉ ቃላት "Secular" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በመተካት የሚያገለግሉ ሲሆን፤ በመለኮታዊ፣ ኢ-ምክንያታዊ፣ አስማታዊና መንፈሳዊ ደግሞ "spiritual" የሚለውን ቃል ይገልጻሉ፤ ይተካሉ::

[25]የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች በሁለት ምድብ ከፍሎ ማጥናት ከኢትዮጵያ ዐውድ አንጻር ሲታይ በጣም ውስብስብና አስቸጋሪ ነው:: ለዚህም ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ የባህል ሐኪሞች በአንድ በኩል መንፈሳዊ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ዓለማዊ የሕክምና ተግባራትን ሲፈጽሙ ይታያል:: ከዚህ አንጻር በዓለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕክምና ምድብ ውስጥ ለማካተት ባለሙያዎቹ የፈለቁበትን ተቋም፣ የሚተገብሩትን የሕክምና ዓይነትና ጊዜያዊ ሁኔታ በማጤን አንፃራዊ በሆነ መልኩ መፈረጅ እንደሚገባ ይገልጻሉ (Mekonen,1988; PP.81-82: Wondwosen, 2006; PP. 30-32)::

ይህ ጥናት በተፈጥሯዊ የባህል መድኃኒት ምድብ ስር የሚጠቀሱ፤ "የዕፀ መድኃኒት አዋቂ" ባለሙያዎች ላይ ትኩረት በማድረግ፤ ለበሽታ መንስኤ ያላቸውን እምነትና ግንዛቤ፣ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ፤ ከሥነ ምህዳር ዐውድ ጋር ያላቸውን መስተጋብር መርምሯል።

ከዚህ አንጻር Young (1970; P.24) እና Konadu (2007; P.67)፤ "የዕፀ መድኃኒት አዋቂ" ሲባል በዋናነት ከሥነ ምህዳር የሚገኙ የዕፅዋት፣ የእንስሳት እና የማዕድናት ግብዓቶችን አጠቃሎ የሚጠቀም ባለሙያን ይመለከታል። የባህል ሕክምና በአብዛኛው ከዕፅዋት የሚገኙ ግብዓቶችን መሰረት ያደረገ፤ የሕክምና ዓይነቶች የሚሰጡ ሲሆን፤ በዚህ ስር የሚመደቡ የባህል ሐኪሞች "የዕፀ መድኃኒት አዋቂ" በመባል ጥቅል መጠሪያ እንዳላቸው፤ ከሚሰጡት አገልግሎትና ሙያ አንጻር ከፍተኛውን ቁጥር እንደሚይዙ ጠቁመዋል።

Wondwosen (1999; PP.29-30: 2006; P.79) ደግሞ "የዕፀ መድኃኒት ባለሙያዎች" በኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ሥርዓት ላይ ጉልህ ሚና እንዳላቸው ጠቁመው፤ እነዚህ የባህል ሕክምና አዋቂዎች ከዕፅዋት ሥር፣ ቅጠል፣ ግንድ፣ ፍሬ፣ አበባ፣ ዘር፣ ቅርፊት፣ ቁጥቋጦ፣ ፈሳሽ፣ ተቀጽላ፣ አትክልትና ፍራፍሬ… ዕፀ መድኃኒት በማዘጋጀትና ሁሉንም የዕፅዋት አካል ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው አስረድተዋል።

Read (1966; P.19) እና ፈቃዱ (2002፣ ገፅ. 51-53)፤ "የዕፀ መድኃኒት ባለሙያዎች" ሲባል፤ በመድኃኒት ግብዓት አሰባሰብና አጠቃቀም ሂደት ጥቅል እሳቤና ተግባር (የዕፅዋት፣ የእንስሳትና የማዕድናት ግብዓትን አዋህዶ በመጠቀም ሕክምና እንደሚሰጡ) እንዳላቸው ጠቁመው፤ በአብዛኛው ከዕፅዋት የሚገኝ ግብዓት መጠቀማቸው፤ ለምድብና መጠሪያቸው ምክንያት እንደሆነ፤ አመዳደቡም ከሚጠቀሙት ግብዓት አንፃር ሲታይ አግባብነት እንዳለው ገልፀዋል።

እነዚህ ባለሙያዎች ከዕፅዋት በተጨማሪ እንስሳትን፣ ማዕድናትን፣ አዕዋፍን እና በዉኃ አካል ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ግብዓቶችን ቀምመው መድኃኒት አዘጋጅተው እንደሚሰጡ Sofowora (1982; PP.27-30) እና Alemayehu (1984;PP.124-125) ይገልፃሉ። የሚቀምሙትና የሚሰጡት መድኃኒት የሥነ ምህዳሩን ዓይነት (Ecological type's) እና ዐውዳዊ ይዘት (ወቅትና ቦታ) በመለየት፤ በአካባቢያቸው የሚበቅሉ የዕፅዋት ዓይነቶችን፣ የማዕድንና እንስሳትና መገኛ ቦታዎችን፣ የአካባቢያቸውን የዐየር ንብረት፣ የበሽታ ዓይነቶችና የሕክምና አሰጣጥ

መመሪያዎችን፣ በሽታ የመለያ ዘዴዎችን፣ የመድኃኒት አሰባሰብ፣ አዘገጃጀት፣ ቅመማና አሰጣጥ ስልቶችን በማቀነባበር ጉልህ ሚና እንዳላቸው ይገልፃሉ (Chavuduka,1994; P.56)፡፡

በዚህ ጥናት "የዕፀ መድኃኒት አዋቂ" (Harbalist) ሲባል፤ ጥቅል አተያይና አተገባበርን መሰረት በማድረግ የሚሰጠውን ሕክምና እና የሚዘጋጀውን የመድኃኒት ግብዓት ይመለከታል፡፡ የዕፀ መድኃኒት ባለሙያዎች ሲባል፤ ከሥነ ምኅዳር የሚገኙ የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የማዕድን፣ የነፍሳት እና የዉኃማ አካላት ግብዓቶችን ሰብስበው፤ በዓይነት፣ በይዘትና በመጠን ለይተው፤ የፈውስ ኃይላቸውን አጥንተው፤ በተናጠል ወይም በመቀላቀል የሚያዘጋጇቸውን የመድኃኒት ግብዓቶች ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ፡- ዕፀ መድኃኒት ተቆርጦ መቀመሚያው ዉኃ ነው፤ ዕፅዋትና ማዕድን ተገናኙ ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዕፅዋት ተቀምመም ለታካሚ ሲሰጡ፤ ለመቀላቀል፣ ለመበረዝ፣ ለማለስለስ፣ ለማጠንከር፤ ለማዋሃድ እና መሰል ተግባራትን ለመፈፀም የማዕድን፣ የእንስሳት እና የነፍሳት ግብዓቶች አገልግሎት ይሰጣሉ (ምዕራፍ ሰባት እና አባሪ ስድስትን ልብ ይሏል)፡፡

በዚህ እሳቤ፤ የዕፀ መድኃኒት አዋቂዎች ተግባር በአብዛኛው ዕፅዋትን፤ በተጓዳኝ ማዕድንና እንስሳትን በመጠቀም፣ በመቀላቀልና በማዋሃድ፤ የመድኃኒት ግብዓት ያዘጋጃሉ፤ የሕክምና አገልግሎት ይሰጣሉ፤ የመድኃኒት ግብዓቶች መረጣ፣ ዝግጅት፣ ቅመማና ትግበራ በንጥል ሙያ፣ ዕውቀትና ክህሎት የሚከወን (ዕፅዋትን ብቻ መሰረት ያደረገ፤ ከእንስሳትና ማዕድናት ግብዓት የተፋታ) አለመሆኑን ያስረዳሉ (መሪጌታ ባሕረጥበብ፣ ሊቀጠበብት አብርሃም እና መሪጌታ ስዩም ቃ.መ፤ 22/01/2011 ፋርጣ፣ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 04/02/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡ "የዕፀ መድኃኒት አዋቂዎ" የሕክምና ሙያቸው በጥቅል ተግባርና እሳቤ ላይ መመስረቱ፤ ከዕፅዋት በተጨማሪ የማዕድን እና የእንስሳት ግብዓቶችን በተናጠል፣ በመቀላቀል፣ በማዋሃድና በመደመር መጠቀሙ፤ ጎልቶ በሚታየው ሙያ፣ ተግባርና ስማቸው መጥራትና መመደቡ ተገቢ ይመስላል፡፡ ጥናቱም ይህን አተያይና ማሕቀፍ በመከተል፤ "የዕፀ መድኃኒት አዋቂዎችን" ምድብ መነሻ በማድረግ ዕውቀትና ተግባራቸውን ፈትሿል፡፡ ከዚህ ይዘት በመቀጠል፤ በባህል ሕክምና ልማድ የሕመም መንስኤ እሳቤ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2.1.6 በባህል ሕክምና የሕመም መንስኤ እሳቤ

በባህል ሕክምና ዕውቀት "የሕመም መንስኤ"[26] የ"ፎክ ቡድኑን" እሳቤ (የባህል ሐኪምና ማኅበረሰቡ፣ ተመክሮ፣ ልምድ፣ እምነት፣ ሃይማኖት እና ተግባር…) መሰረት ያደርጋል (Helman, 1984; P.72: Hufford,1986)፡፡ በባህል ሕክምና የሕመም መንስኤ "የፎክ ቡድኑ" እምነት፣ አካባቢያዊ፣ አካላዊ፣ አዕምሯዊና ሥነ ልቡናዊ ሁነትን መነሻ በማድረግ፤ የግለሰቡ ባሕርይ፣ ጥንቃቄ፣ ድርጊት፣ ተፈጥሯዊ አካባቢ፤ ማኅበረሰባዊ ተግባቦት፣ ግንኙነትና መስተጋብር፤ መለኮታዊ ኃይል…፤ ለሕመም መንስኤ/ ፈውስ ምክንያት እንደሆኑ ይገልጻሉ (Murdock,1980: Helman, 1984: Brady, 2001; P.25)፡፡

ከተፈጥሯዊ አካባቢ ወይም ሥነ ምህዳር የሚነሱ በሽታዎች፤ ከመለኮታዊ ኃይል ጋር በማገናኘት፤ "የፈጣሪ ቁጣ፣ ትዕዛዝ እና ፍርጃ" ተብሎ እንደሚታሰብ ይጠቁማሉ፡፡ ሁለት ሰዎች ሳይግባቡ ቀርተው ቢጣሉ፤ በሂደት አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳት ቢያጋጥማቸው፤ ፎክ ቡድኑ "የአጋንንትና የሰይጣን" ተግባርና ትእዛዝ፤ መሆኑን እንደሚያምኑ ያስረዳሉ (Helman, 1984; PP.72-74)፡፡

Murdock ዋና ዋና የሚባሉ የሕመም መንስኤ ጽንሰ ሃሳቦችን[27]፤ ተፈጥሯዊ እና መለኮታዊ ኃይል በማለት በሁለት መድበዋል፡፡ በተፈጥሯዊ ኃይል የሚከሰቱ የበሽታ መንስኤዎች ከሚባሉት መካከል በድንገተኛ አደጋዎች፣ በወረርሽኝ፣ በተበከለ ምግብና ውኃ፣ በነፍሳት መነደፍና በመሳሰሉት የሚመጡ በሽታዎች በዚህ ምድብ ስር ተካተዋል፡፡ በመለኮታዊ ኃይል የሚከሰቱ የሕመም መንስኤዎች፣ ከፈጣሪ፣ ከቀድመ አያቶች መንፈስ፣ ከአጋንንት፣ ከሰይጣን፣ ከመተት፣

[26]የሰው ልጆች እንደየባህላቸው፣ ሙያና ልምድ፣ ሥርዓትና ተግባር ለሕመም መንስኤ የተለያየ አመለካከት አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሕጻን ተቅማጥ ቢታመም፤ መነሻው ምን ይሆን? ለሚለው ጥያቄ፤ በማኅበረሰቡ ቡዳ በልቶት፣ አጋንንት ወግቶት፣ የአምላክ ቁጣ፣ የአድባር መቅሰፍት ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በዘመናዊ ሐኪም ደግሞ "ኢንፌክሽን" እንደሆነ ያስረዳል፡ የጤና መኮንን፤ በአካባቢ ብክለት፣ በመፀዳጃ ቤት ጉድለት እና በንፁህ ውኃ እጥረት የተከሰተ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በማኅበራዊ ኑሮ፤ በሥነ ምግብና ክብካቤ ባለሙያ ደግሞ፤ በተመጣጠነ በምግብ እጥረት፣ በተበከለ ምግብና መጠጥ፣ የገቢ መጠን እና መተዳደሪያ ዝቅተኛ መሆን፣ የኃብት ክፍፍል ፍትሃዊ አለመሆን፤ የኑሮ ደረጃ መለያየት፤ መሰረተ ልማት፣ ትምህርት፣ ጤና አለመስፋፋት፤ የማኅበረሰብ ትምህርትና ግንዛቤ አለመኖር ለሕመሙ መንስኤ እንደሆኑ ይመክራሉ (Helman, 1984: Brady, 2001: Ember and Ember, 2004: MacLachan, 2006: Winkelman, 2009)፡፡

[27]Murdock (1980; P.6)፤ የበሽታ መንስኤ ጽንሰ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ የተሰጠው ምድብ አንጻራዊ በሆነ መልኩ እንጂ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደማይሆን ይገልፃሉ፡፡ አንዳንድ በሽታዎችን በተፈጥሮም ሆነ በመለኮታዊ ኃይል ስር ለመመደብ ስንነሳ ችግር እንደሚገጥመን ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የተፈጥሮ መዛባት የመሳሰሉትን በተፈጥሮም ሆነ በመለኮታዊ ኃይል ስር ለመመደብ እና የመንስኤ ምንጩን ለመለየት እንደማይቻል ያስረዳሉ፡፡

ከእርግማን፣ ከጅን፣ ከዛር፣ ከቡዳና ከመሳሰሉት እንደሚመደቡ ገልፀዋል። ማኅበረሰቡ ስለሕመም መንስኤ፣ መከላከያ እና መፈወሻ ያላቸው አመለካከትና ግንዛቤ፤ ለጉዳዩ የሚሰጡት ምክንያት በባህል ሕክምና ሥርዓት እና አተገባበር ጥናት ውስጥ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን፤ መክረዋል (1980; PP.8-9)።

Helman ደግሞ፤ "የፎክ ቡድን" የሕመም መንስኤ እሳቤዎች፤ ሕመሙ ከሚያሳየው ምልክት፣ ባሕርይ፣ ፀባይ፣ ተግባርና ለውጥ በተለየ የራሳቸው የሆነ የሕመም መነሻ ምንጭ (Aetiology)፣ እምነት፣ የምርመራ ዘዴ፣ የፈውስ መንገድና የመከላከያ ስልት እንዳላቸው ገልፀዋል። ከዚህም በተጨማሪ፤ በውል ተለይተውና ተመድበው ከሚታወቁ የሕመም ስሜቶች እና አካላዊ ምልክቶች ባለፈ ትዕምርታዊ ውክልና ያላቸው "ሞራላዊ"፣ ማኅበራዊ ወይም ሥነ ልቡናዊ ሁነቶችን/ተፅእኖ እንደሚያስተናግዱ፤ "Folk illnesses are more than specific clusterings of symptoms and physical signs. They also have a range of symbolic meanings—moral, social or psychological—for those who suffer from them." (1984; P.73) ጠቁመዋል።

እንደ Winkelman (2009; PP.60-61) እና Murdock (1980; P.6) ገለፃ የሕመም መንስኤ ሲታሰብ፤ የመጀመሪያ ጉዳይ የባህል ሐኪሙና ማኅበረሰቡ ስለሕመም መንስኤ ምን እሳቤ አላቸው? ጤናቸውን እንዴት ይጠብቃሉ? ከአካባቢያቸው ሥነ ምህዳር ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት አላቸው? ለሕመም መነሻ እና ለፈውስ ያላቸው እምነት ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች በባህል ሕክምና ዘርፎች አንድም በተናጠል፤ አለያም በንጽጽር የሚጠኑ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

እንደ Hufford (1986; P.307) መረጃ፤ በባህላዊ ሕክምና ዘርፍ ከሚጠኑ ዐበይት ጉዳዮች መካከል የባህል ሐኪሙና ታካሚው ቀዳሚውን ቦታ ይወስዳሉ። በተለይ በጤና ሥርዓት ዘዴ ጥናት (A Health Systems Approach) ከባህል ሐኪሙና ታካሚው በተጨማሪ ማኅበረሰቡና መገልገያ ቁሳቁሶቹ፣ የመኖሪያ አካባቢዎች፣ የሥነ ምህዳር ዓይነቶች፣ ወቅትና ጊዜ፣… ለበሽታ ያላቸው ተጋላጭነት ከግምት ውስጥ በማስገባት እያንዳንዳቸው ያላቸውን ፋይዳ (ተግባራዊ ቅንጣት) ማጥናት እንደሚገባ ይመክራሉ። በዚህ ይዘት ስር ከሚጠኑ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል በባህላዊ ሕክምና የሕመም መንስኤ፣ በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልቶች፣ በሽታን ለመፈወስ የሚደረጉ ሃይማኖታዊና አምልኳዊ ሥርዓቶች፣ ተግባራዊና ንድፈ ሀሳባዊ ክህሎቶች፣ የማኅበረሰቡ እምነት ለጤና ሥርዓት መጠበቅ ወይም መዛባት ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው፤ ያስረዳሉ ።

Mishra, and et al (2013; PP.65-66)፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት ለሕመም መንስኤ የተለያዩ ወኪሎች (ርኩሳን መናፍስት)፣ የግለሰብ ባሕርይ (ግለሰባዊ ፍላጎትና ተግባር)፣ የልዕለ ተፈጥሮ ኃይል (Supernatural Power) የአያትና ቅድመ አያት መንፈስና ቆሌ፤ በእድሜ መግፋት ምክንያት የሚከሰት አካላዊ እርጅና፣ የአመጋገብ ልማድ መዛነፍ፣ የወቅት መፈራረቅ፣ የሥራ ባሕርይ፣ የሥራ ጫና እና ውጥረት፣ አካባቢያዊ ሁኔታና የዐየር ብክለት፤ ለሕመም መንስኤ ወይም ምክንያት እንደሆኑ አስረድተዋል፡፡

እንደ Brady (2001; PP.19-20) ገለጻ፤ በፎክ ቡድኑ እሳቤ፤ የጤና ኃይል ሚዛን መዛባትና መጓደል ለሕመም መንስኤ ወይም ምክንያት እንደሆነ ጠቁመው፤ የጤና ሚዛን (ገደብ፣ ልክ እና መጠን ሲዛነፍ ወይም ሲዛባ) ከመጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ሲል ሕመም እንደሚከሰት ገልጸዋል፡፡ በባህል ሕክምና ዕውቀት፤ የሰው ልጅ አካል ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ኃይሎች አካላዊ የጤና ሚዛን ደህንነቱ እንደሚወሰን ጠቁመው፤ በአንጻሩ የጤና ሚዛን ለመዛባት ውጫዊ ምክንያት፤ ምግብ፣ አካባቢ ወይም መለኮታዊ ኃይሎች ሲሆኑ፤ በአዕምሮ ሁኔታ እና በዘር የሚተላለፍ በሽታዎች ተፅዕኖ የሕመም መንስኤ መሆናቸውን Helman (1984; P.12) እንደሚከተለው አስረድተዋል፡፡

> The healthy working of the body is thought to depend on the harmonious balance between two or more elements or forces within the body. To a lesser or greater extent, this balance is dependent on external forces—such as diet, environment or supernatural agents, as well as on internal influences such as inherited weakness, or state of mind.

Hufford (1986; PP.107-109) እና Napier, et al (2014; PP.1608-1610) ደግሞ፤ ለሕመም መንስኤ የሚሰጡ እሳቤዎች፤ ከማኅበረሰቡ "አንኳር" መተዳደሪያ፣ የሕይወት መርህና እሴት፣ የእምነት ሥርዓት፣ የእለት እንቅስቃሴ፣ ሥነ ምግባር፣ ለዓለም እና ለሕመም የአላቸው አተያይ፣ የፈውስ ልማድ፣ የጤና አጠባበቅ ባሕርይ፣ ቡድናዊ ተግባራት፣ ቀያዊ እሳቤዎች (local ideas)፤ ከሣይንሳዊ (ከምዕራቡ አለም እሳቤ) እይታና ተግባር በተቃራኒ የራሳቸውን ባህል ወይም ልማድ የዕውቀት ምንጭ አድርገው እንደሚኖሩ ጠቁመዋል፡፡ የማኅበረሰቡን (የቡድኑን) ባህል መነሻ በማድረግ፤ ለጤና፣ ለሕመም፣ ለፈውስ የአለውን እሳቤ እና ተግባር መመርመር፤ የእምነት ሥርዓቶች፣ ትዕምርቶች፣ ሃይማኖት፣ የኑሮ እሴትን ማጤንና መተንተን ማዕከላዊ ጉዳይ መሆኑን ገልፀው፤ መለኮታዊ ኃይል፣ የወቅቶች መፈራረቅ፣ የመኖሪያ አካባቢ መለያየት፣ የግለሰብ ባሕርይና ጠባይ፣ የዘር ውርስ (ከቤተሰብ)፣ የምግብ ዓይነት ለሕመም መንስኤ ተጠቃሽ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

በአጠቃላይ በባሕል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ ሲባል ውስን ማኅበረሰብና አካባቢያዊ ባህልን መሰረት በማድረግ የሚቀርብ እሳቤን፣ ተግባርን፣ ገለፃና ምክንያትን ማዕከል አድርጎ የሚከወን፤ ከመለኮታዊ ኃይል ቁጣ፣ ከማኅበራዊ መስተጋብር፣ ከሥነ ምህዳር (ከወቅቶችና ከመልክዓ ምድር) ለውጥ፣ ከግለሰብ ጠባይና ተግባር አንፃር ሕመም ሊከሰት እንደሚችል ይታመናል፡፡ ከዚህ በመቀጠል በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ይዘት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 2.1.7 በባህል ሕክምና የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች

በባህል ሕክምና ዕውቀት (ሥርዓትና አተገባበር) የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች በዓይነት፣ በይዘት፣ በተግባር እንደሚለያዩ ምሁራን (Yoder,1972; PP.196-199: Sofowora,1982; P.26: Konadu, 1982; PP.67-68) ይጠቁማሉ፡፡ Sofowora የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ዓይነትና ተግባር በርካታ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በሁለት ዐበይት ምድብ (በዓለማዊና በመለኮታዊ/ መንፈሳዊ) ሥር እንደሚካተቱ ገልፀዋል፡፡ በዓለማዊ ይዘት ሥር እይታዊ ምርመራ (Visual Examination)፣ ክሊኒካዊ ምርመራ (Clinical Examination)፣ ባዮሎጂካዊ ምርመራ (Biological Examinations)፣ የታካሚን ዳራና አጠቃላይ አቋም በማየት የሚደረግ ምርመራ (Observation of the Patient) ይጠቀሳሉ፡፡ በመለኮታዊ ኃይል ይዘት፤ የሥነ ከዋክብት ምልክት ቆጠራን በመጠቀም (Use of Astrological Signs)፣ "ጥንቆላ" (Divination) እና ሕልምን በመፍታትና በመተንተን (Analysis of Dreams) የሚተገበሩ የምርመራ ዘዴዎች… (Sofowora1982; PP.26-28) ይጠቀሳሉ፡፡ ከነዚህ ጥቅል ይዘት አንጻር በመነሳት የሕመም መንስኤ፣ ምልክት፣ ፀባይና ዓይነት እንደሚለያይ፤ (Konadu, 2007; P.67: Young, 1970; PP.34-36: Sofowora, 1982; PP.29-30) ይጠቁማሉ፡፡

Konadu (1982; PP.67-69) እና Sofowora (1982; PP.26-27) በባህል ሕክምና ዕውቀት በሽታን የመለያ ስልቶች እንደ ባህል ሐኪሞቹ ልምድ፣ ዕውቀትና ተመክሮ፤ እንደ "ፎክ ቡድኑ" ልማድ፣ አካባቢያዊ ሁነት፣ ማኅበራዊ መስተጋብር፣ ባህልና ሥርዓት ከቦታ ቦታ፣ ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ እንደሚለያይ ገልፀዋል፡፡ የባህል ሐኪሞቹ የበሽታ መለያ መንገዶችና የዕውቀት መሰረት ከሚኖሩበት አካባቢያዊ ሁነት፣ "ከፎክ ቡድኑ" ልምድ፣ ትምህርት እና እሳቤ፣ ከኢ-መደበኛ ተግባራዊ ልምምድ፣ ከሕመም መንስኤ፣ ዓይነትና ጠባይ፤ ከመለኮታዊ ኃይል እንደሚመነጭ አስረድተዋል፡፡

ከነዚህ ልምድና ተመክሮ በመነሳት የበሽታ መለያና መመርመሪያ ዘዴዎች ዓለማዊ[28]ና መንፈሳዊ ይዘት እንዳላቸው ከዚህ በላይ የቀረቡ ምንጮች ገልፀዋል፡፡ በዓለማዊ ምድብ ከሚጠቀሱ ይዘቶች መካከል ዕይታዊ ምርመራ አንዱ ሲሆን፤ በዕይታ የታካሚን ዓይን፣ የሰውነት ቆዳ፣ ዓይነ ምድርና ሽንትን በማየት የሕመሙን ዓይነት ለመለየት የሚደረግ ሙከራን ይመለከታል (Sofowora, 1982; P.29: Leung, 2010; P.4)፡፡ ክሊኒካዊ ምርመራ ደግሞ፤ የታካሚውን ተክለ ሰውነት (Physical Appearance) እና አጠቃላይ አቋምን በመፈተሽ፤ የልብ ምት፣ የሰውነት ሙቀት መጨመር/መቀነስ፣ የጅማት መሸማቀቅ፣ የመገጣጠሚያ አጥንት እንቅስቃሴ፣ የአጥንት መሰንጠቅና መሰበር፣ የሰውነት ክብደት መጨመር/መቀነስ፣ መዝለፍለፍ፣ መንቀጥቀጥ፣ የድካም ስሜት፣ እራስን መሳት፣ ማላብ፣ የራስ እና የሆድ ሕመምን ይመለከታል (Young, 1970; PP.2-4: Konadu, 2007; P.67)፡፡ ባዮሎጂካል ምርመራ ሲባል፤ የባህል ሐኪሞች የሥሜት ሕዋሶቻቸውን በመጠቀም በማሽተት፣ በማየትና በመንካት እንደሚለዩ Sofowora (1982; P.30) ገልፀዋል፡፡

ከነዚህ የምርመራ ዘዴዎች በተጨማሪ፤ የታካሚን አዕምሮ ጤንነት፣ የሕመም ዓይነት፣ የግለሰቡን ውሎ፣ መኖሪያ አካባቢ፣ የሥራ ሁኔታ፣ ማኅበራዊ ኃላፊነት፣ የቤተሰብ እገዛና እንክብካቤን በማጤን፤ የታካሚን ቀደምት የሕይወት ታሪክ በማዳመጥ፤ የሕመሙን ባሕርይና ሁኔታ መለየት፤ ታካሚን ማበረታታትና መደገፍ ዐበይት ተግባር መሆኑን (Sofowora, 1982; PP.29-30) ጠቁመዋል፡፡ እንደ Amzat and Razum መረጃ ደግሞ፤ ስለበሽታው የሚነገሩ አሉታዎ ዘይቤዎች፣ ሚትና ትረካዎች፤ ከሕመሙ የመግደያ ጊዜና ወቅት በፈጠነ መልኩ የታማሚን ሥነ ልቡና በመጉዳት፤ ሕመምተኛው ሞትን የመጨረሻ ምርጫው አድርጎ እንዲቀበል የመግፋት ኃይል፣ አቅምና ሚና እንዳላቸው፤ አስረድተዋል "…negative metaphors or myths of a disease kill faster than the disease itself, because it forces the patient to accept death as the last resort." (2014; P.158)፡፡

የባህል ሐኪሞች በምርመራ ሂደት፤ የጤና ሚዛን መደላድል ይዘት መጠበቅና መዛባትን በማጤን፤ የአካባቢን ዐየር ንብረት፣ የአመጋገብ ሥርዓት፣ የተፈጥሮ ባሕርይን፣ መለኮታዊ ኃይልን መሰረት በማድረግ፤ የምርመራና የሕክምና ስልታቸው በተቃርኖ (Hot/cold; wet/dry) እና [በተፈጥሮ ባሕርይ መመጣጠን (ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃና መሬት)] ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ገልፀዋል (Helman, 1984; P.12: Brady, 2001; P.19)፡፡

[28] በዚህ ጥናት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ዓለማዊና መለኮታዊ ኃይልን መሰረት በማድረግ ወይም ሁለቱንም በመቀየጥ እንደሚተገበሩ የመስክ መረጃዎች አረጋግጠዋል (ትንታኔ ይዘት፤ ምዕራፍ ስድስትን ልብ ይሏል)፡፡ ጥናቱ፤ በዓለማዊ የበሽታ መለያ ስልቶች ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ዓለማዊ የምርመራ ስልት የሚከተሉ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ሁለት ዓይነት የበሽታ መለያ ዘዴዎችን በመተግበር፤ የምርመራና ሙከራ ጊዜ (Examination and Testing)፤ የውሳኔና ፍርድ (Decision and Judgment) ደረጃዎችን እንደሚተገብሩ ምሁራን (Konadu, 2007: Leung, 2010) ጠቁመዋል፡፡ በምርመራና ሙከራ ሂደት ከታካሚው መረጃ መሰብሰብ፣ ዓይነቱን መለየት፣ ማወቅና ማደራጀን ሲሆን በውሳኔና ፍርድ ደረጃ ደግሞ ቅደም ተከተላዊ መመሪያዎችን በመከተል ግብዓት ማዘጋጀት፣ መተንተን፣ ምክንያታዊ መረጃዎችን መስጠት፣ ውሳኔ ማስተላለፍና ተግባራዊ ማድረግን ይመለከታል፡፡

እንደ Leung (2010; P.4) መረጃ፤ ዓለማዊ የባህል ሐኪሞች ከታካሚ መረጃ ለመሰብሰብ እና ምርመራ ለማካሄድ ከሚጠይቋቸው እና ከሚተገብሯቸው ስልቶች መካከል፤ ሰውነትህን ምን ይሰማሃል? እራስህን እንዴት ያደርግሃል? ምን ዓይነት ምግብ ይጣፍጥሃል/ ይመርሃል? ብርድ ብርድ ይልሃል ወይስ ይሞቅሃል? የሽንትህ ቀለም ምን ይመስላል? በመገጣጠሚያ አጥንትህ አካባቢ ምን ይሰማሃል? ስትተነፍስ ልብህን ይጨንቅሃል? ዉኃ ይጠማሃል? ከዚህ በፊት ምን አሞህ ያውቃል? ሕመሙ እንዴት ተነሳብህ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን ከታካሚዎች እንደሚሰበስቡ አስረድተዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በባህል ሕክምና ባለሙያዎች ተደጋግመው ይነሱና ይተገበሩ እንደነበር፤ በመስክ ቆይታ ጊዜ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ ይዘት በመቀጠል፤ የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ እና ሥነ ምህዳር ከባህል ሕክምና ባለሙያዎች አንፃር ሲታሰቡ ምን ዓይነት ተግባራት አሏቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል፡፡

### 2.1.8 የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ እና ሥነ ምህዳር

ከባህል ሕክምና ተግባራት መካከል የመድኃኒት አሰባሰብ፣ አዘገጃጀት፣ ቅመማና አሰጣጥ ስልትና ሥርዓት በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን ለመድኃኒት የሚውሉ ግብዓቶች የሚሰበሰቡበት ሥነ ምህዳር ምርጫ (Ecological Choice) እና ይዘት ግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ የባህል ሐኪሞች የዕፀ መድኃኒት ግብዓቶችን በሁለት መልኩ ይሰበስባሉ፡፡ በአካባቢያቸው ዕፅዋትን በመትከል (በማልማት) እና ከዱር በመሰብሰብ መድኃኒት ያዘጋጃሉ (Assefa, 1992; P.88)፡፡ እንደ Alemayehu (1984; P.124) መረጃ፤ መድኃኒት የመቀመም ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን

ከተለያዩ አካባቢዎችና ከሥነ ምህዳር መልክዓ ምድራዊ ቦታዎች (በርሃ፣ ቆላ፣ ወይና ደጋ፣ ደጋ፣ ውርጭ ከሆኑ አካባቢዎች) ሰብስበውና ቀምመው መድኃኒት አዘጋጅተው እንደሚሰጡ ያስረዳሉ::

Young (1970; P.45) ደግሞ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ለመለየት፣ ለመሰብሰብ፣ ለማዘጋጀትና ለመቀመም የሥነ ምህዳር ዕውቀትና ተሰጥኦ እንደሚያስፈልግ፤ ይመክራሉ። ስለሆነም የዕፅዋትን ባሕርይ፣ መገኛ ቦታ፣ መጠሪያ ስያሜ፣ የሚሰበሰቡበትን ጊዜና ወቅት፣ የዐየር ንብረት እና መሰል ተግባራትን ጠንቅቆ ማወቅን እንደሚጠይቅ ያስረዳሉ። ከዚህም በተጨማሪ የመድኃኒት ሰብሳቢው ብቃት፣ የመሰብሰቢያ ቁስ፣ ዕፅዋት የሚሰበሰቡበት ዐውድና ሁኔታ (Situations) ለዕፀ መድኃኒት ቅመማ ይዘት ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው፤ መክረዋል።

የባህል መድኃኒት ቅመማ ይዘት፤ እንደ "ፎክ ቡድኑ" ልማድና አተገባበር፣ እንደ ሥነ ምህዳሩ ዓይነት፣ እንደ በሽታው ይዘት ከቦታ ቦታ የሚለያይ ቢሆንም፤ መሰረታዊ ግብዓቶቹ ከዕፅዋት ከእንስሳት፣ ከማዕድናት፣ ከአዕዋፍ እና መሰል ይዘቶች ተዘጋጅተው፣ ተቀምመውና ተመጥነው ለሕሙማን እንደሚሰጡ ገልፀዋል (Yoder, 1972: Alemayehu, 1984; PP.123-124: Wondwosen, 1999; PP.28-30)። የአቀማመሙ ሂደትም፤ በመውቀጥ (በመጨቅጨቅ)፣ በማድረቅ፣ በመሰለቅ፣ በመዘፍዘፍ፣ በመቀቀልና በማጥለል...፤ አዘጋጅተው፤ በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚታኝክ፣ በሚጨስ፣ በሚቀባ መልኩ እንደሚሰጡ፤ ጠቁመዋል (Baquar, 1995; PP.149-150)።

በተመሳሳይ መልኩ Sofowora (1982; PP.6-7) እና Maclachlan (2006, PP.205-206) በዓለማዊ ይዘት የሚመደቡ የዕፀ መድኃኒት አዋቂ ባለሙያዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የዕፀ መድኃኒት ግብዓቶችን ከተለያዩ የሥነ ምህዳር ዓይነቶች በመሰብሰብ ዕፅዋትና መሰል ይዘቶችን በተናጠል ወይም በማቀላቀል ቀምመው፤ ቀጥቅጠው፣ ወቅጠው፣ ቀቅለውና ጨምቀው ባህላዊ መድኃኒት የማዘጋጀት ክህሎት እንዳላቸው ገልፀዋል። የቅመማ ሂደቱ እንደ ማኅበረሰቡ ልማድ የሚለያይ ሲሆን የግለሰብ፣ የቤተሰብና የማኅበረሰብ ዕውቀትና ልማድን አካቶ እንደሚከወን አስረድተዋል።

Alemayehu (1984; P.124)፤ የኢትዮጵያ የባህል መድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ እንደ መድኃኒት ሰጭው ዕውቀትና ተግባር እንደሚለያይ ገልጸዋል። ምንም እንኳ የመድኃኒት አሰጣጡና አተገባበሩ ቢለያይም በዋናነት በመጠጣት፣ በመቀባት፣ በማሽተት፣ በመማግ፣ በማኘክ፣ በማጨስና በክታብ መልክ ተሰርቶ በአንገት ማንጠልጠል፤ በክንድ ላይ ማሰር እና መሰል

ተግባራትን እንደሚያጠቃልል ጠቁመዋል፡፡ የኢትዮጵያን የባህል መድኃኒት ቅመማ፣ አሰጣጥ እና ሕክምና እንደሚከተለው ገልጸውታል፡-

1. የዕፅዋት፣ የእንስሳት እና የማዕድናት ግብዓቶች ላይ በመድገም (አስማታዊ ጥበብን በመጠቀም) የሚሰጥ ሕክምና፤
2. ሕመምተኛው በሌለበት ወይም በሕመምተኛውና በመድኃኒቱ መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት ሳይፈጠር፤ ዕፅን ማዘዝ እና ሕመምተኛን መፈወስ፤
3. ሕመምተኛው በሰውነት አካሉ ላይ እንዲያስር፣ እንዲያንጠለጥል፣ እንዲይዝ፣ በሰውነቱ እንዲቀብረ፣ በማድረግ የሚሰጥ ሕክምና፤
4. እንደ ዘመናዊ ሕክምና፤ በባህላዊ ሕክምና ሥርዓትም በአፍ የሚጠጡ፤ በአፍንጫ የሚሸተቱ፣ የሚማጉ፣ የሚቀቡና በመርፌ መልክ የሚሰጡ መድኃኒቶች እንዳሉ ገልፀዋል (Alemayehu, 1984; PP.123-125)::

ከዚህ አንፃር፤ በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በአካባቢያቸው የሚገኙ የሥነ ምህዳር ዓይነቶችን በመለየት፤ ከዕፅዋት ከእንስሳት፣ ከማዕድናትና ከአዕዋፍ የሰበሰቧቸውን ግብዓቶችን ሲቀምሙ፤ በማድረቅ፣ በመውቀጥ፣ በመሰለቅ፣ በመዘፍዘፍ፣ በመቀቀልና በማጥለል…፤ አዘጋጅተው፤ በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚታኘክ፣ በሚጨስ፣ በሚቀባ… መልኩ እንደሚሰጡ፤ (መሪጌታ ባሕረጥበብ፣ መሪጌታ መኅሪ እና ሊቀጠበብት አብርሃም፤ ቃ.መ፤ 22/01/2011 ፋርጣ፤ 27-30/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል) አስረድተዋል፡፡

በአጠቃላይ የባህል ሐኪሞች ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን በዋናነት ከዕፅዋት የሚጠቀሙ ሲሆን እንስሳትን፣ ማዕድናትን፣ አዕዋፍን እና ነፍሳትን ከተለያዩ የሥነ ምህዳር ቦታዎች ይሰበስባሉ፡፡ የባህል ሐኪሞች የአካባቢያቸውን ሥነ ምህዳር ይዘት፣ ባሕርይና ዓይነት በመገንዘብ፤ ለመድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ሰብስበው ይቀምማሉ፡፡ የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ሲለዩ፣ ሲሰበስቡና ሲቀምሙ ሃይማኖታዊ፣ እምነታዊ እና ልምዳዊ ሥርዓቶችን እንደሚፈፅሙ፤ ምሁራን (Young, 1970: Alemayehu, 1984: Winkelman, 2009) ይመክራሉ፡፡ ከዚህ ይዘት በመቀጠል፤ የጥናቱ ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2.2 ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር፤ ሕዝባዊ የሕመም መንስኤ፣ ሥነ ዕውቀት፣ የማኅበራዊ ግንባታ፣ ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.2.1 የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦች

ሕዝባዊ የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦች (Lay theories of illness Causation) በውስጣቸው ሰፊ ፅንሰ ሃሳቦችን እና እምነታዊ ጉዳዮችን በማካተት፤ የማንኛውም ሕመም መነሻ ምንጭ (Aetiology) ከመለኮታዊ ኃይልና ከተፈጥሯዊ ድርጊት እንደሚሆን ይገልፃሉ (Murdock, 1980; PP.8-12: Helman; 1984, PP.72-73)፡፡ Helman (1984; PP.74-82) የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦችን በአራት ምድብ አጠቃለው እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

1ኛ. ግለሰባዊ የሕመም/ባሕርይ (The Individual Patient) መንስኤ፡- የግለሰብን፤ የግል ባሕርይ፣ ኃላፊነት፣ ጥንቃቄ፣ ንጽህና፣... ለሕመም መንስኤ ያለውን እሳቤ ይመለከታል፡፡ ለምሳሌ፡- አመጋገብ፣ አለባበስ፣ ንጽህና አጠባበቅ፣ የአኗኗር ሥርዓት፣ የማጨስና የመጠጣት ልማድ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን፣... ያጠቃልላል፡፡ የግለሰቡን ጥንቃቄ፣ ኃላፊነትና ባሕርይን... ምክንያት በማድረግ ሕመም ይከሰታል፡፡ ይህም የግለሰቡን ፍላጎትና ተግባር ይመለከታል፡፡ ይህ ልማድ በአውሮፓዉያን የሚዘወተር ሲሆን ግለሰቦች ለሚያጋጥማቸው ሕመም የግል ተግባር፣ ባሕርይና ጠባይን ምክንያት በማድረግ ምላሽ እንደሚሰጡ አስረድተዋል፡፡

2ኛ. ተፈጥሯዊ አካባቢ/ዓለም (The Natural World) የሕመም መንስኤ፡- ተፈጥሯዊ አካባቢ/ሥነ ምህዳር (Ecology) ለሕመም መንስኤ ተደርጎ እንደሚታመን ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ከፍተኛ ሙቀት፣ ቅዝቃዜ፣ ንፋስ፣ ዝናብ፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ ማዕበልን... ይመለከታል፡፡ ማኅበረሰቡ የሚኖርበት መልክዓ ምድራዊ ገፅታ (ሥነ ምህዳር) መሞቅና መቀዝቀዝ፤ የዐየር ንብረት ለውጥ፣ ዐውሎ ንፋስ፤... በምዕራባውያን ማኅበረሰብ የሕመም መንስኤ ተደርገው እንደሚታመኑ መክረዋል፡፡

3ኛ. ማኅበራዊ ዓለም/ሕይወት (The Social World) የሕመም መንስኤ፡- የማኅበረሰቡ ግንኙነት፣ ተግባቦት፣ መስተጋብር፣ እምነት፤ ለቡድናዊና ግለሰባዊ ሥነ ልቡና ውስጣዊ ግጭት፣ ደስታና ፍርሃት ምክንያት እንደሚሆኑ ይታመናል፡፡ ማኅበረሰቡ በአካባቢው ሕመም፣ አደጋና ችግር ሲከሰት፤ "ጠንቋይ፣ አስማተኛ፣ ቡዳ፣ መተተኛ..."

የሚባሉ ግለሰቦችን (ቡድኖችን) ለሕመም እና/ወይም ፈውስ ምክንያት አድርጎ እንደሚያስባቸው መክረዋል (ከምዕራባውያን ውጭ)።

4ኛ. መለኮታዊ ኃይል (The Supernatural World) የሕመም መንስኤ፡- የሃይማኖት ትእዛዝና መመሪያን አለማክበር፤ ሕግና ሥርዓት መጣስና መሻር፣ ልማዳዊ ድርጊቶችን አለመፈፀም፤ "ነውር" የተባሉ ድርጊቶችን መተላለፍ፤... በመለኮታዊ ኃይል እንደሚያስቀጣ ይታመናል። የፈጣሪ ቁጣና ቅጣት፤ "በአጋንንት፣ በዳቢሎስ፣ በጣኦት፤..." ይፈፀማል ተብሎ በአካባቢው ማኅበረሰብ እንደሚታሰብ Helman አስረድተዋል (ከምዕራባውያን ውጭ)። የሕመም መንስኤ ምንጭ ንድፈ ሃሳቦች ማሕቀፍ ምስል (Helman, 1984; P.75) እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ምስል 3፡- የሕመም መንስኤ ምንጭ (Aetiology) ማሕቀፍ




ምንጭ፡- የሕመም መንስኤ አሳቤን የሚገልፅ ይዘት (Helman, 1984; P.75)፤

ከዚህ በላይ የቀረበው ምስል፤ ምን ዓይነት ይዘት አለው? ማዕቀፉ ለምን እያደገ ሄደ? ቅርበት/ ርቀት፤ ማነስና መተለቅ ምን ትርጉም ይሰጣል? ይህ ጥናት የትኞቹን ንድፈ ሃሳቦች ማሻሻያ አድርጎ ተጠቀመ? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል።

እንደ Helman (1984; PP.75-83) መረጃ፤ ግለሰባዊ ባሕርይ እና ተፈጥሯዊ የሕመም መንስኤ እሳቤዎች በምዕራባውያን ማኅበረሰብ የተለመዱ ሲሆን፤ ማኅበራዊ ዓለም/ሕይወትና መለኮታዊ ኃይል ደግሞ በአፍሪካና "በኤሽያ" (በቀሪው ዓለም) የሕመም መነሻ ምንጭ ተደርገው እንደሚታሰቡ ገልፀዋል፡፡ የማዕቀፉ ቅደም ተከተላዊ ሂደትና እድገት፣ ቅርበትና ርቀት፤ ከግለሰብ በመነሳት፣ አካባቢን በመረዳት፤ ማኅበራዊ ሕይወትና መለኮታዊ ኃይልን መዳረሻ ማድረግ፤ የሕመም መገኛ፣ መጀመሪያ ከግለሰብ ቅርበት እና መከሰቻ ዐውድ ጋር በማገናኘት የዕሳቤውን አድማስና ሂደት፤ የመቆጣጠር አቅምን ለማመላከት የቀረበ እንደሆነ በጥናት አቅራቢው ይታመናል፡፡ ይህ ጥናት ከአራቱ የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦች መካከል፤ ማኅበራዊ ሕይወት እና መለኮታዊ ኃይልን በማጣመር የጥናቱ አካልና አባል አድርጎ የመስክ መረጃዎችን ተንትኗል፡፡

በአጠቃላይ የግለሰብ ተግባር፣ ተፈጥሯዊ ዓለም፣ ማኅበራዊ ሕይወት እና መለኮታዊ ኃይል ለሕመም መነሻ ምንጭ ተደርገው እንደሚታሰቡ ከቀረበው ይዘት መገንዘብ ተችሏል፡፡ እነዚህ ንድፈ ሃሳቦች (ማኅበራዊ ዓለምና መለኮታዊ ኃይል)፤ ለዚህ ጥናት ምን ዓይነት ተግባርና አገልግሎት አላቸው? ሲባል ማኅበረሰቡ ለበሽታና ለበሽታ መንስኤ ያላቸውን እሳቤ በመገንዘብ፤ የመስክ ቃለ መጠይቆችን ለማዘጋጀት፣ የመስክ መረጃዎችን በይዘት ለመመደብ እና ለመተንተን አስችለዋል፡፡ እነዚህ ንድፈ ሃሳቦች፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መንስኤ ምን ምን ናቸው? የበሽታ መንስኤ እሳቤና ገለፃ፣ ሚታዊ ተረኮች እና እምነታዊ ሥርዓቶች ይዘት ምን ይመስላል? የበሽታ መንስኤ እና የሥነ ምህዳር ዐውድ ምን ዓይነት መስተጋብር አላቸው? የበሽታ መንስኤ እሳቤ፣ እምነትና ተግባር ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን ዓይነት አስተዋፅኦ አላቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በምርምሩ ሂደት (የጥናቱን ዝርዝር ዓላማ አንድ እና አራትን ይመለከታል) ምላሽ ለመስጠት አስችለዋል፡፡ በቀጣይ ንዑስ ይዘት፤ የሥነ ዕውቀት ንድፈ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

### 2.2.2 የሥነ ዕውቀት ንድፈ ሃሳብ

ሥነ ዕውቀት (Epistemology)፡- የዕውቀት ጥናት ንድፈ ሃሳብ መሰረት የሚያደርገው በዕውቀት ምንነት፣ ተግባር፣ መዋቅር፣ መሰረት፣ ወሰን፣ አድማስ፣ ትክክለኛነት ላይ ሲሆን ይዘቱን በምክንያትና ውጤት ይመረምራል (Greco, 2001; PP.117-119: Sosa, 2007; PP 22-24)፡፡
ሥነ ዕውቀት፤ የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት የሚረዳበት ዘዴና ንድፈ ሃሳብ ሲሆን ተፈጥሮ እና አካባቢን ለመቆጣጠር፣

ለመመርመር እና ለማወቅ የሚደረግ ትግል፤ የማኅበራዊና ግለሰባዊ ፍላጎት እና ቁሳዊ ሐብትን ለማሟላት ሲባል ዕውቀትም እየሰፋ፣ እየዳበረ፣ እየተከማቸ ቅርፅ፣ ሥርዓትና ይዘት እያገኘ ይሄዳል (Greco, 2001; P.118: ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፣ 1978፣ ገ.118)። ሥነ ዕውቀት፤ የዕውቀት አፈጣጠር መንስኤ፣ የድርጊት ስብስብና ሥርዓት ስደራ፣ ተፈጥሮ፣ አጋጣሚ፣ መጠነ ርዕይና አጠቃላይ መርሆዎች የሚያጠና የፍልስፍና ዘርፍ እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ (ጠና፣ 2009፣ ገ.9፤ Denzin and Lincoln 2000; PP.10-11)። Pietila (2003; PP.3-4) ዕውቀትን በዋናነት ነባራዊና ኅሊናዊ በማለት በሁለት ይከፍላሉ። ነባራዊ ዕውቀት (Objective Knowledge) ይዘቱ በነባራዊ ዕውነታ፣ መረጃና ይዘት የሚወሰን፣ በተጨባጭ ምክንያትና ተግባር የሚረጋገጥና የሚገለፅ፣ ነባራዊ ዕውነታን በትክክል ለመረዳት፣ ማኅበራዊ መስተጋብርን ለማጤን፣ ተግባቦታዊ ሥርዓትን ለመገንዘብ፣ ማኅበረሰብ ተኮር ተግባራትን ለመመርመር የሚያገለግል ዕውቀት፤ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ሕሊናዊ ዕውቀት (Subjective Knowledge)፤ በሰው ንቃተ ኅሊና ውስጥ የነባራዊው ዓለም ነፀብራቅ የሆኑ ግላዊ አስተሳሰብ፣ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ተግባር የሚገልጽበት የተለያዩ አስተሳሰቦችን የያዘ፣ ከልምድና ከተግባር የሚገኝ ኢ-መደበኛና የግለሰብ ወይም የቡድን እሳቤ ዕውቀትን ይመለከታል። የሥነ ዕውቀት ጥናት የሚያተኩረው በዕውቀት ምንነት፣ መዋቅርና መሰረቶች ላይ ሲሆን፤ በተለይም የዕውቀት መነሻና መሰረቶች ምንድናቸው? ዕውቀትስ አመጣጡ እንዴት ነው? ዕውነታ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ምን ግንኙነት አለው? የዕውቀት ዳር ድንበሩ እስከ የት ነው? ዕውነትነቱስ በምን ይለካል? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመረምራል (Denzin and Lincoln, 2000; PP.10-11: Sosa, 2007; PP 26-28)።

በዚህ ጥናት፤ የሥነ ዕውቀት ንድፈ ሃሳብ እንዴት ተግባራዊ ሆነ? ሲባል የማኅበረሰቡን (የባህል ሐኪም፤ ታካሚ፤ የአካባቢውን ኗሪ) ዕውቀት፣ እሳቤ፣ ፍልስፍና፣ ምክንያታዊነት እና ተግባራትን ለመገንዘብ፤ ጭምቅ ሃሳብ እና አንኳር ርዕሰ ጉዳይ ለማውጣት፣ የባህል ሕክምና እና የሥነ ምህዳር ተራክቦን ለመረዳት፣ ሥነ ሕይወታዊና አካባቢያዊ ሣይንስን ለመረዳት፤... አገልግሏል። ማኅበረሰቡ (የባህል ሐኪሞች)፤ ለበሽታና ለበሽታ መንስኤ ምን ዕውቀትና ፍልስፍና አላቸው? ለሰው ልጅ አፈጣጠር፣ ለበሽታ ክስተት፣ ለአካባቢያቸውና ዓለም ፍጥረት ምን ዓይነት እሳቤና ዕውቀት አላቸው? ሚታዊ ተረኮች እና የአምልኮ ሥርዓት በሽታ ከየት መጣ ይላሉ? አካባቢያዊ ዕውቀትና ተግባሩ እንዴት ይከወናል? የዕውቀት ማሕቀፍና አደረጃጀቱ ምን ይመስላል? ለሚሉ ጥያቄዎችን ምላሽ ሰጥቷል። በቀጣይ ይዘት የማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 2.2.3 ማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ (Social Constructionist Theory)

ማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ (Social Constructionist Theory) ማዕከላዊ ይዘት፤ ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማኅበራዊ ውቅር ነው፡፡ በማኅበረሰብ መስተጋብራዊ ግንኙነት፣ በዐውዳዊ ሁነት፣ በግልና እና በጋራ ስምምነት የሚፈጠር፣ በግለሰቦች እና በማኅበረሰብ መዋቅራዊ አደረጃጀት የሚከወን፤ የጋራ መግባቢያ፣ ዕውቀት እና አመለካከት ላይ የተመሰረተ ተግባርን ይመለከታል፡፡ ዕውቀት በግለሰብ ደረጃ የሚመሰረት ቢሆንም ከግለሰብ ግለሰብ፣ ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ፣ ከተቋማት ሚና፣ ተግባርና እና አደረጃጀት አንጻር እንደሚለያይ፤ ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማኅበራዊ ስሪት (ውቅር) ነው፡፡ የግልና የማኅበረሰብ ዕውቀትን ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍና ለትውልድ ለማሸጋገር ቋንቋ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው፡፡ የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት ከልምዱ ተነስቶ የሚረዳበት ዘዴና ስልትን (Berger and luckman, 1966; P.1, PP.65-77: Sims and Stephens, 2005; P.43, PP.57-58) ይመለከታል፡፡

ልምድ ደግሞ ከክዋኔና ተደጋጋሚ ከሆኑ ተግባራትና ክስተት የሚገኝ፤ የገሃዱ ዓለም ዕውቀት እና ዕውነታ በማኅበረሰብ አደረጃጀትና መዋቅር የተገነባ መሆኑን Sims and Stephens (2005; P.58) ይገልጻሉ፡፡ የማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ ዋነኛ ትኩረት ማኅበራዊ ዕውቀቶች እንዴት ተፈጠሩ? አንድ ማኅበረሰብ በአካባቢው የሚካሄዱ ሁነቶችንና ድርጊቶችን እንዴት ይተረጉማል፣ ይገልፃል፣ ይማራል፣ ይረዳል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡

በጥናቱ ሂደት፤ የማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ እንዴት ይተገበራል? ሲባል፤ ማኅበረሰቡ (የባህል ሐኪሞች)፤ ለበሽታ መንስኤ ምን ዓይነት ማኅበራዊ እሳቤና መስተጋብራዊ ሕይወት አላቸው? የበሽታ መለያ/ የምርመራ ዘዴ ዕውቀትን እንዴት አዳበሩት/ተገበሩት? ዕውቀትና ተግባሩ ግለሰባዊ እና/ወይም ቡድናዊ ስልት ይከተላል? የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓተ ገቢርና ድርጊት ምን ይመስላል? ለምን ይህን ሥርዓት ይከውናሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች፤ በምርምሩ ሂደት ምላሽ ተሰጥቷል (የጥናት ዓላማ አንድ፣ ሁለትና ሶስትን ልብ ይሏል)፡፡ ከዚህ ይዘት በመቀጠል፤ ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

### 2.2.4. ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ

በፎክሎር ጥናት፤ የዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ (Context-centered Performance theory) መስራች፣ አቀንቃኝ፣ አባትና አራማጅ Richard Bauman[29]፤ የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ፣ ሥርዓትና ተግባር እራሱን ችሎ እንዲጠና አስተዋውቀዋል፡፡ Dundes (1980; PP.20-33) ከ1970ዎቹ በፊት የነበረው የፎክሎር ጥናት በአሀድ (text)፣ "በክዋኔ አላባውያን" (textures) እና በዐውዳዊ (contextual) ሥርዓት ይዘት ላይ የተመሰረተ፤ የአጠናን ስልቱም አሀድ ተኮር (text-centered) እና ዐውዳዊ ስልትን ያልተከተለ እንደነበር ጠቁመዋል፡፡

ዐውድ-ተኮር ክዋኔ (Context-centered performance) የዐውድና እና የክዋኔ አላባውያንን (Elements) በማካተት፣ በማጣመር፣ በማያያዝ፣... የሁለቱን ሕብር፣ ጥምረትና መስተጋብር በማጤን ይዘታዊ ትንተናን ይመለከታል፡፡ የክዋኔ ይዘቶችን ለመተንተን፤ ሁነቶችን፣ ተለዋዋጭ ድርጊቶችን፣ አላባውያንን፣ መቅረቢያ አጋጣሚዎችን፣... ለይቶ ለማጥናት ዐውድ መነሻና መሰረት እንደሆነ፤ የዘርፉ ምሁራን ገልጸዋል (Dundes, 1980: Bauman, 1983,1986, 1992: Ben-Amos, 1975, 1977, 1993: Sims and Stephens, 2005)፡፡

በዐውድ-ተኮር ክዋኔ ወቅት የሚታዩ ግብዓቶች (ቁሶች)፤ የሚሰሙ ቃላት፣ ዜማ፣ ድምፀት፣ ቅላጼ፣ ድግግሞሽ፣ ተመስጦ፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣ የከዋኙ የአቀራረብ ስልት፣ እንዲሁም የተቀባዮቹ ስሜት እንዴት እንደተንፀባረቀ ይመለከታል (Dundes, 1980; PP.25-26)፡፡ ዐውድ አጠቃላይ ድባብን፣ ሁነትን፣ ድርጊትን፣ ሥርዓትን... በማካተት የሚቀርብ ይዘትን ይመረምራል፡፡ ይህም ስለሆነ "ዐውድ፤ ፎክሎርን የመተርጎሚያ መንገድ ነው" (Ben-Amos, 1993; P.210) ወደሚል ማጠቃለያ ሃሳብ ያመራል፡፡

ዐውድ-ተኮር ክዋኔ፡- የ"ፎክ ቡድን" እና የ"ሎር" እሳቤን አጣምሮ በመያዝ ባህላዊና ማኅበራዊ ዐውዶች (Bauman, 1983; PP.363-365)፤ ተግባቦታዊ ሁነቶች፤ በአንድነት የሚቀርቡበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ ሁነት እና ተግባቦታዊ ሥርዓት ይመለከታል፡፡ "Performance is a mode of communicative behavior and a type of communicative events." (Bauman, 1992; P.41)፡፡ በተግባቦታዊ ሂደት መልእክት ሰጪ፣ ተቀባይ፣ ጊዜና ቦታ፣ ርዕሰ ጉዳይ፣ የመግባቢያ አጀንዳ (medium of communication)፣ የተግባቦት ደንቦች (mode of communication); ቅደም ተከተላዊ ሂደት፣ የክዋኔ ቅርጽና መዋቅርን፣... ያካትታል (Ben-Amos,1976, 1993: Bauman, 1992; PP.43-44, 1975;P.299)፡፡

---

[29]Bauman (1975) "Verbal Art as Performance" በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጆርናል (በ1984 በመጸሐፍ ይዘት ታትሚል) አስተዋውቋል (Sims and Stephens, 2005; P.133)፡፡

በዚህ ጥናት “ፎክ ቡድን” ማለት የሚጠናውን ማኅበረሰብ (ኗሪውን)፣ የባህል ሐኪሞች፤ የባህል ሕክምና ተጠቃሚዎች፣ የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎችን፣... መስተጋብር ይመለከታል፡፡ “ሎር” ደግሞ የማኅበረሰቡን የጋራ ዕውቀት፣ ጥበብ፣ እምነት፣ እሴት፣... እና የእነዚህ እሳቤ ምንጭ፣ አሠራር፣ አተገባበር እና ሥርዓት ዐውዳዊ ተግባር፣ ትርጓሜ እና መሰል ጽንሰ ሃሳባዊ ይዘቶችን ያጠቃልላል፡፡

ዐውድ ሲባል የ"ፎክ"ዕውቀት/ጥበብ፣ ተግባር፣ ፍልስፍና፣ እሳቤ፣ ይዘትና አገልግሎትን፤ በቦታ፣ በጊዜ፣ በሁነት እና በዐውዳዊ መስተጋብር ከፋፍሎ ለማየት እና ንድፈ ሃሳባዊ የክዋኔ ማሕቀፍን ለመቀንበብ ይጠቅማል (Ben-Amos,1971; 1993: Bauman,1975; 1992)፡፡ በዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ የተለያዩ የዐውድ ዓይነቶችና[30] የዐውድ መክፈያ መንገዶች ያሉ ቢሆንም በዚህ ጥናት የ"Bauman" (1983; PP.363-365) የዐውድ ምድብና ይዘቶች ተመርጠዋል፡፡ Bauman የዐውድ ይዘቶችን ባህላዊ እና ማኅበራዊ ዐውድ በማለት በሁለት መድበዋል፡፡ ባህላዊ ዐውድ (Cultural context) የፍቺ፣ ተቋማዊ እና የተግባቦት ሥርዓት ዐውዶችን፤ ማኅበራዊ ዐውድ (Social Context) ደግሞ ማኅበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊና ሁነታዊ ዐውዶችን ያካትታል፡፡

የዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ይዘት አላባውያን (Elements)[31] እንደሚከተለው ቀርበዋል)፦

- ✓ የፍቺ ዐውድ[32] (meanings)፦ ትዕምርታዊ ይዘት ያላቸውን የባህል ሕክምና እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር መግለጽ፤ ፍቺ እና ትርጓሜ መስጠት፤

[30]Sims and Stephens (2005; PP.137-139) የፎክሎር ዐውዶችን ተጨባጭ ዐውድ (physical context) እና ማኅበራዊ ዐውድ (social context) በማለት በሁለት ይመድባሉ፡፡ የተጨባጭ ዐውድ ክዋኔ ይዘት፤ ርዕሰ ጉዳዩ የሚካሄድበትን ቦታ፣ ጊዜና አጠቃላይ ድባብ፣ በወቅቱ የነበረውን (ያለውን) ከዋኝ፣ ታዳሚ በመመልከት ብቻ ተጨባጭ ሁነትና ድርጊቶችን ለመግለፅ የሚሞከርበት የዐውድ ዓይነት ነው፡፡ የክዋኔ እና የዐውዱን ግንኙነት ለመመርመር፣ በቴፕ ሊቀረፁ የማይችሉ አንዳንድ አካላዊ ሁነቶችን ለመግለፅ ያስችላል፡፡ ማኅበራዊ ዐውድ፤-በክዋኔ ወቅት የሚታየውን መስተጋብር፤ የክዋኔ መዋቅርና አደረጃጀት፤ የከዋኞች (ማንነት፣ ቡድን፣ ማኅበራዊ ደረጃ፣ ሃይማኖት፣...) እና የታዳሚዎችን ሁኔታ (እድሜ፣ ፆታ፣ ጎሳ፣ መደብ፣ ሙያ እና መሰል ጎዳዮች) ምክንያት በማድረግ የሚመሰረትን ቡድን አጠቃላይ ይዘትና ዐውድ ለመገንዘብ ጠቃሚ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

[31] የዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ይዘት አላባውያን (Elements) የ"Bauman"ን (1983; PP.363-365) ምድብ ሲሆኑ፤ ማብራሪያና መግለጫዎቹ በጥናቱ አቅራቢ የተደራጁ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[32]**የፍቺ ዐውድ (Context of Meaning)፦** የባህሉ ባለቤት የፎክሎር አሀዶቹን እንዴት እንደሚረዷቸው፣ ትርጉም እንደሚሰጧቸው፣ ለእያንዳንዱ ድርጊት፣ ሥርዓት ምን ፍቺ እንዳላቸው ይመረምራል፡፡ ከሕዝቡ አኗኗር ዐውድ፣ ሥርዓት፣ ደንብና መመሪያ የሚገለጹበት መንገድ፣ ፍቺ፣ ትርጉም፤ "አስተማስሎ" (represented)፣ ... የርዕሰ ጉዳዩን ይዘት (content)፣ ትርጉም፣ ፍቺ (meaning)፣ በማኅበረሰቡ ባህል ውስጥ ምን ዓይነት ይዘትና ፍቺ እንዳላቸው ይገልጻል (Bauman, 1983; P.363)፡፡ ማኅበረሰቡ ለበሽታና ለበሽታ መንስኤ ምን እሳቤ አለው? በሽታ ከየት ይመጣል ብሎ ያስባል? ለበሽታ መከሰት ምን ፍቺና ምክንያት ይሰጣል? ማኅበረሰቡ ለፅፀ መድኃኒት አዘገጃጀት፣ ቅመማ፣ አሰጣጥና መመሪያ፤ ለሥነ ምህዳር ይዘት፣ ምን ዓይነት ፍቺና ትርጉም አለው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡ በሚጠናው ይዘት ውስጥ

✓ ባህላዊ ተቋማት (cultural institutions)፡- የባህል ሐኪሞች ማኅበራዊ ደረጃ፣ ዕውቅና፣ ማኅበራዊ ተቀባይነትን ይመለከታል፤

✓ የተግባቦት ሥርዓት (communicative systems)፡- የባህል ሐኪሞች ከማኅበረሰቡ እና ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸው መስተጋብርና ተግባቦታዊ ሥርዓቶችን መግለጽ፤

✓ ማኅበራዊ መሰረት (social base)፡- የባህል ሐኪሞች የገቢ ምንጭ፣ መተዳደሪያ፣ ልማድ፣ የዕውቀት እና የሐብት መሰረትን... መጠቆም፤

✓ የግለሰቦች ባህላዊ አኗኗር (individuals cultural life)፡- የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ግላዊ ዕውቀት፣ የሕይወት ፍልስፍና፣ ለአካባቢና ለዓለም ያለን አተያይ፣ ተግባር፣ ሙያና የሕይወት ክህሎትን ይዳስሳል፤

✓ ሁነቶች (situations)፡- የሥነ ምህዳር ሁኔታ፣ ወቅት፣ መልክዓ ምድር፣ የዐየር ንብረት፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር መስተጋብራዊ ሁነትን፤ ልብ ይሏል፡፡

በፎክሎር ጥናት የመስክ መረጃዎችን ለመተንተን (የማኅበረሰቡን ባህል) እና ተግባቦታዊ ሂደቶችን በውል ለመረዳት፣ የ"ፎክ" እና የ"ሎር" ዐውዳዊ እሳቤዎችን ለመተርጎም፤ ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ ለማቅረብ ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ዐብይ አንጻር መሆኑን ምሁራን ይመክራሉ (Bauman,1975, 1977, 1983: Ben-Amos,1976, 1977, 1993: Shoemaker,1980)፡፡ እንዴት? ለሚለው ጥያቄ በመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ሞዴል ክፍል (3.6.2 ዐውድ-ተኮር ሞዴልን ይመልከቱ) የቀረበውን ይዘት ይመልከቱ፡፡ በዚህ ጥናት ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ እንዴት ይተገበራል? ሲባል፤

ማንኛውም የፎክሎር አሃድ/ቴክስት እንደየዘውጉና ባሕርይው መከወኛ አጋጣሚው፣ ሥርዓትና ሂደቱ ይለያያል፡፡ እንደዘፈን፣ እንደለቅሶ፣ እንደሥርዓተ-ከበራ፣ እንደተረት ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ አካላዊ እንቅስቃሴን እና ዐውዳዊ ሁነትን የግድ የሚሉ ሥርዓቶች እንዳሉ ይታመናል፡፡ የባህል ሕክምና ሥርዓት እና አተገባበር (ክዋኔ) እንደ በሽታው ዓይነት፣ እንደ ሕመሙ ባሕርይ፣ እንደ ሥነ ምህዳሩ ሁኔታ፣ እንደመድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ሂደት፣ እንደ ባህል ሐኪሙ ዕውቀት፣ እንደ አካባቢው ልማድ የክዋኔ ሂደቱ አጭር፣ ረጅም እና ዝርዝር እንዲሆን ምክንያት ይሆናል (አንድ በሽታ በተለያየ ዐውድና አጋጣሚ እንዲከወን

---

የተገነባ ሥርዓት፣ እሳቤ፣ መንስኤና ውጤት፣ አድርግ አታድርግ (modes of action)፣ ተግባቦት፣ ትዕምርት፣ ዘይቤያዊ ንግግሮች (metaphoric) … ለምን ተግባር እንደዋሉ፤ ምን ዓይነት ፍቺ እንዳላቸው ይመረምራል (Bauman, 1983; P.363)፡፡

ያስገድዳል)፡፡ እነዚህን ተግባራት በአንድ ማሕቀፍ ተመልክቶና ለክቶ፣ የባህል ሕክምና ክዋኔ "ይሄ ነው!" ብሎ መደምደም ለስህተት ይዳርጋል፡፡ ለምሳሌ፡- ለእንጥል እና ለአጥንት ነቀርሳ በሽታ ሂደታቸውን ጠብቆ በዐውዳዊ ክዋኔ መሰብሰብ ቢቻልም፣ ተመሳሳይ ድርጊት፣ ጊዜና ማሕቀፍ ማግኘት አይቻልም፡፡

ነጠላና ንዑስ ርዕሰ ጉዳይን መርጦ እንደ ሕመሙ ዓይነትና እንደ መድኃኒቱ ባሕርይ ማስረዳትና ክዋኔውን መግለፅ ይቻላል፡፡ ይህ ተግባር ደግሞ "ቋት" አይሞላም፣ ዝርዝር፣ አሰልቺ እና የሕይወት ዘመን ጥናት ይሆናል፡፡ ይህም የባህል ሕክምና ሥርዓቱን አያሳይም፡፡ ይህ ችግር እንዳለ ከታመነ ለምን በዐውድ ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ማጥናት ተፈለገ? ሲባል፣

አጥኚው በአካል መስክ ላይ ተገኝቶ ኢትኖግራፊያዊ ምርምር ሲያካሂድ በዐውድ ተኮር ክዋኔ የባህል ሐኪሙና ታካሚው ተገናኝተው የሚያደርጉትን መስተጋብር፣ በሽታውን የሚለዩበት ሂደት፣ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ልማድ፣ የቅመማ ሂደትና የመድኃኒት አሰጣጥ ተግባርን ዝርዝር ጉዳዮች በመፈተሽ፣ በባሕርይና በይዘት የሚዛመዱትን በማደራጀት ምን የጋራ ዕውቀት እና ክዋኔ አላቸው? ምን ዓይነት ተጨባጭ፣ ተተንታኝ ዕውቀትና ማሕቀፍ ማግኘት ይቻላል? በዚህ ተግባር የባህል ሕክምና የቆመበት አምድ ምን ሆኖ ተገኘ? ቅድመ-ዝግጅት (የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ)፣ ወቅት (የቅመማ ሂደት) እና ድህረ ዝግጅት (የመድኃኒት አሰጣጥ) ማሕቀፍ በምን ይዘትና ባሕርይ ላይ ተመስርቶ እንደሚከወን በማስረዳትና በመተንተን ላይ ያተኮረ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ዝርዝር የመስክ መረጃዎችን ከነዐውዳቸው ሰብስቦ፣ ባሕርያቸውን ለይቶ፣ ተዛምዷቸውን አጥንቶ፣ ማዕከላዊ ጉዳያቸውን እና የጋራ መሰረታቸውን ለማግኘት ዐውድ ተኮር ክዋኔ የግድ ይሆናል፡፡

ለአብነት ያህል፡- አንድ የባህል ሐኪም "ለሃያ፣ ለአርባና ሃምሳ የበሽታ ዓይነቶች ዕፀ መድኃኒት ቀምሜ እሰጣለሁ" በማለት ይናገራል/ማስታወቂያ ይለጥፋል፡፡ ይሄን ሁሉ በሽታ እንዴት ማከምና ማዳን ይችላል? ሲባል የባህል ሐኪሙ ዕውቀት የበሽታዎችን ጠባይና ዝምድና በመለየት፣ የዕፅዋትን ባሕርይና ጣዕም በማወቅ ላይ ይመሰረታል፡፡ ሥርዓቱንም በተመሳሳይ መንገድ እና ይዘት ይከውናል፡፡ ይህ ተግባር ሌላም ነገር ይጠቁመናል፤ የባህል ሐኪሞች ከአገር በቀል ዕፅዋት በተጨማሪ ባህር ዛፍ፣ ፓፓዬ፣ ኒም እና መሰል ዕፅዋትን በአጭር ጊዜ ባሕርያቸውን ለይተው ለባህል ሕክምና አገልግሎት ይጠቀሚቸዋል፡፡ ከዚህ ተግባር ምን እንማር ይሆን?

ይህ ጥናትም የተግባርና የዕውቀት መሰረታቸውን ፈትሾ፣ የጋራ ክዋኔ ሂደቶችን በመግለፅ፣ የዕውቀቱን ማሕቀፍ ማሳየትና ማብራራት ላይ አተኩሯል፡፡

## 2.2.5 የንድፈ ሃሳቦች ትኩረትና ድክመት፣ ትስስር እና ማሕቀፍ ይዘት

ይህ ጥናት የኤትኖግራፊ (Ethnography) ዘዴን በመተግበር የቀረበ ሲሆን፣ በዐውድ አንፃር የተሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች፣ በይዘት ተደራጅተው በትርጓሜ አንፃር (Interpretive Perspective) ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በትርጓሜ እይታና ማሕቀፍ ሥር የሚካተቱ ንድፈ ሃሳቦችን እና ሞዴሎችን በመለየትና በመከተል ምርምሩ ተካሂዷል፡፡ Amazat and Razum (2014; PP.130-302) የትርጓሜ ንድፈ ሃሳብ (Interpretive theory) ይዘት፣ ትዕምርት፣ መስተጋብር፣ ማኅበራዊ መዋቅር፣ ዐውድ እና መሰል ሥያሜና ተግባር በመያዝ በተለያየ መንገድ እንደሚጠራ ገልፀዋል፣ ሕዝባዊና ማኅበራዊ ዕውቀት፣ ማኅበራዊ ግንባታና መዋቅር፣ ትዕምርት፣ ዐውድና ክዋኔ ንድፈ ሃሳቦች፣ የትርጓሜ ንድፈ ሃሳብ አካልና አባል እንደሆኑ አስረድተዋል፡፡

የንድፈ ሃሳቦቹ ትኩረትና ድክመት፣ ውስን ሁነትን (Micro-phenomena)፣ ማኅበረሰብን፣ አካባቢና ርዕሰ ጉዳይን ነጥለው የሚያጠኑ ሲሆን፣ ሰፊ ርዕሰ ጉዳይና ሁነትን (Macro-events)፣ ቦታ እና ማኅበረሰብን የጥናት ትኩረትና አካል አያደርጉም፡፡ እይታና ትኩረታቸው አካባቢያዊ ዐውድና መስተጋብር፣ ማኅበራዊ ዕውቀትና ተግባር፣ ቡድናዊ ፍቺና መግባቢያ ይዘት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ሲሆን፣ ዓለማቀፋዊ ዕውቀትና ጠንካራ ሣይንሳዊ መርህን፣ ዘዴን፣ ደንብና ተግባርን በመከተል፣ የብዙኀን መግባቢያ ጉዳይን የትኩረታቸው ማሕቀፍና ይዘት አይፈቅድም፡፡ ንድፈ ሃሳቦቹ፣ በግለሰብ፣ በቡድንና በማኅበረሰብ እሳቤ፣ ተግባር፣ ዕውቀት፣ ዐውድና አካባቢ የተገደቡ ሲሆን ዓለማቀፋዊ ተግባር፣ ዕውቀት፣ ትዕምርትና ሽፋን የላቸውም፡፡ ይህም ስለሆነ፣ በዋናነት ዓይነታዊ የምርምር ይዘትን የሚከተሉና የሚተገበሩ ሲሆን፣ በገለፃ፣ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታ፣ በቡድን ውይይትና በንጥል ጥናት የመስክ መረጃዎች ተሰብስበው ይቀርባሉ፣ መጠናዊ (ቁጥራዊ) ይዘትን በዋናነት አይከተሉም፡፡ የናሙና አመራረጥ ሂደቱም ርዕሰ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ግለሰቦች በቀጥታ መምረጥና መረጃ መሰብሰብ ሲሆን፣ ግላዊ አመለካከት፣ አድሎ፣ እሳቤና ተፅዕኖ ሊደርስ እንደሚችል ስለሚታሰብ፣ ዕውነታው ላይ ለመድረስ በተመራማሪው ክትትል፣ ጥንቃቄና ማጣራት ሂደት ላይ ሊወሰን ይችላል፡፡ የንድፈ ሃሳቦቹ ትኩረት ማኅበራዊ አጋጣሚና ልምድን፣ አካባቢያዊ ዕውቀትና ተግባርን መሰረት በማድረግ የማኅበረሰብና የቡድን መለያን፣ ትዕምርትን፣ እሳቤን፣ ፍቺን፣ ዕውቀትና ዐውድን ተንትኖ ማቅረብ ላይ የተገደቡ መሆኑን

(Amazat and Razum, 2014; P.302) አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በታች የንድፈ ሃሳቦች ትስስርና የትንታኔ ይዘት ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ምስል 4፡ የንድፈ ሃሳቦች ትስስር እና የትንታኔ ይዘት ማሕቀፍ




ምንጭ፡- የጥናቱ አቅራቢ. ጥር/2012 ዓ.ም፡፡

ከዚህ በላይ የንድፈ ሃሳቦች ትስስርና የትንታኔ ይዘት ማሕቀፍ ተገልፀዋል፡፡ ጥናቱ የባህል ሕክምና ዕውቀትን መነሻ በማድረግ የሕመም መንስኤ፣ የምርመራ ዘዴ፤ የመድኃኒት ቅመማ፤ አሰጣጥና መመሪያን፤ ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸውን ዐውዳዊ መስተጋብር በቅደም ተከተል አቅርቧል፡፡ በምርምሩ ሂደት የሕመም መንስኤ፣ ሥነ ዕውቀትና ማኅበራዊ ግንባታ፣ ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳቦችን ተከትሎ፤ ባህል ተኮር፣ ዐውድ-ተኮር እና የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴሎችን መተንተኛ ስልት አድርጓል፡፡ የንድፈ ሃሳቦች ትስስርና ይዘት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በማኅበረሰብ እሳቤ ማንኛውም የሕመም መንስኤ መለኮታዊ ኃይልና ተፈጥሯዊ ምክንያት ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በሥነ ዕውቀትና በማኅበረሰብ ግንባታ ደግሞ የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት የሚረዳበት ዘዴ፤ ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማኅበራዊ ውቅር፣ የጋራ ስምምነትና መስተጋብር እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ የጋራ ስምምነትና ዕውቀትን መነሻ በማድረግ፤ አካባቢን ለመቆጣጠር፣ ለመመርመርና ለማወቅ የሚደረግ ትግልና ጥረትን ይመለከታል፡፡ በዚህ ሂደት ለእያንዳንዱ ተግባር፣ ሥርዓት እና እንቅስቃሴ፤ ስም ይወጣል፣ ፍቺ ይሰጣል፤ ትርጉም ይቀመጣል፤ ትዕምርታዊ ውክልና ይካሄዳል፤ የጋራ መግባቢያ

ኮድ ለቁስ፣ ለሁነት፣ ለድርጊት፣ ለባሕርይ ባህላዊ ስምምነትና ፍቺን ምክንያት በማድረግ ትዕምርትና ውክልና ይሰጣል፡፡ በሂደት ማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ፣ እሳቤና ድርጊት በክዋኔ ይገለጻል፣ በተግባር ይለመዳል፡፡ ዕውቀት በሃሳብና በድርጊት ይገለፃል/ይከወናል፤ ያልታሰበ አይከወንም፣ የማይከወን የጋራ ሐብትና ዕውቀት አይሆንም፤ የዕውቀት ተስተላልፎ፣ የድርጊት መገለጫ፣ የሥርዓት መዋቅር መቅረቢያ ስልትና መንገዱ ክዋኔ ይሆናል፤ በዚህ ባሕርያቸው ይተሳሰራሉ፡፡ በምርምሩ ሂደት፤ ፅንሰ ሃሳብ፣ ንድፈ ሃሳብ፣ የመረጃ መተንተኛ ሞዴሎችን እና የመስክ መረጃዎችን በማስተሳሰር፤ የማኅበረሰቡ እሳቤ፣ ዕውቀት፣ ክዋኔ እና ሥርዓት ይዘት፤ በትንታኔ ክፍል ቀርበዋል፡፡ ቀጣይ ይዘት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን ይመለከታል፡፡

## 2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ከባህል ሕክምና ሥርዓትና አተገባበር ጋር በተያያዘ በአስራ ዘጠኝ (19) ቀደምት ጥናቶች ይዘት ላይ ቅኝት ተደርጓል፡፡ የዚህ ቅኝት ዐቢይ ዓላማ፤ የቀደምት ጥናቶችን ርዕሰ ጉዳይ፣ ዐቢይ ዓላማና ትኩረት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ መተንተኛና የናሙና ስልት መጠቆም፤ ማዕከላዊ ይዘትና ግኝታቸውን መግለፅ፤ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ማስረዳት፤ ከጥናቶቹ የተገኘን ልምድ፣ ዕውቀትና ተመክሮን ማመላከት፤ የዚህ ጥናት ትኩረትና ይዘትን ማስረዳት፤ የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ተቃኝተው ቀርበዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ሰባት፣ በሥነ ሰብ ስድስት፣ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ሁለት፣ በታሪክ ትምህርት ክፍል ሁለት፣ በሥነ ሕይወት ትምህርት ክፍል አንድ፤ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል አንድ፤ በድምሩ 19 ጥናቶች ለሁለተኛ(13) እና ለሶስተኛ(6) ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ምርምሮች ተቃኝተዋል፡፡

ጥናቶቹ በአላቸው ጭብጥና ይዘት በአራት ምድብ ተከፍለዋል፡፡ በምድብ አንድ የባህል ሕክምና ልማድን መሰረት ያደረጉ ጥናቶች፤ በምድብ ሁለት የባህል እና የዘመናዊ ሕክምና ጥምረትን፤ የማኅበረሰብ አመለካከትን የዳሰሱ ጥናቶች፤ በምድብ ሶስተኛ የባህል ሕክምና ዳራና ታሪክን ትኩረት ያደረጉ ጥናቶች፤ በምድብ አራት የባህል ሕክምና ግብዓትን በሣይንስ ቤተ ሙከራ የፈተሹ ጥናቶች ይዘት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.3.1 የባህል ሕክምና ልማድን መሰረት ያደረጉ ጥናቶች

በዚህ ንዑስ ክፍል፤ የባህል ሕክምና ልማድን መነሻ ያደረጉ 13 የቀደምት ጥናቶች ይዘት፣ ትኩረት፣ የአጠናን ዘዴ፣ ግኝት እና መሰል ጉዳዮች እንደሚከተለው ተዳሰዋል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጥናቶች መጀመሪያ፤ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተካሄዱ ጥናቶች በቀጣይነት ባላቸው ዓመተ ምህረት ቀደም ተከተል ቀርበዋል[33]፡፡

ዓለማየሁ (2000) "የኑዌር ማኅበረሰብ ባህላዊ ሕክምና እውቀት፣ አመለካከት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ በጋምቤላ ክልል በኑዌር ዞን ውስጥ በሚገኙ ሁለት ወረዳዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የኑዌር ማኅበረሰብን የባህል ሕክምና ዕውቀት፣ አመለካከት፣ የመድኃኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ ሂደትና ተግባር ምን እንደሚመስል መመርመርና የባህል ልማዱን ማስረዳት ነበር፡፡ በጥናቱ ሂደትም፤ በባህላዊ ሕክምና የሚፈወሱ በሽታዎች ምን ምን ናቸው? ሕክምናውን የሚሰጡ እነማን ናቸው? የመድኃኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ ሂደት ምን ይመስላል? ባለሙያዎቹ መድኃኒቶቹን ከየትና ከምን ግብዓት ይቀምማሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች በጥናታቸው ይዘት መልስ ሰጥተዋል፡፡ እነዚህን የምርምር ጥያቄዎች ከግብ ለማድርስ ገላጭ ትንተና ስልት እና ዓላማ ተኮር ናሙናን መሰረት ያደረጉ ሲሆን የመስክ መረጃዎችን በምልከታና በቃለ መጠይቅ ሰብስበዋል፡፡

በኑዌር ማኅበረሰብ በባህላዊ ሕክምና ከሚፈወሱ በሽታዎች መካከል የአንጀት ውስጥ ትላትል፣ ተቅማጥ፣ ቁርጠት፣ የሰውነት ቁስል፣ ወባ፣ የሆድ ትላትል፣ ስብራት፣ የቆዳ በሽታ እና የመሳሰሉትን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በአካባቢው የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን የሚፈውሱ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች "ቴትዋል (tetwal)፣ ይስ (yieth)፣ ጋም (gam) እና ጎክ (gok)" በመባል እንደሚጠሩ በጥናታቸው ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች መድኃኒቶችን በአብዛኛው ከዕፅዋት፣ ቀሪውን ደግሞ ከእንስሳትና ከማዕድናት ውጤቶች በመቀመም፤ ቴክኒካዊ የሕክምና ተግባራትን በማከናወን እና በመንፈሳዊ ኃይል በመታገዝ የኅብረተሰቡን የጤና ችግሮች እንደሚፈቱ አስረድተዋል፡፡ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች፤ በክልሉ ባህልና ቱሪዝም፣ ጤና ቢሮ እና መሰል ሰናይ ድርጅቶች ምንም ዓይነት ትኩረት ያልተሰጣቸው መሆኑን በመጠቆም የሚመለከታቸው አካላት (የክልሉ ባህልና ቱሪዝም፤ ጤና ቢሮ) ሃገረሰባዊ ልማዱን ጠብቆ ለማቆየት እና የሕዝቡን ጤንነት ለመጠበቅ ሲባል የሕክምና ባለሙያዎችን እንደ ሙያ

[33] ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተዛምዶና ልዩነት፤ በዚህ ንዑስ ርዕስ መጨረሻ የቀረበ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ችሎታቸው መዝግቦ በመያዝ፤ ለባህላዊ እሴቱ ትኩረት መስጠት  እንደሚገባ የይሁንታ ሃሳብ በማቅረብ፤ ጥናታቸውን አጠናቀዋል።

የዓለማየሁ ጥናት የኑዌርን  ማኅበረሰብ  የባህል ሕክምና  ዕውቀት፣ አመለካከት፣ የመድኃኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ ሂደት፣ ተግባር፣ ገለፃና የመረጃ ዓይነት፣ ክለሳ ድርሳን እና ትንተና ክፍል ጠንካራና በሥርዓት የተደራጁ ናቸው። የምርምሩን ርዕሰ ጉዳይና ጥያቄዎች ከግብ ለማድረ ምን ያህል መረጃ ሰጪዎች (በአውራና በንዑስ መረጃ ሰጭነት) ተመረጡ? የተመረጡበት መሰረታዊ መስፈርት ምን ነበር? የቡድን ተኮር ውይይት ለምን እንዳልተመረጠ? በምልከታና በቃለ መጠይቅ  ምን ዓይነት መረጃዎች ተሰበሰቡ?  የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች ምን ምን ነበሩ? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ የማይሰጥ መሆኑ፤ የጥናቱን ክፍተት ያመላክታል[34]። ዓለማየሁ፤ የባህል ሕክምና ይዘትን በማጥናት በኢትጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ መሆናቸው፣ የኑዌርን የባህል ሕክምና ጥበብና ልማድን ማጥናታቸው ልዩ ያደርጋቸዋል።

ምህረት (2000) "በአዲስ አበባ ከተማ የባህል መድኃኒት አዘገጃጀት፣ አሰጣጥና አጠቃቀም" በሚል ርዕሰ ጥናት አቅርበዋል። የጥናቱ ማዕከላዊ ይዘት፤ የዘመናዊ ሕክምና አገልገሎት በተሻለ ሽፋን በሚሰጥበት የአገራችን ዋና ከተማ፤ የባህል ሕክምና በስፋት እንደሚሰጥ አስረድተዋል። ጥናታቸው ዘመናዊ ሕክምና በስፋት በሚሰጥበት ቦታ የባህል የሕክምና በስፋት መገኘቱን፤ የባህል ሕክምና አሰጣጡን፣ ፈውስና እና ውጤታማነቱን ከታማሚዎች ማረጋገጥ፤ ከዚህም በተጨማሪ ህገረሰባዊ እምነት በባህል ሕክምና ያለውን ሚና፤ መመርመርና በጽሁፍ አስፍሮ ማሳየት ዋና ዓላማቸው ነበር። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የባህል መድኃኒት ባለሙያዎች የሕክምና ጥበብ መነሻና መድኃኒት አጠጣጥን ማሳየት፤ የባህላዊ መድኃኒት የሚገኙበትን አካባቢና አዘገጃጀት ማመልከት፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች አዘውትረው የሚፈውሷቸውን በሽታዎች በመረጃ አስደግፎ ማቅረብ፤ ሃይማኖትና እምነት በባህላዊ መድኃኒት ላይ ያለውን ሚና ማሳየት የሚሉ ናቸው። የጥናት ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ፤ ገላጭ አቀራረብ ስልትን የተከተሉ ሲሆን የመስክ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በጽሁፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል።

---

[34]ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ተዛምዶና ልዩነት ለማጤን፤ በዚህ ንዑስ ይዘት መጨረሻ የቀረበውን ማብራሪያ ልብ ይሏል።

ምህረት በጥናታቸው ሂደት ዘመናዊ ሕክምና በተሻለ ሁኔታ በሚገኝበት አዲስ አበባ፣ "የባህላዊ መድኃኒት ሕክምና አገልግሎት" በስፋት እየተሰጠ መሆኑን ጠቁመው፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች አዘውትረው የሚፈውሷቸው በሽታዎች አልማዝ ባለጭራ፣ ኪንታሮት፣ ችፌ፣ የወፍ (የጉበት) በሽታ እና የሰውነት ቁስል እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያ ዘመናዊ ሕክምና በተሻለ ሁኔታ በሚሰጥበት አዲስ አበባ፣ የባህል ሕክምና አገልግሎት በስፋት እየተሰጠ መሆኑን በጥናቱ አስረድተዋል፡፡ የባህላዊ ሕክምና ባለሙያዎች "ሁሉም በቂ ችሎታ ያላቸውና ታማኝ ናቸው ባይባልም" በዘርፉ የሚሰጠው አገልግሎት ከፍተኛ እንደነበር ጠቅሰዋል፡፡ የባህል ሕክምና ዘርፍ በዘመናዊ የሕክምና ባለሙያዎች ታግዞ ቢቀጥል ያለውን የጤና ችግር ለማቃለል አስተዋጽኦው የጎላ መሆኑን፤ የሚመለከታቸው የጤና ቢሮዎች ጉዳዩን በመፈተሽና በመመርመር፤ ዕውቀቱና ክህሎቱ ለአላቸው ባለሙያዎች ሕጋዊ ፈቃድ ቢሰጡ መልካም መሆኑን በመጠቆም ጥናታቸውን አጠቃለዋል፡፡

የምህረት ጥናት፤ ይዞት የተነሳውን ርዕሰ ጉዳይ ከግብ ለማድረስ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን (ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ) ተግባራዊ ያደረገ፤ ሃይማኖትና እምነት በባህላዊ መድኃኒት አሰጣጥና ፈውስ ሂደት ውስጥ ጉልህ ሚና እንዳላቸው የጠቆመ ቢሆንም የምርምሩ ዐቢይ ዓላማ በግልጽ አልተቀመጠም፡፡ ጥናቱ ቀጥተኛ ገለጻና ዘገባዊ አቀራረብን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በጥናቱ ክለሳ ድርሳን በቂ ጽንሰ ሃሳብና ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ ያልቀረበ ሲሆን በማጣቀሻነት የተመረጡ መጻሕፍትም ሃይማኖት እና እምነት በባህላዊ መድኃኒት ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ የሚያትቱ ናቸው፡፡ ጠቅለል በአለመልኩ ሲታይ ጥናቱ፤ በርዕስ ጉዳይ አተገባበር፣ በዐቢይና ንዑስ ዓላማዎች ይዘት፣ በናሙና አመራረጥ ስልት፣ በክለሳ ድርሳን አደረጃጀትና በመረጃ አተናተን ስልት ክፍተት ይታይበታል፡፡ ምህረት፤ በአዲስ አበባ ከተማ የሚካሄደውን የባህል ሕክምና ይዘት ማጥናታቸው፣ የጽሑፍ መጠይቅን መጠቀማቸው፣ ዘመናዊ ሕክምና በበዛበት አዲስ አበባ የባህል ሕክምና ተቀባይነት እንዳለው መቃኘታቸው፤ የጥናታቸውን ዐውድ የተለየ አድርጎታል፡፡

መስፍን (2002)፤ በሃገረሰባዊ መድኃኒት አሰጣጥና አተገባበር ዙሪያ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው ርዕስ ጉዳይ "የሃገረሰባዊ መድኃኒቶች ቅመማና ባህላዊ አጠቃቀም በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ" የሚል ነበር፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ፤ በምሥራቅ ጎጃም ዞን በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚከናወነውን የሃገረሰባዊ መድኃኒት አዘገጃጀትና አጠቃቀም ምን

እንደሚመስል በመመርመር ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውን ገልፆ ማሳየትን ታላሚ አድርጓል፡፡ ይህን ዐቢይ ዓላማ ለመመለስ፤ የሃገረሰባዊ መድኃኒት አዘገጃጀትና አጠቃቀም ከማኅበረሰቡ እምነትና ልማድ አንፃር ምን እንደሚመስል ማሳየት፤ የባለሙያዎቹ የሕክምና ጥበብ መነሻና መተላለፊያ መንገድ ምን እንደሆነ መጠቆም፤ ለሃገረሰባዊ መድኃኒቶች መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሶችና ግብዓቶች ትዕምርታዊ ፋይዳ ምን ምን እንደሆኑ ጥናቱ መርምሯል፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ከዋና ሃገረሰባዊ ሐኪሞች፣ ከዘመናዊ የሕክምና ባለሙያዎች፣ ከሃገረሰባዊ መድኃኒት ተጠቃሚዎች የቃለ መጠይቅና የምልከታ ዘዴዎችን በመጠቀም በጽሑፍ፣ በመቅረፀ ድምፅ እና በፎቶ የተሰበሰቡ ስለመሆኑ በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በገላጭ እና በይዘት ትንተና ስልት ቀርበዋል፡፡

በጥናቱ ሂደት በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚኖሩ የባህል ሐኪሞች በብዛት መር ጌታዎች፣ ደብተራዎች፣ ሃጂዎች እና ሼኾች ሲሆኑ የሕክምና ጥበቡን ከየመጡበት ሃይማኖታዊ ተቋም እንደተማሩት ተጠቆሟል፡፡ ሃገረሰባዊ የሕክምና ባለሙያዎች ለፈውስ ሕክምና የሚገለገሉባቸው መድኃኒቶች በአብዛኛው የሚቀመሙት ከዕፅዋት ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ ከእንስሳትና ከመዓድናት ውጤቶች መሆናቸውን ጥናቱ ያስረዳል፡፡ የሃገረሰባዊ ሐኪሞች ለበሽተኞች የሚያደርጉት የሥነ ልቡና ድጋፍ እና ማኅበራዊ ቀረቤታ የሕክምና ዘርፉን ተመራጭ እንዳደረገው ተገለጿል፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት ዘመናዊና ሃገረሰባዊ የሕክምና ባለሙያዎችን በማቀራረብ የዕውቀት ሽግግር የሚያደርጉበትን እና በጋራ የሚሰሩበትን ስልት መንደፍ የተሻለ መሆኑን በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

የመስፍን ጥናት ርዕሰ ጉዳይ፣ ዐቢይ ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች በሥርዓት የተደራጁ፤ የምርምር ጥያቄዎች በትንታኔው ይዘት ምላሽ አግኝተዋል፡፡ በጥናቱ ክለሳ ድርሳን ንድፈ ሃሳባዊ[35] [ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝትን ይመለከታል] እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ከጥናቱ ትንታኔ ክፍል ጋር ተደራጅተውና ተሰናስለው ቀርበዋል፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ርዕሰ ጉዳይና ዓላማ ግብ ያደረሰ ቢሆንም በጥናቱ ዘዴና አተገባበር ላይ ክፍተት ይስተዋላል፡፡ ለዓብነት ያህል፤ ጥናቱ የትኛውን የምርምር ዓይነት ተከትሏል? የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ ስልት ምንድን ነው? ዐቢይና ንዑስ መረጃ ሰጪዎች እንዴት ተመረጡ? በምልከታና በቃለ መጠይቅ ምን ዓይነት መረጃዎች ከመስክ ተሰበሰቡ? የቡድን ተኮር ውይይት ያልተመረጠበት ምክንያት ምንድን ነው? ለሚሉ

[35]ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት በጥናቱ ሂደት ያልቀረበ ሲሆን በቀጥታ ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝትን የሚተካ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ጥያቄዎች ምላሽ አይሰጥም። መስፍን፤ በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢው የሚሰጠውን የባህል ሕክምና መዳሰሳቸው፤ ልማድና ሥርዓቱን መቃኘታቸው በዚህ ይዘት ከቀረቡ ጥናቶች ይለያል።

ተመስገን (2003)[36]፤ "በባህላዊ ሕክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በግሼ ወረዳ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ በባህላዊ ሕክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልት ምን እንደሚመስሉ ከልማድ፣ ከእምነትና ከባህል አኳያ መመርመር ነው። ጥናቱ፤ በባህላዊ ሕክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች መግለጽ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደቶችን መጠቆም፤ የባህል ሕክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶችንና የባህል ሕክምና ምስጢራዊነትን ማሳወቅ፤ የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን አካቷል። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከአውራና ከንዑስ የባህል ሐኪሞች፣ ከዘመናዊ የሕክምና ባለሙያዎችና ከባህል መድኃኒት ተጠቃሚዎች ተመርጠዋል። የመስክ መረጃዎች በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በታላሚ ቡድናዊ ውይይት የተሰበሰቡ ሲሆን በገላጭና በተንታኝ የምርምር ስልት ተተንትነው ቀርበዋል።

በትንታኔው መሰረት በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በዋናነት በሽታን የመለያ ዘዴዎቻቸው እይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባዮሎጅካዊ እና የሕሙማንን ማኅበራዊ ሁኔታ በማጤን (በመጠየቅ) ምርመራ እንደሚያካሂዱና በሽታን እንደሚለዩ ጥናቱ አሳይቷል። የባህል ሐኪሞች ሃይማኖታዊ ተቋምን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው፣ ለሕሙማን ሥነ ልቡናዊ ድጋፍ ማድረጋቸው፣ በዝቅተኛ ወጭ አገልግሎት መስጠታቸው እና ሕሙማን በሕክምናው እንፈወሳለን የሚል ጽኑ እምነት ማሳደራቸው የሕክምና ዘርፉን ተመራጭ አድርጎታል። ይሁን እንጅ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ከበሽታ መለያ ዘዴያቸው፣ ከመድኃኒት ቅመማ፣ ምጣኔና አሰጣጥ ስልታቸው ጋር በተያያዘ በሕሙማን ላይ አልፎ አልፎ ጉዳት እንደሚያደርስ በጥናቱ ተጠቁሟል። ይህን የባህል ሕክምና ለማዘመን፤ በዘርፍ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የዘመናዊ ሕክምና አስተማማኝ አጋር እንዲሆን ለማድረግ፤ የባህላዊና የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ተቀራርበው ቢሰሩ መልካም መሆኑን በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል።

የተመስገን ጥናት፤ ርዕሰ ጉዳይ፣ ዐቢይ ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች፣ ክለሳ ድርሳን፣ ትንታኔ እና ማጠቃለያ ክፍል የተደራጁ ናቸው። ይህ ጥናት ከቀደሙ ጥናቶች የተለየ (ዓለማየሁ፣ 2000፤ ምህረት፣ 2000፤ መስፍን፣ 2002) የሚያደርገው፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን

[36]በዚህ ጥናት አቅራቢ በ2003 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት መሆኑን ልብ ይሏል።

የምርመራ ዘዴና አተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል ለመጠቆም መሞከሩ ነው። በጥናቱ ሂደት ንድፈ ሃሳባዊና ጽንሰ ሃሳባዊ ይዘቶችን በውል አለመለየት፤ የመተንተኛ ንድፈ ሃሳብ ወይም አንጻር አለመጠቆም፤ የመረጃ ሰጪዎች የናሙና አመራረጥ ስልት በምንና እንዴት እንደተመረጡ በግልጽ አለማቅረቡ፤ የጥናቱን ክፍተት አመላክቷል። ይህ ጥናት፤ የሰሜን ሸዋ የግሼ ራቤል (መንዝ) ወረዳ ማኅበረሰብን የባህል ሕክምና ልማድ ማቅረቡ፣ የበሽታ መለያ ዘዴዎችን መጠቆሙ፣ የዕፀ መድኃኒት መቀመሚያ ቁሶችን ትዕምርት ማቅረቡ፤ በዚህ ይዘት ከቀረቡ ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል።

ደነቁ (2003)፤ "የሃገረሰባዊ መድኃኒቶች አዘገጃጀትና አሰጣጥ በወላይታ ሶዶ ከተማና አካባቢዋ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። ይህ ጥናት በወላይታ ሶዶ ከተማና አካባቢዋ እየተካሄደ ያለውን የሃገረሰባዊ መድኃኒቶች አዘገጃጀትና አሰጣጥ ተግባራትን ፈትሿል። የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ በወላይታ ሶዶ ከተማና አካባቢዋ የሃገረሰባዊ መድኃኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ ሂደትን በመመርመር ሃገረሰባዊ ልማዱን መግለፅ እንደነበር ተጠቁሟል። የምርምሩ ማዕከላዊ ይዘት የሃገረሰባዊ መድኃኒቶች አዘገጃጀትና አሰጣጥ ሂደትና ተግባር ምን ይመስላል? በሃገረሰባዊ ሕክምና የሚፈወሱ በሽታዎች ምን ምን ናቸው? ማኅበረሰቡ ለሃገረሰባዊ ሐኪሞች ምን አይነት አመለካከት አለው? የሕክምና ጥበቡ መተላለፊያ መንገዶች ምን ምን ናቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከባህል ሐኪሞች፣ ከባህል መድኃኒት ተጠቃሚዎች፣ ከዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች እና ከአካባቢ ሽማግሌዎች በምልከታና በቃለመጠይቅ ተሰብስበዋል። ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በምድብ በምድብ ተደራጅተው ዓይነታዊ ምርምር ዘዴን መሰረት በማድረግ በገላጭና በይዘት ትንተና ምርምር ስልት እንደቀረቡ፤ ተገልጿል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ከሆነ የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት የሚውሉ ግብዓቶችን ከተራራ፣ ከወንዝ፣ ከደንና ከእርሻ ቦታዎች እንደሚሰበስቡ፤ የሃገረሰባዊ መድኃኒት አዘገጃጀት፣ ቅመማና አሰጣጡም ሃገረሰባዊ እምነትን (የአባትና የአያት መንፈስን መለመን፣ መጥራት) መሰረት ያደረገ መሆኑን፤ የባህል ሕክምና ጥበቡም ከአባት ወደ ልጅ በሥጦታ፤ በዉለታ፣ በረጅም ግዜ አገልግሎት፣ በመለዋወጥ ዕውቀቱ እንደሚተላለፍ፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ ለባሕል ሕክምና ባለሙያዎች አዎንታዊ አመለካከት እንዳለው፤ በጥናታቸው ገልጸዋል። በመጨረሻም የዞኑ ጤና መምሪያ በወላይታ ሶዶ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን

በማሰባሰብና በማደራጀት ስለመድኃኒት ምጣኔ፣ አሰጣጥ፣ ልኬት ሥርዓት ስልጠና መስጠት እንዳለበት የመፍትሔ ሃሳብ በመጠቀም ጥናቱን አጠናቀዋል።

ጥናቱ የወላይታን ማኅበረሰብ ሃገረሰባዊ መድኃኒት አዘገጃጀትና ቅመማ ልማድን ማቅረቡ፤ የጥናቱን ዓላማን በግልፅ ማስቀመጡ፤ የመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተደረገው ጥረትና የመስክ ተመክሮ፤ በጠንካራ ጎን ይጠቀሳሉ። የጥናቱ ክፍተት፤ የጥናት መዋቅርና ቅደም ተከተል መዛነፍ፤ የዋቢ ምንጭ አጠቃቀስ ችግር፤ የመስክ መረጃ ትንታኔ ውስንነት፤ የቋንቋና የሰዋስው አጠቃቀምና የአጻጻፍ (የአንቀፅ፣ የዓረፍተ ነገር) ግድፈት፤ በጥናቱ ይዘት ጎልተው ታይተዋል። ይህ ጥናት፤ የወላይታ ሶዶ ከተማና አካባቢዋን የባህል ሕክምና ልማድ ማቅረቡ  ከቀደምት ጥናቶች (ዓለማየሁ፣ 2000፤ ምህረት፣ 2000፤ መስፍን፣ 2002) ይዘት የተለየ ያደርገዋል።

ፍቅርተ (2009)፤ "ከዕፅዋት የሚገኙ ሃገረሰባዊ መድኃኒቶች እውቀት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ በከምባታ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የከንባታ ብሔረሰብን፤ ሃገረሰባዊ የመድኃኒት ዕውቀት አዘገጃጀትና አሰጣጥ መመርመር እና ባህላዊ ልማዱን ገልጾ ማሳየት ነበር። በጥናቱ ሂደትም፤ በከንባታ ብሔረሰብ የሚገኙ ሃገረሰባዊ ሐኪሞች የሕክምና ዕውቀትን ከየትና እንዴት እንዳገኙት መግለፅ፤ የሃገረሰባዊ መድኃኒት ምስጢራዊነትን መለየት፤ ለሃገረሰባዊ መድኃኒት መቀመሚያ የሚያገለግሉ ግብዓቶች ከምን ከምን እንደሚያገኙ ማሳየት፤ የሃገረሰባዊ ዕፅዋት መድኃኒት አዘገጃጀትና አሰጣጡን መግለፅ፤  ሃገረሰባዊ መድኃኒቶች የሚቀመሙበትና የሚሰጡበትን ቀንና ሠዓት ትዕምርታዊነት መግለፅ፤ በአካባቢው ሃገረሰባዊ መድኃኒቶች የሚፈውሷቸውን በሽታዎች መለየት፤ የሚሉ ይዘቶችን ትኩረት አድርጓል። የጥናቱ መረጃዎች፤ ከቁልፍ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች፣ ከዘመናዊ ሐኪሞች፣ ከአገር ሽማግሌዎች እና ከሃገረሰባዊ መድኃኒት ተጠቃሚዎች፤ በቃለመጠይቅ እና በምልከታ ስልት ተሰብስበዋል። እነዚህ መረጃዎች በሚዲካል ኢኮሎጂ እና በተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ተቃኝተው፤ በገላጭና በተንታኝ ምርምር ስልት  ተተንትነው ቀርበዋል።

በጥናቱ ትንታኔ ይዘት፤ በከምባታ ብሔረሰብ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የሕክምና ዕውቀቱን ከቤተሰብ (ከአያትና አባት) እና ከመለኮታዊ ኃይል እንደሚያገኙት፤ የውርስ ሂደቱም ከአያትና ከአባት ወደ ወንድ ልጅ የሚተላለፍ ሲሆን፤ የሕክምና ዕውቀቱን ለመጠበቅ ሲባል ለሴት ልጅ እንደማያወርሱ (በትዳር የሌላ ቤተሰብ አባል መሆኗን ታሳቢ ያደርጋል)፤ የሃገረሰባዊ መድኃኒት ምስጢራዊነት ከባለቤትነት መብት (የገቢ ምንጭ)፣ "ይረክሳል" ተብሎ መታሰቡና ዕፅዋት

በማንኛውም ሰው እንዳይቆረጡ ፋይዳ አለው ተብሎ መታሰቡ፤ ለሃገረሰባዊ መድኃኒት መቀመሚያ የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ከአካባቢያቸው፣ ከወንዝ፣ ከተራራማ ቦታዎች እንደሚሰበስቡ፤ የዕፅዋት መድኃኒት መሰብሰቢያ፣ መቀመሚያና መስጫ ቀናት ረቡዕ፣ ዐርብና እሁድ (በብሔረሰቡ አባላት ቅዱስ ቀናት ተደርገው እንደሚታሰቡ) እንደሆኑ፤ በጥናታቸው አረጋግጠዋል። የሃገረሰባዊ የዕፅዋት መድኃኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ፤ የዕፅዋትን ቅጠል፣ ሥር፣ ቅርፊት፣ ግንድ፣ ቀንበጥ፣ አበባና ፍሬዎችን ሰብስበው፤ ወቅጠው፣ ቀቅለውና በዱቄት መልክ አዘጋጅተው በሚጠጣ፣ በሚቀባ፣ በሚታሸና በሚታሰር እንደሚሰጡ፤ የመድኃኒት መስጫ ቁሶችም ኩባያ፣ የሻይ ብርጭቆ፣ የእጅ መዳፍና ማንኪያ እንደሆኑ ጥናቱ ገልፀዋል። በመጨረሻም፤ በሃገረሰባዊና በዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች መካከል ያለውን የሃሳብ ልዩነትና አመለካከት ለማጥበብ፤ የዞኑ ጤና መምሪያ ቢሮ (የከባታ) ሁለቱ አካላት ተቀራርበው የሚወያዩበትን መድረክ ቢያመቻች ችግሩ እንደሚቀረፍ በመጠቆም ጥናታቸውን አጠናቀዋል።

ጥናቱ፤ የከምባታ ብሔረሰብን ሃገረሰባዊ የዕፅዋት መድኃኒት ዕውቀት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ ልማድን ማቅረቡ፤ የጥናቱን ዓላማ በግልፅ ማስቀመጡ፤ ፅንሰ ሃሳብና ንድፈ ሃሳብን መለየቱ እና ተነባቢ መሆኑ፤ በጠንካራ ጎን ይጠቀሳሉ። የጥናቱ ክፍተት፤ በትንታኔ ክፍል፤ በዓላማ፣ በፅንሰ ሃሳብና በንድፈ ሃሳብ ያልተካተቱ ርዕሰ ጉዳዮችን ማንሳቱ (የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎችና የአካባቢው ማኅበረሰብ ለሃገረሰባዊ ሐኪሞች ምን ዓይነት አመለካከት እንዳላቸው መግለጽ)፣ የጥናት ወሰንን አለመለየት፣ የጥናት አደረጃጀትና የዋቢ ምንጭ አጠቃቀስ ችግር፤ በጥናቱ ይዘት ጎልተው ታይተዋል። ይህ ጥናት፤ የከምባታ ብሔረሰብን ሃገረሰባዊ የዕፅዋት መድኃኒት ዕውቀት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ ልማድን ማቅረቡ ከቀደምት ጥናቶች (ዓለማየሁ፣ 2000፤ ምህረት፣ 2000፤ መስፍን፣ 2002፤ ተመስገን፣ 2003፤ ደነቀ፣ 2003) ይዘት የተለየ ያደርገዋል።

ዐቢዩ (2010)፤ "የቦሮ ሽናሻ ብሔረሰብ ሃገረሰባዊ መድኃኒት ምንጩ፣ ተስተላልፎውና ገቢሩ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የቦሮ ሽናሻ ብሔረሰብን ሃገረሰባዊ መድኃኒት ምንጭ፣ ተስተላልፍና ገቢር ገልጾና ተንትኖ ማሳየት ነበር። የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎችም፤ የቦሮ ሽናሻ ማኅበረሰብ "ሥለጤና እና የጤና እክሎች" ያለውን ሃገረሰባዊ አረዳድ መግለፅ፤ ሃገረሰባዊ ዕውቀቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት እንደሚተላለፍ ማስረዳት፤ በሃገረሰባዊ መድኃኒት ዕውቀትና ገቢር ቀጣይነትና ተከታታይነት ላይ አዎንታዊና አሉታዊ (አስጊ) ሁነቶችን መጠቆም፤ ሃገረሰባዊ እና ዘመናዊ ሕክምና ሊቀናጁ የሚችሉ መሆን/

አለመሆናቸውን ማስረዳት እንደነበር፤ ጥናቱ ይገልጻል። እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ከሃገረሰባዊ ፈዋሾች፣ ከታካሚዎች፣ ከሃገረሰባዊ ሽማግሌዎች፣ ከወጣቶችና ከዘመናዊ የሕክምና ባለሙያዎች፤ በቃለመጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይት፣ በተሳትፏዊ ምልከታ፣ በንጥል ጥናት እና በሰነድ ምርመራ የመስክ መረጃዎችን ሰብስበዋል። ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች በምድብ በምድብ ተደራጅተው ዓይነታዊ ምርምር ዘዴን መሰረት በማድረግ "ተንታኝ ዕይታ" (Interpretive Approach)፣ "ሃያሽ ወተንታኝ ትውር" (Critical Interpretive Theory)፣ "ሃያሽ የሥነ ሰብዕ ወሕክምና ትውር" (Critical Medical Anthropology) እና "አካባቢ ተኮር ትውር"ን (Epidemological Approach) አቀናጅቶ በመጠቀም "በመረጃ መር ንድፈ ሃሳብ" (Grounded Theory) እና "ወደ ምንጩ መልሶ የማስመስከር አካሄድ" (Reflexive Approach) ስልትን በመጠቀም እንደተተነተነ፤ ጥናቱ ያስረዳል።

በትንታኔው መሰረት የቦሮ ሽናሻ ብሔረሰብ ለጤና እና ለጤና እክሎች ያለው አረዳድ "በማኅበራዊ መስተጋብሮች መስመርና አለመስመር፣… የመቻልና አለመቻል፣ የመደነቃቀፍና አለመደነቃቀፍ፣ … የአካባቢያዊም ሆነ ህሊናዊ ቁስለት መኖርና አለመኖር" ምክንያት እንደሆኑ፤ የጤና እክሎችን ለመፈወስ የዕፅዋት፣ የእንስሳት እና የማዕድናት ግብዓቶችን እንደሚጠቀሙ፤ ጥናቱ ያስረዳል። በጥናቱ ሂደት የሃገረሰባዊ ሕክምና ጥበቡ የሚመራዉና የሚተገበረው ታላቅ ማኅበራዊ ደረጃ ባላቸው ሶስት የሽናሻ ዘሮች (ፀሰኒሃዎች) እንደሁነ፤ ዕውቀቱም ከፈጣሪ (በሕልም ወይም በሆነ ኀይል እንደሚሰጥ)፣ ከጠቢቡ ሰሎሞን ጥበብ፣ ከቀደምት አባትና አያቶች ሙያና ተግባር እንደተገኘ፤ የሃገረሰባዊ መድኃኒት ገቢሮቹም፤ በመታጠን፣ በመቀባት፣ በመጠጣት፣ ሥርዓተ ከበራ በማካሄድ (ዕፅን ይዞ ወደ ላይ በመነሳት፣ ወደ ዉኃ በመጣል፤…) የሚተገበር ሙያ እንደሆነ፤ የሕክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዱም፤ በዘር እና/ወይም በጎሳ (ለዚህ ተግባር የተመረጡ የማኅበረሰቡ አባል ጎሳዎች)፣ በጾታ (ለወንድ ልጅ ብቻ)፣ በውለታ፣ የሙያው ባለቤቶች ዕርስ በርስ በሚያደርጉት ልውውጥ የሕክምና ዕውቀቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደሚተላለፍ፤ ጥናቱ ጠቁሟል።

ለሕክምና ዕውቀቱ ቀጣይነት ሃገረሰባዊ ተረኮች ጉልህ ሚና እንዳላቸው የተገለጸ ሲሆን የዘመናዊ ትምህርት እና ሕክምና መስፋፋት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሃገረሰባዊ ሕክምና ዕውቀት ቀጣይነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፤ የማኅበረሰቡን ዕውቀት፣ ልማድና ተግባር የሚወርሱ ተተኪ ወጣቶችን ማጣት የሃገረሰባዊ ሕክምና ተስተላልፎ ተግዳሮት ውስጥ እንዳለ፤ ጥናቱ አስረድቷል። በጥናቱ ሂደት፤ ሃገረሰባዊ እና ዘመናዊ የሕክምና መስኮች ሊዋሃዱ፣ ሊቀላቀሉ እና

ሊገናኙ የማይችሉ "የዱባና ቅል" ባሕርይ እንዳላቸው፤ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ የቦሮ ሽናሻ ሃገረሰባዊ መድኃኒት ገቢሮች የሚመሩባቸው መርሆዎች "ሣይንሳዊ የመግነጢስ ትውርን" የሚሞግቱ፤ የ"Frazern"ን "የአስማት ትውሮች" እና የ"Pavlov"ን "የአነሳሽ ወዳው መላሽ ትውርን" እንደሚደግፉ፤ ጥናቱ ይገልጻል፡፡ በመጨረሻም ሃገረሰባዊ መድኃኒት፤ የዕውቀት፣ የፍልስፍና፣ የትውሮች መፍለቂያ መሆኑን እና "የአገሪቱን የጤና ሽፋን ስለሚመለከት ለሙያው ባለቤቶች ዕውቅና ቢሰጥ"፣ ዕውቀቱም የሚሰበሰብበትና የሚጠናበት ቦታ ቢከለል መልካም መሆኑን፤ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

የጥናቱ ጠንካራ ጎን፤ የጥናቱን ዝርዝር ዓላማዎች ተግባራዊ ማድረጉ፤ የተለያዩ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ስልትና ቴክኒኮችን መጠቀሙ፤ ከቀደምት ጥናቶች ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በግልፅ ማስረዳቱ፤ የቋንቋ አጠቃቀም ግልፅና ወጥነት ያለው መሆኑ፤ የመስክ መረጃዎችን ከማኅበረሰቡ አተያይና ክፍፍል አንጻር መተንተኑ፤ የተለያዩ የመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሃሳቦችን አገናኝቶ የመስክ መረጃዎችን ለመተንተን መሞከሩ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ያመላክታል፡፡

በአንጻሩ በጥናቱ ሂደትና አጠቃላይ አደረጃጀት መልካም ቢሆንም ሁለት አስተያየቶችን ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡ አስረጅ አንድ፡- "በዘመናዊ ሕክምና ስልት ስም ያልተሰጣቸውን (አስማታዊ) የማኅበረሰቡን ጤና የሚያውኩ የሕመም ዓይነቶችን ለይቶ ማጥናቱ፤... በቀደምት ጥናቶች ያልተዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዮችን ማንሳቱ" ከቀደምት ጥናቶች በእጅጉ እንደሚለይ (ዐቢዩ፣ 2010፣ ገፅ.46-48) ይጠቁማል፡፡ በጥናቱ ትንታኔ ይዘት በዘመናዊ ሕክምና የሚታወቁ መደበኛ ስም ያላቸው የበሽታ ዓይነቶች (ስንፈተ ወሲብ፣ ነቀርሳና የዕባብ መድኃኒት) የጥናቱ አካል በመሆን ተተንትነው (ዐቢዩ፣ 2010፣ ገፅ.166-189) ቀርበዋል፤ በዓለማዊና በመንፈሳዊ (ለመስተፋቅር፣ ለሐብት...) የባህል ሕክምና ዘውግ ስር የሚጠቀሱ ርዕሰ ጉዳዮችን በአንድነት የጥናት አካል አድርጓል፡፡ ሁለቱ ሃሳቦች እንዴት ይታረቃሉ? ሲባል ምላሽ ለመስጠት የሚያዳግት ይመስላል፡፡ ይህ ጥናት፤ የቦሮ ሽናሻ ማኅበረሰብ የባህል ሕክምና ልማድን ማቅረቡ፣ ለጤና እና ስለጤና ያላቸውን አመለካከት መቃኘቱ፣ በዘመናዊ ሕክምና የማይታወቁ የሕመም ዓይነቶችን በመለየት "አስማታዊ" ድርጊትና ገቢሮችን መተንተኑ፣ ሃገረሰባዊና ዘመናዊ ሕክምና የሚቀናጁ መሆን/ አለመሆናቸውን መፈተሹ፤ ከቀደምት ጥናቶች (በዚህ ይዘት ከቀረቡ) በእጅጉ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ማኅሌት (2011)፤ "ሃገረሰባዊ ሕክምና፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ

የሃገረሰባዊ መድኃኒት ሕክምና አተገባበርን ማሳየትና መግለፅ ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹም የአካባቢውን ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች መለየት፤ ለሕክምና የሚውሉ ግብዓቶችን መለየት፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደቶችን መግለጽ፤ የሙያ ለመዳና የሕክምና ጥበቡ መተላለፊያ መንገዶችን መጠቆም፤ የሕክምና አዋቂዎችን ማኅበራዊ ደረጃ... የሚሉ ናቸው፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የመስክ መረጃዎች በምልከታና በቃለመጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በምድብ በምድብ ተደራጅተው ዓይነታዊ ምርምር ዘዴን መሰረት በማድረግ በገላጭ ስልት፤ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

የዚህ ጥናት ማዕከላዊ ይዘት በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ የሚገኙ ዋና ዋና በሽታዎችን "የቆላ ቁስል፣ ችፌ፣ ቂጥኝ፣ የካንሰር በሽታ፣ ኪንታሮት፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ የአጥንት ስብራት..." በመለየት የሕክምና ሥርዓትና ተግባሩን ለማጥናት ተሞክሯል፡፡ ለመድኃኒት ግብዓት የሚያገለግሉ ዕፅዋት፣ እንስሳት እና ማዕድናት እንደሆኑ ተጠቁሟል፡፡ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደቱም በመፍጨት፣ በማድቀቅ፣ በመሰለቅ በመገርደፍ ወዘተ የሚተገበር ሲሆን አሰጣጡም በዱቄት፣ በፈሳሽ፣ በእርጥብ፣ በደረቅ እና መሰል ይዘት ተሰርቶ ይሰጣል፡፡ የሕክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዱ "ከፈጣሪ በሚገለፅ ገፀ በረከት፣ ከዕናትና አባት በመውረስ፣ ከባሕል ሐኪሞች በመማር፣ በዝምድና፣ በገንዘብ በመግዛት" እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ማኅበራዊ ደረጃቸው፤ አዎንታዊና ማኅበራዊ ተቀባይነት ያላቸው ቢሆንም የኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በመጨረሻም የባህል ሕክምና ዕውቀት በባህል ሐኪሞች ተግባርና አመለካከት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ "ባህላዊ ይዘቱን፣ ጥንታዊ ልማዱን፣ ይዘውና ጠብቀው እንዲቆዩ ቢበረታቱ" መልካም መሆኑን በማስረዳት ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

የዚህ ጥናት ጠንካራ ጎን የአርባ ምንጭ ማኅበረሰብን የሃገረሰባዊ ሕክምና ዕውቀት፣ ሥርዓትና ተግባርን ማስተዋወቁ፤ በአካባቢው በዋናነት የሚከሰቱ በሽታዎችን መለየቱ፣ የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን ማኅበራዊ ሁነት መዳሰሱ ይጠቀሳሉ፡፡ የጥናቱ ክፍተት፤ ከዚህ በፊት የቀረቡ ጥናቶችን (ምህረት፣ 2000፤ መስፍን፣ 2002፤ ተመስገን፣ 2003) ዓላማና ይዘት እንዳለ መቅዳትና መገልበጥ (ለዓብነት ያህል፤ ከምህረት የቅመማ ሂደትና ተግባርን፤ ከመስፍን ፅንሰሃሳብና የመስክ ግብዓትን፤ ከተመስገን የምርመራ ዓይነቶችን ልብ ይልዋል) ይታያል፡፡ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የሰዋስው ግድፈት፣ የአንቀፅ አደረጃጀት ክፍተት ጎልቶ ይታያል፡፡ የጥናቱ ትንታኔና ይዘት የአካባቢውን ማኅበረሰብ (ጋሞን) ቋንቋ፣ ዘዬ፣ ልማድ፣ ሥርዓት፣ ገቢር፣ በጋሞ ቋንቋ የበሽታ እና የዕፅዋት ስምን በሥርዓት አያመላክትም፤ (ማለትም የጥናቱ ርዕስ በሌላ ቦታና

ማኅበረሰብ ቢቀየር፤ የተጠቀሰውን ማኅበረሰብ ዐውድ ይመስላል)። በአጠቃላይ፤ የጋሞ ማኅበረሰብን የባህል ሕክምና ሥርዓትና ልማድ ማጥናቱ በዚህ ይዘት ከቀረቡ ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል።

Young (1970)፤ "Medical Beliefs and Practices of Begamder Amhara" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። የጥናታቸው ማዕከላዊ ጉዳይ የአማራን ማኅበረሰብ (በተለይ የጎንደርን /በድሮው በጌምድር) የባህል ሕክምና እምነት፣ አምልኮና ተግባርን ማስረዳት፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን ዕውቀትና ተግባር በማጤን በምድብ መለየት፣ የሕክምና ጥበቡ መተላለፊያ መንገዶችን መግለፅ፤ ማኅበረሰቡ "ተፈጥሯዊ" እና "መለኮታዊ" ለሚላቸው በሽታዎች የመከላከያ ስልቶችን መርምረዋል።

በጥናታቸው ሂደት የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን ተግባር፣ ልማድ፣ ሙያና ዕውቀት በማጤን በሃያ አንድ (21) ዓይነትና ይዘት መድበዋል። እነዚህ ዝርዝር ምድቦች በሁለት (ዓለማዊና መንፈሳዊ በማለት) ጥቅል ይዘትና ምድብ እንደሚካተቱ አስረድተዋል። በዓለማዊ ዘርፍ የዕፀ መድኃኒት አዋቂዎች፣ ወጌሻዎች፣ የልምድ አዋላጆች ይጠቀሳሉ፤ በመንፈሳዊ ይዘት ደግሞ ደብተራዎች፣ ሼኮች፣ አጥማቂዎች፣ መሪጌታዎች ተካተዋል።

Young የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን እንደዕውቀት ምንጫቸው በሁለት ከፍለው ማየታቸው ተገቢ ቢሆንም በጥናታቸው ምድብ መደበላለቅ ይታያል። የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች መታየትና መቃኘት ያለባቸው፤ ከተግባራቸው፣ ከዕውቀት ምንጫቸው እና ማኅበረሰቡ ከሚሰጣቸው ስያሜ አንጻር እንጂ የዕውቀት መነሻ ምንጫቸውን ብቻ መሰረት በማድረግ መመደቡ ተገቢ (መሪጌታ/ደብተራ በጥቅሉ በመለኮታዊ/አስማታዊ ኃይል ሥር መካተቱ ምደባውን ያፈርሳል፤ ቢያንስ ቅይጥ ዕውቀት እንዳላቸው ሊጠቆም ይገባል) አይመስልም። የጥናታቸው አድማስና ትኩረት ማኅበረሰቡ ጤናውን ለመጠበቅ፣ በሽታን ለመከላከል እና ከሕመም ለመፈወስ የሚፈፅሙ እምነታዊና አምልኳዊ ሥርዓቶችን (ዛር፣ "ጥንቆላ"፣ ክታብ) እና አስማታዊ ተግባራትን ዳሰዋል።

Young በጥናታቸው ግኝት፤ በመለኮታዊ ኃይል እየታገዙና እየተመሩ ሕሙማንን የሚፈውሱ "ባለዛሮች፣ ቃልቻዎች፣ ጠንቋዮች" እንዳሉ ገልጸዋል። የቤጌምድር ማኅበረሰብ ከዘመናዊ ሕክምና ይልቅ፤ ለሕሙማን ፈውስ የሚፈልገው ከባህል ሕክምና ባለሙያዎች፣ አምልኳዊ ሥርዓትና ተግባራት ከሚፈጸምባቸው ቦታዎች እንደሆነ አስረድተዋል። የበሽታን ውስጣዊና ውጫዊ

ገፅታዎችን በመለየት ከማኅበረሰቡ ልማድ አንጻር ተንትነው ማቅረባቸው፤ የማኅበረሰቡን የባህል ሕክምና ዓይነትና ምድብ ማቅረባቸው፣ የሥነ ሰብ ጥናት ንድፈ ሃሳብን ማካተታቸው፤ ለባህል ሕክምና ዘርፍ ጥናት እንደግብዓት የሚታይ ሥራ መሆኑን መገንዘብ፤ ተችሏል፡፡

Mirgissa (1993) "Indigenous Medical Beliefs and Practices among the Oromo of Illubabor" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው ትኩረት በኢሉባቦር የሚካሄደውን የባህል ሕክምና ሥርዓት ከማኅበረሰቡ እምነትና ተግባራት አንፃር መመርመርና መፈተሽ ነበር፡፡ የMirgissa ጥናት ማዕከላዊ ትኩረት፤ ባህላዊ ሕክምና የማኅበረሰቡን እምነት እና አመለካከት መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከማኅበረሰቡ አምልኮና ተግባራዊ ዐውድ አንጻር መታየት እንዳለበት ይገልጻሉ፡፡ የባህል ሕክምና ዘርፉ መንፈሳዊና ዓለማዊ  ተግባራትን እንደሚያካትት አብራርተዋል፡፡  በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በመንፈሳዊ ኃይል በመታገዝ ሕመምተኛን ለመፈወስ ጥረት የሚያደርጉ፤ በሂደትም  የጫት መቃም እና የፀሎት ሥነ ሥርዓት እንደሚያካሂዱ ያስረዳሉ፡፡ በሽታን ለማስወገድ፣ ሕመምተኛን ለመፈወስ፤ ልመና፣ ጸሎትና ዱዓ (Duai) ዐበይት ተግባራት ሲሆኑ ዓለማዊ የባህል ሐኪሞች ደግሞ በአካባቢው የሚገኙ ዕፅዋትን፣ እንስሳትንና ማዕድናትን እንደግብዓት በመጠቀም መድኃኒት አዘጋጅተው እንደሚሰጡ ያስረዳሉ፡፡ በጥናታቸው ማጠቃለያ የተለያዩ በሽታዎች ለመፈወስ ከዘመናዊ ሕክምና ይልቅ ባህላዊ ሕክምና ተመራጭ እንደሆነ፤ በጥናታቸው ጠቁመዋል፡፡ የMirgissa ጥናት በኢሉባቦር አካባቢ የሚካሄደውን የባህል ሕክምና ሥርዓት ከሼኮች እና ዱዓ ከሚያደርጉ የሙስሊም ሃይማኖት ተከታዮች እንጻር መጠናቱ፣ የአካባቢውን ልማድ፣ እምነትና የአምልኮ ሥርዓት ማካተቱ ጥናቱን ልዩ ያደርገዋል፡፡

Zerihun (2001)፤ "Culture, Belief and Mental Illness Among the Zay" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው ትኩረት የዛይ ማኅበረሰብ ለአዕምሮ ሕመምተኞች ያለውን አመለካከት፣ ክትትልና ቁጥጥር መጠቀም፤ ለአዕምሮ ሕመም ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች መለኮታዊ (እርግማን፣ አጋንንት) የሆኑ የማኅበረሰብ አመለካከት፤  ማኅበረባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መንስኤዎችን መግለጽ ነበር፡፡

በጥናታቸው ማዕከላዊ ይዘት ለአዕምሮ ሕመምተኛ የሚሰጠው ሕክምና እና እገዛ በባህላዊ እና በዘመናዊ ሐኪሞች መካከል የተለያዩ ይዘት፣ ተግባርና እሳቤ እንዳለው አስረድተዋል፡፡ የባህል ሐኪሞች በጸበል፣ በጸሎት እና በመለኮታዊ ኃይል (አጋንንት/ እርኩስ መናፍትን በማስወጣትና በማባረር) በመታገዝ ሕመምተኞችን እንደሚፈውሱ፤ የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ደግሞ

ከዘመናዊ ሕክምና ውጪ የሚደረጉ ሕክምናዎችን እንደማይደግፉ፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች "በአዕምሮ ሕሙማን ላይ የባሰ ጉዳት እንደሚያደርሱ" የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎችን ዋቢ በማድረግ ጠቁመዋል፡፡ Zerihun የአዕምሮ ሕመም ከመንፈስ ጭንቀት፣ ከማኅበረ-ባህላዊ ተግባራት፣ ከኢኮኖሚ ቀውስ እና ከፖለቲካ አንጻር የሚከሰት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ለአዕምሮ ሕመምተኞች የሚደረገው እንክብካቤና ከማኅበረሰቡ ያለው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመው፤ በጥናታቸው ማጠቃለያ የስነልቡና አማካሪዎችንና የባህል ሐኪሞችን በማቀናጀት የሕክምና አገልግሎቱ፣ የጤና አጠባበቅ ሥርዓቱ እንዲሻሻል፤ በሁለቱ መካከል የልምድ ልውውጥ ቢደረግ ለአዕምሮ ሕመምተኞች ተገቢውን ሕክምና እና እንክብካቤ ለመስጠት አመቺ መሆኑን በመጠቆም፤ ጥናታቸውን አጠቃለዋል፡፡ Zerihun የአዕምሮ ሕመምተኞችን ነጥለው ማጥናታቸው በዚህ ይዘት ከተጠቀሱ ቀደምት ጥናቶች የተለዩ ያደርጋቸዋል፡፡

Mekonen (2010)፤ “Indigenous Medicine, Beliefs and Practices Among the Kunama in Sheraro, Tigray” በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው ማዕከላዊ ይዘት በአገር በቀል ሕክምና የሚተገበሩ እምነታዊና አምልኳይ ሥርዓትና ተግባራትን መርምረዋል፡፡ ማኅበረሰቡ እና ባህላዊ ሐኪሞች ለበሽታ መንስኤዎች ያላቸውን አመለካከት፣ የባህል ሐኪሞች የሕክምና ዕውቀቱን ከምን እንዳገኙት፣ ማኅበረሰቡ ለባህላዊና ለዘመናዊ ሕክምና ያለውን አመለካከት ቃኝተዋል፡፡ በኩናማ ማኅበረሰብ የበሽታ መንስኤ በተፈጥሯዊና በመለኮታዊ ኃይል እንደሚመጣ ይታመናል፡፡ ከተፈጥሯዊ ኃይል፤ በድንገተኛ አደጋ የሚደርሱ ጉዳቶችን፣ ከሰውነት ቁስል ጋር የተያያዙ በሽታዎችን ጠቁመዋል፡፡ በመለኮታዊ ኃይል የሚሏቸው ከቅድመ አያቶቻቸው በሚላክ መንፈስ፣ ቡዳ፣ አጋንንት፣ ዛር እና በመሳሰሉት ቁጣ የሚመጡ በሽታዎች መሆናቸውን፤ በጥናታቸው አብራርተዋል፡፡ Mekonene አዲስና የተለየ የጥናት አቅጣጫ ባይኖራቸውም የኩናማን ማኅበረሰብ የባህል ሕክምና አምልኮና ተግባር ማጥናታቸው በዚህ ይዘት ከቀረቡ ጥናቶች ልዩ ያደርጋቸዋል፡፡

Tebaber (2015)፤ “Indigenous Medical Knowledge and Practices: Cultural and Environmental Values of Medicinal Plants Used by the Konso People of South Western Ethiopia.” በሚል ርዕስ ምርምር አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው መሰረታዊ ይዘት የሃገረሰባዊ ሕክምና ዕውቀትና ተግባር፤ ዕፀ መድኃኒት የኮንሶን ሕዝብ ባህል እና አካባቢያዊ እሴት ከመጠበቅ አንጻር የአላቸውን ጥቅም መርምረዋል፡፡ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎችም የኮንሶ ሃገረሰባዊ መድኃኒት እምነትና ተግባር መቃኘት፤ ለሃገረሰባዊና ለዘመናዊ ሕክምና የአላቸውን አመለካከት ማነጻጸር፤ ሃገረሰባዊ መድኃኒት ለመጠቀም እና ጤናን ለመጠበቅ ተግዳሮት የሆኑ ጉዳዮችን መለየት፤ በጥቅሉ የዕፀ

መድኃኒት ጥቅም ለማኅበረ-ባህላዊ እሴት፤ በንዑስ "የሞሪንጋ"ን አገልግሎት ማጥናት፤ ዕፀ መድኃኒት ለአካባቢያዊ ጥበቃ ያላቸውን እሴት መወያየት እና የሃገረሰባዊ ሕክምና ተግዳሮትን መለየት የሚሉ ናቸው። ጥናቱ ዓይነታዊና መጠናዊ የምርምር ይዘቶችን በመተግበር የመስክ መረጃዎች በጭብጥ ይዘት እና በ"SPSS" ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል።

በጥናታቸው ማዕከላዊ ትኩረትና ግኝት የኮንሶ ሕዝብ ለጤና እና ለጤና ነክ ርዕሰ ጉዳዮች የአላቸው አተያይ፤ በየዕለቱ ከሚሰሩት ሥራ፣ ከሚያመልኩት ኃይል (ከጣኦትና ከፈጣሪ ከሚመጣ ቅጣት)፣ ከሚኖሩት ሕይወት ጋር የተዛመደ ሲሆን የተማሩና በከተማ የሚኖሩ አባላት የጤና እክል (ሕመም) "በጀርም እና በባክቴሪያ" እንደሚከሰት እምነት እንዳላቸው ጠቁመዋል። የኮንሶ ሕዝብ የጤና እክል ሲያጋጥማቸው የባህል እና የዘመናዊ ሕክምናን በጥምረት ወይም በተናጠል የመጠቀም ልማድ የአላቸው ቢሆንም በተደረገ የዳሰሣ ጥናት ሃምሣ ዘጠኝ ፐርሰንት (59%) የሚሆኑት የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫቸው የሃገረሰባዊ ሕክምና መሆኑን አስረድተዋል። ለዚህም ዐበይት ምክንያቱ፤ የባህል መድኃኒት ባህላዊ ተቀባይነት ያለው መሆኑ፤ በዝቅተኛ ዋጋና በውለታ መገኘቱ የሕክምና ዘርፉን ተመራጭ እንዳደረገው ገልጸዋል። ዕፀ መድኃኒት ለኮንሶ ሕዝብ የሃገረሰባዊ መድኃኒት ምንጭ (በተለይ ሞሪንጋ)፣ ባህላዊ፣ አካባቢያዊ፣ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ መሰረትና እሴት እንዳላቸው ገልፀዋል።

ለኮንሶ ሃገረሰባዊ ሕክምና ልማድ መዳከም እና ተከታይ አልባ እየሆነ ለመምጣቱ እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል፤ የደን ምንጠራ፣ የዐየር ንብረት ለውጥ፣ የመሬት መሸርሸር እና የግጦሽ መሬት መራቆት ተደማምረው ለሃገረሰባዊ ሕክምና ሥጋት እና ለዕፀ መድኃኒት መጥፋት ምክንያት መሆናቸውን፤ በጥናታቸው አሳስበዋል። ይህን ችግር ለመፍታት ዕፅዋትን በአሉበት ቦታ መንከባከብ፣ ዕፀ መድኃኒትን መርጦ በተወሰነ ቦታ ማልማት እና በዘርፉ ቀጣይ ምርምሮችን በማካሄድ ችግሩን መፍታት እንደሚቻል ጠቁመው፤ ጥናታቸውን አጠናቀዋል። Tebaber የኮንሶ ሕዝብ ሃገረሰባዊ ሕክምና ልማድን፣ ዕፀ መድኃኒት ለባህል እሴት እና ለአካባቢ ጥበቃ ያላቸውን አስዋፅኦ ማጥናታቸው፤ በዚህ ይዘት ከተዳሰሱ ጥናቶች ልዩ ያደርጋቸዋል። በቀጣይ ይዘት፤ የባህል ሕክምና እና የዘመናዊ ሕክምና ጥምረት፣ የማኅበረሰብ አመለካከትን መነሻ ያደረጉ ጥናቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 2.3.2 የባህልና የዘመናዊ ሕክምና ጥምረት፤ የማኅበረሰብ አመለካከትን መነሻ ያደረጉ ጥናቶች

Abraraw (1998)፤ "Traditional Medicine in an Urban Center: Beliefs and Practices (The Case of Dessie Town, Northern Ethiopia)" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። የጥናቱ ዓላማ በደሴ ከተማ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ለጤና ያላቸው እሳቤ፣ እምነትና አተገባበር፣ ለባህላዊ ሕክምና ባለሙያዎች ያላቸው አመለካከት፣ የባህል ሐኪሞች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና፣ ባህላዊ ሕክምና ለዘመናዊ ሕክምና ያለውን አጋዥነትና አስተዋፅኦ መርምረዋል። በጥናቱ ሂደት፤ የደሴ ከተማ ማኅበረሰብ የጤና እክል ሲገጥማቸው ሁለቱንም የባህል ሕክምና ዓይነቶች በአማራጭነት እንደሚጠቀሙ ተገልጿል። በአካባቢው ዘመናዊ ሕክምና የሚገኝ ቢሆንም አብዛኛው ማኅበረሰብ ባህላዊውን የሕክምና ዘርፍ እንደሚመርጥ፤ የጥናቱ ግኝት ጠቁሟል። ባህላዊ ሕክምና በማኅበረሰቡ ዘንድ ተመራጭ ያደረገው መንፈሳዊና መለኮታዊ የሕክምና አማራጮችን ያካተተ መሆኑ፣ የማኅበረሰቡን የኢኮኖሚ አቅም ያገናዘበ፣ የባህላዊ ሕክምና ባለሙያዎች እንደማኅበረሰቡ ልማድ እና ሁኔታ ተዓምራዊ ፈውስ ይገኝባቸዋል ተብሎ መታሰቡ፤ የሕክምና ዘርፉን ተመራጭ እንዳደረገው አስረድተዋል። የ"Abraraw" ጥናት፤ በደሴ ከተማ የሚካሄደውን የባህል ሕክምና ልማድ፣ ይዘትና ተግባር መፈተሹ፤ የማኅበረሰቡን የሕክምና ምርጫና ፍላጎት መዳሰሱ፣ የማኅበረሰቡን አመለካከት መቃኘቱና በዘርፉ ያለውን እሳቤ ማስረዳቱ ልዩ ያደርገዋል።

Wondwosen (2006) "Medical Pluralism in Ethiopia" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። የጥናታቸው ዐቢይ ዓላማ የዘመናዊ እና ባህላዊ ሕክምና ጥምረትን መመርመር ነበር። በጥናታቸው ሂደት፤ በባህላዊና በዘመናዊው ሕክምና መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት የሚተገበሩትና የሚከተሉት ፍልስፍና፤ የሚሰጡት የሕክምና አገልግሎት ምክንያታዊ እና ተጨባጭ መሆንና አለመሆኑን፤ የዕውቀት ምንጫቸው (በመደበኛ እና በኢ-መደበኛ ትምህርት የሚገኝ) መሰረትና እሳቤ መለያየትን፤ የባህላዊና ሣይንሳዊ አስተምህሮ መለያየት፤ ዓለማቀፋዊ ዕውቀትና ባህላዊ (አካባቢያዊ፣ ቡድናዊ፣ ሃይማኖትና እምነት ተኮር) ጥበብን መነሻ ማድረጋቸው…፤ ለልዩነታቸው ዋና ዋና ምክንያት መሆናቸውን ገልፀዋል።

ሁለቱን ሙያዎች ለማቀራረብ፣ እንዲተጋገዙ ለማድረግ፣ የማኅበረሰቡን ጤና ለማሻሻል፤ የመንግስት የጤና መመሪያዎች፣ የአዕምሮ ንብረት ባለቤትነትና መብት ጥበቃ፣ የጤና ፖሊሲ አውጭዎች፤ የባህልና የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች በመወያየትና በመግባባት የሕክምና መስኩን ማሻሻል እንደሚቻል ጠቁመዋል። በጥናታቸው ማጠቃለያ ዘመናዊውም ሆነ ባህላዊ

ሕክምና በሚሰጡት የሕክምና አገልግሎት በየመስካቸው ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳላቸው በጥናታቸው አስረድተዋል፡፡

የ"Wondwosen" ጥናት፤ የባህልና የዘመናዊ ሕክምና ጥምረትን ትኩረት ማድረጋቸው፤ የሙያ መስኮቹን ልማድ፣ መሰረትና ይዘት መመርመራቸው፤ አገር አቀፍና ዓለማቀፍ ተመክሮና ልምዶችን መዳሰሳቸው፤ በዘርፉ ያለውን የጥናት ክፍተትና ክርክር ማንሳታቸው፤ ከቀደሙ (በዚህ ይዘት ከተጠቀሱ) ጥናቶች የተለዩ ያደርጋቸዋል፡፡

Mekonen (2008)፤ "The Attitude of Traditional Practitioners Biomedical workers and the public towards traditional Medicines with Particular Reference to Rabies Healers in West Gojjam" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው ዐቢይ ዓላማ፤ የእብድ ዉሻ በሽታን ለመፈወስ የሚሰጠውን የባህል ሕክምና፤ ከባህል ሐኪሞች፣ ከዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች እና ከማኅበረሰቡ አመለካከት አንጻር መመርመር ነበር፡፡ እንደ Mekonen ገለጻ፤ ማኅበረሰቡ ከእብድ ውሻ በሽታ ለመፈወስ ከዘመናዊ ሕክምና ይልቅ ባህላዊ ሕክምና እንደሆነ በጥናታቸው አስረድተዋል፡፡

በባህላዊ ሕክምና የሚሰጠው አገልግሎትና ፈውስ በባህል ሐኪሞቹና በማኅበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ሲሆን፤ የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች በመስኩ ለሚካሄደው ሕክምና አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች በማኅበረሰቡ የተመረጡበትን ምክንያት፤ አንድም በየአካባቢው (በየቦታው) መገኘታቸው፣ ለእብድ ውሻ በሽታ የሚሰጡት መድኃኒት እንደሚፈውስ መታመኑ፤ በዝቅተኛ ዋጋ አገልግሎት መስጠታቸው፣ የሕክምና ዘርፉን ተመራጭ እንዳደረገው በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡ Mekonen በባህላዊ ሕክምና ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ለእብድ ውሻ በሽታ የሚሰጠውን ሕክምና ለይተው ማጥናታቸው፤ ስለእብድ ዉሻ በሽታ በባሕላዊና በዘመናዊ ሕክምና ያለውን ባህላዊና ሣይንሳዊ እሳቤ መመርመራቸው፤ ማኅበረሰቡ ከእብድ ውሻ በሽታ ለመፈወስ የትኛውን የሕክምና አገልግሎትና ተቋም እንደሚመርጥ በንፅፅር ማጥናታቸው፣ ከዚህ በፊት ከተካሄዱት ጥናቶች (በዚህ ጥናት የተቃኙትን ብቻ ይመለከታል) በተለየ መልኩ አዲስ አቅጣጫን አመላክተዋል፡፡ ከዚህ ይዘት በመቀጠል የባህል ሕክምና ታሪክን ማዕከል ያደረጉ ጥናቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.3.3 የባህል ሕክምና ታሪክን ማዕከል ያደረጉ ጥናቶች

የባህል ሕክምና ታሪክን ማዕከልና ትኩረት ካደረጉ ጥናቶች[37] መካከል የAssefa Balcha (1992) ተከታታይ ሥራዎች ይጠቀሳሉ። የጥናታቸው ርዕስ "Traditional Medicine in Wallo: Its Nature and History" በሚል የቀረበ ነው። የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የወሎን የባህል ሕክምና ገጽታ (Nature) እና ታሪክ ማጥናት ነው። ማኅበረሰቡ ከአምልኮ ጋር በተያያዘ የሚፈፅማቸውን የባህል ሕክምና ሥርዓት፣ ባህላዊ ሐኪሞች ለበሽታ እና ለመድኃኒት ያላቸውን አመለካከት፣ በዘመናዊና በባህላዊ ሕክምና መካከል ያለው ግንኙነት ቃኝተዋል። በጥናታቸው ሂደት፤ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ልማድ፣ ሥርዓትና ተግባር የረጅም ዓመት ልምድና ተመክሮ እንዳለው፤ ይህ ልማድ መቼ እንደተጀመረ፤ አነሳሱ፣ እድገትና ቀጣይነቱ ምን ይመስል እንደነበር፤ በየትኛው መንግሥትና አስተዳደር ተግባራዊ እንደሆነ የታሪክ ማስረጃዎችን ለማቅረብ እንደሚያዳግት አስረድተዋል። የባህል ሕክምና ጥበብ አጀማመርና እድገት በውል ባይታወቅም አካላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና አዕምሯዊ ሕመሞችን ለመፈወስ፣ ለማስወገድና ለመከላከል (ቀድሞም ቢሆን) ጠቃሚ እንደነበር ገልፀዋል።

ኢትዮጵያ በሃይማኖት፣ በንግድ፣ በጦርነት እና መሰል መስተጋብር ከጎረቤት አገሮችና ከሌላውም ዓለም ስለምትገናኝ የሕክምና ጥበቡ፣ ልምድና ተመክሮው፤ ከጥንታዊያን ግብፅ፣ ፐርሺያ፣ እስራኤል፣ ዐረቢያ፣ ግሪክና ሱዳን አገሮች ተፅእኖ እንደሚኖረው አስረድተዋል። በጥናታቸው ግኝት የማኅበረሰብ ጤና ለማሻሻል፤ የባህላዊ እና ዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ተቀራርበው በጥምረት ቢሰሩ መልካም መሆኑን ጠቁመዋል። የAssefa ጥናት፤ የወሎን የባህል ሕክምና ተፈጥሮ፣ ባሕርይና ታሪክን ማጥናታቸው፤ በየዘመኑ የተከሰቱ በሽታዎችን መጠቆማቸው፤ የሕክምና ታሪክና ተግባሩን በዘመን ይዘት ወስነው ማቅረባቸው፤ የበሽታዎችን ዳራ እና ታሪክ መጠቆማቸው፤ ከቀደምት ጥናቶች (በዚህ ይዘት ከተጠቀሱት) ይለያሉ።

አሰፋ (2008)፤ "የኢትዮጵያ ባሕላዊ መድኃኒትና ሕክምና የምዕተ ዓመት ጉዞ" በሚል ርዕስ መጽሐፍ አሳትመዋል። የጥናታቸው ዐቢይ ዓላማ የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ታሪክ፣ ለውጥ፣ የመንግሥታትን ውሳኔና የዘመን መንፈስን ዳሰዋል። በጥናታቸው ሂደት ወደ ባህላዊ ሕክምና

---

[37]የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ታሪክና ዳራ በስፋትና በጥልቀት ከመረመሩ ምሁራን መካከል Richard Pankhurst (1965; 1976; 2004; 2005; 1990 ሥራዎች) በዋናነት ይጠቀሳሉ። ለዚህ ጥናት ዐውድና ይዘት የአሰፋ ባልቻ ሥራዎች ቅርብ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ የጭብጥና ይዘት ቅኝት ተደርጎባቸዋል።

ጥበብ የሚገቡ የሃይማኖት ተማሪዎች፣ የመድኃኒትና ሕክምና ጥበብ የመማር ማስተማር ሂደት፣ የቤተክህነት መድኃኒትና ሕክምና ዐዋቂዎች በጣሊያን ወረራ ዘመን የነበራቸው ተግባር፣ የዘመናዊ ጤና ተቋማት አገልግሎት፣ ቢሮክራሲያዊ ተግዳሮቶችና አማራጭ ሕክምና፣ ወታደራዊ መንግሥት በአገር በቀል የሕክምና አዋቂዎች ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ መርምረዋል። በጥናታቸው ሂደት፤ ከአፄ ሚኒሊክ እስከ ደርግ ዘመነ መንግሥት ማብቂያ ድረስ ያለውን የባህል ሕክምና አስተምህሮ፣ ተግባርና ሂደት ዳሰዋል። በሂደትም፤ የባህል ሕክምና ጥበብ አስማታዊ፣ መለኮታዊና ሃይማኖታዊ ይዘት እንዳለው ጠቁመው፤ ይህን ዕውቀትና ልምድ ለማግኘትና ለመማር የአብነት "የቆሎ" ተማሪዎች እረጅም ዓመት እንደሚፈጅባቸው፤ ጥበቡን ከባለሙያው ለመውረስና ለማግኘት "የረጅም ጊዜ አገልግሎት"፣ መልካም ሥነ ምግባር፣ እርጋታና ጥልቅ አስተዉሎት፣ የዕፅዋት፣ የእንስሳትና የማዕድን ዓይነቶችን በውል መለየትን እንደሚያካትት አስረድተዋል። በጥናታቸው ማጠቃለያ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና "ውጣ ውረድ የበዛበትና በተለያዩ መንግሥታት ተቀባይነት ሲያገኝና ሲያጣ ዘመናትን ያስቆጠረ ሙያ" መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህ ይዘት በመቀጠል የባህል ሕክምና ግብዓትን በሣይንስ ቤተ-ሙከራ የፈተሹ ጥናቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 2.3.4 የባህል ሕክምና ግብዓትን በሣይንስ ቤተ ሙከራ የፈተሸ ጥናት

የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ግብዓት (ዕፀ መድኃኒቶችን በዋናነት) ምን ዓይነት ባሕርይ፣ ቀለም፣ ጣዕም፣ "አሲድ፣ ቤዝ" ይዘት፣… እንዳላቸው በሣይንስ ቤተ-ሙከራ የፈተሹ የሥነ ሕይወት፣ የ"ኬሚስትሪ"፣ የሕክምና ሣይንስ ምርምሮች… ይጠቀሳሉ። ለዚህ ጥናት የ"Fekadu Fullas" ምርምር ተመርጧል። ለምን ዓይነት ፋይዳና ይዘት ተመረጠ ሲባል፤ የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ዳራ፣ ታሪክ፣ ልማድ እና ልምድ፣ ባህል ማካተቱና ከሣይንስ ቤተ-ሙከራ ጋር ያለውን መስተጋብር መዳሰሱ፤ በዚህ ይዘት ቅኝት ተመራጭ አድርጎታል።

Fekadu (2001)፤ "Ethiopian Traditional Medicine: Common Medicinal Plants in Perspective" በሚል ርዕስ ያሳተሙት ጥናት ይጠቀሳል። የጥናታቸው ማዕከላዊ ትኩረት በባህላዊ ሕክምና ጉልህ ሚና ያላቸውን ዕፅዋት በመለየትና ከአገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች በመሰብሰብ በቤተ ሙከራ ምርመራ አካሂደዋል። በጥናታቸው ሂደት፤ የዕፅዋትን ዓይነት መለየት፣ የመርዛማነታቸውን መጠንና ደረጃ በቤተ ሙከራ ፍተሻ ማውጣት፣ በሽታ የመከላከል ኃይልና አቅማቸውን ማረጋገጥ

የሚሉ ይዘቶችን አካተዋል፡፡ ይህ ጥናት የ99 (ዘጠና ዘጠኝ) ዕፅዋትን ዝርዝር ስም፣ መገኛ ቦታ፣…መሰል ነገሮችን አካቶ የያዘ ሰነድ ነው፡፡ Fekadu ከቀደሙ ጥናታዊ ጽሑፎች የሚለዩት የሥነ ዘዴ መረጣቸው እና የናሙና አጠቃቀማቸው፤ የዕፅዋትን የመድኃኒት አቅም በቤተ ሙከራ ማረጋገጣቸው፣ በባህላዊና በዘመናዊ ሕክምና ያላቸውን ሚና መዳሰሳቸው፣ በባህል ሕክምና የሚሰጡትን ጠቀሜታና አገልግሎት መጠቆማቸው፣ በሽታን የመፈወስ ኃይላቸውን፣ መርዛማነታቸውን፣ አካባቢያዊና ሣይንሳዊ መጠሪያቸውን፣ የሚበቅሉበትን ቦታና የዐየር ፀባይ በመዳሰስ ሰፊ ትንታኔ ማቅረባቸው፤ በዚህ ይዘት ከተቃኙ ጥናታዊ ጽሑፎች የተለዩ ያደርጋቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር፣ በሥነ ሰብ እና በታሪክ… ትምህርት ክፍል የተካሄዱ ጥናቶች የተለያዩ ማኅበረሰቦችን የባህል ሕክምና ልማድ፣ ሥርዓትና አተገባበር ከማኅበረሰቡ እምነት፣ ዕውቀትና ተግባር አንፃር ማጥናታቸው፤ የማኅበረሰቡን የጤና አጠባበቅ ልማድና ጥበብ መመርመራቸው፤ ለባህል ሕክምና ጥናት ትኩረት መስጠታቸው፤ ዘርፉን ለማስተዋወቅ፣ ሰነድ ለማሰባሰብ፣ መረጃ ለመጠቆም፣ የመስኩን ምርምር ለማዳበር፣ የጥናት መነሻ በመሆን… ከፍተኛ አበርክቶ አላቸው፡፡ የጥናቶቹ ርዕሰ ጉዳይ ሣይንሳዊ የምርምር ይዘት፣ ደንብና ሕግን በመከተል፤ መዋቅራዊ የጥናት አደረጃጀታቸው ተቀራራቢ ቢሆንም የማኅበረሰቡ የባህል ሕክምና ልማድ እና አተገባበር አካባቢያዊ ዕውቀት፣ ክስተት፣ እምነት፣ ሥርዓት፣ ሃይማኖት፣ አምልኳዊ አተያይን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው፤ የጥናቶቹን ስብጥር እና አዲስነት ያመለክታል፡፡ ከዚህ አንጻር ጥናቶቹ ትኩረት ያደረጉበትን ማኅበረሰብ የባህል ሕክምና ልማድ ንዑስ ክፍል መዳሰሳቸውና ለዘርፉ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ በማበርከታቸው፤ ሊመሰገኑ ይገባል፡፡

ከዚህ በላይ የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ልማድና ተግባር በተለያየ ፈርጅ፣ ይዘት፣ ዓይነትና ከየሙያ መስካቸው አንፃር የመረመሩ አሥራ ዘጠኝ (19) ቀደምት ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡ ከቀደምት ጥናቶች ቅኝት ምን ዓይነት ልምድ፣ ዕውቀትና ትምህርት ተገኘ? ሲባል፤ በዘርፉ የተካሄዱ የምርምር ይዘት እና ክፍተቶችን ለመለየት፤ የጥናታቸውን መሰረት፣ ፅንሰ ሃሳብና ንድፈ ሃሳብ ለመገንዘብ፤ ሣይንሳዊ (የምርምር ሥነ ዘዴ እና አተናተን ስልት…) እና ቴክኒካዊ (የአጻጻፍ፣ የምንጭ አጠቃቀስ ሥርዓት…) የምርምር አቀራረብን፤ የመስኩን የምርምር ደረጃ ለመረዳት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡

ቀደምት ጥናቶች የመረጃ ምንጭና ግብዓት ከመሆናቸውም በተጨማሪ፤ በየማኅበረሰቡ የሚካሄዱ የባህል ሕክምና ልማድና ተግባራትን፣ እምነታዊ ሥርዓትን ማቅረባቸው፤ የባህል ሕክምና ዘርፍ ውስብስብ ይዘት፣ ልማድና ተግባር እንዳለው፤ የዕውቀት ምንጩና ባለቤቱ የአካባቢው ማኅበረሰብ እንደሆነ፤ የባህል ሕክምና ጥናት አካባቢያዊ ዐውድን፣ ማኅበራዊ ልማድን፣ እምነታዊ ሥርዓትን ማሕቀፍና መነሻ እንደሚያደርግ፤ (ዓለማየሁ፣ 2000፤ አሰፋ፣ 2008፤ ዐቢዩ፣ 2010፤ Young, 1970: Mirgissa 1993: Fekadu, 2001: Wondwosen, 2006)፤ ከቀደምት ጥናቶች ይዘት (ልምድና ዕውቀት ተገኝቷል) ተገንዝቢያለሁ። ከዚህ በፊት በባህል ሕክምና ዘርፍ ከተጠኑ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይዘቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡-

በባህል ሕክምና የዕፅ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ልማድ፤ የባህል ሕክምና አተገባበርና ሥርዓት፤ ለባህል ሕክምና የሚያገለግሉ የግብዓት ዓይነቶች፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ማኅበራዊ ደረጃ፤ ምስጢራዊነትና መተላለፊያ መንገዶች፤ ማኅበረሰቡ ለባህል ሕክምና ሙያና አተገባበር ያለውን አመለካከት፤ የባህል ሕክምና እምነት፣ ሃይማኖት እና የአካባቢ ልማድን መሰረትና መነሻ ማድረጉ፤ በባህል ሕክምና በተደጋጋሚ የሚጠቀሱ የበሽታ ዓይነቶችን በመጠቆም (ዓለማየሁ፣ 2000፤ ምህረት፣ 2000፤ መስፍን፣ 2002፤ ተመስገን፣ 2003፤ ደነቁ፣ 2003፤ ፍቅርተ፣ 2009፤ ማኅሌት፣ 2011)፤ ጤና እና ስለጤና የማኅበረሰብ ዕውቀትና አመለካከትን (Young, 1970: Mirgissa, 1993: Zerihun, 2001: Mekonen, M. 2010) ፈትሸዋል፤ ዕፀ መድኃኒት ባህላዊ እሴትን ለማጠናከር እና የአካባቢን ዐየር ንብረት ለመጠበቅ ሚና እንዳላቸው፤ የባህል ሕክምና የማኅበረሰብ እሴት፣ መገለጫ፣ የማንነት መለያና ጥበብ ስለመሆኑ፤ (ዓለማየሁ፣ 2000፤ ተመስገን፣ 2003፤ አሰፋ፣ 2008፤ Tebaber, 2015)፤ በዘመናዊ ሕክምና ስምና ይዘት ያልተሰጣቸው (የማይታወቁ) የሕመም ዓይነቶች እና "አስማታዊ" ድርጊቶች ገቢርና ልማድ መጠቆም (ዐቢዩ፣ 2010)፤ የባህል ሕክምና ጤናን በመጠበቅ/ በማሳጣት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ/ጉዳት እንዳለው፤ የባህል ሕክምና ዘርፍ በማኅበረሰቡ፣ በዘመናዊና በባህል ሕክምና ባለሙያዎች መካከል አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከት እንዳለ፤ ማኅበረሰቡ የጤና እክል/ሕመም ሲገጥመው የትኛውን ተቋም እንደሚመርጥ፤ የባህል እና የዘመናዊ ሕክምና ጥምረትና ግንኙነት ምን ዓይነት ይዘትና መስተጋብር እንዳላቸው የፈተሹ (Abraraw, 1998: Mekonen, W. 2008: Wondwosen, 2006: ዐቢዩ፣ 2010)፤ የባህል ሕክምና ግብዓቶችን ይዘት በሣይንስ ቤተ ሙከራ ማረጋገጥ (Fekadu, 2001)፤ የባህል ሕክምና የዘመን ጉዞና ሂደት፣ ዳራና ታሪክን (Assefa, 1992: አሰፋ፣ 2008) በዋናነት ዳሰዋል።

ቀደምት ጥናቶች በቀጣይነት ምን ይጠና ይላሉ? ሲባል Tebaber (2015) የባህል መድኃኒት ባህልን፣ አካባቢያዊ ዕሴትን፣ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ መሰረትን ገላጭ መሆናቸውን በመጠቆም፤ ቀጣይ ጥናቶች ትኩረታቸውን ከአካባቢው ሁነት እና ከማኅበረሰቡ የሕይወት መስተጋብር ጋር አገናኝተው እንዲያጠኑ መክረዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ዐቢዩ (2010፣ ገ.276) የባህል ሕክምና ዕውቀትና ክዋኔን የሚመለከቱ ጥናቶች ላይ ክፍተት እንዳለ ጠቁመው፤ ቀጣይ ምርምሮች የባህል ሕክምና ዕውቀት እና ክዋኔን ርዕሰ ጉዳይ ቢያደርጉ የዘርፉን ክፍተት እንደሚሸፍኑ ጠቁመዋል፡፡ ይህ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች ልብ ይላቸዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተቃኙ ምርምሮች እና ይህ ጥናት የሚያመሳስላቸው ማዕከላዊ ይዘት የባህል ሕክምና ርዕሰ ጉዳይን ማንሳትና ማጥናታቸው፤ የጥናታቸው ትኩረትና ይዘት ማድረጋቸው ነው፡፡ ከነዚህ ምርምሮች በተለየ ያልተዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዮችን በማጤን፤ የጥናቱን ትኩረት እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

አንደኛ፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን በማጤን እና በሁለቱ መስኮች መካከል ያለውን ባህል-ተኮር ተመጋጋቢነት (ተላውጦ)፤ "የፎክ ቲዎሪን" (Folk Theories) እሳቤ፤ የሕመም መንስኤ እና የሥነ ምህዳር ዐውድ (መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የዐየር ንብረት፣ የበሽታ መከሰቻ ወቅትና ባህላዊ እሳቤ) ግንኙነት፤ ሚታዊ ተረኮች እና አምልኳዊ ሥርዓቶች፤ "ለሕመም መንስኤ ናቸው" የሚባሉ ተግባራትን "ማራቅ"፤ ወቅትና ቦታን መለየት፡፡ በተቃራኒው ለፈውስ የሚውሉ ግብዓቶችን "ማቅረብ"፤ ከአኗኗር ሥርዓታቸው እና ከሕይወት መስተጋብራቸው ጋር ማስተሳሰር፤ ለባህል ሕክምና ቀጣይነትና ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን አስተዋፅኦ የአቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ አለመገኘቱን[38] ታሳቢ አድርጓል፡፡ ይህ ጥናት፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳርን ዐውዳዊ መስተጋብር መመርመሩ፤ አካባቢያዊ ዕውቀት እና ዐውዳዊ ሥርዓትን ማጤኑ፤ የማኅበረሰብ የበሽታ መንስኤ እሳቤ፤ ከሥነ ምህዳር ጋር ያለውን ትስስር ማጥናቱ ከቀደሙ (በዚህ ይዘት ከተዳሰሱ) ጥናቶች ልዩ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን መርምሮ የዘርፉን ክፍተት ለመጠቆምና ለማጥበብ፤ የቀረበ ጥናት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[38]የተመራማሪውን ጥረት፣ ተደራሽነት፣ ዕይታ፣ አድማስና ልምድ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ እስካሁን ጥናት አለመካሄዱን ምን ያህል እርግጠኛ ነህ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ከ2003 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ የሚካሄዱ የምርምር ውጤቶችን በማሰባሰብ በዘርፉ ያለውን ክፍተት በማጤንና በመገንዘብ የተሰጠ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ሁለተኛ፡- ይህ ጥናት የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን፣ የምርመራ ዘዴና የበሽታ ዓይነት፣ ባሕርይ፣ ተዛምዶና ስልት፣ በሽታና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን በዋናነት መርምሯል። በጥናቱ ሂደትም፣ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች የምርመራ ዘዴን፣ የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ (Health Balance Equilibrium) (መመለሻ) ስልቶችን፣ የበሽታ ባሕርይ፣ ስሜት እና የፈውስ ሥርዓት ተዛምዶን፣ የበሽታዎች ምድብ (አካላዊ መከሰቻ ቦታ)፣ ምልክት እና አተገባበርን መርምሯል። የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ባለሙያዎች የምርመራ ስልት፣ ዘዴ፣ ሥርዓት እና አተገባበር ቅኝት ወይም በትኩረት ጥናት ያደረገ ምርምር አለመገኘቱን ልብ ይሏል። ይህም ስለሆነ፣ በዘርፉ ያለውን የዕውቀትና ተግባር ይዘት በማደራጀት፣ የምርምር ክፍተትን ለማጥበብ እና ሙያውን በውል ለመረዳት፣ የመስክ መረጃዎች ተሰብስበው፣ በይዘት ተደራጅተው ተተንትነው ቀርበዋል።

ሶስተኛ፡- በባህል ሕክምና ዘርፍ የዕፀ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በስፋት ከተጠኑ ይዘቶች መካከል አንዱ ነው (ዓለማየሁ፣ 2000፣ ምህረት፣ 2000፣ መስፍን፣ 2002፣ ተመስገን፣ 2003፣ ደነቁ፣ 2003፣ ዐቢዩ፣ 2010፣ ማኅሌት፣ 2011)። በምን ስልት፣ ይዘትና አንጻር ተጠና? ሲባል የመስክ መረጃን ይዘት በጥቅሉ መድቦና ከፋፍሎ "እንደዚህ ይቆረጣሉ፣ ይቀመማሉ፣ ይሰጣሉ... " ብለው ከመግለፅ ባለፈ የማደራጀት እና የመተንተኛ ንድፈ ሃሳባዊ አንጻሮችን በውል ለይተው አያስረዱም፣ ምናልባት ከጥናቶቹ ባሕርይ፣ ይዘት፣ መጠንና ትኩረት አንፃር ውስን መረጃን በማካተት ይዘቱ ይታለፋል። ይህ ጥናት፣ የዕፀ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ሥርዓት እና ክዋኔ ይዘትን በትኩረት ተንትኗል። የመስኩን የጥናት ክፍተት ለመሙላትና የተደራጀ የመስክ መረጃን ለመሰብሰብ ዐውድ-ተኮር ክዋኔ የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ ይዘት በመሆን አገልግሏል (ይህ ጥናት በዐውድ-ተኮር ክዋኔ ይዘት መቅረቡ ልዩ ያደርገዋል)።

የመድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማ፣ አተገባበር፣ አሰጣጥና መመሪያ ዐውድ-ተኮር ተግባራትን (ጊዜና ቦታን) እና የመከወኛ አጋጣሚዎችን (Kapchan, 1995; PP.481-483) ይለያል። ይህን ታሳቢ በማድረግ፣ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች የዕፀ መድኃኒት አዘገጃጀት፣ መገኛ ቦታ (ሥነ ምህዳር)፣ የቅመማ ልማድ፣ ለሕመምተኛ መድኃኒት ቀምመው ከሰጡ በኋላ "ብላ/ አትብላ"፣ "አድርግ/ አታድርግ" የሚሉ ማዘዣና መመሪያዎችን ይሰጣሉ (ዓለማየሁ፣ 2000፣ መስፍን፣ 2002፣ ተመስገን፣ 2003)። ለምን? ዕውቀቱ፣ እምነቱና ተግባሩ ከምን ይመነጫል? የዕውቀቱ መሰረትና ማሕቀፍ ምን ይመስላል? "አድርግ አታድርግ/ ብላ አትብላ" ክልከላና መመሪያ ከበሽታ መንስኤ፣ ከአመጋገብ ልማድ፣ ከምግብ ዓይነት (ምግቡ በሽታን ያባብሳል/ ይጠግናል፣...ለምን?)፣ የጤና

ሚዛን ማስተካከያ/መመለሻ ስልት ምንድን ነው? የበሽታ መንስኤዎች ከሥነ ምህዳር ጋር ምን ዓይነት ዐውዳዊ ተዛምዶና መስተጋብር አላቸው? የበሽታዎች ባሕርይና ስሜት ከሚሰጠው መድኃኒት (ሕክምና) ጋር የአላቸው ተቃርኖ/ተዛምዶ ምንድን ነው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠቱ፤ በዚህ ይዘት ከቀረቡ ቀደምት ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡

አራተኛ፡- የባህል ሕክምና ዕውቀት (ሥርዓትና አተገባበር) ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን አስተዋፅኦ በመለየት፤ ትንታኔ እና የመፍትሔ ሃሳብ አቅርቧል፡፡ የማኅበረሰቡ እምነት፣ የአምልኮ ሥርዓት እና ተግባር ሥነ ምህዳሩን (ገዳማት፣ አድባራት፣ ወንዝና ተራራ…) እንዴት ጠበቀው? የትኛውን ዕፅዋትና እንስሳት "ያቀርባል/ያርቃል"? ለምን? ዕፅዋት የማይቆረጡበት፤ እንስሳት የማይገደሉበት፤… ምክንያት ምንድን ነው? ቢቆረጡና ቢገደሉ ምን ይደርሳል ተብሎ ይታመናል? የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ከማዛባት አንጻር ምን ዓይነት ተፅዕኖ ይኖራቸዋል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት፤ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ አዕዋፍ፣ ነፍሳት… እና የምግብ ሰንሰለት ሥርዓት (Food chain System)፤ ከአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር ጥበቃ እና ከባህል ሕክምና (ከማኅበረሰብ እምነት) አንጻር ያላቸውን ትስስር እና መስተጋብር መርምሯል፡፡ ይህ ርዕሰ ጉዳይ በቀደምት ጥናቶች (በዚህ ቅኝት) ያልቀረበ መሆኑ፤ የምርምሩን ይዘትና ባሕርይ በእጅጉ የተለየ ያደርገዋል፡፡

አምስተኛ፡- ይህ ጥናት፤ በዚህ ይዘት ከተዳሰሱ ቀደምት ምርምሮች በተለየ የመስክ መረጃ መተንተኛ ንድፈ ሃሳቦች፣ ሞዴልና የጥናት አንጻር መጠቀሙ፣ የማኅበረሰቡን ዕለታዊ ተግባር እና "ቀያዊ" አመዳደብ ስልት መከተሉ፣ የጥናቱን ዐውድ ከማኅበረሰቡ ተግባርና የዕለት ሕይወት ጋር ማስተሳሰሩ፤ የአካባቢውን የባህል ሕክምና ተግባርና ዕውቀት ማሕቀፍ ማዘጋጀቱ፤ የባህል ሕክምና ልማድን መነሻ በማድረግ የማኅበረሰብ እና የሥነ ምህዳር መስተጋብርን ማቅረቡ፤ ጥቅል የባህል ሕክምና አተያይን መተግበሩ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ይዘት በመቀጠል የጥናቱ ሥነ ዘዴ እና አተገባበር በምዕራፍ ሶስት ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ሥነ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱን ዓይነት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ ስልት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃር፣ የጥናቱ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች፣ የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ሞዴል፣ የመስክ ልምድ እና ተመክሮ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 3.1 የምርምሩ ዕይታ መሰረት

እንደ Higgs, Tred and Rothwell (2007) መረጃ፤ አንድ የምርምር ሥራ የተነሳበትን ዓላማ፣ ይዘትና ተግባር ከግብ ለማድረስ ተገቢውን የዕይታ መሰረት (Philosophical Foundation) መርጦ መከተል እና መተግበር እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡ በምርምሩ ዓለም ሶስት መሰረታዊ የዕይታ መንገዶች (Positivist, Interpretive, and Pragmatism) እንዳሉ ይገልፃሉ፡፡ ከነዚህ የዕይታ መንገዶች መካከል "ተርጓሚ የዕይታ መንገድን" (Interpretive Paradigm) ማዕከል በማድረግ ምርምሩ ተካሂዷል፡፡ "ተርጓሚ የዕይታ መንገድ" ትኩረት አንድን ርዕሰ ጉዳይ በዓይነት (qualitative) ለመግለፅ፣ ለመተርጎም፣ ለመተንተን፣ ለማብራራት፣ ዐውድና ትዕምርቱን ለማስረዳት፤ ኢትኖግራፊያዊ ምርምር ለማካሄድ ተመራጭ ስልት እንደሆነ Blaxter, Hughes and Tight (2006) መክረዋል፡፡

ይህ ጥናት ከርዕሰ ጉዳይና ዓላማ፣ ከሚሰበሰቡ የመስክ መረጃ ዓይነቶች፣ ከአተናተን ስልትና ዘዴ አንፃር፤ ጥናቱ ዓይነታዊ ምርምር ይዘትን (Qualitative research methods) ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ዓይነታዊ ጥናት በሰዎች የዕርስ በዕርስ ግንኙነት እና መስተጋብር ላይ የተመሠረተ፤ የአጠናን መንገዱም ከተለያዩ ነጠላ ርዕሰ ጉዳዮች ተነስቶ በገለፃና በሃተታ መልክ በሂደት እየዳበረ፣ እየጎለበተና እየበለፀገ አንድ ማጠቃለያ ይዘት ላይ የሚደርስ ሣይንስ ነው (Dawson, 2009; P.20፤ Creswell, 2014; P.36)፡፡ ጥናቱም፤ ውስን አካባቢን፣ ውስን መረጃ ሰጪዎችንና ውስን መረጃዎችን በመውሰድ የሚጠናውን ርዕሰ ጉዳይ በስፋት፣ በጥልቀትና በዝርዝር የሚፈትሽና የሚተነትን ይዘት ነው (Kothari, 2004; P.3; Vanderstoep and Johnston, 2009; P.8)፡፡ በዚህ ጥናት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች፤ በተፈጥሮ ባሕርይ፣ በዐውድ-ተኮር ክዋኔ እና በባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል ይዘት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በዚህ ንዑስ ይዘት ስር የካልዓይ እና የቀዳማይ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችና ተግባር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 3.2.1 የካልዓይ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

ካልዓይ መረጃዎች፤ ከክለሳ ድርሳናት በተለየ፤ በጥናት ቦታ ላይ የተገኙ የባህል ሕክምና ማስታወቂያ እና የበሽታ ዝርዝሮች፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ የሚገኙ ለርዕሰ ጉዳዩ አስረጂ የሆኑ ጽሑፎች፣ ቁሳቁሶች፣ ፎቶዎች፣ ካርታዎች በመረጃ ምንጭነት ተሰብስበዋል (Hammersley & Atkinson, 2007)፡፡ ለምን ዓላማ?

የባህል ሕክምና ዕውቀትና ተግባርን ለመገንዘብ፤ የማኅበረሰቡን ማኅበረ-ባህላዊ ዳራ ለመረዳት፤ በአካባቢው ላይ በተደጋጋሚ የሚከሰቱና የሚፈወሱ የበሽታ ዓይነቶችን ለማጤን፤ የባህል ሐኪሞችን ሙያ፣ ተግባር እና ገደብ ለማወቅ፤ የጥናቱን ዐውድና ትኩረት ለመቀንበብ፤ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

#### 3.2.2 የቀዳማይ መረጃዎች አሰባሰብ ዘዴዎች

ይህ ጥናት ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል፤ ምልከታ (Observation)፤ ቃለመጠይቅ (Interview)፣ ንጥል ጥናት (Case Study) እና ተተኳሪ ቡድናዊ ውይይትን (Focused Group Discussion) የጥናቱ አካልና አባል አድርጓል፡፡ ከምልከታ ይዘት፤ ተሳትፏዊ ምልከታ (Participatory Observation)፣ ጽሞናዊ ምልከታ (Passive Observation)፤ ከቃለመጠይቅ ደግሞ መደበኛ (Formal) እና ኢ-መደበኛ (Informal) ቃለመጠይቅ ተካተዋል፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንደ አስፈላጊነታቸው እያፈራረቁ መጠቀም፤ ለመረጃ ግብዓትና ጥራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የመስኩ ምሁራን ጠቁመው፤ በተለይ የፎክሎር መስከኛ የሚያጠናውን ርዕሰ ጉዳይ ከነሙሉ ዐዉዱ ለመገንዘብና ለመተግበር በተጠኚው ማኅበረሰብ ክፍል ውስጥ ገብቶ መረጃ መሰብሰብ እንዳለበት ይመክራሉ (ፈቀደ፣ 1991፣ ገፅ. 90-99፤ Jackson, 1987; P.13: Kothari, 2004; P.3)፡፡

አንድ አጥኚ የምርምሩን ሥራ ከግብ ለማድረስ የተለያዩ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን እንደ አመቺነታቸው አፈራርቆ ይጠቀማል (Mack, and et al, 2005; PP.2-5)፡፡ ከነዚህ ግብዓቶች መካከል ፎቶ ግራፍ፣ መቅረጸ-ድምጽ፣ ቪዲዮ ካሜራ እና ማስታወሻ ደብተሮች ይጠቀሳሉ

(ፈቀደ፣ 1991፣ ገፅ. 90-99)። Toelken (1996, PP.359-360)፤ በመስክ ቆይታ ወቅት የፎክሎር መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች እየታገዙ መሰብሰብ፣ ማደራጀትና መመዝገብ አስተማማኝ መረጃዎችን ለመያዝ እንደሚያግዙ መክረዋል። በዚህ መነሻ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ከመስክ ለመሰብሰብ መቅረፀ ድምፅ፣ የፎቶ ግራፍ ካሜራ፣ ቪዲዮ ካሜራ እና ማስታወሻ ደብተር አገልግሎት ላይ ውለዋል።

**መቅረጸ ድምፅ፡-** በተደራጀ፣ በከፊልና ባልተደራጀ ቃለመጠይቅ ወቅት፤ ከመረጃ ሰጪዎቹ ይሁንታና ፈቃድ የተገኘባቸውን መረጃዎች በመቅረጸ ድምፅ ተሰብስበዋል። በመቅረጸ ድምፅ የተሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች ወደ ወረቀት ተገልብጠዋል/ተቀድተዋል (Transcribe)። እነዚህ መረጃዎች በዓይነትና በይዘት ተመድበው፤ መለያ ኮድ ተሰጥቷቸው ከተደራጁ በኋላ፤ ለጥናቱ ትንታኔ አስፈላጊ የሆኑ ይዘቶች ቃል በቃል (የመረጃ ሰጪዎች ድምፅ)፣ ይዘት እና ጭምቅ ሃሳባቸውን በመውሰድ ተተንትነው ቀርበዋል።

**ቪዲዮ ካሜራ፡-** በመስክ ምልከታና ትግበራ ወቅት ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዚህ ወቅት ከመረጃ ሰጪዎች ይሁንታ የተገኘባቸውን የዕፀ መድኃኒት ግብዓቶች፣ በባህል ሐኪሞች የቀረቡ ገለጻና ማስረጃዎች፣ የሕክምና መስጫ ቦታዎችና አተገባበር፣ መስክ ላይ የሚገኙ የዕፅዋት ዓይነቶችን ለመሰብሰብ የምስልና ድምፅ መቅረጫ መሳሪያ ተግባራዊ ሆኗል።

**የፎቶ ግራፍ ካሜራ፡-** በቃለመጠይቅ፣ በንጥል ጥናትና በተተካሪ ቡድናዊ ውይይት ወቅት የመረጃ ሰጪዎቹን ማንነት ለመግለፅ፤ ፈቃድ የተገኙባቸውን፤ አካላዊ የቁስል ሕመምን፤ የምርመራ ዘዴን፣ የዕፅዋት፣ የማዕድናት እና የእንስሳት ዓይነቶችን በተገኙበት ዐውድና ሥነ ምህዳር ለመሰብሰብ፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ለጥናቱ አቅራቢ ተግባራዊ የምርመራ ዘዴያቸው፣ የመድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ስልታቸው በፎቶ ግራፍ ካሜራ ተሰብስበዋል። እንደ አስፈላጊነታቸው እየተመረጡ ለጥናቱ ትንታኔ ይዘት ቀርበዋል።

**ማስታወሻ ደብተር፡-** ከሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ግብዓቶች ጋር በተጓዳኝ አገልግሎት ላይ የዋለ ቢሆንም፤ ምስላቸው በፎቶ ግራፍ እንዲነሳ፣ ቃላቸው በመቅረጸ ድምፅ እንዲያዝ፣ ሥራና ተግባራቸው በቪዲዮ እንዲቀረጽ ፍቃደኛ ያልሆኑ መረጃ ሰጪዎች ደግሞ ተግባርና ሃሳባቸው በማስታወሻ ደብተር ተመዝግቧል። በተለይ ምስጢራዊና ድብቅ የሚባሉ የባህል

ሕክምና ተግባራት (በማኅበረሰቡ "ነውር" የሚባሉ የመድኃኒት ግብዓቶች)፤ "በይፋ" የማይነገሩ እምነታዊ ጉዳዮች በማስታወሻ ደብተር ከመረጃ ሰጪዎች አንደበትና ተግባር ተሰብስበዋል፡፡

እነዚህ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ግብዓቶች ምን ዓይነት ጥቅም፣ ተግባርና ውስንነት አለባቸው? ሲባል፤ መቅረጸ ድምፅ በቃለመጠይቅ ወቅት የመረጃ ሰጪዎችን ድምፅና ንግግር ሳይቆራረጥ ለመቅዳት፤ የንግግሩን ድምፀት እና ዐውድ ለመረዳት፤ ቅጂውን ለማዳመጥና ወደ ወረቀ ለመገልበት አመቺ ሲሆን፤ ምስልና እንቅስቃሴን አለማካተቱ በተግዳሮት ይጠቀሳል፡፡ ቪዲዮ ካሜራ በዐውድና በክዋኔ የሚገለጹ ተግባራትን በተሟላ ሁኔታ ለመሰነድ ማገዙ፤ የአካባቢውን ድባብ፣ እንቅስቃሴ፣ አካላዊ መልክና ቅርፅን ለመለየት፤ ድርጊት እና መሰል ሁነቶችን ለመሰብሰብ አስችሏል (ተመራማሪው በድምፅ እየሰማ፤ በምስል እያየ የመስክ መረጃን ከነዐውዱ አደራጅቶ ለመረዳትና ለመሰነድ ይጠቅማል)፡፡ ፎቶ ግራፍ የምስል መረጃዎችን ለማስቀረት፤ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ነጥሎ ለማንሳት፤ አስረጂ የሆኑ ዋቢዎችን በምስል፣ በቀለምና በቦታ ለይቶ ለመሰነድ አመቺ ነበር፡፡ የድምፅና የእንቅስቃሴ ሂደቱ እንደ ቪዲዮ ካሜራ በተሟላ መልኩ ለማግኘት ቢያዳግትም፤ የሚፈለገውንና በተግባር የሚገለፀውን የመስክ መረጃ በአካል፣ በምስልና በቀለም ይዘቱ ለማስቀረትና ለማስረዳት አጋዥ መረጃ መሰብሰቢያ ግብዓት በመሆን አገልግሏል፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ የመረጃ መሰብሰቢያ ግብዓቶችን አገልግሎትና ገደባቸውን በመለየት፤ የተሟላ የመስክ መረጃን ለማደራጀት ጥረት ተደርጓል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ድብልቅ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፤ የተመረጡበት ዓላማ፣ ተግባር፣ ጥቅምና አገልግሎት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### I) ተሣትፏዊ ምልከታ (Participatory Observation)

ይህ ምልከታ በአምስት ዙር የመስክ ቆይታ በተካሄዱ ምልልሶች የተሰበሰበ ነው፡፡ በመስክ ምልልስና ቆይታ ሂደት የምርምር ዓላማዎችን ታሳቢ በማድረግ፤ የመስክ ምልከታ መከታተያ ቅፅ ተዘጋጅቶ አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በባህል ሕክምና መስጫ ቦታዎች በመገኘት ከነተፈጥሯዊ መቼታቸው (Natural Settings) የምርመራ ዘዴዎችን፣ የሕክምና ሥርዓትና ተግባርን፣ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ (የመስክ ገቢርን/ክዋኔን)፣ ቅመማና አሰጣጥ ሂደቶችን ተመልክቻለሁ፡፡ የሙያ መስኩ (የባህል መድኃኒት አሰባሰብ ሂደትና ቅመማ) እጅግ ምስጢራዊና ድብቅ ከሚባሉ ተግባራት መካከል ይጠቀሳል፡፡ በዚህ ዘርፍ ከአባቴ መጠነኛ

ዕውቀትና ልምድ ያለኝ መሆኑ፤ ከባህል ሐኪሞች ጋር የነበረኝ ቅድመ ትውውቅ፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች አባል መሆኔ፤ በዘርፉ የሚካሄዱ ይዘቶችን እና የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን ምስጢር ጠብቂ፤ ይሁንታና ፍቃዳቸውን ተከትዬ ለጥናት የሚበቁ ጉዳዮችን በእጄ ዳስሼ፣ በምላሴ ቀምሼ፣ በአፍንጫዬ አሽትቼና በዓይኔ አይቼ፤ የመድኃኒት ግብዓቶችን ጣዕም፣ ባሕርይና ይዘት ለመገንዘብና ለመሳተፍ ችያለሁ (የመስክ ቆይታና ተግባር ይዘት፤ አባሪ ሰባትን ይመልከቱ)። ይሁንታና ፈቃድ የተገኘባቸውን ተግባራት (የምርመራ ዘዴዎችን እና ዕፅዋትን) ፎቶ በማንሳት እና በመቅረፅ፤ ምስልና ድምፃቸውን አስቀርቻለሁ።

ተሳትፏዊ ምልከታ የመስክ መረጃዎችን በተሻለ መልኩ ለመረዳት፣ ለመገንዘብና ርዕሰ ጉዳዩን ለመመርመርና ለማጤን አስፈላጊ ዐውድ መሆኑን (Dawson, 2009; P.32: O'Reilly, 2012; P.86) ይመክራሉ። ተመራማሪው ምን ጊዜም የማኅበረሰቡ ዐውድ በሚከወንበት ቦታ በመሄድና በመሳተፍ የማኅበረሰቡ አባልና አካል በመሆን ርዕሰ ጉዳዩን እንደባለቤቶቹ (የውስጥ አዋቂ በመሆን) ለመገንዘብና ለመከወን ጥረት የሚያደርግበት፤ ምን ዓይነት ተግባር፣ ሂደትና ሥርዓት እንዳለ ከነዐውዱ መረጃ የሚሰበስብበት ተግባር ቢሆንም እንደውጪ ተመልካች በመስክ ዐውድ የሚተገበሩ ይዘቶችን ተከታትሎ መመዝገብ፣ መቅረፅ፣ የማኅበረሰቡን ኢ-መደበኛ ግንኙነት እና መስተጋብር ማጤንና በመስክ ማስታወሻ ደብተር መጻፍ እንዳለበት Mack, N and et al (2005; P.13) እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡-

> Participant observation always takes place in community settings, in locations believed to have some relevance to the research questions. … [The researcher] engaged in participant observation tries to learn what life is like for an "insider" while remaining, inevitably, an "outsider. … [Researcher] make careful, objective notes about what they see, recording all accounts and observations as field notes in a field notebook. Informal conversation and interaction with members of the study population are also important components of the method and should be recorded in the field notes, in as much detail as possible.

በዚህ ጥናት ተሳትፏዊ ምልከታ ለምን ዓላማና ተግባር ዋለ? በተሣትፏዊ ምልከታ ለጥናቱ ዋና መረጃ አቀባይ ከሆኑ የባህል ሐኪሞች ጋር በመሆን የመድኃኒት ግብዓት በሚገኙበት መስክና ቦታ በመሄድ ዕፅዋት እንዴት ቅጠላቸው እንደሚለቀም፣ ግንዳቸው እንደሚቆረጥ፣ ሥራቸው እንደሚማስ በማጤንና በመሳተፍ፤ በተግባር ቅጠላቸውን መልቀም፣ ግንዳቸውን መቁረጥና ሥራቸውን መማስ ለምን ዓይነት መድኃኒት እንደሚውሉ፤ እንዴት እንደሚቀመሙ በተወሰኑ (ለቁስል እና ለሆድ ውስጥ ትላትል መፈወሻ የሚውሉ ግብዓቶችን ለመማር ተችሏል) ይዘቶች ላይ የመስክ ትምህርትና ተግባር የተገኘ ቢሆንም፤ የመስክ መከታተያ ቅፅ በማዘጋጀት በዕለቱ

የነበረውን ዐውድ-ተኮር ክዋኔ እግር በግር በመከታተል በመስክ ማስታወሻ ደብተር ተመዝግቧል (አባሪ አንድን ልብ ይሏል)።

ተሳትፏዊ ምልከታ የራሱ ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም ብቸኛው የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተደርጎ አይታሰብም። በክዋኔ ወቅት የመስክ ማስታወሻ ተከታትሎ ለመጻፍ፣ ለመቅረጽና ፎቶ ለማንሳት ያዳግታል፤ ይህን ክፍተት ለመቅረፍ፤ ጎን ለጎን ፅሞናዊ ምልከታ ማካሄድ እንደሚገባ፤ የመስኩ ምሁራን (Mack, N and et al, 2005; PP.26-27: Blaxter, Hughes and Tight, 2006; P.176) መክረዋል።

### II) ፅሞናዊ ምልከታ (Passive Observation)

በፅሞናዊ ምልከታ ሂደት፤ በባህል ሕክምና ጣቢያዎች በመገኘት የታካሚዎችን ሥሜት፣ መስተጋብር እና በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ፅሞናዊ ምልከታ አካሂጃለሁ። በተለይ የማኅበረሰብ እና የሥነ ምህዳር መስተጋብር ምን እንደሚመስል፤ የትኞቹ አካባቢዎች፣ ዕፅዋትና እንስሳት ለሕመም መንስኤና ፈውስ ተደርገው እንደሚታሰቡ መገንዘብ ችያለሁ። የማኅበረሰቡ መኖሪያ ቤት አጥር በምን ዓይነት ዕፅዋት እንደታጠረ፤ የዕፅዋቱ ባሕርይና የማኅበረሰብ እሳቤ፤ ማራቅና ማቅረባቸው ከሕመም መንስኤ ጋር ምን ዓይነት መስተጋብር እንዳላቸው፤ በፀበልና በገበያ ቦታዎች፣ በአጨዳና እና በአውድማ፤ በሠርግና በቀብር ሥርዓቶች ላይ በመገኘትና በመሳተፍ ልማዳዊ እምነቱንና ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ተከታትያለሁ። የሕመም፣ የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የማዕድናት ዓይነትና ባሕርይን ለመረዳት፤ የበሽታ መለያና መመርመሪያ ዘዴ ክዋኔዎችን ("የወፍ"/የጉበት፤ የዉሻ "ከለባት"፤ የጡት ካንሰር፣ የኪንታሮት፣ የእከክ፤...ምርመራዎችን) በፅሞና ለመከታተል እና መረጃ ለመሰባሰብ አግዟል።

በምልከታ መረጃ አሰባሰብ ሂደት ፍፁም ተሳታፊ (Complete participant) ወይም ፍፁም ተመልካች (Complete observer) ከመሆን ሁለቱንም ስልቶች ‹‹ሚዛናዊ›› አድርጎ እያፈራረቁ መጠቀም ተገቢ መሆኑን ምሁራን ይመክራሉ (Jackson, 1987; P.65: O'Reilly, 2012; P.104)። ስለሆነም በፅሞናዊ ምልከታ፤ የባህል ሐኪሞች ምርመራ ሲያደርጉ፤ መድኃኒት ቀምመው ሲሰጡ፤ የታካሚዎችን ንግግር፣ ማኅበረሰቡ የትኛውን ዕፅዋትና እንስሳት በአካባቢው እንደሚያቀርብና እንደሚያርቅ፤ ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸው ዐውዳዊ መስተጋብር (መቼ ከቤት ይወጣሉ? የቱን ሠዓት ይፈራሉ?...)፤ የባህል ሐኪሞች እና የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ለዘርፉ ያላቸውን እሳቤ

ለማጤን፣ ማኅበረሰቡ ለምን ዓይነት በሽታ የባህል ሕክምናን ይመርጣል፤ የጤና አጠባበቅ ልምዱና ተመክሮው ምን ይመስላል የሚሉ ይዘቶችን ለመታዘብና መረጃ ለመሰብሰብ አግዟል፡፡ ፅሞናዊ ምልከታ የተካሄደው፤ የባህል ሕክምና መስጫ ቦታዎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ታካሚዎች በሚገኙበት መኝታ ቤት፣ በተለያየ ዐውድ በአካባቢው ማኅበረሰብ መኖሪያ ቤቶች መገኘት፣ አብሮ መብላት፣ መጠጣት፣ ሰላምታ መለዋወጥና ቤተሰባዊ ግንኙነት በመመስረት፤ ስለማኅበረሰቡ እምነት፣ ስለበሽታ፣ ጤና፣ ሕይወት እና መሰል መስተጋብሮችን ለማጤን፤ እጅጉን የተመቸ በመሆኑ ፅሞናዊ ምልከታን ተመራጭ አድርጎታል፡፡

### III) ቃለመጠይቅ

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የመስክ መረጃዎች በመደበኛ (Formal) እና በኢ-መደበኛ (Informal) ቃለመጠይቅ ይዘት ተሰብስበዋል፡፡ ከቃለመጠይቅ ዓይነቶች፤ ውስን ቃለመጠይቅ (Structured interview)፣ ከፊል ነፃ ቃለመጠይቅ (Semi-structured Interview) እና ነፃ ቃለመጠይቅን (Unstructured Interview) በማስተሳሰር እንደአመቺነታቸው እያፈራረቁ የመስክ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን (ያለው፣ 2004፣ ገ.178፤ O'Reilly, 2012; P.113) ገልፀዋል፡፡ Schoemaker (1990; P.6)፤ የፎክሎር ጥናት ባሕርይ በቢሮና በተፃፉ ነገሮች ላይ ተመስርቶ የሚከወን ሳይሆን መስክ መውጣትና ለርዕሰ ጉዳዩ የቀረቡ መረጃ ሰጪዎችን በአካል አግኝቶ መጠየቅ ዐቢይ ተግባር መሆኑን ጠቁመው፤ ለዐውድ ተኮር ክዋኔ ጥናት የመረጃ ሰጪዎች አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ስሜት፣ ድምጽ እና መሰል ጉዳዮች ግብዓት እንደሆኑ አስረድተዋል ፡፡

የመረጃ ሰጪዎችን መሰረታዊ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ስምና ፍቺ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች መደበኛ ቃለመጠይቅ (ስም፣ እድሜ፣ መኖሪያ አካባቢ፤ "የዚህ ዕፅ/በሽታ ስም ማን ይባላል?" ለሚሉ ጥያቄዎች) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ለጥናቱ ተሳታፊ መረጃ ሰጪዎች ቀድመው የተዘጋጁ ውስን፣ ከፊል-ነፃ እና ነፃ ቃለመጠይቅ ይዘቶች፤ ቀርበው የመስክ መረጃዎች ተሰብስበዋል (አባሪ ሁለትን ልብ ይሏል)፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊና ዝርዝር መረጃዎች ለመሰብሰብ ነፃ ቃለመጠይቅ በዋናነት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ እንደ አመቺነቱ ወቅትና ጊዜ (ዐውድ) በሚፈቅድ ቦታና ይዘት ላይ በመገኘት፤ ከባህል ሐኪሞች፣ ከታካሚዎች፣ ከዘመናዊ የሕክምና ባለሙያዎች፣ ከአካባቢው አዛውንትና ማኅበረሰብ አባላት ጋር በመገናኘት፤ ለበሽታ መንስኤ፣ ለጤና፣ ለምርመራ ዘዴ፣ ለመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ፣ ለሥነ

ምህዳር ጥበቃ ያላቸውን እሳቤ ለመጠየቅ፣ ለመገንዘብ እና መረጃ ለመሰብሰብ አስችሏል፡፡ ነፃ ቃለመጠይቅ የተለያዩ የመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አመቺ ከመሆኑም በተጨማሪ፤ መረጃ ሰጪዎች ሳይፈሩ፣ ሳይጠነቀቁ፣ ሳይጨነቁ ተፈጥሯዊ የሆነውን አመለካከት፣ ግንዛቤና ዕውቀት ለማግኘትና ለመቃኘት አመቺ መሆኑን በማሰብ፤ በዕለቱ ለመረጃ ሰጪዎች የቀርቡ ጥያቄዎች በጥንቃቄ ተለይተው፤ እንደየሙያ መስካቸው፣ እንደየዕድሜ መጠናቸው፣ እንደየማኅበራዊ ግንኙነታቸው… በማለዘብ ትህትና በተሞላበት መልኩ ለማቅረብ ተችሏል (በአጥኚው እሳቤ)፡፡ ምን ዓይነት ርዕሰ ጉዳይ ለነማን በቃለመጠይቅ ይዘት ቀረበ? ሲባል፤

ስለሕመም መንስኤ እሳቤ ከባህል ሐኪሞች እና ከአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት (ከእናት እና አባቶች፣ ከሃይማኖት አባቶች፤ ከታካሚዎች፣ ከጤና እና ከተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች) በቃለመጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች ስለሕመም መንስኤ "ኬት መጣነት"፤ በፈጠራዊ ሚት (Creation Myth)፣ በቃል ግጥም፣ በምሳሌያዊ ንግግር፣ በግል ተመክሮና በአካባቢያዊ ልማድ የሚፈፀሙ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት አስረድተዋል፡፡ በባህል ሕክምና የበሽታ መለያና መመርመሪያ ዘዴዎችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በዋናነት ለባህል ሐኪሞች ሲሆን በተጓዳኝ ለዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች በባህል ሐኪሞች እሳቤ፣ ዕውቀትና ተግባር የሚከወኑ፤ በሕይወት ልምድና ተመክሮ ላይ የተመሰረቱ፤ አካባቢያዊ ልማድን መነሻ አድርገው የሚፈፀሙ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት በቃለመጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ከዚህ ይዘት በመቀጠል በባህል ሕክምና የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔዎች ተግባር፣ ትዕምርት፣ ፍቺ፣ ሃይማኖታዊና እምነታዊ ጉዳዮች እንዴት፣ መቼ፣ በማን፣ ለምን እንደሚፈፀሙ፤ የተብራሩ የመስክ መረጃዎችን ለማግኘት ሲባል የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን ትኩረት በማድረግ ቃለመጠይቅ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በመጨረሻም፤ የማኅበረሰብ ልማድና የባህል ሕክምና ተግባር ለሥነ ምህዳር ምን ዓይነት አስተዋፅኦ እንደነበራቸው ለመመርመር ከአካባቢው ማኅበረሰብ አባላትና ከባህል ሐኪሞች በቃለመጠይቅ ይዘት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የመረጃዎቹ ትኩረት የማኅበረሰብ ልማድ/እምነት እና የሥነ ምህዳር መስተጋብርን የሚያስረዱ ፈጠራዊ ሚቶች፤ እምነታዊ ተግባራት፣ አምልኳዊ ሥርዓት፣ የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎችን ገለፃ መነሻ በማድረግ የመስክ መረጃዎች በቃለመጠይቅ ዘዴ ተሰብስበዋል፡፡

## IV) ንጥል ጥናት

በደቡብ ጎንደር ዞን ከሚገኙ የባህል ሐኪሞች መካከል አምስት ግለሰቦችን ለጉዳይ ምርመራ ጥናት በመለየት ከደጋ (ደብተራ መልኩ፤ ከፋርጣ)፣ ከወይና ደጋ (ሊቀጠበብት አብርሃም እና አቶ ደሴ ሊቦ ከምከም) እና ከቆላ (መሪጌታ ስዩም እና መሪጌታ ስንታየሁ እብናት) አካባቢዎች ተመርጠዋል። በዐውድ-ተኮር ክዋኔ የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ከመስክ ለመሰብሰብ፣ ሥርዓትና ተግባሩን ለማስረዳት (ደብተራ መልኩ)፣ የቅመማ ሂደትን ለማሳየት፣ የምርመራ ሂደቶችን ለመከታተል፤ የግል ታሪካቸውን፣ የሕክምና ልምዳቸውን፣ የምርመራ ዘዴያቸውን፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልታቸውን (ሊቀጠበብት አብርሃም፣ መሪጌታ ስዩምና መሪጌታ ስንታየሁ)፣ የኮከብ ቆጠራ ሂደት (አቶ ደሴ) በዝርዝር ማስረዳታቸው፤ አራት ታካሚዎች (በአቶ ደሴ፣ በአቶ ጌጡ፣ በመሪጌታ ስንታየሁ፣ በሊቀጠበብት አብርሃም) ለጉዳይ ምርመራ ይዘት በመለየት ስለሕመማቸው ዓይነት፣ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ፣ የባህል ሕክምና አተገባበር፣ ሥርዓትና ይዘት በትኩረት ለመሰብሰብ ተችሏል።

በንጥል ጥናት (Case study) ሂደት ውስን ርዕሰ ጉዳይን ለይቶ እና ግለሰብን መርጦ ከተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች አንፃር በጥልቀትና በዝርዝር ለማጥናት ተገቢና አመቺ ስልት እንደሆነ Blaxter, Hughes and Tight (2006; PP.71-72) እና ያለው (2004፣ገፅ.134-135) ይመክራሉ። ንጥል ጥናት፤ በልዩና በንዑስ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተመስርቶ በጥንቃቄ ሲተገበር እና ርዕሰ ጉዳይን ከንድፈ ሃሳብ ይዘት ጋር በማስተሳሰር ሲቀርብ ለአዲስ የምርምር ግኝትና ውጤት ምክንያት እንደሚሆን Blaxter, Hughes and Tight (2006; P.72) እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> Case studies, as the name indicates, concentrate on special cases. Generalizations from case studies must be handled with care. To serve as a foundation for generalizations, case studies should be related to a theoretical framework, which in turn may be adjusted as case study results provide new evidence.

ስለሆነም፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት እና በሥነ ምህዳር መካከል ምን ዓይነት ዐውዳዊ መስተጋብር እንዳለ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት፤ ርዕሰ ጉዳይንና ግለሰብን መነሻ በማድረግ የሕመም መንስኤ፣ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዐውድ-ተኮር ክዋኔዎች፣ ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸውን መስተጋብር ለመመርመር እድል ሰጥቷል፤ አስችሏል።

### V) ተተኳሪ ቡድናዊ ውይይት

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ቡድናዊ ውይይት ለምን አስፈለገ? ከመስክ በተለያየ ይዘትና ዐውድ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በዓይነት በመክፈል፣ በምድብ በማደራጀት ዐቢይ ጉዳዮችን ለይቶ ለማቅረብ፤ የጋራ ዕውቀት መሆን/አለመሆኑን ለማረጋገጥ፤ በምርምሩ ሂደት አጠራጣሪና ግልፅ ያልሆኑ መረጃዎችን ለማጣራት፣ ተጨማሪ እና አዳዲስ አሳቤዎችን ለማግኘትና ለመሰብሰብ አመቺ መሆኑን ይገልጻሉ (Schensul, and et al, 1999; PP.52-53: Dawson, 2009; P.32: ያለው፣ 2004፣ ገ.192)። የዚህ ጥናት መወያያ ጭብጦች ምን ነበሩ? ሲባል፤

ለባህል ሐኪሞች የሕመም መንስኤ፣ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዐውድ ተኮር ክዋኔ፤ የሥነ ምህዳር ምርጫና ሁነት፤ ለዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች፤ የበሽታ መንስኤ እና መለያ ስልቶች፣ የሥነ ምህዳር እና የበሽታ ሥርጭት፣ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ሚና እና ተግባር፤ ለአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት ደግሞ ባህላዊ እምነት፣ የሕመም መንስኤ፣ ሥነ ምህዳር፣ የሕክምና ምርጫና ልማድን መነሻ ያደረጉ የመወያያ ጭብጦች ቀርበው፤ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

በተመሳሳይ መልኩ Schensul and et al ደግሞ፤ በተተኳሪ ቡድን ውይይት የባህል ዐውድና ይዘቶችን ለማግኘት፣ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ዐንኳርና ጭብጥ መረጃዎችን ለማውጣት፣ በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተለያየ አመላካከት እና አስተያየቶችን ለመገንዘብ፣ የጋራ ሃሳብን ለማጤን፣ ቀድመው የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለማጣራት ጠቀሜታና አገልግሎት እንዳለው እንደሚከተለው (Schensul, and et al, 1999; P.51) ያስረዳሉ።

> Focus group interviews can be used for many purposes: to collect information on a cultural domain, to develop listings for pile sorts, to identify the range of variation in opinions or attitudes on a set of topics, to collect simple numerical data on reported experiences, or to react to the results of previously collected data.

በዚህ ጥናት አራት ቡድኖች ተመርጠው የመስክ ውይይት ተካሂዷል። በውይይቱ ሂደት፤ ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ አባላት የተሳተፉ ሲሆን፤ ቡድን አንድ በእብናት ወረዳ ከሚገኙ አምስት የባህል ሕክምና ባለሙያዎችና አንድ ከወረዳው ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ባለሙያ ጋር በመሆን ውይይት ተካሂዷል። በዚህ ውይይት የምርምሩ አንኳር ነጥቦች ተለይተው፤ ለሕመም መንስኤ የሚባሉ የአጋንንት ዓይነቶች፣ መለከፊያ ዐውዶች፣ መገኛ ቦታዎች ወንዝና ተራራ፤

የምርመራ ዘዴዎች፣ የበሽታ ባሕርያት፤ የመድኃኒት ቅመማ፣ አሰጣጥና የሥነ ምህዳር ጉዳዮች ተነስተው ውይይት ተካሂዶባቸዋል።

በዚህ ውይይት በምርምሩ ይዘትና ጥያቄዎች ያልተዳሰሱና ያልታሰቡ አዳዲስ ርዕሰ ጉዳዮች ተገኝተዋል። ለአብነት ያህል፦ "በኛ አስተምሮና ሃይማኖት"፤ የሰው ልጅ ተክለ ሰውነት፣ አካላዊ አወቃቀርና አቋም ከእንስሳት በተለየ በሁለት እግሩ ቆሞ ይሄዳል። እንደ እንስሳት ከአናቱ አጎንብሶ አይሄድም፣ በልብና በሆዱ ተኝቶ አይሳብም፣ ክንፍ አውጥቶ አይበርም፤ ተፈጥሮው ይለያል። በዚህ ተግባርና ተፈጥሮው፤ የሰው ልጅ አካል አንቀሳቃሽ ኃይል አዕምሮ "ብራያል" ይባላል። ይህም ስለሆነ፤ የውስጥ አካል ሕመም፣ "ሳንካና ችግር" ብዙውን ጊዜ "ከብራያል" ይነሳል ይላሉ፤ መሪጌታ ስንታየሁ። ለምን? ሲባል የአዕምሮ አንቀሳቃሽ ሞተር (ኃይል) "እንደመረብ ተዘርግቶ፤ ሰውነትን ሰፍቶ በመያዝ ውስጥ አካልን ይቆጣጠራል" አንድ የውስጥ አካል ሲጎዳ አዕምሮ ይጨነቃል፣ ግራ ይጋባል፣ ማሰብ ያዳግተዋል፤ "ሰው በድንገት ደንግጦ እራሱን ይስታል፣ ይሞታል፤ …መብራቱ ሲጠፋ ክሩ ሲበጠስ ሞት ይመጣል፤ ዋናው ሕክምና አዕምሮ ላይ ነው" ይላሉ። ሰው እና "የማያመነዥጉ" እንስሳት "ጨጓራ የላቸውም" ተብሎ ይታሰባል። አድቀውና አልመው የሚበሉ፤ ደም የሚመጡ ማጠራቀሚያ ከረጢት ካልሆነ በስተቀር፤ የበሉትን መልሰው እያመነዠኩ አይውጡም፤… "የጨጓራ ሕመም ሲባል በናንተ ትምህርት ነው [በዘመናዊ ሣይንስ]" በማለት አስረድተዋል (መሪጌታ ስንታየሁ፣ ከተቡው አባላት መካከል፣ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት)። በአጠቃላይ የሰው ልጅ ሕመም ከአዕምሮ ይነሳል፤ የጉዳቱ መጠን በአካል ይገለጻል፤ ይታያል። በዚህ እሳቤ፤ የጤና ሚዛን ማስተካከያ ስልትና ተግባር ከአዕምሮ ፍርሃትና ድፍረት፤ ጭንቀትና ደስታ፤ ተስፋ መቁረጥና ማድረግ፤ ክህደትና እምነት፤ እንደሚጀምር ይታመናል።

ቡድን ሁለት በእብናት ወረዳ ከሚገኙ አምስት የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ጋር የተካሄደ ውይይትን ይመለከታል። የሕመም መንስኤዎች፣ ወቅትን ተከትለው የሚከሰቱ የበሽታ ዓይነቶች፤ የሥነ ምህዳር ልዩነትና በሽታ፣ ውስጣዊ ሕመምን ከውጫዊ አካል መለየት፣ ለበሽታ የሚዳርጉ ሁነቶች፣ የማኅበረሰብ እምነት እና የባህል ሕክምና ተግባራትን፤ በሚመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ውይይት ተካሂዷል።

ቡድን ሶስት እና አራት (ስድስት ወንድ እና ሰባት ሴት አባላት) በፋርጣ ወረዳ ከሚገኙ የአካባቢው ማኅበረሰብ አባል አባትና እናቶች ጋር ሲሆን፤ የሕመም መንስኤ (ቡዳ፣ ዛር፣

አጋንንት)፣ ጤና ለመጠበቅና ለመለመን፤ ልማዳዊ ተግባራት (ሃይማኖታዊና እምነታዊ)፤ በአካባቢያቸው ለመንቀሳቀስ የትኛውን ወቅትና አካባቢ እንደሚመርጡና እንደሚፈሩ፤ እንስሳትና ዕፅዋትን ለምን እንደሚያቀርቡና እንደሚያርቁ፤ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አድባራት፣ ገዳማት፣ የሃይማኖት ደብሮች፣ የመቃብር ቦታዎች ከሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳት ምን ዓይነት መስተጋብር እንዳላቸው፤ ከሥነ ምህዳር የሚገኙ ግብዓቶችን እንዴት፣ መቼ እና ለምን ተግባር እንደሚጠቀሟቸው ገለጻና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በዚህ ጥናት የወንድ እና የሴት ቡድን ማደራጀት (ማለያየት) ለምን አስፈለገ? ሲባል፤ ከሥራ እና ከማኅበራዊ ደረጃ፤ ከእምነት፣ ከሃይማኖት፣ ከአካባቢያዊ ሁነት፣ ከግላዊ ተመክሮና ሕይወት፤ ከፆታ፣ ከቡድናዊ ተግባርና ባሕርያት አንፃር የሚቀርቡና የሚገለጹ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የታለመ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የመድኃኒት አዘገጃጀት፤ የመስዋዕት ዓይነት፣ አካባቢያዊ ተግባር እና ማኅበራዊ ደረጃን በማስረዳት ወንዶች ላቅ ያለውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ በአንፃሩ፤ የቤት ውስጥ ዝግጅትና ተግባራትን፤ አካባቢያዊ እና እምነታዊ ሁነቶችን፤ የግል ሕይወት ተመክሮን በማስረዳት (ምስጢራዊ ተግባር ወይም የሴት "ገበና" የሆኑ ጉዳዮችን ለመቃኘት- ከማኅፀን/ ከመራቢያ አካል የተገናኙ፤ "ለዛር፣ ለአድባር" የሚደረጉ ዝግጅቶችን) መረጃና ገጠመኞችን ለመሰብሰብ አመቺ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

በአጠቃላይ በተተኳሪ ቡድናዊ ውይይት ዐውድ ላይ የቀረቡ የመወያያ ርዕሶች፤ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በንጥል ጥናት የተከወኑና የቀረቡ ዐንኳር ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ሲሆን፤ በዓይነት፣ በምድብ፣ በይዘት ተከፋፍለው የጋራ ዕውቀት፣ ተግባርና እሳቤ መሆን/ አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ፣ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ለማግኘትና ግልፅ ያልሆኑ መረጃዎችን ለማጣራት ሲባል ተተግብሯል፡፡

### 3.3 የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ ስልት

ይህ ጥናት በዓላማ ተኮር (Purposive sampling) ስልት እና በአጋዥነት ጠቋሚ ናሙና ስልት (Network or snowball sampling) የመስክ መረጃ ሰጪዎችን ለይቷል፡፡ ያለው (2004፣ ገፅ.132-134)፤ "ጠቋሚ ናሙና" ሲባል - በሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ዕውቀት ያለውን አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ጠይቆ "አለኝ" የሚለውን መረጃ ከሰጠ በኋላ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎችን ወይም ቡድኖችን ለይተው ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጡ የሚያደርጉትን ጥቆማ ይመለከታል፡፡ ዓላማ ተኮር ናሙና የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይና ትኩረት መነሻ አድርጎ ለጥናቱ

አስፈላጊና መረጃው አላቸው የሚባሉ ሰዎችን መርጦ በቀጥታ ማነጋገርን ይመለከታል፡፡ አጋዥ ጠቋሚ ናሙና ሰንሰለታዊ የመረጃ ቅብብሎሽን የሚከተል ሲሆን በተመራማሪው የማይታወቁና በመረጃ ሰጪዎች ጥቆማ የሚመረጡ መረጃ ሰጪዎችን እንደሚመለከት Mack, N and et al, (2005; P.5) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> Purposive... sampling... seeks to identify participants based on selected criteria. …[Snowballing] also known as chain referral sampling. …[participants or informants] with whom contact has already been made use their social networks to refer the researcher to other people who could potentially participate in or contribute to the study. Snowball sampling is often used to find and recruit "hidden populations," that is, groups not easily accessible to researchers through other sampling strategies.

ከዚህ በላይ እንደተጠቆመው፤ በተመራማሪው የማይታወቁና በማኅበረሰቡ የሚጠቆሙ መረጃ ሰጪዎችን በማካተት፤ የባህል ሕክምና ልምድ፣ እድሜ፣ ማኅበራዊ ደረጃ፣ የሥራ መስክ እና ሙያን መሰረት በማድረግ ተለይቷል፡፡ በዚህ መነሻነትም፤ የመረጃ ሰጪዎች ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ ምርጫ፣ ልምድ፣ ተባባሪነት እና በዕድሜ በገፉት የባህል ሐኪሞች ላይ ልዩ ትኩረት ተደርጓል (ለምን? የሕይወት ልምድና ተግባራቸውን፤ የዘመን ለውጥና ታሪካዊ ሁነቶችን ለመገንዘብ ሲባል፤ ከሰባ ዓመት በላይ የሚገኙ ባለሙያዎችን አካቷል)፡፡

ከቦታ አንጻር፡- የደቡብ ጎንደር ዞን፤ አካባቢያዊ መልክዓ ምድርን (ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ ቦታዎችን) መነሻ በማድረግ ሶስት ወረዳዎች ተለይተዋል፡፡ በሶስቱም ወረዳዎች 114 (በፋርጣ 43፣ በሊቦ ከምከም 34፣ በእብናት 37) ቀበሌዎች የሚገኙ ሲሆን፤ ለዚህ ጥናት መረጃ የሰጡ የባህል ሐኪሞች የሚገኙባቸው 16 ቀበሌዎች (ፋርጣ፣5፤ ሊቦ ከምከም፣ 6፤ እብናት፣5) የጥናቱ አባልና አካል ተደርገው ተካተዋል፡፡ ከነዚህ ቀበሌዎች 27 የባህል ሐኪሞች፤ 9 የባህል መድኃኒት ተጠቃሚዎች፤ 3 የባህል ሕክምና ተጠቅመው የማያውቁ ግለሰቦች፤ 9 የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች፤ 19 የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሽማግሌና እናቶች፤ 4 የግብርና እና የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች፣ 5 የዞንና የወረዳ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች፤ በድምሩ 76 መረጃ ሰጪዎች ተሳትፈዋል፡፡ የመረጃ ሰጪዎች እድሜ ከ24-95 ዓመት ባለው ክልል ውስጥ ይገኛል፡፡ ጥናቱ፤ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ሃይማኖትና ብዛት ፣ አሰፋፈርና ተደራሽነት፣ የጥናቱ ተሳታፊና ታላሚ አባላትን (የባህል ሐኪሞችን) እንደ መነሻ ጉዳይ እና አስገዳጅ ሁነት በመውሰድ፤ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ላይ ብቻ (በአማካይ በሶስቱም ወረዳዎች 98% ይሸፍናል፤ ምዕራፍ አራት የሥነ ሕዝብ መረጃን ልብ ይሏል) ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

የባህል ሐኪሞችን ልምድ፣ እድሜና ማኅበራዊ ደረጃን በማጤን 15 ዋና መረጃ ሰጪዎች፤ 12 ደግሞ በአጋዥ መረጃ ሰጪነት ተለይተዋል። ለንጥል ጥናት ከባህል ሐኪሞች አራት ከታካሚ ሶስት በድምሩ ሰባት አባላት፤ በተተኳሪ ቡድናዊ ውይይት፤ አንድ ከባህል ሐኪሞች፣ አንድ ከዘመናዊ ሕክምና፣ ሁለት ከአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት የሃይማኖት አባቶች፣ አባትና እናቶች በድምሩ አራት ተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካሂዷል። እያንዳንዱ ቡድን ከአምስት እስከ ሰባት ተወያይ አባላትን አካቷል። የቡድን አደረጃጀቱም የመረጃ ሰጪዎችን የሙያ መስክ እና የጥናቱን ይዘት መነሻ በማድረግ ተመርጠዋል። የመረጃ ሰጪዎች አመራረጥ ሂደትም የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ፣ የመረጃ ሰጪዎችን ሙያና ልምድ፣ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛና ተባባሪ የሆኑ፣ በመስኩ ዕውቀትና መረጃ አላቸው የሚባሉ (በአጋዥ ጠቋሚ) እና ከማኅበረሰቡ ጋር በሚኖረኝ ግንኙነት የተሻለ የገለጻና የማስረዳት ብቃት ያላቸውን ታሳቢ በማድረግ፤ የመስክ መረጃ ተሰብስቧል፤ ጥናቱም ተካሂዷል። ምን ዓይነት ጥያቄዎች ለነማን መረጃ ሰጪዎች ቀረቡ? ለሚለው አባሪ ሁለትን ልብ ይሏል።

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃር እና ትንተና

በዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃሮች[39] እንዴት ተግባራዊ ተደረጉ? ምን ዓይነት መረጃዎች በየትኛው አንፃር ከመስክ ተሰበሰቡ/ተተነተኑ? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል። በጥናቱ ሂደት፤ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች በውስጣዊ (emic/insider) እና በውጫዊ (etic/out-sider) አንፃርና ዕይታዎች ተሰብስበዋል። በውስጣዊ ዕይታ (emic/insider)፤ ውስን ቦታ፣ ማኅበረሰብ፣ ርዕሰ ጉዳይ፣ አካባቢያዊ ሁነትና ዐውድን መነሻና መሰረት በማድረግ፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ የሕመም መንስኤ እሳቤ፣ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማ፣ አሰጣጥና መመሪያ፣ አካባቢያዊ ልማድ፤ ለሥነ ምህዳር ጥበቃና መራቆት ያለውን ሚና፤ ፈትሿል። በዚህ ሂደት ኢትኖግራፊያዊ የመስክ ቆይታና ተመክሮን ታሳቢ በማድረግ፤ ከተመራማሪው አንፃር፤

[39]የመስክ መረጃዎች ሲሰበሰቡ፤ ዐውድ ተኮር ክዋኔዎች ሲደራጁ፣ ውስጣዊ (emic/insider) እና ውጫዊ አንፃር (etic/out-sider) ግምት ውስጥ ገብተው መረጃ መሰብሰብ እንዳለበት ይገልጻሉ (ፈቃደ፣ 1991፤ Schoemaker, 1990)። በተለይ ተመራማሪው የባህሉ አካል ከሆነ እንደውስጣዊ አባል መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘትና ከማኅበረሰቡ ለመግባባት መልካም ቢሆንም ንዑስና ጥቃቅን እንቅስቃሴና ተግባራትን ሊዘነጋ ይችላል፤ በአንጻሩ የውጭ ተመልካች ሲሆን ንዑስና የተለዩ ጥቃቅን እንቅስቃሴዎችን ሲያጋጥሙ በትኩረት ማየት፣ መጠየቅና መመዝገብ ቢችልም ማኅበረሰቡን በቀላሉ ለመግባባት፣ የባህሉን ሥርዓትና ተግባር በውል ለመለየትና በቅጡ ለመረዳት እንደሚቸገር ጠቁመው፤ ሁለቱን አንፃሮች ተገንዝቦ በአግባቡ መጠቀም ተገቢ መሆኑን የመስኩ ምሁራን ይመክራሉ (Schoemaker, 1990: Hammersley & Atkinson, 2007)። እንደ Ben-Amos (1975; PP.165-167) መረጃ፤ በአፍሪካ የሚካሄዱ የኢትኖግራፊ ጥናቶች የማኅበረሰቡ እሳቤ፣ ምድብ፣ ይዘትና ማሕቀፍን ተከትለው፤ መቅረብና መተንተን እንዳለባቸው መክረዋል።

ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር በቋንቋ መግባባት፤ አካባቢያዊ ዕሴቶችን እና ልማዳዊ ሥርዓቶችን መገንዘብ፤ እንደውስጣዊና የራሱን ባህል እንደሚያጠና ባለሙያ ይታሰባል።

እንደ Ben-Amos (1997) ገለፃ፤ የመስክ መረጃ መተንተን ያለበት የባህሉ ባለቤቶች በሚሰጡት ፍች፤ መረጃዎቹ ከተሰበሰቡበት ማኅበረ-ባህላዊ ዐውድ የመነጨ መሆን እንዳለበት ነው። በሌላ የጥናት መጽሔታቸው"Folklore in African Society" በሚል ርዕስ በአቀረቡት ሥራ የማኅበረሰቡን እሳቤ፣ ምድብ፣ የአዕምሮ ብስለት "Cognitive" ተከትሎ የመስክ መረጃዎችን መተርጎም፣ መተንተን፣ ይዘቱን ከባለቤቶቹ ድምጽ (voice) እና እሳቤ አንጻር መመርመር፤ የማኅበረሰቡን ፍልስፍና ለማጤን፣ ሥርዓትና ተግባሩን ለማወቅ፤ ትክክለኛ መንገድና ስልት መሆኑን ይመክራሉ (Ben-Amos, 1975; PP.167-175)።

ከምርምሩ ይዘትና ትኩረት አንጻር ደግሞ፤ አካባቢያዊ ዕውቀትን፣ ልማዳዊ ሥርዓትን፣ ዐውዳዊ ሁነትን፣ እይታና ተግባርን መርምሮ፤ የሕመም መንስኤ እሳቤዎችን፤ መከሰቻ ዐውዶችን፤ አካባቢያዊና ልማዳዊ የምርመራ ዘዴዎችን፣ የጤና ሚዛን ማስተካከያ ስልቶችን፤ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሥርዓተ ገቢሮችን፣ ማስተካከያ ዐውዳዊ ሁነቶችን፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔዎችን፤ እምነታዊና ሃይማኖታዊ እሳቤዎችን መተግበሩ፤ በውስን ቡድንና ዐውድ ላይ ተመስርቶ ጥልቅና የተብራራ አካባቢያዊ እሳቤ፣ ዕውቀትና ክዋኔን በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በንጥል ጥናት እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የመስክ መረጃዎችን ሰብስቦ መተንተኑ፤ በውስጣዊ እይታ፣ አካባቢያዊ ዕውቀትና ተግባር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ይገልፃል።

ከውጫዊ ዕይታ (etic/out-sider) አንፃር፤ ተመራማሪው ሣይንሳዊና ዓለም አቀፋዊ የምርምር ስልትና ዘዴዎችን በመከተል፤ የአካባቢውን ዕውቀትና ተግባር ሰብስቦ፣ በይዘት መድቦ፣ አደራጅቶ፤ ጽንሰ ሃሳቦችን እና ንድፈ ሃሳቦችን በማቀናጀትና በማስተሳሰር ተንትኖ ሣይንሳዊ የምርምር ሥራ ማዘጋጀቱን ይመለከታል።

ከምርምሩ ሂደት አንፃር ደግሞ፤ ከአካባቢያዊ ዕውቀት፣ ተግባር፣ ዐውድና ይዘት ባሻገር የሰው ልጆች የሚጋሯቸው ዓለማቀፋዊ ሁነቶች እና ዕውነታዎች በምርምሩ ሂደት ተገኝተዋል። ለምሳሌ:- የመድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች፤ የበሽታዎች ምልክት፣ ባሕርይ፣ የሚያደርሱት ጉዳትና የሚያጠቁት የሰውነት አካል ዓለማቀፋዊ ይዘትና ተግባር እንዳለው፤ መገንዘብ ተችሏል። በአጠቃላይ ሁለቱን አንፃሮች በማስተሳሰር፤ እንደውስጣዊ ሁነት የራሱን ባህል እንደሚያጠና እና እንደውጫዊ አንፃር ደግሞ ሣይንሳዊ የምርምር ስልቶችን በመከተልና በመተግበር፤ ምርምሩ ተካሂዷል።

## 3.5 የጥናቱ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች

በዚህ ጥናት፤ ከካልዓይና ከቀዳማይ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ሲሰበሰቡ፣ ሲደራጁ እና ሲተነተኑ የመረጃዎቹን ይዘት መሰረት በማድረግ፣ የምርምር ሙያ፣ ሥነ ምግባራዊ ደንብና መርህን በመከተል ተግባራዊ ተደርጓል። የመስክ ምርምር ሲካሄድ፤ የማኅበረሰቡን ባህል ማክበር፣ የጥናቱን ዓላማ በግልፅ ማስተዋወቅ፣ ለመረጃ ሰጪዎች ተገቢውን ትህትና ማሳየት፣ መግባባት፣ ክብር መስጠት፣ ምስጢር መጠበቅ፤ እንደሚገባ (Dawson, 2009; PP.152-154: Blaxter, Hughes and Tight, 2006) ይመክራሉ።

ይህ ጥናት የባህል ሕክምና ዕውቀት (ተግባር፣ ሥርዓት፣ ክዋኔ፣ እምነት) እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር መረጃዎችን ከመስክ ሰብስቧል። በምን ዓይነት ሥነ ምግባር የመስክ መረጃዎች ተሰበሰቡ? እንዴት ተደራጁ? ምን ዓይነት ጥንቃቄና ፈተናዎች ነበሩ? የመረጃ ሰጪዎች ምስጢር እንዴት ተጠበቀ? ጥብቅና ጠንካራ የሥነ ምግባር መርሆዎችን ለመከተል ምን አስገዳጅ ሁነቶች ነበሩ? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ተሰጥቷል።
የጥናቱ ባሕርይ፣ ተግባርና ይዘት፤ ከመድኃኒት ቅመማ፣ ከጤና፣ ከበሽታ፣ ከግለሰብ ሕይወት፣ ከእምነት፣ ከሃይማኖት እና ከሥነ ምህዳር ጉዳዮች ጋር የተገናኙ ይዘቶችን ተመልክቷል። እነዚህ ጉዳዮች ውስን በሆኑ የባህል ሐኪሞች የሚተገበሩ፤ የዕውቀት፣ የኃይል፣ የገቢ ምንጭ እና መተዳደሪያ ሲሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከመድኃኒት ቅመማ፣ አሰጣጥ፣ አተገባበርና ሥርዓት መዛነፍ ጋር በተገናኘ ለሕመም መንስኤ እና ለሰው ሕይወት መጥፋት ምክንያት እንደሚሆኑ የመስኩ ባለቤቶችና ተመራማሪዎች ይመክራሉ (መሪጌታ ባሕረጥበብና መሪጌታ ስዩም፣ ቃ.መ፤27/02/2011 ፋርጣ እና 04/02/2011 እብናት በቅደም ተከተል፤ Wondwosen, 2006: ተመስገን፣ 2003፤ ዐቢዩ፣ 2010)። የሥነ ምግባር ጉዳዮች ከመስክ ተመክሮ እና ከመረጃ ሰጪዎች አንጻር እንደሚከተለው ተግባራዊ ተደርጓል።

### የሥነ ምግባር ጉዳዮች ከመስክ ተመክሮ አንጻር

በዚህ ጥናት ርዕስ ጉዳይ ምርምር ከማካሄዱ በፊት ሙያው የሚጠይቀውን ዝግጅትና የሥነ ምግባር መርሆዎችን በማሟላት ወደ መስክ ተገብቷል። መጀመሪያ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከአማርኛ ቋንቋዎች፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ፤ ከደቡብ ጎንደር ዞን ፖሊስ ጣቢያ ፀጥታና ደህንነት፣ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ ከአማራ

ክልል የባህል ሐኪሞች ፕሬዚዳንት ተጨማሪ የትብብር ደብዳቤዎችን በማጻፍ የመስክ ስምሪት ተካሂዷል።

በመስክ ስምሪት ወቅት፤ የፎክሎር ተማሪ[40] የነበሩ ባለሙያዎችን ጥናት በማካሂድባቸው ወረዳና መስሪያ ቤቶች ማግኘቴ፤ የመስክ ጉዞዬን በታቀደው ጊዜ፣ ቦታና ወቅት ለመተግበር፣ በተደራጀና ሥርዓት ባለው መልኩ መረጃዎችን በየቦታው ተንቀሳቅሼ ለመስራት፤ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ለመተዋወቅ፣ ልማድና መስተጋብሩን ለመለየት፤ ከአካባቢው የባህል ሐኪሞች ጋር በቅርበት ለመተዋወቅ፣ ቤተሰባዊ ግንኙነት ለመመስረት ጉልህ ሚና ነበራቸው።

በሁለተኛ ደረጃ የአማራ ክልል የባህል ሐኪሞች ማኅበር ፕሬዚዳንት (ሃጂ ሼህ ዓሊ ዓደም)[41] እና ጸሐፊ (መሪጌታ ብሩህ ዘላለም) በየወረዳው የሚገኙ የባህል ሐኪሞችን ደውለው መረጃ በማስተላለፍና በማስተዋወቅ፤ የትብብር ደብዳቤ በመጻፍ፣ በየአካባቢው የሚገኙ የባህል ሐኪሞችን አድራሻና መገኛ ቦታ በመስጠት፣ ልምድ ያላቸውን የባህል ሐኪሞች በመምረጥ፤ ከጥናት አቅራቢው በተጨማሪ በዘርፉ የሚካሄደው ጥናት ለባህል ሕክምና ግብዓት ፋይዳ እንዳለው ለመሰል ጓደኞቻቸው በማስረዳት፤ የሙያውን ምስጢር ጠብቄ መረጃ እንደምሰበስብ እና የአማራ ክልል የባህል ሐኪሞች ማኅበር አባልና አካል[42] መሆኔን በመግለጽ፤ በየአካባቢው ከሚገኙ የባህል ሐኪሞች ጋር በቀላሉ ለመግባባት፣ ቀጣይ ግንኙነት ለመመስረት፣ መልእክት ለማድረስና ለመለዋወጥ፣ ቤተሰባዊ ግንኙነትን ለማጠናከር እድል ፈጥሮልኛል።

---

[40]አቶ አበበ ጋሻዬ በሊቦ ከምከም ወረዳ የአዲስ ዘመን ከተማ ባህልና ቱሪዝም ኃላፊ፤ አቶ አራጋው ዘውዴ የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ፤ አቶ ሰሎሞን ካሳ የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ፤ አቶ አዲሱ አዝመራ እና አቶ ዐባይነህ አድማስ የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ፤ ለዚህ ጥናት በምንቀሳቀስበት ቦታ አብረውኝ በመሆን በየአካባቢያቸው የሚገኙ የባህል ሐኪሞችን፣ የአካባቢውን ባህል እና እምነት ያውቃሉ የሚባሉ ግለሰቦችን በማገናኘት፤ በጽሑፍ የተዘጋጁ የቢሮ ሰነዶችን፣ ካርታዎችንና መሰል መረጃዎችን አዘጋጅቶ በመስጠት ትብብር አድርገዋል (በመስኩ ያደረጉት አስተዋጽኦ በመስክ ተመክሮ ክፍል ወደፊት በስፋት የሚጻፍ መሆኑን ልብ ይሏል)።

[41] አሁን የኢትዮጵያ ባህላዊ መድኃኒት ሕክምና አዋቂዎች ማኅበር ፕሬዚዳንትሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

[42]በምን መስፈርትና ሙያ የማኅበሩ አባል መሆን ቻልክ? ማኅበሩ በባህል ሕክምና ዘርፍ ምርምር ለሚያካሂዱ እና የረጅም ጊዜ ልምድና ተመክሮ (ከስድስት ዓመት በላይ) ያላቸውን የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ምሁራንን አባል በማድረግ የዘርፉ ጥናት እንዲበረታታ በሃሳብ እና መረጃ በመስጠት እገዛ ያደርጋሉ። የዚህ ጥናት አቅራቢም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በዐባይ ምርምር ማዕከል የአገር በቀል ዕውቀት ንዑስ ዘርፍ አስተባባሪ በመሆን በባህል ሕክምና ዘርፍ በክልሉ ጤና ቢሮ፣ በዩኒቨርሲቲና በአማራ ክልል የባህል ሐኪሞች ማኅበር ስብሰባዎች ላይ በመጋበዝ ውይይቶችን እንድከታተል፤ በዘርፉ የሚካሄዱ ጥናቶችን ለማሰባሰብ፣ የዘርፉን ተግዳሮት እና የጥናት ክፍተት ለመለየት እድልና አጋጣሚ ፈጥሮልኛል (አነሳሽ ምክንያትን ልብ ይሏል)።

## የሥነ ምግባር ጉዳዮች ከመረጃ ሰጪዎች አንጻር

የፎክሎር ተመራማሪ በተለይ ከባህል ሕክምና፤ ከእምነት፣ ከሃይማኖት፣ ከአምልኮ ሥርዓት ጋር የተገናኙ ተግባራት በሥርዓት ካልተመሩ፣ በአግባቡ ካልተያዙ ማኅበረሰቡን በቀላሉ ለማስቆጣትም ሆነ መረጃ ለማሳጣትና ምርምሩን ለማቋረጥ ምክንያት እንደሚሆኑ ምሁራን ይመክራሉ (Schoemaker,1990: Mack, and et al, 2005, PP51-52; Hammersley and Atkinson, 2007: Creswell, 2014)። የዚህ ጥናት አቅራቢም ርዕሰ ጉዳዩን ለመረጃ ሰጪዎች በግልፅ በማስረዳት፤ በፍላጎታቸው መረጃ እንዲሰጡ፤ የሚሰጡት መረጃ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀና ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ የሚውል መሆኑን በማሳወቅ ቀጣይ ግንኙነት በመመስረት የፈቀዱትንና ይሁንታ የተገኘባቸውን መረጃዎች ብቻ በማስታወሻ ደብተር በመጻፍ፣ ፎቶ ግራፍ በማንሳት፣ በመቅረጸ ድምጽ እና በቪዲዮ ድምጽና ምስላቸውን በመቅዳት፣ የዕፅዋት ግብዓቶችን ናሙና በመውሰድ ለጥናቱ ግብዓት እንዲውሉ ተደርጓል።

ከበሽታ፣ ከጤና፣ ከግለሰብ ሕይወት እና ከማኅበረሰብ እምነት ጋር የተገናኙ ምርምሮች ልዩ ትኩረት፣ ጥንቃቄና ምስጢራዊ በሆነ መልኩ መቅረብ እንዳለባቸው የመስኩ ምሁራን ጠቁመው፤ ስም መቀየር፣ ኮድ መስጠት የተለመደ፤ ሙያዊ ሥነ ምግባር መሆኑን ያስረዳሉ፤ ይመክራሉ (Oring, 1986: Mack, and et al, 2005;P.8, 16, 29,51: Hurreize, 2006)። በዚህ ጥናት በተለይ፤ ለንጥል ጥናት የተመረጡ ታካሚዎች ፎቶ ግራፍ፣ ስም እና መሰረታዊ አድራሻዎች ኮድ በመስጠት እና ስም በመቀየር የመስክ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

አስረጅ አንድ፡- የባህል ሐኪም አቶ ደሴ በኮከብ ቆጠራ ሂደት፤ የታካሚያቸውን የሕመም መንስኤ፣ መለከፊያ ቦታ፣ የታካሚውን ኮከብ ባሕርይ ሲገልጹ፣ ሲያስረዱና ሲያነቡ በንጥል ጥናት ሂደት መረጃ ተሰብስቧል። የታካሚን የግል ምስጢር፣ ደህንነት፣ የምርምሩን ሙያዊ ሥነ ምግባር ለመጠበቅ ሲባል የታካሚ ስምና አድራሻ በምስጢርና ኮድ በመስጠት መረጃው ተተንትኗል። ከዚህም በተጨማሪ አጋንንት ሲያስለፈልፉ፣ ርኩስ መንፈስ ሲያስወጡ እና መለኮታዊ ተግባራትን ሲፈጽሙ እስከ ፈቀዱት መረጃ ድረስ በቪዲዮ ለመቅረጽ ተሞክሯል። እነዚህ መረጃዎች ለተመራማሪው ግብዓት ቢሆኑም የታካሚን ሥነ ልቡና ስለሚጎዱ ፎቶ ግራፍ፣ ስምና ግላዊ መረጃዎች በግልጽ አልተካተቱም። በአንጻሩ በዐውዱ ላይ የተገኙ መረጃዎችን ኮድ በመስጠትና ስም በመቀየር ከዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ማስተሳሰር ተችሏል።

እስረጅ ሁለት፡- የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ለሕክምና ግብዓትና መድኃኒት የሚጠቀሟቸውን ይዘቶች ሲያስረዱ፤ በማኅበረሰቡ "ነውር" የሚባሉ ተግባራት በምስጢር እንዲያዙ፤ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት፣ ከነፍሳትና ከማዕድናት የሚዘጋጁ የመድኃኒት ግብዓቶች በሃይማኖት የሚከለከሉ፣ የማይበሉ፣ የማይጠጡ እና "ርኩስ" መሆናቸው ታምኖ በማኅበረሰቡ የተወገዙ ግብዓቶች በምርምሩ ይዘት እንዳይንፀባረቁ ጥረት ተደርጓል። ይህን ክፍተት ለመሙላት የተፈጥሮ ባሕርይ መተንተኛ ሞዴልን በመጠቀም፤ የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የማዕድን እና የነፍሳት ባሕርይ ሥር መሰረት በመለየት፤ ክፍተቱን ለመሙላት ተችሏል። ለምሳሌ፡- የዕፅዋትን መሰረታዊ ጣዕም ከተፈጥሯዊ ባሕርይ ይዘታቸው ተግባርና አገልግሎታቸውን መለየት ይቻላል። ጣፍጭ፣ ለስላሳ፣ መራራ፣ ጎምዛዛ፣ አቃጣይ ወይም ለብላቢ ባሕርይ አላቸው። የመጣፈጥና የመለስለ ጣዕም ያላቸው ዕፅዋት የሕመም መንስኤ፤ የመጎምዘዝ፣ የማቃጠልና የመምረር ባሕርይና ጣዕም ያላቸው ለሕክምና አገልግሎት እንደሚውሉ፤ የመስክ መረጃ ትንታኔ ይዘት ምዕራፍ አምስትን ልብ ይለዋል (ለተጨማሪ መረጃ 3.6.3 የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴልን ይመልከቱ)።

## 3.6 የመረጃ አደረጃጀት እና መተንተኛ ሞዴል

የመስክ መረጃዎች እንዴት ተደራጁ? ምን ዓይነት መረጃዎች ተሰበሰቡ? የመረጃዎቹ ምንጭ በዋናነት እነማን ነበሩ? የመስክ መረጃዎቹ ይዘት ምን ነበር? በምን ሞዴል ተተነተኑ? ሲባል፤ እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል።

ይህ ጥናት ዓይነታዊ እንደመሆኑ መጠን፤ በተሳትፏዊና በዕሞናዊ ምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ ቡድን ውይይት እና በንጥል ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በዓይነትና በይዘት መድቦ የመስክ ትርጎማና ትንተና ተካሂዷል። የመስክ መረጃዎችን ለመተንተን የተመረጠው ዘዴ ገላጭ እና የይዘት ትንተና (Content analysis) ሲሆን፤ በመረጃዎቹ መካከል የሃሳብ ዝምድና እና የባሕርይ መመሳሰልን በመመርመር የዕውቀቱን መሰረትና ማሕቀፍ ማደራጀት ተችሏል። በአደረጃጀቱ ሂደት የጋራ የሆነ ምድብ/ልክ (Pattern) በማውጣት በባሕርይ፣ በጣዕም፣ በተግባር፣ በዝምድና የሚገናኙበትን ዐውድ በመለየት "ማዋገን" ተችሏል። በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት፣ በሕመም፣ በወቅቶች፣ በሥነ ምህዳር ውስጥ ያለውን ሁነት፣ ተፈጥሯዊ እሳቤና ተግባር በመመርመር፤ እነዚህ ሁነቶች የሚከሰቱበትን እና የሚተነተኑበትን ተፈጥሯዊ ባሕርይ መነሻ በማድረግ ተተንትነዋል። ምን ዓይነት መረጃዎች በየትኛው የመስክ ጉዞ ተደራጁ? ሲባል፤

በመጀመሪያ ዙር ጉዞ፤ ለጥናቱ በተመረጡ ወረዳዎች በመገኘት የባህል ሐኪሞችን መተዋወቅ፣ ዓላማና ጉዳይን ማስተዋወቅ፣ ማስረዳትና ይሁንታ ማግኘት፤ በቅኝት ወቅት የተገኙ መረጃዎችን መሰብሰብ፤ በሁለተኛ ዙር ጉዞ በየወረዳዎቹ (ለጥናት በተመረጡ) በመሰማራት፤ ከባህል ሐኪሞች እና ከማኅበረሰብ አባላት ጋር በመገናኘት፤ ስለሕመም መንስኤ፣ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ክዋኔዎች እና የሥነ ምህዳር ጉዳዮች በዝርዝር ተነስተው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

በሶስተኛ እና በአራተኛ ዙር ዋና ዋና የሚባሉ ርዕሰ ጉዳዮችን (የሕመም መንስኤ፣ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማ ክዋኔ እና ሥነ ምህዳር) በመለየት ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና ንጥል ጥናት ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ አጋዥ እና አካል የሆኑ ተጨማሪ መረጃዎች ከዞንና ከወረዳ ተሰብስበዋል፡፡ የምርምሩን ማዕከላዊ ይዘትና የመስክ መረጃዎችን መነሻ በማድረግ፤ ለዘመናዊ ሕክምና፣ ለባህልና ቱሪዝም፣ ለግብርና ባለሙያዎች ቃለመጠይቅ ቀርበዋል፡፡ በአምስተኛ ዙር የመስክ መረጃዎችን በዓይነትና በይዘት ተመድበው፤ የምርምሩ ጭብጦች ተለይተው ተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካሂዷል፡፡ በጥናቱ ሂደት የመረጃዎቹን ዓይነት፣ ባሕርይ፣ ይዘት፣ ምድብና መዋቅር በማውጣትና በማደራጀት ትንታኔ ቀርቧል፡፡ የምርምር ጥያቄዎችና የትንታኔ ምዕራፎች ትስስር ምን ይመስላል?

ይህ ጥናት፤ የምርምሩን አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ እና አንኳር ጥያቄዎችን ታላሚ በማድረግ፤ ርዕሰ ጉዳይን እና ማዕከላዊ ጭብጥን አጉልቶ ለማሳየት የምርምሩ ትንታኔ ክፍል በአራት ምድብ ተደራጅቶ ቀርቧል (ከምዕራፍ አምስት እስከ ስምንት)፡፡ በመጀመሪያው ትንታኔ ክፍል የሕመም መንስኤ እሳቤዎች ተነስተው ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡ የመስክ መረጃዎችም፤ ከባህል ሐኪሞች፣ ከአካባቢው ሃይማኖት አባቶች፣ ሽማግሌና እናቶች፣ ከጤና እና ከተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች ተሰብስበዋል፡፡ በምርምሩ ሂደት የሕመም መንስኤ ዕሳቤን የሚያስረዱ በፈጠራዊ ሚት (Creation Myth)፣ በቃል ግጥም፣ በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በግለሰብ የሕይወት ተመክሮ እና ዕሳቤ ላይ የተመሰረቱ ገለፃዎች በጥናቱ ይዘት ተካተዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች በዐውድ ተኮር እና በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል ተተንትነዋል፡፡

በምዕራፍ ስድስት ትንታኔ ይዘት፤ የበሽታ መለያ እና መመርመሪያ ዘዴዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች በዋናነት ከባህል ሐኪሞች የዕለት ተግባር፣ ዕውቀት እና የሕይወት ልምድ ጋር የተገናኙ ሲሆን አካባቢያዊ ልማድን መነሻ በማድረግ ገለፃ ሰጥተዋል፡፡ የባህል ሐኪሞቹ የጋራ ዕውቀትና ተግባር ምን ነበር? ሲባል፤ የሕሙማንን አካላዊ ቁስልና መንፈሳዊ ጭንቀት ለመለየት

በዋናነት የታካሚን የሕይወት ታሪክ በመጠየቅ፣ ዕይታዊ፣ ክሊኒካዊ እና ባዮሎጂካዊ ምርመራ ማካሄዳቸው፤ የበሽታዎችን ባሕርይ ምድብ በማውጣትና በመለየት ድንገተኛ እና አጣዳፊ (ተቅማጥ፣ ትውከት)፤ ቆንጣጭና ሰርሳሪ (ኪንታሮት፤ ነቀርሳ)፤ አቃጣይና አስለፍላፊ (የወፍ/የጉበት እና የወባ በሽታ)፤ አንቀጥቃጭና አርገብጋቢ (ነርቭ እና ዳፍንት/ የሚጥል በሽታ)፤ አደንዛዥ እና አወፋሪ (ዝሆኔ፤ ጋንግሪን)፤ አብራጅና አድካሚ (ስንፈተ ወሲብ፣ ኩላሊት) መተግበራቸው፤ የተቃርኖ ሕክምናን መከተላቸው (ለሚያሳብጥ ሕመም የሚያላላ መድኃኒት)፤ የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶችን መፈፀማቸው፤ የመስክ መረጃዎች በባህል ተኮር፣ በዐውድ-ተኮር እና በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴሎች እንዲተነተኑ ምክንያት ሆነዋል፡፡

ምዕራፍ ሰባት የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ክዋኔዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች በዋናነት ከባህል ሐኪሞች የተሰበሰቡ ሲሆን የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሥርዓተ ገቢር ዐውዳዊ ክዋኔ፤ ሥርዓተ ገቢር ማስፈፀሚያ ዐውዳዊ ስልቶች፤ የመድኃኒት ቅመማ ዓይነትና ባሕርይ፤ የቅመማ ሂደት፤ የመድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ ሥርዓቶችን በመከተል፤ "በወል" ዕውቀትና ተግባራቸው ላይ በማተኮር በዐውድ-ተኮር ክዋኔ እና በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴሎች ተተንትነዋል፡፡ የዕፅዋትን ዓይነትና ባሕርይ ለመለየት በአፍንጫ ማሽተት፣ በምላስ መቅመስ፣ በዓይን ማየት እና በሥሜት ኅዋሳት ማረጋገጥን፤ የዕፅዋት ባሕርይ ምድብን (ጣፋጭ፣ መራራ፣ አቃጣይና ዉኃማ) በመከተል ተግባራቸውን መለየት፤ ለየትኛው የበሽታ ባሕርይ ምድብ እንደሚሰጡ በማጤን የመስክ መረጃዎች ተደራጅተውና ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ ስምንት፤ የባህል ሕክምና እና የማኅበረሰብ ልማድ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አስተዋፅኦ አላቸው? በሚል የመስክ መረጃዎች ከባሕል ሐኪሞችና ከአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት ተሰብስበው፤ በባህል ተኮርና በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴሎች ተተንትነዋል፡፡

በክዋኔ ዐውድ የተሰበሰቡ ዝርዝር የመስክ መረጃዎች ወደ ትንታኔ ሲሄዱ በጋራ ባሕርይ፤ ምድብ እና ማሕቀፍ ገላጭ በሆኑበት ዐውድ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ለአብነት ያህል፡- ለኮሶ መድኃኒት አዘገጃጀት፣ ቅመማና አሰጣጥ አስራ ሶስት ክዋኔዎች ተመዝግበዋል፡፡ 1ኛ. የዕፅዋት ፍሬን ቆልቶና በምጣድ አምሶ በመስጠት፤ 2ኛ. የዕፅዋት አበባን አድርቆና ወቅጦ በዉኃ በጥብጦ በማጠጣት፤ 3ኛ. የዕፅዋት ሥር አድርቆ፣ ወቅጦ፣ አጣርቶ፣ በዱቄት መልክ አዘጋጅቶ፤ በኑግና በቀይ ጤፍ ቂጣ ለውሶ በማብላት ይከወናል (አባሪ ስድስትን ልብ ይሏል)፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በክዋኔ ይዘት የቀረቡ ንዑስ አስረጂዎች በዋናነት ሥነ ምህዳርን፣ ግለሰብና የአንድ አካባቢ ቡድን ዕውቀት ገላጭ ከመሆን ባለፈ፤ የባህል ሕክምናን ሙሉ ተግባር፣ ዕውቀትና

ማሕቀፍ አያመለክቱም፡፡ ይህን ክፍተት በማጤን ጥቅል አተያይና ማሕቀፍ መከተልና መተግበር ተመራጭ እንደሆነ (ምዕራፍ ስምንትን ልብ ይሏል) ይታመናል፡፡

በዚህ ጥናት የመስክ መረጃዎቹን የጋራ ባሕርይ በመለየት "የተፈጥሮ ባሕርይ" ሞዴል የሚባል መተንተኛ ስልት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ ምርምሩ የ"ኢትኖግራፊ" ይዘትን (ባህል ተኮር ማብራሪያ ሞዴል እና ዐውድ ተኮር ክዋኔን) በመከተል፤ የመተንተኛ ሞዴሎችን በማስተሳሰር የመስክ መረጃዎችን ተንትኗል፡፡ የባህል ተኮር ማብራሪያ ሞዴል ትኩረት የሐኪም እና የታካሚን መስተጋብር በመፈተሽ፤ ለጤና፣ ለበሽታ፣ ለምርመራ፣ ለሕክምና… ያላቸውን ተግባር፣ ግንዛቤ እና እሳቤን መርምሯል፡፡ ዐውድ ተኮር ክዋኔ ደግሞ የባህል ሐኪሙ ዕፀ መድኃኒት እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ ለምን፣ ለማን፣… እንደሚያዘጋጅና እንደሚቀምም፣ እንዴት እንደሚቆርጥ፣ ምን ዓይነት ገቢር እንዳለው ሂደቱን በዝርዝር እና ደረጃ በደረጃ እየገለፀ ተግባርና ሥርዓቱን አስረድቷል፡፡
የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል ዐቢይ ጉዳይ፤ የሰው፣ የዕፀዋት፣ የእንስሳት፣ የበሽታ፣ የሥነ ምህዳር የተፈጥሮ ባሕርይ ሥር መሰረትን በመለየት ትንታኔ ቀርቧል፡፡ ማንኛውንም ጉዳይ፣ ይዘትና ድርጊት በያዘው ባሕርይ፣ በሚኖረው ስሜት፣ ባለው ጣዕም፣ ተመሳስሎና ተቃርኖ፣ የወቅት መፈራረቅ፣ የሕመም ባሕርይን፤… በመከተል ማብራሪያ፣ ትዕምርት፣ ምክንያትና ገለጻ መስጠት ላይ አተኩሯል፡፡ እነዚህን ሞዴሎች ከፅንሰ ሃሳብ፣ ከንድፈ ሃሳብ እና ከመስክ መረጃ ይዘቶች ጋር በማስተሳሰር፣ በማዛመድና በማዋሃድ ትንታኔ ቀርቧል፡፡

በዚህ ጥናት ጥቅል አተያይን (Holistic View) በመከተልና በመተግበር፤ የመስክ ተግባራትን በይዘት፣ በዓይነት እና በባሕርይ ለይቶ በማደራጀት፤ የመረጃዎቹን የጋራ ባሕርይ፣ ተግባር፣ ዕውቀት እና ማሕቀፍን እንደ መምረጫ መስፈርት በመውሰድ ትንታኔ ቀርቧል፡፡ ምርምሩ ጥቅል አተያይን ተግባራዊ በማድረግ የባህል ሕክምና እና የሥነ ምህዳር መስተጋብርን በመመርመር፤ የሕመም መንስኤን፤ የምርመራ ዘዴዎችን፤ የመድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ዐውዳዊ ክዋኔዎችን ፈትሾ የዕውቀት ማዕቀፎችን አዘጋጅቷል/አደራጅቷል፡፡ በዚህ ባሕርይው ከቀደምት (በዚህ ይዘት ከተዳሰሱ) ጥናቶች በእጅጉ ይለያል፡፡ የሞዴሎች ትኩረትና ዝርዝር ተግባር እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

### 3.6.1 ባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል

Kleinman፤ ባህል-ተኮር ማብራሪያ "ሞዴልን"[43] (Culture-Centered Explanatory Model) በ1980 "Patients and healers in the context of culture" በሚል ሥራቸው አስተዋውቀዋል (Helman, 1984; P.72: Brady, 2001;P.26):: ባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል ማዕከላዊ ይዘት፤ ሐኪሙና ሕመምተኛው ለበሽታና ለሕመም መንስኤ፤ ፈውስና ተግባር ምን እሳቤ እንዳላቸው ይመረምራል። አንድ ሰው ሕመም ሲጀምረው፤ እንዴት፣ ለምን፣ መቼ፣ የት… እንደታመመ፤ የሕመሙን መንስኤ፣ ምክንያት፣ ተግባር፣ ዓይነት፣ ምልክት፣ ይዘት… ለሐኪሙ ያስረዳል፤ የባህል ሐኪሙም ከሕመምተኛው ጋር በመወያየት የበሽታውን መንስኤ በመለየት ሕክምና ይሰጣል (Pool and Geissler, 2005; P.59: Winkelman, 2009; P.77)። የሕክምና ሥርዓቱም፤ ሕመምተኛውና ሐኪሙ በመመካከር፣ በመወያየት፣ በመግባባት፤… በተከሰተው ሕመም ላይ የጋራ ግንዛቤና ማጠቃለያ ሃሳብ በመያዝ "አስፈላጊና ተገቢ ነው" የተባለውን የፈውስ መድኃኒት ሐኪሙ አዘጋጅቶ ለታማሚው ይሰጣል። በዚህ ሞዴል የታማሚው ፍላጎት፣ ገለጻ፣ እሳቤ፣ ምክንያት፣ መፍትሔ… ግምት ውስጥ ይገባል (Helman, 1984; PP.72-73)።

ባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል የሕመምተኛውን እና የባህል ሐኪሙን እሳቤ፣ ክህሎት፣ መስተጋብር፣ ዕውቀት፣ ተግባር፣ ልማድ፣… መነሻ በማድረግ፤ በታካሚውና በሐኪሙ መካከል ያለውን መግባባት፣ ሥርዓትና ተግባር ይፈትሻል። ሕመሙ እንዴት ተከሰተ? የሕመሙ መንስኤ እና የሕክምና ሥርዓቱ ምንድን ነው? የሕመም መንስኤው በታካሚውና በሐኪሙ እንዴት ይተረጎማል፤ ይተነተናል፤ ምን ዓይነት ፍቺ ይሰጠዋል? ሕመሙ እንዴት ይፈወሳል? ለሚሉ ጥያቄዎች የጋራ ማብራሪያና መግባቢያ ምክንያቶችን በመንደፍ የሚተገበረውን ሕክምና ይመለከታል። Winkelman (2009; P.77) የማብራሪያ ሞዴል ይዘት እና ትኩረትን እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡-

> Explanatory model, which examines how patients interpret the causes and progress of a malady and how they think it should be treated. ... The explanatory model provides a format for eliciting how a malady is interpreted by both patient and provider, making explicit the models used by both to interpret and explain a malady and decide among possible therapies.

[43] በዚህ ይዘት ሞዴል ማለት፤ ቅጂ፣ ዓይነት፣ መልክ፣ ይዘት፣ ማሳያ፣ ንድፈ ሃሳብን… ይመለከታል።

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው፣ የማብራሪያ ሞዴል ትኩረት የባህል ሐኪሙና ታካሚው ለሕመም ያላቸው እሳቤና ትርጉም፣ ለሕመሙ የሚሰጠው ሕክምና እና ተግባር ማዕከላዊ ጉዳዮች እንደሆኑ ይጠቁማል። በተመሳሳይ መልኩ Pool and Geissler (2005; P.60) ባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል ለሕመም መንስኤ እና እሳቤ አምስት ዓይነት ሁነት/ይዘት እንዳለ ገልፀዋል። እነርሱም የሕመም መንስኤ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ምልክቱ መቼና እንዴት ታየ፣ የምልክቱ ባሕርይ፣ የሕመም አቅጣጫ/ይዘት፣ የሕክምና ሥርዓትና ተግባርን እንደሚያጠቃልል፣ "In particular they provide explanations for five aspects of illness: cause, when and how symptoms first appeared, the nature of the symptoms, the course of sickness, and treatment." በማለት አስረድተዋል።

ባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል ይዘት በሐኪሙ እና በታካሚው መስተጋብር፣ ግንኙነት፣ የጋራ እሳቤ እና ባሕርይ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ሁለቱ አላባውያን (ሐኪሙና ታማሚው)፣ ለሕመም መንስኤ ያላቸውን የጋራ ግንዛቤ፣ ዕውቀት፣ ስሜትን..፣ ይዳስሳል (Pool and Geissler, 2005; PP.59-60)። የባህል ሕክምና ዕውቀትን ለማጥናት ባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል ቀዳሚና ዐበይት መተንተኛ መንገድ እንደሆነ ገልፀዋል (Helman, 1984: Brady, 2001;P.26: Winkelman, 2009; PP.77-78)። ለዓብነት ያህል፡- የሕመም መንስኤ እሳቤን፣ የምርመራ ዘዴን፣ የባህል ሐኪሙና ታማሚው ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸውን ዐውዳዊ መስተጋብር… መመርመር እና መገንዘብ እንደሚቻል አስረድተዋል (Helman, 1984; PP.72-73: Winkelman, 2009; PP.77-79)።

ባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል ይዘትና ትኩረት፣ የባህል ሐኪሙና ታማሚው መስተጋብራዊ ሂደት ምን ይመስላል? የሕመሙ መንስኤ ምንድን ነው? እንዴት አሁን ተከሰተ? ምን ዓይነት ምልክትና ስሜት አለው? የሕመሙ ዓይነት ለታማሚው አካላዊ አቋም ያሰጋዋል? የሕመሙ መነሻ ሁነት እና ዳራ ምን ይሆን? ለሕመሙ ተገቢው ሕክምና ምንድን ነው? ምን ማድረግ አለብኝ? ለሚሉ ጥያቄዎች ከባህል ሐኪሙና ከታማሚው የሚገኘውን ምላሽ ይመለከታል (Helman 1984; P.72: Brady, 2001; PP.26-27: Pool and Geissler, 2005; PP.59-61: Winkelman, 2009; P.78)።

በአጠቃላይ ባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል፣ የባህል ሐኪሙና ታማሚው ለሕመም መንስኤ፣ ለምርመራ ዘዴ፣ ለሥነ ምህዳር ዐውዳዊ ሁነት ያላቸውን እሳቤ፣ ዕውቀትና አተገባበርን ይመረምራል። ሕመሙ መቼ እና እንዴት ተከሰተ? ለምን አሁን ተከሰተ? የሕመሙ መከሰቻ ምንጭ ምንድን ነው? እኔ ላይ ለምን ተከሰተ? የሕመሙን ዓይነት እንዴት መለየት ይቻላል? የምርመራ ስልቱ ምንድን ነው? ምን ዓይነት ሕክምና አለው? ለሚሉ ጥያቄዎች ማብራሪያና

ምክንያት በማቅረብ የሚተገበረውን ይዘት ያጠቃልላል። ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ (በፋርጣ፣ በሊቦ ከምከምና በእብናት ወረዳዎች) የሚካሄደውን የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ይዘትን መርምሯል። ይህ ሞዴል በሕመም መንስኤ (Illness Causation) ንድፈ ሃሳቦች ይዘት ሥር ይካተታል። የማኅበረሰቡን ተግባርና ግንዛቤ ለመረዳት፤ ባህል ተኮር ማብራሪያ ሞዴል (የጥናት ዝርዝር ዓላማ አንድ፣ ሁለት እና አራት ይዘትን ልብ ይሏል) ተግባራዊ ሆኗል።

### 3.6.2 ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ሞዴል

በዐውድ-ተኮር ክዋኔ፤ ባህላዊ እና ማኅበራዊ ድርጊቶች እንዴት እንደሚከወኑ፤ የክዋኔ አላባውያን (Elements of Performance) በዐውድ ውስጥ ምን ሚና እንዳላቸው ለመረዳት፤ የፎክሎር ድርጊቶችን አፈፃፀምና አጠቃላይ ሁነት ለመተንተን፣ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለመመደብ፣ ለመተርጎም፣ ለመፈከር፣ አቅጣጫና ይዘትን ለመለየት…፤ ማን? ምን? እንዴት? መቼ? የት? ለምን? የሚሉ ዐበይት ጥያቄዎች ማንሳትና ምላሽ መስጠት የተሟላ መረጃን ለመሰብሰብ እና ለመተንተን እንደሚያስችሉ የመስኩ ምሁራን ይመክራሉ (Sims and Stephens, 2005; P.134: Bauman, 1975; P.299; 1983: Shoemaker,1990)። የፎክሎር አጥኚ እነዚህን መሰረታዊ ጥያቄዎች በማንሳት የመስክ መረጃውን አንድም ይሰበስባል፤ አንድም ይተነትናል።

የፎክሎር ክዋኔ በዐውድ ሲጠና የይዘት ገለፃ፣ ትንታኔ፣ ቅርጽ፣ መዋቅርና ድርጊትን ለማሳየት ያስችላል። ማንኛውም ዐውድ በክዋኔ እና በድርጊት የታጀበ ሲሆን ከባህሉ፣ ከማኅበረሰቡ እና ከሁኔታ ዐውድ አንፃር መመልከት፣ መመርመርና መተንተን ተገቢ መሆኑን ምሁራን ገልፀዋል (Bauman, 1977; 1986; 1992: Ben-Amos,1993; 1997)። በፎክሎር ጥናት፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት በሃገረሰባዊ ልማድ ሥር ይጠቀሳል (Yoder, 1972)። Bauman (1975; 1983) ማንኛውም ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ሲጠና የክዋኔ አላባውያን እና አሃድ/ቴክስት ማካተት እንዳለበት ይመክራሉ። እነርሱም፦መቼት (setting) (ክዋኔው የተፈፀመበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ ሁኔታ…)፤ ሕግ/ ደንብ (rule) (የክዋኔው ሥርዓት፣ ሂደት፣ ቅደም ተከተል፣ መመሪያ፣ ትዕዛዝን ይመለከታል)፤ ተሳታፊ (Participant) (የተሳታፊዎችን ሚና፣ ሁኔታ፣ ተግባር… ማጤን)፤ ከዋኝ (Performer)፦ (የከዋኙን የአከዋወን ስልት፤ ድርጊት፣ ተግባር፣ ተመስጦን… ይጠቁማል)፤ ተመልካች (Audience)፦ (ሥርዓተ ክዋኔውን የሚታደሙ ግለሰቦች ለክዋኔው ያላቸው ስሜት፤ ምላሽ…)፤ የድርጊት ቅደም ተከተል (Act sequence) (የክዋኔው ሥርዓት ቅደም ተከተል፤ መመሪያና ሂደት)፤ ማሕቀፍ፤

የታዳሚዎች ግብረ መልስን "ሜታፈርን" ይመለከታል። እነዚህን አላባውያን ለመመለስ ድርጊቱን ማን ፈፀመ? (ከዋኙን)፤ ምን ተፈፀመ? (ፎክሎራዊ አሀድን)፤ ለምን ተፈፀመ? (የክዋኔን ተግባር)፤ ድርጊቱ ለማን ቀረበ ወይም ተፈጸመ (ተመልካች)፤ ድርጊቱ መቼና የት ተፈጸመ? ዐውድ (መቼት)፤ ድርጊቱ እንዴት ተፈፀመ? (የአከዋወን ስልት) የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ምላሽ ቀርቧል።

የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ፤ ዓላማ፣ ፅንሰ ሃሳብ፣ ንድፈ ሃሳብና ሥነ ዘዴን ለማስተሳሰር ዐውድ-ተኮር ክዋኔ የጥናቱ ማዕከላዊ አምድ መሆኑን ልብ ይሏል። በዚህ ይዘት የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ዕፀ መድኃኒት ከመስክ ሲሰበስቡ፣ ሲቀምሙና ሲሰጡ… ምን ዓይነት ሥርዓትና ክዋኔን ይከተላሉ? እንዴት ይፈፅማሉ? መቼ እና ለምን ይፈፅማሉ?…፤ የወቅት መፈራረቅ፤ የመልክዓ ምድር መለያየት፤ የዐየር ንብረት ለውጥ፤… በባህል ሕክምና እና በሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ሂደት ላይ ምን ተፅዕኖ/ አበርክቶ አለው? ዕፀ መድኃኒት ለመሰብሰብ የትኛውን ወቅት፣ ጊዜ፣ ዘመን፣ ሥነ ምህዳርን ይመርጣሉ? ለምን? ምን ዓይነት ሥርዓት (Rituals) እና ተግባራትን ይፈፅማሉ? ለሕመምተኛ መድኃኒትን በምን መንገድና መልክ አዘጋጅተው ይሰጣሉ? ለሕመምተኛ መድኃኒት ሲሰጡ "ብላ/ አትብላ፤ ጠጣ/ አትጠጣ፣ አድርግ/ አታድርግ" በማለት የተወሰኑ ድርጊቶችን፤ የምግብ ዓይነቶችን፣ የመድኃኒት መቀላቀያ ይዘቶችን ይፈቅዳሉ/ይከለክላሉ? ምን ዓይነት ጥቅምና ጉዳት አላቸው ተብሎ ይታሰባል? ሕሙማን በየትኛው ቀን፣ ሠዓት፣ ቦታ፣ ዐውድ… መድኃኒት እንዲወስዱ ይደረጋል? ለምን? የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አበርክቶ/ተግዳሮት ይኖረዋል? ሚታዊ ተረኮች፤ እምነታዊና አምልኳዊ ሥርዓቶች ለሥነ ምህዳር መጠበቅና መጥፋት ምን አስተዋጽኦ አላቸው? ከሆነስ እንዴት? (የጥናት ዝርዝር ዓላማ ሶስትና አራትን ይመለከታል) ለሚሉ ጥያቄዎች በምርምሩ ሂደት ምላሽ ቀርቧል።

### 3.6.3 የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል

በዓይነታዊ ምርምር እና በኢትኖግራፊ ጥናት፤ የመስክ መረጃዎችን በዓይነት፣ በይዘት፣ በባሕርይ እና በተግባር መድቦ መተርጎም፤ ፅንሰ ሃሳብንና ንድፈ ሃሳብን ከመስክ መረጃና ሞዴል ጋር አስተሳስሮ መተንተን የተመራማሪው ዐቢይ ተግባር ይሆናል (Schoemaker, 1990: Hammersley & Atkinson, 2007: Ben-Amos,1975,1977,1993)። የዚህ ጥናት መተንተኛ ሞዴልን ከመስክ መረጃዎች ይዘት ለመቅረፅ ተችሏል። ሞዴሉም "የተፈጥሮ ባሕርይ" ይባላል። ለሞዴሉ ይዘት

ስምና ስያሜ በተመራማሪው የተሰጠ ቢሆንም፣ የፅንሰ ሃሳቡ ይዘት፣ የእሳቤ መሰረት፣ የትግበራ ሂደት፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ፣ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ተግባር የተለመደ፣ በባህል ሕክምና ባለሙያዎች የሚተገበር የእሳቤና የዕውቀት መሰረት ተደርጎ እንደሚታሰብ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል። ይህ ሞዴል "በሥነ ዕውቀት (Epistemolog) እና በማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ (Social constructionist theory)" ይዘት ውስጥ የሚካተት ሲሆን፣ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ በሆኑ እንደ ደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ ባሉ አካባቢዎች ይተገበራል። የእሳቤውን መሰረት፣ ርዕዮተ ዓለም፣ ፍልስፍና፣ ሥርዓትና ተግባርን ተገንዝቦ፣ የዕውቀት ምንጫቸውን ለመመርመር፣ የሥርዓት፣ የተግባርና የባሕርይ መሰረታቸውን ለመተንተን በእጅጉ አስፈላጊና ጠቃሚ ሞዴል እንደሆነ በአጥኚው ይታመናል።

በማኅበረሰቡ እሳቤ "የተፈጥሮ ባሕርይ" መሰረት፣ የሕይወት ምንጭ፣ የሥጋ ባሕርይና ግብሮች የፍጥረት ሥሮች አራቱ ባሕርያት እንደሆኑ ይታሰባሉ። አራቱ የፍጥረት ባሕርያት፣ የሕይወት ሥር ነፋስ፣ እሳት፣ ውኃ እና መሬት በመባል ይጠቀሳሉ። እነዚህ ባሕርያት የሥጋ መሰረት፣ የፍጥረት አካል ውሕድ፣ አካልን የሚያስገኙ፣ የደም፣ የአጥንት፣ የሥጋና የነፍስ መሰረት ተደርገው ይቆጠራሉ (ሊቀጠበብት አብርሃም እና መሪጌታ ስዩም፣ ቃ.መ፣ 30/01/2011 እና 04/02/2011 ሊቦ ከምከም እና እብናት በቅደም ተከተል)።

ከነዚህ አራት ባሕርያት አንዱ ቢጎድል ወይም ቢጠፋ ከሰውነት ወደ ግዑዝነት (ቁስ) መሸጋገርን ያስከትላል። አራቱ ባሕርያት፣ በዚህ ዓለም ሥርዓት ውስጥ በመጠን፣ በልክ፣ በሚዛን ተመጥነው፣ ከፋጣሪ የተሰጡ፣ ልክና መጠናቸውን ጠብቀው የሚሄዱ፣ በተመደበላቸው መጠን ላይ ሲገኙ የጤና መደላድል፣ የሕይወት መሰረት እንደሆኑ ይታመናል። ከተጠቀሱት ባሕርያት መካከል አንዱ መጠኑን ቢያልፍ ወይም ልኩን ቢስት ደግሞ የሕመም መንስኤ፣ የሞት ምክንያት ተደርጎ ይቆጠራል (ደብተራ መልኩ፣ ቃ.መ፣23/01/2011 ፋርጣ)።

መሪጌታ መኅሪ እና ሊቀጠበብት አብርሃም፣ የባሕርይ ሥር ሲዛባ አካላዊ ሕመምና መንፈሳዊ ጭንቀት እንደሚከሰት ገልፀዋል። አካላዊ ቁስለት እና መንፈሳዊ ጭንቀት የትኛውን ባሕርይ አዛባ? የጤና ኃይል ሚዛን እንዴት ይስተካከላል? ሲባል፣ በንፋስ ኃይል ወይስ በዉርጭና ቅዝቃዜ ተነሳ? በሙቀት መጠን መብዛትና ማነስ ሕመም ተከሰተ? ዉኃን አብዝቶ በመሸከም ወይስ ዉኃ በማጣት ድርቀት መጣ? የሰውነት አካል ሥጋን አብዝቶ፣ አጠራቅሞና አከማችቶ በመያዝ መንቀሳቀስ ከበደው? የትኛው ባሕርይ በታካሚው አካል ላይ ጎልቶ ይታያል? ይህን ባሕርይ በምን ዓይነት ስሌት፣ መጠንና ሥርዓት ማስተካከልና ማስታረቅ ይቻላል? አካሉ

ለቀለለና ለደከመ፤ በማብላትና በማጠጣት ማደርጀት፤ ኃይልና ጉልበቱ ለበዛ፤ መመለሻ፣ ማረጋጊያ እና ማደላደያ ስልት "ንስሃ" (ጾም፣ ፀሎትና ስግደት)፣ ምርቃት፣ ምፅዋት እና የንስሃ ተግባራት እንደመፍትሔ አካል ቀርበዋል (ቃ.መ፤27-30/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

ከአራቱ ባሕርያት በተጨማሪ ሶስት የነፍስ ባሕርያት (ልባዊት፣ ነባቢትና ሕያዊት) በሰው ልጅ የሕይወት ዑደት ውስጥ ይጠቀሳሉ። የማሰብ መሰረት የሆነችው "ልባዊት"፤ የልሳን አካልና አንደበት "ነባቢት"፤ የእስትንፋስና የሕይወት ምንጭ "ሕያዊት" እንደሆነች በኦርቶዶክስ ሃይማኖትና ፍልስፍና ይታሰባል (ሡናይ፣ 2009)። የነፍስና የሥጋ ባሕርያት ሲዋሃዱ፣ ሲገናኙና ሲቀላቀሉ "ሰብዕና" ወይም "ግላዊ ተውህቦ" ባሕርይ ይገኛል፤ ተብሎ ይታመናል (ቄስ አብርሃምና መሪጌታ በረከት፣ ቃ.መ፤ 01/05/2011 እብናት፤ 12/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። በዚህ ጥናት የሥጋዊ ባሕርያትና ግብሮች ምድብና ይዘት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ አንድ፡- የሥጋ ባሕርያትና ግብሮች ይዘት

| | የሥጋ ባሕርያት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ነፋስ | እሳት | ዉኃ | መሬት |
| ገቢሮች | ቀዝቃዛነት | ደረቅነት | ሞቃትነት | ደረቅነት |
| | ብሩሕነት | ብሩሕነት | ቀዝቃዛነት | ርጥብነት |
| | ርጥብነት | ሞቃትነት | ጥቁርነት | ጥቁርነት |
| መታረቂያ መንገዶች አስረጅ አንድ | ነፋስ እና እሳት በብሩሕነት | | ነፋስና መሬት በርጥብነት | |
| | ነፋስ እና ዉኃ በቀዝቃዛነት | | | |

በዚህ ጥናት ሞዴል፤ ሰው፣ እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ መልክዓ ምድርና የዓለም አፈጣጠር በነዚህ አራት ባሕርያት ሥርዓት፣ ሚዛንና ስሌት እንደሚመሩ ይታሰባል። እነዚህ ባሕርያት የሚገኙበት፣ የሚጎሉበት፣ የሚሰለጥኑበት፤ በአንጻሩ የሚከስሙበት፣ የሚደክሙበትና የሚጠፉበት ወቅትና ጊዜ እንዳላቸው ይታመናል። የእነዚህ ባሕርያት መለዋወጥ በፍጡራን ባሕርይ፣ ጤና እና ተግባር ላይ ተፅእኖ እንደሚያሳድር ይታሰባል። በተለይ የኮከብ ቆጠራ ሥርዓትና ገቢሮች በአራቱ ባሕርያት እንደሚመሩ፤ የባህል ሐኪሞች መክረዋል (መሪጌታ ፍሬ ስብሃት እና አቶ ደሴ፣ ቃ.መ፤ 25-29/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

በዚህ ጥናት የማኅበረሰቡን እሳቤ ለመገንዘብ፣ የዕሳቤ መሰረታቸውን ለማወቅ "የተፈጥሮ ባሕርይ" ሞዴል በምርምሩ ትንተና ይዘት ተግባራዊ ተደርጓል። ይህ ሞዴል ከሥነ ዕውቀትና ከማኅበረሰብ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ የሚመነጭ ሲሆን፤ ዕውቀት እንዴት ተገነባ? በግለሰብ/በቡድን? በመለማመድ/በመደጋገም? ምን ዓይነት ሥርዓትና ተግባር እንዳላቸው ለመፈተሽ በእጅጉ የሚጠቅም ሞዴል እንደሆነ በአጥኚው ይታመናል። በዚህ ስልት ሰው፣ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ መልክዓ ምድር፣ በሽታ ምን ዓይነት ባሕርይ አላቸው? የሕክምና ስልቱ በተቃርኖ ወይስ በማዛመድ ይተገበራል፤ የዕፅዋት ባሕርይ ከጣዕም አንጻር የቱ ይመረጣል/ይፈራል፤ ከእንስሳት አመጋገብ ባሕርይ ሥጋ በል፣ ሣር በል፤ በማኅበረሰቡ የቱ ይፈራል/ይመረጣል? የሚሉ ይዘቶችን አንስቶ ምላሽ ለመስጠት አመቺ በመሆኑ፤ በጥናቱ ይዘት ተግባራዊ ሆኗል።

### 3.7 የመስክ ልምድና መረጃ መሰብሰቢያ ጊዜያት

ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር ዞን በፋርጣ፣ በሊቦ ከምከም እና በእብናት ወረዳዎች ላይ የተካሄደ ነው። ጥናቱን ለማካሄድ አምስት ዙር የመስክ ጉዞና ምልልስ የተደረገ ሲሆን፤ የሰባት ወር ቆይታ ነበረው። በመጀመሪያው ዙር ጉዞ፤ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የትብብር ደብዳቤ በማፃፍ፤ ጥናቱ በሚካሄድበት አካባቢ ለሚገኙ የዞንና የወረዳ አስተዳደር አባላት የጥናቱን ዓላማ በማስተዋወቅ፤ የበኩላቸውን ትብብር እንዲያደርጉ ፈቃድ ተጠይቋል። ቀጥሎም የእነሱን ይሁንታ፣ ትብብርና የፈቃድ ደብዳቤ (ከደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ለሶስት ወረዳዎች ተጨማሪ ደብዳቤ አጽፎ) በመያዝ፣ ከወረዳ አስተዳደሮች፣ ከባህልና ቱሪዝም፣ ከጤና፣ ከተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች፤ በአካባቢው ከሚገኙ የባህል ሐኪሞች ጋር ለመተዋወቅ እና ቀጠሮ ለመያዝ ተችሏል (ከ22/12/2010-03/13/2010 ዓ.ም)።

በዚህ ጉዞ ስለአካባቢው ዳራ (ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁነት) የሚገልጹ የሕትመት መረጃዎች ከዞንና ከወረዳዎች (ከደቡብ ጎንደር ዞን ፕላንና እቅድ ኮሚሽን፣ ከጤና፣ ከግብርና ከባህልና ቱሪዝም፣ ከማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት) ተሰብስበዋል። በተለይ የክልሉን፣ የዞን እና የወረዳ የባህል ሕክምና ማኅበር አመራሮችን[44] በመተዋወቅ፤ የጥናቱን ዓላማ፣ ግብና ፋይዳ

[44] የክልል እና የዞኑን የባህል ሕክምና አስተዳደር (ሃጂ ሼህ ዓሊ ዓደም፤ የአማራ ክልል የባህል ሐኪሞች ማኅበር ፕሬዚዳንት) እና አመራሮች (መሪጌታ ብሩህ ዘላለም የአማራ ክልል የባህል ሐኪሞች ማኅበር ፀሐፊና የደቡብ ጎንደር ዞን ተወካይ) ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ትውውቅ፣ ቀረቤታና ግንኙነት ስለነበረኝ፤ ይህ ጥናት በሚካሄድበት አካባቢ የሚገኙ የወረዳ የባህል ሐኪሞች ማኅበር አስተባባሪና ተጠሪ አካላትን ለመተዋወቅ፤ በየቦታው የሚገኙ ቀደምትና ነባር የባህል ሐኪሞችን ለማግኘትና ለመምረጥ ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮልኛል። በተለይ ከክልል እስከ ወረዳ ያለው

ማስረዳት ተችሏል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ አባላት (የባህል ሐኪሞች) ሲመረጡ በባህል ሕክምና ሙያ ላይ የተሰማሩ፣ በአካባቢው ማኅበረሰብ የታወቁ፣ ቋሚ ቤት ይዘው የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ፤ በመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ የረጅም ዓመት ልምድ፣ ተመክሮና ሙያ ያላቸው፣ መረጃ ለመስጠት ካላቸው ፍላጎት፣ ቅንነትና ትብብር አንጻር ተመርጠዋል፡፡ ከእነዚህ አባላት ጋር ሁለት/ሶስት ጊዜ ውይይትና ምክክር በማካሄድ ለጥናት በተመረጡ ወረዳዎች በባህላዊና በዘመናዊ ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና በሽታዎችን ዝርዝተር መሰብሰብ ነበር፡፡

የዘመናዊ ሕክምና መረጃዎችን ከጤና ጣቢያዎች በቀላሉ ለማግኘት ተችሏል፡፡ በባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ በሽታዎችን ለመለየት፤ ከአንድ ወረዳ በዋና መረጃ ሰጪነት አምስት የባህል ሐኪሞችን በመምረጥ፤ እንደ ምርጫቸው መዝግበው የሰጧቸው እና በዝርዝር የጠቀሷቸው የበሽታ ዓይነቶች፤ በጥናቱ አቅራቢው ተሰንደዋል (አባሪ አምስትን ይመልከቱ)፡፡ እነዚህ የመስክ መረጃዎች ለቀጣይ ዙር ጉዞና ምርምር ምን አስተዋፅኦ ነበራቸው? ሲባል፤

1ኛ. አንፃራዊ በሆነ መልኩ (በየወረዳዎቹ ጎልተው የታዩ) የበሽታዎችን ዓይነት ለመለየት፤

2ኛ. የበሽታዎችን ምድብና ባሕርይ ለማወቅ፤

3ኛ. ለቀጣዩ የመስክ ስምሪት ትኩረት የሚደረጉባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች ለመለየት፤

4ኛ. ለባህል ሕክምና ባለሙያዎች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ጥያቄዎች ለማቅረብ፤

5ኛ. የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን የጋራ ዕውቀትና ተግባር ለመለየት፤

6ኛ የምርምሩን ይዘት፣ ቅንብብ እና ትኩረት ለመምረጥ፤

7ኛ. የምርምሩን አቅጣጫ፣ ሂደትና ተግባር ለመወሰን እገዛ አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ተግባራትን በመከወን፤ ለቀጣይ ጥናት ዝግጅትና ቀጠሮ በመያዝ የመጀመሪያ ዙር የመስክ ጉዞ ተጠናቋል፡፡

በሁለተኛ ዙር የመስክ ጉዞ ከመረጃ ሰጪዎች ጋር በቀጥታ በመነጋገር፤ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በጉዳይ ምርመራ ዘዴ የመስክ መረጃዎች ተሰብስበዋል (ከ18/01/2011- 10/02/2011 ዓ.ም)፡፡ በተለይ በዋና መረጃ ሰጪዎች በመታገዝ ከእነተፈጥሯዊ መቼታቸው (Natural setting)

---

የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ማኅበር አደረጃጀትና መዋቅር በየአካባቢው የሚገኙ የባህል ሐኪሞችን በማስተዋወቅና እነሱም የዚህ ጥናት አካል በመሆን፤ ጉልህ ሚና ነበራቸው (አቶ ደሴ፤ የሊቦ ከምከም ወረዳ፣ መሪጌታ ፋንታሁን፤ የፋርጣ/ደብረታቦር፣ አቶ ደርሶ የእብናት ወረዳ የባህል ሐኪሞች ማኅበር ተጠሪ ናቸው)፡፡

የተገኙ የዕፀ መድኃኒት ግብዓቶችን (በዋናነት) ዐውድና ክዋኔ፤ የባህል ሕክምና አሰጣጥ፣ ምርመራ፣ የመድኃኒት አዘገጃጀት፣ ቅመማ፣ መመሪያ እና መሰል ሂደቶችን በመከታተልና በማጤን፤ የመስክ መረጃዎች ተደራጅተዋል፡፡ ይህ ወቅትና ጊዜ ለምን ተመረጠ? በባህል ሕክምና ልማድና አተገባበር የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ዋና መሰብሰቢያ ወቅት ከመስከረም እስከ ኅዳር ያለውን ዐውድ ይመለከታል (መሪጌታ ፋንታሁን እና መሪጌታ ፍሬስብሃት፤ ቃ.መ፤ 19-29/01/2011 ፋርጣና ሊቦ ከምከም ወረዳ በቅደም ተከተል)፡፡ ይህ ወቅት ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት ተፈጥሯዊ ኃይልና መዐዛቸውን ሳያጡና ሳይደርቁ ወይም ለጋ እና "ጮርቃ" ሳይሆኑ ከነሙሉ "ጣዕምና ይዘታቸው" ከመስክ ለመሰብሰብ አማካይ ጊዜ፤ ተመራጭ ዐውድና ወቅት (Harvesting season) መሆናቸውን፤ በማሰብ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

የባህል ሐኪሞች ስለሕመም መንስኤ ምን ዕውቀትና እሳቤ እንዳላቸው፤ የበሽታ መለያና ምርመራ ዘዴዎች አተገባበር፤ የመድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ዐውድ-ተኮር ክዋኔ ሂደት፤ የባህል ሐኪሞች (ማኅበረሰቡ) ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸው ዐውዳዊ መስተጋብር ምን ዓይነት ይዘትና ተግባር እንዳለው በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በንጥል ጥናት ዘዴ የመስክ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በአካባቢው ታዋቂ የሆኑ የባህል ሕክምና ባለሙያዎችን በመለየት በንጥል ጥናት (Case Study) ዘዴ የሙያ ዘርፉን በጥልቀት ለመመርመርና ለማጥናት፤ ዝርዝር መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ የዚህ ጥናት ዐቢይና ንዑስ ተሳታፊ አባላት፤ የባህል ሐኪሞች፣ የባህል መድኃኒት ተጠቃሚ የሆኑና ያልሆኑ ግለሰቦች፣ የዘመናዊ ሕክምና፣ የባህልና ቱሪዝም፣ የተፈጥሮ  ሐብት ጥበቃ ባለሙያዎች (የሥነ ምህዳር ባለሙያዎች)፣ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ልማድ እና ዳራ የሚያስረዱ አዛውንቶች የመስክ መረጃ በመስጠት ተሳትፈዋል፤ ተካተዋል፡፡

ከሶስተኛ እስከ አምስተኛ ዙር የተካሄዱ የመስክ ጉዞዎች[45]፤ በአንደኛና በሁለተኛ ዙር የተሰበሰቡ የመስክ መረጃዎችን መነሻ በማድረግ በባህል ሕክምና ሙያቸው የተከበሩ፣ በማስረዳትና በገለጻ ብቃታቸው የተሻሉ (በእኔ እይታ) እና ፍቃደኛ የሆኑትን በመለየት፤ ጉዳይ ምርመራ ለማካሄድና እና ዐውድ ተኮር የመስክ መረጃዎች ለመሰብሰብ፣ መደበኛ ግንኙነት ለመመስረት ተችሏል፡፡ በነዚህ ሶስት ዙሮች (ከሶስተኛ እስከ አምስተኛ ዙር የተካሄዱ ተግባራት) ለጥናቱ አስፈላጊ የሚባሉ መረጃዎችን በድጋሚ ከዞን እስከ ወረዳ ካሉ አመራሮችና ሙያተኞች፤ የባህል ሐኪሞች፣

[45]ከሶስት እስከ አምስተኛ ዙር የተካሄዱ ጉዞዎች፤ ከጥቅምት 27/2011-ሕዳር 14/2011፤ ከታሕሳስ 16/2011-ጥር 04/2011 እና ከየካቲት18/2011- መጋቢት 06/2011 ዓ.ም ባሉ ቀናት ውስጥ የመስክ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ከአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት በቃለመጠይቅ፣ በምልከታ፣ በጉዳይ ምርመራ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማደራጀት ተችሏል። በአምስተኛ ዙር ጉዞ ከባህል ሐኪሞች፣ ከዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ነዋሪ አባላት አባትና እናቶች ጋር ተተኳሪ ቡድን ውይይት (Focused Group Discussion) ተካሂዷል።

ከሁለተኛ እስከ አራተኛ ዙር የተሰበሰቡ የመስክ መረጃዎችን በዓይነትና በይዘት በመመደብ ዐበይት ርዕሰ ጉዳዮችን መለየት፤ አጠራጣሪና ግልፅ ያልሆኑ መረጃዎችን በማስታወሻ በመያዝ፤ የመስክ መረጃዎችን ባሕርይ፣ ሂደት፣ ምድብ እና ሥርዓት በማውጣት፣ ለተተኳሪ ቡድን ውይይት የሚቀርቡ ጭብጦችን በማዘጋጀት፤ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታ፣ በንጥል ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለማመሳከር፣ ለማገናዘብና ለማስተሳሰር (Triangulation)፣ በውይይቱ ሂደት የሚገኙ አዲስ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማካተት፤ የጋራ እምነት፣ ዕውቀት፣ ተግባርና ልማድ መሆን/አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ፤ ከአራት አባላት ጋር ተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካሂዷል፤ መረጃም ተሰብስቧል።

ከነዚህ ተግባራት በተጓዳኝ፤ በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ በመገኘት፤ በፀበል፣ በለቅሶ፣ በአውድማ ሥርዓት፣ በገበያ ቦታዎች፣ በሰርግ፣ በተዝካር እና በወርሃዊ በዓላት ዐውዶች ላይ በመሳተፍ የመስክ ምልከታ (ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ዙር ጉዞ) ተካሂዷል። በነዚህ ዐውዶች ምን ዓይነት መረጃ ተገኘ? ሲባል፡-

በሁለት የፀበል ቦታዎች (በዋንዛዬ እና በዜና ማርያም ፀበል ቦታዎች) ተገኝቼ ዕለታዊ ተግባራትን፤ መንፈሳዊ ስብከቶችን እና የማከሚያ መንገዶችን፣ ሥርዓተ ፀሎትን በመከታተል፤ "አጋንንት ሰፍሮባቸው፤ መንፈስ አድሮባቸው ነው!" ተብለው የሚጮሁ፤ የሚያለቅሱ፣ የሚሮጡ ሰዎችን አይቻለሁ፤ በአጥማቂና በፀበልተኛ መካከል የነበረውን ግንኙነት ለመቃኘት ሞክሬያለሁ። በለቅሶ ቦታዎች (በክምር ድንጋይ አማኑኤል፤ በሊቦ ከምከም መድኃኒያለም ቤተክርስቲያን) በመገኘት የለቅሶ፣ የሐዘን፣ የማፅናናት እና የስንብት ሥርዓት፤ በሃይማኖት አባቶች የሚመራ የፍታት እና የፀሎት ተግባራትን፤ በምን ሕመም ሕይወታቸው እንዳለፈ፤ ሕመሙ ምን ያህል ጊዜ እንደቆየባቸው፤ ምን ዓይነት ሕክምና አድርገው (ባህላዊ፣ መንፈሳዊ/ፀበል እና ዘመናዊ ሕክምና) እንደነበር፤ የሚደረጉ ውይይቶችን መደበኛ ባልሆነ መልኩ ተከታትያለሁ፤ ተሳትፌያለሁ፣ አዳምጫለሁ።

በአጨዳ እና በእህል ማሳዎች በመገኘት፤ በአውድማ (እህል "ሲያበራዩ") ሥርዓት ላይ በመሳተፍ፤ የእህል ነዶ "ጥለው" ከብት ሲነዱ፤ ገለባ ከምርቱ ሲለዩና ሲጠርጉ፤ ምርቱን "ሰላቢ" እንዳይገባው ፌጦና መሰል የቅመማ ቅመም ዘሮችን በጥብጠው ሲረጩ፤ የአውድማ መጥረጊያ ዕፆችን መርጠው ሲጠቀሙ፤ የዕፅዋትን ዓይነት እና የቅመማ ቅመም ዘሮችን በማስታወሻ ደብተር መዝግቤ ይዣለሁ፡፡ በገበያ ቦታዎች በመገኘት ሲሸጡና "ሲሸምቱ"፤ ማኅበራዊ ተግባቦታቸውን ቃኝቻለሁ፤ ገበያተኞች ምን ዓይነት ዕፅዋትን በእጃቸው፣ በብብታቸው፣ በጆሮና በፀጉራቸው ይዘዋል፤ በሥጋና በቅቤ ተራ ምን ምን ዕፅዋት ተጥለዋል፤ ምን ዓይነት ባሕርይ አላቸው? የሚሉ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸው ተሰብስበዋል፡፡

በሁለት የሰርግ ሥርዓቶች ላይ በመታደም የሃይማኖት አባቶች፣ የአካባቢው ሽማግሌዎች እና ወላጆች ሙሽሮችን ሲመርቁ፤ የጥሎሽ ሥርዓቶችን፣ የምግብና መጠጥ ተግባራትን፤ "በሰው ዓይን ያስወጋሉ፣ በአጋንንት ያስመታሉ፤ በቡዳ ያስበላሉ" ተብለው የሚፈሩ ልማዶችን በጥንቃቄ ሲተገብሩ ተከታትያለሁ፡፡ በዚህ ምልከታ ለሙሽሮች ሥርዓት መፈፀሚያ የተመረጡ ዕፅዋት፤ ለሰርግ ዳስ የተጣሉ፤ ለዕግር መረገጫ የተጎዘጎዙ የሣርና የቅጠል ዓይነቶች ባሕርይና ባህላዊ እሳቤዎች፤ በማስታወሻ ደብተር ተመዝግበዋል፡፡ በዓመታዊ ክብረ-በዓላት እና በወርሃዊ ንግሶች፤ በተዝካር ሥርዓቶች ላይ በመገኘት ጠቃሚ የሚባሉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህ ዐውዶችና ማኅበራዊ ሁነቶች ምን ዓይነት ጠቀሜታ ነበራቸው? ሲባል፤

ከሚጠናው ማኅበረሰብ ጋር ጠለቅ ያለ ትውውቅ፣ ተላምዶ፣ ቅርበትና ትስስር እንዲኖረኝ ምክንያት ሆነዋል፡፡ በዚህ ቆይታዬ የማኅበረሰቡን የዕለት ኑሮ እና ተግባር በመጋራት እምነቱን፣ ደስታውን፣ ሃዘኑን፣ ለዓለምና ለአካባቢው ሁነት ያለውን እሳቤ፤ ለሕመምና ለጤና የሚሰጠውን ፍቺ ለመረዳት እድል ፈጥረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ማኅበረ-ባህላዊ ሁነት ለመገንዘብ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

### 3.8 የመስክ ተመክሮ

ከዚህ በፊት፤ በጥናቱ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች፤ በመስክ ልምድና መረጃ መሰብሰቢያ ጊዜያት የተገለጹና የተሰሩ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው፤ አጥኚው ምርምሩን ሲያካሂድ ምን ዓይነት ፈተናዎች ገጠሙት? እንዴት አለፋቸው? የመስክ ልምድና ተመክሮው ለቀጣይ ተመራማሪ ምን ትምህርት እና ግንዛቤ ይሰጣል? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል፡፡

ለጥናት የመረጥኩት ርዕስ የዕውቀት፣ የገንዘብ፣ የኃይል ምንጭና መተዳደሪያ ከመሆኑም ባለፈ፤ ምስጢራዊ ነገሮች የበዙበት፤ በሕይወትና በሞት መካከል በሚደረግ ትግል ህቡዕ ተግባራት የሚፈፀሙበት፤ አስፈሪና አስገኒ ሁነቶች የሚከወኑበት፤ አግላይ ታሪኮችና ወንጀል ነክ ሥራዎች የሚከሰቱበት ስለሆነ፤ ሂደቱ በእጅጉ ፈታኝ ነበር።

በመጀመሪያ ደረጃ የርዕሰ ጉዳይ ምርጫና ውሳኔዬን የሚመለከት ነበር። በትምህርት ሙያ እና በቅርበት የሚያውቁኝ ጓደኞቼ "ምን ለማጥናት ታስባለህ?" ሲሉኝ "የባህል ሕክምና" የሚል ምላሽ ስሰጣቸው፤ ግራ በመጋባት "መረጃዉን ማን ይሰጥሃል፤ አስማትና ጥንቆልና ልትማር ነው!" የሚል መልስ ይሰጡኝ ነበር።  በሌላ በኩል ደግሞ የባህል ሕክምና እጅግ ድብቅ፣ ውስብስብ ተግባርና ምስጢራዊ መሆኑን በማሰብ፤ "አርፈህ ተቀመጥ! ተወው ይቅርብህ! በቦታው ከሕመም እና ከጭንቀት ባለፈ ምን ታያለህ። በየሰፈሩ ስትዞር በሽታ ሸምተህ ትመለሳለህ! በዚህ ዘመን የባህል መድኃኒት የሚያሳይ ማን ሞኝ አለ? የማይመስል ነገር አጠናለሁ ብለህ ጊዜህን አታጥፋ!" የሚሉ ምክሮችና ማስፈራሪያዎች እሳቤዬን በመግታት፤ ጉልበቴን በማድከም ሚና ቢኖራቸውም፤ ረጅም ጊዜ እንዳስብበት እና ከውስጤ እንድማከር እድል ፈጥረውልኛል። በአንፃሩ ለባህል ሕክምና ልማድ የነበረኝን መሰረት፣ ቅርበትና ፍቅር በማጤን፤ ከባህል ሐኪሞች ጋር አብሬ መስራቱን ሳስብ ድፍረት ይሰማኛል። ዕፀ መድኃኒቱን ይነግሩኛል ብዬ ሳይሆን፤ ቢያንስ ልማድና ሥርዓቱን ያስረዱኛል፤ ከሚል ፅኑ አቋም በመነሳት፤ ርዕሰ ጉዳዩን እንደማጠናው ሳልም ጭንቀትና ፍርሃቴ ይጠፋል።

ይህን ሃሳቤን ወደ ተጨባጭ ተግባር ለመቀየር በ2009 ዓ.ም ከአባቴ (ደብተራ በየነ የባህል ሐኪም) እና ከኢትዮጵያ ባህላዊ መድኃኒት ሕክምና አዋቂዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ሃጂ ሼህ ዓሊ ዓደም ጋር ስለባህል ሕክምና ልማድ እና አተገባበር፤ እንዴት መጠናት እንዳለበት፤ በማኅበሩ በኩል ምን ዓይነት ድጋፍና ትብብር እንደሚደረግልኝ ተማከርኩ (ትውውቃችን ከ2005 ዓ.ም ይጀምራል)። በተለይ አባቴ "እንደ ቆሎ ተማሪ በያገሩ ዞረህ የዕፅዋትን ምስጢርና ጥበብ ተማር፤ ሙያው ባሕር ነው፤ ወንዝ ያሻግርሃል፤ እንደዘመኑ ወጣት ከተማ ለከተማ አትውሸልሸል [አትዙር]" በማለት ከመምከር ባለፈ፤ ቁጣ በቀላቀለ መልኩ ሙያውን እንዳጠና ይገፋፋኝ ነበር። ሃጂ ሼህ አሊ ደግሞ፤ የባህል ሕክምና እንዲጠና ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከዐባይ ጥናትና ምርምር ማዕከል ጋር በ2007 ዓ.ም (የጋራ) ስምምነት ፈጥረው (በወቅቱ የዚህ ጥናት አቅራቢ በዐባይ ጥናትና ምርምር ማዕከል የአገር በቀል ዕውቀት ንዑስ ክፍል አስተባባሪ ነበር)፤ አብረው ለመስራት እና በዩኒቨርሲቲው በኩል በባህል ሕክምና መስክ ምርምር ለሚያካሂዱ አባላት

የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ፤ ለዞንና ለወረዳ የባህል ሐኪሞች ማኅበር ተወካዮች በማሳወቅ፤ ለጥናት አቅራቢዎች እገዛ እና ትብብር እንደሚያደርጉ አስረድተዋል (ይህ ተግባር /ለባህል ሐኪሞች/፤ የባህል ሕክምና ፈቃድ ለማግኘትና ውል ለማሳደስ፤ የማኅበሩ አባል ሆኖ ለመቀጠል እንደ አንድ ተግባርና ግዴታ ይታያል)። እኔም የነበረኝን ቀረቤታና ትውውቅ መነሻ በማድረግ በባህል ሕክምና ዘርፍ፤ ጥናት ለማካሄድ ፍላጎት አደረብኝ።

በ2009 ዓ.ም፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች የሚሰጠውን "Issues in Popular Culture and Environmentalism" ኮርስ ስከታተል፤ የባህል ሕክምና እና ሥነ ምህዳርን በማገናኘት፤ እንዴት አጣምሮ ማጥናት እና መመርመር እንደሚቻል በቂ ትምህርትና ግንዛቤ አገኘሁ። በዚሁ አጋጣሚ ለምንማረው ኮርሱ ማሟያ ርዕስ መርጠን እንድናስገባ ተጠየቅን። "የባህል ሕክምና ሥርዓትና አተገባበር ከሥነ ምህዳር አንፃር በፎገራ ወረዳ" በሚል ርዕስ አስገባሁ። ጉዳዩ ተቀባይነት አግኝቶ የመስክ ስራዬን ለመተግበር ከምማርበት ዩኒቨርሲቲ የትብብር ደብዳቤ አፅፌ፤ ከፎገራ ወረዳ የባህል ሐኪሞች ጋር በመተዋወቅ ሥራ ጀመርኩ።

የመስክ ሥራ ስጀምር እንዳሰብኩት አልሆነም፤ አጭር ትውውቅ አድርጌ፤ ጉዳዩን አስረድቼ፤ ቀጠሮ ይዤ በተባለው ቀን ውይይት ስናደርግ፤ ለማቀርብላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጡ ግራ በመጋባት፤ አጭር፣ ቁጥብና የተገደበ መልስ ይሰጣሉ። ጥቂቱ ደግሞ በጥርጣሬና በስጋት እንቅስቃሴዬን እየተከታተሉ የኔን ማንነት እና ከየትነት ማጣራት ላይ እንዳተኮሩ ገባኝ? ለዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተፃፈልኝ የትብብር ደብዳቤ ማሳየት፤ ከመንግስት ተቋማት ባለፈ ዋጋ አልነበረውም፤ ከምርምሩ ይልቅ እራሴን በማስተዋወቅ ሂደት ጊዜ አጠፋሁ። በወቅቱ የባህል ሐኪሞችን በአጭር ጊዜ ቀርቦና ተዋውቆ መረጃ ለመሰብሰብ ከባድ እና አደገኛ እንደሆነ ገባኝ። አንተ ማነህ? ከየት ነህ? ማን ላከህ? ለምን ፈለከው? የትኛው ጤና ቢሮ ነው የላከህ? ለኛ ምን ጥቅም አለው? ምን ትሰጠናለህ? እኛን አጥንተህ ግብር ልታስጨምርብን ነው? ወንጀል ይሰራሉ ለማለት ነው? ፈቃድ አላወጣችሁም ልትለን ነው?፤ ነፍስ አጥፍታችኋል "እየተባልን" ስንቶች ናቸው በእስርና በስደት እሚከራተቱ? በማለት በእኔ ላይ ያላቸውን ሥጋትና እምነት፤ በዘርፉ ላይ ያለውን ተግዳሮች አቅማቸው በፈቀደ መልኩ አስረዱኝ።

በሌላ በኩል ደግሞ "አድባር፣ ቡዳ፣ ዛር፣ አጋንንት፣ ጋኔል" ማጥናት ምን ይጠቅማል? (በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ ካለማግኘት፤ ጉዳዩን አቅልለው ከማየት ወይም ከተመራማሪው የማስረዳት ድክመት ይመነጫል)፤ እስቲ ስለአጋንንት ማውራት ለአንተስ ለጤናህ ጥሩ ነው?

(ለተመራማሪው ከማሰብ ይመስላል)"፤ "አዳል ሞቲ፤ አዳኝ ወርቁ፣ እራሄሎ የትም ቦታ አይጠሩም፤ በማንም አንደበት አይነሱም፤ መንፈሶቹ ይቆጣሉ፤ መቅሰፍት ይጥላሉ" በማለት ያስፈራራሉ (ለዛር እና ለአድባር ያላቸውን ክብር እና ፍርሃት ይጠቁማል)፤ በየመስሪያ ቤቱ አጉል ልማድ እየተባለ ሲወገዝ የኖረ እንዴት ጥናት ይሆናል? ይሄ የድሮ ባህል ነው? በማለት የማቀርበውን ጥያቄ አጥብቀው ሲሸሹ፤ እንደማያውቁት ሲያስመስሉ ታይቷል።

ርዕሰ ጉዳዩ እየከበደኝ፤ ነገሮች እየተወሳሰቡ ሲመጡ በቀጥታ የቀረብኩበት መንገድ፣ ትውውቅና ሂደት ተገቢ አለመሆኑ ገባኝ። የመስክ ሥራዬን አቋርጬ ወደ ባሕር ዳር ተመለስኩ። ጉዳዩን ለሃጂ ሼህ አሊ አማከርኩ፤ በጣም ሣቁ! "አይ ልጄ አጉል ተንገላታህ፤ በሩ እያለ በጓዳ ልግባ ብለህ ነው፤ እኔ ሰው ሳልሰጥህ መሄድህ ነው ጥፋቱ" በማለት ጉዳዩን አስረዱኝ፤ በዕድሜ የበሰሉና የታወቁ የባህል ሐኪሞችን መርጠው፤ በሞባይል ስልካቸው ደውለው "ልጃችን ነው ተቀበሉት! አብሮን ነው የሚሰራው፤ የማኅበራችን አባል ነው! በአካባቢያችሁ ያሉትን የባህል ሐኪሞች አስተዋውቁት፤ ሰው እንዳይተናኮለው ጠብቁት!" በማለት አሳስበውና አስተዋውቀው፤ የትብብር ደብዳቤ ፅፈውልኝ ተመልሼ ሄድኩ። የተባሉትን ሰዎች አገኘሁ፤ እንደቤተሰብ ተቀብለው፤ ከምሰበስበው መረጃ ባለፈ በመልካም ሰብዕና አስተናግደው፤ አብልተውና አጠጥተው ሸኙኝ። ከዚህ በላይ ይነሱ የነበሩ የማንነትና የከየትነት ጥያቄዎች ቀሩ፤ በምትኩ ቤተሰባዊ ግንኙነት፣ አመኔታ እና ትውውቅ እየተጠናከረ ሄደ። የተሰጠኝን የመስክ ስራ አጠናቅቄ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመለስኩ (ሐምሌ 2009)። እግረ መንገዴን ከፋርጣ እና ከሊቦ ከምከም ወረዳ የባህል ሐኪሞች ጋር ተዋወቅሁ።

ይህ ልምድና ተመክሮ፤ በ2010 ዓ.ም ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚሆነኝን ርዕስ "የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ" በሚል ይዘት አቅርቤ ጥናቱ ፀደቀ። ለምርምር በተመረጡ ወረዳዎች በመሄድ የባህል ሐኪሞች ማኅበር ተወካዮችን አማክሬና ፈቃድ አግኝቼ፤ በአካባቢያቸው የሚገኙ የባህል ሐኪሞችን መርጠውና አስተዋውቀው ሲሸኙኝ (የደቡብ ጎንደር ዞን የባህል ሐኪሞች ተወካይ መሪጌታ ብሩህ፤ የፋርጣ ወረዳ፤ መሪጌታ ፋንታሁን፤ የሊቦ ከምከም አቶ ደሴ እና የእብናት አቶ ደርሶ) ሸክሜን አቀለሉልኝ፤ ጉዞዬን አሳጠሩልኝ፤ መልካም ግንኙነት ፈጠሩልኝ። በተለይ ሃጂ ሼህ አሊ የፃፉልኝ ደብዳቤ በየቀበሌው ለሚገኙ የባህል ሐኪሞች በማሳየት ስቀርባቸው፤ በይሁንታ ተቀብለው፤ የምፈልገውን መረጃ ሰጥተው፤ በቤታቸው አርፌ፣ በልቼ፣ ተጫውቼ፣ አድሬ (በእብናት መሪጌታ ስዩም እና በፋርጣ ደብተራ መልኩ) እና ዘመድ አፍርቼ ስመለስ፤ ከምርምሩ በላይ እኔን

ለማስተናገድ የነበረው ውጣ ውረድ (ከባድ መስሎ ታየኝ)፤ ለእንግዳ ያላቸው ክብር እና ፍቅር፤ ማኅበራዊ ጨዋታቸው በእጅጉ ይስብ ነበር፡፡

እኔም አካባቢውን ስላመድ፤ አብሬያቸው ፀበል፣ ቤተክርስቲያ፣ ለቅሶ፣ ሰርግ፣ ተስካር፣ ገበያ እና ማኅበራዊ ጉዳዬች ላይ በመሳተፍ ማኅበረ-ባህላዊ ሁነቶችን በቀጥታ፤ የባህል ሕክምና እና ሥነ ምህዳርን በተጓዳኝ የማጥናት ሥራዬን ቀጠልኩ፡፡ አካልና መንፈሴን፤ ቀልብና ሥጋዬን ከከተማው ድባብ ነጥዬ፤ ከገጠሩ ማኅበረሰብ ጋር በማስተሳሰር ውሎና አዳሬ፤ ቁርስ ምሳዬ በዛው ሆነ፡፡ ለምን? ሲባል፤ የሚኖሩትን፣ የሚበሉትን፣ የሚሰሩትን፣ የሚረግጡትን፣ የሚያሸቱትን፣ የሚያስቡትን፤ ከመጠየቅ ይልቅ አብሮ በመኖርና በመሆን መንፈሱን መላመድ፤ ድባቡን ማወቅ፤ አብሮ መስራት፣ መሳቅና መጫወት የእለት ስንቅ እና የሕይወት ትጥቅ ይሰጣል፡፡ እኔም እንዲህ ገጠመኝ፡-

በፋርጣ ወረዳ ጋሳይ ቀበሌ በአንድ የባህል ሐኪም ቤት ተገኝቼ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፤ "እስቲ ትንሽ ቁራሽ ነገር አፋችን ላይ ጣል አድርገን እንጫወት፤ ጥቁር እንግዳ [አዲስ እንግዳ] እኮ ነህ፤ ና! ግባ" በማለት ጋበዙኝ፡፡ ስለአካባቢው እየተጫወትን ባለቤታቸው ቡና ጥደው፤ በገበቴ እንጀራ አቅርበው አቦል ቡና ሲወርድ (ሲወጣ)፤ አባወራ መርቀው፤ መብላትና መጠጣቱ ተጀመረ፡፡ የቀረበውን ምግብ እየበላን፤ ወደ ማሳረጊያው ስንደርስ፤ ትኩስ የዳቦ ሙልሙል በየፊታችን ቀረበ፤ "ዳቦ ተበልቶ ሳያልቅ ገበታ አይነሳም፤ ቀስ እያልክ ብላ ቡናው እስከሚነሳ [እስከ ሶስተኛ ዙር]" አሉኝ የቤቱ ባለቤት፡፡ የዳቦው ጣዕም ከተለመደው ዳቦ የተለየ ቃና እና ሽታ ነበረው፡፡ ባለቤታቸው የኔ ግራ መጋባት የገባቸው መሰለኝ "አይዞህ የባህር ዛፍ ዳቦ ነው፤ ትኩስ ነው፤ አይ የከተማ ሰው እንዲህ ያል ነገር አይወዱ" አሉ፡፡ የባህል ሐኪሙ "በርታ አይዞህ! ጎረምሳ አይደለህ እንዴ፤ ለሆድ መዳኒት ነው፤ እንዳትንቀው" አሉኝ፡፡ የተሰጠኝን የባህር ዛፍ ዳቦ በልቼ ጨረስኩ፡፡ ነጭ ባህር ዛፍ፤ ለምች፣ ለጉንፋን፣ ለራስ ምታት (አፍልቶ መታጠን)፣ ለመጥፎ ሽታና ጠረን፤ ለተባይ ማጥፊያ፣ እንጀራ እና ዳቦ እንዳይሻግት፣ እህል እንዳይነቅዝ የማድረግ ኃይልና ምስጢር እንዳለው አጫወቱኝ፡፡ ምርምሩ ተጀመር ማለት ነው፡፡

አንድ ጊዜ ደግሞ በእብናት ወረዳ "ጀማን ደንጋህ" ቀበሌ ከመንገድ መሪ ረዳቴ ጋር ስንሄድ ትልቅ ወራጅ ወንዝ አገኘን፤ በወንዙ ዳር በርከት ያሉ የአካባቢው ሰዎች ልብስ ያጥባሉ፤ በሁኔታው ግራ ተጋብቼ፤ ሰላምታ አቅርበን እኛም ተቀላቅለን እግራችንን መታጠብ ጀመርን፡፡ ለመመሳሰል ያህል እንጂ እግሬን ለመታጠብ አቅጄ አልነበረም፡፡ አንድ አባት ደክሚቸው ጥላ ስር አረፍ ብለዋል፡፡ ሰላምታ ሰጠሁና ቀስ ብዬ፤ አባቴ፤ ሁል ጊዜም እንደዚህ ይታጠባል እንዴ?

አልኳቸው። "ወረርሽ ገብቶ ነው፤ የእከክ ወረርሽኝ፤ እጃችን ሰውነታችን አልተረፈም፤ ኩታራውን ጨረሰው" አሉኝ። እሳቸውን አመስግኜ በምን እንደሚያጥቡ ለማየት ወደ ወንዙ ተጠጋሁ፤ የሳሙና ዘር በአካባቢው የለም። በሳሙና ምትክ፤ የእንዶድ ቅጠል እና ፍሬ፤ የወፍጠጭ ሥር፣ የብሳና ቅጠል በአለት ድንጋይ ጨቅጭቀው፤ በአረፋው ጋቢና ብርድልብስ ያጥባሉ። አንዱን ጎበዝ ጠጋ ብዬ ሳሙና አይሻልም እንዴ ወንድሜ? ስለው "ሳሙና፤ ለቆሻሻ ነው፤ እከክን መቼ ያስለቅቀዋል አለኝ" ጉዳዩ ገርሞኝ አመስግኜ፤ ቀጠሮ ወደ ያዝኩበት የባህል ሐኪም ቤት ሄድኩ።

በቀጠሮ ቦታዬ ደርሼ፤ ሰላምታ ተለዋውጠን፤ ገጠመኜን ለባህል ሐኪሙ አስረዳሁ። እሳቸውም ንግግሬን ቀበል አድርገው፤ "የእከክ ወረርሽኝ ተነስቶ ሕዝቡ እጅና እግሩን እየፎከተ[እያከከ] ነው፤ ሊጨርሰው ነው" አሉኝ፤ በዚህ አጋጣሚ ጎረቤት በአልጋ ላይ ተኝተው የሚታከሙ አዛውንት እንዳሏቸው፤ በመጠቆም የዘፈዘፉትን ዉኃ እና የቀመሙትን መድኃኒት ይዘው ሄዱ፤ ሰውነታቸውን በማጠብ የቀመሙትን መድኃኒት ቀቧቸው። ስራቸውን ሲጨርሱ፤ ዘፍዝፈው በአስቀመጡት ዉኃ እጃቸውን ታጠቡ (የእንዶድ ፍሬ፣ ቅጠልና ሥር፣ የወፍ ጠጭ ሥር፣ የብሳና ቅጠል፣ የግራዋ ቅጠል ወቅጠውና ጨቅጭቀው በእንስራ ዉኃ ዘፍዝፈው በማሳደር፤ በእከክ የተያዙ ሕሙማንን አካልና ልብስ በማጠብና በማሳጠብ በሽታውን እንደሚፈውሱ አስረዱ)። ለምን? ስላቸው፤ "ታካሚ ነክተህ በዚህ መታጠብ አጋንንት ያርቃል፤ ተስቦ አያመጣም፤ ዋናው መከላከያ ይሄ ነው" በማለት አስረዱኝ።

ይህ ተግባር ባህላዊ የአጋንንት መከላከያ/ማፅጃ ወይም "ሳኒታይዘር" ይሆን?፤ ብቻ ልብ ብሎ ለተመለከተ አጥኚ፤ ዐፈርና ቅጠሉ፤ ምግብና ዉኃው ምስጢራቸውን ይናገራሉ፤ ገቢራቸውን ያስረዳሉ። የባህል ሕክምና ዕውቀትና ተግባርም፤ የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የማዕድናት፣ የሥነ ምህዳርን ባሕርይ፣ ዓይነት እና ሙያን በመለየት የሕክምና አገልግሎት መስጠትን ግብ ያደርጋል። ሰው፣ ልማድ እና ሥነ ምህዳር ተጣምረው፤ ለአካላዊ ቁስል እና ለመንፈሣዊ ጭንቀት ድኅነትና ፈውስን እንደሚሰጡ ከመስክ ተመክሮ መገንዘብ ተችሏል። በቀጣይ ምዕራፍ የደቡብ ጎንደር ዞን መልክዓ ምድራዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ዳራ ቀርቧል።

## ምዕራፍ አራት፡- የደቡብ ጎንደር ዞን መልክዓ ምድራዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ዳራ

ደቡብ ጎንደር ዞን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከሚገኙ 13 (አሥራ ሶስት) ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን የዞኑ ዋና ከተማ ደብረ ታቦር ነው፡፡ ደብረ ታቦር ከክልሉ ርዕሰ መዲና ባሕር ዳር በ98 ኪሎ ሜትር፣ ከአዲስ አበባ በ666 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ደቡብ ጎንደር ዞን፤ በሰሜን ሰሜን ጎንደር፣ በደቡብ ምሥራቅ ጎጃም፣ በምሥራቅ ሰሜን ወሎ፣ በምዕራብ ምዕራብ ጎጃም፣ ጣና ሐይቅ እና ምዕራብ ጎንደር ያዋስኑታል፡፡ ዞኑ በአስር ወረዳዎች (ፋርጣ፣ ሊቦ ከምከም፣ እብናት፣ ላይ ጋይንት፣ ታች ጋይንት፣ ስማዳ፣ ደራ፣ አንዳቤት፣ እስቴ፣ ፎገራ) እና በአምስት የከተማ አስተዳደር (ደብረ ታቦር፣ ሊቦ ከምከም፣ ወረታ፣ ላይ ጋይንት፣ ክምር ድንጋይ) የተዋቀረ ሲሆን በ299 የገጠርና በ29 የከተማ በድምሩ በ328 ቀበሌዎች ተደራጅቷል፡፡ የዞኑ የመሬት ቆዳ ስፋት 14,175.85 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን ከአጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ 56.1 በመቶ ለእርሻ፣ 13.1 በመቶ ለግጦሽ፣ 0.63 በመቶ በደን የተሸፈነ፣ 22.5 በመቶ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል ጥብቅ መሬት፣ 7.4 በመቶ ጠፍ መሬትን (ደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ /ደ.ጎ.ዞ.ባ.ቱ.ቢ/፣ 2007፤ ገፅ 17-28) ይሸፍናል፡፡

ደቡብ ጎንደር ዞን ከባሕር ጠለል በላይ 1300 እስከ 4232 ሜትር (ከኒቋራ እስከ ጉና ተራራ ጫፍ) ያለውን የከፍታ መጠን ያካልላል፡፡ በዚህ ከፍታ አራት ዓይነት የዐየር ንብረቶች የሚገኙ ሲሆን 55.34 በመቶ ቆላማ፣ 46 በመቶ ወይና ደጋ፣ 21.89 በመቶ ደጋ፣ 1.97 በመቶ በውርጭ ተሸፍኗል፡፡ ዞኑ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ የመስሕብ ሐብቶች ባለቤት ሲሆን በዐባይ (118 ኪሎ ሜትር) እና በተከዜ (74 ኪሎ ሜትር) ተፋሰስ ወንዞች መሃል ይገኛል፡፡ በዞኑ ከሚገኙ ዋና ዋና ወንዞች መካከል ርብ፣ ጉማራ፣ በሸሎ ይጠቀሳሉ፤ ከተፈጥሯዊ ተራሮች መካከል አንዱና ዋናው ጉና ተራራ (4232 ሜትር ከፍታ) ሲሆን እስቴ ዴንሣ፣ ሹም ገደል፣ ቋላ ዮሐንስ፣ "አባ ዝንጀር" ተራራዎች ይገኛሉ፤ ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ የሰባት ወንዞች መነሻም፤ እንደሆነ መረጃዎች (ደ.ጎ.ዞ.ባ.ቱ.ቢ፣ 2007፤ ገፅ 18-20) ጠቁመዋል፡፡ ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል ፋርጣ፣ ሊቦ ከምከምና እብናት ወረዳዎችን በመለየት የመስክ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በነዚህ ወረዳዎች በአማካይ የኦርቶዶክስ (98%)፣ የእስልምና (1.5%) እና የሌላ እምነት ተከታዮች (0.5%) ይገኛሉ፡፡ በቀጣይ ይዘት ለጥናት የተመረጡ ወረዳዎችን የሚያሳይ ካርታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## የካርታ መግለጫ፡- ለጥናት የተመረጡ የደቡብ ጎንደር ዞን ወረዳዎችን የሚያሳይ ካርታ

የጥናት ቦታን የሚያሳይ ካርታ




ምንጭ፡- የደቡብ ጎንደር ዞን ፕላንና ካርታ ቢሮ ጥቅምት/2011 ዓ.ም

ከዚህ በላይ የቀረበው ካርታ እንደሚያመለክተው፤ ጥናቱ ፋርጣ፣ ሊቦ ከምከም እና እብናት ወረዳዎችን ማዕከል አድርጎ የተካሄደ ሲሆን፤ መረጃ የተሰበሰቡባቸውን ቀበሌዎች አመላክቷል፡፡

በቀጣይ ይዘት ለጥናት የተመረጡ ወረዳዎች መልክዓ ምድር፣ ሥነ ሕዝብ፣ የትምህርትና የጤና ሽፋን፤ በዞኑ የሚገኙ ዋና ዋና የተፈጥሮ እና የሃይማኖት መስሕቦች መገኛ ቦታና አገልግሎት፤ የማኅበረሰቡ ባህላዊ እምነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 4.1 ለጥናት የተመረጡ ወረዳዎች መልክዓ ምድር፣ ሥነ ሕዝብ፣ የትምህርትና ጤና ሽፋን

በዚህ ንዑስ ይዘት ሥር የወረዳ መገኛና አዋሳኝ ቦታዎች፤ መልክዓ ምድር፣ የዐየር ንብረት፤ ሥነ ሕዝብ፣ የመሰረተ ልማት ሽፋን መረጃዎች እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠዥ ሁለት፡- የወረዳ መገኛና አዋሳኝ ቦታዎች፤**

ለጥናት የተወረጡ ወረዳዎች አዋሳኝ ቦታዎች፣ ዋና ከተማ፣ የመሬት ቆዳ ስፋት በሄክታር፣ የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች ብዛት፣ ከዞንና ከክልል ርዕሰ ከተማ ያላቸው ርቀት በኪሎ ሜትር፤

| ተራ ቁጥር | የወረዳው ስም | የወረዳው አዋሳኝ ቦታዎች | | | | የወረዳው ዋና ከተማ | የወረዳው መሬት የቆዳ ስፋት በሄክታር | የወረዳው ቀበሌ ብዛት | | | የወረዳው ርቀት ከዞንና ክልል ከተማ በኪሎ ሜትር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በሰሜን | በምሥራቅ | በደቡብ | በምዕራብ | | | ገጠር | ከተማ | ድምር | ደ.ታቦር | ባሕርዳር |
| 1. | ፋርጣ | እብናት እና ሊቦ ከምከም ወረዳ | ላይ ጋይንት ወረዳ | እስቴ ወረዳ | ፎገራ ወረዳ | ደብረ ታቦር | 107,076.57 | 41 | 2 | 43 | 0 | 98 |
| 2 | ሊቦ ከምከም | በለሳ ወረዳ | እብናት ወረዳ | ፎገራወረዳ | ጣና ሐይቅና ከጎንደር ዙሪያ ወረዳ | አዲስ ዘመን | 95,157.00 | 32 | 2 | 34 | 67 | 85 |
| 3 | እብናት | ምሥራቅ በለሣ ወረዳ | ድሃና ቡግና ወረዳ | ፋርጣ ወረዳ | ሊቦ ከምከም ወረዳ | እብናት | 249,427.00 | 35 | 2 | 37 | 109 | 122 |

ምንጭ፡- የፋርጣ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፤ 2010፤ የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010፤ የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010፡፡ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረ-ኢኮኖሚ መረጃ፤ 2006፡፡

## ሰንጠረዥ ሶስት፡- የወረዳ መልክዓ ምድራዊና የዐየር ንብረት ሁኔታ፤

### ለጥናት የተመረጡ ወረዳዎች ከፍታ ከባሕር ጠለል በላይ፣ አማካይ የዝናብና የሙቀት መጠን፤

| ተራ ቁጥር | የወረዳው ስም | የወረዳው ከፍታ ስርጭት ከባሕር ጠለል በላይ በሜትር በመቶኛ (%) | | | | | የወረዳው አማካይ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴንቲግሬድ | የወረዳው አማካይ የዝናብ መጠን በሚሊ ሊትር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ውርጭ | ደጋ | ወይና ደጋ | ቆላ | ድምር | | |
| | | ከ3500.ሜ.በላይ | ከ2500-2500.ሜ | ከ1500-2500.ሜ | ከ1500-500.ሜ | - | | |
| 1. | ፋርጣ | 1.6 | 44.0 | 54.4 | 0 | 100 | 9 - 25 ዲ.ሴ | 1250-1497 ሚ.ሊ. |
| 2 | ሊቦ ከምከም | 0 | 4.1 | 95.9 | 0 | 100 | 11 - 27.9 ዲ.ሴ | 900-1400 ሚ.ሊ. |
| 3 | እብናት | 0 | 15.0 | 15.0 | 50.0 | 100 | 10 - 32 ዲ.ሴ | 800-1400ሚ.ሊ. |

ምንጭ፡- የፋርጣ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፤ 2010፤ የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010፤ የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010። የደቡብ ጎንደር ዞን ማኀበረ-ኢኮኖሚ መረጃ፤ 2006።

## ሰንጠረዥ አራት፡- የወረዳ ሥነ ሕዝብ መረጃ፤

### ለጥናት የተወረጡ ወረዳዎች ሕዝብ ብዛት፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት እና መተዳደሪያ፤

| ተራ ቁጥር | የወረዳው ስም | የወረዳው ሕዝብ ብዛት*[46] | | | የወረዳው ሕዝብ ዋና መግባቢያ እና የሥራ ቋንቋ | የወረዳው ሕዝብ በዋናነት ሚከተሉት ሃይማኖት በመቶኛ(%) | | | | የወረዳው ሕዝብ መተዳደሪያ የኢኮኖሚ መሰረት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | | የኦርቶዶክስ | የሙስሊም | የሌላ እምነት ተከታይ | ድምር | ግብርና | እደ ጥበብ | ንግድ | ሌሎች | ድምር |
| 1. | ፋርጣ | 139,927 | 136,221 | 276,148 | አማርኛ | 97.4 | 2.0 | 0.6 | 100 | | | | | |
| 2 | ሊቦ ከምከም | 111,880 | 108,808 | 220,688 | አማርኛ | 98 | 1.5 | 0.5 | 100 | 92.0 | 1.8 | 1.59 | 4.61 | 100 |
| 3 | እብናት | 135,563 | 128,557 | 264,120 | አማርኛ | 99 | 1.0 | 0 | 100 | 93.3 | 1.9 | 1.45 | 3.35 | 100 |

ምንጭ፡- የፋርጣ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፤ 2010፤ የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010፤ የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010። የደቡብ ጎንደር ዞን ማኀበረ-ኢኮኖሚ መረጃ፤ 2006።

---

[46]*የወረዳዎቹን ሕዝብ ብዛት፤ ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን እ.ኤ.አ በ2007 የቀረበውን የቤቶችና ሕዝብ ቆጠራ ውጤት መሰረት ያደረገ መሆኑን ልብ ይሏል።

**ሰንጠረዥ አምስት፡- የወረዳ መሰረተ ልማት፤**

**ለጥናት የተመረጡ ወረዳዎች መሰረተ ልማት፣ የትምህርት እና ጤና ሽፋን፤**

| ተ.ቁ | የወረዳው ስም | የመሰረተ ልማት ሽፋን መንገድ፣ መብራት፣ ውኃ እና መገናኛ (ስልክ) በፐርሰንት (%)/፤በቁጥር(ቀበሌዎች) | | | | የትምህርት ሽፋን አፀደ ሕፃናት ት/ቤት፣ 1ኛ ደረጃ (1-8)፣ 2ኛ ደረጃ (9-12)፣ ሙያ ቴክኒክ ኮሌጅ | | | | | የጤና ሽፋን ጤና ጣቢያ፣ ጤና ኬላ፣ ሆስፒታል፣ የክትባት ጣቢያ፣ የግል ክሊኒክ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መንገድ (%) | መብራት በቁጥር | ንዑህ የመጠጥ ውኃ (%) | ስልክ በቁጥር | አፀደ ሕ. | 1-8 | 9-12 | ሙ.ቴ.ኮ | ድምር | ጤ.ጣ | ጤ.ኬ | ሆ/ል | የክ.ጣ | የግ.ክ | ድምር |
| 1. | ፋርጣ | 48.78 | 16 | 83 | 42 | 6 | 63 | 4 | 1 | 74 | 10 | 41 | 0 | 39 | 2 | 92 |
| 2 | ሊቦ ከምከም | መ/የ | 11 | መ/የ | 26 | 5 | 60 | 3 | 1 | 69 | 8 | 36 | 1 | 26 | 2 | 73 |
| 3 | እብናት | መ/የ | መ/የ | መ/የ | መ/የ | 1 | 87 | 4 | 1 | 93 | 10 | 43 | 1 | 21 | 3 | 78 |

ምንጭ፡- የፋርጣ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፤ 2010፤ የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010፤ የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010። የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረ-ኢኮኖሚ መረጃ፤ 2006።

## 4.2 የደቡብ ጎንደር ዞን ዋና ዋና ተፈጥሯዊና ሃይማኖታዊ መስሕቦች

በዚህ ንዑስ ይዘት ሥር የደቡብ ጎንደር ዞን ዋና ዋና የፀበል፣ ፍል ውኃ እና የማዕድን "አምቦ" ውኃ መገኛ ቦታዎችና አገልግሎት፤ የተፈጥሮ ጥብቅ ደን፣ ጥንታዊ ገዳማትና የሃይማኖት መገኛ ቦታና አገልግሎት እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

### 4.2.1 የፀበል፤ ፍል ውኃ እና "የማዕድን አምቦ" ውኃ መገኛ ቦታና አገልግሎት

በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ከሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻ መንፈሣዊ መስሕብ ሐብቶች መካከል ፀበል፤ ፍል ውኃ እና "የማዕድን አምቦ ጠበል" ቦታዎች ይጠቀሳሉ። እነዚህ አካባቢዎች "የተፈጥሮ ሕክምና ቱሪዝም" (Natural Medical Tourism)[47] አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ተብለው እንደሚጠሩ፤ አቶ መልካሙ ይጠቁማሉ (ቃ.መ፤ 17/04/2011 ደብረ ታቦር)።

**ከፀበል ቦታዎች መካከል፡- ዜና ማርያም፣ ሊቦ ጊዮርጊስ እና ዋሻ ተክለኃይማኖት ፀበል** (በሊቦ ከምከም ወረዳ)፤ አካለ ክርስቶስ ገዳም እና "ሰጥላ" የፀበል ዋሻዎች (በላይ ጋይንት ወረዳ፤ በዚህ

[47]በዚህ ጥናት የተጠቀሱ ቦታዎች ለጥናቱ ባላቸው ቅርበት፣ ተደራሽነት እና "በወፍ በረር" ዋና ዋና ተብለው በዞኑ ባህልና ቱሪዝም የተጠቀሱትን ይመለከታል። ከዚህም በተጨማሪ የጥናቱ ትኩረት በሆኑ ቦታዎች (ፋርጣ፣ ሊቦ ከምከም እና እብናት ወረዳዎች) የሚገኙ ተፈጥሯዊ እና ሃይማኖታዊ መስሕብ ቦታዎች ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ልብ ይሏል።

ቦታ 12 የፀበል ዋሻዎች የሚገኙ ሲሆን የአሥራ ሁለቱም ፀበል ጣዕም እንደሚለያይ ተጠቁሟል)፤ ደብረ ዕንቁ ማርያም፣ "እንጉም" አቦ ገዳም እና ገዳም ሥላሴ ፀበል (በስማዳ ወረዳ)፤ ወለተ ጴጥሮስ ገዳም፣ ጋፋት ተክለ ኃይማኖት ፀበል (በእስቴ ወረዳ)፤ ደብረ ተክለ ኃይማኖት ገዳም ፀበል (በእብናት) እና ገብሩ አምባ እየሱስ ፀበል (በፋርጣ ወረዳ) ይገኛሉ (የደ.ጎ.ዞ.ባ.ቱ፤ 2007)፡፡ የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ የሆኑት አቶ ሰሎሞን፤ ዞኑ ተፈጥሯዊና መንፈሳዊ የፀበል፤ ፍል ውኃዎች እና "የማዕድን ጋዝ ወይም አምቦ ጠበል" መገኛ ቦታዎች፤ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጎብኝዎችን በመሳብ ከፍተኛ የቱሪዝም ሐብት እና የገቢ ምንጭ እንደሚያስገኙ፤ ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 16/04/2011 ደብረ ታቦር)፡፡

በሊቦ ከምከም ወረዳ በአገላ ማንቶራ ቀበሌ በዜና ማርያም የፀበል ቦታ ሲጠመቁ ያገኘኋቸው ወ/ሮ ምህረት "የዜና ማርያም ጠበል ብዙ ታምር አላት፤ ድዉይ [በሽተኛ] ታድናለች፤… ዓይን ታበራለች፤ የሆድ ሥራይ [ሕመም] ታወጣለች…" በማለት ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 08/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ መሪጌታ ልሳነወርቅ የፀበል ቦታዎች በቅዱሳን አባቶች የተባረኩ፣ የረድኤታቸው እና የቅድስናቸው ማስታወሻ ስለሆኑ እንደቅድስናቸው፤ "የጠበሉም" ዓይነት፣ ባሕርይ፣ ጣዕምና መልክ ከቦታ ቦታ እንደሚለያይ ገልፀው፤ የዜና ማርያም ፀበል ለሆድ፣ ለጆሮ እና ለዓይን ሕመም መድኃኒት ሲሆን የሊቦ ጊዮርጊስ ፀበል ደግሞ "ለመተትና ለአጋንንት"፣ ለራስ ፍልጠት [ሕመም]፣ ለሆድ ቁርጠት መድኃኒት እንደሆነ፤ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 27/04/ 2011 ሊቦ ከምከም) ፡፡

**ከፍል ውኃ ቦታዎች መካከል፡-** በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ከሚገኙ ዋና ዋና የፍል ውኃ መስሕብ ቦታዎች መካከል ዋንዛዬ እና ወንቅሸት ፍል ውኃ በደራ ወረዳ፤ ጉር አምባ ፍል ውኃ በፎገራ ወረዳ፤ ጎኖ ገብርኤል፣ ገብረ መርዓዊ እና ቸሬ ማይ ፍል ውኃ በአንዳቤት ወረዳ፤ "ጅብና አህያ" ፍል ውኃ በስማዳ ወረዳ (የደ.ጎ.ዞ.ባ.ቱ.ቢ፤ 2007) ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የፍል ውኃ መስሕብ ሐብቶች ተፈጥሯዊ የሕክምና አገልግሎት (Medical Tourism) ከመስጠት ባለፈ ለወረዳና ለዞኑ "የቱሪዝም" ገቢ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው፤ የፍል ውኃዎቹ ዓይነት፣ የሙቀት መጠን፣ የሚሰጡት አገልግሎት ተለይቶ፣ መሰረተ ልማት ተሟልቶ (ማረፊያ ቤት…)፣ "ከባህላዊ አሰራር ወጥቶ" እና ከመንፈሳዊ አገልግሎት በተለየ፤ የጤና ባለሙያ ተመድቦ አገልግሎት እንዲሰጡ (ዋንዛዬ፣ ወንቅሸት…) ጥረት እየተደረገ መሆኑን፤ ገልጸዋል (አቶ ሰሎሞን እና ወ/ሮ ሙሉ፣ ቃ.መ፤ 16/04/2011 ደብረ ታቦር፤ ፋርጣ)፡፡

Lindstrom (1997; PP.13-15)፤ "Melting in to Great Waters" በሚል ሥራቸው፤ ባህላዊ የፍል ውኃ እጥበት ቀደምት፣ ጥንታዊና ልማዳዊ ተግባር ሲሆን የሰውነት ቆሻሻን በላብ መልክ

ለማስወጣት፣ አካላዊ ጥንካሬ ለማግኘት፣ አዕምሮን ለማዝናናት፣ አካላዊ ውበትን ለማሳመር፣ የቆዳ ጤንነትን ለመጠበቅና ለማለስለስ፣ ጡንቻን ለማፍታታት፣ የአጥንት መገጣጠሚያ ሕመምን ለመፈወስ፣ የአተነፋፈስ ሥርዓትን ለማስተካከል፣ ክብደት ለመቀነስ፣ በሽታ ለመከላከል ፋይዳ እንዳለው፤ አስረድተዋል። አብዛኛው ማኅበረሰብ በአካል እና በመንፈስ "ለመንጻት"፣ ለመታደስ (ሃይማኖታዊ ይዘት)፣ ሥነ ልቡናዊ እረፍት እና እርካታ ለማግኘት፣ በተመስጦ እራስን ለማዳመጥ፣ ከበሽታ ለመፈወስ፤ አስበው እንደሚጠቀሙ (Lopatin,1960; PP.977-979; Lindstrom, 1997; PP.13-15) ገልፀዋል።

የጤና ባለሙያ አቶ ፀሐዬ (ቃ.መ፤ 21/01/2011 ፋርጣ)፤ የዋንዛዬ ፍል ውኃ እና ሌሎችም ለጡንቻ መሸማቀቅ፣ ለሰዉነት ቆዳ መድረቅና መሸብሸብ፤ ለአጥንት መገጣጠሚያ "ኢንዛየም" [ንጥረ ነገር ቅባት] መመረት፣ "አሲዳማ" ኬሚካሎችን ከሰውነት ለማስወጣት፣ የማይፈለጉ የቆዳ "ፈንገሶችን" ለማስወገድ፣ የመገጣጠሚያና የጡንቻ ሕመምን ለማስታገስ፣ የደም ዝውውር ሥርዓትን ለማስተካከል፤ ጠቀሜታ እንዳለው አስረድተዉ፤ ከመንፈሣዊና ሃይማኖታዊ ሐብቱ ባሻገር ለአካላዊ ጤንነት፣ ለአዕምሮ እረፍት፣ ለተለያዩ ሕመሞች የፈውስ ቦታና ምንጭ መሆኑን ገልፀዋል።

**ከ"ማዕድን አምቦ ጠበል"/ውኃ ቦታዎች መካከል፡-** በደቡብ ጎንደር ዞን ከሚገኙ ዋና ዋና የተፈጥሮ "ማዕድን አምቦ" ውኃ መስሕብ ቦታዎች መካከል ደራሞ እና ዘንግ የተፈጥሮ "ማዕድን አምቦ ጠበል" በፋርጣ ወረዳ፤ አሞራ ገደል የተፈጥሮ "ማዕድን አምቦ ውኃ" በፎገራ ወረዳ ይገኛሉ (ደ.ጎ.ዞ.ባ፣ቱ.ቢ.፤2007)።

የደቡብ ጎንደር ዞን የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ የሆኑት አቶ መልካሙ "በዞናችን የተፈጥሮ ማዕድን ውኃ በዋናነት በሶስት ቦታዎች ይገኛሉ፤ የጉና ማዕድን ውኃ ማውጫ ፋብሪካ በአካባቢው ተሰማርቶ የማዕድን ውኃ አሽጎ እንደሚሸጥ" ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 17/04/2011 ደብረ ታቦር)። በአጠቃላይ የአካባቢው ማኅበረሰብ የፀበል፣ የፍል ውኃና "የተፈጥሮ ማዕድን አምቦ ጠበል" ቦታዎች፤ ለተለያዩ የሕመም ዓይነቶች የፈውስ፣ የዕረፍት፣ "የምህረት፣ የዕድቅ፣ የመንፃት" ምንጭ ተደርገው እንደሚታዩ፤ ከአዕምሮ ሕመም፣ ከውስጣዊና ውጫዊ አካል በሽታ ለመፈወስና ለመጠበቅ፣ ለመንፈሳዊ አገልግሎት፣ ለመዝናናት እና አካልን ለማፍታታት አገልግሎት እንዳላቸው የመስክ መረጃዎች አመላክተዋል (መሪጌታ ዘላለም፣ ቃ.መ፤ 20/04/2011 ፋርጣ፤ አቶ ፀሐዬ፣ ቃ.መ፤ 21/01/2011 ፋርጣ)። በዚህ መስክ በቂ ጥናት አላጋጠመኝም፤ ይህን ታሳቢ

በማድረግ ቀጣይ የባህል ሕክምና ምርምሮች ባህልና ጤናን መነሻ በማድረግ "በፀበል፣ በፍል ዉኃ፣ በማዕድን ዉኃ እና በዕፅዋት ጭስ እጥነት" ይዘት ላይ ትኩረት ቢደረግ መልካም መሆኑን እጠቁማለሁ፡፡

### 4.2.2 የተፈጥሮ ጥብቅ ደን፤ ጥንታዊ ገዳማትና የሃይማኖት መገኛ ቦታ እና አገልግሎት

በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ከሚገኙ ዋና ዋና የተፈጥሮ ጥብቅ ደን መስሕብ ቦታዎች መካከል ጣራ ገዳም ጥቅጥቅ ደን እና "ቋላ" ዮሐንስ (በሊቦ ከምከም ወረዳ)፤ አባ መርዓዊ ደን፣ "ፈረዴ" ደን፣ አብርሐም ደን፣ "ዉሻ ጥርስ" ደን፣ ገላውዴዎስ ደን እና "ሐረጊተ" ደን (በአንዳ ቤት ወረዳ)፤ አምባ ደን፣ ድንግል "ፋሮ" ደን፣ "እፍ በይኝ" እና "ዣፍ" ንጉስ ደን (በእብናት ወረዳ) (የደ.ጎ.ዞ.ባ.ቱ.ቢ፤ 2007) ይጠቀሳሉ፡፡

ዞኑ አራት ዓይነት (ዉርጭ፣ ደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላማ) የዐየር ንብረት መገኛ ቦታ መሆኑ ለዕፅዋት፣ ለእንስሳት፣ ለአዕዋፍ እና ለማዕድናት መለያየት እና ስብጥር ምክንያት ይሆናል (አቶ መልካሙ፤ ቃ.መ፤ 17/04/2011)፡፡ የበሽታ ስርጭቱም እንደ ዐየር ንብረቱ ይዘት ከቦታ ቦታ መለያየቱ፤ ለሕመም መንስኤና ፈውስ በመሆን አስተዋጽኦ እንዳለው፤ ምሁራን ጠቁመዋል (Trostle, 2005)፡፡

በዞኑ ከሚገኙ ዕፅዋት መካከል፤ "ውርጫማ እና ደጋማ" በሆኑ አካባቢዎች፤ ጅብራ፣ አዋጁ፣ አስታ፣ ባህር ዛፍ፣ ጽድ፣ ኮሶ እና ቀጋ ይጠቀሳሉ፡፡ ከሣርና ከችፍርግ ዝርያዎች ደግሞ "ጓሴ፣ ጓሣ፣ አሸንዳ፣ ጓንጭሌ-ነጭ ሣር፣ ጭማ"... ይካተታሉ፡፡ በወይና ደጋ ከሚገኙ የዛፍና የቁጥቋጦ ዝርያዎች መካከል፤ ብሳና፣ ዋንዛ፣ ወይራ፣ ጽድ፣ ደድሆ፣ ክትክታ፣ ጥንዡት፣ ሚጥሚ፣ አባሎ፣ ግራዋ፣ ንብ ጥራ፣... ሲሆኑ፤ ከሣርና ከሐረግ ዓይነት ሰንበሌጥ፣ ሰርዶ፣ አዞ ሐረግ፣ አረግ ሬሣ፣ ሙት አንሣ፣ አሰርኩሽ ተበተብኩሽ፣... ይጠቀሳሉ፡፡ በቆላማ ቦታዎች ከሚገኙ የዛፍና የቁጥቋጦ ዝርያዎች ውስጥ፤ ነጭ ግራር፣ ዝግባ፣ ቀረሮ፣ ዋርካ፣ ዶቅማ፣ ሮቃ፣ ብርብራ፣ እንኮይ፣ ቀርቀሃ፣... ይገኛሉ (አቶ ታደሰ፣ ቃ.መ፤ 23/04/2011 ሊቦ ከምከም፤ አቶ አበባው፣ ቃ.መ፤ 02/05/2011 እብናት)፡፡

ከእንስሳት መካከል፤ ዝንጀሮ፣ "ደሜ" ዝንጀሮ፣ ጅብ፣ ሽኮኮ፣ ጃርት፣ አፍንጮ፣ ሚዳቋ፣ ጥንቸል፣ ቀይ ቀበሮ እና ፍልፈል በዋናነት በደጋ እና በወይና ደጋ አካባቢ የሚገኙ ሲሆን የዱር ድመት፣ አነር፣ ጦጣ፣ ድኩላ፣ ሰስ፣ ሚዳቋ፣ ኸግራ፣ ሶረኔ፤... ደግሞ በቆላማ ቦታዎች እንደሚገኙ፤ (አቶ ታደሰ፣ ቃ.መ፤ 23/04/2011 ሊቦ ከምከም) አስረድተዋል፡፡

በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ከሚገኙ ጥንታዊ ገዳማትና የሃይማኖት መስሕብ ቦታዎች መካከል ዋሻ እንድሪያስ፣ "አቢንጋ" ኪዳነ ምህረት፣ "ዳራ" ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ "ጎዛ" እግዚአብሔር አብ በሊቦ ከምከም፤ አካለ ክርስቶስ ገዳም፣ ዙር አባ አቡነ አረጋዊ ፅርሐ አርያም ገዳም፣ "መሠና" መድኃኒያለም፣ የበቅሎ አግት ጨጨሆ መድኃኒያለም፣ "ሽታን" አቦ ቤተ ክርስቲያን፣ ቅዱሣት ቅዱሣን ሰጥላ ማርያም ገዳም፣ ደብረሲና ማርያም፣ አፍ ዋሻ ኪዳነምህረት በላይ ጋይንት፤ "ሣይኮ" ደብረ መድኃኒያለም ኪዳነ ምህረት ገዳም፣ አምስተያ ገዳም፣ ደብረ ተክለሃይማኖት ገዳም በእብናት፤ ዉቅሮ መድኃኒያለም፣ "አትከና" ጊዮርጊስ፣ "ደፋኝ" ማርያም፣ ገብሩ አምባ እየሱስ፣ ማኅደረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን፣ ሕሩይ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በፋርጣ ወረዳ (ደ.ጎ.ዞ.ባ.ቱ.ቢ፤ 2007) ይጠቀሳሉ፡፡ የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ የሆኑት አቶ ሰሎሞን፤ በዞኑ ከሰባ ስድስት (76) በላይ ጥንታዊ ገዳማት እና አብያተ ክርስቲያን እንደሚገኙ ጠቁመው፤ የምስረታ ዘመናቸውም፤ ከክርስቶስ ልደት በፊት 5500 ዓመት እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለውን ዘመን እንደሚሸፍኑ አስረድተዋል (ቃ.መ፤16/04/2011ደብረ ታቦር)፡፡

### 4.3 የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እምነቶች

በዚህ ንዑስ ይዘት ሥር የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እምነቶች (ደንቃራ መተት፣ አንደርቢ፣ ተፈጥሮን መረዳትና የመቆጣጠር ኃይል፣ የበሽታ ሽኝት፣ የዓለሞቼ /ወተቴ በሽታ ሥርዓትና አተገባበር ልማድ) ይዘት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

*ደንቃራ መተት፡-* እንደ መሪጌታ አማረ መረጃ "ደንቃራ መተት" ሲባል፤ ሰውና እንስሳትን ለሕመምና ለሞት የሚዳርግ፤ ሐብት ንብረትን የሚያወድም፣ ሰላምና ጤና የሚነሳ፤ በሕመም ተመስሎ ሰው፣ የቤት እንስሳት እና ሐብት ንብረትን የሚያጠፋ ርኩስ አጋንንት ሲሆን፤ የደንቃራ መተት የሚሰራው፣ የሚጣለውና የሚዘጋጀው ጤናን ለመንሳት፣ ሥራ እና ገበያ ለማሳጣትና ለማስጠላት፣ ሐብት ንብረት ለመበተን፣ ትዳር ለማፍረስ ወይም ለመንሳት፤ ከሰፈርና ከመኖሪያ አካባቢ ለመንቀልና ለማባረር፤ ይሰራል፡፡ ሕይወታችን፣ ትዳራችን፣ ቤተሰባችን፣ ሐብት ንብረታችን፣ ዕውቀታችንን በሚጠሉ፣ በሚቀናቀኑና በሚወዳደሩ ሰዎች ጥላቻ ደንቃራ ይጣላል፡፡ ደንቃራ የመጣል ወይም የማውጣት ዕውቀት ባላቸው ደብተራዎች/መሪጌታዎች የሚዘጋጅና የሚሰራ፤ የተቀበረን ደንቃራ ቆፍረው የማውጣትና የማርከስ፤ ጤና፣ ሐብት፣ ገበያን፤ የመመለስ (የመስራትም የማርከስም) ክህሎት እንዳላቸው (ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም) ይነገራል፡፡

ደንቃራ መተት፤የሚሰራው፣ የሚጣለው፣ የሚመተትበት እና የሚጣልባቸው ቦታዎች በሰውና በከብት መውጫና መግቢያ በር፣ በሥራ ቦታ፣ በምግብና መጠጥ ማስቀመጫ አካባቢ፣ በመኖሪያ ቤት፣ በመኝታ፣ በእህል ማስቀመጫ ጎተራ ሥር፤ በከብቶች በረት ማደሪያ አካባቢ ናቸው፡፡ ደንቃራ በሚታወቁና በማይታወቁ፣ ጠላቶች ተሰርቶ ስለሚጣል፤ የተጣለው ደንቃራ ሳይታይ ቢረገጥ ለቁም ሕመም እና ለሞት ይዳርጋል ተብሎ ይፈራል፡፡ በአጋጣሚ ደንቃራ ተጥሎ ወይም ወድቆ በቤት በር ወይም ግቢ ሲታይ፣ ሲገኝ በማን እንደተጣለ ስለማይታወቅ "አማትባችሁ ውኃ አፍሱበት፤ ውኃ መተት ያረክሳል፤ ደብተራ ጠርታችሁ አስነሱት፤..." ይባላል፡፡ ደንቃራ መተት ተሰርቶ የሚጣለው በዋናነት ለዕይታ በሚያስጠሉ፣ በሚያስፈሩ፣ በሚያስደነግጡ ግብዓቶች ሲሆን፤ በዓይነ ምድር፣ በሞተ አይጥ፣ በድመት፣ በዶሮ፣ በወፍ፤ ተሰርቶ ደንቃራ (አቶ ሞገስ፣ቃ.መ፤22/06/2011 ፋርጣ) ይጣላል፡፡

በዓይነ ምድር ተሰርቶ የሚጣል ደንቃራ በሰዎች ቢረገጥና ቢቀመጡበት፤ በደንቃራው ላይ የሰፈሩ አጋንንት መተላለፊያ መንገዳቸው አንድም በሽታ፤ አንድም በንክኪ ስለሚሆን የተፈለገውን አካል ወይም ሰው ለማጥቃት፣ በሕመም ለማሰቃየት፣ ጤናውን ለመንሳት ቅርብና አመቺ እንደሆነ (መሪጌታ መንግስቴ፣ቃ.መ፤10/03/2011 እብናት) ይታሰባል፡፡ እንደ መሪጌታ ፋንታሁን መረጃ በሰው ዓይነ ምድር የሚጣል "ደንቃራ መተት" በቀላሉ የማይፈታ፣ ሰውን የሚያሳብድ፣ ለአልጋ ቁራኛ እና ለሞት የሚዳርግ፤ ተግባር እና የአጋንንት ሥራ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህ ተግባር የተደገመበትን ሰው ችግር፣ ሥቃይ፣ ጭንቀት፣ መከራ፣ እንግልትና ልፋት ለማወቅ እና ችግሩን ለመፍታት ከባድ እንደሆነ፤ (ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ) አስረድተዋል፡፡

የዓይነ ምድር መተት የተሰራበት ሰው፤ የሕመም መንስኤ ደንቃራ ሲሆን፤ በደንቃራ የተለከፈ ሰው መለያ ባሕርይ፤ አጠቃላይ ሰውነቱ ይቆስላል፣ ከዓይነ ምድር ባልተናነሰ ሰውነቱ ይሸታል፤ ይቆስላል፤ ተብሎ ይታመናል፡፡ ሰውነትን በድንገት መውጋት፣ ራስ ምታት፣ ሆድ ቁርጠት፣ እጅና እግር መሸማቀቅና ማዞር፣ መንቀጥቀጥ፣ እረፍት የሌለው ቁርጥማት፣ ዉጋት፤ የሕመሙ ምልክቶች እንደሆኑ (መሪጌታ ሠረቀብርሃን፣ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት) ይታመናል፡፡

አይጥ፣ ድመት፣ ዶሮና ወፍ አድኖ በመያዝ፣ "ገድሎና ገንዞ"፤... የሚጣል ደንቃራ ቤተሰብን፣ እንስሳትን፣ ሐብት ንብረትን ለማውደም፣ ለማጥፋትና ለመንቀል ታስቦ የሚሰራና የሚጣል ደንቃራ እንደሆነ፤ ማንኛውም ሰው ተገንዘው የተጣሉ ዓይጥ፣ ድመትና የወፍ ዝርያን ወድቆ እና ተጥሎ እንዳገኘ በእጁ ቢነካ ወይም አንስቶ ቢጥል፣ ቢረግጥ አካሉ ደንዝዞ፣ ማስታወሱን ረስቶ ቀስ በቀስ ያሳብደዋል፤ ልቡን ይሰውረዋል፤ ልብሱን ጥሎ እንዲሄድ ያደርገዋል፤ (ወ/ሮ

አበበች፣ቃ.መ፤ 26/06/2011 ሊቦ ከምከም) ተብሎ ይፈራል። በሕይወት ያሉ እንስሳትን (አይጥ፣ ድመት፣ ወፍ) አጥምዶ በመያዝ፣ ቆዳቸውን ገፎ፣ ላባቸውን ነጭቶ፣ በነጭ፣ በጥቁር፣ በአርንጔ ወይም በቀይ ክር ገንዞ መጣል፤ ዐበይት ተምሳሌቱ መተት የሚጣልበት ሰው በቁሙ ተገንዞ በሕይወት ይኖራል፤ በሕመም ይሰቃያል፤ (መሪጌታ በረከት፤ ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት) ተብሎ ይታመናል።

አንደርቢ፦ እንደ ደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እምነት "አንደርቢ" ሲባል አንድ ሰው የጠላቱን ቤት በእሣት ማቃጠል፣ በድንጋይ መደብደብ፤ በነፋስ፣ በነጎድጓድ ዝናብና በረዶ ማስመታት፤ በገበታ ማዕድ ምግብ ላይ አሸዋ፣ ትላትል፣ ድንጋይ እና የተለያዩ ነፍሣትን መጣል እና መሙላት፤ እረፍት መንሳት እና ማረፊያ ማሣጣት እንደሆነ (መሪጌታ ስዩም፣ ቃ.መ፤ 04/02/2011 እብናት) ገልጸዋል። ደስታ (1962፤ገ.120) "አንደርቢ" የሚለውን ቃል "አንደርቤ (ደርበየ)፤... ምትሀት፣ በጨለማ የሚወረወር፤ ደንጊያ፣ ወርዋሪው የማይታይ፣ የማይታወቅ፤ በማእድ ላይ የሚወድቅ ፋንድያ፣ ዐይነ ምድር፣ ዐፈር፣ ጉድፍ" በማለት ይፈቱታል።

"አንደርቢ ሲባል ሰይጣንን በጥበብ መጥራትና ማዘዝ፣ ተግባር እና ሥርዓት ማለት ነው" ይላሉ (መሪጌታ አዲሱ፣ ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ)። የአንደርቢ መድኃኒት ሲዘጋጅ ለምን ዓላማ፣ ተግባርና አገልግሎት እንደሚውል መጀመሪያ ይለያል። ቤት ለማቃጠል፣ በድንጋይ ለመደብደብ፣ በነጎድጓድ ዝናብ ለማስደብደብ፣ የገበታ ማዕድ ምግብን በቆሻሻና በትላትል ለመሙላት፤... መሆን/አለመሆኑን በመለየት የመድኃኒት ቅመማ ዝግጅቱ ይጀምራል። ቤትን ለማቃጠልና በድንጋይ ለመደብደብ የታለመ ከሆነ፤ ለአንደርቢ የሚውሉ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ ማዕድናት እና ነፋሣት፤ ድግምቱ የሚጣልበት ግለሰብ ክርስትና ስም እና "ወዝ" [የሰው ገላ የነካው ልብስ፣ ገመድና ማተብ] የነካው ጨርቅና ክር ይሰበሰባል። ከነዚህ ግብዓቶች አንዱ ቢጎል ወይም በሥርዓቱ ተመጣጥኖ ባይኖር፤ ፀሎቱና ጽሕፈቱ ቢጓደል፤ ቅደም ተከተሉ ቢዛነፍ፣ የአስማት ቃልና ቁጥሮች ቢቀነሱ ወይም ቢጨመሩ መድኃኒቱ "ይረክሳል" ወይም አይሰራም ይባላል። ሥርዓቱ በሚያዘው ገቢር [አደራረግ፣ አከዋወን፣ ቅደም ተከተላዊ ሥርዓት ማለት ነው] ልክ መጥኖ መቀመም (ደብተራ ጥላሁን፣ ቃ.መ፤03/03/2011 ሊቦ ከምከም) ያስፈልጋል።

የአጋንንት ጦር ሰራዊትና መናፍስት ኃይላቸውን እንዲለቁ፣ ክብራቸውን እንዲያወርዱ፣ ለጊዜው ተነስተው እንዲሄዱ፣ መቅሰፍትና በሽታ እንዳይጥሉ "ምስና ግብራቸው" ይቀርባል፤ "የጥቁር ዶሮ ደም፣ እንቁላል፣ እጣን፣ የመልክዓ ሣጥናኤል ድጋም የያዘ ክታብ" ቀርቦና ተነቦ፤ ከደሙና ከእንቁላሉ ተቋድሰው፣ ቀምሰው እና ምሣቸውን ይዘው እንደሚሄዱ፤ ማንኛውም ደብተራ ወይም

መሪጌታ ዕውቀትና ሙያ ቢኖረው እራሱን፣ ቤተሰቡን እና አካባቢውን አደጋ ላይ እንዳይጥል ተጠንቅቆ ሥርዓተ ገቢሩን ይፈፅማል። ይህን ጥበብ ለመማርና ለመተግበር ሞክሩ እና ሥርዓተ ገቢሩን አዛብተው [መጣያና መመለሻውን ረስተው] የአልጋ ቁራኛ የሆኑ፣ ታመው የቀሩና የሞቱ ደብተራዎች እንዳሉ፤(መሪጌታ ዘላለም፣ቃ.መ፤20/04/2011 ፋርጣ) ተርከዋል።

የአንደርቢ መድኃኒት ሲዘጋጅና "በጥላት" ሰው ቤት ላይ ሲጣል፤ ጥንቃቄ ማድረግ፣ መመለሻውን ተጠንቅቆ ማወቅ፣ መያዝ፣ ማስታወስ እና በአንደበት ወይም "በለሆሳስ" [ድምጽ ሣያሰሙ] መድገምና ማነብነብ፤ ክታቦችን ጽፎ በእጅ ወይም በአንገት ማንጠልጠል፤ የሥርዓቱ አካል እንደሆኑ (ደብተራ ጥላሁን፣ ቃ.መ፤ 03/03/2011 ሊቦ ከምከም) ገልጸዋል። ጠቅለል ባለመልኩ የአንደርቢ መድኃኒት ለማዘጋጀት፤ የዕፅዋት ዓይነቶችን መርጠው፤ በቀንድ ካራ ቆርጠው፤ በጦር አንካሴ ቆፍረው፤ አድርቀው፣ ቀምመው ለተፈለገው ዓላማ እንዲውል ይደረጋል። አንደርቢ ለመጣል የተቀመመው መድኃኒት ከተሰቀለበት የጸሎት ቤት ይወርድና አንደርቢ በሚጣልበት ቤት ፊት ለፊት ይቀበራል፤ (ዐፈር እንዳይነካው በዕፀ ጳጦስ ቅጠል ይሸፈናል)። ድግምቱን የቀበረው ደብተራ ወይም መሪጌታ ዕፀ መሰውር (በአካባቢው ከሚንቀሳቀሱ ሰዎች ዕይታ የምትሰውር ዕፅ) በግራ እጁ በመያዝ፤ በአካባቢ የሚገኝ ሰይጣን ጠርቶ "ምስና" ግብሩን ሰጥቶ የጠላቱን ቤት ለይቶ እንዲመታ "ለሰይጣኑ" ትዕዛዝ ይሰጣል። ሰይጣኑም የተላከበትን ቦታ፣ ቤት እና ግለሰብ በመለየት ቤቱን በድንጋይ ይደበድባል፤ ያቃጥላል ወይም በነፋስ ነጎድጓድ ጣራውን አንስቶ ይጥላል (አቶ ቃከለ፣ቃ.መ፤ 04/03/2011 ሊቦ ከምከም) ተብሎ ይታመናል።

የአካባቢው ማኅበረሰብ በአንደርቢ የተመቱ ቤቶችን፣ ግለሰቦችን እና ቦታዎችን በመጥቀስ ይተርካሉ[48]። በተለይ በእብናት እና በሊቦ ከምከም ወረዳ በአንደርቢ ድግምት ቤትን በድንጋይ ማስደብደብ፣ ግለሰብን ከመኖሪያ አካባቢ ማባረር፣ በገበታ ማዕድ ምግብ ላይ አሸዋ መሙላት፣ የአህያ ፋንድያ መርጨት፣ መጣል እና ሰውን ማሳበድ የተለመደ ተግባር መሆኑን የአካባቢው ማኅበረሰቦች (ወ/ሮ ጠጂ እና ወ/ሮ ጀማነሽ፤ ቃ.መ፤ 28/06/2011 እብናት፤ 02/07/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል) ይገልጻሉ። ሰውን ከሞቀ ቤቱ እና ትዳሩ ነጥለው፤ "በሰይጣን እና በጋኔል" አስመትተው፤ የጎዳና ኗሪ፣ የበረሃ መናኝ ያደርጋሉ። በዚህ ሥራ የተጠረጠሩ ደብተራና መሪጌታዎች አካባቢውን ለቀው እንዲሄዱ ወይም "ከእኩይ" ተግባራቸው ተለይተው ሰላማዊ ኑሯቸውን እንዲመሩ፤ በአካባቢው ሽማግሌ ወይም የሃይማኖት አባቶች በኩል ተመክረው፤ "ተገዝተው" ከድርጊታቸው ታቅበው የሚኖሩ ግለሰቦች እንዳሉ ጠቁመው፤ ደብተራና መሪጌታዎች

[48] ተመቱ የተባሉ ቤቶችንና ግለሰቦችን በአካል ቀርቤ ለማየትና ለማናገር እድሉ ያልገጠመኝ መሆኑን ልብ ይሏል።

በማኅበረሰቡ እንደሚከበሩና እንደሚፈሩ የመስክ መረጃዎች (መረጌታ ገብረመድኅን፣ ቃ.መ፤ 25/04/2011 ሊቦ ከምከም) አስረድተዋል፡፡

***ተፈጥሮን መረዳትና የመቆጣጠር ኃይል፡-*** ሲባል የተፈጥሮ ሁነቶችን ለመረዳት፣ ባሕርያቸውን ለማወቅ፣ ለመቆጣጠር፣ አቅጣጫ ለማስቀየር፣… የሚደረጉ እምነታዊ ሥርዓቶችን ይመለከታል፡፡ ዝናብ፣ በረዶ፣ መብረቅ፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ነፋስ፣… የመሳሰሉ የተፈጥሮ ኃይሎችን የመቆጣጠርና የማዘዝ መለኮታዊ ኃይልና ሥልጣን አላቸው የሚባሉ ግለሰቦች፤ የእህል ማሳ በዝናብና "በበረድ" [በበረዶ] እንዳይመታ አቅጣጫ ለማስቀየር ወይም ለማስደብደብ፤ ዝናብ እንዲጥል ወይም እንዳይጥል ለማድረግ፤ መብረቅ ቤት እንዳይመታ ለመከላከል፤ የንፋስ አቅጣጫን ለመተንበይ፤ ሙከራ እንደሚደረግ (መሪጌታ ብሩህ፣ቃ.መ፤ 18/06/2011 ፋርጣ) ጠቁመዋል፡፡

በእብናት ወረዳ ኒቋራ እና አቋሽሞች ቀበሌ፤ "መብረቅ ሲጥል ሰይጣን አይቶ ነው! ሰይጣን ለመምታት ነው" ይባላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ "ብረት ሰይጣን አያቀርብም፤ ከሰይጣን ይከላከላል" እየተባለ ይነገራል፤ ይተገበራል፡፡ "ሰይጣን" ደግሞ ከዝናብና ከመብረቅ ለመሰወር "ትልቅ ዛፍ፣ ዋሻና መኖሪያ ቤት" ይመርጣል፤ ተብሎ ይታመናል (መሪጌታ ስንታየሁ፣ ቃ.መ፤ 14/03/2011 እብናት)፡፡ ይህን አደጋ ለመከላከል፤ ብረት ነክ ይዘት ያላቸውን ማጭድ፣ ቢላዋ፤ ማረሻ፣ መጥረቢያ (የተገኘውን አንዱን መርጠው)፤ በቤት በር "ትይዩ" ቦታ ላይ ይጥላሉ፤ በአጥር ወይም በቤት ጣራ ላይ ይሰካሉ፤ ለምን? ሲባል "ብረት ሰይጣን አያስጠጋም"፤ ወልዳ የተኛች አራስ በመኝታዋ ትራስ ሥር (እራስጌና ግርጌ) ማጭድና ቢላዋ ማስቀመጥ፤ በፀጉሯ ወስፌ መሰካት፤ ለግብር ውኃ ስትወጣ ብረት መያዝ፤ ከአጋንንት ይከላከላል፤ተብሎ ይታሰባል (መሪጌታ መንግስቱ፣ ቃ.መ፤11/04/2011 እብናት)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፤ የእህል ማሳና አዝመራቸውን ከበረዶና ከዶፍ ዝናብ ለመከላከል፤ "ጸሎተ በረድ" በማስደገም የዝናብና የበረዶ ኃይል ለመቆጣጠር፣ ለመቀነስና አቅጣጫ ለማሳት፣ በሌላ ቦታ ለመጣል ዕውቀቱና ትምህርቱ አላቸው በሚባሉ ደብተራና መሪጌታዎች ዝግጅት ይደረጋል፡፡ "የበረድ" ድግምትና ፀሎት የሚያደርጉ ደብተራዎች ለድግምት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ከመስክ ሰብስበው እና ቀምመው ተግባራዊ ለማድረግ "ሶስት ሰባት" (ሃያ አንድ ቀን) እንደሚቆጥሩ፤ ከምግብ ዓይነት ውኃ ነክ ይዘት የአላቸውን ምግቦች (እንደ ድንች እና ቅባት ምግቦችን) ከመብላት እንደሚቆጠቡ (ደብተራ መኅሪ፣ ቃ.መ፤ 13/03/2011 እብናት) ጠቁመዋል፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ በመለኮታዊ ኃይል "ከበረዶና ከዶፍ ዝናብ" ሰብላቸውንና ማሣቸውን ለሚጠብቁ

ደብተራዎች፤ እህል ታጭዶ፣ "ተወቅቶ" ወደ ጎተራ ከመግባቱ በፊት በዓመት አንድ ጊዜ አንድ ቁና እህል ተሰፍሮ "አስራት" ወይም "ግብር" ይከፈላል፡፡ ይህን ልማድ በመጣስ "አስራት" የማይከፍል ግለሰብ፤ በሽማግሌ ተመክሮ እንዲከፍል ይጠየቃል፤ ይህ ባይሆን በቀጣይ ዓመት የእርሻ ማሣው ተለይቶ "በበረድና በዶፍ ዝናብ" ይመታል ተብሎ፤ (አቶ ታከለ፣ ቃ.መ፤ 04/03/2011 ሊቦ ከምከም) ይታመናል፡፡

**የበሽታ ሽኚት ልማድ፡-** በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ ወረርሽኝ ሲከሰት፣ የበረሃ "ንዳድ" የወባ ሕመም ሲነሣ፤ እህል ታጭዶ ቃርሚያ ሲቃጠል፣ "ሕመም እና መቅሰፍት" ገብቷል (ተቅማጥ፣ ኩፍኝ፣ እከክ)" ተብሎ ሲታመን፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት በመሰባሰብ "የበሽታ ሽኝት ሥርዓት" ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ፡- "የማጅራት ገትር፣ ኩፍኝ፣ ተቅማጥ እና መሰል አጣዳፊ በሽታዎች" ሲከሰቱ ከሕሙማን ላይ ለማባረር እና ወደ ሌላ አገር ለማሸጋገር፤ ጥይት ይተኮሣል፣ ጅራፍ ይጮሃል፣ ብረት ይንኳኳል፣ በየሰፈሩ የቤት ጥራጊዎች ተሰብስበው እንዲቃጠሉ፤ በየወረዳው የበሽታ ሽኝትና ቅብብል ሥርዓት (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደመቀና ቄስ ካሳ ያቀረቡት ሃሳብ፤ ቃ.መ፤ 19/06/2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት) ይደረጋል፡፡ በሽታው ተነሳ ከተባለበት ቦታ ጀምሮ ከለሊቱ አሥር ሠዓት የአካባቢው ሰዎች ተሰብስበው፤ በሽታ የመሸኘት፣ አጋንንት የማናገር እና የማዘዝ መለኮታዊ ኃይል አላቸው የሚባሉ ሶስት ሰዎች ተመርጠው፤ ዝግጅቱ ይጀመራል፡፡

የአካባቢው ኗሪም፤ ቡና፣ እጣን፣ የቀይ ጤፍ ቂጣ፣ ኑግ፣ ተልባ፣ ወተት፣ ቆሎ፣ ፈንድሻ፣ ጠላ፣ ቀሪቦ፣... የመሳሰሉ ግብዓቶችን በመያዝ በዝግጅት ቦታው ይገናኛሉ፤ በሽታ የመሸኘትና መናፍስትን የማናገር መለኮታዊ ኃይል አላቸው የሚባሉ ሰዎች ሥርዓቱን "በፀሎት" አስጀምረው፤ ቡና ተፈልቶ አገር ይመረቃል፤ የአካባቢው አድባር፣ ቆሌ እና ውቃቢ ይለመናል፤ በሽታው፤ "በክፉ ሥራችን፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት እንደመጣ... አካባቢው በሚገኙ መናፍስት ቁጣ" እንደተከሰተ፤ በሥርዓቱ መገባደጃ የአካባቢው ሴት፣ ሕጻናት እና አቅመ ደካማ ሽማግሌዎች ወደ ቤት ሲመለሱ፤ ቀሪዉ ማኅበረሰብ ከቡና ቁርስ ወይም "ከሰደቃ" የተረፉ ምግቦችን በመያዝ ከአካባቢያቸው አርቀው፤ በመስቀለኛ መገድ ላይ ጥለው በሩጫ ይመለሳሉ፤ ዞሮ ማየትና መቀመጥ ለበሽታ ይዳርጋል፤ ተብሎ ይታሰባል፤ "የበሽታ ሽኝት ሥርዓቱ" በዚህ ይዘት (መሪጌታ ዘላለም፣ቃ.መ፤20/04/2011 ፋርጣ) ይጠናቀቃል፡፡

መሪጌታ በረከት የበሽታ ሽኝት ሥርዓት በግለሰብ ደረጃ በስውር የሚፈጸም መሆኑን ጠቁመው፤ ለረጅም ጊዜ ታመው "የአልጋ ቁራኛ [ታመው ለተኙ] ለሆኑ፤ አጋንንት ለመታቸው፣ የዐየር

ጋኔል ለተጸናወታቸው [የአዕምሮ ሕሙማንን በዋናነት ይመለከታል]፤ ዳፍንት ለያዛቸው [ድንገት ለሚጥል በሽታ]... ሕሙማን" የበሽታ ወይም የአጋንንት ማስወጣት፣ ማባረርና መሸኘት ሥርዓት ይደረጋል (ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት)፡፡ ሕሙማን በሚኖሩበት፤ ቤት ቡና ተፈልቶ፣ ኑግ፣ ቂጣ፣ ወተት፣ ቆሎ፣ ማር፣ እንቁላል ተዘጋጅቶ፤ "ለጭዳ" ጥቁር ዶሮ ተይዞ፤ በደብተራ ወይም በመሪጌታ ድግምት ተነቦ በመስቀለኛ መንገድ ላይ በስውር ከመጣሉ በፊት፤ ለማቋደሻ የተያዙ ምግብ እና መጠጥ በአንድ ላይ ተደምረው፤ የጥቁር "ቁብ" ዶሮ ደም [እንቁላል መጣል ያልጀመረች] ፈሶ፤ እጣን ተጨሶ፣ የቡና አተላና ሌሎችም ተደምረው፤ "የመልክዓ ሣጥናኤል ድግምት" ተነቦ፤ በአንድ ቦታ ቀብረው ወደ ቤት ይመለሳሉ፡፡ ቤት ደርሰው ወደ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት፤ ከመኖሪያ ቤት ጣራ ላይ "ጥቀርሻ" [ጭስ] የነካው ሣር ይመዘዝና በመውጫ በር አጠገብ እንዲቃጠል ይደረጋል፡፡ ለምን? ሲባል የታማሚው ሕይወት በአጋንንት እኩይ ሥራ መጨለሙን ለማስታወስ፤ ጥቀርሻ ሣር የተመረጠበት ምክንያት፤ ጥሩ መልክና ወዝ የነበረው ሣር በጭስ ምክንያት መልኩን እንደቀየረ ለመጠቆም፤ የታማሚውን ሕይወት፣ የሰንበሌጡን ጥቁረትና የመልክ ለውጥ በማነጻፀር፤ በጥቀርሻ የተበከለው ሰንበሌጥ ሲቃጠል፤ "በታማሚው ግለሰብ ውስጥ የነበረ በሽታና አጋንንት አብሮ ይቃጠላል፤ አመድ ይሆናል፤ ለቆ ይሄዳል፤" ተብሎ ይታመናል (መሪጌታ አዲሱ፣ቃ.መ፤19/01/2011 ፋርጣ)፡፡

**"የዓለሞቼ/ወተቴ" በሽታ ሥርዓትና አተገባበር ልማድ[49]፡-**

"የኩፍኝ" በሽታ ሲነሣ " የዓለሞቼ ወይም ወተቴ" ወረርሽኝ ተከሰተ ይባላል፡፡ ይህ በሽታ በዋናነት ልጆችን የሚያጠቃ ሲሆን አልፎ አልፎ አዋቂዎችን እንደሚይዝ ተጠቁሟል (ወ/ሮ ጀማነሽ፣ ቃ.መ፤ 02/07/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ በአንድ አካባቢ፣ መንደር ወይም ቤት "የዓለሞቼ" ወረርሽኝ ሲከሰት፤ ልጆች የሏቸው ቤተሰቦች ይደነግጣሉ፤ የልጆቻቸውን እንቅስቃሴ ይቆጣጠራሉ፤ ይገድባሉ፡፡ ከዚህ ሁሉ ሙከራና ጥረት በኋላ ወይም በአጋጣሚ ሕመሙ በቤት ውስጥ ቢከሰት ልዩ ዝግጅትና ሥርዓት ይደረጋል፡፡ ሕመሙ በተከሰተ በመጀመሪያው ቀን የልጆች ሰውነት እና ቆዳ "የሽንብራና የአተር በሚያህል መጠን፤... በሰውነታቸው ላይ እትር እትር እያለ ይወጣል"

[49] "የዓለሞቼ" ወይም የኩፍኝ በሽታ ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት "ባህላዊ ክትባት" ይሰጥ እንደነበር መሪጌታ ስዩም (ቃ.መ፤04/02/2011 እብናት) ጠቁመዋል፡፡ አንድ አካባቢ የዓለሞቼ በሽታ ሲከሰት፤ ከታማሚው ሕጻን ሰውነት መግልና ደም በጥጥ ተወስዶ፤ የጤናማ ሕጻን ክንድ በምላጭ ይበጣና በጥጥ የተያዘው ደምና መግል በክንድ ይቀበራል፡፡ ሕመሙን የማስተላለፍ፣ የማላመድ፣ የማራባትና የማሰራጨት ሥራ ይሰራ እንደነበር፤ ገልጸዋል፡፡ ባሕላዊ ክትባቱ፤ የሕመሙን ስርጭት ለመቆጣጠር፣ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ፤ በሽታውን ቀድሞ ለመከላከል መፍትሔ እንደነበር ጠቅሰው፤ ልጆች ባሕላዊ ክትባት ሳያገኙ በሽታው ቢከሰት ለቆዳ ጠባሳ፣ ለዓይነ ስውርነት፣ ለከፋ ስቃይና መከራ እንደሚዳርግ መክረዋል፡፡ የልጆች ክትባት መኖሩ፣ የኤች.አይ.ቪ. በሽታ በደም ይተላለፋል መባሉ፣ ዘመናዊ ሕክምና እየተስፋፋ ሲመጣ ባህላዊ ክትባት እየቀረ መሄዱን አስረድተዋል፡፡

(ወ/ሮ አበበች፣ቃ.መ፤26/04/2011 ሊቦ ከምከም) በቀጣዩ ቀን ቀድሞ ያበጠው ይቀላል፤ ሌላው ማበጥ ይጀምራል፤ ከሶስት አራት ቀን በኋላ መግል በመያዝ ይፈነዳል። የልጆች መላ ሰውነት ይተኩሳል፤ የማቃጠል፣ የመለብለብ ስሜት፤ የማበጥና የመፍረጥ፤ የአቅም ማነስ እና የምግብ ፍላጎት መቀነስ (ወ/ሮ ጠጂ፣ ቃ.መ 28/06/2011 እብናት) ይታይባቸዋል። ወላጆች የልጆቻቸውን ሕመም እና ስቃይ በመገንዘብ "ዓለሞቼን" እንደበሽታ አይጠሩም፤ በጸጋና በክብር ተቀብለው፤ ሥርዓትና ግብሩን ፈጽመው፤ በልጆች ላይ የከፋ አደጋ ሣይደርስ "ልጆች በዓለሞቼ ተሸልመው" ከወጡ የምስጋና ቡና ጠጡ ሥርዓት እንዳለ ወ/ሮ አበበች ጠቁመው፤ የልመና ሥርዓቱን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡-

እነዓለሞቼ ማሬ ማሬ፤

ወየት ኑሯችኋል፤ እስተ ዛሬ፤

ጣል ጣል አድርጉልኝ፤ ተግባሬ፤…

በማለት እንደሚለመን አስረድተዋል (ወ/ሮ አበበች ቃ.መ፤ 26/04/2011 ሊቦ ከምከም)። በአንድ አካባቢ ወይም ቤት ውስጥ "በዓለሞቼ" ሕመም የተያዙ ልጆች ከቤት እንዳይወጡ፤ ፀሐይ እንዳይመታቸው፣ ከእንግዳ ሰው እንዳያገኙ እና አጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው ይገደባል። በመኝታ ቦታቸው ላይ ተቀምጠው፤ የፈለጉት የምግብ ዓይነት ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው፤ ገልፀዋል። የሚበሉበት፣ የሚጠጡበት እና የሚተኙበት ቦታ በንፅህና ተዘጋጅቶ፤ ከሰውና ከእንስሳት እንቅስቃሴ ተለይተው እንዲቀመጡ ወይም እንዲተኙ ይደረጋል። እናት ከዚህ ቦታ አትለይም፤ ገበያ አትሄድም፣ ከግቢ ውጪ ያሉ ሥራዎችን አትሰራም፤ የታመሙ ልጆችን መከባከብ፤ የሚፈልጉትን ምግብ ማብላትና ውኃ ማጠጣት፤ የልጆችን ወቅታዊ ሕመም ለማስረሣት መዝፈን፣ ማጨብጨብ፣ መቀለድ፣ "መጨፈር"፣ ልጆችን ማሣቅ፣ … ይጠበቃል። እናቶች ለዓለሞቼ ቡና በማፍላት፣ እጣን በማጨስ፣ ሰንደል በመለኮስ፣ ሽቶ በመርጨት፣ ቆሎ፣ ፈንድሻ፣ ቂጣ፣ ኑግ አዘጋጅተው፤ የዓለሞቼ ልመና ሥርዓት ይጀመራል። በእለቱ ከሚባሉ ቃል ግጥሞች መካከል የሚከተለውን በማስታወስ (ከወ/ሮ አበበች፣ ወ/ሮ ጠጂ እና እማሆይ ለተብርሃን፤ ቃ.መ፤26/04/2011 ሊቦ ከምከም፤ 28/06/2011፤ እብናት፤ 21/06/2011 ፈርጣ በቅደም ተከተል) ጠቁመዋል፡-

እነአለሞቼ፣ ወለሎቼ፤ ኑ በመንገዱ፤

ሃሣብ አይቀርም፤ ልጅ ተወለዱ፤…

ወተቴ ወተቴ፤ ነይ አበቡ
ኩታሮቹ ሁሉ፤ እንዲያብቡ..
ወተቴ ተገቡ፤ ጥሩ ዘመን፤
በይ ማሪልኝ፤ ልጆቼን፤
እነሰንሣለሁ፤ ጨፌውን፤
አጨሣለሁ፤ ወገርቱን፤
እከለክላለሁ፤ ጥላውን፤...
ልትሄዱ ነው አሉ፤ ታገራችሁ፤
ሙጫዎቼን ሸልማችሁ፤ ደባብሣችሁ፤
ተለመለመው ሣር፤ ያድርሳችሁ፤
በግዜ ግቡ፤ ታገራችሁ፤... ይባላል።

በማለት እናቶች "ለዓለሞቼ" ቃል ግጥም እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል። የዓለሞቼ ሕመም ቤት ገብቶ እስከሚወጣ፤ ቡና ማፍላት፣ እጣን ማጨስ፣ ሽቶ መርጨት፤ ቡና ቁርስ ማዘጋጀት፤ "ልጆቼን ማሪልኝ/ ሸልሚልኝ" ብሎ "ቆሌዋን" መለመን እና "መካደም" (የሚፈለገውን ሥርዓትና ገቢር መፈጸም፤መለመን) እንደሚያስፈልግ (ወ/ሮ ጠጄ፤ ቃ.መ፤ 28/06/2011 እብናት) ጠቁመዋል።

የዓለሞቼ ሕመም በልጆች ላይ ሲከሰት በጥንቃቄ ካልተያዙ፣ እንክብካቤ ካላገኙ፤ ዓይናቸው ይጠፋል፤ በሰውነት ቆዳቸው ጠባሳ ይጥላል፣ አጥንታቸው ይወጣል፣ እግራቸው ይቆስላል፣ አጋንንት "ይጣባቸዋል" [እድሜ ልካቸውን የማይለቅ የአዕምሮ ሕመም ያጋጥማቸዋል]፣ ለሞት ይዳርጋል፤ ተብሎ እንደሚፈራ፤ የሕመሙ የቆይታ ጊዜም "ቢያንስ አንድ ሰንበት፤ ቢበዛ ሁለት ሰንበት" (ሰባት ወይም አሥራ አምስት ቀን) ይሆናል። በሽታው እየለቀቀ ሲሄድ ቡና የማፍላትና የልመና ሥርዓቱ እየደመቀ፤ የተስፋ፣ የምህረት፣ የሽኝት ቃል ግጥሞች እንደሚቀርቡ፤ "ንፍሮ ተቀቅሎ ይበላል፤ የእጅ መዳፍ የሚያካክሉ ሰባት ቂጣ ተጋግሮ በወንዝ እና በመንገድ ዳር ይጣላል" ይህ ሥርዓት የሚተገበረው ልጆች የመዳን ምልክት ሲያሳዩና የበሽታው ሽኝት ሥርዓትና ገቢር አንዱ አካል ተደርጎ (ወ/ሮ አበበች፣ቃ.መ፤ 26/04/2011 ሊቦ ከምከም) ይቆጠራል።

ከዚህ በላይ የቀረቡ ቃል ግጥሞች እንደሚያስረዱት፤ የበሽታውን ባሕርይ፣ ቅድመ ጥንቃቄ፣ የሚደረጉ ሥርዓቶችን ያስረዳሉ፡፡ የባህል ሐኪም መሪጌታ ልሳነ ወርቅ (ቃ.መ፤ 27/04/ 2011 ሊቦ ከምከም) "የዓለሞቼ ወረርሽኝ መንደር ተገባ ጠሎትና ልመና በጎ ነው፤ … መዳኒቱ የኩታራውን [የልጆች] ዙረት ማቆም እና ቤት ማዋል፤ የወገርት፣ የወይራ፣ የአደሥ፣ የአርቲ እና የበርሃ ዕጣን ማጨስ፤ ቁስሉ ሲፈነዳ ቦታው ላይ ሽቶ መርጨት፤… እስቲድኑ ገላቸውን አለማጠብ፤ አድባር እና የቤት ቆሌን መለመን" መፍትሔ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ማኅበረሰቡ ለምን "ለኩፍኝ" በሽታ የተለየ ትኩረት ይሰጣል? ለምን ይዘፈናል፤ ፀሎትና ሽኝት ይደረጋል? ሲባል በታሪክ በኢትዮጵያ ከተከሰቱ በሽታዎች "ኩፍኝ" አሳሳቢ፣ አደገኛና በፍጥነት የሚዛመት ወረርሽን መሆኑ፤ የመዛመት አቅሙ፣ የሚያደርሰው ጉዳት፣ የበሽታው ምልክት፣ ዳራና ታሪክ፤ በማኅበረሰቡ እንዲፈራ ምክንያት (Pankhurst,1990) ሆኗል፡፡ ሕመሙን ለመቋቋም፣ አካባቢያዊ መፍትሔ ለመሻት፣ የመከላከያ ስልትና ቴክኒኮችን ለመጠቆም፣ ልማዳዊ ሥርዓቶችን ለማጠናከር፤ አካላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቡናዊ እና መንፈሣዊ ጥንካሬ ለማግኘት፤ የልጆችን ስቃይና ለቅሶ ለማስረሳት፣ ለማስተንፈስና ለማዝናናት፤ የማኅበረሰቡን እንክብካቤ እና ግንዛቤ ለማዳበር፤ ማኅበራዊ "ቅቡልነትን" ለማስረፅና ለማጠናከር፤ ሲባል ይከወናል፡፡

## 4.4 በደቡብ ጎንደር ዞን በባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች

በደቡብ ጎንደር ዞን ከሚገኙ የባህል ሐኪሞች የተሰበሰቡ የመስክ መረጃዎችን[50] በማደራጀት፤ በዞኑ ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች (Top Ten Diseases) ናሙና ይዘት፤ እንደሚከተለው በሰንጠረዠ ቀርበዋል (ዝርዝር ይዘት፤ አባሪ አምስትን ልብ ይሏል)፡፡

[50]ማሳሰቢያ፡- በባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች በባህል ሐኪሞች መረጃና ምርጫ የተሰጡ ናቸው፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል የቀረቡ ይዘቶች፤ ከባህል ሐኪሞች የተገኙ መረጃዎችን መነሻ በማድረግና በመስክ ምልከታ ወቅት ጉልተው የታዩ የበሽታ ዓይነቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት፤ ለናሙና ማሳያነት ታላሚ ተደርገው የተደራጁ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት በተካሄደባቸው ወረዳዎች የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በቁጥር ደረጃ ዝቅተኛ 23 (ሃያ ሶስት)፤ ከፍተኛ 89 (ሰማኒያ ዘጠኝ) የበሽታ ዓይነቶችን እንደሚፈውሱ፤ በመስክ ስምሪት ወቅት አስረድተዋል፡፡ ይህም ስለሆነ፤ ለናሙና ማሳያነት የቀረቡ የበሽታ ዓይነቶች፤ በጥናቱ ትንታኔ ይዘት በአስረጅነት፣ በምሳሌ እና መሰል ተግባራትን ለመግለጽ የቀረቡ ቢሆንም፤ የመስክ መረጃዎች በዋና ዋና በሽታዎች ላይ ብቻ ተወስነው እና ተመስርተው የተሰበሰቡ አለመሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በዚህ ሂደት በአካባቢው ጎልተው የሚታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶችን መለየት፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ተግባርና ሥርዓትን ለመገንዘብ እና ከሥነ ምህዳር ጋር ያላቸውን ዐውዳዊ መስተጋብር ለማጤን አመቺ መሆኑን፤ ታሳቢ አድርጓል፡፡ በዘመናዊ ህክምና ጤና ጣቢያ (ለጥናት በተመረጡ ወረዳዎች) ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች (Top Ten Diseases) ዝርዝር ይዘት፤ በአባሪ አምስት ንዑስ ክፍል ሁለት ተጀራጅተው ቀርበዋል፡፡

ይህ ጥናት በተካሄደባቸው ወረዳዎች (ፋርጣ፣ ሊቦ ከምከም እና እብናት) ከሚገኙ የባህል ሐኪሞች የተሰበሰቡ የመስክ መረጃ እና ምርጫዎችን መነሻ በማድረግ ተደራጅተው ለናሙና የቀረቡ ይዘቶች መሆናቸውን፤ ታሳቢ አድርጓል፡፡

**ሰንጠረዥ ስድስት፡- በባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች** (Top Ten Diseases) **ለጥናት በተመረጡ ወረዳዎች ማሳያነት፤**

| ተ.ቁ | **ፋርጣ ወረዳ** | **ሊቦ ከምከም ወረዳ** | **እብናት ወረዳ** |
|---|---|---|---|
| 1 | የወፍ (የጉበት) በሽታ | ስፈተ ወሲብ | የወባ በሽታ |
| 2 | ስንፈተ ወሲብ | ኪንታሮት | የኪንታሮት |
| 3 | ቁርጥማት(ሪህ) | የወፍ (የጉበት) በሽታ | የቆላ ቁስል |
| 4 | ነቀርሳ | እከክ (ልክፍት) | የውሻ ከለባት |
| 5 | እከክ (ልክፍት) | የጡት ነቀርሳ | የሞኝ ባገኝ (ማንጅራት ገትር) |
| 6 | አስም | ለውሻ ከለባት | ስፈተ ወሲብ |
| 7 | የጡት ነቀርሳ | ወስፋትና የኮሶ ትል | የጎርምጥ እና የልፌ ቁስል |
| 8 | ወስፋትና የኮሶ ትል | የወባ በሽታ | የተቀማጥ |
| 9 | ስኳር | የፎረፎርና የቺፌ በሽታ | የኩላሊት |
| 10 | የእንጥልና የጉፋን | ቁርጥማት (ሪህ) | የዉኃ ልክፍት (እከክ) |

ምንጭ፡- የደቡብ ጎንደር ዞን የባህል ሐኪሞች፤ በጥናት አቅራቢው ተደራጅቶ የቀረበ፤ ኅዳር 2011 ዓ.ም፡፡

በሰንጠረዥ ከቀረቡ መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው፤ በባህል ሕክምና መስክ  በዞኑ ጎልተው ከሚታዩ በሽታዎች መካከል፤ የጉበት "የወፍ" በሽታ፣ ስንፈተ ወሲብ፣ ኪንታሮት፣ የወባ በሽታ፣ ቁርጥማት፣ የቆላ ቁስል፣ ጥገኛ ትላትል (ወስፋትና የኮሶ ትል)፣  እከክ፣ የስኳርና የኩላሊት ሕመም፤… በዋናነት እንደሚጠቀሱ፤ ከመስክ መረጃዎች ማጤን ተችሏል፡፡ በቀጣይ ምዕራፍ በባህል ሕክምና ዕውቀት፤ የሕመም መንስኤ ይዘት ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፡- በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤ ይዘታዊ ትንተና

በዚህ ይዘት ሥር የሕመም መንስኤ፣ የአጋንንት ዓይነትና መለያ ባሕርያት፣ የተቃርኖ ኃይል ስበትና የለውጥ ጥሪ፣ መለከፊያ ዐውዶች ይዘት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ የመስክ መረጃዎችም፤ በዐውድ-ተኮር ክዋኔ እና በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል ስልት ተተንትነዋል፡፡

## 5.1 የሕመም መንስኤ

በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሣናት ይዘት 2.1.4 እንደቀረበው፤ የሕመም[51] መንስኤ በማኅበረሰብ እምነትና እሳቤ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ለበሽታና ለጤና ያላቸው ፍልስፍና፣ ለተፈጥሮ (Cosmological) እና ለዓለም ያላቸውን አተያይ (World views)፤ የአኗኗር ልማድ፣ ግለሰባዊ ባሕርይ፣ ሃይማኖት፣ ሥነ ምህዳር እና መለኮታዊ ኃይልን መነሻ እንደሚያደርግ ተጠቁሟል (የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳብን ልብ ይሏል)፡፡ አብዛኛው የባህል ሕክምና ሥርዓት ውስብስብ የሆነ የአካል፣ የአዕምሮና የመንፈስ መስተጋብርን እንደሚያካትት Brady ገልፀዋል፤ "Most folk healing systems assume a complex interconnectedness of body, mind, and spirit" (2001;P.19):: የሕመም መንስኤ ምንድን ነው? ከየት መጣ? እንዴት መጣ? ተብሎ በማኅበረሰቡ ይታሰባል፡፡ በባህል ሕክምና ሂደት የአካል፣ የአዕምሮና የመንፈስ መስተጋብር ምን ይመስላል? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል፡፡

እንደ ደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤና መረጃ፤ ለሕመም መንስኤ “አጋንንት ወይም ርኩስ” መናፍስት ሲሆኑ፤ ዲያቢሎስ፣ ጋኔል፣ ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ ብሄሞት፤ በመባል ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ መናፍስት በዐየር፣ በዛፍ፣ በወንዝ፣ በተራራ፣ በባሕር እና በመሬት ተበትነው እና ተሰራጭተው ስለሚገኙ፤ የዐየር፣ የመሬት፣ የባሕር "ርኩስ"[52] መናፍስት ተብለው እንደሚጠሩ ይገልጻሉ፡፡

---

[51]በመስክ ቆይታዬ የባህል ሐኪሞች "በሽታ" ለሚለው ቃል “አጋንንት” የሚለውን አቻ ፍቺ ይመርጣሉ፡፡ የሕመም መንስኤ/ የበሽታን ምንነት፣ ተግባርና ባሕርይ ለማስረዳትና ምላሽ ለመስጠት ሲጥሩ የመጨነቅ እና ግራ የመጋባት ስሜት ይታይባቸዋል፤ በአንጻሩ የሕመም መንስኤ/ አጋንንት የሚል ጥያቄ ሲቀርብ አካላቸውን ዘና፣ ፊታቸውን ፈታ፣ ፈገግና ሳቅ በማለት የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ በቀላሉ ይገልፃሉ፣ ያብራራሉ፣ ያስረዳሉ፡፡ በባህል ሕክምና አጋንንት ማለት “በሽታ” የሚለውን ቃል እንደሚተካ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች የባህል ሐኪሞች ጠቁመዋል (መሪጌታ ፋንታሁን፣ አቶ ጌጡ፣ ቃ.መ፣ 19-24/01/2011 ፋርጣ፤ አቶ ደርሶ፤ ቃ.መ፤03/02/2011 እብናት)፡፡ በዚህ ጥናት ይዘት እና ሂደት ውስጥ በሽታ እና ሕመም የትርጉም፣ የፍቺና የይዘት ለውጥ ሳይኖራቸው በአቻ ይዘት የቀረቡ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[52]በዚህ ጥናት ይዘት ርኩስ መናፍስት፣ ሰይጣን፣ አጋንንት የሚሉ ቃላት ተመሳሳይ ይዘትና ፍቺ አላቸው፡፡ እንደ አመቺነታቸው በማፈራረቅ የተጠቀምኩ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ርኩሳን መናፍስት፤ የሰው ልጆችን ማሰቢያ "ሕሊና" [አዕምሮን] በመቆጣጠር፣ በተለያየ መንገድ "በመዋረስ" [ሰዎች በሚበሉት፣ በሚጠጡት፣ በሚያሸቱት፣ በሚነኩት፣ በሚያዩት ነገር ተዛምደውና ተዋርሰው እንደሚገቡ ይታሰባል]፤ በአዕምሯቸው ተሰውረው አካላዊ ሥጋቸውን በማድከም፣ ተግባራቸውን በማሳት፣ ፍላጎታቸውን በመቆጣጠር፣ ማደሪያና መዋያ አድርገው፤ ሰውን ለመከራ፣ ለአዕምሮ ጭንቀት፣ ለሕመም፣ ለስቃይና ለሞት ይዳርጋሉ፤ ተብሎ እንደሚታመን መሪጌታ ፍሬስብሃት እና ሊቀጠበብት አብርሃም (ቃ.መ፤ 29-30/01/2011 ሊቦ ከምከም) ያስረዳሉ፡፡

ከተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት መካከል ቄስ አብርሃም እና መሪጌታ ስንታየሁ የሕመም መንስኤ፣ መከሰቻ ቦታ፣ ባሕርይን እና ማስለቀቂያ መንገዶችን እንደሚከተለው ያስረዳሉ (ከተቡው አባላት መካከል ቄስ አብርሃም እና መሪጌታ ስንታየሁ ያቀረቡት ሃሳብ፤ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)፡፡ ቄስ አብርሃም መለከፊያ መንገድ እና መለያ ስልቱን እንዲከተለው ጠቁመዋል፡-

> አንድ ሰው በአጋንንት መለከፊያ መንገዱ ብዙ ነው፡፡ … በሚበላ፣ በሚጠጣ፣ ይሆናል፤… በአጋንንት የተለከፈ ሰው በአፍንጫው የሚሸተት ነገር ስንሰጠው፤ ያዞረዋል፤ እራሱን ስቶ ይወድቃል፤ ያለቅሳል፤ ይቀጠቀጣል፤ ፍርሃት ፍርሃት ይለዋል፣ ያልበዋል፤'… ተቃጠልኩ፣ ነደድኩ'፣… ይላል፡፡ … ግንባሩን በመዳፌ [በቀኝ የውስጥ እጅ] ዳበስ ዳበስ! መታ መታ! አደርግና ዓይኔን ተመልከት እለዋለሁ፤ አጋንንት ከሆነ ትክ! ብሎ ያየኝና፤ ድርቅ ብሎ ሳይንቀሳቀስ ይመለከታል፤ ያስፋሽጋል፤ ሰውነት ያንጠራራል፣ ይዝላል፡፡ ቡዳና ዛር ከሆነ ማየት ይፈራል፤ ይቅለሰለሳል፤ ይስቃል፤… 'ማነህ ተናገር' ስትለው፤ እንደመሳቅ፣ እንደማልቀስ፣ እንደጉሪ ይለዋል፡፡… በምን እንደለከፋው ይናገራል፡፡ ምስህ ምንድን ነው! ሲባል በደም የለከፈ ከሆነ ምሱ ደም ነው [የታማሚው/ዋ ኮኮብ ተቆጥሮ የዶሮ ወይም የበግ ጭዳ (ደም) አድርግ/ጊ ይባላል]፤ በአተላ፣ በአመድ፤… የለከፈ መንፈስ ከሆነ፤ በአካባቢ የሚገኝ አተላ፣ ፋንድያ፣ አመድ፤… ምስና ግብሩ ይሆናል፡፡

በማለት ገልጸዋል፡፡ መሪጌታ ስንታየሁ (ከተቡው አባላት፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ) ደግሞ የአጋንንት መልቀቂያ መንገዱን እንደሚከተለው አስረድተዋል፡-

የአጋንንት ስምና ዓይነታቸውን ለማወቅ የመርበብተ ሰሎሞንን ድጋም [የአጋንንት ማስለፍለፊያና ማባረሪያ ፀሎት] እየተደገመ፤ ማነው ስማችሁ?... ስንት ናችሁ? እንዴት ያዛችኂት?... እየተባለ ሲጠየቅ፤... በታማሚዋ ላይ የሰፈረው መንፈስ ይናገራል። የአጋንንት፣ የጅን፣ የዛር መንፈስና ውላጅ [ከዛር የተወለደ/የዛር ልጅ ማለት ነው] መሆናቸውን ያጋልጣሉ፤ የት፣ መቼ እንደያዛት፣ በምን እንደያዛት ይለፈልፋል።... በማን ትለቃለህ? ዋስ ጥራ? ይባላል። ከመላእክት [ሚካኤል፤ ገብሬል፣ አማኑኤል፣ ፋኑኤል፣] አንዱን ዋስ ይጠራል። ... ላይመለስ ይምላል፣ ይገዘታል፤ ወቶ ይሄዳል። በፀበል፣ በመስቀል እና በቃለ እግዚአብሔር ብቻ የሚለቅ አጋንንት አለ፤ ሌላው ደግሞ በማጨስ፣ በማሸተት፣ በማጠጣት፣ በጽፈት [በክታብ መልክ የተዘጋጀ የአጋንንት ማራቂያ ድግምት] አለ።... መንፈሱ ለቆ ሲሄድ ታማሚዋ ትነቃለች። ፀሎት ተደርጎ ድና ወደ ቤቷ ትሄዳለች።

በማለት አስረድተዋል። በተመሳሳይ መልኩ ደብተራ ጥላሁን (ቃ.መ፤ 03/03/2011 ሊቦ ከምከም) የአጋንንት አለቃ፣ አዛዥ እና አባት ዲያቢሎስ እንደሆነ ጠቁመው፤ ዓለምን ለማሳት፣ ዓለምን ለማጥፋት እና ለመቅጣት የመጣ መቅሰፍት መሆኑን ያስረዳሉ። "ሣጥናኤል [ዲያቢሎስ] ፈጣንና የመላእክት አለቃ ነበር፤ እግዚአብሔር በሰጠው ፀጋና ጥበብ ተመክቶ፤ የፍጡራን አለቃና ፈጣሪ እኔ ነኝ በማለት ታበየ [ዋሸ]።... 'እግዚአብሔርም ድርጊቱን በማየት አዘነ'፤ ክብርና ፀጋውን ገፎ ወደ ምድር ጣለው፤ የአጋንንት አለቃ እሱ ነው" በማለት ገልፀዋል።

ከዚህ በላይ የቀረቡ የመስክ መረጃዎች እንደሚያስረዱት፤ የሕመም መንስኤ በዋናነት አጋንንት (ጋኔል) ሲሆኑ በሚበላ፣ በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚለበስ፣ በሚታይ፣ በሚረገጥ እና በሚታሰብ [እኩይ ሥራ ለመተግበር] የሚዋረሱና የሚመጡ፤ አካላዊ ሥጋን በማድከም፣ አዕምሮን ሰላም በመንሳት፣ መንፈሳዊ ሕይወትን በማስተጓጎል፣ እኩይ ተግባራትን በማሳሰብና በማስፈጸም፣ ቀና መንገድን በማሳት፣ የማኅበረሰብ መተዳደሪያ ልማድን በመጣስ፤ ከዓለማዊና ከመንፈሳዊ የሕይወት መስተጋብር መነጠል፤ የአጋንንት ዐቢይ ሥራ፣ ሙያና ተግባር እንደሆነ በማኅበረሰቡ (ቄስ ማስረሻ፤ ቃ.መ፣ 21/06/2011 ፋርጣ) ይታመናል። "ምግብ ቀርቦ ሳይባርኩ፣ ሳይቀድሱ እና ሳያማትቡ መብላት፤ በረከት ይነሳል፤... ለበሽታ ይዳርጋል፤... ማተብ ማሰር፣ መስቀል[53] መያዝ፣ ማሳለም ርኩስ መንፈስን ያርቃል፤...መስቀል መድኃኒታችን ነው!..." (ቄስ ብርሃኑ፣

[53]ማተብ፣ መስቀል እና የመስቀል ዓይነት፣ ይዘት፣ ቅርጽና ብዛት አሰራርና ሃይማኖታዊ እሳቤ፣ ትዕምርታዊ ተንታኔ፤ ከዚህ ይዘት ጋር በመጠኑ የሚገናኝ ቢሆንም በዚህ ቦታ መተንተን፣ ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ትስስርና ዝምድና ማመልከት፣ ፋይዳውን መግለጽና ማሳየት፤ የዚህ ጥናት ዐውድና ማዕከላዊ አለመሆኑን ልብ ይሏል። ይህ ጥናት፤ በመለኮታዊ ኃይል እና በአስማታዊ ጥበብ እየታገዙ፣ በሃይማኖትና በእግዚአብሔር ፀጋና በረከት እየተመሩ የሚፈውሱትን አይመለከትም። የዕፀዋት፣ እንስሳት፣ ማዕድንና መሰል ግብዓትን ተጠቅመው የመፈወስ ልምድና ተመክሮ ያላቸውን የባህል ሐኪሞች ይመለከታል። በመንፈሳዊና በዓለማዊ የባህል ሕክምና መካከል ያለው ዝምድና፣ ቅልቅልና መዋረስ የተለመደ ተግባር መሆኑን ልብ ይሏል።

ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት) ተብሎ ይታመናል። ማንኛውም እንቅስቃሴ፣ ሥራ እና ድርጊት መባረክ እንዳለበት ይመክራሉ። ሳይባረክ የሚበላ፣ የሚጠጣ ወይም የሚሰራ ነገር፤ "ሰይጣን ይቀርበዋል፤ ሰይጣን አብሮ ይበላል! አብሮ ይጠጣል! አብሮ ይሰራል! በረከት የለውም..." (እማሆይ ለተብርሃን፣ ቃ.መ፤ 21/06/2011 ፋርጣ) ይባላል።

ይህ አስተምህሮ፣ ተግባር፣ ልማድና እንቅስቃሴ፤ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት፤ ፀሎት ማድረግ፣ "ትዕምርተ መስቀል" መስራት (ማማተብ)፣ መስገድ፤ የእለት ሰናይ ተግባር ተደርገው ይታሰባሉ። እነዚህ ተግባራት የፀጋ፣ የኃይል፣ የብርታት እና የጤና በረከት ተደርገው ይቆጠራሉ። ዲያቢሎስን ለማራቅ፣ አጋንንትን ለመዋጋት፤ የሚሰሩት፣ የሚበሉትና የሚጠጡት "ረድኤት" እንዲያገኝ "መባረክ ወይም መቀደስ" እንዳለበት ይመከራሉ። ምግብን ሳይባርኩ መብላት፣ ውኃን ሳይባርኩ መጠጣት፣ ሥራን ሳይባርኩ መስራት፤ ለሕመም ይዳርጋል፤ በአጋንንት ያስለክፋል፤ በረከት ያርቃል፤ ጤና ይነሳል፤ ተብሎ እንደሚታመን የማኅበረሰቡ አባላት ያስረዳሉ (ወ/ሮ አበበች፣ ቃ.መ፤ 26/04/2011 ሊቦ ከምከም)።

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ማኅበረሰብ አባላት እሳቤ "ማማተብ ወይም ትዕምርተ መስቀል" መስራት የሕይወት መርህ፣ እሴትና ተግባር ሲሆን፤ ጤና ለማግኘት፣ አካባቢያዊና ሥነ ልቡናዊ ሰላምን ለመፍጠር (Environmental and Psychological Peace)፤ ከአጋንንት ለመዳን፣ ለመሰወርና ለመጠበቅ፣ ለማስወጣትና ለማባረር፤..."ማማተብ" የእለታዊ ሕይወት መርህ፤ የጤና መጠበቂያ፤ "የአጋንንት መዋጊያና ድል መንሻ" ትዕምርት ተደርጎ ይወሰዳል። ከዚህ ተግባር፣ እሴትና ሙያ መውጣት፣ "ማፈንገጥ" እና "መነጠል" ያስረግማል፣ ሰይጣናዊ ድርጊት ያስብላል፤ ማኅበራዊ ልማድ እና ሃይማኖታዊ ሥርዓትን ይጥሳል፤ ተብሎ በማኅበረሰቡ እንደሚታሰብ የመስክ መረጃዎች ገልፀዋል።

በአንጻሩ የአጋንንት ጭፍሮች በእኩይ ተግባር፤ እንደሚደሰቱ፣ እንደሚረኩ፣ የወጥመድ ጽዋቸው እንደሚሞላ፤ መሪጌታ መኅሪ (ቃ.መ፤ 27/01/2011 ሊቦ ከምከም) ጠቁመው፤ "የሕይወት ዉሎና አዳር" በጠባቂ መላእክት እና በርኩስ መናፍስት መካከል የምትገኝ መሆኑን እንደሚከተለው ያስረዳሉ፦

> ማንኛውም ፍጡር ጠባቂ መላእክት አሉት።... የሰው ልጅ ከአካሉ ሥጋ ለብሶ፤ ከመንፈሱ ነፍስ ዘርቶ አልተፈጠረም፤ የአምላካችን እየሱስ ክርስቶስ የእጁ ስራትና ጥበብ እንጂ፤... ሕይወት የአለው ማንኛውም ፍጡር ጠባቂ መላእክት አሉት፤... እነዚህ መላእክት የቀንና

የማታ ተራ እና ዘብ ገብተው፤ የሕይወትን ውሎና አዳር በየቀኑ፤ በየአሥራ ሁለት ሠዓት ልዩነት ይነገራል፤... 'ይቺ ነፍስ ዛሬ እንደምን ዋለች?' ሲባል፤ 'የእግዚአብሔርን ቃል አክብራ እየዘመረች፣ ተደስታ፣ በፀሎትና በበረከት ዋለች!" ይባልና ለቀጣዩ ተረኛ መልአክ፤ አሥራ ሁለት ሠዓት ሲሆን ተላልፋ ትሰጣለች፡፡ የምሽቱ ተረኛም፤ ለቀጣዩ መለአክ፤ የነፍስ አዳሯ እንዴት እንደነበር ያስረዳል፡፡... 'ይቺ ነፍስ እንደምን አደረች' ይለዋል፤... ቅጥቃጤ [ቅዠት፣ ሕልም፣ በእንቅልፍ ሰመመን መናገር፣ መርበትበትና መደንገጥ... ማለት ነው] በዝቶባት ስትጨነቅ፣ እረፍትና ማረፊያ አጥታ ስትባትት፤ ... ኤሎሄ ድረሱልኝ እያለች ስትጮህ! አጋንንት ከበው ሲያስጨንቋት፣ የዛር ውላጅ እባብን ተመስሎ ሲጠመጠሙባት! የጅን አለቃ ውሻ መስሎ፤ ሲከተላት ባሕር ውስጥ ሲጥላት አደረች'፤... በማለት ይናገራል፡፡ ክፉ ቅጥቃጤ ሲያጋጥም ሶስት ጊዜ አማትቦ ሰውን ሳያናግሩ ማልዶ ቤተክርስቲያን መሄድ፤... 'ለመልካም አድርግልኝ! ከክፉ ነገር ሰውረኝ!... ከዛር ውላጅ! አድነኝ፤... ከጅን ልክፍት ጠብቀኝ...' በማለት ይፀለያል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበው ይዘት እንደሚያስረዳው፤ ሕይወት ሥጋዊ ፍላጎቷን ለማሟላት፣ መንፈሳዊ ተግባሯን ለመፈጸም ምን ጊዜም ትንቀሳቀሳለች፡፡ በዚህ ድርጊት፣ ሂደትና እንቅስቃሴ ጠባቂ መላእክት እንዳላት ሁሉ ርኩሳን መናፍስት የሕይወት እንቅፋት፣ የሕመም መንስኤ በመሆን አካላዊ ሕመምን፣ አዕምሯዊ ሰላምን፣ ማኅበራዊ ሕይወትን በመንሳት ለሞት እንደሚዳርጉ፤ ይታመናል፡፡ በዚህ ይዘት፤ ሕይወት በሁለት ተቃራኒ ኃይሎች (በመላእክትና በአጋንንት) መሃል የምትገኝ፣ በሰናይና በእኩይ ተግባር የተከበበች፣ በሥጋዊ ፍላጎትና በመንፈሳዊ ኃይል ምርጫ "የምትናጥ"፣ በተስፋና ምኞት የምትመራ፣ በመላእክት ፈቃድ የምትቀሳቀስ፣ በርኩሳን መናፍስት ወጥመድ የምትቀሰፍ፤ እረፍት አልባ እንቅስቃሴ እንዳላት፤ የመስክ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ ከዚህ በታች የበሽታ፣ የሕይወት እና የጤና መስተጋብርና የስበት ኃይል ይዘትን የሚጠቁም ምስል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ምስል 5.፡- የሕመም፣ የሕይወት እና የጤና መስተጋብርና የስበት ኃይል ሚዛን




ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች፤ በጥናት አቅራቢው የተዘጋጀ ጥር/2011 ዓ.ም

በጤና ኃይል ሚዛን፤ ሕይወት በምጣኔና በልክ ስትገኝ የጤና መደላድል (ልክ) ሲሆን፤ ሚዛኗን ስትስት የሕመም መንስኤ ይከሰታል። በጤና ኃይል ሚዛን ጫፍ የምትገኘው ቀስት የሕይወትን ሂደትና አቅጣጫ በመጠቆም፤ ጤና ከሕመም፣ መላእክት ከአጋንንት፣ ሰናይ ከዕኩይ የሚደረግ ለውጥና ትግልን ይመለከታል። ጤና እና ሕመም ተቃራኒ ኃይሎች ሲሆኑ ሕይወት በሁለቱ መስተጋብር፣ ኃይልና የስበት መጠን ልክ "በመዋለል" [በእንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ] እንደምትገኝ በማኅበረሰቡ ይታሰባል።

ማኅበረሰቡ በእለታዊ እንቅስቃሴ፣ ማኅበራዊ ኑሮና መስተጋብሩ በቅድሚያ "እንደምን አደርክ! አደርሽ! አደራችሁ!" በማለት የአካባቢና የግለሰብ ጤና፣ ሰላምና ደህንነትን ማረጋገት የመጀመሪያ ተግባር ይሆናል። መሪጌታ ፋንታሁን፤ "...የሰው ልጅ በአካለ ሥጋው ያነሰ በአካለ ነፍሱ የከበረ ፍጡር ነው...፤ እንደምን አደርክ! ዋልክ! ሲባል በሱ ላይ ላለው መልአክ ሰላምታ ማቅረብ ነው፤...በሰው እጅ የጠፋች ነፍስ አትተኛም፤ ትቅበዘበዛለች፣ ለፈጣሪዋ አቤቱታ ታቀርባለች፤ ከአካለ ሥጋ የነጠላትን ሰው ቆማ ታስፈርዳለች..." (ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ) ይባላል።

ማኅበረሰቡም "ከጤና በላይ ፀጋ የለም" በማለት ዕለታዊ ሕይወቱን፣ ማኅበራዊ እንቅስቃሴውን ለማረጋጋት፤ አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ሕመሙን ለመፈወስ፣ ከአካባቢው ሥነ ምህዳርና መልክዓ ምድር ለመግባባትና ለመስማማት፤ ባህላዊ፣ አካባቢያዊና ማኅበራዊ ደህንነቱን ለማረጋገጥ፤ ለመልካም ግንኙነት መዳበር፣ ለአኗኗር ልማድና ሥርዓት መገዛት የመልካም ባሕርይ መገለጫ ሲሆን "የፈጣሪን ነፍስ" ማስቃየት፣ ለአደጋ ማጋለጥና ማጥፋት የአጋንንት ተግባር፣ "የሰይጣን" መንፈስ ማደሪያ ተደርጎ ይታመናል። ሁለት ሰዎች በአጋጣሚ ተጣልተው ቢደባደቡ "ሰይጣን አሳሳታቸው!" በድንገተኛ አደጋ የሰው ልጅ ደም ቢፈስና ቢሞት "ደም የጠማው ሰይጣን፤ ደሙን አፈሰሰ! ደሙን ጠጣ!... ሰው ወድቆ ቢሰበር ፍርጃ ነው!.. ትእዛዝ ነው!... ቢሞት ቀኑ ደርሶ ነው! ይቺን ቀን አያልፋትም!" ይባላል (ወ/ሮ ውዲቱ፣ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም)።

እንደ Helman (1984)፤ የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦች ይዘት፤ የሕመም መንስኤ መለኮታዊ ኃይል፣ ማኅበራዊ ሕይወት፣ ተፈጥሯዊ ዓለም እና ግለሰባዊ ባሕርይ እንደሆኑ ገልጸዋል። በዚህ ጥናት "ተፈጥሯዊ ዓለም እና ግለሰባዊ ባሕርይ" በማኅበረሰቡ አይጠቀሱም፤ የተፈጥሮ አደጋና ማዕበል ቢከሰት የፈጣሪ ቁጣ፣ በክፉ ሥራና ድርጊት የመላእክት ቅጣት ወይም የአጋንንት

መቅሰፍት ተደርጎ ይቆጠራል። ግለሰባዊ ባሕርይም ቢሆን "ሰው ሲፈጠር እንደ ውኃ ንዑሕ ነው" ይባላል፤ በዚህ ዓለም ተግባር፣ ፍላጎትና ሥራ ነፍስ ትረክሳለች፣ ሃጢያት ትሰራለች፣ ሥጋዊ ባሕርይ የነፍስን ንጽሕና ያረክሳል፤ ተብሎ ይታሰባል። በግለሰቡ ላይ ያደሩ ርኩሳን መናፍስት "ጠጪ፣ አጫሽ፣ ዝሙት እንዲሰራ ምክንያት ናቸው"፤ ተብሎ ይታመናል።

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ፤ የሕመም መንስኤ "በርኩስ" መንፈስ ተላላኪነት፤ የጻድቃን፣ የሰማዕታት እና የመላእክት ትዕዛዝ፣ መመሪያና ሕግን በመጣስ የሚመጣ ቅጣትና ቁጣንም ይመለከታል። አንድ ሰው በእባብ ድንገት ቢነደፍ "ፍርጃ ነው! የሰይጣን ወጥመድ ነው!" ይባላል። በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በአገር፤ "እልቂት" ሲከሰት፣ ድርቅ ሲገባ፣ ርሃብ ሲነሳ፣ ሰው ሲሰደድ፤... የፈጣሪ ቅጣት፣ የሃጢያት ብዛትና መንስኤ እንደሆነ፤ የፈጣሪን ቃል፣ ትዕዛዝና መመሪያ ባለማክበር፣ ለሕጉ አለመገዛት፣ በቃሉ አለመኖር፣ በሥርዓት አለመመራት፤ ያመጣው ቅጣት ተደርጎ በማኅበረሰቡ ይታመናል። መፍትሔው፤ መጾም፣ መጸለይ፣ መስገድ፣ ፈጣሪን መለመን፣ ምህረትና በረከት እንዲያወርድ መማጸን መሆኑን የሃይማኖት አባቶች (ቄስ ብርሃኑ እና ቄስ ማስረሻ፣ ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት እና 21/06/2011 ፋርጣ) መክረዋል።

የሰው ልጅ ከጸሎት ሲለይ፣ ፈጣሪውን ሲረሳ፤ ሰይጣን "ይደሰታል"፣ ገበታና ዋንጫው ይሞላል፤ ፀሎቱ ይሰምራል፤ "ግዳዩ" ይበዛል፤ አካላዊ ሥጋ ታብባለች፣ መንፈሳዊ ሕይወት ትረክሳለች፣ መቆሚያ፣ መቀመጫ፣ ማረፊያና መሸሸጊያ ታጣለች፤ ነፍስ ትጨነቃለች "ለጌታዋ ጥሪ ታቀርባለች" ይባላል (መሪጌታ ሠረቀብርሃን፣ ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት)። አሰፋ "መንፈሳዊ ፀሎቶችን የመድገም ዋነኛ ዓላማ፣ የበጎ መናፍስትን ያላሰለሰ ጥበቃ (ከለላ) ለማግኘት፣ ርኩሳን መናፍስትን ለመዋጋትና ለማራቅ፣ በመጨረሻም ከመንፈሳዊ፣ አካላዊ ጭንቀትና ስቃይ ነፃ በመሆን ጤናማ ሕይወት [መምራትን]..." (2008፣ገ.77) ግብ ያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። በአጠቃላይ የአጋንንትን መንስኤ ለመለየት፤ "ለመዋጋት እና ድል" ለመንሳት፤ ጾም፣ ጸሎት እና "ድጋም" በማድረስ የአጋንንቱን ባሕርይ፣ ምስና ግብር ለማወቅ፤ ማሰሪያ፣ ማናገሪያ፣ ማስለፍለፊያ፣ ማስወጫ፣ መገዘቻና ማባረሪያ ዕውቀት፣ ጥበብ እና ክህሎት ለማግኘት፤ አካባቢያቸውን ለመገንዘብና ምክንያታዊ ምላሽ ለመስጠት የባህል ሐኪሞች ጥረት እንደሚያደርጉ፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል። በቀጥይ ንዑስ ይዘት፤ የአጋንንት ዓይነትና መለያ ባሕርያት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 5.2 የአጋንንት ዓይነት እና መለያ ባሕርይ

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤ፤ አጋንንት እንደሰማይ ከዋክብት እንደ ምድር አሸዋ በዐየር፣ በተራራ፣ በወንዝ፣ በመሬት ላይ ተበትነው እንደሚገኙ እና እንደሚኖሩ ይታሰባል (መሪጌታ ፍሬስብሃት እና መሪጌታ ስዩም፣ ቃ.መ፣ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 04/02/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። መሪጌታ ስዩም ለሕመም መንስኤ የሚባሉ የአጋንንት ዓይነትና መለያ ባሕርይ (ቃ.መ፣ 4/02/2011፤ ከተቡው አባላት በድጋሚ የጠቀሱት ሃሳብ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ) እንደሚከተለው አስረድተዋል፡-

> በአገራችን [በአካባቢያችን] ዛር፣ ቡዳ፣ ቆሌ እየተባለ፤ ጭዳ ይሰጣል፤… የአጋንንት ጭፍራ ናቸው፤ ግብራቸው ሲጓደል ሰው፣ እንስሳት ይጣላሉ [ለሕመም ይዳርጋሉ]፤… የዛር ዓይነቶች ብዙ ናቸው፤ አገው ብርሌ፣ ሻንቂት፣ ራሄሎ፣ አዳል ሞቲ፣ ሻንቆ፣ እንቁላሊት፣ ሰየፉ ጨንገር፣ እሳት ባፉ፣ ቡዳ… ይባላሉ።…አጋንንት ጠጅ፣ አረቄና የጠላ አተላ በሚፈስበት፣ አመድና ቆሻሻ በሚደፋበት ቦታ…ይኖራሉ፤ በእኩለ ቀን ቡና ይጠጣሉ፤ በድንገት የደረሰ ሰው ሲኒያቸውን ቢረግጥ፤… በዐየር ጋኔል ተመቶ ጠብ [ይወድቃል] ይላል፤… ባሕር ጠባቂ ጅን በጠራራ ፀሐይ ሲደርሱባቸው፤… ቡዳ… ሳይባረክ በሚበላ ምግብ፣ መጠጥ፣ በደም መፍሰስ እና በእይታ ይተናኮላል። …ለታማሚ መድኃኒት ሲሰጥ መንፈሱ ይለፈልፋል። አጋንንት… በወንዝ፣ በተራራ፣ በዛፍ፣ በመሬት በየሰፈሩ… ተበትነው አሉ፤… በዛር መናፍስት የተያዘ ሰው፤ ይንቀጠቀጣል፤ ወባው ይነሳል፤ ያጎራል…፣ ሆዱ ይታመማል፣ ያንጠራራዋል፣ ያስታዉከዋል፤… ምሱን [ግብሩን፣ መልቀቂያና መቋደሻውን] ይጠራል።

ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃና ማኅበረሰቡ፤ ለሕመም መንስኤ የሚባሉ የዛር፣ የጋኔል፣ የቡዳ እና የጅን ዘሮች… የአጋንንት ጭፍሮች እንደሆኑ ገልጸዋል። ከነዚህ ርኩስ መናፍስት ለመጠበቅ፣ ለመሰወር፣ ለመዳን፣ ለመፈወስ የባህል ሐኪሞችን[54]፣ የሃይማኖት አባቶችን፣ መጽሐፍ ገላጮችን፣ ስኒ አንባቢዎችን፣ ደጋሚዎችን፣ “በረድ ጣዮችን” ማማከር ዐቢይ ተግባር እንደሆነ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል። Ben-Amos (1975; PP.165-166) ፤ የማኅበረሰቡን እሳቤ፣ ቀያዊ ምደባ፣ ትዕምርት፣ ክፍፍል እና እይታ መነሻ አድርጎ መመደብ እና በእነሱ አተያይ መተርጎም እንደሚገባ መክረዋል። ለሕመም መንስኤ የሚባሉ የአጋንንት ተላላኪ "አለቃና ጭፍሮች" ይዘትና ምድብ እንደሚከተለው ቀርቧል። የምድቡ ሥርዓት እና ይዘት የማኅበረሰቡን አከፋፈል፣ አተያይና እሳቤን መነሻ በማድረግ ተዘጋጅቶ ቀርቧል::

---

[54]በዚህ ይዘት የባህል ሐኪም ማለት፤ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናት፣ ከነፍሳት፣ ከውኃማ አካላት የሚገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም በመድኃኒት መልክና ይዘት ቀምመው ለታካሚ የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይመለከታል።

ምስል 6፡- ለሕመም መንስኤ የሚባሉ ዋና ዋና የአጋንንት ምድብና የማኅበረሰብ ክፍፍል እሳቤ




ምንጭ፡- በጥናት አቅራቢው የተዘጋጀ መዋቅራዊ ምድብ ጥር/2011 ዓ.ም

በዚህ ጥናት ዲያቢሎስ የአጋንንት አለቃ ሲሆን ዋና ዋና የሚባሉ የአጋንንት ዓይነትና ምድብ ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ የዐየር እና የምድር አጋንንት እንደሆኑ፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል። መሪጌታ ባሕረጥበብ፣ ደብተራ መልኩ እና መሪጌታ ስዩም፤ መናፍስት ከየት እንደመጡ፤ ከሰው ልጆች ጋር ተዛምደው፣ ተዋልደው፣ ተዋርሰውና ተላምደው እንዴት እንደኖሩ፤ በተመሳሳይ ይዘትና በተለያየ ቅርፅ የተረኩ ቢሆንም ይዘቱ ጠቅለል በአለ መልኩ እንደሚከተለው ቀርቧል (ቃ.መ፤ 27/02/2011፤ 23/01/2011 ፋርጣ፤ 04/02/2011)።

ሚት (Myth/Mythology) አንድ፡- የ"ሮሐንያን" መናፍስት ከሰው ልጆች ጋር ተዋርሰው "ረዓይት" የሚባሉ አጋንንት ስለመውለዳቸው፡-

> የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ወታደሮች የነበሩ በአምስተኛው ሰማይ ሥር "በኤረር" ክልል "ሜምሮስ" በሚባል ቦታ የሚኖሩ "ሮሐንያን" መናፍስት፤ "በእዮር" ክልል [በመሬት] ውስጥ የሚገኙ "ኔፊሊምና ግያን" መናፍስት ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ምድር መጡ። የ"ሮሐንያን" መናፍስት ከዘመዶቻቸው ይልቅ፤ በሰዉ ልጆች ውበት፣ ደም ግባት፣ ቁንጅና ተማረኩ፤ ከሰው ልጆች ጋር ለመኖር ተመኙ፤ አሰቡ። "እግዚአብሔር ለምን መልከ ጥፉ አድርጎ እንደፈጠራቸው በልባቸው አማረሩ፤ አዘኑ"፤ እግዚአብሔርም የልባቸውን መሻትና መመኘት አየና፤ በሰው ልጆች አዕምሮ ተሰውረው እንዲኖሩ ፈቀደላቸው። መናፍስቱም ተደሰቱ! ዘለሉ! ጨፈሩ፤ ፍቃዳቸውን ለመፈጸም፣ ምኞታቸውን ለማሳካት፣ ፍላጎታቸውን ለማሟላት፤ በሰው ልጆች ደም ተሰራጭተው፣ ሕሊናን ተቆጣጥረው መኖር ጀመሩ። በሂደትም በውበታቸውና በደም ግባታቸው

የሚያማልሉ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶችን (የሰው ልጆችን) በመንፈስ ተዋርሰው፣ አግብተውና ተዛምደው፤ መልከ ቀና የሆኑ ደምግባት ያላቸው ወንድና ሴት ልጆች ከሰው ልጆች ወለዱ፡፡

በሁለት ዓለም ከሚኖሩ ሰውና መናፍስት [ከሜምሮስ ዓለም በመጡና እና በምድር ዓለም በሚኖሩ ሰዎች መካከል በአለ ግንኙነት] የተወለዱ ልጆች "ረዓይት" ተብለው ተጠሩ፡፡ "ረዓይት" ተዋልደው፣ ተራብተው፣ ቁጥራቸው ከሰው ልጆች ቁጥር በዝቶ ሲኖሩ የተፈጥሮን ባሕርይ በመቀየር እና በማዛባት፣ እርስ በርሳቸው ግብረ ሥጋ እየፈጸሙ፤ ለጋኔል እየታዘዙ የፍጥረትን ደም ማፍሰስ፣ ዓለምን ማቃወስ ጀመሩ፡፡ እግዚአብሔር በዚህ እኩይ ሥራና ድርጊታቸው ተቆጥቶ፤ ከሰው ልጆች እይታ ተከልለውና ተሰውረው በምድር እንዲኖሩ ፈረደባቸው፡፡

እነዚህ መናፍስት፤ የሰው ልጆችን በሚረግጡት መሬት፣ በሚጠጡት ውኃ፣ በሚተነፍሱት ዐየርና በእሳት ተዋርሰው፤ ለፍጥረት ዓለሙ መቅሰፍት ሆኑ፡፡ እነዚህ (የ"ረዓይት") መናፍስት የሰው ልጆችን ሕሊና እየሳቡ፣ አዕምሮን እየሰወሩ፣ ልብን እያሳቱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እየፈጸሙ፤ በምድር መኖር ጀመሩ፡፡ በመናፍስት (ሮሐንያ) እና በሰው ጥምረት የተወለዱ "ረዓይት" መናፍስት "ጂኒ፣ ቆሌ፣ የዛር ውላጅ" ተብለው ይጠራሉ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጆችን መንፈስና ሕሊና ተቆጣጥረው፣ በመንፈስ ተዋርሰው በምድር ተሰውረው እንዲኖሩ ተፈረደባቸው፡፡

ከነዚህ መናፍስት መካከል፤ ባሕር ሰገድ፣ እሳት ባፉ፣ አዳኝ ወርቁ፣ ፈንዞ፣ ሰየፉ ጨንገር፣ አዳል ሞቲ፣ ሸህ አንበሶ፤... በሴት ልጅ መንፈስና ሕሊና ውስጥ አድረው ይገኛሉ፡፡ ራሄሎ፣ እንቁላሊት፣ ዱፍቲ፣ ሻንቂቲ፣ ወርቂት፤... ደግሞ የወንዶች ሕሊናን ተቆጣጥረው፤ እንደ ዓይነ ጥላ ተመስለው፤ በመንፈስ ተዋርሰውና ተጋብተው ይኖራሉ፡፡ የዚህ ዓለም ፍጡራን (የሰው ልጆች) በሚገኙበት ምድር እና ዐየር ተበትነው፤ በወንዝ፣ በዛፍ፣ በተራራ፤... ሰፍረው፤ የሰው ልጆችን እንደሚያጠቁ፤ ይታሰባል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበው ተረክ እንደሚያስረዳው፤ የደቡብ ጎንደር ማኅበረሰብ በዕለት ውሎና አዳሩ፤ ለሕይወት፣ ለጤና እና ለበሽታ ምን ዓይነት እሳቤ አለው? ሕይወትን የሚሰጥ እና ጤናን የሚነሳ ማነው? ሲባል፤ የሕይወት ምንጭ ፈጣሪ፤ የሞት መንስኤ አጋንንት እንደሆኑ በማኅበረሰቡ ይታሰባል (ወ/ሮ ጠጂ እና ወ/ሮ ዉዲቱ፣ ቃ.መ፤ 28/06/2011 እብናት እና 03/07/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ በእለታዊ ፀሎትና ምርቃቱ፣ በማኅበራዊ መስተጋብሩ (በሥራ፣ በሰላምታ፣ በሃይማኖት እና በልማዳዊ ተግባራት)፤ "በሰላም አውለኝ፤ ከሸረኛ ምቀኛ፤... ከአባይ ጠንቋይ ሰውረኝ፤ ከአጋንንት መቅሰፍት ጠብቀኝ፤ መተትና ድግምትን አርቅልኝ" እየተባለ በዕለት ውሎ እና አዳር እንደሚለመን ገልፀዋል (እማሆይ ለተብርሃን፣ ቃ.መ፤ 21/06/2011 ፋርጣ)፡፡ አጋንንት፤ የሕይወት፣ የሥጋና የነፍስ አካል እና መሰረትን ለማዛባት ዐየር፣ እሳት፣ ውኃ እና ዐፈርን ተዋርሰው እና ተዋኅደው ፍጥረትን ያጠቃሉ፤ ለሕመም ይዳርጋሉ፤ ለሞት ያጋልጣሉ

ተብሎ በማኅበረሰቡ ይታመናል። ለምን እነዚህ የሕይወት ሥር መሰረት ባሕርይ ተመረጡ? ምን ፋይዳ አላቸው? ሲባል፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ አራቱ ባሕርያት የተለመዱ፤ የፍጥረት አካል መነሻ፣ መገንቢያ፣ ሕልው ሆኖ መታያ፣ የሥጋዊ ባሕርይ መመስረቻ፣ የባሕርይ ሥር ወይም መሰረት ተደርገው እንደሚቆጠሩ መሪጌታ ገብረመድኅን ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 25/04/2011 ሊቦ ከምከም)።

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤ የሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር፣ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ ባሕርይን ለማሟላት ዐየር፣ እሳት፣ ውኃና ዐፈር ለአካላዊ አቋሙና ለባሕርይ ሥር መሰረቱ እንደሚያስፈልጉት ይታመናል። ከነዚህ ይዘቶች መካከል አንዱን ቢያጣ ሰው ከመሆን ውጪ ይሆናል። በባህል ሕክምና ልማድና ተግባር አራቱ ባሕርያት፤ ለሰው ልጅ እና ለፍጡራን እንደየ ባሕሪያቸው፣ ዝርያቸው፣ ዓይነታቸውና ፍጥረታቸው በልክና በመጠን ተሰፍረው፤ በፈጣሪ እንደተሰጡ፤ ሊቀጠበብት አብርሃም ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም)። በባህል ሕክምና ዕውቀት የተፈጥሮ ባሕርይ የሚባሉ የሕይወት ሥር በልክና መጠን መገኘት እና አለመገኘት አካላዊ ደህንነትን ለማረጋገጥ፤ የሕመም መንስኤን ለመለየት፤ የታማሚውን አቋምና ጤንነት ለማጤን እና ምክንያቱን ለማወቅ እንደሚያግዙ ጠቁመዋል። በሕሙማን ሥጋዊ ባሕርይው ውስጥ ምን ጎደለ ወይም በዛ፤ ከእንቅስቃሴ፣ ከግብሩ፣ ከድርጊቱ፣ ከፍላጎቱ፤ በመነሳት የሕመሙን ዓይነት እና የሚሰጠውን ሕክምና መለየት እንደሚቻል፤ መክረዋል (መሪጌታ መንግስቱ፣ ቃ.መ፤ 11/04/ 2011 እብናት እና አቶ ታከለ፣ ቃ.መ፤ 04/03/2011 ሊቦ ከምከም)። ከዚህ በታች አራቱን የተፈጥሮ ሥርና ሁለቱን የመንፈስ ባሕርያት ሥር መሰረት የሚያሳይ ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ምስል 7፡- አራቱን የተፈጥሮ ባሕርያት (የነገር ሁሉ/የሕይወት ሥር) እና ሁለቱን የመንፈስ ባሕርያት ሥር መሰረት የሚያሳይ ምስለ ማሕቀፍ




ምንጭ፡- የባህል ሕክምና ባለሙያዎች፤ በጥናቱ አቅራቢ የተዘጋጀ ምስለ መዋቅር ሚያዚያ/ 2011 ዓ.ም

ይህ እሳቤ እና ተግባር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥነ ፍጥረት ፍልስፍና መሰረት መሆኑን ሠናይ (2009) ጠቁመዋል። አራቱ የተፈጥሮ ባሕርያት (ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃ እና መሬት)፤ የሕይወት ሥርና የነገር ሁሉ መሰረት ተደርገው ይቆጠራሉ። የተፈጥሮ ባሕርይ መሰረታቸው ከእሳትና ነፍስ ወገን የሆኑ "በመንፈስ" ባሕርይ ሥር ይመደባሉ።

መሪጌታ መልኩ፤ ሰናይ እና እኩይ መናፍስት አካል አልባ፤ እንደ ትንፋሽ ረቂቅና በማንኛውም ቦታ የሚገኙ፤ የተፈጥሮ ባሕርይ ሥር መሰረታቸው፤ ከእሳትና ንፋስ ወገን የሚመነጭ፤ ከእይታ የተሰወሩ፣ በየትኛውም ቦታና ጊዜ የሚከሰቱ፤ ዓለምን ከበው የሚገኙ በዐየር፣ በየብስና በውኃ የሚኖሩ፤ "ከእይታ የተሰወሩ"፣ ኃይልና ጉልበታቸው ዓለምን የሚያጠፉ፣ የሚለውጥና "የሚያናውጥ" ባሕርይ እንዳላቸው (ቃ.መ፤ 23/01/2011 ፋርጣ) ጠቁመዋል። በዘመናዊ ሕክምና ሣይንስ "አካባቢያችን... ሰውነታችን ሁሌም በባክቴሪያና በቫይረስ እንደተወረረ ነው። እነዚህ ጎጂ

ነገሮች በምንበላው ምግብ፣ በምንተነፍሰው አየር፣ ከቆዳችን ጋር በሚነካኩ ነገሮች አማካይነት ወደ ሰውነታችን በመግባት በሰውነት አሰራር ላይ ቀውስ ይፈጥራሉ።" (ይሁኔ፣ 2010፤ገ.12) ይባላል። ከዚህ አንጻር በሁለቱም የሕክምና ዓለም ለሕመም የሚዳርጉ ምክንያቶች እንዳሉ ተጠቁሟል።

የሕይወት ሥራቸው ከንፈስና እሳት ወገን መሆኑ፤ በየትኛውም ቦታና ጊዜ በቀላሉ እንዲከሰቱና እንዲገኙ ምክንያት ሲሆናቸው፤ ከምድር ፍጡራን (አካላዊ ሥጋ ለብሰው ከሚቀሳቀሱ) ተቃራኒ ባሕርይን ተላብሰው የሚኖሩ መናፍስት አይበሉም፣ አይጠጡም፣ አይተኙም፣ አያንቀላፉም፤ አካላዊ ድክመት፣ መንፈሳዊ ጭንቀት፤ የለባቸውም ይባላል። ይህ ባሕርይ እና ተግባር የሚገኘው አካላዊ ሥጋ ለብሰው በየብስና በውኃ ለሚኖሩ ፍጡራን የተሰጠ ፀጋ ወይም ገደብ ሲሆን፤ የውኃና የመሬት ባሕርያት የፍጡራን መገለጫ፣ ቀሪ፣ "ረጋፊ"ና በስባሽ የአካላዊ ሥጋ እና የምድራዊ ሕይወት ተምሳሌት፤ መወለድ፣ ማደግ፣ መጎልመስ፣ ማርጀትና መሞት የሕይወት ሂደትና ተግባር ባላቸው፤ ጤና፣ ሕመምና ሞትን የተሸከሙ የምድር ፍጡራን ትዕምርት ተደርጎ፤ ይቆጠራል (ደብተራ መጎሪ እና መሪጌታ ፍሬስብሃት፣ ቃ.መ፤ 13/03/2011 እብናት፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል) ይታሰባል።

"ለሕመም መንስኤ ናቸው"፤ የሚባሉ አጋንንት፤ የሰው ልጆችን አዕምሮ በመቆጣጠር፣ ልብን በመሰወር፣ ጉልበትና ኃይልን በማድከም፤ ከማኅበራዊ ኑሮ (ከማግባት፣ ከመውለድ ተቆጥበው ለብቻ መኖር) መነጠል፣ ከመንፈሳዊ ሕይወት መገደብ ተግባራቸው እንደሆነ፤ በማኅበረሰቡና በባሕል ሐኪሞች ይታመናል። ለምሳሌ:- ከማኅበረሰቡ ተለይቶ መኖር፤ "በአጋንንት ወጥመድ ተጠልፎ፤ [ተጣብተውት፣ ተዋርሰውት፣ አብሮ አደግ አድርገውት]፤ ፈሪና ገርጋሪ [ከልካይ፣ ደንጋጣ] ሲሆን!... ጠበል ውሰዱት፣... ኮኮቡን እዩለት [ቁጠሩለት]፣ መጠሀፍ ግለጡለት፤..." ይባላል (ከተቡው አባላት መካከል፤ ብላታ ንዴ የገለጹት ሃሳብ፤ ቃ.መ፤ 19/06/2011 ቡድን ሶስት ፋርጣ)።

ከማኅበረሰቡ እሴት፣ ሃይማኖት፣ ማኅበራዊ ሕይወትና መስተጋብር ተለይተው ወይም ተነጥለው የሚኖሩ፤ ከተለመደው ሥርዓት፣ ልማድና ተግባር "አፈንግጠው" የሚሰሩ፤ በሃይማኖት የማይመሩ፣ የማይጾሙና የማይጸልዩ... ከማኅበረሰቡ ልማድ ተቃራኒ የሆኑ ሰዎች የ"ዲያቢሎስ" መልዕክተኛ፣ የሕመም መንስኤ ተደርገው ይታሰባሉ። ለምን? ሲባል "ሰይጣን ለወዳጁ ፍሪዳ ይጥላል!... [የጠየቁትን ይሰጣል፣ የፈለጉትን ያቀርባል፤ የተመኙትን ያወርሳል]፤... ውጤቱ...

በማይበርድና በማያቀላፋ፤ ገሃነመ እሳት መግባት ነው፤...የዘላለም ሕይወትን ያሳጣል" ተብሎ ይገመታል (ቄስ ብርሃኑ፣ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት)፡፡

ይህም በመሆኑ፤ ከማኅበረሰቡ ሥርዓትና ልማድ ሲወጡ፤ "የርኩሳን መናፍስ ማደሪያ፣ ተልእኮ ፈጻሚ፣ የአጋንንት መልእክተኛ፣ መተተኛ፣ ድግምት ሰሪ፣ ሰላቢ" እና መሰል ስያሜዎችን ያሰጣል፤ በዚህ ድርጊት የሚጠረጠሩ ግለሰቦች፤ የሕመም መንስኤ ተደርገው እንደሚታሰቡ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል (ወ/ሮ ዉዲቱ፣ ቃ.መ፤ 03/07/2011 ሊቦከምከም)፡፡ ማኅበራዊ ሥርዓት የሚያፈርሱ፣ ሃይማኖት የሚጥሱ፣ ማኅበራዊ ሕይወት የሚረብሹ፤ አጋንንት የሚጠሩ፣ ሰይጣን የሚያናግሩ፣ ዓይነ ምድር የሚጥሉ፣ ደም የሚያፈሱ፣ መንገድ ለመንገድ የሚያስፈሱ፣ ድግምት ጣይ፣ ተብታቢ፤ ተብለው በማኅበረሰቡ እንደሚወገዙ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ውለታዉ እና አቶ ደመቀ፣ ቃ.መ፤ 19/06/2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት)፡፡ ለአብነት ያህል፡-

አልቻል ቢላቸው በሰው ባይገፉት
ምናምንቴ አዙረው ቤቱን ዘረፉት፤
(አቶ አስማማው፣ቃ.መ፤08/03/2011 እብናት)

ምነው ሆዴ ፈራ ውስጤ ተንገላታ
ሄደሽ ነበር እንዴ ከነመሪጌታ፤
(አቶ መኮንን፣ቃ.መ፤29/04/2011 እብናት)

ይባላል፡፡ ማኅበረሰቡ ርኩስ መንፈስን ተዋርሰው፤ የሙት መንፈስ ጠርተው፣ መተትና ድግምት ሰርተው የሚኖሩ ግለሰቦችን አጥብቆ ይፈራል፡፡ ለምን? ሲባል፤ የማኅበረሰብን ልማድና ጤና የሚያዛቡ፣ ሥርዓት የሚያፈርሱ፣ ሐብት ንብረት የሚነሱ፤ እንደ ልዕለ ሰብ (Superhuman) አድራጊና ፈጣሪ፤ አምጪና ነሺ ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ አንድ ሰው ከልክ በላይ፤ ገንዘብ፣ ሐብትና ንብረት አከማችቶና ሰብስቦ ሲገኝ፤ ማኅበረሰቡ ይፈራል፤ "መተት አሰርቶ፤ ለሰይጣን ገብሮ ያከማቸው ሐብት ነው" ይባላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፤ "በወዝና በጉልበታቸው አዳሪ፤ ታታሪ ገበሬና ነጋዴዎች"፤ ሐብትና ንብረት ሰብስበው ወገን ዘመድ አብልተው የሚኖሩ ምስጉን ግለሰቦች፤ "በሚርትና በሰላቢ ስራና ተንኮል፤ ትዳራቸውን ጥለው፣ ቤተሰባቸውን በትነው፤ ሐብት እና ንብረታቸውን ሲያጡ ይታያል/ይሰማል"፤ ተብሎ በማኅበረሰቡ ይነገራል (አቶ አስማማው፣ ቃ.መ፤ 08/03/2011 እብናት)፡፡ ስለሆነም "መተት ይጥላሉ፤ ድግምት ይሰራሉ" የሚባሉ ግለሰቦች የሰይጣን አምሳል፤ የአጋንንት ተባባሪ ተደርገው፤ በማኅበረሰቡ ይታመናሉ፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡ የመስክ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ የበሽታ መንስኤ ምን እንደሆነ፤ ከየትና እንዴት እንደተነሳ፤ በየትኛው ሥነ ምህዳር እንደሚከሰት የሚያስረዳ ቢሆንም፤ የማኅበረሰቡን ሃይማኖት፣ የአኗኗር ልማድ፣ ማኅበራዊ ግንኙነት፣ ለዓለም እና ለተፈጥሮ የአላቸውን እሳቤ፤ ልማዳዊ ሥርዓት፣ ደንብ፣ ወግ፣ መመሪያና ሕግን በተጓዳኝ ይተርካል። Destro (2010, PP.227-228) "Cosmology and Mythology" በሚል ርዕስ በአቀረቡት ጽሑፍ የሰው ልጆች ተፈጥሮን ለመረዳትና አካባቢያቸውን ለማወቅ፤ ባህላቸውን መነሻ አድርገው ዓለም እንዴት እንደተፈጠረች፣ ሰው ከየት እንደመጣ፣ "ገነትና ሲኦል"፣ ቁሳዊ ዓለም ከየት እንደተገኘ ምላሽ ለማግኘት፣ ቅርፅና ሥርዓት አልባውን (The Formless void and chaos) ዓለም ትርጉም ለመስጠት የሚያደርጉትን ሂደት ይመለከታል።

የዚህ ጥናት ተተኳሪ ማኅበረሰብ አባላት ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች፣ ሕመምና መከራ ፈጣሪያቸውን፣ መላእክትን፣ አጋንንትን፣ የአያትና የቅድመ አያት ውቃቢን፤ የሰፈር አድባርና ቆሌን፤ ፈውስና ምኅረትን እንዲያወርዱ ይለምናል፤ ይጠይቃል፤ ይማፀናል። ይሄ ነገር ለምን በኔ ተከሰተ? ምን ሰርቼ ይሆን? የአያት ቅደመ አያት መንፈስ ተቆጥቶ ነው? በዓላትን ሽሬ ወይስ የሰፈር አድባር "ሳልካድም" ወጥቼ? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፤ ለሕመማቸው መንስኤና ፈውስ፤ ትርጉም እና ምክንያት በመስጠት ለዓለምና ለተፈጥሮ የአላቸውን እሳሴ እንደሚገልጹ፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል። ምሁራንም፤ ከምዕራባውያን ውጪ በማንኛውም ማኅበረሰብ እሳቤ ለሕመም መንስኤ ፈጣሪን፣ መላእክትን፣ አጋንንትን፣ የቅድመ አያት መንፈስና ውቃቢን ምክንያት እና መፍትሔ እንደሚያደርጉ (Heman, 1984; PP.74-83: Winkelman, 2009; PP.60-65) አስረድተዋል።

## 5.3 የተቃርኖ ኃይል ስበት እና የለውጥ ጥሪ

በአካባቢው ማኅበረሰብ እሳቤ ዓለም (መሬት) በሁለት ተቃራኒ ኃይሎች ስበት፣ ግንኙነት፣ ለውጥና ጥሪ ምክንያት ከመኖር ወደ አለመኖር፣ ከሕይወት ወደ ሞት የሚያሸጋግር ኃይል እንዳለ ይታሰባል። የተቃርኖ ኃይል መኖር ዓለምን ለመረዳት፣ የፍጥረት ምስጢርን ለማወቅ፣ የፈጣሪን ተዓምር፣ ሥራና ጥበብ ለመገንዘብና ለማመስገን ምክንያት እንደሚሆን፤ በተቃርኖ ኃይል ለውጥና ጥሪ፤ ብርሃን ባይኖር ጨለማ፣ ደግ ባይኖር ክፉ፣ ሐጢያት ባይኖር ጽድቅ፣ ሐሰት ባይኖር ዕውነት፣ ርሃብ ባይኖር ጥጋብ፤ ዲያቢሎስ ባይኖር ክርስቶስን፣ ክህደት ባይኖር

እምነት፣ መላእክት ባይኖሩ ርኩሳን፣ በሽታ ባይኖር ጤንነት፤... እንደማይታወቁ ይታመናል (ቄስ ብርሃኑ፣ ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት)፡፡ ከዚህ አንጻር፤ በሽታ፣ ሕይወትና ጤና፤ ምን ዓይነት መስተጋብር አላቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች የማኅበረሰቡ እሳቤ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ዓለም በሁለት ተቃራኒ ኃይሎች "በብሄሞትና ሊዋታን" ታስራ፣ ተጠፍራና ተከባ እንደተያዘች ይታሰባል፡፡ እነዚህ ኃይሎች ቢለያዩ፣ ቢላቀቁና ቢፋቱ "ዓለም ትጠፋለች፣ ትቢያ ትሆናለች" ተብሎ (መሪጌታ በረከት፣ ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት እና አቶ ሞገስ፣ቃ.መ፤ 22/06/2011 ፋርጣ) ይገመታል፡፡ ኪዳነ ወልድ (1948፣ገ.257፣561) ዓለምን ከበውና ጠፍረው የያዙ፤ "የብሄሞት" እና "የሌዋታን" ፍጥረት ምንነት፣ ባሕርይና ተግባርን እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

> ብሄሞት...የወንዝ አውሬ የባሕር ፈረስ... በየሐይቆቹ የሚገኝ ከዉሃ እየወጣ ሣር ቅጠል የሚበላ ታላቅ ገናና ቁርበተ ወፍራም፤ አንገተ ደንዳና... ዲኖ ጅን የባሕር የበርሃ ጎሽ፤ ጠባዩ ያውሬ መልኩ የበሬ፡፡ ... ከባሕር ተፈጥሮ በየብስ የሚኖር... አራዊት የሚፈሩትና የሚገዙለት ከአራዊት ሁሉ የሚበልጥ መጨረሻ ግዙፍ የእንስሳት እራስ፤ የአራዊት ንጉስ፤ በኩራቸው ቀዳሚያቸው፤ በተፈጥሮ የሌዋታን ወንድም ባኣ መሰሏ፡፡ ...[ሌዋታን] የባሕር አውሬ እንስሳ ዘንዶ፤...[ዓለምን ወይም ምድርን] እንደ ዝናር፣ እንደ ጋን ሰንበር ወይም እንደ ቀለበት፤ እንዳንባር ዙሪ ተጠምጥማ፣ ዐቅፋ የያዘች የብሄሞት ዘውግ፤ ጣምራው ኹለተኛው፤ ዘሩ ሰወየ [መሰሉ፤ አምሳሉ] ነው፤ ሌዋ አቃፊ ተጠምጣሚ፤ ታን ዘንዶ ወይም ወርድና ቁመት ግዘፈ ምድር፤ በተገናኘ የምድር መታጠቂያ ቅናት [የፀሐፊው ቃል ነው]፤ መቀነት ማለት ነው፡፡

እንደ ኪዳነ ወልድ መረጃ እና የባህል ሐኪሞች (ማኅበረሰብ) እሳቤ፤ ዓለም (መሬት) በሁለት ተቃራኒ ጾታ ባላቸው ኃይሎች ተከባ፣ ታስራና "ተጠፍራ" እንደተያዘች እና እንደቆመች ተጠቁሟል፡፡ እነዚህ ተቃራኒ (በጾታ) ኃይሎች እርስ በርሳቸው የሚተሳሰሩ፣ የሚዋዋጡ፤ በዝርያ፣ በአካልና በአምሳል አንድ ዓይነት በጾታና በግብር ተቃራኒ፤ መቀራረብ፣ መወራረስ፣ መፈላለግ፣ መግባባት ያለበት፤ የሁለቱ መለያየት የዓለም "ፍፃሜና ጥፋት" የአንዱ አለመኖር ለሌላው መጥፋት ምክንያት እንደሚሆን አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በታች ዓለምን "ጠፍረው" የያዙ የ"ብሄሞትና ሌዋታን" ዘንዶዎች ተምሳሌት የፎቶ ምስል ይዘት እንደሚከተለው፤ ተጠቁሟል፡፡

ፎቶ ግራፍ አንድ፡- ዓለምን (መሬትን) ከበውና አስረው የያዙ የ"ብሄሞትና ሌዋታን" እሳቤ ምስል



ዓለምን ከበውና አስረው የያዙ "የብሄሞትና የሌዋታን" ዘንዶዎች እሳቤ

ምንጭ፡- ከመሪጌታ መኀሪ የብራና መጽሐፍ ቅጠል፤ በቀን 28/01/2011 ዓ.ም የተወሰደ፤

ከዚህ በላይ በፎቶ ግራፍ አንድ ይዘት እንደተጠቀሰው፤ "መልክዓ ራጉኤል የፍጥረት ዓለሙ ጠባቂ እና አጋንንት የሚያሳድድ [አባራሪ]፤ ሩፋኤል ማሕፀን የሚፈታ፣ ፈዋሽና ፈጥኖ ደራሽ፤ ፋኑኤል ጠባቂና ከአደጋ የሚሰውር፤..." ተልዕኮ እንዳላቸው፤ ለምስጋና የሚተጉ የመላእክት ስምና ነገዶች፤ ለሳምንቱ ሰባት ቀናት ተምሳሌትና ምሳሌ ተደርገው እንደሚታሰቡ፤ ይመክራሉ (መሪጌታ መኀሪ፣ ቃ.መ፤ 28/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

በተቃርኖ ዓለም፤ ወንድ ባይኖር ሴት፣ ጥቁር ባይኖር ነጭ፣ ብርሃን ባይኖር ጨለማን፤ ቅዱስ ባይኖሩ ርኩስ፣ ሕይወት ባይኖር ሞትን መረዳት እንደሚያዳግት የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል።

የሕይወትን ጣዕም፣ ልፋት፣ ምኞትና ተስፋን ለማወቅ፤ ሞት[55] ምክንያት ይሆናል። የሕመም መጨረሻው "ሞት" ነው፤ "ሞት ደግሞ በመውለድ ይሸነፋል" ይባላል (መሪጌታ ገብረመድኅን፤ ቃ.መ፤ 25/04/2011 ሊቦ ከምከም)።

የሰው ልጅ ሞተ የሚባለው መቼ ነው? ሲባል፤ የሥነ ሕይወት ባለሙያና የዘረመል ተመራማሪ ሣይንቲስቶች "አንድ ሰው ሞተ የሚባለው የዘረ መል ሞት ሲሞት ነው።... ልጅ ሳይተካ ሲሞት ነው።... የአባትና እናት ማንነት በልጅ በኩል ይቀጥላል፤..." እንደሚባል፤ ይሁኔ ገልጸዋል (2010፤ ገገ.272-273)። "የሕይወት ዋናው ዓላማ ዘርን ተክቶ ማለፍ ነው"፤ ልጅ ወልዶ መሳም የማንነት መትከያና ማስቀጠያ ምሰሶ፤ ክርና ገመድ ተደርጎ ይታመናል። "መውለድ"[56]

---

[55]የሕይወትና የሞት እሳቤ፤ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ እሳቤን፤ ሰፊና ውስብስብ አተያይን የሚያካትቱ ይዘቶች ናቸው። በዚህ ጥናት የቀረበው ርዕሰ ጉዳይ በሕመም ምክንያት የሚከሰተውን ሥጋዊ፣ ምድራዊና አካላዊ ሞትን ብቻ ታሳቢ ያደርጋል። ከዚህ ይዘት በራቀ ማስረዳት ከርእሰ ጉዳዩ በተወሰነ ይዘት የሚነጥል ስለሆነ፤ የሕመም መንስኤ፣ እሳቤና የዓለም ዓተያይን ለመጠቆም የቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች መሆናቸውን ልብ ይሏል።

[56]በማኅበረሰቡ እሳቤ "መውለድ"፤ የማንነት፣ የዘርና የዕሴት ማስቀጠያ ክር እና ገመድ ተደርጎ ይወሰዳል። መሐን ሴት ስትሞት "ሐዘኑ መሪር ነው፤ ቋሚን ይፀፅታል፤ ፈጣሪን ያስረግማል" ተብሎ ይታሰባል (ወ/ሮ ሙሉ፣ ቃ.መ፤16/04/2011 ፋርጣ)፤ በቀብሯ ዕለት እንደሚከተለው ሙሾ ይቀርባል፡-

እኔ ሞኝ አንቺ ሞኝ ሁላችን እንስሣ
ከጨዋታው ሁሉ ሞተን ሳንነሣ
የመሃን ምን አላት ያለመቀነቷ
ቀባሪ ሲመለስ ይወረሳል ቤቷ...፤

ይባላል። ማኅበረሰቡ ማንነቱን ለማስቀጠል "ሞትን ድል ለመንሳት" መውለድን ያከብራል፣ ያደንቃል፣ ይመኛል። ከቀረበው ቃል ግጥም መገንዘብ እንደሚቻለው፤ "እኔ ሞኝ አንቺ ሞኝ ሁላችን እንስሳ" ሲባል ልጅ ወልዶ በማሳደግ ሂደት፤ ክፉ ደጉን ሳናይ፤ ውጣውረዱን ሳንረዳ፤ ደስታ ሐዘኑን ሳንጋራ እንደ እንስሳት ኖረን ለስማችን መጠሪያና ለዘራችን መቀጠያ አሻራ ሳይኖረን፤ ከዚህ ዓለም መሰናበትን ይጠቁማል። በቀጣዩ መስመር "ከጨዋታው ሁሉ ሞተን ሳንነሳ" የሚለው ስንኝ በፈጣሪ ፍቃድ በወንድና ሴት ጾታዊ ተራክቦና ግንኙነት ልጅ ይወለዳል፣ አምሳል ይተካል፣ ዘር ይቀጥላል። የፈጣሪን ፍቃድና ፀጋ ሳያገኙ ልጅ ለመውለድ ሳይታደሉ፣ እንደተመኙ "መሐን" ሆነው እንዳለፉ ይገልጻል። በተለይ "...ሞተን ሳንነሳ" የሚለው ሃረግ፤ አብራክን ለማግኘት፣ መሰልን ለመተካት የሚካሄደውን ሥነ ሕይወታዊ ዑደትና ሂደትን ይገልፃል። ፈጣሪ "በአካል ላይ ነፍስን ዘርቶ..." እንደሚባለው፤ ወደ ሕይወትና ሕያውነት መሸጋገሪያ መንገድ ሲሆን፤ በዚህ ዐውድ "ሞተን ሳንነሳ" ማለት ዘር ሳይተኩ፣ የአብራክ ክፋይ ሳያዩ ማለፍን፤ ትቢያ ሆኖ መቅረትን ይመለክታል። በስንኝ ሶስት የቀረበው ይዘትም "የመሃን ምን አላት ያለመቀነቷ" ሲል፤ "መቀነት" ወገብን ደጋፊ፣ ጠጋኝ እና አበርቺ ተደርጎ የሚታሰብ ሲሆን፤ አንድ ሴት ትዳር መስርታ፣ ልጆች ወልዳና ወግ ማዕረግ ስታይ በሥራ ብዛትና ጫና ወገቧ ይላላል፣ አጥንቷ ይሳሳል፣ ጉልበቷ ይደክማል። በድንግልናዋ ጊዜ የነበራትን ኃይልና ጉልበት ታጣለች ተብሎ ስለሚታሰብ፤ "መቀነት" የብርታት፣ የድጋፍ፣ የኃይልና የጠጋኝ ሚናን ስለሚወስድ ትዳር የመሰረተች ሴት ያለመቀነት አትንቀሳቀስም። ከቃል ግጥሙ እንደምንረዳው፤ የመሐን ሴት ድጋፍ፣ ብርታት፣ ኃይልና ምርኩዝ "በመቀነት" ተወክሎ ቀርቧል። ከ"መቀነቷ" በስተቀር፤ በስሟ የሚጠራ፣ ዘሯን የሚያስቀጥል፣ ደጋፊ፣ ጧሪና ተንከባካቢ ልጅ ስለሌላት ሐብት ንብረቷ በማይመለከተው አካል እንደሚወረስ ከቀረበው ቃል ግጥም መገንዘብ ተችሏል። በማኅበረሰቡ እምነትና እሳቤ ሳይወልዱ መሞት "ሁለት ሞት ነው" ይባላል። አንድም የዘርና የማንነት መቋረጥ፣ በስማቸው የሚጠራ ሲጠፋ፣ "ዐፈር ትቢያ" መሆናቸው ሲታሰብ፤ "እንደግር እሳት ያገበግባል" ይባላል። በሌላ በኩል ደግሞ በዓለማዊ ሕይወት ልጅ ለመውለድ መመኘት፤ መለመን፣ መፀለይ፤ ሳይሳካ ሲቀር በሃሳብ፣ በቁጭት፣ በፀፀት ኖረው ሲያልፉ ("ሲሞቱ")፤ "ሁለት ሞት ነው" እንደሚባል ይገልጻሉ (ወ/ሮ ጠጄ፤ ቃ.መ፤ 28/06/2011 እብናት)። የሰው ልጅ በሕይወት ለመቆየት፣ "ሕልው" ሆኖ ለመታየት፣ "ምድራዊ" ፍላጎቱን ለማሟላት፣ ነገን ለመኖር ዛሬ በተስፋ ይሰራል፤ ምኞቱን የሚገድብ፣ ፍላጎቱን የሚገታ፣ ተስፋውን የሚያጨልም፤ የነበረ ሲሔድ አዲስ ሲተካ፤ "ነበረ የለም" እየተባል የሕይወት ሂደትና ዑደት እንደሚቀጥል፤ ይታመናል።

የሕያውነት ማረጋገጫ፣ የዘላለማዊነት ተምሳሌት ተደርጎ ይቆጠራል (ወ/ሮ ጠጂ፤ ቃ.መ፤ 28/06/2011 እብናት)፡፡

የተፈጥሮ ሥርዓት፣ ክስተት እና ሕይወት እንዲቀጥል የተቃርኖ ኃይል ስበት መኖሩ ይታመናል፡፡ እንደ ማኅበረሰቡ እምነትና እሳቤ በተግባር፣ በባሕርይ፣ በመልክ፣ በዘር የሚመሳሰሉ፤ በአላቸው ጾታና ግብር የተፈጥሮ ሥሪት፣ ሕግና ሥርዓት የተለያዩ፤ ሕይወት ይጀመራል፣ መኖር ይቀጥላል፤ በአንጻሩ ሞት ተከስቶ መቀነስ፣ መለወጥ ይመጣል፡፡ በአንድ በኩል የተፈጥሮ ሚዛን (Nature Balance)፣ ምጣኔና ልኬት መጠበቂያ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የተፈጥሮ ምስጢር፣ መቆጣጠሪያ ሥርዓትና ደንብ ተደርጎ ይገመታል፡፡ በተቃርኖ ኃይል የሕይወት ዑደት (Life Cycle) ይቀጥላል፤ የነበረ ያልፋል አዲስ ይተካል፤ ሕይወት ይጀመራል፣ ሕመም ይከሰታል፣ ሞት ይቀጥላል፤ ሞት ደግሞ "በመውለድ ድል ይነሳል" ተብሎ በማኅበረሰቡ ይታመናል (ወ/ሮ ጀማነሽ፤ ቃ.መ፤ 02/07/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ የተፈጥሮ ኃይል ስበት፣ ሕመም፣ መተላለፊያ መስመርና የለውጥ ጥሪ ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ምስል 8፡- የተቃርኖ ኃይል ስበት፣ ሕመም፣ መተላለፊያ መስመርና የለውጥ ጥሪ




ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ የተዘጋጀ ምስል መዋቅር ሚያዚያ/2011፤

ሕይወት፣ መላእክት እና ብርሃን የዓለምን ፍጥረት፣ ድህነት እና ወቅትን ሲያመለክቱ፤ ሞት፣ አጋንንት እና ጨለማ ደግሞ የፍጥረትን ሞት፣ ጥሪ እና የወቅት ለውጥ ሂደትን ይጠቁማሉ፡፡

እንደ ደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ አተያይ ሕይወት በሁለት ተቃራኒ ኃይሎች (በቅዱሳንና በርኩስ መናፍስት) ትጠበቃለች፣ ትፈተናለች፤ ተብሎ ይታሰባል። ቅዱሳን መናፍስት ለሕይወት ተስፋ፣ ለችግር ደራሽ፣ ሕግ መስራች፣ ለሕመም ፈዋሽ፣ ለኑሮ ደስታ፣ ለጭንቅ አማላጅ፣ ኃይልና ጉልበት ሆነው ይቀርባሉ፤ በአንጻሩ ርኩሳን መንፈስ ሕግ አፍራሽ፣ ሥርዓት በታኝ፣ ለሕይወት ሞትን፣ ለደስታ ሐዘንን፣ ለፍስሐ ርሃብን፤ ለጤና ሕመምን ፤... በማውረስ የለውጥ ኃይል እንደሆኑ (መሪጌታ ባሕረጥበብ እና ደብተራ መልኩ፣ ቃ.መ፤ 22-23/01/2011 ፋርጣ) አትተዋል። ቄስ አብርሃም የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ጠቅሰው (ዘዳ፣18፤9-15)፤ "ሟርተኛ፤ በአባብ የሚጠነቁል አስማተኛ አይገኝብህ። ተራጋሚ መናፍስትን... [የሚጠራ]፣ የሞቱትን የሚጠይቅ ጠንቋይ ከቶ አይኑርብህ" መባሉን በማስታወስ፤ ርኩስ መናፍስት የሰው፣ የእንስሳት፣ የዕፅዋትና የተፈጥሮ ዓለምን ሕይወት በማናጋትና በማዛባት፤ ለሕመም እና ለሞት መዳረግ ቀዳሚ ተግባራቸው እንደሆነ (ቃ.መ፤ 01/05/2011 እብናት) ጠቁመዋል።

መሪጌታ ብሩህ ደግሞ "ሕይወት"፤ የሁለት ተቃራኒ ኃይሎች ፍላጎትና ተቃርኖ ድምር ውጤት ስትሆን፤ በዓለማዊ (በሥጋዊ) ፍላጎትና በመንፈሳዊ ሕይወት ምርጫ መካከል እንደምትገኝ ጠቁመው፤ "ፍጥረት ሁሉ፤ ሁለት ሁለት እየሆነ ጠባቂ እና ተጻራሪውን [አጥፊውን] ይዞ ተፈጥሯል" ይላሉ፤ ይህን ኃይል (ዓለማዊና መንፈሳዊ ባሕርይና ፍላጎቱን) አመጣጥኖ፣ አቻችሎ ለመኖር የሕይወት ምስጢርና ተግባር እንደሆነ መክረዋል (ቃ.መ፤ 18/06/2011 ፋርጣ)። የሰው ልጅ ያሰበውን እንዲሰራ፣ የፈለገውን እንዲመርጥ፣ የተመኘውን እንዲኖር፤ "ማሰቢያ አንጎል" [አዕምሮ]፣ ማመዛዘኛ ሕሊና ከፈጣሪ እንደተሰጠው፤ ዓለማዊ ሕይወትን መርጦ፤ ያገኘውን ቢበላ፣ ስግብግብ፣ ስስታም፣ ንፉግ፣ ዘራፊና በደረሰበት ሕይወት ቢያጠፋ "የዲያቢሎስን መንገድ ተከተለ፤ ርኩስ መንፈስ ተጣባው፤ ሰይጣን አደረበት፤ ገፋፍቶ ሕይወት እንዲያጠፋ አደረገው..." (አቶ ሞላ፣ ቃ.መ፤26/06/2011 ፋርጣ) ይባላል።

በተመሳሳይ መልኩ መሪጌታ አማረ እና ደብተራ መልኩም፤ ዓለም (ሕይወት) በሁለት ተቃራኒ ኃይሎች (በመላእክና በአጋንንት) ተከባ እንደምትገኝ ጠቁመው፤ መላእክት የምህረት፣ የጤና፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የበረከት፣ የልምላሜ፣ የውልደት፣ የደህንነት፣ የእድሜና ጤና ተምሳሌት ተደርገው ይታሰባሉ። አጋንንት ደግሞ የቅጣት፣ የቁጣ፣ የመቅሰፍት፣ የደዌ [የውስጥ አካል ሕመም]፣ የሕመም፣ የጦርነት፣ የርሃብ፣ የሁከት፣ የሞት መለዓክ በመሆን፤ የሰውን ደም የሚያፈሱ፣ ሕይወት የሚያጠፉ፤ እንስሳትን የሚገድሉ፣ ዕፅዋትን የሚያደርቁ፣ ሥራቸውን የሚያነግሉ፣ ዘራቸውን የሚያጠፉ፤ ሕይወት ባላቸው ነገሮች ላይ "ተዋርሰው" በምድር የሚኖሩ

ርኩሳን መናፍስ እንዳሉ ይገልፃሉ (ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም፤ ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ በስማቸው ቅደም ተከተል)፡፡

በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ ለሚኖርበት ዓለም (መሬት) ትርጉም ለመስጠት፣ ሥርዓት ለማበጀት፣ ፍቺና ተምሳሌቱን ለመወከል፤ ሥነ ምህዳራዊ መስተጋብርን ለማወቅና ለመረዳት (የዐየር ንብረት፣ መልክዓ ምድር፣ አካባቢ፣ እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ሰው…)፤ ዓለም በሁለት ተቃራኒ ኃይሎች ስበትና ክስተት እንደምትመራ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፤ Destro (2010; PP.231-232) ሰዎች ለሚኖሩባት ዓለም (መሬት) እና ለችግራቸው ትርጉም ለመስጠት ሲነሱ፤ ፈጣሪ፣ መላእክት፣ ቅዱሳን ሰማእታት ሕይወት እንዲፈጠርና እንዲቀጥል አማላጅ፣ ጠባቂና ተራዳኢ ሆነው ይቀርባሉ፤ ከዚህ በተቃራኒ አጋንንት፤ ጭራቅ፣ ሰይጣን ሕይወትን ለችግር፣ ለመከራ፣ ለሕመምና ለሞት የሚዳርጉ አጥፊ እና ቀሳፊ ሆነው እንደሚገለጹ፤ ጠቁመዋል፡፡ በሁለቱ ተቃራኒ ኃይሎች ፍልሚያ ሕይወት እንደምትፈተን፤ የምህረትና የቅጣት፣ የድሕነትና የሞት፣ የገነትና የሲኦል ምክንያት በክርስትና ሃይማኖት እሳቤ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

## 5.4 መለከፊያ ዐውዶች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር፤ ከሕመም መንስኤ እና "መለከፊያ" ዐውዶች (መንገዶች) መካከል፤ በሕሊና ተሰውረው፣ በዐየር ተበትነው የሚኖሩ አጋንንት፤ በዕፅዋት የሰፈሩ፣ በእንስሳት የሚበሩ አጋንንት፤ በቆሻሻ የሚኖሩ፣ በወንዝ የሰፈሩ አጋንንት፤ በደም፣ ምግብና መጠጥ የሚነሱ አጋንንት፤ የዓመትና ወቅት ዑደትን ጠብቀው የሚከሰቱ አጋንንት፤ የኮከብ ባሕርይ መግነንና መክሰም ይዘቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 5.4.1 በሕሊና ተሰውረው፤ በዐየር ተበትነው የሚኖሩ አጋንንት

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤ፤ የዛር መናፍስት በሰው ሕሊና በመሰወር፣ በመላው አካል በመሰራጨት መራቢያ አካልን በማድከም፤ ትዳር መከልከል፣ በሕልመ ሌሊት "መመታት"፣ ፈሪና ገርጋሪ ማድረግ፣ በጨለማ ማስቀመጥ፣ መደበትና የሕሊና መናወጥ፣ የፍላጎት መቀያየር እና ለብቻ ማልቀስ፤ የሕመሙ መንስኤ እና መለያ ምልክት ተደርጎ ይቆጠራል (መሪጌታ ባሕረ ጥበብ እና መሪጌታ ስዩም፤ ቃ.መ፤ 27/02/2011 እና 04/02/2011 ፋርጣ እና እብናት ወረዳ በቅደም ተከተል)፡፡ ለምሳሌ፡- "ቅጥቃጤ አደረብኝ! ሕልመ ሌሊት መታኝ! እባብና ዘንዶ ሲያባርረኝ

አደረ፤ ዛር ሳትሆን አትቀርም፤ የቤት በር ወደ ጎን ሆናችሁ ክፈቱ፤ ቤት የዋለ ሰይጣን/መጋኛ እንዳይመታችሁ!..." (ከተቡው አባላት፣ቃ.መ፤19/06/2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት) ይባላል፡፡ የዛር መንፈስ ምን ዓይነት ስሜትና ተግባር እንዳለው መሪጌታ ስዩም (ቃ.መ፤ 04/02/2011 እብናት) እንደሚከተለው በቃል ግጥም ይገልጻሉ፡-

አይነቁም አይነቁም የሴት ዛር አይነቁም
እንደቀበኛ ላም ይገፋሉ በቁም፤...

ይባላል፡፡ የዛር መንፈስ አካልን ማንቀጥቀጥ፣ ማንገላታት፣ ስሜትን ማናወጥ፣ ቀስ በቀስ ሕሊናን የመሰውር ተግባርና ይዘት እንዳለው የቀረበው ቃል ግጥም ይጠቁማል፡፡ ሊቀጠበብት አብርሃም እና መሪጌታ ስዩም ዛር ማለት፤ ዘር፣ ነገድ፣ በዘር የሚወረስ፣ በዘር የሚመጣና የሚሄድ፤ በቤተሰብ ሲመለክ፣ ሲመረቅ፣ ሲገበር የቆየ ወደ ልጅ የሚተላለፍ፤ የቤት ጣጣና ልማድ መሆኑን ገልጸው፤ በባሕር፣ በዛፍና በተራራ የሚኖሩ ልቡሳነ ሥጋ (ሥጋ ለበስ አካል) የሆኑ፤ እንደሰው የሚዋለዱ፣ የሚበሉ፣ የሚጠጡ እና የሚሞቱ፤ ከሰው፣ ከእንስሳት፣ ከዛፍ፣ ከገደል፣ ከተራራ ተጠግተው እና ተሰውረው በመኖር የሚታወቁ፤ የአጋንንት ዘር የጅን ዘመድ ናቸው፤ ይባላል (ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም፤ 4/02/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡ ደስታ (1962፤ገ.508) "ዛር" ማለት "ክፉ መንፈስ፣ ከግዜር ከመላእክት፣ የተለየ ውቃቢ፣... በሰው ላይ እያደረ ሰውን የሚያስጓራ የሚያስገዝፍ..." መንፈስ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

መሪጌታ ባሕረጥበብ ደግሞ፤ የዛር መንፈስ የተዋረሱትን ሰው ሕሊና በመቆጣጠር፣ የመራቢያ አካልን በማድከም፣ ነፍሰ ጡር እናቶችን (ሾተላይ) በማሶረድ፣ ልጅ በመከልከል፣ ከተቃራኒ ፆታ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፍራት፣ የብልት አለመታዘዝ፣ ስሜት፣ ፍላጎትና አካልን በማፋታት ማድከም፤ በሕልመ ሌሊት መንፈሱ እየተመሰለ ሩካቤ መፈጸም፤ ትዳር ማፍረስ፣ ልጅ መበተን፣ አጋር መከልከል፣ የቤተሰብ ውርስና ልማድ፤ የዛር መንፈስ ባሕርይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ የኮከቡ ባሕርይ ሸርጣን ዉኃ የሆነ ሰው "...በምንጭ በገደል የምትቀመጥ ሴት ጋኔል ትመታዋላች፤ እርስዋ ከዘማዊነቷ የተነሳ እንደ ቅናት አድርጋ ራሱን፣ ሆዱን፣ ልቡን እየቀሰቀሰች በቀኝ እግሩ እንደ ቁርጥማት ትገባበታለች፤ ብልቱን እንደ ሽንት ማጥ አድርጋ አሳብጣ ታመዋለች በሕልሙ በውድቅተ ሥጋ ትገናኘዋለች..." በማለት (መሪጌታ ባሕረጥበብ 22/01/2011 ፋርጣ) አስረድተዋል፡፡

መሪጌታ መኅሪ፤ "የዛር መንፈስ እንኳን መዕመኑን [የሃይማኖቱ ተከታይ አማኝ] የሃይማኖት አባቶችን ይፈትናል" ይላሉ። የሃይማኖት አባቶች ለፀሎት፣ ለሱባኤ፣ ለምናኔ ሲገቡና ሲወጡ፤ ፀሎት እንዳይስቱ፣ ሱባኤ እንዳያፈርሱ፤ ወደ ፀሎትና ሱባኤ ሲገቡ፤ አካላዊ "የፍትወት" ፍላጎታቸውን እንዳይቀሰቀስ እና ሕልመ ሌሊት እንዳይመታቸው፤ ስሜታቸውን የሚያጠፋ፣ የሚቀንስ፣ የሚገድብ፣ የሚያደክም "ዕፀ" እንደሚወስዱ፤ በአንጻሩ ፀሎትና ሱባኤ ጨርሰው ሲወጡ ተፈጥሯዊና አካላዊ "የፍትወት" ስሜታቸውን ወደ ነበረበት የሚመልስ ዕፀ መድኃኒት እንደሚጠቀሙ፤ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 28/01/2011 ሊቦ ከምከም)። የዛር መንፈስ መንስኤ፤ በዋናነት ከቤተሰብ በውርስ ወይም በዘር የሚመጣ ሲሆን፤ የዛር ማደሪያና መኖሪያ የሆኑ ዕፅዋት መቁረጥ፣ እንስሳትን[57] መግደል በዛር መንፈስ ለመያዝ ምክንያት መሆናቸውን (መሪጌታ ፍሬስብሃት፣ ቃ.መ፤ 29/01/2011 ሊቦ ከምከም) ገልጸዋል።

በባህል ሐኪሞች እሳቤና ገለጻ፤ የዛር መንፈስ ከቤተሰብ የሚወረስ፣ ከባሕርና ከየብስ በመነሳት ሰዎችን የሚለክፍ፣ "ቁራኛ" መንፈስ ተደርጎ ይቆጠራል። በማኅበረሰቡ እሳቤና እምነት፤ በዛር የተያዙ ሰዎች (ውቃቢ፣ ቃልቻ፣ ከራማ፣ አውሊያ በሚባሉ ቃላት ይጠራሉ) የመፍረድ፣ የመተንበይ፣ የመጠንቆል እና አጋንንትን የማናገር ኃይል እንዳላቸው ይታሰባል። የዛር መንፈስ ለጊዜውም ሆነ በዘላቂነት በሰው ሕሊና ላይ አርፎ አንደበታቸውን ቀይሮ እንደሚናገር ይታሰባል። ለመንፈሱ የሚስማማ፣ "ምስ" (ግብሩን) እና የደም መስዋዕት ካቀረቡ፤ ሥርዓቱን በወር እና በዓመት ከፈጸሙ ጠባቂያቸው፤ ሥርዓቱ ሲቀርና ሲጓደል ሕሊናቸውን ሰውሮ፣ አካላቸውን አጉድሎ፣ ሐብት ንብረታቸውን በትኖ ለሕመም መንስኤ፤ ለሞት ምክንያት እንደሆነ ይነገራል (አቶ ጌጡ፣ቃ.መ፤24/01/2011 ፋርጣ)። የዛር መንፈስ ሲጀምርና ሲለመን፣ የመዋረሻ ስልትና መንገዱን፤ የሚጠቁሙ ቃል ግጥሞች ይዘት እንደሚከተለው ቀርበዋል፦

የበርሃው የሽመሉ ጓዴ
ና ዘመዱ ና ዘመዴ
በሽንጧ ግባ በመቀነቷ
በጣቷ ግባ በቀለበቷ
በጥርሷ ግባ በጥቁራቷ… እየተባለ ይለመናል።

(መሪጌታ ስዩም፣ቃ.መ፤ 04/02/2011 እብናት)

አንተን የጠላ የለውም በረከት

[57]የዛር መናፍስት በተራራ፣ በወንዝ፣ በዛፍ፣ በዋሻ እና ወጣት በሆኑ እንስሳት ላይ ይኖራሉ/ይሰፍራሉ፤ ተብሎ ይታመናል። ወጣት የሆኑ የደጋና የበርሃ እንስሳት መግደል፤ የአድባር ማደሪያ የሆኑ ዛፎችን መቁረጥ፤ በዛር መንፈስ ያስመታል፤ ተብሎ ይፈራል (መሪጌታ ፍሬ ስብሃት፣ ቃ.መ፤29/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

በኖ በኖ ያልቃል እንደ ፊኖ ዱቄት…
አጠር ያለ ቁምጣ ወጨፎ ትራሱ
የራሄሎ ጌታ መጣ ነፍስ ቢሱ… ይባላል፡፡
(ደብተራ ጥላሁን፣ ቃ.መ፤13/03/2011 ሊቦ ከምከም)

ከዚህ በላይ የቀረቡ ቃል ግጥሞች እንደሚያስረዱት፤ የዛር መንፈስ ወደ ቤት አባል ሲገባ፤ መንፈሱን መለመን፣ መጥራት፣ መካደም፣ መውደድ፤ ለሥርዓቱ፣ ለግብርና መስዕዋቱ እራስን ማዘጋጀት፣ በጸጋ መቀበል፤ በአካላዊ ውበትና ደም ግባት መንፈሱ ወደ ሰውነት ሲገባ፣ ሲዋሃድ፣ ሲዋረስ፤ የአካል፣ የአጥንት፣ የደም አባል ሲሆን፤ የዛር መንፈሱ እንደ ጠባቂ፣ ተንከባካቢ ተደርጎ ይታመናል፡፡ በአንፃሩ የዛር መንፈስ ተነስቶ "ፈረሱን" [ባለዛሩን/መንፈሱ ያደረበት ሰው] "ሲያጎራ፣ ሲስቅ፣ ሲያጨበጭብ፣ ሲዘል እና ሲጨፍር" አይቶና ሰምቶ መሳቅ፣ መቀለድ፤ ለርኩስ መንፈስ ወይም በሽታ ይዳርጋል፤ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ማንኛውም ተግባርና እንቅስቃሴ ለመንፈሱ ተፃራሪ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ መሆኑን እንደሚከተለው (ደብተራ መኅሪ፣ቃ፣መ፤13/03/2011 እብናት) ጠቁመዋል፡፡

አውለያ ሳቀ ብሎ አይሳቅም፤
ተጠንቅቆ መሄድ እሾህ አያሶጋም፤

በማለት የዛር መንፈስ መከበር እና መፈራት እንዳለበት፤ ይህ ካልሆነ ለጤና ሕመምን፣ ለአካል ቁስለትን፣ ለሕሊና ጭንቀትን እንደሚያወርስ፤ ይታሰባል፡፡ የዛር መንፈስ አድሮባቸው የተለያየ ድርጊት ቢሰሩ፣ ቢስቁ፣ ቢጮሁ፣ ቢዘሉ፣ ቢዘፍኑ፣ ቢጨፍሩ፣ ዛፍ ቢወጡ፣ ባሕር ቢገቡ፣ እሳት ቢጭሩ፣ ቢጨብጡ፣ ቢቅሙና ቢበትኑ፤… መንፈሱ ምህረት እንዲያወርድ ይለመናል፣ ይካደማል፡፡ ይህ ሁሉ ድርጊት የመንፈሱ ቁጣ ወይም ኃይል ተደርጎ ይታሰባል፤ ግለሰቦቹ ከመንፈሱ ሲመለሱ እራሳቸውን ሲያውቁና ሲረጋጉ እያስታወሱ መንገር፣ መቀለድና መሳቅ፤ የዛር መንፈሱ በጋኔል ያስመታል፤ ተብሎ ይፈራል (ደብተራ ጥላሁን፣ ቃ.መ፤ 93/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

የደቡብ ጎንደር ዞን ክልልና ማኅበረሰብን "አዳኝ ወርቁ እና ራሔሎ" የሚባሉ ሁለት ዐበይት የዛር መናፍስት እንደሚያስተዳድሩት፤ ይታመናል፡፡ አዳኝ ወርቁ በርብ ወንዝ እና በጉና ተራራ፤ ራሔሎ ደግሞ "በዓለም ሳጋ" ጥብቅ ደን እና በአድባራት ቦታዎች በመኖር፤ የማኅበረሰቡን እንቅስቃሴ፣ ሕይወት፣ ተግባርና የዕለት ዉሎን እንደሚከታተሉ (መሪጌታ ባሕረጥበብ እና አቶ

ደሴ፣ ቃ.መ፤22/01/2011 ፋርጣ፤ 25/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል) ይታሰባል፡፡ መሪጌታ ባሕረጥበብ፤ አዳኝ ወርቁ በሕሊናዋ ተሰውሮ የተዋረሳትን፤ ሴት "ጠባይ"፣ ተግባር እና ሁነት እንደሚከተለው (ቃ.መ፤ 22/01/2011 ፋርጣ፤) ተርከዋል፡፡

**ሚት (Myth/Mythology) ሁለት፤ አዳኝ ወርቁ፡-**

> አዳኝ ወርቁ፤ መልካም መዓዛ፣ ሽቶ፣ እጣን፣ ወርቅና ጌጣጌጥ በብዛት ይወዳል፡፡ አካላዊ መልክ፣ ቁመና እና ደም ግባት ያላትን ሴት ከሌላ ወንድ አስቀድሞ ለራሱ ይመርጣታል፡፡ በዚህ ዛር የተለከፈች ሴት ማጌጥ፣ መኳኳል፣ መሽቀርቀር ታበዛለች፣ ወንድ ሲቀርባት ትርቃለች፣ በውበቷ ትመካለች፣ በእድሜ ዘመኗ ትዳር ሳታይ፣ ልጅ ሳትወልድ፣ ከርታታ ሆና ትቀራለች፡፡... የአዳኝ ወርቁ ዛር መልክና ጠባይ የተዋረሳት ሴት፤ መኳኳል፣ በአንገቷ ወርቅ፣ በጆሮዋ ጌጥ ማንጠልጠል እና በፀጉሯ ማሰር ታበዛለች፡፡ በእግሯና በእጇ ላይ ጌጥ ታስራለች፤ የዛር መንፈሱ ልዩ ውበት እና ግርማ ሞገስ ይሰጣታል፡፡... ብዙ ጊዜዋን ከወንድ ጋር አትሆንም፤ ቤት ዘግታ ትቀመጣለች፤ ውጭው ዓለም ያስፈራታል፣ ከቤተክርስቲያን ትርቃለች፤ ለመንፈሱ ቁራኛ ሆና ትኖራለች፤...

በማለት ይገልጻሉ፡፡ በባህል ሕክምና ዕውቀት፤ የዛር መንፈስ የአዕምሮ አካልን በመቆጣጠር፣ የሰውነት መራቢያ አካልን ማድከምና ሥርዓትን ማዛባት፤ ማኅበራዊ ኑሮን ማናጋት፤ ማኅበራዊ ሕይወትን ማቃወስ፤ ትዳር አልባ ማድረግና ማፍረስ፣ ልጆችን መበተን፣ ግለሰቡን ማስጨነቅ፣ ሥነ ልቡናዊ ጉዳት ማድረስ፤... የዛር መንፈስ ባሕርይና ተግባር ተደርጎ እንደሚታሰብ፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡

በዐየር "ተበትነው እና ተሰውረው" የሚኖሩ የዐየር አጋንንት (ጋኔል) ይባላሉ፡፡ እነዚህ አጋንንት ለሰው፣ ለእንስሳት፣ ለዕፅዋት እና ለፍጡራን ዓለም (ሕይወት ለአላቸው) አስፈሪ፣ አስቸጋሪ፤ ከያዙ የማይለቁ፣ ከዐየር የሚወረወሩ፣ ታማሚን የሚያንገላቱ፣ "ቁራኛ" እና የእድሜ ልክ ሕመም፣ አብረው የሚያድጉና የሚኖሩ የዕድሜ ልክ መከራ፤ "ክፉ" መቅሰፍት ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ እንደመሪጌታ ስዩም መረጃ፤ በዐየር የሚኖሩ አጋንንት ለሰው ብቻ ሳይሆን ለፍጥረት ዓለሙ መቅሰፍት እንደሆኑ ጠቁመው፤ "የምድር ጋኔል ማር እንደ ነካ እጅ ይቆጠራሉ፤ የዐየር ጋኔል ደግሞ ቅቤ እንደነካ እጅ ቶሎ አይለቁም" ይላሉ (ከተቡው አባላት መሪጌታ ስዩም፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)፡፡

ማር የነካ እጅ በውኃ ሲታጠቡት ቶሎ ይለቃል፣ ይጠራል፣ ታጥቦ ይሄዳል፤ እጅ ላይ ተጣብቆ የሚቀር ሽታና ኃይል የለም፤ በዚሁ ትይዩ የመሬት ጋኔል በባህል ሐኪሞች ፈውስና መፍትሔ

እንዳላቸው ጠቁመው፤ በሽታው የማይመለስ፣ የማያዳግም፣ ለቶ የሚሄድና የሚወጣ ተደርጎ ይታሰባል። በአንጻሩ የዐየር ጋኔል ተወርዋሪ፣ ድንገት "መቺ"፣ ለአዕምሮ ሕመም፣ ለአካል "ጥመት" የሚዳርጉ፤ የፈውስና የሕክምና ሂደቱም ፈታኝ፣ ትግስት ጨራሽ፤ ለታማሚው ስቃይ፣ ለአስታማሚ መከራ፤ ምንም ዓይነት መድኃኒት ቢሰጥ ያስታግሳል፣ ያበርዳል፣ ያረጋጋል፣ ለጊዜው እረፍት ከመስጠት ባለፈ ዘላቂ መፍትሔ እንደሌለው፤ የሕመሙ ጉዳትና መጠን እየቀነሰ ቢሄድም አሻራ ሳይጥል፣ ምልክት ሳይተው እንደማይጠፉ ይመክራሉ (መሪጌታ ስዩም፣ ቃ.መ፤ 04/02/2011)።

መሪጌታ መጎሪ፤ የዐየር ጋኔል ተወርዋሪና ፈጣን መሆናቸውን ጠቁመው፤ የብርሃን ጨረር ተከትለው እንደሚወጉ፤ በር ሲከፈትና ሲዘጋ ጠብቀው እንደሚመቱ፣ ከወንዝ እና ከድንጋይ በሚነሳ ነፀብራቅ (ብርሃን)፣ በመብረቅ መመታት፣ ከዛፍ ላይ መውደቅ፤ አልኮል ጠጥቶ እራስን ስቶ ትቦ ውስጥ መተኛት፣ ደም መፍሰስ፣ አፍ ከፍቶ እና ምላስ "ጎልኩሎ" ማንከራፋት፤... ለአዕምሮ ሕመም፣ ለአጋንንት ልክፍት፣ ለአካል መሸማቀቅ፣ ለፊት መጣመም፣ ለዓይን መንሸዋረር፤... ምክንያት እና ለሕመም መንስኤ መሆኑን (ቃ.መ፤ 27/01/2011 ሊቦ ከምከም) ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በባህል ሕክምና እሳቤና ዕውቀት፤ "የስንፈተ ወሲብ" መንስኤ በዋናነት በዛር፤ የዐየር ጋኔል ደግሞ በፀሐይ ጨረር፣ በዐየር መጋጨት፣ "በብርድ ሕመም"፣ በድንገት መውደቅ፣ ጠጥቶ መስከር እና ደም መፍሰስ፣ በር ሲከፈትና ሲዘጋ በሚከሰት አጋጣሚ፤... የአዕምሮ ሕመም፣ የአካል መሸማቀቅ፣ የፊት መጣመም ይከሰታል፤ ተብሎ ይታመናል።

### 5.4.2 በዕፅዋት የሰፈሩ፤ በእንስሳት የሚበሩ አጋንንት

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ማኅበረሰብ እምነትና እሳቤ፤ የተወሰኑ ዕፅዋትና እንስሳትን የዛር፣ የቆሌ፣ የሰይጣን፣ የቡዳና የአጋንንት መኖሪያና መስፈሪያ ቦታዎች ተደርገው ይቆጠራሉ። የአጋንንት ማደሪያ የሚባሉ፤ ዕፅዋትን ከአካባቢያቸው ያርቃሉ፤ ከግቢያቸው ይነቅላሉ፤ በተመሳሳይ መልኩ ከእንስሳት ዓይነት የአጋንንት ተሸካሚ የሚባሉትን፤ ከቤታቸው ማራቅ፤ ወደ ግለሰብ እንዳይቀርቡ፣ እንዳይነካኩ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። በአንጻሩ ከአጋንንት ይጠብቃሉ፤ ከሰይጣን ይከላከላሉ፣ ከቡዳ መንፈስ ይሰውራሉ፤ ይፈውሳሉ የሚሏቸውን ዕፅዋትና እንስሳት በማቅረብ፤ ዕፅዋትን በግቢያቸው ይተክላሉ፤ እንስሳትን ያረባሉ (መሪጌታ ገብረመድኅን እና ወ/ሮ ጀማነሽ፣ ቃ.መ 25/04/2011 ሊቦ ከመወከም፤ 02/07/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። ለምሳሌ፡- "ዕፀ

ልባዊ/ት የአጋንንት ሰራዊት መኖሪያ፤ ዋርካ የዛር መንፍስ ማደሪያ፤ ዋንዛ የሰይጣን መከለያ (በመብረቅ ያስመታል)፣ ሾላ ጋኔል ይጠራል፣ ማንጎ አባወራ ይገፋል፤... ጅብ አጋንንት ተሸክሞ ይዞራል፤... እባብ የሰይጣን ውላጅ ነው፤ ቀበርቾ አጭሱበት ከቤት እንዲወጣ..." ይባላል (መሪጌታ ፍሬስብሃት፣ ቃ.መ፤ 29/01/2011 እብናት፤ ከተቡው አባላት የተሰበሰበ ፤ቃ.መ 19/06/2011 ፋርጣ)፡፡

ከነዚህ ይዘቶች መካከል ከዕፅዋት፤ ዕፀ ልባዊት፣ ዋርካ፣ ሾላ፣ ዋንዛ፣ ማንጎ፤... ከእንስሳት፤ ሥጋ በል የሆኑ (ጅብ፣ እባብ፣ ዘንዶ፣ ጥቁር ሙጨጭላ ወይም "ፋደት/ሸለምጥማጥ" ዘር)፤... በማኅበረሰቡ ይፈራሉ፡፡ ከነዚህ ዕፅዋትና እንስሳት በተቃራኒ፤ ከዕፅዋት ዓይነት ጌሾ፣ ብሳና፣ ግራዋ፣ ሎሚ፣ የቅመማ ቅመም ዘር በሙሉ፤... ከእንስሳት ሣርና ቅጠል የሚበሉ እንስሳትን ያቀርባሉ (ከተቡው አባላት መካከል ወ/ሮ እታገኝ እና ወ/ሮ ብሬ የጠቆሙት ሃሳብ፤ ቃ.መ፣ 19/06/2011 ፋርጣ)፡፡ ለምን ያርቃሉ/ያቀርባሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው፤ ከማኅበረሰቡ እሳቤና ተግባር አንፃር ምላሽ ቀርቧል፡፡ በማኅበረሰቡ እምነትና እሳቤ የአጋንንት ማረፊያና መስፈሪያ፤ ቡዳ የሚያሲዙ፣ ጋኔል የሚያስመቱ ተብለው ከሚፈሩ ዕፅዋት መካከል የዕፀ ልባዊ/ት ትረካ መሪጌታ ፍሬስብሃት (ቃ.መ፤ 29/01/2011 ሊቦ ከምከም) እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

**ሚት** (Myth/Mythology) **ሶስት፤ ዕፀ ልባዊ/ት (ገፀ ሰብእ)፡-**

> *ዕፀ ልባዊ/ት በቆላና በወይና ደጋ አካባቢ የምትገኝ፤ ከሣር ወይም ከችፍርግ ወገን የምትመደብ፤ አበቃቀልና ዕድገቷ እንደ ካሮት ነው፡፡... በዕጿ ሥር ገፀ ሰብዕ የመሰለ፤ ትዕምርተ ተባዕትና ትዕምርተ ዕንስት ምልክት አላት፡፡ በግንድና ቅጠሏ አካል ላይ እንደ ሰው፤ የእጅ መዳፍ እና አምስት የጣት ምልክት አላት፡፡ ዕጿ፤ አርባ አራት የአጋንንት ጠባቂ ሰራዊት የሰፈሩባት፣ የቡዳ እና የዛር መንፈስ ተሸካሚ ናት፡፡ ...በተለይ አነስታይ የሆነችው ዕፀ ልባዊ/ት ወር በገባ በሃያ ዘጠነኛው ቀን የወር አበባ ታያለች፡፡...ይህም፤ የሔዋን መርገምት ተምሳሌት ነው፤ ዕዳዋን እየከፈለች ነው፡፡ ...በሃያ ዘጠነኛው ቀን ቀረበው ሲመለከቷት በቅጠሏና በስሯ መጋጠሚያ ቦታ በግንዷ ዙሪያና ቀለበት ክርክር ላይ ደም ይፈሳታል፣ ታዣለች፤ ከሌላው ቀን በተለየ የምድር ቁጫጭና የጉንዳን ሰራዊት ግንዷንና ቅጠሏን ወረው፤ የሚፈሰውን ደም ይልሳሉ፡፡ ...የዕጿን መልክ፣ ዓይነትና ባሕርይ የማይለይ ሰው በእጁ ቆርጦ ቢቀምሳት ቡዳ ታደርጋለች፣ ጋኔል ታስመታለች፣ አዕምሮን ትሰውራለች፤... የዛር መንፈስ አሲዛ ዛፍ ላይ ትሰቅላለች፣ ባሕር ትከታለች፣ እሳት ላይ ትጥላለች፣ ገደል ትሰዳለች፤ አደገኛ ናት! ... ዕጿን፤ ለመቁረጥ ቢያንስ የሶስት ቀን ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡... ፀሎተ ድግምት ሲደረግ፤ የአቆራረጥ ገቢር፣ ለአጋንንት ቀለብ የሚሆን የነጭ ዶሮ ደም መስዋዕት አቅርቦ፣ ቡና፣ እጣን፣ ቆሎ፣ ቂጣና አረቄ... ተይዞ፤ በሥርዓትና በአግባቡ ከተቆረጠች፤ ለማንኛውም ሕመም ፈውስ አላት፡፡*

በማለት አስረድተዋል። ከዚህ በላይ የቀረቡ የመስክ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ዕፅዋት፤ በሽታን ወይም አጋንንትን የመሸከምና የማስተላለፍ ኃይል እንዳላቸው፤ በአንጻሩ የድኅነትና የፈውስ ምክንያት እንደሆኑ ተጠቁሟል። ለጋኔል፣ ለሰይጣን፣ ለቆሌና ለዛር መኖሪያና መስፈሪያ የተመረጡ ዕፅዋት በመልካም ሽታቸው፣ በጥሩ መዓዛቸው፣ በጣፋጭ ፍሬያቸው አገልግሎት የሚሰጡ ዛፎች ለአጋንንት መኖሪያ ተስማሚ እንደሆኑ ይነጋራል። ለምን? ሲባል የዛርና የጅን መንፈስ... "ጥሩ ሽታና መዐዛ ስለሚወዱ" ይባላል።

የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያ የሆኑት አቶ እሸቱ (ቃ.መ፤ 22/04/2011 ሊቦ ከምከም) በሰው፣ በአዕዋፍ እና በእንስሳት የሚበሉ፤ ጣፋጭ ይዘት ያላቸው አትክልትና ፍራፍሬ መገኛ ቦታዎች በፍሬያቸው መብሰልና መበስበስ ምክንያት፤ ለባክቴሪያ፣ ለፈንገስ፣ ለቫይረስ እና ለተለያዩ ተሕዋሲያን መራቢያና መኖሪያ መንስኤ እንደሚሆኑ አስረድተዋል። በሂደትም ወቅትና ጊዜ ያለፈባቸው የበሰሉና የበሰበሱ አትክልትና ፍራፍሬዎችን የሚመገቡና የሚጠቀሙ ሰዎች፣ እንስሳትና አዕዋፍ በቀላሉ ለሕመም እንደሚጋለጡ፤ መክረዋል። በተመሳሳይ መልኩ ይሁኔ (2010፤ገገ 141-142) የአትክልትና ፍራፍሬ ምግቦችን ወቅትና ጊዜያቸውን ጠብቆ ቢቻል በየቀኑ መመገብ ተገቢ መሆኑን ገልጸው፤ "...በሽታ በራሳችን ስህተት እንዲከሰት የምናደርገው ምግባችንን በተስተካከለ ሁኔታ ሳንመገብ ስንቀር፣ በተበከለ አካባቢ ስንኖር [ሰው፣ አዕዋፍ እና እንስሳት የሚበሏቸው ፍራፍሬ ሚገኙባቸው ዛፎች በተለያየ ብስባሽ፣ ሽታና ባክቴሪያ የተበከለ ዐየር እና አካባቢ መገኛ መሆናቸውን ታሳቢ ያደርጋል]" መሆኑን ጠቁመዋል።

የሥነ ምግብ ባለሙያ አቶ ጋሻው (ከተቡው አባላት መካከል የአቀረቡት ሃሳብ ቃ.መ፤ 26/06/2011 እብናት ቡድን ሁለት) በተፈጥሯዊ፤ ይዘታቸው ጣፋጭ የሆኑ አትክልትና ፍራፍሬዎች በቀላሉ የመበስበስ፣ ይዘትና ጣዕማቸውን የመቀየር ባሕርይ እንዳላቸው፤ ወቅትና ጊዜያቸውን ጠብቆ ሳይበላሹ መመገብ ተገቢ መሆኑን መክረዋል። የስኳር ጣዕም ያላቸው ጣፋጭ ምግቦችን አዘውትሮ መመገብ የጤና አመጋገብ ልክን በማዛባት ለአጥንት መሳሳት፣ ለሰውነት ውፍረት እና ለተለያዩ በሽታዎች እንደሚዳርግ፤ አቶ እሸቱ ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 22/04/2011 ሊቦ ከምከም)። በይዘታቸው ጣፋጭና ለስላሳ የሆኑ ምግቦች በአጭር ጊዜ ውስጥ የመሻገት፣ የመበስበስ፣ የመበላሸትና ጣዕማቸውን የመቀየር ኃይል እንዳላቸው፤ ለምግብ መመረዝ፣ ለተቅማጥ፣ ለአንጀት ተስቦ፣ ለታይፎይድ እና ለተለያዩ አካላዊ ሕመም መንስኤ እንደሆኑ፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል። የዕፅዋት ጣዕም ባሕርይ፣ ዓይነትና ባህላዊ ምደባ ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ምስል 9፡- የዕፅዋት ጣዕም ባሕርይ፣ ዓይነት እና ባህላዊ ምደባ ማሕቀፍ




ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች ምድብ፤ በጥናቱ አቅራቢ ተዘጋጅቶ የቀረበ የካቲት/2011 ዓ.ም፤

በባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ሥርዓትና ተግባር መሰረታዊ የዕፅዋት ጣዕም ዓይነቶች፤ ጣፍጭ፣ መራራ፣ ለስላሳና ጎምዛዛ/አቃጣይ[58] ይዘቶች ናቸው። ከነዚህ ይዘቶች መካከል፤ ጣፋጭና ለስላሳ ጣዕም እና ጠረን ያላቸው ዕፅዋትና ምግቦች ለአጋንንት፣ ለዛር፣ ለቡዳና ለጅን መንፈስ ማደሪያ በመሆን፤ ለሕመም አጋላጭና ምክንያት ተደርገው ይታሰባሉ። በተቃራኒው መራራ፣ ጎምዛዛ፣ ኮምጣጣ፣ አቃጣይ ይዘትና ጣዕም ያላቸው ዕፅዋት ርኩስ መንፈስ ለማናገር፣ ለመጥራት፣ ለማስለፍለፍ፣ ለማስወጣት፣ ለመገዘት፣ ከአጋንንት ለማላቀቅና ከሕመም ለመፈወስ ግብዓት ሆነው በዋናነት ይቀርባሉ። የአካባቢው ማኅበረሰብም በይዘታቸውና በጣዕማቸው መራራ፣ ጎምዛዛና አቃጣይ (ጌሾ፣ ሎሚ፣ ብሳና፣ ጉሎ፣ ግራዋ፣ ሰንሰል፣ ቃጫ፣ ቅንጭብ...) ጣዕም ያላቸውን ዕፅዋት፤ በግቢያቸው መትከልና አጥር ማድረግ፣ ማቅረብና መንከባከብ፤ ርኩስ መንፈስን ለማራቅ፣ ከሕመም ለመፈወስ ምርጫቸው እንደሆኑ፤ መገንዘብ ተችሏል። ጠቅለል

[58]የዕፅዋትን ባሕርይ፣ ይዘትና ተግባር በማጤን ለሐብት፣ ለዕውቀት፣ ለመስተፋቅር... አገልግሎት የሚውሉ የዕፀ መድኃኒት ዓይነቶች በዋናነት ከዕፅዋቱ ተፈጥሯዊ ባሕርይና ይዘት እንደሚመነጭ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ ለዓብነት ያህል፡- ለሐብት፡-የሚውሉ ዕፅዋት በብዛት የሚያፈሩና ግዙፍ የዛፍ ዓይነቶች ሲሆኑ፤ በሐብታቸው ምክንያት "አጋንንት ይከባቸዋል፣ ዘራፊ ይጠጋቸዋል" ይባላል። ለዕውቀት፡- በይዘታቸው ቀጥ ብለው የሚያድጉ ምንም ዓይነት ቅርንጫፍ፣ ቅጣይ፣ ግንድና ቅጠል የማይዙ ዕፅዋትን ይመለከታል፤ ለመስተፋቅር፡- የመተብተብ፣ የማሰር፣ የመጠምጠም፣ የመቆንጠጥ እና የማሰር ኃይል ያላቸው፤ እራሳቸውን ችለው የማይቆሙ፤ በአጥርና በዕፅዋት ላይ ተንጠላጥለው የሚኖሩ ዕፅዋትን ይመለከታል፤ ተብሎ ይታመናል። ይህ ጥናት ድግምትና አስማታዊ ተግባራትን አይመለከትም፤ በዚህ ምክንያት ከጥናቱ ውጪ መሆናቸውን ልብ ይሏል።

በአለመልኩ፤ ጣፍጭ ይዘት እና ጣዕም ያላቸው የዕፅዋት ፍራፍሬና አትክልት፣ ምግብና መጠጦች በአጭር ጊዜ ውስጥ ጣዕማቸውን የመቀየር፣ ይዘታቸውን የመለወጥ፣ የመበስበስ ባሕርይ እንዳላቸው፤ አካባቢን የመበከል ኃይላቸው ከፍተኛ እንደሆነ፤ ለጉንፋን፣ ለአስም፣ ለምግብ መመረዝ፣ ለአንጀት ተስቦ፣ ለአካላዊ ቁስለት፤... መንስኤ እንደሆኑ፤ ከቀረበው ይዘት መገንዘብ (ይሁኔ፣ 2010) ተችሏል።

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ማኅበረሰብ እሳቤ፤ የአጋንንት ተሸካሚ፣ የሰይጣን ፈረስና መንፈስ ይዘው ይዞራሉ፤ ተብለው ከሚፈሩ እንስሳት መካከል፤ ጅብና እባብ ይጠቀሳሉ። እንደ ማኅበረሰቡ እምነትና እሳቤ፤ "ጅብ የሰይጣን ፈረስ ነው፤... ጅብ ጋላቢው ቆሌ፤... 'እከሌ ጅብ ጋላቢ ነው' ተብሎ ይታማል፤ 'በውድቅት ሌሊት አመድ ላይ ሲከባለል' ታየ፤... ጅብ የለከፈው [የነከሰው] አይድንም፤..." (ከተቡው አባላት ቃ.መ፤19/06/2011 ቡድን አራት) ይባላል።

በማኅበረሰቡ እምነትና እሳቤ ሥጋ በል፣ ተናካሽ፣ ተናዳፉ፣ ቆንጣጭና ደም መጣጭ፤ ባሕርይ እና ጠባይ ያላቸው እንስሳት አጋንንት ተሸክመው "ይዞራሉ፣ ይጠራሉ፣ ይበራሉ"፤ ይባላል። ከነዚህ በተቃራኒ ሣር እና ቅጠል በል እንስሳትን በማቅረብ፤ ለምግብ (የቀንድ ከብት) እና ለሥራ (የጋማ ከብት) አገልግሎት ይጠቀማሉ። ሥጋ በል እንስሳት አጋንንት ተሸካሚ፤ ሣርና ቅጠል በል እንስሳት "ቅዱስ" ተደርገው ይቆጠራሉ (ሸሆናቸው ድፍንና የማያመነዥጉ ከጋማ እንስሳት ውጪ) ለምግብ አገልግሎት ይውላሉ።

እንደ ባህል ሐኪሞች መረጃ፤ ጅብ፣ እባብ፣ መዥገር እና በአጠቃላይ ሥጋ በል እና ደም መጣጭ እንስሳት ይብዛም ይነስ፤ አጋንንት ተሸክመው እንደሚኖሩ እና እንደሚዞሩ፤ ከአጋንንት እየታገሉ "ሥጋ ይበላሉ፤ ደም ይመጣሉ፤ ይጠጣሉ" ተብሎ ይታመናል፤ ይተርካል። እነዚህ እንስሳት የለከፉት፣ የቀመሱት፣ የላሱት፣ የረገጡትና ያሸተቱት ምግብና መጠጥ በጋኔል ያስመታል፤ ተብሎ ይፈራል (መሪጌታ በረከት፣ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት)።

በማኅበረሰቡ ሃይማኖትና እምነት ሥጋ በል እንስሳት፤ ደም አፍሳሽ፣ ደም መጣጭ፣ የአጋንንት ማረፊያ፣ መገኛ እና ተሸካሚ ተደርገው ይቆጠራሉ፤ በጅብ የተነከሰ ወይም የተለከፈ እንስሳ አይድንም ተብሎ በማኅበረሰቡ ይታመናል። ጅብ የሰይጣን ፈረስ፤ የአጋንንት መንፈስ ተሸክሞ ስለሚዞር "ጥላውን ያጠላበት ሰው መናገር አይችልም፤ ተርበትብቶ ይወድቃል፤ አንደበቱ ይተሳሰራል" ይባላል (መሪጌታ ሠረቀ ብርሃን፤ ቃ.መ፣ 12/03/2011 እብናት)። በባህል ሕክምና ልማድ ጅብ ከምርመራ ዘዴ (አንድ ሰው በአጋንንት መያዝ/ አለመያዙን ለማረጋገጥ በጅብ ቆዳ

ላይ አስቀምጦ ምርመራ ይደረጋል) እስከ መድኃኒት በአለው ሂደት ውስጥ አገልግሎት እንደሚሰጥ ጠቁመዋል (መሪጌታ መንግስቱ፤ ቃ.መ፤ 14/03/2011 እብናት)፡፡

የጤና ባለሙያ አቶ ግርማ፤ ሥጋ ተመጋቢ እንስሳት ባክቴሪያ፣ ቫይረስ እና የተለያዩ በዓይን የማይታዩ፤ ረቂቅ የጀርም ተሕዋሲያን ተሸክመው እንደሚኖሩ ጠቁመው፤ የእብድ ውሻ በሽታ፤ ሥጋ በል በሆኑ እንስሳት እንደሚከሰት፤ በመንከስ፣ በመላስና፣ የተንጠባጠበ "ልሃጭ" በመንካት ቫይረሱ ወደ ሰውና እንስሳት እንደሚዛመት ገልጸዋል (ቃ.መ፤21/01/2011 ፋርጣ)፡፡

ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ፤ የምግብ ዝርዝር ምርጫ ውስጥ በዋናነት ከዕፅዋት እና ከዕፅዋት ተመጋቢ እንስሳት ወገን ያሉትን (ሸሆና ክፍትና የሚያመነዥጉ እንስሳትን) ይመረጣሉ፤ በአንፃሩ ሥጋ ተመጋቢ እንስሳት በሃይማኖት የማይፈቀዱ፤ በምግብ ዝርዝር ሥርዓት ውስጥ የማይካተቱ፤ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡ እንደ ማኅበረሰቡ እሳቤና ፍልስፍና፤ ለባክቴሪያ፣ ለቫይረስ፣ ለፈንገስ፤... የቀረቡና በዋናነት ተጋላጭ የሚባሉ እንስሳትን በማራቅ፤ ዕፅዋት ተመጋቢ የሆኑትን በማቅረብና በማላመድ ለምግብና ለሥራ መጠቀማቸው፤ ከሥጋ በል እንስሳት ጋር ያላቸውን ቅርበት፣ ተራክቦ፣ ንክኪ እና ይዘት መገደብና ማራቃቸው፤ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ማኅበራዊ ጤናቸውን ለመጠበቅ፤ አስተዋጽኦ እንዳለው መገንዘብ ተችሏል፡፡

### 5.4.3 በቆሻሻ የሚኖሩ፤ "በወንዝ" የሰፈሩ አጋንንት

እንደባህል ሐኪሞች እና ማኅበረሰቡ እሳቤ፤ መለከፊያ ምክንያት አጋንንት ተደርገው ይታሰባሉ፤ መነሻና መተላለፊያ መንገዳቸው፣ መከሰቻ ቦታና ወቅት፣ ሠዓትና ጊዜ፣ ለይተውና መርጠው እንደሚነሱ ይመክራሉ፡፡ የአጋንንት መኖሪያ አካባቢና መከሰቻ ዐውዶች ከሚባሉ ይዘቶች መካከል፤ ቆሻሻ መድፊያና መጣያ ቦታ፣ ብስባሽ ያለበት አካባቢ፣ ሞተው በሚገኙ እንስሳት (አህያ፣ ፈረስ እና የዱር እንስሳት)፣ ምግብና መጠጥ፣ ከብት የታረደበትና ደም የፈሰሰበት ቦታ መለከፍያ መንገዶች እንደሆኑ፤ በማኅበረሰቡ ይታመናል (ከተቡው አባላት፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 ቡድን አንድ)፡፡

የአጋንንት አለቃ፣ ታዛዥ፣ ውላጅና ጭፍራ የሆኑ "የጋኔል እና ጅን" ዘሮች በቆሻሻ እና በወንዝ (በባሕር) አካባቢ ሰፍረው፤ እንደሰው የሚሰሩ፣ የሚበሉ፣ የሚጠጡ፣ ተዋልደው የሚኖሩ፤ የዚህ ዓለም ግልባጭ ሕይወት በነሱም እንዳለ፤ የራሳቸው ግዛት፣ ቦታና ሥልጣን እንዳላቸው ይታሰባል፡፡ በቆሻሻ፣ በብስባሽ፣ "በጥንብ" [በሞቱ እንስሳት አካላይ ሰፍረው የሚገኙ] እና በመሬት ግዛትና ቦታ ላይ "ወረው" የሚኖሩ፤ ሥልጣንና ኃይል ያላቸው "የመሬት ጋኔል" በመባል

ይጠራሉ (መሪጌታ ባሕረጥበብ እና መሪጌታ በረከት፤ ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ፤ 12/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

እነዚህ አጋንንት "ልቡሳነ ሥጋ" የነበሩ፤ እንደሰው ሰርተው፣ ለፍተው፣ ምግብ በልተው እንደሚኖሩ፤ ከሥራ ተመልሰው በእኩለ ቀንና ሌሊት (ከአምስት እስከ ዘጠኝ ሠዓት ባለው ጊዜ) ቤታቸው ገብተው ቡና አፍልተውና ጠጥተው እንደሚተኙ፤ በማኅበረሰቡ ይነገራል (ከተቡው አባላት መካከል ብላታ ጓዴ እና ቄስ ዐቢይ ያቀረቡት ሃሳብ፤ ቃ.መ፤ 19/06/ 2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት)። አጋንንት ይኖሩበታል በሚባል ቦታ መንቀሳቀስ "ያስለክፋል፣ በጋኔል ያስመታል"፤ ይባላል። ጋኔል፤ "ፈጣን፣ ቁጡና አደገኛ" ስለሆነ በቁም ይጥላል፣ "አናት" (እራስ) ያዞራል፣ ሆድ ይነፋል፣ ተቅማጥ ይለቃል፣ ብርድ ብርድ ይላል፣ በመላው የሰውነት "ጅስም" [በመላ ሰውነት ይሰራጫሉ] ይበተናል፤ ይሰራጫል፤ ተብሎ ይታሰባል (ከተቡው አባላት መካከል መሪጌታ ስንታየሁ እና መሪጌታ ስዩም ያቀረቡት ሃሳብ፤ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ እብናት)። በተለይ የመቃብር ቦታ ጠባቂው ጋኔል "ሞርሞሪዎን" በእኩለ ቀንና ሌሊት የመቃብር ቦታ የረገጡ ሰዎች በዚህ ጋኔል እንደሚመቱ፤ "የአካል ቁስለት ያለባቸው" እና ነፍሰጡር እናቶች በአካባቢው ቢደርሱ ቁስሉ ይብሳል፤ ነፍሰጡር እናቶችን "ይጣላል" [ለሕመም ይዳርጋል] ተብሎ ይፈራል (መሪጌታ ስንታየሁ፤ ቃ፣መ፤ 14/04/2011 ሊቦ ከምከም)።

ከማኅበረሰቡ አባላት፤ መቃብር፣ ሰርግ፣ ገበያ ቦታ… ደርሶ የተመለሰ፤ "ፀሐይ ላይ ቆይቶ" የመጣ ሰው፤ "ሕመምተኛ አይጠይቅም፤ ለታማሚው 'ጥላ' ይሆናል" [ሕመሙን ይቀሰቅሣል፤ እንዲባባስ ወይም እንዲያገረሽ ያደርገዋል] ተብሎ የታመናል። በርቀት ቆመው፤ ወደ ቤት ሳይገቡ ሰላምታ አቅርበው፤ "ምሕረት ይላክልህ!" ብለው፤ ከማለፍ ውጪ በአካል ቀርበው፣ በእጅ ዳብሰው ሕመምተኛን አይጠይቁም፤ ይባላል (ከተቡው አባላት መካከል እማሆይ እና ወ/ሮ የዛብ ወንዴ የገለጹት ሃሳብ፤ ቃ.መ፤19/06/2011 ፋርጣ)። ለምን?፤ በመቃብር ቦታ፣ በገበያና በፀሐይ አካባቢ ውለው የሚመጡ ግለሰቦች፤ ዶሮና እንስሳት በተለያየ የሰውነት አካላቸው አጋንንት (አባራና ቆሻሻ) ይዘውና ተሸክመው እንደሚመጡ ይገመታል። ይህ ተግባር ለሕመም መባባስና ማገርሸት ምክንያት እንደሚሆን፤ ከረጅም የሕይወት ተመክሮ፣ ፍልስፍና፣ እሳቤና ተግባር እንደተማሩት፤ የታካሚን ጤና መጠበቂያ ሥርዓት እንደገነቡ፤ መገንዘብ ተችሏል።

በተመሳሳይ መልኩ ደብተራ ጥላሁን፤ የባሕር ዓለም አስተዳዳሪ፣ ገዥና ባለስልጣን "ጂን" ነው፤ ይላሉ። "ጅን፣ ቆሌና ዛር" እንደሰው ተጋብተውና ተዋልደው የሚኖሩ "ልቡሳነ ሥጋ" [ሥጋ የለበሰ አካል] እንደነበሩ፤ ጠቁመው። "ጅን" እንደሰው ደምግባት ያላቸው ቆንጆና ጥቁር መልክ

ይዘው የተፈጠሩ የሰው አምሳል እንደሆኑ ይነገራል። በእኩለ ቀንና ሌሊት፣ ጀበና ጥደው፣ ስኒ ደርድረው፣ ገበታ ዘርግተው፣ እየበሉና እየጠጡ ማዕዳቸውን የረገጠ፣ ቡናቸውን ያፈሰሰ፣ ስኒያቸውን የሰበረ፣ የዕጣን ማጨሻቸውን የደፋ፣ ሰውም ሆነ እንስሳት፣... "ደሙን አፍሰው፣ አካሉን አስረው፣ ባሕር ጎትተው፣... ደሙን መጠው ስጋውን ይጥላሉ"፣ ተብሎ ይተረካል (ደብተራ ጥላሁን፣ቃ.መ፣ 23/01/2011 ሊቦ ከምከም)። የወንዝ (የባሕር) እና የመሬት ጋኔል "ካልደረሱባቸው አይነኩም" ይባላል። ወራጅ ወንዝ ለምን ይፈራል? በየቦታው የወደቁና የሞቱ እንስሳትን ተሸክሞ ከመሄዱም በተጨማሪ፣ ውኃ ወለድ በሽታዎችን በማስተላለፍ ለአካላዊ ቁስለትና ለውስጥ ሕመም፣ ለተቅማጥና ለወረርሽኝ በሽታ መንስኤ እንደሆኑ ጠቁመዋል (የተቡው አባላት፣ ቃ.መ፣ 26/06/2011 ቡድን ሁለት)።

ከዚህ በላይ የቀረቡ የመስክ መረጃዎች እንደገለጹት፣ የሰው ልጅ በእኩለ ቀን (ከ5-9 ሠዓት) ቆሻሻና አመድ በሚጣልበት፣ የጠላ አተላ፣ የጠጅ አንቡላ እና የአረቂ ብሪንጥ በሚደፋበትና በሚፈስበት ቦታ ማለፍ፣ መገኘት፣ መቀመጥ እና በወንዝ ዳርቻ መንቀሳቀስ በ"ጅን" እና በመሬት "ጋኔል" ያስመታል/ ያስለክፋል፣ ተብሎ ይፈራል። ቆሻሻን፣ መኖሪያና መከለያ አድርገው በሚኖሩ፣ በሞተ አካል ላይ በሰፈሩ የምድር አጋንንት ያስመታል፣ ለሕመም ይዳርጋል፣ ለዐየር ጋኔል ያጋልጣል፣ ተብሎ በማኅበረሰቡ ይፈራል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደመቀ፣ቃ.መ፣ 19/06/2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት)።

ማኅበረሰቡም በዚህ ሠዓት ከአመድ መድፊያ፣ ከቤት ጥራጊ ቆሻሻ መጣያ፣ ከአተላ ማፍሰሻ፣ ከሰው "ግብረ" ውኃና ዓይነ ምድር መውጫ፣ ከሞቱ (አህያ፣ ፈረስ...) እንስሳት መጣያ፣ ከብስባሽ (የከብት እበት፣ የፍየልና በግ ፍግ፣ የፈረሰና ባዶ ቤት) መገኛ አካባቢና ቦታዎች ከመሄድ ይቆጠባሉ። አካባቢያቸውን ከበሽታ መጠበቅ፣ ቆሻሻ መጣያ ተብለው በተለዩ ቦታዎች በእኩለ ቀን አለመገኘትን፣ ይመክራሉ። ለምን? ሲባል "አጋንንት ሲለፈልፉ"፣ የለከፉበትን ቀን፣ ሠዓት፣ ቦታና ጊዜ፣ ዘራቸውን፣ ዓይነታቸውን፣ መገኛ ቦታቸውን፣ ስማቸውን፣ ምስና ግብራቸውን፣ ሲናገሩ ቦታውን መለየት እንደሚቻል፣ የባህል ሐኪሞች ይገልጻሉ (ከተቡው አባላት መካከል ቄስ አብርሃም እና መሪጌታ ስንታየሁ የሰጡት ሃሳብ፣ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)። የአካባቢው ማኅበረሰብም አቅም በፈቀደ መልኩ በዚህ አካባቢ ማለፍ ወይም መቆየት ግድ ቢሆንበት፣ የፀሐይ ጮራ ከመውጣቱ በፊት ጉድጓድ ተቆፍሮ ቦታው ዐፈር እንዲለብስና እንዲቀበር፣ ይደረጋል። ይህ ተግባር ከማኅበረሰብ ጤና አንጻር እንዴት ይታያል? ለሚለው ጥያቄ ዶ/ር አስናቀ እንደሚከተለው አስረድተዋል፡-

በዘመናዊ ሕክምና የሕመም መንስኤ፤ ባክቴሪያ፣ ቫይረስ፣ ፈንገስ፣ ጥገኛ ትላትል መሆናቸውን በዋናነት፤ ጠቁመው፤ መተላለፊያ መንገዳቸው በትንፋሽ፣ በተበከለ ውኃ እና ምግብ፣ ንጽህናው ባልተጠበቀ መኖሪያ ቤትና ሽንት ቤት፣ በባክቴሪያና በፈንገስ የሚከሰቱ የሰውነት ቁስለትን፤... ይመለከታል። ቆሻሻ የሚጣልበት (የቡና፣ የአረቄ፣ የጠጅና ጠላ አተላ የሚደፋበት) ማንኛውም አካባቢ፤ ለፀሐይ ሙቀት ተጋላጭ ሲሆን፤ ከፍተኛ የሆነ የመብላላት ወይም "የፈርሜንቴሽን ፕሮሰስ" ሥርዓት ይካሄዳል፤ በሙቀትና በንፋስ እየታገዙ ባክቴሪያዎች (ታይፎይድ፣ የአንጀት ተስቦ፣ ቲቢ፣ ትኩሳት፣ ኮሌራ...) አካባቢያቸውን በመበከል፤ በየቦታው ሲሰራጩ ለታይፎይድ፣ ለምግብና መጠጥ መመረዝ ምክንያት እንደሚሆኑ አስረድተዋል (ዶ/ር አስናቀ፤ ደብረ ታቦር፤ ቃ.መ፤ 18/04/2011 ፋርጣ) ።

ከዚህ አንጻር የማኅበረሰቡ እና የባህል ሐኪሞች ባህላዊ ዕውቀትና ልማድ፣ እምነትና ተግባር፣ ልምድና ሥርዓት፣ እለታዊ እንቅስቃሴዎች፣ ማኅበራዊ መስተጋብር፣ የዘመንና የሕይወት ተመክሮ መነሻ በማድረግ፤ የሰው ልጅ በእኩለ ቀን በቆሻሻ ቦታ፣ በወንዝ ዳርቻ፣ በአድባር እና በመቃብር ቦታዎች መንሳቀስ ለሕመም መንስኤ፤ ለሞት ምክንያት እንደሚሆን በማኅበረሰቡ ልማድ ተለይቷል። በአንጻሩ የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎችም በማንኛውም ሠዓት ወይም እኩለ ቀን በቆሻሻ ቦታ መገኘት፣ መንቀሳቀስ ወይም በአቅራቢያ መኖር፤ ለሕመምና ለሞት መነሻ መሆኑን ጠቁመዋል። በማኅበረሰቡ እሳቤ ቆሻሻ ቦታና ወራጅ ወንዝ የአጋንንት መገኛ ተደርገው ይታሰባሉ፤ አጋንንት ረቂቅ፣ በቆሻሻ ቦታ የሚኖሩ፤ በእኩለ ቀን ሰውና እንስሳት እንደሚለክፉ፤ ተጠቁሟል። በዘመናዊ ሕክምናም ቢሆን በዓይን በማይታዩ "ረቂቅ ተሕዋሲያን" [ባክቴሪያ፣ ቫይረስ፣ ፈንገስ፤] አማይኝነት፤ በዐየር እየተገፉ፣ በሙቀት እየተነሱ፣ በልብስ፣ በእግርና በእንስሳት ንክኪ እየተዛመቱ፣ በመመገቢያ እቃዎች እና መሰል ቦታ በመባዛትና በመራባት [ይስት ወይም ሸጋታን ልብ ይሏል]፤ ለሕመም እንደሚዳርጉ ተጠቁሟል። በሁለቱም ዘርፎች ያለው አተያይ፣ እሳቤና ተግባር ተቀራራቢ ቢሆንም መሰረታቸው፣ እድገትና ምንጫቸው፣ የባህልና የሣይንስ እሳቤ እና ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ግቡና ተግባሩ ተዛማጅ መሆኑን ልብ ይሏል።

### 5.4.4 በደም፣ ምግብና መጠጥ የሚነሱ አጋንንት

በደቡብ ጎንደር ማኅበረሰብ እምነትና እሳቤ፤ ደም የአካል እና የነፍስ ድልድይ፣ የድሕነትና የምህረት መንገድ፣ የዕርቅ ማፅኛ እና የፈውስ ምክንያት በመሆን ይቀርባል። በሌላ በኩል ደግሞ የመርገምት ተምሳሌት (የሄዋን የወር አበባ)፣ የአጋንንት ማረፊያ፣ የሕመም መነሻ እና የሞት ምክንያት ተደርጎ ይቆጠራል። "ከእንስሳት እርድ የሚፈስ ደም አይቀመስም/አይጠጣም" ይባላል፤

ለምን? ሲባል "ሕይወት አለው" ተብሎ (አቶ ታከለ፣ቃ.መ፤04/03/2011 ሊቦ ከምከም) ይታመናል፡፡ ለምሳሌ፡- "ደንቃራ ጣለብኝ፤ ደንቃራ ገባሁ፣ ቡዳ በደም ይገባል፤... ደም ስታዩ ዐፈር አልብሳቸው እለፉ፤ በሰው ፊት ምግብና ወተት ለልጆች አትስጡ፤... እንዳይጣላቸው" (ከተቡው አባላት 19/06/2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት) ይባላል፡፡

እንደ ደብተራ መኀሪ መረጃ፤ ደም የአካልና የነፍስ መጋጠሚያ፣ የሕይወት ድልድይ፣ የምህረት መንገድ፣ የዕርቅ ማፅኛ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ከሃይማኖታዊ እሳቤ፤ አካላዊ ሥጋን ከሚያስገኙ ባሕርያት ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃ እና መሬት የተሰራ የሕይወት መሰረት፣ የእስትንፋስ አካል ተደርጎ ይታመናል፡፡ ሰው ተጣልቶ ደም ቢፈስ፣ ሕይወት ቢጠፋ ማስታረቂያ፣ ማስማሚያ፣ ማግባቢያና የዕርቅ ማፅኛ፣ መገዘቻ ስልትና መንገድ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ "የሽማግሌ ቃልና ግዝት ባፈርስ.. ደሜ ይፍሰስ፤... ብከዳ፤ የቆምኩበት መሬት ይክዳኝ!..." እየተባለ መሃላ ይደረጋል (ቄስ ማስረሻ፣ ቃ.መ፤21/06/2011)፡፡

በጠና ታሞ በአልጋ የዋለን ሰው ከሕመም ለመፈወስ፣ ስቃዩን ለመቀነስ በሽታውን ወደ ሌላ አካል ለማስተላለፍ፤ "መጸሐፍ ተገልጦ"፣ ኮከብ ይቆጠራል፤ በተቆጠረውና በተጠቀመው ኮከብ መሰረት እየታገዙ (እየተመሩ)፤ የዶሮ፣ የበግ፣ የፍየል መልክ፣ ዓይነት፣ መጠን፣ የጭዳ ልክና ሥርዓት ይነገራል/ይዘጋጃል (መሪጌታ አማረ፣ ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ ለዓብነት ያህል፡- ታሞ በአልጋ ለከረመና ለዋለ ሰው፤ ቡና ተፈልቶ፣ ቆሎ፣ ቂጣ፣... ተዘጋጅቶ፤ የታማሚው ሰው ኮከብ፣ ዘመን፣ ወር እና ባሕርይ ተለይቶ ሥርዓቱ ይጀመራል፡፡ "ነጭ የዶሮ ጫጩት ገዝተህ በራስህ ላይ ሶስት ጊዜ አዙረህ ጣል"፤ ለኮከቡ ባሕርይ የሚመጥን ድግምት እየተነበበና እየተደገመ የተመረጠችው ጫጩት በእጅ ተይዛ በታማሚው ሰውነት ላይ ሶስት ጊዜ በማዞርና በማሽከርከር በግቢ ውስጥ መልቀቅን ይመለከታል፡፡ በግቢ የተለቀቀችው ጫጩት ወዲያው ከሞተች በሽታው ለቆ እንደሄደ፤ ይታሰባል፡፡ እያደገች ከሄደች እና ሕመምተኛው ከዳነ የታማሚው ሰው ኮከብ ማረፊያ፣ "ከአጋንንት ጠባቂና ገድ ተደርጋ ትቆጠራለች"፤ መሸጥ፣ መለወጥና ማረድ እንደማይቻል ገልጸዋል (አቶ ደሴ፣ቃ.መ፤ 25/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የደም መስዋዕት ወይም ጭዳ የሚጠይቁ የአጋንንት ዓይነቶች እንዳሉ ይነገራል፡፡ እንደ አቶ ደሴ ገለጻ፤ የታማሚው ሰው ኮከብ ሲቆጠር፤ ሥሙ፣ የእናቱ ስም፣ የታመመበት ወር እና ዘመኑ ተለይቶ በሰባት ይገደፋል (ይቆጠራል)፡፡ የታማሚው ኮከብ

ተቆጥሮና ተለይቶ ቀሪው አምስት ቢሆን በዕለተ ሐሙስ[59] የተጻፈው ይዘት ተግባራዊ፤ ይደረጋል (አቶ ደሴ፣ቃ.መ፤ 25/01/2011 ሊቦ ከምከም)። ለዓብነት ያህል፦

> ሐሙስ ቀን አባ መጋል የሚባል የመቃብር ጋኔል ራሱን በጭራ መትቶት ለክፎታል። በሕልሙም አስደንግጦታል፤ ሐሙስ ወደ ማታ ነው የጀመረው፤ ራሱን ጫንቃውን ልቡን ግራ ቀኝ ጎኑን ይወጋዋል። እስከ አስራ ሁለት ቀን በጸና ይታመማል። ይህን ካለፈ ግን ሞት የለበትም። እራሱን እያዞረ ያቃጀዋል፤ መድኃኒቱ በኮከቡ እንደተጻፈው፤ ነጭ ዶሮ፣ የቀይ ዳልቻ በግ ይረድ፤ ጥቁር ነጠላ ዶሮ አዙሮ አርዶ ይጣል።

በማለት ለዕርድና ለመስዋዕት የሚቀርቡ የዶሮ፣ የፍየል፣ የበግ ዓይነቶች ተለይተው እንደሚቀርቡ ገልጸዋል። በኮከቡ ልክና ይዘት የተመረጡ፣ ለመስዋዕት የሚቀርቡ ግብዓቶች፤ አንድም የሕመም "መሻሪያ"(መዳኛ)፣ መከላከያ፣ ማሸጋገሪያ፣ መጠበቂያ፣ የመንፈስ ማደሪያ፣ ጠባቂ እና ተከላካይ ተደርገው ይቆጠራሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተቆጠረው ኮከብ ልክ እና መጠን ሥርዓቱ ባይፈጸም የተጠቀሱት አጋንንት ደም ሳይቀምሱና ሳይልሱ፤ ምስና ግብራቸው ቢቀር "ሕመሙ ይፀናል፣ ታማሚው ይሞታል"፤ ተብሎ ይፈራል (መሪጌታ ፋንታሁን፣ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ)። የደም መስዋዕት ለሕመም እንደ ፈውስ፣ ለአጋንንት እንደቀለብ፣ መቃመሻ፣ ማረፊያ፣ መኖሪያ፣ መገኛ ቦታ፤ በሌላ ይዘት ደግሞ ደም፤ ግብራቸው፣ ምሳቸው፣ መታረቂያ መንገዳቸው፣ የኃይል ምንጫቸው ተደርጎ፤ ይታመናል (ሊቀጠበብት አብርሃም፣ ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ማኅበረሰብ እምነትና እሳቤ "ደም" የመለከፊያ ምክንያት ተደርጎ ይታሰባል። የደንቃራ ሕመም፤ "በእግር ገብቶ ሙሉ ሰውነትን ይቆረጥማል፣ እግር ይሸመቅቃል፤..." ተብሎ ይነገራል (ደብተራ መልኩ፤ቃ.መ፤23/01/2011 ፋርጣ)። አንድ ሰው ለእምነታዊ ሥርዓት፤ እርድ እና መስዋዕት ሲያቀርብ "ልጅና ከብቶቻችሁን ያዙ ደንቃራ እንዳይገቡ" በማለት ለወዳጅ ዘመዱና ጎረቤት እንደሚያሳውቅ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ደንቃራ መጣሉን ሳይናገር ሰው ገብቶ ሲወጣ የቤቱን በሽታ ይዞት ይሄዳል ተብሎ ስለሚታመን በምስጢር እንደሚያዝ ጠቁመው፤ በተለይ በጥር፣ በግንቦትና በሰኔ ወር ደንቃራ መግባት ለከፋ ሕመምና ስቃይ ይዳርጋል ተብሎ ይታሰባል (ወ/ሮ ዉዲቱ፣ ቃ.መ፤03/07/2011 ሊቦ ከምከም)። ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ ደም፤ መለከፍያ

---

[59]በሥነ ፍጥረት የሣምንት ቀናት ቁጥር ከእሁድ ዕለት ይጀምራል። እሁድ አንድ፣ ሰኞ ሁለት… ቅዳሜ ሰባት ተብሎ ይቆጠራል። የሳምንቱ መጀመሪያ ዕለት እሁድ ሲሆን መጠናቀቂያው ደግሞ ቅዳሜ እንደሆነ ይታሰባል (ሠናይ፣2009)። በኮከብ ቆጠራ ሂደትና ቀመር እሁድ አንድ ተብሎ ይቆጠራል።

መንገድ፣ ለሕመም መነሻ፣ ለአጋንንት ማረፊያ፣ መኖሪያ፣ ማቋደሻ ሆኖ ሲቀርብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የደም መስዋዕት፤ ለምህረት፣ ለፈውስና ለጤና ተብሎ ተግባራዊ ይደረጋል።

ምግብና መጠጥ በአግባቡ ካልተያዙ፤ በማንኛውም ቦታ ቢበሉና ቢጠጡ በአጋንንት ያስመታሉ፤ ለምች ያጋልጣሉ፣ ለክፉ ዓይን (ለቡዳ) ይዳርጋሉ፣ ለሕመም መንስኤ ይሆናሉ፤ ተብሎ ይፈራል (ቄስ አብርሃም፣ቃ.መ፤01/05/2011 እብናት)። ለምን? ሲባል ከተፈጥሯዊ ባሕርያቸው ተለይተው ሲገኙ ኃይልና ተግባራቸውን በመሳት፤ ገቢራቸውን በመዘንጋት የአጋንንት ማደሪያ ይሆናሉ፤ ተብሎ ይታሰባል። እንደ ቄስ አብርሃም መረጃ፤ የቡዳ አጋንንት ዋና መነሻ ቦታና ምንጫቸው፣ ደም፣ ምግብና መጠጥ፤ መሆኑን ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 01/05/2011)። ዋልተንጉስ (2007፤ገፅ.182-183) ደግሞ፤ ተፈጥሯዊ ባሕርያቸውን ጨርሰው፣ ኃይላቸውን አሟጠው የሚገኙ ምጣጭ፣ ዝቃጭ፣ እንጥፍጣፊ፣ ቅራሪና ውዳቂ የሆኑ የአመድና አተላ ወገን የክፉ ዓይን ማደሪያና ማረፊያ ተደርገው እንደሚቆጠሩ ገልጸዋል።

በሰው ፊትና በማንኛውም ቦታ የማይበሉና የማይጠጡ፤ ለሕመም አጋላጭ ከሚባሉ ዐውድና ምክንያቶች መካከል ከምግብ (አትክልትና ፍራፍሬ፤ ቅባትና ሥጋ ነክ ይዘት ያላቸው)፤ ከመጠጥ (ወተት እና በቀላሉ የሚበላሹ ጣፋጭ ጣዕም ያላቸው) በዋናነት ይጠቀሳሉ። "በእንግዳ ፊት ለልጆች ምግብና ወተት አትስጡ፤..." ይባላል (ወ/ሮ ዳሳሽ፣ቃ.መ፤ 03/07/2011 ሊቦ ከምከም)፤ በክፉ ዓይን (ቡዳ) ይበላሉ፣ ይለከፋሉ ተብሎ ይፈራል። ለሕመም አጋላጭ፣ አስጠቂ፣ መነሻ የሚባሉ ምግብና መጠጦች በአጭር ጊዜ ውስጥ ይዘታቸውን፣ ባሕርያቸውን፣ ጣዕምና ቃናቸውን በመለወጥ ለሕመም መንስኤ እንደሚሆኑ የሕክምና ባለሙያዎች ይመክራሉ (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ጋሻውና አቶ መንገሻ ያቀረቡት ሃሳብ፣ ቃ.መ፤26/06/2011 እብናት ቡድን ሁለት)።

Dundes (1980; P.129) በአፍሪካና በኢሲያ አገሮች፤ አንድ ሕጻን ወተት ጠጥቶ፣ ፍራፍሬ በልቶ ቢታመም የወተቱና የፍራፍሬው ባሕርይና ይዘት ሳይሆን የክፉ ዓይን መንፈስ (ቡዳ) እንዳረፈበት ይታሰባል። በቤተሰብ እንክብካቤ፣ ጥንቃቄ፣ ጉድለትና ዕውቀት ምክንያት ሕጻን ምግብ በልቶ ታሞ ቢሞት፤ ቡዳ በልቶት ወይም ክፉ ዓይን ወግቶት አጣድፎ እንደገደለው ይታመናል። በቤተሰብ እንክብካቤ፣ ጥንቃቄ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማነስ ሕጻን ልጅ ታሞ ሞተ ቢባል፤ ለቤተሰቡ ትልቅ ውርደት፣ ሽንፈትና ጥቃት ተደርጎ እንደሚቆጠር ጠቁመዋል። ይህ እሳቤ ችግርን እና ክፍተትን በሌላ አካልና ወገን ላይ የማሳበብና የማሽጋገር ተግባር (Projective Function) ቢኖረውም፤ ለልጆች ምግብና መጠጥ ሲሰጥ በወላጆቻቸው ልዩ ክትትል፣ ቁጥጥር፣ ትኩረትና ድጋፍ እንዲያገኙ ምክንያት በመሆን፤ የክፉ ዓይን ጥበቃ ስልትና ቴክኒክ ምግብ

እንዳይበከል፤ ማኅበራዊ ተቀባይነት እንዲኖር፣ ሥነ ልቡናዊ ድጋፍና ጥንካሬ (Psychological Supports) ለማግኘት አስተዋፅኦ እንዳለው፤ መክረዋል።

በአጠቃላይ ከይዘት 5.4.1 እስከ 5.4.4 የቀረቡ የመስክ መረጃዎች ጠቅለል በአለ መልኩ ሲታዩ፤ የዐየር ጋኔል ለአዕምሮ መሰወር፣ ለዓይን መጥፋት እና ለፀሐይ ጨረር "ዉጋት" በመዳረግ፤ የመሬት ጋኔል የፊት አካልን በማጣመም እና ለብርድ ሕመም መንስኤ በመሆን፤ የዛር አጋንንት አዕምሮን እና መራቢያ አካልን ማድከምና ሥርዓት ማዛባት፤ የቡዳ መንፈስ፤ በደም፣ በምግብ፣ በመጠጥ ምክንያት በደም ሥር በመዘዋወር ሰውነትን በማንቀጥቀጥና በማዛል አቋምን ማሳት፤ የጅን መንፈስ ደግሞ በወንዝ አካባቢና ዉኃ ላይ ሰፍረው ለዉኃ ልክፍት፣ ለአካላዊ ቁስልና ለሆድ ሕመም በመዳረግ ጉዳት እንደሚያደርሱ ይታሰባል። ከዚህ አንጻር፤ የሕመም መንስኤ የሚባሉ "የአጋንንት ዓይነቶች" የትኛውን የሰውነት አካልና ክፍል በዋናነት እንደሚያጠቁ በሚከተለው ምስለ መዋቅር፤ ተጠቁሟል።

ምስል 10፡- የሕመም መንስኤ የሚባሉ አጋንንት በዋናነት የሚያጠቁት የሰውነት አካል ክፍል




ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች፤ በጥናት አቅራቢው ተዘጋጅቶ የቀረበ ምስለ መዋቅር፤ የሰውነት አካላዊ መዋቅር www.http;//thumbs.human-Body-System-chart-52821831.jpg የተወሰደ።

በዚህ ይዘት ዐበይት የሕመም መንስኤ ተብለው የተጠቀሱ አጋንንት በዋናነት የሚያጠቁት የሰውነት አካል የተጠቆመ ቢሆንም፤ አንዱ ሕመም ለሌላው መንስኤ በመሆን ትስስር እንዳላቸው፤ በባህል ሕክምና ባለሙያዎች ይታመናል (መሪጌታ ባሕረጥበብ እና ቄስ አብርሃም፣ ቃ.መ፤ 27/02/ 2011 ፋርጣ፤ 01/05/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡

### 5.4.5 የዓመትና ወቅት ዑደትን ጠብቀው የሚከሰቱ አጋንንት

በባህል ሕክምና ልማድ፤ ዓመትና ዘመን ጠብቀው፤ ወቅትና ወራት ለይተው፤ የሳምንት፣ የቀንና የሠዓት ዐውድን መነሻ አድርገው፤ የዓመትና የወቅቶች ዑደትን ተከትለው የሚከሰቱ የጤና እክሎች፤ ለበሽታ መለያየት፣ መመሳሰል ወይም መደጋገም ምክንያት እንደሆኑ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ይመክራሉ (ከተቡው አባላት፣ቃ.መ፤ 23/06/2011 ቡድን አንድ)፡፡

በዓመት ውስጥ የወቅቶች መፈራረቅና ሂደት፤ ለሕመም መነሳትና መክሰም አስተዋጽኦ እንዳለው፤ የዓመቱ (አሥራ ሁለቱም) ወራት በጠባቂ መላእክት እና ቀሳፊ አጋንንት ባሕርይ እንደተመደቡ፤ የወራት ባሕርይ ለአጋንንት መነሳት፣ መስፋፋት፣ መጠንከርና መክሰም ምክንያት እንደሆኑ፤ "ፀደይ የነፋስ፣ በጋ የእሳት፣ መኸር የውኃ፣ ክረምት የመሬት" ባሕርይ ተምሳሌት ተደርገው እንደሚታሰቡ ጠቁመዋል (መሪጌታ አዲሱ፣ቃ.መ፤19/01/2011 ፋርጣ)፡፡

በፀደይ (መስከረም፣ ጥቅምትና ኅዳር) ወቅት፤ አዲስ ዓመት ገባ "መስከረም ጠባ" ይባላል፡፡ በዚህ ወቅት ወንዞች ሞልተው ይፈሳሉ፤ ዕፅዋት አብበው ያፈራሉ፤ እንስሳት በልተው ይጠግባሉ፤ ይህ "የፀጋና የፍስሃ ወቅት" አልፎ በጋ (ታህሳስ፣ ጥርና የካቲት) ሲገባ ዕፅዋት ጠውልገው፣ ቅጠላቸው ረግፎ፣ ፍሬያቸው ወድቆ ይታያል፡፡ ውልደታቸው በክረምት ሞታቸው ደግሞ በበጋ ይሆናል፡፡ እንስሳትም ይጠማሉ፣ ይራባሉ፣ ይደክማሉ፤ አካባቢው ይደርቃል፣ ይሞቃል፣ የነበረው ሥርዓት ይዛባል፤ በዚህ ወቅት በሽታ ይከሰታል[60] ተብሎ ይፈራል (ደብተራ መኀሪ፣

[60] የበጋው (የእሳቱ) ዘመን አልፎ መኸር (መጋቢት፣ ሚያዚያ ግንቦት) ሲገባ መሬቱ ይጠብቃል፣ ይረጋል፣ "የበልግ ዝናብ" ይከሰታል፤ ቅጠላቸውን ያረገፉ ዕፅዋት ማቆጥቆጥ፣ መለምለም ይጀምራሉ፤ እንስሳት ቅጠል ይቀነጥባሉ፣ ሣር ይግጣሉ፤ መሬት መብረድ፣ መስከን ትጀምራለች ይባላል (የዉኃ ባሕርይ)፡፡ በዚህ ወቅት ዝናብ ሲጥል፣ ጎርፍ ሲወርድ፣ ሽታ ሲነሳ አካባቢ ይበከላል፡፡ የሚበላውና የሚጠጣው በጥንቃቄ ካልተያዘ ለበሽታ (ከተቡው አባላት፤ቃ.መ፤ 26/06/2011 እብናት ቡድን ሁለት) ይዳርጋል፡፡ የመኸር ወቅት አልፎ ክረምት (ሰኔ፣ ሐምሌና ነሐሴ) ሲገባ ውልደቱን በመስከረም ያደረገ ወቅት ሞቱ በክረምት ይሆናል (የመሬት ባሕርይ)፡፡ ክረምት "የጨለማና የሞት" ተምሳሌት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በዚህ ወቅት መሬት "አፏን ከፍታ፤ መሰረቷን ትስታለች፣ ትናጣለች" በሂደት በየቦታው በጎርፍና ዝናብ ትመታለች፣ በረዶ እና መብረቅ ሲወርድባት፤ የፀናው መሰረት ይፈርሳል፣ የቆመው ይወድቃል፤ በከፍተኛ ውጥረት፣ ጭንቀት፣ ግጭትና ግፊት ውስጥ ስትገባ፤ "በውስጧ ያረገዘችውን ሕይወት ትተፋለች" ይባላል (መሪጌታ ፍሬስብሃት እና መሪጌታ ሠረቀብርሃን፣ቃ.መ፤07/03/2011 ሊቦ ከምከም፤ 12/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡

ቃ.መ፤13/03/2011 እብናት)፡፡ በተለይ ከዓመቱ ወራት መካከል ኅዳር፣ ጥር፣ ግንቦት እና ሰኔ አጋንንት ይበረታሉ፣ ኃይልና ጉልበት ያገኛሉ፤ ተብሎ ይነገራል፡፡ ለምን? ሲባል የወቅት መለወጫና መጀመሪያ ወራት መሆናቸውን ታላሚ ያደርጋል፡፡ በነዚህ ወቅት/ወራት የበሽታ ወረርሽኝ ይከሰታል፣ ይነሳል፣ ይሰራጫል (እከክ፣ ተቅማጥ፣ ኩፍኝ ዓለሞቼ)፤ የዐየር ንብረት ለውጥ ይካሄዳል፣ የወቅቶች መፈራረቅ ይከሰታል፡፡ የተመረጡ ወቅትና ወራት በማኅበረሰቡ ለምን ይፈራሉ? ለአብነት ያህል፤ የአዝርዕት አበቃቀልና አከሳሰም ባሕርይ፡-

አዝርዕት በክረምት በቅለውና አድገው፣ በመስከረም ጠንክረውና አብበው፤ በጥቅምት አሽተውና አፍርተው፤ በኅዳር ጠውልገው፣ ደርቀውና ከስመው ወደ መሬት አገዳቸውን አጎንብሰው፤ ፍሬያቸውን ማርገፍ፣ ዘራቸውን መርጨትና መበተን ይጀምራሉ፤ የአዝርዕት ውልደት በክረምት፤ ሞታቸው ደግሞ በኅዳር ይሆናል፡፡ ፀደይ አልፎ በጋ ሲተካ የአካባቢው ልምላሜ ይጠወልጋል፣ ይከስማል፣ ይደርቃል፣ ይረግፋል፡፡ በዚህ ወቅት የዐየር ንብረት መለወጥ ሲከሰት፤ የዕፅዋትና የአዝርዕት ግብዓቶች አበባ፣ አገዳ፣ ፍሬ ሲረግፍ ለአካባቢ ብክለት፣ ለበሽታ ወረርሽኝ መነሳት፣ መቀስቀስና መዛመት ምክንያት ይሆናል፡፡ አዝመራ ሰብስበው ከማሳ ሲያነሱ የእርሻ ማሳን የማቃጠል ልማድ፤ አካባቢን ማፅዳት፣ መመንጠር፣ ሰብስቦ ማቃጠል ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተለይ በእህል መሰብሰቢያ፣ "ቃርሚያ"ና መውቂያ ወቅት አጋንንት እንደሚበረቱ ይነገራል (መሪጌታ ስንታየሁ፣ቃ.መ፤ 14/03/211 እብናት)፡፡

የእህል አዝመራ "በአውድማ" ዙሪያ ሲሰበሰብ፣ ሲከመር፣ ሲወቃ፣ ምርትና ገለባው ከተለየ በኋላ የተጣራው "እህል በትኩሱ" ጎተራ አይገባም ይባላል፡፡ "እህሉ ይተንፍስ፣ የአውድማ ጠባቂ አድባራት ከአዲሱ ዘመን ምርት ይቅመሱ፣ ይቋደሱ"፤ ተብሎ ቂጣ፣ ኑግ፣ ቆሎ፣ ፈጦ፣ አረቄ፣ ቡና ተፈልቶ ይጠጣል፤ የቡና ቁርስ ይረጫል፡፡ የአውድማ ምርት ጧት በጧት ወይም ማታ ዐየሩ ሲበርድና ሲቀዘቅዝ ምርቱ ይነሳል፡፡ በሙቀት ሠዓት ብስባሽ ማንሳት፣ ምርት ማገላበጥ፣ ገለባ ላይ መተኛት፣ ከላይ መቀመጥ ምች ያስመታል፤ ለሕመም ይዳርጋል፤ (ከተቡው አባላት መካከል ግራጌታ ወንድማገኝ ያቀረቡት ሃሳብ፣ ቃ.መ፤19/06/2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት) ይባላል፡፡

በተለይ ዝናብ ጥሎ አድሮ በጓያ ክምር ላይ መቀመጥና መተኛት፣ ትኩሱን የጓያ ንፍሮ መብላት፣ ትኩስ የጓያ ዳቦ በወተት መብላት፣ ጓያ ተቀቅሎ በተደፋበት ቦታ መቆም፣ መቀመጥ፤ እንፋሎቱና የክምር ሽታው "እግር ይሰብራል/ይሸብባል፣ አካል ይሰነክላል" ተብሎ በጥብቅ ይፈራል፡፡ "ባርያ ከጣለው፤ ጓያ የሰነከለው" መዳኛ የለውም ይባላል (መሪጌታ ልሳነወርቅ፣ቃ.መ፤

27/04/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ "ባርያ ጣለው"[61] ሲባል፤ (የመሬት ጋኔል መታው ማለት ነው) በድንገት ወደቀ፣ ለጌዎን የሚባል በቆሻሻ ቦታ የሚኖር "ልክስክስ የጉድፋ ጋኔል" ደበደበው፣ በቁሙ ጣለው፣ ዓይኑን ሰወረው፣ ዳፍንት ሆነበት ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህ ሕመም በማኅበረሰቡ የሚፈራና ከባድ በሽታ ቢሆንም "ጓያ" የሰበረውና የሰነከለው ሰው መዳኛ መንገድ፣ መፍትሔና መድኃኒት እንደሌለው፤ በማኅበረሰቡ ይታመናል (መሪጌታ መንግስቱ፣ ቃ.መ፤ 11/04/2011 እብናት)፡፡ ለምን "አውድማ" ይፈራል?

አውድማ፤ እርጥብና ደረቅ ሰብል፣ ብስባሽና ሽጋታ የሚገኝበት፣ "የክምር እና ነዶ" ሙቀት፣ ከአካባቢው ዐየር ንብረት ተደማምረው፤ በዕኩለ ቀን ክምር ማፍረስ፣ ነዶ ማንሳት፤ በክምር ድርድር ላይ መቀመጥ፣ መተኛት፤ ለመጥፎ ጠረን፣ ሽታና ግማት መንስኤ ይሆናል፡፡ "ክምር ሲፈርስ የዳመና ግላጭ [ፀሐይ] ከመታ ከመቀመጫ አያስነሳም" ይባላል (አቶ ታከለ፣ ቃ.መ፤ 04/03/2011 ሊቦ ከምከም)፤ ሙቀት ያለው እንፋሎት ሲነሳ እና መጥፎ ጠረን ሲከሰት ለሕመም መንስኤ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡ በዚህ ወቅትና ወር በሽታ ስለሚከሰት አድባር፣ ጭዳ፣ ልመና፣ የበሽታ ሽኝት ሥርዓት እንደሚካሄድ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡

ወቅትና ዓመትን ጠብቀው (በተለይ ኅዳር፣ ጥር፣ ግንቦትና ሰኔ)፤ ከሚከሰቱ ወረርሽኝ በሽታዎች መካከል፤ የሆድ ሕመም፣ ተቅማጥ፣ እከክ፣፣ ኩፍኝ፣ የውኃ ወለድ በሽታዎች ይጠቀሳሉ፡፡ በተለይ የበሽታ ወረርሽኝ እንዲከሰት፣ እንዲባባስና እንዲዛመት ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል የፀበል ቦታዎች ተካተዋል፡፡ የፀበል ቦታዎች አካላዊ ሕመምን በመፈወስ፣ ሃይማኖታዊና ሕሊናዊ እርካታን ለማግኘት ፋይዳ ቢኖራቸውም፤ ለወረርሽኝ በሽታ መቀስቀስ ጉልህ ሚና እንዳላቸው የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡ ፀበልተኛው የሚኖርበትና የሚፀዳዳበት አካባቢ በዓይነ ምድር የተበከለ፤ ከሕሙማን የሚወጣ ማንኛውም ፈሳሽና ቆሻሻ፤ ዝናብ ሲጥል ከፍተኛ ሽታና ጠረን በማስነሳት፤ የአካባቢ ብክለት እንደሚከሰት ይመክራሉ፡፡ በየቦታዉ የተጣለ ቆሻሻ በጎርፍ እየተገፋ ከፀበል ዉኃ ጋር ተዳምሮ ፀበልተኛ ሲጠቀሙት ለሆድ ሕመም፣ ለተቅማጥ እና ለመተንፈሻ አካል ሕመም፤መነሳት፣ መቀስቀስ፣ መባባስ መንስኤ እንደሚሆን አስረድተዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደሳለኝ ቃ.መ፤ ቃ.መ፤ 26/06/2011 እብናት ቡድን ሁለት)፡፡ ጠቅለል ባለመልኩ የወቅት መለያየት፣ መፈራረቅ፣ የዐየር ንብረት መለዋወጥ፣ የዝናብና ጎርፍ መከሰት ለተለያዩ የሕመም ዓይነቶች መንስኤ እንደሚሆን መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ በባህል

[61] በዘመናዊ ሕክምና "ኤፒሌፕሲ" ወይም ዳፍንት ተብሎ ይጠራል፡፡

ሕክምና ዕውቀት የፀበል ቦታዎች የፈውስና የምህረት ቦታ ቢሆኑም፤ በዘመናዊ ሕክምና ደግሞ የሕመም መንስኤ ተደርገው ይታሰባሉ።

መኖሪያ አካባቢና መልክዓ ምድር[62]፤ ለበሽታ ሥርጭት እና ገደብ ምክንያት መሆኑን ምሁራን ጠቁመው፤ ከወቅቶች መፈራረቅ፣ ከዐየር ንብረት ለውጥ፣ ከመኖሪያ አካባቢ፣ ከሥነ ምህዳር ባሕርይ (መቀዝቀዝና መሞቅ)፣ ከአመጋገብ ልማድ፣ ከምግብ ግብዓትና ምርጫ…፤ ከቦታ ቦታ እንደሚለያይ (Trostle, 2005; PP.4-6: Winkelman, 2009; PP.250-252) ይመክራሉ። በአካባቢው ማኅበረሰብ ምርጫና እሳቤ "የደጋ ሰው እድሜው ረጅም ነው፤ በሽታ አይነካውም፤ ቶሎ አያረጅም፤ አቅሙ ቢደክምም ቁጭ ብሎ በመንፏቀቅና በመንደባለል... ይኖራል" ይባላል። በደጋ አካባቢ የተለያዩ በሽታዎች የማይከሰቱ መሆናቸውን በማሰብ፤ ለኑሮ ምቹ እንደሆነ ይነገራል። በአካባቢው ማኅበረሰብ ልማድ ባልና ሚስት ጎጆ ቀልሰው፣ ትዳር መስርተው ከቤት ሲወጡ እንደሚከተለው ይመረቃሉ (ቄስ ማስረሻ፣ቃ.መ፤21/06/2011ፋርጣ)፦

*ምግባችሁ ይሁን ሥጋ*

*መኖሪያችሁ ይሁን ደጋ*

*መኝታችሁ ይሁን አልጋ…*

ይባላል። በማኅበረሰቡ እሳቤ ሥጋ መብላትና ጮማ መቁረጥ በሐብት ይዘቱ የላቀ፣ በማኅበራዊ ደረጃው የተከበረ እና በኑሮው "የተሟላለት" ሰው፤ ሥጋ ቢበላ፣ ሙዳ ሥጋ ቢቆርጥ፣ ጠላና ጠጅ ቢያስቀዳ የተረፈውና የተመቸው ተደርጎ ይታሰባል። በዚህ ይዘትና አግባብ፤ አቅም ቢፈቅድ፣ ኑሮ ቢሟላ የምግብ ምርጫና ፍላጎት ከሥጋ ወገን እንዲሆን ይመከራል። ከምግብና መጠጡ በተጨማሪ ለመኖሪያ አካባቢ ደጋን ይመርጣሉ፤ የምርጫቸው ዐበይት ጉዳይ በተለያየ

---

[62]በባህል ሕክምና ልማድና አተገባበር መልክዓ ምድርን (ሥነ ምህዳርን) መነሻና መሰረት ያደረጉ የበሽታ ዓይነቶችን ምን ምን ናቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ባይገኝም፤ የሕክምና ዕውቀታቸው፣ ልማድና ተግባራቸው፣ የበሽታ መንስኤ እሳቤያቸው ተመሳሳይ፣ ተቀራራቢና ተወራራሽ ይዘት እንዳለው፤ የመስክ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በደጋ፣ በወይና ደጋና በቆላ አካባቢ የሚተገበሩ የባህል ሕክምና ልማዶች፣ አስተምህሮ፣ ሃይማኖትና አካባቢያዊ እሳቤዎች ፈርጃቸው ቢመሳሰልም፤ በዕፀ መድኃኒት ግብዓት ምርጫና አጠቃቀም ጉልህ ልዩነት ይታያል። የሥነ ምህዳር ዓይነት፣ የዐየር ንብረት ለውጥ እና የዕፅዋት ሥርጭት ልዩነት መኖሩን ታሳቢ ያደርጋል። የባህል ሐኪሞች በደጋ አካባቢ ውስን በሽታዎችን ጠቁመዋል፤ ከመተንፈሻ አካል አስም፣ የጉሮሮ ሕመም፣ ስንፈተ ወሲብ፣ ጉበት… ይጠቅሳሉ፤ በወይና ደጋ፤ ጉበት፣ ስንፈተ ወሲብ፣ ኩላሊት፣ አስም፣ ነቀርሳ፣…፤ በቆላ፤ ወባ፣ ኪንታሮት፣ የቆላ ቁስል፣ ጉበት፣ … ተጠቁመዋል። በመኖሪያ አካባቢና መልክዓ ምድርን (ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ቆላ) ታሳቢ በማድረግ ከዘመናዊና ከባህላዊ ሕክምና አስር ዋና ዋና አደገኛ እና ገዳይ በሽታዎች ዝርዝር የተሰበሰቡ ቢሆንም፤ በሁለቱም የሕክምና መስኮች መካከል ተመሳሳይ ይዘት አልተገኘም፤ በራሳቸው መስክ (ዘመናዊ-ከዘመናዊ)፤ በደጋ፣ በወይና ደጋ እና በቆላ ያላቸው መረጃ ተቀራራቢ ይዘት እንዳለው መገንዘብ ተችሏል።

በሽታ ሳይጠቁ፣ በሕመም ሳይሰቃዩ በሰላምና በጤና እርጅም እድሜ ለመኖር፤ ደጋማ ቦታ ተመራጭ መሆኑን ይጠቁማል። የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያ የሆኑት አቶ ዐባይ፤ የደጋ አካባቢ ዐየር ንብረት ቀዝቃዛ መሆኑ ለባክቴሪያ፣ ለፈንገስ እና ለተለያዩ ረቂቅ ተሕዋሲያን መዛመትና መራባት አመቺ እንዳልሆነ ጠቁመው፤ ቆላማ አካባቢ ለነፍሳት ንድፍት፣ ለወባ ወረርሽኝ መቀስቀስ፣ ለመጠጥ ውኃ ብክለት፣ ለሆድ ሕመም፣ ለምግብ መመረዝና መበላሸት፣ ለአካባቢ ብክለት፣ ለበሽታዎች መከሰት፣ መስፋፋት እና ሥርጭት የዐየር ንብረት ለውጥና የመልክዓ ምድር ልዩነት ተፅእኖ እንዳለው፤ (አቶ ዐባይ፣ቃ.መ፤ 30/05/2011 እብናት) ገልፀዋል።

በአጠቃላይ የዓመት መለያየት፣ የወቅት መፈራረቅ፣ የዐየር ንብረት መለዋወጥ (ውርጭና በርሃ፣ ቀዝቃዛና ሞቃት)፣ የሥነ ምህዳር ልዩነት (ቆላ፣ ወይና ደጋ እና ደጋ) ለሕመም መከሰት፣ ለወረርሽኝ መነሳት፣ መዛመትና መሰራጨት አስተዋጽኦ እንዳላቸው፤ የቆላ ቁስል፣ የወባ በሽታ፣ የውኃ ብክለት፣ የሆድ ሕመምና ተቅማጥ፣ የቆዳ በሽታና አካላዊ ቁስለት፣ ስንፈተ ወሲብ፣ የአዕምሮ ሕመም፣ "የወፍ"/ጉበት፣ የጎርምጥ ቁስል፣ ኩላሊት፣ ኪንታሮት፤ በዋናነት በቆላና በወይና ደጋ አካባቢ፤ የመተንፈሻ አካል፣ አስም፣ ቁርጥማት፣ የጉሮሮ፣ ስንፈተ ወሲብ፣ ጉንፋን እና "የወፍ"/ጉበት ሕመም በደጋ/ማ አካባቢ በተደጋጋሚ እንደሚከሰቱ የመስክ መረጃዎች ገልፀዋል። በዚህ ጥናት የማኅበረሰብ እምነቶች (ሚታዊ ትረካዎች፣ ቃል ግጥሞች፣ ልማዳዊ ሥርዓት) መኖሪያ አካባቢና ቦታን ገላጭ/ጠቋሚ ሆነው ተገኝተዋል። ወንዝ በሚበዛባቸው (ተከዜ እና ርብ ወንዝ) በቆላ እና በወይና ደጋ አካባቢዎች "የጅን" ትረካዎች፤ ተራራ፣ አድባርና ደን በሚበዛባቸው ደጋማ ቦታዎች ደግሞ "አዳኝ ወርቁና ራሄሎ" የሚባሉ የዛር መናፍት ትረካዎች ቦታና አካባቢውን እንደሚያስተዳድሩት ይታሰባል።

### 5.4.6 የኮከብ ባሕርይ መግነንና መክሰም

የባህል ሐኪሞች የሰው ልጅ እድሜ፤ በቀን፣ በዓመትና በወራት ሂደትና ዑደት የኮከብ ባሕርይው የተመደበና የተገደበ መሆኑን ጠቁመዋል። "ኮከቤን እይልኝ፤ በዚህ ቀን አጋንንት ለከፈኝ፤ መመለሻው ምንድን ነው፤ ጭዳውን ንገረኝ፤..." ይባላል (መሪጌታ ባሕረጥበብና መሪጌታ መልኩ፤ቃ.መ 22-23/01/2011 ፋርጣ)። በሥነ ከዋክብት ጥናት (Astrology) የዓመቱን አስራ ሁለት ወራት ባሕርይ ለመተንበይ፤ የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት አቀማመጥ፣ እንቅስቃሴና ይዘት፤ ከፕላኔት ሁነት ጋር በማገናኘት እና በማዛመድ የተፈጥሮን ምስጢርና ክስተት፣ የሰው ልጅ ባሕርይ፣ በሽታና እጣ ፋንታን፤... ለመተንበይ ሙከራ (Lewis, 2003; Heindel and Heindel, 2011;PP.5-6) ይደረጋል። በከዋክብት-ተኮር ምርመራ የፕላኔት አቅጣጫና ይዘትን በማጤን

ሳይንሳዊ፣ ጥበባዊ ክህሎትና ዕውቀትን በማገናኘት የበሽታ፣ የሕመም መንስኤ እና የወደፊት ገጠመኝን ጨምሮ ለመተንበይ ይሞከራል፤ እንደ Heindel and Heindel መረጃ "Astro-Diagnosis is the science and art of obtaining scientific knowledge regarding disease and its causes as shown by the planets, as well as the means of overcoming it" በማለት (2011;P.5) ጠቁመዋል።

የሥነ ከዋክብት ቆጠራና ትግበራ አካባቢያዊ ዕውቀትን፣ ሃይማኖታዊ እሳቤን፣ መልክዓ ምድራዊ ሁነትና አቀማመጥ፣ ባህላዊ ተግባርን፣ ልማዳዊ ሥርዓትን መሰረት ያደርጋል። የሰው ልጅ በሽታን የመከላከል፣ የመቋቋምና የመጠቃት ኃይሉ እንደግለሰቡ ሁነት እና ባሕርይ ይለያያል (Lewis, 2003: Heindel and Heindel, 2011)። የግለሰቡን የኮከብ ባሕርይ በማጤን፤ ምን ዓይነት በሽታ ግለሰቡን ያጠቃል? የትኛው ሕመም ይብስበታል? የትኛውን የሰውነት አካል ለይቶ ያመዋል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል። የኢትዮጵያውያን ኮከብ አቆጣጠር እና አተገባበር ከምዕራቡ ዓለም ይለያል[63]።

ሊቀጠበብት አብርሃም እና መሪጌታ ባሕረጥበብ፤ የኢትዮጵያውያን ኮከብ አቆጣጠር፤ በጨረቃ፣ በፀሐይና በከዋክብት እንቅስቃሴና ባሕርይን እንደሚመለከት ጠቁመው፤ በዘመን፣ በወር እና በሳምንት የተመደቡ ኮከቦችን በመመርመር፤ በየወሩ የተሾሙ የኮከብ ባሕርያትን በማጤን ምርመራ እንደሚያካሂዱ፤ የተፈጥሮ ባሕርይ ሥር መሰረት የሚባሉ ነፋስ፣ እሳት፣ ውኃና መሬት በምርመራ ሂደት በምጣኔና በሚዛን መገኘት/አለመገኘታቸውን ማረጋገጥና ማጥናት የመጀመሪያ ተግባር መሆኑን ገልጸዋል። የዓመት ጭዳ፣ ስለት፣ ግብር፣ መስዋዕት ማቅረብና መሰዋት፤ ከጤና እና ከሕመም ዐውድና ተግባር ጋር እንደሚዛመድ ጠቁመው፤ እነዚህ ተግባራት ዓመት ጠብቀው፣ ወርና ዘመንን መነሻ አድርገው የሚፈፀሙ ቢሆንም፤ የታማሚው ሰው ኮከብ ተቆጥሮ፣ መለከፊያ ቦታና ዕለት ተለይቶ፤ ለባህል ሐኪሙ ያደሩ፣ የተገዙ፣ ታዛዥ የሆኑ አጋንንት የፈውስና የሕክምና ዘዴውን እንደሚጠቁሙ፤ አስረድተዋል (ቃ.መ፤22-30/01/2011 ሊቦ ከምከም እና ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

[63]ምዕራባውያን የትውልድ ዘመን፣ ዓመት፣ ወርና ሠዓትን ታሳቢ ሲያደርጉ ኢትዮጵያን የፊደል ቀመርን በመከተል፤ የመጀመሪያ ስምና የእናት ስም እንደመነሻ ተግባራዊ ይሆናል። የኮከብ አቆጣጠር ይዘትና አገዳደፍ ሥርዓት ከሶስት እስከ ሰላሳ ሁለት ቤት ይደርሳል። እንደ ርዕሰ ጉዳዩ የአቆጣጠር ብልሃቱ ይለያያል።

በአቶ ደሴ[64] የባህል ሕክምና መስጫ ቦታ የተካሄደ የንጥል ጥናት ይዘት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

**ንጥል ጥናት አንድ፡- አቶ ደሴ ከታካሚያቸው ጋር የነበራቸው መስተጋብር**

የባህል ሐኪም፡- አቶ ደሴ ገብሩ[65] በሊቦ ከምከም ወረዳ በአዲስ ዘመን ከተማ በ 01 ቀበሌ ኗሪ ሲሆኑ፤ በባህል ሕክምና ሙያ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ አቶ ደሴ በአካባቢው ማኅበረሰብ የሚታወቁበትን፤ የአባታቸውን የባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ተግባርና ሥርዓት ተምረው፣ ለምደውና ወርሰው፤ ለአካባቢው ማኅበረሰብ የባህል ሕክምና አገልግሎት በመስጠት ከሰላሳ አምስት ዓመት በላይ እንደሆናቸው ይገልጻሉ፡፡ አባታቸው ባወረሷቸው የብራና መጻሕፍት (ዕፀ መድኃኒት) እና ዐውደ ነገስት (ኮከብ መቁጠሪያ) በመታገዝና በመመራት፤ የባህል ሕክምና እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በዕለቱ በአቶ ደሴና በታካሚ መካከል የነበረው መስተጋብር እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

የባህል ሐኪም፡- ሰላም ነህ አብዬ! ለምን ነበር የመጣኸው?

ታካሚ[66]፡- …ተግሬ [ከእግሬ] ጀምሮ ባቴን ሸምቆ ይዞ!… በግራ ጎኔ ሽቅብ እየንጎጠ [እየወጋኝ]፤… ሰቅዞ ይዞኝ ነው!… አላላውስ አለኝ! በመከራ ተደግፌ መጣነ…፡፡

የባህል ሐኪም፡- መቼ ጀመረህ?

ታካሚ፡- በቀደም ለታ ተሲያት ነው! ከብቶች ወደ ውኃ አዳፍቼ [የወንዝ ውኃ እንዲጠጡ አሰማርቼ] ስመለስ?… እግሬን ጠዝጠዝ! ጠዝጠዝ!… አርጎ ጀመረኝ፡፡… ማታ ነው

---

[64]ከአቶ ደሴ ገብሩ፤ በቀን 06/03/2011 ዓ.ም በሕክምና መስጫ ቦታቸው በመገኘት ለንጥል ጥናት የሚያግዘኝን ምርምር ለማካሄድ ፍቃድና ቀጠሮ በመያዝ ተለያየን፡፡ በቀን 23/04/2011 ዓ.ም ከጧቱ ሁለት ሠዓት ከሩብ በባህል በሕክምና መስጫ ጣቢያቸው ደረስኩ፡፡ አቶ ደሴ የተለመደ የሕክምና አገልግሎት እየሰጡ፤ ልጃቸው (አብነት) እንግዳና ታካሚዎችን በመቀበል፣ በማስተናገድና ወረፋ በማሲያዝ ይጣደፋል፡፡ በእለቱ ከታካሚዎች በተለየ፤ ከዚህ በፊት የነበረንን ግንኙነት በማስታወስ ሰላምታ አቀረበልኝ፤ እንደዘመድና ቤተሰብ ተጠያይቀን ትንሽ ከተጫወትን በኋላ፤ የመጣሁበትን ጉዳይ በማስረዳት፤ ከአባቱ ጋር ቀጠሮ እንዳለን ጠቁሜው፤ ወረፋ እንድይዝ ነገርኩት፡፡ "ቅድሚያ ለቀጠሮ ታካሚዎች ስለሚባል ሶስተኛ ሰው ሆነህ ትገባለህ" ሲለኝ፤ ከሁለቱ ሰዎች ቀጥዬ ወረፋ እንድይዝ አቅጣጫ አመላከተኝ፡፡ ወረፋዬ ደርሶ ገባሁ፤ ከመቀመጫቸው ተነስተው ሰላምታ ሰጡኝ፤ ጤና፣ ቤተሰብ እና የሥራዬ ጉዳይ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ጠየቁኝ፡፡ በሰጡኝ ቀጠሮ መሰረት እንደመጣሁ በማስታወስ፤ እኔ በተገኘሁበት ፍቃደኛ የሆነ/ች ታካሚ ምርመራ ሲያደርጉ፣ ኮከብ ሲቆጥሩ፤ ከታካሚዎች ጋር ያለውን ግንኙነትና መስተጋብር ማየት የምፈልግ መሆኑን ጠቁሜ፤ መጀመሪያ ከታካሚያቸው ፍቃድ እንዲጠይቁ እና እንዲያስተዋዉቁኝ በማድረግ፤ የታካሚውን ፍቃድ በማረጋገጥ በአጭሩ እኔንና ርዕሰ ጉዳዬን አስተዋውቄ የሕክምና ሥርዓቱን መከታተል ጀመርኩ፡፡

[65]በሊቦ ከምከም ወረዳ በአዲስ ዘመን ከተማ 01 ቀበሌ በቀን 23/04/ 2011 ዓ.ም፤ ከረፋዱ 3፡05፣ ጀምሮ፤ ከባህል ሐኪም አቶ ደሴ ገብሩ እና ከታካሚ (ሀ) ጋር የተካሄደ የንጥል ጥናት ይዘት፡፡

[66]ታካሚው በአማካይ የአርባ አምስት ዓመት ጎልማሳ ይሆናሉ፤ በተወሰነ መጠን ግራ እግራቸውን ጠቁመው፤ ከግራ ብብታቸው በታች፤ ከቀበቶ መታጠቂያቸው ጀምሮ ወደ ላይ ገለጥ አድርገው፤ ወደ ባህል ሐኪሙ በመዞር በተጨነቀ ስሜት፤ በተቆራረጠ ትንፋሽ ማስረዳት ቀጠሉ፡፡

የባሰኝ፤… ከለከለኝ መሄድ! ቀና ስል እንደ ጦር ጠቅ! ያረገኛል፡፡…እንደ ጅብ አጎብሼ ነው! ስራመድ…፡፡

የባህል ሐኪም፡- ከመቀመጫቸው ተነስተው፤ የታካሚውን ሰውነት ወደ ብርሃን አዙረው፤ እግሩን ቀና አድርገው፤ ባትና ታፋውን ጨበጥ፣ ጨበጥ!፤ መታ! መታ! አጠፍ ዘርጋ! በማድረግ ወደ ቀበቶ መታጠቂያ ቦታ ከፍ ብለው፤ ልብሱን ሰብሰብ አድርገው በጣታቸው ጠቅ፣ ጠቅ! (ጫን፣ ጫን!) ሲያደርጉ፤ ታካሚው እኽ፣ እኽ!... እዚህ ነው! አዎ!፤… እሱ! እሱ! ሲል፤ ሐኪሙ "በል ልብስህን መልስው፤ አይዞህ" በማለት አይተው ወደ መቀመጫቸው ተመልሰው ተቀመጡ፡፡ እጃቸውን ጠራርገው፤ ደብተር ገልጠውና ብዕር አንስተው፤ ማነው ስምህ? የናትህ ስም? በማለት ጠየቁ፡፡

ታካሚ፡- እከሌ እባላለሁ፤ የእናቴ እከሊት [የመረጃ ሰጪዬን ምስጢር ለመጠበቅ ሲባል በጥናት አቅራቢው የተዘለለ] በማለት መለሰ፡፡

የባህል ሐኪም፡- እሺ! …አሁን ያተ ኮከብ ሲገደፍ [ሲነበብ]፤ በማለት የእጅ ጽህፈታቸውን ቀጠሉ፤ በነጭ ወረቀት የታካሚያቸውን የመጀመሪያ ስም፣ የእናት ስም፣ የታመመበትን ወር እና ወንጌል ጽፈው፤ ቁጥሩን በሰባት "ገድፈው" ደምረውና ቀንሰው ሲጨርሱ፤ ዐውደ ነገስት ገልጠው፤ የሕመሙን መንስኤ፣ የተለከፈበትን ቀንና ቦታ ለመለየት "ሐሳበ ሕሙም ወዕለት[67]" የሚለውን አንቀጽ አውጥተው ማንበብ ጀመሩ፤

ታካሚ፡- አይ አባቴ! … ቅጥቃጤውም [ቅዠቱ] ባሰኝ! እህህ! እህህ!...

የባህል ሐኪም፡- አይዞህ በርታ! ኮከብህ ማለፊያ [ጥሩ] ነው፡፡

ታካሚ፡- እሺ! እስቲ ይሁና! አዲዩ ከማረኝ (ፈጣሪ)፡፡

የባህል ሐኪም፡- ዐውደ ነገስቱን ገልጠው፤ ከቤት ሲወጣ እሁድ ቀን ጋኔል አገኘው፤ ከፍሳሽ ውኃ ፀሐይ ሞቅ ሲል ለከፈው፤… በሽታው ሲጀምረው በመላ አካላቱ ይበተናል፤ እጁን እግሩን ወገቡን ይቆረጥመዋል፤ በኋላ ግን ያስታውከዋል፤… ራስ ምታት፤ ቁርጠት ያመዋል፤ እግሩን ይሸመቀቀዋል ብርድ ብርድ ይለዋል፤ በሽታው በሆዱ ይፀናበታል፤… ነጭ ዶሮ አርዶ ሥጋዋን ይብላ፣ መረቋን ይጠጣ፤ በማለት ዐውደ ነገስቱን አንብበው ይዘቱን መልሰው በቃል አስረዱ፡፡ ሌላውን የዐውደ ነገስት ክፍል ገልጠው የኮከብ ባሕርይን ማንበብ እስከሚጀምሩ፡፡

ታካሚ፡- እሺ! እሺ!... ነጭ ዶሮ! ነጭ ዶሮ ሥጋዋን ይብላ፤ መረቋን ይጠጣ! መልካም፤ ይሁን!

የባህል ሐኪም፡- ኮከብህ ሐመል ነው!... በዘመነ ማቴዎስ ሞት ያስፈራዋል፡፡ በጥቅምት ወር ሆዱን፣ ራሱን፣ ግራ እግሩን ያመዋል፤ ሥራይ ያስፈራዋል፡፡… በዘመነ ሉቃስ በመስከረምና ህዳር፤ በሚያዚያና ሐምሌ ውኃትና ሳል ያመዋል፡፡ በታመመ ጊዜ የዝግባ

[67]"ሐሳበ ሕሙም ወዕለት" ማለት፤ በዐውደ ከዋክብት ንባብና ቆጠራ ሂደት የሕመም መንስኤ እና መለከፊያ ዕለትን የሚጠቁምና የሚገልፅ ጽሑፍ ነው፡፡

ቅጠል ዘፍዝፎ ይታጠብ፤ ሙጫውንም ይቆርጥም። ጋኔል… አጥፊው ነው። ሲታመም ጽጌረዳና ሰሊጥ፤ የእርግብ ሥጋ ይብላ፤ መረቋን ይጠጣ፤ ደሟንም ይቀባ፣ ክንፏንም ይታጠን። …መዳኒቱ ባዳል በግ ወይም በነጭ ፍየል ብራና መፍትሔ ሥራይን ላይነ ጥላ [ለሰው ዓይን/ለቡዳ]፤ መርበብተ ሰሎሞንን ለማዕሰረ አጋንንት [አጋንንትን ለማሰር]… አጽፎ ይያዝ።… ደዌ ያስፈራዋል… መዳኒቱ ቀይ፣ ነጭ ወይም ጥቁር ቡሃ በግ አርዶ ሐሞቱን ይጠጣ። በማለት አንብበው ጨርሰው ይዘቱን ደግመው በቃል አስረዱ።

ታካሚ፡- እሺ!… አጀብ ነው!… ሰው በቁሙ ስንት አሳር አለበት! እህህ፣ እህህ!

የባህል ሐኪም፡- የታካሚያቸውን የሕመም መንስኤ፣ የኮከብ ባሕርይ ከለዩና ካነበቡ በኋላ ለታካሚው፤ ከቀመሙት መድኃኒት የሚጠጣ እና የሚቀባ (በወገብና በታፋ) መርጠው፤ ቅደም ተከተልና አተገባበሩን አስረድተው፤ የአዘጋጁትን መድኃኒት ሲሰጡ፤ "አንድዬ ምህረቱን ይላክልህ! የጊዮርጊስን ጠበል ጠጣ፣ አንድ ሰንበት ተጠመቅ! ግንባርህ ነው!" በማለት ታካሚያቸውን ከ28 ደቂቃ ቆይታ በኋላ አሰናበቱ (23/04/2011)።

ታካሚ፡- "ሀ"ን ከአራት ቀን ቆይታ በኋላ (26/04/2011 ዓ.ም) በመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ምርኩዝ ይዘው ከብቶች ሲጠብቁ አገኘኋቸው። ሰላምታ ተለዋውጠን ውይይታችንን ቀጠልን፤

ተሽሎኛል! አሁን ደህናነኝ፤ …እንደልቤ መላወስ ችዬ፤ እድዬን ምስጋና ይግባውና ፋታ አገኘሁ፤ ትንሽ ባቴና ቋንዣዬ ላይ ያዝ አርጎኛል። …ተጊዮርጊስ ጠበል ሂድ ተብያለሁ።…የቤት ጣጣ አለብነ፤ ተቤትና ተበረት እማይጠፉ ወሰራ ዶሮና ነጭ ፍየል ታባቴ ጀምሮ ነበር። …አልሞላልህ ብሎኝ ጥቅምት ጭዳ ሳልሰጥ አለፈ።…የቤት ቆሌ ተጣልታኝ ነው፤ ጥር ሚካኤል እካድማለሁ፤ ምህረቱን ልካልኝ!.. አቶ ደሴ ዓይናችን ናቸው። ቸሩ እግዛቤር የፈውስ እጅ አድሏቸው፤ መጣፍ ገልጠው፤ ኮከቤን ቲነግሩ አንዱም ጠብ አላለም።…ጥሩ መጣፍ ገላጭ ናቸው።…የሰጡኝነ መዳኒት በጠበል በጥብጬ እየጠጣሁ፤ ባትና ወገቤነ አሙቄ እየቀባሁ ነው።… አሁንማ ድኜ፤ አንድዬ ምን ይሳነዋል።

በማለት በተሰጣቸው ሕክምና ምህረትና ፈውስ እንዳገኙ ገልፀው፤ ሙሉ ለሙሉ ለመዳን ቀጣይ ትዕዛዝና ተግባር እንደሚቀራቸው አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 26/04/2011 ሊቦ ከምከም)። የኮከብ ባሕርይ ሐመል እሳት፣ ከሰውነት አካል መገኛ ቦታ አናት (እራስ)፣ ወር መጋቢት፣ የባሕርይ እንስሳ ተምሳሌት አውራ በግ። ይህ ኮከብ ምን ዓይነት አንድምታና ትርጓሜ አለው? እንዴት ይገለጻል/ ይተነተናል?

"ሐመል እሳት" የእሳት ነበልባል ይባላል። ይህ ኮከብ ከመጋቢት አሥራ አራት ጀምሮ ማታ ማታ እንደሚታይ ተጠቁሟል። ሐመል እሳት እጅግ ኃይለኛ፣ ቁጡ፣ ቀልጣፋ፣ ደፋር፣ አትንኩኝ ባይ የብሩህ አዕምሮ ባለቤት፤ ተናግሮ እሚያሳምን፣ አንደበቱ "ትንታግ"፣ ሥራው አስደሳች፣

ተከታይና አጀብ ያለው ተደርጎ ይመሰላል፡፡ ኮከቡ የእሳት ባሕርይ ሥላለው፣ የሚያጠፋው ኃይል ሥለሌለ፣ በአጠገቡ የሚገኙ ወዳጆቹን ያበረታል፣ ያሞቃል፣ ይደግፋል፣ በአንጻሩ ጠላቶቹን አቃጣይ፣ አድራቂ፣ አፈናቃይና አባራሪ ባሕርይ ቢኖረውም ቂመኛ፣ ተንኮለኛ እና ተበቃይ አይደለም፣ እንደበግ የዋህ ነው፣ ይባላል፡፡ ኮከቡ ተናጋሪ፣ ተዋጊ፣ በጉልበቱ አዳሪና ኃይለኛ መሆኑ፣ ለእራስ ምታት ሕመም፣ ለዳፍንት፣ ለትኩሳት፣ ለእራስ ማዞር፣ ለፊት መቅላትና መሽብሸብ፣ ለሰውነት ቆዳ መቆጣት፣ ለአዕምሮ መዛባትና መቃወስ፣ ለነስር፣... ሕመም ተጋላጭ እና ተጠቂ እንደሚሆን መክረዋል (አቶ ደሴ እና ደብተራ መልኩ፣ ቃ.መ፣ 23/04/2011 ሊቦ ከምከም፣ 01/03/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)፡፡

ይህ ኮከብ በልጅነት ዘመኑ ልበ ብሩህ፣ ማስተዋልና ማገናዘብ ችሎታው ከእኩዮቹ የላቀ ቢሆንም በጉርምስና ዘመኑ የማቃጠል ባሕርይው ተቀስቅሶ፣ ኃይልና ጉልበቱ አይሎ ሥሜቱ ገንፍሎ ስለሚወጣ፣ ሴት ይቀርባል፣ ያፈቅራል፣ ተበድሮም ቢሆን ይጋብዛል፡፡ በዚህ ባሕርይው "ቅንዝረኛ ነው፣ ዘማዊነት አለበት፣ የሴት በሽታ ያስፈራዋል" ይባላል፡፡ በወጣትነት ዘመኑ የእሳትነት ባሕርይው ስለሚገፋው ኃይልና ጉልበቱን ለማሳየት ሌላውን ይነቅላል፣ እራሱን ይተክላል፡፡ ይህ ተግባሩ ብዙ ጠላት እንዲነሳ፣ በሰው እጅ እንዲጠፋ ምክንያት ስለሚሆን በወጣትነት ዘመኑ ጥንቃቄ ያሻዋል፣ ፀሎት፣ ፆም፣ ስግደትና ንስሃ ይበጀዋል፡፡ ኃይልና ጉልበቱን ለማብረድ፣ ለማረጋጋት፣ ቀልብ እንዲገዛ፣ አስቦ እንዲራመድ፣ ሽምጥጦ እንዳይሄድ የባሕርይ ማመጣጠኛ፣ ማስተካከያ "ልጓም" ያስፈልገዋል፣ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በሽምግልና ዘመኑ የእሳት ባሕርይው እየደከመ፣ እየከሰመ፣ እየበረደ፣ አካላዊ ጥንካሬ እየሸሸው፣ የማስታወስ አቅሙ እየጠፋ ሲሄድ፣ በሞት መቃረቢያ ዘመኑ፣ ትካዜና ሃዘን ይገባዋል፣ ተብሎ (አቶ ደሴ እና መሪጌታ አማረ፣ቃ.መ፣23/04/2011፣ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል) ይነገራል፡፡

መሪጌታ ፋንታሁን እና ደብተራ መኳሪ የሰው ልጅ አራቱን የተፈጥሮ ሥጋዊ ባሕርይ (ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃና መሬት) በሕይወት ዘመኑ በየተራ ፈፅሞና ተግብሮ እንደሚያልፍ፣ ጠቁመዋል (ቃ.መ፣ 19/01/2011 ፋርጣ፣13/03/2011 እብናት)፡፡ የሰው ልጅ ከልደት እስከ ሃያ ዓመት፣ የነፋስ ባሕርይ ይታይበታል፣ ይባላል፡፡ እድገቱ ዘገምተኛ፣ ተግባርና ይዘቱ ለስላሳ፣ እየጠነከረ፣ እያደገ ሲሄድ፣ መሮጥ፣ መብረር፣ መነሳት፣ እረፍት ማጣት፣ መቅዥቀዥ፣ የሥሜት መዋለል፣ ያገኘውን ልብላና ልጠጣ ስለሚል የምርጫ ማጣትና የፍላጎት መብዛት ሲታይ የልጅነት ባሕርይ ነው፣ ይባላል፡፡ በወጣትነት እድሜ (ከሃያ እስከ አርባ ዓመት) የእሳት ባሕርይ በመውረስ፣ ኃይል፣ ጉልበት፣ ሥሜት፣ ፍላጎት፣ አቅምና ችሎታን በማስተባበር የፈለገውን ይሰራል፣

በአንጻሩ ኃይልና ጉልበቱን ተመክቶ የነገን ማግኘት ተስፋ አድርጎ፤ ያገኘውን ገንዘብ፤ ጥሪትና ሐብት በደረሰበት ይበትናል። በዚህ ተግባሩ "ገንዘብ በሃያ ዓመት፤ ልብ በአርባ ዓመት" ይባላል፤ በጉርምስና ዘመኑ "ሥሜት ይነዳዋል፤ ፍላጎት ይጥለዋል" ተብሎ ይታሰባል። በጎልማሳነት ዘመን (ከአርባ እስከ ስልሳ ዓመት) የዉኃ ባሕርይን ይወርሳል፤ ጉልበት ይሰክናል፣ ኃይል ይበርዳል፣ ነገሮችን በትኩረት ማየት፣ ማስተዋል፣ መረጋጋትና ሚዛናዊ ፍርድ መስጠት መገለጫ ተግባርና ባሕርይ ይሆናል። በጉርምስና ዘመን የተገኘን ዕውቀትና ሐብት መንከባከብ ይጀምራል፤ የማስታረቅ፣ የማስማማት፣ የማዋሃድ፣ የማረጋጋት ባሕርይን ተላብሶ፤ ማኅበራዊ ሥርዓትና ግንኙነትን ለማጠናከር ይለፋል፣ ይተጋል፣ ይደክማል። አካባቢን ይዳኛል፣ አገር ያስታርቃል፤ ይህ የእድሜ ዘመን "የትውልድ መሰረት፤ የሕይወት መብራት ነው" ይባላል።

መሪጌታ ፋንታሁን እና ደብተራ መኅሪ (ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ፤ 13/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፤ የሰው ልጅ በሽምግልና ዘመኑ (ከስልሳ እስከ ሰማኒያ ዓመት) የመሬት ባሕርይን ይወርሳል፤ ተብሎ እንደሚታሰብ ጠቁመዋል። መሬት ሁሉን ቻይ፣ ታጋሽ፣ ተቀባይ፤ ቢዘሉባት፣ ቢረግጧት፣ ቢሰድቧት አይከፉት፤ የመስከን፣ የመብረድና የመድከም፤ አቅምና ጉልበትን አሟጦ መጠቀም፣ በተስፋ መኖር፣ አካላዊ መድከምና የጤና መታወክ የሽምግልና መገለጫ ባሕርይ እንደሆኑ፤ መክረዋል። ከሰማኒያ ዓመት በላይ፤ ሲኖር በራስ ጉልበት፣ ፋቃድ፣ ሃሳብ፣ ተግባር ማደር ይቀራል። ቆሞ ከመሄድ ማጎብደድ፣ ከማጎብደድ መቀመጥ፣ ከመቀመጥ መዳህ፣ ከመዳህ መንደባለል ይመጣል። ሃሳብ ይኖራል፣ ጉልበት ይዝላል፤ ማስተዋል ይቀራል፤ መርሳትና መዘጋት ይከሰታል፤ አካላዊ ሥጋ ይንገላታል፣ ሕመም ይበረታል፤ ይህ እድሜ "እንደ ሕጻን ያደርጋል፤ እራስን ያስረሳል" ተብሎ ይታመናል።

በአጠቃላይ የኮከብ ባሕርይ መግነንና መክሰም ለሕመም መንስኤ መሆኑን የመስክ መረጃዎች አስረድተዋል። የኮከብ ባሕርይ የግለሰብን ዕጣ ፈንታና የሕመም ምክንያት ከዘመን፣ ከወቅት፣ ከዓመት፣ ከወራት፣ ከሳምንት፣ ከቀናትና ከዕለት ዐውድና ተግባር ጋር በማገናኘትና በማገናዘብ የሕመሙን መንስኤና መፍትሔ ምላሽ ለመስጠት ጥረት ይደረጋል። የኮከብ ቆጠራ ሂደት የሥነ ከዋክብት (ፀሐይ፣ ጨረቃና መሬት) ምርመራን፣ ወቅትን፣ ሃይማኖትን፣ ሥነ ምህዳርን (መልክዓ ምድርን) ወይም መገኛ አካባቢን መነሻና መሰረት እንደሚያደርግ፤ ከዚህ በላይ ከቀረቡ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል። በቀጣይ ንዑስ ይዘት የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች ማጠቃለያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 5.5 የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤ ትንታኔ ይዘት ቀርቧል፡፡ በትንታኔው መሰረት የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

- በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብና የባህል ሐኪሞች እሳቤ ዐበይት የሚባሉ የሕመም መንስኤ ዓይነቶች ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ የመሬትና የዐየር ጋኔልና አጋንንት እንደሆኑ ተስተውሏል፡፡ ጅን በወንዝ አካባቢ በመገኘት እና በዉኃ ልክፍት የሚነሳ፤ ለአካላዊ ቁስለትና ለሆድ ሕመም ምክንያት ሲሆን ዛር ደግሞ የሰውን አዕምሮ በመሰወርና በመቆጣጠር በዋናነት የመራቢያ አካልን ማድከም እና ልጅ መውለድን ይከለክላል (ሾተላይ) ተብሎ ይታመናል፡፡ ቡዳ፤ በደም መፍሰስ፣ በምግብና መጠጥ፣ ለዓይን እይታ አጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች በመገኘት፣ መብላትና መጠጣት፤ በቡዳ ለመያዝና ለመለከፍ መንስኤ ተደርገው ታስበዋል፡፡ የሕመሙ ባሕርይ የደም ዝውውርን በመከተል አካልን የማድከም፤ አዕምሮን የመሰወር፣ አካልን የማጠራራት፣ የማስጮህ፣ የመደበትና የማስለፍለፍ ጠባይ እንዳለው፤ ይነገራል፡፡
- የዐየር ጋኔል፤ ለአዕምሮ ሕመም፣ ለድንገተኛ አካል ጉዳት፣ በፀሐይ ጨረር ለሚከሰት ሕመም፣ ለዓይነ ስውርነት በመዳረግ፤ ድንገት ለሚጥል በሽታ መንስኤ እንደሆነ፤ ይታያል፡፡ የመሬት ጋኔል፤ በቆሻሻ ቦታ በመገኘት፣ በር በመክፈትና በመዝጋት፣ በሞቃትና ቀዝቃዛ ዐየር መጋጨት ምክንያት በሚደርስ ጉዳት፤ ለሰውነት አካል መሸማቀቅ፣ ለፊት መጣመም፣ ለዓይን መሸዋረር፣ ለምች፣ "ለብርድ ሕመም" መነሻ እንደሆነ፤ ይስተዋላል፡፡
- በማኅበረሰቡ እሳቤ፤ ሕይወት በጤና እና በሕመም፣ በሰናይ እና ዕኩይ መናፍስት መሃል የምትገኝ፤ በሁለቱ ተቃራኒ ኃይሎች ስበትና ሂደት ትፈተናለች፡፡ የዓለም አፈጣጠር፣ ሂደትና ቀጣይነት በሁለት ኃይሎች ስበት እና መወራረስ የተገኘ ሲሆን፤ የሥነ ፍጥረት የለውጥ ሂደት፣ ዑደትና ጥሪን (መውለድ-ማደግና መሞት) ለፍጥረተ-ዓለሙ የተሰጠ ባሕርይና ፀጋ እንደሆነ፤ ይመስላል፡፡
- በማኅበረሰቡ ልማድ፤ ከዕፅዋት ጣፍጭና ፍሬ የሚያፈሩ የዛፍ ዓይነቶች የዛር ማደሪያ እና የቆሌ ማረፊያ በማለት ከግቢያቸው ያርቃሉ፡፡ በአንጻሩ፤ መራራና አቃጣይ ጣዕም ያላቸውን ዕፅዋት በማቅረብ በግቢና በአካባቢያቸው ተክለው፤ ለሕክምና አገልግሎት ይጠቀማሉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ሣር በል እንስሳትን በማቅረብ፤ ሥጋ በል እንስሳትን በማራቅ ጤናቸውን እንደሚጠብቁ፤ ይታያል፡፡

- የባህል ሐኪሞች፤ ዓመት፣ ወቅትና ወራትን ጠብቀው፤ መከሰቻ ዐውድን ለይተው ለሚነሱ በሽታዎች ዝግጅት ማድረጋቸው፤ በኮከብ ቆጠራ የሕመም መንስኤ ባሕርያትን በመለየት እና የፈውስ አማራጮችን በመጠቀም የሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ፤ የጥናቱ ትንታኔ አረጋግጧል፡፡ በቀጣይ ምዕራፍ በባህል ሕክምና ዕውቀት፤ የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ይዘታዊ ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት፡- በባህል ሕክምና ዕውቀት፤ የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ይዘታዊ ትንተና

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች፣ በምርመራ ሂደት የበሽታ ባሕርይ ምድብ፣ የተቃርኖ ሕክምና፣ የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ቀርበዋል። በዚህ ንዑስ ክፍል፤ ባህል-ተኮር፣ ዐውድ-ተኮር እና የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴሎችን በማስተሳሰር ትንተና ተካሂዷል።

## 6.1 የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች

በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት ንዑስ ክፍል 2.1.7 እንደተገለፀው፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ዓለማዊና መለኮታዊ በመባል በሁለት ዐበይት ምድብ እንደሚከፈሉ ተጠቁሟል። በዓለማዊ ይዘት ሥር እይታዊ ምርመራ፣ ክሊኒካዊ ምርመራ፤ ባዮሎጅካል ምርመራ፣ የታካሚ የሕይወት ዳራና አጠቃላይ ሁኔት ምልከታ (Anamnesia and Observation of the Patient) ይጠቀሳሉ፤ በመለኮታዊ (Divination) ይዘት ሥር በሚሸተትና በሚጠጣ የሚካሄድ ምርመራ (Snuff and mind changing drugs)፣ በሥነ ከዋክብት ቆጠራ (Astrological Signs)እና በሕልም ትንተና (Dreams Analysis) የሚደረጉ ተግባራትን ይመለከታል።

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች እንደግለሰቡ እምነትና ተግባር፣ የዕውቀት ምንጭ፣ የሕይወት ተመክሮ፣ የዓለም አተያይ፣ ሃይማኖታዊ መሰረት፣ የመልክዓ ምድር ልዩነት፣ ግለሰባዊ ፍላጎትና ተሰጥኦ ከቦታ ቦታ የሚለያይ ቢሆንም ዓለማዊና መለኮታዊ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም፤ የሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ የመስክ መረጃዎች እንደሚከተለው አስረድተዋል። በዚህ ንዑስ ይዘት ሥር ዓለማዊና መለኮታዊ የበሽታ መለያ ዘዴዎችና አተገባበር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 6.1.1 ዓለማዊ የበሽታ መለያና ምርመራ ዘዴዎች አተገባበር

በዚህ ንዑስ ይዘት ሥር እይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባዮሎጂካዊ፣ የታካሚን ዳራና አጠቃላይ ጤናን የሚመለከቱ የምርመራ ዘዴዎች አተገባበር፤ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## ሀ) እይታዊ የምርመራ ዘዴ አተገባበር

የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ በአካባቢው የሚከሰቱ በሽታዎችን ዓይነት፣ ባሕርይ፣ ፀባይ እና መሰል ጉዳዮች ለመለየት፤ በምልከታ የበሽታውን ይዘት፣ ሁኔታ፣ መጠንና ልክ ለመግለፅ ይሞከራል። ለምሳሌ፡- "ዓይኑ ቢጫ ሆኗል ወፍ ሳትሆን አትቀርም፤ ጣት የሚከረክር፣ የሚለበልብና ዉኃ የሚያዥ የልፌ ቁስል ምልክት ነው፤ ገላን የሚያሳክክ የሰውነት ቁስል በዉኃ ንድፍት የሚመጣ የቆላ በሽታ ነው!..." ይባላል (ከተቡው አባላት፤ *ቃ.መ*፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን ሁለት)።

የባህል ሐኪም አቶ ደርሶ፤ የታካሚን አካላዊ ቁስለት፣ የቆዳ መቅላት፣ መሸብሸብ፣ መጥቆር፤ የዓይን ቀለም ነጭ፣ ቀይ፣ ቢጫ መሆን/አለመሆን፤ የሽንት ቀለም (ነጭ፣ ቢጫ፣ ቀይ፣ ቡኒ) መለዋወጥ፤ የዓይነ ምድር መቅጠን፣ መወፈር፣ መድረቅ፣ ደም እና "ንፍጥ" መሰል ፈሳሽ የተቀላቀለበት መኖርና አለመኖሩን በማየት የሕመሙን ምልክት፣ የጉዳት ደረጃና መጠን በእይታ መለየት እንደሚቻል ገልጸዋል (*ቃ.መ*፤ 03/02/2011 እብናት)። የባህል ሐኪም አቶ ሞላ ለውጫዊ የአካል ቆዳ ቁስለት እና እብጠት ዐበይት መለያ መንገድና ስልቶችን እንደሚከተለው ያስረዳሉ (*ቃ.መ*፤ 22/06/2011 ፋርጣ)።

> የቆዳ ቁስል በማየት ይለያል። የቁስሉን ዓይነት፣ ፈሳሽ፣ እብጠት፣ መገኛ ቦታ፣ አቀማመጥ፣ ቀለም አይተህ ምን ዓይነት ቁስል እንደሆነ ይታወቃል። የእከክ፣ የብጉንጅ፣ የጎርምጥ፣ የጡት ነቀርሳ፣ እጢ፣ የጆሮ ቁስል፣ በየራሳቸው የተለያየ ምልክት አላቸው። መግልና ደም ቋጥሮ ጫፉ የሚቀላ ብጉንጅ፤ ሰውነትን የሚያሳክክ እጅና እግርን የሚበላ ከሆነ እከክ፤ አንድ ቦታ ተቋጥሮ ሞራ ተሽክሞ ከተቀመጠ ዕጢ ይባላል።... የቁስል ታካሚ ሲመጣ፤ ሕመሙ መቼ ጀመረህ? ምን ያህል ጊዜ ቆየብህ? ያቃጥልሃል ወይስ ይበላሃል? እየተባለ ይጠየቃል።... የቁስል መንስኤ፤ በልክፍት፣ በመውደቅ፣ በእሾህ እና በስለት መቆረጥ ይሆናል። ... የቁስል ዓይነቶች ዘርና ቤተሰብ አላቸው፤ በጠባይ በጠባያቸው ይለያሉ፤ ከይሲ ነቀርሳ [የአጥንት ነቀርሳ]፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ የጡት ነቀርሳ ይባላሉ፤ ኪንታሮት ከስድስት በላይ ዘር አለው፤ የአህያ ኪንታሮት [በዓይነ ምድር መውጫ የውስጥ ክፍል የሚከሰት]፣ የራስ እና የውስጥ እግር ኪንታሮት፣ ወንዴና ሴቴ ኪንታሮት፣ የፊንጢጣ ዳር ኪንታሮት በመባል ይለያሉ።

በማለት አስረድተዋል። እንደ አቶ ደርሶ መረጃ፤ አካላዊ ቁስልን ለመለየት እይታዊ ምርመራ ተመራጭ መሆኑን ጠቁመው፤ የሕመሙን ዓይነት፣ ባሕርያት፣ መገኛ ቦታ፣ ቀለም፣ ቤተሰብ፣ ፀባይ፣ ዘር እና ምድብን ለማወቅ እንደሚያግዝ ገልጸዋል።

የባህል ሐኪም አቶ ጌጡ እና አቶ ታከለ ደግሞ፤ ውስጣዊ ሕመምን፤ ከውጫዊ የሰውነት አካል ቆዳ፤ እጅና ጥፍር፣ ዓይንና ጆሮ፣ ምላስና ቅንድብ ቦታዎችን በማየት መለየት እንደሚቻል ይመክራሉ። የታካሚን የሕመም ዓይነት ለመለየት፣ ምልክቱን ለማጤን፣ የደረሰውን ጉዳት ለማወቅ፣ የበሽታውን ደረጃ ለመገንዘብ፤ የሰውነት አካል "እንደብራና ጽሑፍ ይነበባል"[68] ይላሉ። የወፍ (በዘመናዊ ሕክምና የጉበት) በሽታን ለመለየት የታካሚን ዓይን፣ ምላስ፣ ጥፍር፣ ጣት፣ የእጅ መዳፍ እና ሽንት በማየት፤ በሽታውን ማወቅ እንደሚቻል ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 24/01/ 2011 ፋርጣ፤ 04/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)። ከዚህ በታች፤ ባህላዊ "የወፍ" (የጉበት) በሽታ ምርመራ ሂደትና አተገባበር በአቶ ጌጡ (በምልከታ፤ 20/06/2011 ፋርጣ) እንደሚከተለው ቀርቧል።

አስረጂ አንድ፡- የ"ወፍ"/ጉበት በሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች፤

የባህል ሐኪም፡- አቶ ጌጡ[69]

ታካሚ፡- ሀ

የባህል ሐኪም፡- ተረኛ ግባ!

ታካሚ፡- ወድህ ነኝ አለሁ፤ ደህና አደራችሁ!

የባህል ሐኪም፡- እግዛሄር ይመስገን! እሷ ላይ አረፍ በል። ምን ፈልገህ መጣህ?

ታካሚ፡- ሆዴን ነፍቶ ይዞ፤... መቀሳቀስ ከለከለኝ፤

የባህል ሐኪም፡- ተየት ነው የመጣህ፤ (የባህል ሐኪሙ በአዘኔታ መልክ ታካሚያቸውን እያዩ ጥያቄያቸውን ቀጠሉ፤ በማስታወሻ ደብተራቸው ስምና አድራሻ አልፃፉም)

---

[68]የደቡብ ጎንደር ዞን የባህል ሐኪሞች እና ማኅበረሰቡ ውስጣዊ የሕመም ስሜቶችን ከውጫዊ የሰውነት አካል ቦታዎች (ቆዳ፣ ጥፍር፣ ፀጉር፤) መለየት እንደሚቻል የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል። የሕክምና ሂደቱም ውጫዊ አካልን በማየትና በመዳሰስ (በማሸት) በሁለት መልኩ እንደሚተገበር የባህል ሐኪሞች ገልጸዋል። ከሰውነት አካሎቻችን መካከል ከእጅና እግር መዳፍ መስመርና ቦታዎች ሃምሳ አንድ (51) የውስጥ አካል በሽታዎችን መለየት እንደሚቻል አስረድዋል። በተለይ የፊት አካል (ቅንድብ፣ ጉንጭ፣ አፍንጫ)፣ ዓይን፤ ጥፍር፣ ጆሮ፤ ምላስ በዋናነት ይጠቀሳሉ፤ ከሰውነት አካል የሚወጡ ፈሳሾች (ሽንት፣ ደም፣ ላብ፣ ንፍጥ) እና ዓይነ ምድር የሕመሙን ምልክት ዓይነትና ደረጃ ጠቋሚ ተደርገው እንደሚቆጠሩ፤ መክረዋል (መሪጌታ ባሕረጥበብና የተቡው አባላት፣ ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣና 23/06/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። በዚህ ዘርፍ ቀጣይ ምርምሮች፤ የባህል ሕክምና የምርመራ ሂደትና አተግባር፤ በመጠናዊና ዓይነታዊ የምርምር መስኮች ቢፈተሽ፤ በዘመናዊ ሕክምና ቤተ-ሙከራ ውጤታማነቱ በንጽጽር ቢቃኝ፤ በአገራችን የሚተገበረው የባህል ሕክምና ዕውቀት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል።

[69]በፋርጣ ወረዳ በክምር ድንጋይ ከተማ፤ 03 ቀበሌ በቀን 20/06/2011 ዓ.ም፤ ከጧቱ 2፡50፣ ጀምሮ፤ ከባህል ሐኪም አቶ ጌጡ ነጋሽ እና ከታካሚ (ሀ) ጋር የተካሄደ የምርመራ ይዘት ክዋኔ።

ታካሚ፡- ተስማዳ

የባህል ሐኪም፡- ሰውነትህን ምን ይሰማሃል?

ታካሚ፡- ሆዴን፤ ሆዴን ነው! እዚህ ሆዴ ላይ ቅብትት አርጎ ነፋቶ ይዞኛል፤ እጀራ ሲሸተኝ ወደ ላይ ይጓጉጠኛል [ማቅለሽለሽ]...(የታካሚ ትንፋሽ ይቆራረጣል፤ በእጁ የሆዱን አካባቢ በማሳየት)

የባህል ሐኪም፡- ሕመሙ ሲነሳብህ እንዴት ያረግሃል?

ታካሚ፡- ሲነሳብኝ ምጥ እንደያዛት ላም ተመሬት ጧ አድርጎ ይዘርረኛል፤...ቆየት ይልና ክልብሽ፤ ክልብሽ [እንደ ማስታወክ] እያለ ልቤን [ይፍቀኛል] ይመታኛል፤ ...ባፌ አስር ጊዜ ምራቂ ግጥም እያለ፤ ጢቅ! ጢቅ! [ምራቁን ስተፋ] ስል ነው፤ እምውል፤

የባህል ሐኪም፡- ምን ያህል ጊዜ ሆነህ?

ታካሚ፡- አይ!...አሁን ነው የባሰኝ፤ ሄድ መጣ እያለ፤ ...ጥቅምት ሚካኤል ለት [ቀን] ነው፤ ገበያ ውዬ ስመለስ የጀመረኝ፤...ስንት ሆነ ማለት ነው? ...አራት ወር ጥር ሚካኤል አለፈኝ፤

የባህል ሐኪም፡- ሕመሙ ከርሞብሃል፤ ምን ዓይነት ምግብ ይበላሃል?

ታካሚ፡- ከወር ወዲህ ነው የባሰኝ፤ እንደልቤ ያገኘሁትን አልበላም፤ ለምላስ የጣመችውን [ጣፋጭ የሆነ] ብቻ ነው የምቀምስ፤ ...ሻይ እና በዉኃ ተበጥብጦ እሚጠጣው ጆሊ ጁስ ነው፤ ተጉሮሮዬ የሚወርድልኝ፤ ሌላ ምግብ ሲሸተኝ ሆዴ ይናወጣል፤ ባፌ ምራቅ ግጥም ይልና፤ የበላሁት ይወጣል [ማስመለስ]፤ ትንሽም አይቆይልኝ፤

የባህል ሐኪም፡- የሽንትህ ቀለም ምን ዓይነት ነው? ስትሸና አረፋ አለው?

ታካሚ፡- ተወትሮው ይለያል፤ የገረጣ [ወደ ቢጫ ቀለም የተለወጠ] ቅጠል ይመስላል፤ ይሄን ቢጫውን ማዳበሪያ መልክ አለው፤...ስሸና እንደ ሳሙና አረፋ አለው፤

የባህል ሐኪም፡- ከመቀመጫቸው ተነሱና፤ መጀመሪያ የወጣቱን የእጅ ጣት ጥፍሮች ገልብጠው፤ በአውራ ጣታቸው ከአስሩ ጣቶች መካከል ጎላ ብለው የሚታዩ ስድስቱን የጣት ጥፍሮች ጫን ጫን አድርገው አዩ። በጣት ጥፍሮቹ ላይ የሚታይ ቀለም ቢጫ መሆን/አለመሆኑን አረጋገጡ፤ "ጤነኛ ቢሆን ስትነካው ነጭና ቀይ ይሆናል" ለዚህ ጥናት አቅራቢ ሲያስረዱ፤ ሁለተኛ የታካሚውን ዓይን ገልጠው፤ "እስቲ ወደ ቀኝ ተመልከት፤ ወደ ግራ፤ ወደ ላይ፤ ወደታች፤ በል ዓይንህን መልሰው [ተስተካከል]፤ ጠቅላላ አልብሳው ቢጫ ሆኗል። ወይኔ ልጄን! ተጫውታበት!" በማለት እጃቸውን አፋትገው ጠራርገው አራገፉ፤ ሶስተኛ የታካሚውን አፍ በማስከፈት የምላሱን መደብ ቀለም ከላይ አረጋገጡ፤ ቀጥለው ታካሚው በጠመጠመው ሻርፐ ጫፍ ምላሱን ቆንጥጠው በመያዝ፤ ወደ ጎን ገልብጠው፤

የምላሱን ሰንበርና መስመር መጥቆር ካረጋገጡ በኋላ፤ "ና ጉድ ተመልከት ምላሱ ላይ ሰርታበት፤ የወፏ መልክ [ቅርፅ] ነው፤ በሆዱ እንቁላሏን ጥላለች ወደ ጭቅላቱ አልሄደችም፤ ቶሎ ደርሰሃለ፤ ሳምት ቢቆይ አይተርፍም፤

በማለት ለጥናቱ አቅራቢ አስረድተው፤ ምርመራቸውን[70] ጨርሰው ወደ ወንበራቸው ተመልሰው ተቀመጡ፡፡ እንደ አቶ ጌጡ መረጃ፤ ከሰውነት አካል፤ ምላስ፣ ዓይን፣ ጥፍርና ጣት፣ ጆሮ፣ ቅንድብ፣ ዓይነ ምድር፣ ሽንት እና የፊት ቆዳ ውስጣዊ ጉዳትና ሕመምን ለመለየት፤ ዋና ዋና ቦታዎች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ በተለይ "ምላስ የሰውነት አካል ሥር መሰረት ነው" ይላሉ፡፡ የምላስ መደብ፤ መቅላት፣ መጥቆር፣ ነጭ መሆን፣ መሰንጠቅ፣ መሸብሸብ፣ መተርተር፣ መሳሳት፣ መቆራረጥ እራሱን የቻለ መልክና ግብር፤ ሥራና ተግባር፣ ይዘትና ባሕርይ እንዳለው ጠቁመው፤ የወፍ (የጉበት) በሽታን ለመለየት፤ የምላስ የደም ሥር ተገልብጦ ሲታይ፤ የደም ሥሩ አቀማመጥ፣ መቅላትና መጥቆር፤ መወፈርና መቅጠን፤ መደበኛ መስመሩን መሳት፣ የተለየ ቅርጽ ማውጣት የበሽታውን ሁኔታና የጉዳት ደረጃ ለመለየት እንደሚያስችል፤ (ቃ.መ፤ 20/06/2011 ፋርጣ) ገልጸዋል፡፡

ፎቶ ግራፍ 2፡- ባህላዊ የወፍ (የጉበት) በሽታ ምርመራ ሂደትና አተገባበር



የዓይን ምርመራ ሂደት



የምላስ ምርመራ ሂደት

ምንጭ፡- የባህል ሐኪም አቶ ጌጡ ነጋሽ፤ በፋርጣ ወረዳ ክምር ድንጋይ፤ በቀን 20/06/2011 ዓ.ም በጥናቱ አቅራቢ የተነሳ፤

[70]በዚህ ክፍል የ"ወፍ"/የጉበት በሽታ መለያና መመርመሪያ ዘዴን የተመለከተ ሲሆን፤ የመድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ ይዘት፤ በምዕራፍ ሰባት በንዑስ ክፍል 7.5 የቀረበ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፤ አቶ ደርሶ እና መሪጌታ መኅሪ ውስጣዊ ሕመምን፤ ከውጫዊ አካላችን እጅ፣ እግር፣ ግንባር፣ ዓይን፣ ከንፈር፣ አፍንጫ፣ ጆሮ፣ ቅንድብና የፊት ገፅ፤ በማየት የተለያዩ በሽታዎችን እንደሚለዩ ጠቁመው፤ የአፍንጫ መሃል ሲጠቁርና ማዲያት ሲያወጣ የሆድና የማኅፀን ጉዳትን፤ የመተንፈሻ አካል ችግር የአፍንጫ ጫፍ መቅላትን፤ የልብ ችግር ከሆነ የግንባር መጥቆር፣ መሸብሸብና መቅላትን፤ የኩላሊት ሕመም ከሆነ የጆሮ እና የአፍንጫ ጫፍ መቅላት፤ ምላስ፣ ዓይን፣ ጥፍርና መዳፍ ደግሞ የጉበት፤... ሕመም ምልክቶች እንደሆኑ ጠቁመዋል። የሆድ ውስጥ ትላትል፤ ሆድ መንፋት፣ ማቅለሽለሽ፣ ከንፈርን ነጭ ማድረግ፣ ፊንጢጣ ማሳከክ፣ ከዓይነ ምድር ጋር አብሮ መውጣት፤ መለያ ባሕርያቸው እንደሆነ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 03/02/2011 እብናት፤ 28/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

እንደ Sofowora እና Leung መረጃ፤ የባህል ሐኪሞች ውስጣዊ ሕመምን ለማወቅ ውጫዊ የሰውነት አካል ምልክቶችን በማጤን፣ ይዘትና ተግባራቸውን በመለየት ባህላዊ ምደባና ፍረጃ እንዳላቸው ገልጸዋል (1982; PP.29-30: 2010; PP.3-5 በቅደም ተከተል)። የባህል ሐኪሞች ውስጣዊ ሕመምን ከውጫዊ የሰውነት አካል ምልክት በመውሰድ፤ የበሽታ ዓይነት፣ ተግባር እና ባሕርይን እንደሚለዩ፤ ከሰውነት አካል ዓይን፣ ምላስ፣ ጆሮ፣ ግንባር፣ ጉንጭ፣ አገጭ፣ ቅንድብ፣ አፍንጫ፣ የእጅና እግር ሥሮች፤ በሽታን ለመለየት ተመራጭ ቦታዎች እንደሆኑ፤ የመስክ ምልከታ መረጃዎች ጠቁመዋል። በአጠቃላይ በእይታዊ ምርመራ ሂደት የበሽታን ዓይነት፣ መጠን፣ ተግባር፣ ሁነት፣ ድርጊት፣ ጉዳት እና ባሕርይን መለየት እንደሚቻል፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል።

### ለ) ክሊኒካዊ የምርመራ ዘዴና አተገባበር

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ "የልብ ምቱ ቀንሷል፤ ሰውነቱ ቀዝቅዟል፤ ግንባሩ ያተኩሳል፤ እግሩን ሽምቆ ይዞታል፤ አጥንቱ ተሰንጥቋል፤..." ይባላል (አቶ ክንዳለም እና አቶ ምትኩ፣ ቃ.መ፤ 20/06/2011 ፋርጣ፤ 28/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

ደብተራ መልኩ፤ በሰው ተደገፎ፣ ደክሞ ወይም መናገር ተስኖት የሚመጣ ታካሚ ሲመረመር የልብ ምቱን፣ የሰውነት ሙቀት መጠኑን፣ የጉዳት ዓይነቱን ለማጤን፤ የልብ ምት ሥርዓቱን፣ የትኩሳት መጠኑን፣ አቅምና ጉልበቱን፣ ጥንካሬና ድካሙን፣ የጡንቻ አወራረዱን፣ የደም ሥር ትርታውን፤ በማረጋገጥ አካላዊ ዳበሳና ዳሰሳ በማካሄድ በሽታን መለየት እንደሚቻል ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ)። እንደ አቶ ደርሶ ገለፃ፤ "ሕጻናት የታመሙትን ነገር መናገር

ስለማይችሉ፤ በቀላሉ ሕክምና ለመስጠት" እንደሚያዳግት ጠቁመው፤ የሕመሙን ዓይነት፣ መነሻ ምክንያትና ባሕርይ ለመለየት፤ ሰውነታቸውን መዳበስ፣ የደም ሥራቸውን መፈተሽ፣ መገጣጠሚያ አጥንታቸውን ማረጋገጥ፣ አተነፋፈስ ሥርዓታቸውን ማዳመጥ፣ የልብ ምት ሂደትና ፍጥነቱን መከታተል፤ በሽታውን ለመለየት እንደሚያስችል አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 03/02/2011 እብናት)፡፡ መሪጌታ ስዩም፤ "የሞኝ ባገኝ" ሕመም በመዳበስና በመዳሰስ መለየት እንደሚቻል እንደሚከተለው ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 04/02/2011 እብናት)፡፡

> ሞኝ ባገኝ [ማንጅራት ገትር/መነጃይት] በፀሐይ ጨረር ውጋትና ፍላት ይነሳል፡፡ ፀሐይ ላይ ቁጭ ብለው ሲነሱ እራስ ያዞራል፣ መሬቱ ይጨልማል፡፡ ታካሚው ሲጠየቅ 'እራሴን ያዞረኛል፣ ሰውነቴን ብርድ ብርድ ይለኛል' ሲል ትኩሳቱን ለማወቅ ግንባሩን፣ ደረቱን፣ ብብቱን በእጅ ዳብሰህ ትለያለህ፡፡ የግንባሩን ደም ሥር ፈልገህ ጫን ጫን ስታደርግ ግትር ይላል፤ ደሙ አይሄድም፡፡ ከዚህ በኋላ ግራ ክንዱን በመቀነት አስረህ፤ በእጁ መታጠፊያ ያለውን የደም ሥር አሸት አሸት፤ ጫን ጫን፤ መታ መታ ስታደርገው፤ ሞኝ ባገኝ ከሆነ ሰንበሩ እንደ ዘንዶ ይጋደማል፤ መልኩ ጥቁር ይሆናል፡፡ ቤሳ [ምላጭ] ሰብረህ ጠቅ! ስታረገው ፊን... ብሎ ወደ ሰማይ ይወጣና ይወርዳል፡፡ የደሙ ጥቁረት ጥቀርሻ ይመስላል፡፡... የክንዱን ቋጠሮ ሳትፈታ ክንዱን ቀጥ አድርገህ ትይዝና ደሙን ታያለህ፤ የተበላሸው ደም ፈሶ ሲያልቅ መልኩን ቀይሮ፤ የቀይ ዳማ ወይም አጋም መስሎ ንጹህ ደም ሲመጣ የተጠበሰ ነጭ ሽንኩርት እና ጥጥ አድርገህ የተበጣው ላይ ታስራለህ፡፡ ታካሚው ወዳው ተነስቶ ይሄዳል፡፡... ሞኝ ባገኝ የቆላ በሽታ ነው፡፡

በማለት አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በላይ የቀረቡ የመስክ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ክሊኒካዊ ምርመራ ሲባል፤ በዳበሳ፣ በንክኪ፣ በማሸት፣ በማጠፍና በመዘርጋት፣ በመጨበጥና በማላላት፣ በመጫንና በመልቀቅ፤ የአተነፋፈስ ሥርዓት፣ የልብ ትርታ፣ የደም ዝውውር፣ የጡንቻ መሸማቀቅ፣ የጅማት መሳሳብ፣ የእግር ወለምታ፣ የትኩሳት መጠንን ለመለካት፣ የተለያዩ የበሽታ ምልክቶችን ለማረጋገጥ እና መረጃ ለመሰብሰብ ሲባል፤ የሕክምና ስልቱ እንደሚተገበር ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

ሐ) ባዮሎጂካዊ ምርመራ

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የተለያዩ በሽታዎችን ለመለየት፤ የስሜት ሕዋስን ተጠቅመው፤ በማሽተት፣ በማሸተት እና "በማስቀመስ" የሕመሙን ዓይነት ለመለየት ጥረት እንደሚያደርጉ የመስክ መረጃዎች አስረድተዋል፡፡ ለምሳሌ፡- "ክንድህን ጥባው፤ ሽንትህን ቅመሰው፤ ምን ምን አለህ? ዓይነ ምድሩ ደም ቀላቅሏል፤ በጣም ይሸታል፤ የቁስሉ ግማት አያስደርስም፤ ..." ይባላል (አቶ ሞገስ 22/06/2011 ፋርጣ)፡፡ በክለሳ ድርሳናት እንደተጠቀሰው፤

ባዮሎጅካል ምርመራ በዘመናዊ ሕክምና የተለመደ ቢሆንም በባህል ሕክምና ባለሙያዎች ተግባራዊ እንደሚደረግ ምሁራን ጠቁመዋል፡፡

አቶ ታከለ፤ በባህል ሕክምና ልማድ የሕመም ዓይነትና ባሕርይን ለመለየት ከውጫዊ አካል ቁስል ጀምሮ እስከ ውስጣዊ የሰውነት አካልና ስሜት የሚደርስ የምርመራ ሂደቶች እንዳሉ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 04/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ አቶ ደርሶ (ቃ.መ፤ 03/02/2011 እብናት) ደግሞ፤ የስኳር በሽታ የምርመራ ዘዴ እና አተገባበር ይዘትን እንደሚከተለው አስረድተዋል ፡፡

> የስኳር ሕመምን ለማረጋገጥ መጀመሪያ የታካሚው የምግብ ፍላጎት ይጠየቃል፡፡ 'ቶሎ ቶሎ ይርበኛል፤ ሽንት ሽንት ይለኛል' ሲል የስኳር በሽታ ሊሆን እንደሚችል ይጠረጠራል፡፡... የስኳር በሽታ መሆንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ፤ አንደኛ ክንዱን እንዲጠባ ታደርጋለህ፤ ክንዱን ሲመጥ ከጣፈጠው ስኳር ነው፤ ጨው ጨው ካለው ስኳር አደለም፡፡ ሁለተኛ ሽንቱን እንዲቀምስ ይደረጋል፤ ሽንቱን ሲቀምስ ከጣፈጠው፤ የስኳር ሕመም ምልክት ይሆናል፤ ከጎመዘዘው እና ክርፋት ካለው፤ የስኳር ምልክት አይሆንም፡፡ ሶስተኛ ሽንቱን ንቦች እና ጉንዳን በሚገኙበት አካባቢ በሳህን ማስቀመጥ ነው፤ ሽንቱ የስኳር ጣዕም ካለው፤ በሳህኑ ዙሪያ ከበው ይቀስማሉ፤ የስኳር ጣዕም ከሌለው አይጠጉትም፤ በተመሳሳይ መልኩ የታካሚውን ሰው ሽንት ወስደህ በጥቁር ድንጋይ ላይ ማፍሰስ፤ የስኳር በሽታ ከሆነ ድንጋዩን ዝንብ ይወረዋል፤... ሽንቱ ሲደርቅ ዱቄት የተደፋበት ይመስላል፡፡ ቦታውን የጉንዳን ሰራዊት ይወረዋል፡፡ በመጨረሻም፤ የስኳር ሕመም ያለበት ሰው ዓይነ ምድር ከሌላው በተለየ በዝንብ፣ በጉንዳን እና በተለያዩ ነፍሳት ይወረራል፤ በሰውነቱ ላይ ቁስል ይወጣል፡፡ በዚህ ደረጃ ታካሚ ቢመጣ ለማዳን ይከብዳል፡፡

በማለት ገልፀዋል፡፡ የስኳር ሕመምን ለማረጋገጥ ታካሚው ክንዱን እንዲጠባ፣ ሽንቱን እንዲቀምስ፣ ንብ እና ጉንዳን በሚገኙበት አካባቢ ሽንቱን ወስዶ በዕቃ በማስቀመጥ፣ በጥቁር ድንጋይ ላይ ሽንቱን በመድፋት፤ ዓይነ ምድሩ በዝንብ እና መሰል ነፍሳት መወረርና አለመወረሩን በማረጋገጥ በሽታውን መለየት እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡ በአጠቃላይ የባህል ሐኪሞች ውስጣዊ ሕመምን ለመለየት፤ በሰውነት አካል ላይ ምልክት ማግኘት ለሚከብዱ የሕመም ዓይነቶች የስሜት ሕዋስን በመጠቀም ምርመራ እንደሚያደርጉ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ የስኳር ሕመምን ለመለየት፤ ክንድ ማስመጠጥና ሽንት ማስቀመስ፤ ንብ፣ ጉንዳን እና ዝንብ በሚገኙበታ ቦታ ሽንት ማስቀመጥና መድፋት፤ በድንጋይ ላይ ማፍሰስ የሕመሙን ዓይነት ለማረጋገጥ አማራጭ መንገዶች መሆናቸውን፤ ለማጤን ተችሏል፡፡

### መ) የታካሚን ዳራና አጠቃላይ ጤንነት ለመገንዘብ የሚደረግ ምርመራ

የባህል ሐኪሞች የታካሚያቸውን ቀደምት ታሪክ፣ የሕመም ዓይነት፣ ማኅበራዊ ሁኔታ፣ ግንኙነት፣ ሃይማኖት፣ ሥነ ልቡና፣ አካባቢያዊ ልማድን መነሻ በማድረግ ተስፋ መስጠት፤ ማወያየት፣ ማበረታታት፣ እገዛ ማድረግ፤ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ምሳሌዎችን በማቅረብ ጽናት እና ብርታትን መስበክ፤ ሕመምን በፀጋ መቀበልና ማስታመም፤ አዕምሯዊ እረፍት እንዲያገኙ ማጫወት፤ "ሞት" ሥጋዊና ምድራዊ ዓለም መሆኑን አምነው እንዲቀበሉና ለዘላለማዊ ሕይወትና ፅድቅ ንስሃ እንዲገቡ መምከርን ይመለከታል (መሪጌታ መኅሪ እና መሪጌታ ዘላለም፤ ቃ.መ፣ 27/01/2011 ሊቦ ከምከም፤ 20/04/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

መሪጌታ በረከት እንደ ዝሆኔ፣ ጋንግሪን፣ ሪህ፣ የስኳር፣ የነቀርሳ እና የአዕምሮ ሕመም ታካሚዎች ክትትልና የእለት ውይይት እንደሚፈልጉ ጠቅሰው፤ ሃይማኖታዊ ፀሎት፣ "ምህረት እንዲያገኙ ለቤተክርስቲያን መሳል" ፀበል ቦታ መውሰድ፣ መፍትሔ መሆኑን አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 20/03/2011 እብናት)። አቶ ሞላ ደግሞ፤ "ማረኝ እንጂ አትመመኝ አይባልም" ይላሉ። ታካሚዎችን ማፅናናት፣ በየዕለቱ ማነጋገር፣ የሚበሉትንና የሚሰሩትን ማወያየት፣ የግል ባሕርያትን ማጥናት፣ የሌላን ሰው ድኅነትና ፈውስ ማውራት፣ በእግዚአብሔር ፈቃድና ስጦታ መኖራችንን ማስታወስ ተገቢ መሆኑን ጠቁመው፤ ሕመም የአካላዊ ሥጋ ስቃይ፣ የመንፈስ መታወክና መድከምን ሲያመለክት ድኅነትና ፈውስ ደግሞ የመንፈስ ብርታትና ፅናትን፣ መታደስን፣ ለንስሃ መብቃትን፣ "ከሐጢያት"[71] መውጣትን፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብን፣ ፆም/ፀሎት ማድረግን፤ እራስን ማረጋጋትና በፀጋ መኖርን የምህረቱ በረከት ተደርጎ እንደሚቆጠር (ቃ.መ፤ 22/06/2011 ፋርጣ) ገልጸዋል።

በአጠቃላይ የባህል ሐኪሞች የታካሚን የሕይወት መሰረት፣ ታሪክና ማኅበራዊ ግንኙነት በማጤን፤ የሕመሙን ባሕርይ በመገንዘብ፤ የታካሚን ሥነ ልቡና ማበረታታት፣ መደገፍ፣ ማጽናናት፣ ተስፋ መስጠት፣ ዘላቂ ቀረቤታ መመስረት መገለጫ ተግባራቸው እንደሆነ ከመስክ መረጃዎች ትንታኔ ይዘት መገንዘብ ተችሏል። መንፈሳዊ የበሽታ መለያ ዘዴዎችና አተገባበር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

[71] በዚህ ዐውድ ከሕመም መዳንና መፈወስን፣ ለፈጣሪ ምስጋና ማቅረብን፣ ንስሃ መግባትን ይመለከታል።

### 6.1.2 መንፈሳዊ የበሽታ መለያ ዘዴዎችና አተገባበር

መንፈሳዊ የበሽታ መለያ ዘዴዎች በዓይነት፣ በተግባር፣ በባሕርይ የተለያዩ ቢሆኑም በተዋርሶ (በትምህርት)፣ በኮከብ ቆጥራ እና በመለኮታዊ ኃይል ፀጋና በሕልም ዕውቀቱን እንደሚያገኙ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል። ዐበይት የሚባሉ መንፈሳዊ የምርመራ ዘዴዎችና አተገባበር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሀ) አሾክሿኪ፦ በተዋርሶ ትምህርት የሚገኝ መንፈሳዊ ጥበብ ሲሆን፤ በጎረቤት፣ በሰፈር፣ በአካባቢ፤ የሚሰሩ፣ የሚወሩ፣ ግጭትና መረጃዎችን ሰብስቦ የሚያመጣ ታዛዥ ጋኔል ሲሆን የሕመሙን መንስኤ (በዛር፣ በቡዳ)፣ ዓይነት፣ መለከፊያ ቦታ፣ ለፈውስ "የሚበጀውን" ዕፀ መድኃኒት በጆሮ ቀርቦ "ሹክ የሚል፣ የሚያነጋግርና ምስጢሩን የሚጠቁም፤... ሲጠራ የሚመጣና ሲታዘዝ የሚሰራ የተገዘተ አገልጋይ ጋኔል" እንደሆነ ጠቁመዋል (ሊቀጠበብት አብርሃም፤ ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም)። በሰው አካል ላይ የሚደርሱ የቁስል መንስኤ፣ ውስጣዊ ሕመምን ለመለየት፤ መፈወሻ መንገዱን ለማወቅ፤ መድኃኒት ቆርጦና ቀምሞ ለመስጠት፤ መፍትሔውንና ምስጢሩን በማስረዳት ጉልህ ተግባር እንዳለው ገልፀዋል (ደብተራ መልኩ፤ቃ.መ፤ 23/01/2011 ፋርጣ)።

ለ) አፈ ሕጻን፦ ማለት በሕጻን ልጅ አንደበት የሚነገር፣ የሚገለጽ፣ የሚዘረዝር እና የሚቀርብ መረጃን ይመለከታል። ይህ መንፈሳዊ ጥበብ በተዋርሶ ትምህርት የሚገኝ ሲሆን ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ወይም ለፆታዊ ግንኙነት ያልበቃ ሕጻን ልጅ አቅርበው፤ ከሕጻን ልጅ ንግግር ለሕመሙ ዓይነት፣ መንስኤ እና መፈወሻ መንገድ መረጃ መሰብሰብ እና ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል። በሕጻን ልጅ ንግግርና አንደበት ተመስሎ የሚቀርብና የሚናገር ታዛዥ ጋኔል መኖሩን ገልጸዋል (መሪጌታ ፋንታሁን እና መሪጌታ መንግስቱ፣ ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ፤ 11/04/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

በማኅበረሰቡ ወይም በባህል ሐኪሞች እሳቤ "ባልባለቀ ሕጻን [ለጾታዊ ግንኙነት ያልደረሰ] አንደበት የሚነገር፤ ዕፀ መድኃኒት ማሰብሰብና ውኃ ማስቀዳት" የተለመዱ ተግባራት እንደሆኑ (መሪጌታ አዲሱ እና ደብተራ መኅሪ፤ ቃ.መ፣ 19/01/2011 እና 13/03/2011 ፋርጣ እና እብናት በቅደም ተከተል) ጠቁመዋል። በተለይ ለፆታዊ ግንኙነት ያልደረሱ ልጆች "ንፁሕ ናቸው" ተብሎ በማኅበረሰቡ ይታመናል። ድንግልና የተፈጥሮ የኃይል ምንጭና አቅም፣ የንፅሕና መሰረት፣ የፀጋና የበረከት እድሜ ተደርጎ ስለሚታሰብ፤ በስሜት ተገፋፍተው ሥጋዊ ፍላጎት አድሮባቸው

ሐጢያት አይሰሩም፤ የዚህን ዓለም ተንኮል አይረዱም፤ ክፉና ደጉን አይለዩም፤ የተፈጥሮ ኃይልና ፀጋቸውን ይዘው ስለሚገኙ፤ ሕሊናቸውን የሚያስት፣ ሃሳባቸውን የሚያስቀይር አጋንንት አይቀርባቸውም ተብሎ ይታመናል። ፆታዊ ግንኙነት መጀመር ከተፈጥሮ ባሕርይ መሰረት ያርቃል/ያፋታል፣ ፀጋና ኃይልን ያሳጣል፣ ክብርና ሞገስን ያጠፋል፣ አካላዊ ድክመትን ያመጣል፣ የኃጢያት መንገድን ይከፍታል፤ ተብሎ እንደሚታሰብ መሪጌታ ልሳነወርቅ ያስረዳሉ (ቃ.መ፤ 27/04/2011 ሊቦ ከምከም)። በመንፈሳዊ ኃይል በመታገዝ ከሕጻን ልጅ ንግግር መረጃ መሰብሰብ፣ ዕፀ መድኃኒት ማስቀረጥ፣ ለዕፀ መድኃኒት መቀመሚያ የሚውል "ወፍ ያልቀመሰው ዉኃ" ማስቀዳት፤ የፅዳት፣ የንፅሕና እና የበረከት ተምሳሌት ተደርገው፤ በማኅበረሰቡ እንደሚታሰቡ መገንዘብ ተችሏል።

**ሐ) አዕጋረ ፀሐይ** (የፀሐይ እግር/ ጨረር)፡- አዕጋረ ፀሐይ በመንፈሳዊ ተዋርሶ፣ ፀሎትና ትምህርት የሚገኝ መንፈሳዊ ጥበብ መሆኑን ደብተራ ጥላሁን እና መሪጌታ ዘላለም ጠቁመው፤ መጠኗ ክብና የፊት መስታወት የምትመስል ከመዳፍ ያነሰች መመርመሪያ "አጋንንት መመልከቻ" መሳሪያ ስትሆን፤ የታካሚውን ግንባር፣ ምላስ፣ አንገት፣ ደረት እና እጅን በመስታወቷ አስተካክሎና አነጣጥሮ በማየት፤ የበሽታውን መንስኤ፣ ቦታ፣ ባሕርይ፣ መለከፍያ መንገድን መለየት እንደሚቻል፤ ይገልጻሉ። ይህ ተግባር በመንፈሳዊ ትምህርትና ተዋርሶ በመታገዝ አጋንንት ማናገር፣ መሳብ፣ ማዘዝና ማሰራት ሲሆን፤ አጋንንት በቁሷ (በመስታወቷ) ላይ አድረውና ተመስለው የታዘዙትን ይሰራሉ፤ የተሰወረ ጥበብና በሽታን ይገልጻሉ፤ የፈውስ ዓይነቱን ይናገራሉ፤ ተብሎ ይታሰባል። የአዕጋረ ፀሐይ መንፈሳዊ ጥበብና ተዋርሶ ወደ ቤተሰብና ሶስተኛ ወገን የማይተላለፍና የማይሸጋገር ሙያ ሲሆን፤ ዕውቀትና ተግባሩ በጥቂት ሰዎች እጅ፤ እንደሚገኝ ይነገራል (ደብተራ ጥላሁን እና መሪጌታ ዘላለም፣ቃ.መ፤ 03/03/2011 ሊቦ ከምከም፤ 20/04/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)። መንፈሳዊ ጥበቡን ለመማርና ለመዋረስ፤ አጋንንት ለመሳብ፣ ለማናገርና ለማዘዝ የረጅም ጊዜ ፀሎት፣ ትምህርት፣ ተስፋ፣ ትጋት፣ ጥረትና ትዕግስት እንደሚያስፈልግ አሰፋ (2008) ጠቁመዋል።

**መ) የዐየሩ ጼጥሮስ**፡- የዐየር መዛባት፣ መቃወስ፣ የወቅት መዛነፍ፣ የወረርሽኝ መከሰት፣ የንፋስ መብዛትና ማነስ ሥርዓትን የሚቆጣጠር፤ የዐየሩን ዓለም አስተዳዳሪና ገዢ፤ የመናፍስት ሁሉ የበላይ ተቆጣጣሪና አለቃ ተደርጎ ይታሰባል። ድርቅ ሲከሰት፣ ርሃብ ሲወርድ፣ ወረርሽኝ ሲነሳ፤ ዐየሩን የሚቆጣጠሩ፣ ምህረት የሚጠይቁ፣ ሥርዓቱን የሚተገብሩ፣ ምክንያቱን የሚያስረዱ፤ በፀሐይ፣ በዐየር ንብረት ለውጥ፣ በፈጣሪ ቁጣና በሰዎች ኃጢያት የመጣ ክስተት

መሆን/አለመሆኑን የሚለዩ፤ ሥልጣንና ኃይላቸው በዐየር ሥርጭትና ግንኙነት መረብ ላይ የሚያተኩሩ ተግባራትን ይመለከታል። በማኅበረሰቡ ላይ ይደርሳል ተብሎ የሚፈራው የተፈጥሮ አደጋና ኃይልን አቅጣጫ ማሳት፣ ወደ በርሃ መላክ፣ ከመብረቅ መጠበቅ፣ ከጎርፋና ከወረርሽኝ በሽታ መከላከል (የዐየር ጋኔልን ይመለከታል) ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን እንደሚመለከት ገልጸዋል (መሪጌታ መንግስቴ እና ደብተራ መኅሪ፣ ቃ.መ፤ 10-13/03/2011 እብናት)።

**ሠ) ሞርሞሪዎን፡-** ይህ መንፈስ በወራጅ ወንዝና ባሕር ውስጥ የሚገኝ  የውኃን ዓለም ተቆጣጣሪና አስተዳዳሪ፣ አለቃና ተጠሪ፣ ኃይልና ሥልጣን ያለው፤ ግዛቱ በወንዝና በባሕር የተገደበ እንደሆነ መሪጌታ ስዩም እና መሪጌታ ስንታየሁ (ቃ.መ፣ 04/02/2011 እና 14/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል) ጠቁመዋል። ይህ ጥበብ በመለኮታዊ ተዋርሶና ትምህርት የሚገኝ ሲሆን፤ ጅን ለመጥራት፣ ለማዘዝ፣ ለማስወጣትና ለመገዘት እንደሚያገለግል፤ ይነገራል። ሞርሞሪዎን በቀትር ሠዓት ከወንዝ ተነስቶ ሰው እና እንስሳትን የሚመቱ ጅን እና የጅን ጭፍሮችን ለመቆጣጠር፤ ባሕር ውስጥ ገብቶ የጠፋ ሰው አስክሬን ለማውጣትና ለመፈለግ፤ የባሕር፣ የወንዝ ጅን እና አጋንንትን ለመቆጣጠር፣ ለመገዘት፣ ለመለመን፣ ለማቋደስ፣ ለማዘዝ፤ በሰው እና እንስሳት ላይ የጣሉትን መቅሰፍት፣ ሕመም እና "ደዌ" ለማስወጣት፤ በወንዝ ዳር የሚቀርቡ መስዋዕቶችን ለማቋደስና ለማዋረስ ሲባል፤ የሚተገበሩ ይዘቶችን ያጠቃልላል። በሰው አካል ላይ የሰፈሩ የጅን አጋንንት ጠርቶ ማናገር፣ ዘራቸውን መጠየቅ፣ ማስነሳት፣ ማስለቀቅ፣ ማስወጣትና ወደ ግዛታቸው መመለስና መላክን ይመለከታል። ሞርሞሪዎን የባሕር ጅን በመጥራት የሕመሙን መንስኤ ለመለየት፣ ታካሚው የሚድን መሆንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ፤ የሚተገበር ሙያ እንደሆነ አስረድተዋል (ከተቡው አባላት መሪጌታ ስዩም ያቀረቡት ሃሳብ፣ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)።

**ረ) ከልከሊዎስ፡-** የመቃብር ጠባቂና አስተዳዳሪ ጋኔል ይባላል። ይህ ጋኔል በጣም ጥቁር፣ ፀጉሩ ሉጫና ረዥም፣ አካሉ ወፍራም መሬት ለመሬት የሚጎተት፣ የፊቱ ወዝ በፀጉሩና በሰውነቱ የሚጠባጠብና የሚጠፈጠፍ "ግማታምና ክርፋታም" እንደሆነ፤ አካላዊ ምስል፣ መልክና ገጹን ይጠቁማሉ። ከልከሊዎስ "ሽማግሌና የትልቅ ሰው አምሳል  ነው" ይባላል። የመቃብር ቦታ አስተዳዳሪ፤ የሙት መንፈስ ጠሪና አናጋሪ ታዛዥ ጋኔል (የመሬት ጋኔል) እንደሆነ ይነገራል። ትልቅ ሰው ሳይናዘዝ በድንገት ሲሞት ሐብቱን ለማወቅ፤ በስውር የተገደለን ሰው ጠላትና ደመኛ ፈልጎ ለማግኘት፤ የተሰወረና የተቀበረ አስክሬን ቆፍሮ ለማውጣት፤ ሐብት ንብረት ደብቆ፣ የሰው ገንዘብ በልቶ እዳ ሳይከፍል "ቢሞት"፤ የሟች ወራሽና ቤተሰቦች እንዲከፍሉ ለማድረግ፤ የሞቱ

ዘመድና ቤተሰቦችን መንፈስ ጠርቶ የሚያገናኝ፣ የሚያናግር፤ የሙት መንፈስ አናጋሪ፣ የመቃብር ጠባቂ፣ አለቃና አስተዳዳሪ እንደሆነ፤ ገልጸዋል (ከተቡው አባላት መካከል መሪጌታ ስንታየሁ ያቀረቡት ሃሳብ፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 አብናት)።

**ሰ) ኮከብ ቆጠራ፡-** በዐውደ ነገስት በመታገዝ የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት አቀማመጥን በማየትና በማጤን፤ በዘመን፣ በዓመት፣ በወቅት፣ በወር፣ በሳምንት፣ በቀንና እና በሠዓት ወቅቶችን በመከፋፈል፤ የሰው ልጆችን ባሕርይ፣ የዕፅዋት (መቼ እንደሚቆረጡ/ እንደማይቆረጡ፤ እንደሚተከሉ/እንደማይተከሉ)፣ የእንስሳት እና የሥነ ምህዳርን ባሕርይ፣ ተግባርና ይዘት ለመመርመር፣ ለመጠቆም እና ለማወቅ የሚደረግ ተግባርን (ደብተራ መጎሪና መሪጌታ አማረ፤ ቃ.መ፣ 13/03/2011 አብናት እና 26/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል) ይመለከታል።

እንደ አቶ ደሴና ደብተራ መልኩ ገለጻ፤ ኮከብ ቆጠራ መለኮታዊ ኃይል እና ዓለማዊ ዕውቀትን በማገናኘት የሚተገበር ሙያ ሲሆን፤ የኮከብ አቀማመጥ፣ ወቅትና ባሕርይን መማር፤ የፊደል ተራ አሰያየምን እና የቁጥር ውክልናን መለየትና ማጥናት የመጀመሪያ ተግባር ቢሆንም አስማታዊ ቃላትን እና ውስብስብ ባሕርያትን መገንዘብ፣ መለኮታዊ ኃይልን መላበስ፤ አስፈላጊ እንደሆነ መክረዋል። በዐውደ ነገስት የኮከብ አቆጣጠር ልማድ፣ ሂደት እና መደብ ከሶስት እስከ ሰላሳ ሁለት ቤት የሚገደፍና የሚቆጠር ይዘት እንዳለው ጠቁመው፤ ኮከብ ቆጠራ ለሕመም መንስኤ፣ ለዓይነ ጥላ፣ ለጠባይ፣ ለእድል፣ ለፍቅር፣ ለሐብት፣ ለንግድ፣ ለዘመን፣ ለአድባር፣ ለፈውስ፤... እየተባለ፤ በተለያየ ይዘትና ዐውድ የሚቆጠሩ ተግባራትን ይመለከታል (አቶ ደሴ እና ደብተራ መልኩ፤ቃ.መ፤ 23/04/2011 ሊቦ ከምከም፤ 23/01/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)። አካላዊ እና መንፈሳዊ ሕመምን ለመፈወስ የሚደረጉ የኮከብ ቆጠራ ተግባራትን ብቻ በመነጠል፤ በዚህ ጥናት ጥቅል በሆነ መልኩ ለመግለፅ ተሞክሯል።

**ሸ) ሕልመ ዮሴፍ፡-** በመለኮታዊ ኃይል፣ በፆምና ፀሎት፣ ፀጋና በረከት በመታገዝ፤ በሕልም የሚታይ፣ የሚነገር፣ የሚገለጥ ምስጢርን ይመለከታል። የታካሚውን የሕመም መንስኤ ለመለየት፣ የበሽታውን ዓይነት ለማወቅ፣ የሕመምተኛውን ደህንነትና አቋም ለማረጋገጥ፣ የመድኃኒት ግብዓት ለማዘጋጀት፣ ለመቀመም፣ ለመስጠትና መመሪያ ለማውጣት፤ በሕልመ ዮሴፍን "ራዕይ" በመታገዝ የሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ ገልጸዋል (መሪጌታ ሠረቀብርሃን እና መሪጌታ አዲሱ፣ ቃ.መ፤ 12/03/2011 አብናት፤ 19/01/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

ከዚህ በላይ የቀረቡ የመስክ መረዳዎች እንደገለጹት፤ በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ዓለማዊ፣ መለኮታዊና ቅይጥ የምርመራ ተግባራትን እንደሚከተሉ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ ዐበይት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ይዘት፣ ምድብና ማሕቀፍ ምስለ መዋቅር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ምስል 11፡- ዐበይት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ምድብና ማሕቀፍ




ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች፤ በጥናት አቅራቢው የተዘጋጀ ምስለ መዋቅር፤ ግንቦት/2011 ዓ.ም

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ዓለማዊ፣ መለኮታዊና ቅይጥ የበሽታ መለያና ምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም የምርመራ አገልግሎት እንደሚሰጡ፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ በዓለማዊ ይዘት ሥር እይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባዮሎጂካዊ፣ የታካሚ ዳራና አጠቃላይ እይታን በማጤን የሚሰጡ የምርመራ ስልቶች እንዳሉ ተገልጿል፡፡ በተጓዳኝ በመለኮታዊ ኃይል ይዘት ሥር በተዋርሶ (በትምህርት)፣ በሥነ ከዋክብት ቆጠራና እና በመንፈሳዊ ኃይል (በሕልምና በፀሎት) በመታገዝ የምርመራ ዘዴዎችን እንደሚያካሂዱ፤ ከዚህም በተጨማሪ ዓለማዊና መለኮታዊ ኃይልን በማቀላቀል ቅይጥ የምርመራ ዘዴዎችን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ (ከተቡው አባላት፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት) ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በባህል ሕክምና ዕውቀትና አተገባበር የበሽታ መንስኤን ለማወቅ፣ ለመለየት እና የምርመራ ዘዴዎችን ለመተግበር እንደ ዘመናዊ ሕክምና (የውስጥ ደዌ፣ የማሕፀን፣ የዓይን፣ የጥርስ፣ ባለሙያ እየተባለ) በየንዑስ ዘርፉ እራሱን የቻለ ሙያ፣ የምርመራ ዘዴ፣ አተገባበር፣ የዕውቀት ምንጭ፣ ዓላማ፣ ተግባርና ይዘት እንዳላቸው መገንዘብ ተችሏል። ከዚህ ይዘት በመቀጠል በምርመራ ሂደት የበሽታዎች ባሕርይ ምድብ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 6.2 በምርመራ ሂደት የበሽታ ባሕርይ ምድብ

በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት (2.1.7) እና በጥናቱ ሥነ ዘዴ (3.6.1) እንደተጠቀመው፤ የባህል ሐኪሞች የበሽታ ዓይነት፣ ባሕርይ፣ ምልክትና ምድብን ለመለየት የሕሙማንን አካላዊ አቋም እና አካባቢያዊ ዐውድን መነሻ በማድረግ ምርመራ እንደሚያካሂዱ ምሁራን ገልፀዋል። በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች አካላዊ ምርመራ ሲያካሂዱ የታካሚን አካልና አቋም በማጤን፤ የበሽታውን ባሕርይ፣ ምልክት፣ ዓይነት፣ ቅጥአባር (መልክ)፣ ዘርና ዝምድናን በመለየት አካባቢያዊ አሰያየም፣ አከፋፈል እና ምደባ እንዳላቸው የመስክ መረጃዎች፤ አስረድተዋል (መሪጌታ ፋንታሁን እና ሊቀጠበብት አብርሃም፣ ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ እና 05/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

Ben-Amos እና Amzat and Razum ባህላዊ እና ዐውዳዊ ጥናቶች ሲካሄዱ የማኅበረሰቡን አካባቢያዊ የቃላት አጠቃቀም፣ አሰያየም፣ አጠራር፣ አከፋፈል እና "ቀያዊ" ምድብን (Local Taxonomy) መነሻ በማድረግ ማሕቀፍ ማዘጋጀትና መተንተን እንደሚገባ ገልጸዋል (1975; PP.167-168: 2014; PP.125-127)። ይህን ታሳቢ በማድረግ በጥናቱ ተተኳሪ ማኀበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች አካላዊ ምርመራ ሲያካሂዱ፤ የበሽታ ዓይነቶችን ለመለየት በዋናነት ምን ምን ቦታዎችን ይፈትሻሉ? የሕመም ዓይነቶችን እንዴት ይመድባሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል።

መሪጌታ ልሳነወርቅ እና ቄስ አብርሃም፤ ከሕሙማን አካል እና አቋም፣ ስለበሽታው ዓይነት፣ ሁኔታ፣ የጉዳት ደረጃ፣ መረጃ ለመሰብሰብ በዋናነት የልብ ምት፣ ሽንት፣ ዓይነ ምድር፣ የሰውነት ቆዳ ቀለም፣ ድምፅ እና ምላስን በመፈተሽ የሕመሙን ዓይነት መለየት እንደሚቻል አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 27/04/2011 ሊቦ ከምከም እና 01/05/2011 እብናት)። ደብተራ መኀሪ ደግሞ፤ ከዓይን፣ ከሰውነት ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ ከእጅና እግር መዳፎች በሽታን መለየትና መረጃ መሰብሰብ እንደሚቻል ጠቁመዋል (ቃ.መ፤13/03/2011 እብናት)። ከነዚህ መረጃዎች በተጨማሪ የደም

ሥር፣ ትውከት፣ የሰውነት ፈሳሽ እና የምግብ ፍላጎት የሕመሙን ዓይነት ለመለየት መነሻ እንደሚሆኑ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች አረጋግጠዋል (አቶ ጌጡ እና መሪጌታ መንግስቴ ከተቡው አባላት መካከል፣ ቃ.መ፤ 20/06/2011 ፋርጣ እና 23/06/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በሕሙማን አካል ላይ ምርመራ ሲያካሂዱ በዋናነት ዘጠኝ ቦታዎችን መነሻ እና መዳረሻ በማድረግ፤ ከልብ ምት፣ ከዓይን፣ ከምላስ፣ ከሰውነት አካል በሚወጡ ፈሣሾች (ሽንት፣ ዓይነ ምድር፣ ንፍጥ፣ ትውከት ላብ)፣ ከሰውነት አካል ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ ከእጅ እና እግር መዳፎች፣ ከደም ሥር መስመሮች፣ ከድምጽ፣ ከምግብ ፍላጎትና ጣዕም ጋር ያለውን መስተጋብር በመፈተሽ፤ ስለሕመሙ ዓይነት፣ ባሕርይ፣ ደረጃ እና ጉዳት መረጃ ሰብስበው የሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ፤ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በሽታዎች ምን ዓይነት ባሕርይ አላቸው?

መሪጌታ ሠረቀብርሃን እና አቶ ደሴ፤ የሕመም ዓይነቶችን ለመለየት እና ለመመደብ የታካሚውን አካል፣ ሁኔታና እንቅስቃሴ ፈትሸው፤ የበሽታውን ምልክት፣ ባሕርይ እና የጉዳት መጠን ማወቅና ምደባ ማካሄድ እንደሚቻል ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት እና 23/04/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)፡፡ ከተቡው አባላት መካከል መሪጌታ ስዩም እና ቄስ አብርሃም በምርመራ ሂደት የታካሚውን ስሜት እና የሕመም ምልክቶችን መነሻ በማድረግ የበሽታዎችን ባሕርይ ምድብ ለይተው፤ የመድኃኒት ዝግጅት፣ መረጣ፣ ቅመማና አሰጣጥ ሂደቶችን እንደሚከውኑ አስረድተዋል (23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)፡፡ በአጠቃላይ የሕመም ዓይነቶች በሁለት ጥቅል ይዘት እና በስድስት ዝርዝር ባሕርያት ምድብ ውስጥ እንደሚካተቱ፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ እነርሱም፤ ድንገተኛ፣ ቆንጣጭ፣ አቃጣይ፣ አብራጅ፣ አንቀጥቃጭ እና አደንዛዥ በመባል የሚጠቀሱ ሲሆን የምደባ ማሕቀፍ ምስለ መዋቅር ይዘት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ምስል 12፡- በባህል ሕክምና ምርመራ የበሽታ ባሕርያት ምድብና ማሕቀፍ




ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች፤ በጥናት አቅራቢው የተዘጋጀ ምስለ ማሕቀፍ ግንቦት/2011 ዓ.ም

ከዚህ በላይ የቀረቡ የበሽታ ባሕርያት ምድብና ማሕቀፍ ይዘት እንደሚያመለክተው፤ የቀስት ምልክቶች በተቃራኒ ምድብ የሚጠቀሱ የበሽታ ዓይነቶችን ለማሳየት፤ በክብ ማሕቀፍ እና በመስመር ተሳስረው የቀረቡ ይዘቶች ደግሞ የበሽታዎችን ባሕርያት ምድብ እና የእርስ በእርስ ትስስር፣ ግንኙነትና መስተጋብርን ለማስረዳት፤ ቀስት የሌለውና ክቡን ማሕቀፍ ለሁለት የከፈለው መስመር የበሽታዎችን ጥቅል የባሕርያት ምድብና ይዘት ያመለክታል፡፡ የበሽታዎች ባሕርያት ምድብ ዝርዝር ይዘትና ተግባር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

### 6.2.1 ድንገተኛ እና አጣዳፊ

ድንገተኛ ባሕርይ ያላቸው የሕመም ዓይነቶች አጣዳፊ፣ ወራሪና ገስጋሽ በመሆን ድንገት ተከስተው ለከፋ ጉዳትና ሞት ይዳርጋሉ፤ ተብሎ በማኅበረሰቡ ይታመናል፡፡ ድንገተኛ ሕመም፤ ውጫዊና ውስጣዊ አካልን በፍጥነት በመዉረር፣ በመቆጣጠር፣ በማዳረስና በማዳከም ትውከት፣ ተቅማጥ፣ ሆድ መቁረጥና መንፋት፤ የደም መጥቆርና መርጋት፣ አክታና የዓይነ ምድር

መለወጥ፤ አካላዊ ድካም፣ ጥድፊያና ውጥረት እንዳላቸው፤ ደብተራ ጥላሁን እና መሪጌታ ዘላለም ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 03/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 20/04/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)፡፡ በዚህ ምድብ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች፤ ድንገተኛ [ሞን ባገኝ/ማጅራት ገትር/መነጃይት]፣ አጣዳፊ ተቅማጥ፣ ወረርሽኝ፣ የሳንባ ምች፣ ኩፍኝ፣ "ዓይነ ወግ" ወይም ቡዳ[72]፣ የዉኃ ንድፍት እና መሰል በሽታዎችን ይመለከታል (ከተቡው አባላት መካከል መሪጌታ ስዩም እና አቶ ደርሶ፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)፡፡

መሪጌታ ባሕረጥበብ፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ ድንገተኛ እና አጣዳፊ ሕመም ሲያጋጥማቸው በቀጥታ ወደ ዘመናዊ ሕክምና ጣቢያ በመሄድ ምርመራ አድርገው መርፌ እንደማይወጉ ይገልጻሉ (ቃ.መ፣ 27/02/2011 ፋርጣ)፡፡ ለምን? ሲባል በዘመናዊ ሕክምና አገልግሎት "የሚታዘዝ መርፌ የአጋንንት መጥሪያ፤ የደም መቃመሻ፣... የሞት መልእክተኛ ነው"[73] ተብሎ ይታሰባል (መሪጌታ ስንታየሁ፣ ቃ.መ፤ 14/03/2011 እብናት)፡፡ መሪጌታ በረከት ደግሞ አንድ ታካሚ በባህል ሐኪም ሳይታይ ወደ ዘመናዊ ሕክምና አገልግሎት በመሄድ መርፌ ቢወጋ፤ በአጋንንት ልክፍት የመጣ ሕመም ከሆነ "ሕመሙ ይደበቃል፣ ይሰወራል፤ ለሞት ይዳርጋል" ተብሎ እንደሚታመን (ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት) አስረድተዋል፡፡

[72]የቡዳ ሕመም በምግብና መጠጥ ምክንያት እንደሚነሳ፤ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ ይታመናል (ከተቡው አባላት መካከል ቄስ ዐቢይ እና ግራጌታ ወንድማገኝ፣ ቃ.መ፤ 19/06/2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት)፡፡ በዘመናዊ ሕክምናም፤ የምግብና መጠጥ መመረዝና መበከል፤ በፀሐይ ጨረርና ሙቀት የሚከሰቱ እና የሚነሱ የሕመም ዓይነቶች በዋናነት ታይፎይድ፣ ታይፈስ፣ ቶንሲል፣ ጃርዲያ፣ አጣዳፊ ተቅማጥ፣ ጥገኛ ትላትል፣ አሜባን፤ እንደሚያስከትሉ ጠቁመው፤ አጣዳፊና አደገኛ በሽታ መሆናቸውን አስረድተዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ መንገሻ እና አቶ ጋሻው፣ቃ.መ፤ 26/06/2011 እብናት ቡድን ሁለት)፡፡ የባህል ሐኪም መሪጌታ ስንታሁ እና መሪጌታ ልሳነወርቅ በድንገተኛ ሕመም ተለክፈው ዘመናዊ ሕክምና ጣቢያ ሲሄዱ "ታይፈስና ታይፎይድ" እየተባለ "የኪኒና" (መድኃኒት) ዓይነት እየሰጡ እና መርፌ እየወጉ ለጨጓራ በሽታ እና ለሞት እንደሚዳርጓቸው (ቃ.መ፤ 14/03/2011 እብናት እና 27/04/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል) ገልጸዋል፡፡

[73]በዘመናዊ ሕክምና አገልግሎት የሚታዘዝ መርፌ፤ በአጋንንት የሚነሱ የሕመም ዓይነቶችን በማባባስ ለሞት ይዳርጋል ተብሎ በአካባቢው ማኅበረሰብ ይታመናል፡፡ በአጋንንት የተለከፈ ግለሰብ መርፌ ከተወጋ " ...ፀሎታችን ሰመረ፣ ፍሪዳ ተጣለ፣ ጽዋችን ሞላ፤ ...የኛ አገልጋይ፣ ታዛዥና አሽከር እናደርገዋለን፤ እንደበሬ እናሳርሰዋለን፣ እንደ አጋሰስ እንጭነዋለን፣ እንደ ባርያ እህል ስናስፈጭ እናሳድረዋለን፤..." በማለት አጋንንት እንደሚደሰቱ መሪጌታ መንግስቱ ተርከዋል (ቃ፣መ፤11/04/2011 እብናት)፡፡ ይህን ትረካና ልማድ በማሰብና በመፍራት በድንገት ሰው ሲሞት "ያ ምናምንቴ ሰላቢ እንዳይሆን አስክሬን አንስታችሁ አትቅበሩ፤ ሩሁ [ነፍሱ] መኖርና አለመኖሯን ፈትሹ፡፡ አስክሬን ገልብጣችሁ በፊንጢጣው በኩል አመድ በመነስነስ ነፍሱ ከስጋው መለየቷን አረጋግጡ" ይባላል፡፡ በአጋንንት ተይዞ በተሰጠው መርፌ ቢደክም፣ እራሱን ቢስት እና ሞቷል ተብሎ አስክሬን ተገንዞ ቢሰጥ፤ በቀጥታ ወደ ቀብር እንደማይኬድ ጠቁመው፤ ነፍሱ ከስጋው መለየቷን ለማረጋገጥ ፍተሻ እንደሚደረግ መሪጌታ ፋንታሁን ገልፀዋል (ቃ.መ፤19/01/2011 ፋርጣ)፡፡ ደብተራ ማኅሪ ደግሞ፤ በአጋንንት ተለክፎ መርፌ ተወግቶ ሞቷል የተባለ ሰው፤ ሁለት ሶስት ቀን ነፍስና ሥጋው ሳይላቀቁ እንደሚቆይ ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ሂደት ቶሎ ቢቀበር "አጋንንት ነፍስና ሥጋውን ይዘውት ይሄዳሉ፤ ልቡን ሰውረው እንደ መጋዣ አገልጋይ ያደርጉታል" ተብሎ እንደሚጠረጠር ጠቁመዋል (ቃ.መ፤13/03/2011 እብናት)፡፡

የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያ የሆኑት አቶ ዐባይ ከገጠር የሚመጡ ብዙኀኑ ታካሚዎች በመርፌ የሚሰጥ ሕክምናን በመጠራጠርና በ"ማንገራገር" በቀጥታ አገልግሎቱን ለማግኘት ፍላጎት እንደሌላቸው ጠቁመው፤ የሕክምና አገልግሎቱን በእንክብል እና በሚዋጥ መድኃኒት እንዲቀየር ጥያቄ ሲያቀርቡ፤ ልጆቻቸው መርፌ እንዳይወጉ ሲከላከሉ፤ የታዘዘላቸውን መርፌ ሳይወጉ የሚሄዱ ታካሚዎች እንዳሉ ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 30/05/2011 እብናት)። ሊቀጠበብት አብርሃም ደግሞ፤ አንድ ታካሚው በባህል ሕክምና ሲመረመር ምንም ዓይነት ምልክት፣ መንቀጥቀጥና መርበትበት፣ መለፍለፍና ንግግር ካላሳየ፤ ከአጋንንት መንፈስ ነፃ መሆኑን በመጠቆም ወደ ዘመናዊ ሕክምና በመሄድ ምርመራ አድርጎ የታዘዘለትን መርፌና መድኃኒት ያለ ስጋትና ጥርጣሬ እንዲጠቀም ምክር ሰጥተው እንደሚያሰናብቱ (ቃ.መ፤ 05/03/2011 ሊቦ ከምከም) ገልጸዋል።

ቄስ አብርሃም እና መሪጌታ መኀሪ፤ በባህል ሕክምና የሚሰጥ ምርመራ ታካሚውን ምን ዓይነት ጋኔል እንደለከፈው ለማወቅ፣ በአጋንንት የተከሰተ ሕመም መሆን/አለመሆኑን ለማጣራት፣ የሕመሙን ባሕርይ እና ዓይነት ለመለየት ምርመራ እንደሚያካሂዱ ገልጸዋል። ታካሚው በአጋንንት የተለከፈ ከሆነ በግንባሩ መስቀል ሲያሳልሙት፣ በአፍንጫው የሚሸተት ዕፅ ሲሰጡት፣ በጭስ ሲያጥኑት፣ በጅብ ቆዳ ላይ ሲያስቀምጡት፣ የመርበብተ ሰሎሞንን [የአጋንንት ማናገሪያ፣ ማስለፍለፊያ፣ ማስወጫና መገዘቻ] "ፀሎተ-ድግምት" ሲደግሙበት፤ ይቀጠቀጣል፣ ይቅለሰለሳል፣ "ያጉተመትማል፣ እንደ ጅብ ይጮሃል፣ ያጎራል፣ ነደድኩ፣ ተቃጠልኩ፣…" በማለት ይለፈልፋል። የሕመሙ መንስኤ "በዓይነ ወግ" ወይም "በቡዳ" እንደመጣ ሲጠረጠር፤ በምግብና መጠጥ ግብዓቶች ላይ በማረፍ ወደ ሰውነት አካል የገባ ድንገተኛ፣ ደራሽ፣ "ሰላቢ" [ሕመሙ ሳይታወቅ በድንገት ማረፍ] እና ቀሳፊ ጋኔል ነው፤ ይባላል። ይህ ጋኔል አካልን በማድከም፣ በማስለምለም እና ሙሉ ሰውነትን በመቆጣጠር አቅምና ሚዛንን በማሳት፣ ሕሊናን በማስረሳት፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሞት ይዳርጋል፤ ተብሎ ይታሰባል (የሕመም መንስኤ ንዑስ ክፍል 5.4.4ን ልብ ይሏል)። በዚህ ሂደት ውስጥ አስፈላጊው መድኃኒት ተቀምሞ ሲሰጥና ፀሎት ሲደረግ ጋኔል ለቆ ይሄዳል። የሕክምና አሰጣጡም ጊዜ የማይፈጅ እና በቀላሉ የሚተገበር፤ የሚያስነጥስ፣ የሚያቃጥልና የሚሰረስር፤ ጎምዛዛ ጣዕም ያላቸው ዕፅዋት እና የቅመማ ቅመም ዘሮች ለመድኃኒት አገልግሎት እንደሚውሉ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 01/05/2011 እብናት እና 28/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

በአጠቃላይ ድንገተኛ እና አጣዳፊ ሕመም በበራሪ ጋኔል የሚከሰት፤ ጊዜ የማይሰጥ፣ በፍጥነት የሚዛመት እና የሚስፋፋ ሲሆን ተቅማጥ፣ ትውከት፣ አጣዳፊ ውጋት፣ ቁርጠት እና ራስ ምታት፣ ተዝለፍልፎ መውደቅና እራስን መሳት የሕመሙ መገለጫና መለያ ባሕርይ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ለድንገተኛና አጣዳፊ ሕመም፤ ተገቢው መድኃኒት ከተሰጠ መዛመትና መስፋፋቱን በመግታት፤ በሠዓታት እና በአጭር ቀናት ቆይታ ውስጥ ፈውስ የሚገኝበት፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጡም በቀላሉ የሚተገበር፤ በተለይ የቅመማ ቅመም ግብዓቶች እና ኮምጣጣ ጣዕም ያላቸው የዕፅዋት ዓይነቶች ለመድኃኒትነት አገልግሎት እንደሚውሉ፤ መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 6.2.2. ቆንጣጭ እና ሰርሳሪ

የቆንጣጭነት ባሕርይ ያላቸው የሕመም ዓይነቶች በሕመምተኛው አካል ላይ "ብቃይ"፣ ተለጣፊ፣ አዳጊ፣ ቆንጣጭና ሰርሳሪ በመሆን የረጅም ጊዜ ቆይታ፣ ትውውቅና እድገት አላቸው፤ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ባሕርይ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች በተወሰነ የሰውነት አካል ላይ እብጠት በመጀመር እና በመቋጠር ሕመም ይከሰታል፡፡ በሂደት አካልን መሰርሰር፣ መቦርቦር፣ መተብተብ፣ ሥርና "ሰንኮፋቸውን" በመላክ ጡንቻና የደም ሥርን ማሰርና ማድከም፤ ቀስ በቀስ አካልን ሽምቅቆ እና "ሰቅዞ" መያዝ፣ ማድረቅ፣ የሰውነት እንቅስቃሴን መግታትና "ሁለመና ጅስምን" [የሰውነት ጡንቻን] የመቆጣጠር ባሕርይ እንዳላቸው የባህል ሐኪሞች አስረድተዋል (አቶ ደርሶ እና መሪጌታ ፍሬስብሃት፣ ቃ.መ፤ 03/02/2011 እብናት እና 29/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)፡፡
እብጠቱ የሚገኝበት አካባቢ የሕመሙ "ጥንስስ"፣ "ማቆሪያ" እና "ማሰራጫ" ቦታ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ መሪጌታ አማረ፤ የእብጠቱ መጠን፣ ባሕርይ፣ መገኛ ቦታ ሲታወቅ የሕመሙ ዓይነት እንደሚለይ ጠቁመው፤ በዚህ ባሕርይ የሚጠቀሱና የሚጠረጠሩ የበሽታ ዓይነቶች በዛፍ አካል ላይ እንደሚበቅሉ ተቀጽላ እና ተገድራ ዕፅዋት[74] እንደሚመስሉ ገልጸዋል (ቃ.መ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

---

[74]በዛፍ እና በቁጥቋጦ ዕፅዋት ግንድና ቅርንጫፍ አካል ላይ ተለጥፈውና ተጣብቀው የሚወጡ "ባዕድ አካላት" ተቀጽላና ተገድራ ይባላሉ፡፡ እነዚህ ባዕድ አካላት ከዛፍና ከቁጥቋጦ ዕፀዋት የሚያገኙትን ምግብ በመጠቀምና በመሻማት እድገታቸው ይቀጥላል፡፡ የዛፉን ቅርንጫፎችና ግንድ እድገት በሂደት በመግታት፤ አዲስ የበቀለው ተገድራ የዛፉን "መቅኔ" [የምግብ ማመላለሻ ቦታዎችን] በመቆጣጠር በነባሩ ዛፍ ላይ እራሱን በማብቀል የተለየ ቅጠል እና ቅርንጫፍ ያወጣል፡፡ በዘመን ሂደት የዛፉን እድገት እየገታና እያደረቀው ይሄዳል፡፡ በዚህ ትይዩ በሰውነት አካል ላይ የሚከሰቱ እና የሚጣበቁ እባጮች ከመደበኛው የሰውነት አካላችን በተለየ እራሳቸውን በማጠጠር እና ቀስ በቀስ እያደጉ የሰውነት አካልን ቆንጥጠው በመያዝ የደም ሥርና ጅማትን መሰብሰብ፤ አለፍ ሲል አካልን በመቆጣጠርና ቆንጥጦ በመያዝ ለሞት እንደሚዳርጉ፤ መሪጌታ ፍሬስብሃት (ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም) ገልጸዋል፡፡

በቆንጣጭና ሰርሳሪ ባሕርያቸው የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች አካልን ቆንጥጦ በመያዝ፤ ሰውነትን ማድረቅ፤ ጡንቻና የጅማት ሥርን መሰብሰብ፣ መቆለፍ፣ አካላዊ እንቅስቃሴን ቀስ በቀስ የመግታት ባሕርይ እንዳላቸው ጠቁመው፤ እንደ እድገትና ቆይታ ዘመናቸው የፈውስ ጊዜያቸውም ረጅም ቀን እና ወራትን እንደሚወስዱ፤ መሪጌታ ፍሬስብሃት ይገልጻሉ (ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ የመድኃኒት አዘገጃጀት፣ ቅመማና አሰጣጡም ቢሆን እንደ እድገታቸው ቀናት፣ ሳምንትና ወራትን እንደሚወስድ ጠቁመው፤ "ሥርና ሰንኮፋቸውን" ሰብስቦ ለማውጣት ፅናትና ትግስትን እንደሚጠይቅ መሪጌታ አዲሱ (ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ) ይመክራሉ፡፡

በዚህ ማሕቀፍ ሥር የሚመደቡ የበሽታ ዓይነቶች በዋናነት አካላዊ እብጠትን በማስከተል ተቀራራቢ ዘርና ዝምድና እንዳላቸው ጠቁመው፤ ኪንታሮት፣ ነቀርሳ [ካንሰር]፣ እንቅርት፣ ብጉንጅ፣ ዕጢ እና መሰል ሕመሞች ይጠቀሳሉ (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደርሶ እና መሪጌታ ስንታየሁ፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት)፡፡ ለመድኃኒት አገልግሎት የሚውሉ ዕፅዋት በይዘታቸው፤ መራራ፣ አቃጣይ እና የዘይትነት ባሕርይ ያላቸውን ዕፅዋት መርጦ፣ መጥኖ እና ደባልቆ በመውቀጥ፣ በመቀቀል፣ በማፍላት እና በማጥለል፤ ከእንስሳት እና ከማዕድናት ግብዓቶች ጋር ደባልቀው በማንጠር፤ በሚቀባ፣ በሚጠጣ፣ በሚታሰር አዘጋጅተው እንደሚሰጡ መሪጌታ ፍሬስብሃት ያስረዳሉ (ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያ የሆኑት ዶ/ር አስናቀ እና አቶ እሸቱ አካላዊ እብጠትን የሚያስከትሉ በሽታዎች ወደ ሌላ ሰው የማይዛመቱና የማይተላለፉ "None Communicable Diseases" በመባል ጥቅል መጠሪያ ስም እንዳላቸው ጠቁመው፤ በዘመናዊ ሕክምና የሚሰጠው አገልግሎት፣ የምርመራ እና የመድኃኒት አሰጣጥና አወሳሰድ ሂደት ረጅም ቀናት እና ሳምንትን እንደሚፈጅ ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 23/04/2011 ደብረ ታቦር እና 22/04/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ በአጠቃላይ በቆንጣጭ እና ሰርሳሪ ባሕርይ ምድብ ውስጥ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች በሰውነት አካል ላይ እብጠት በማስከተልና በመለጠፍ አካልና ሥጋን ሰርስረው በመግባት፤ በጡንቻና በደም ሥር ላይ ተጠምጥመው ለአካላዊ ስቃይና ጉዳት ምክንያት በመሆን ለሞት እንደሚዳርጉ፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

### 6.2.3 አቃጣይ እና አስለፍላፊ

በአቃጣይ እና አስለፍላፊ ባሕርይ ምድብ ውስጥ የሚጠቀሱ የበሽታ ዓይነቶች ትኩሳት፣ እረፍት አልባ እንቅስቃሴ፣ መነጫነጭ፣ መለፍለፍ፣ መጮህ፤ መገለጫ መንገዳቸው እንደሆነ መረጌታ መኀሪ ጠቁመዋል። አቃጣይ ባሕርይ ያላቸው የሕመም ዓይነቶች እንደ "ዕፀ ሙጋድ" [ሣማ] እና አለብላቢት ሃረግ አካልን የማቃጠል፣ የመቆጥቆጥ እና የመለብለብ ስሜት እንዳላቸው ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 28/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

አቃጣይ እና አስለፍላፊ የሕመም ዓይነቶች ውጫዊና ውስጣዊ የሰውነት አካልን በማተኮስና በመለብለብ እረፍት መንሳት፤ ማቃሰት፣ "ማቃተት"፣ ከፍተኛ ትኩሳት፣ እራስ ምታት፣ "በላብ መጠመቅ"፣ የፊት መገርጣት፣ የልብ ምት መጨመር፣ የደም ሥር መቆጣትና ማበጥ፣ የሽንት መጥቆርና ቢጫ መሆን፣ የምላስ መደብ መቅላትና የደም ሥር መወፈር፤ ዐበይት ምልክቶች እንደሆኑ መሪጌታ መንግስቴ እና አቶ ሞላ ገልፀዋል (ቃ.መ፤10/03/2011 እብናት እና 22/06/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

በዚህ ባሕርይ ምድብ ውስጥ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች የወፍ በሽታ [የጉበት]፣ የውሻ ልክፍት፣ የወባ ሕመም፣ አልማዝ ባለጭራ፣ የጥርስ ሕመም፣ ቁርጥማት መሆናቸውን፤ አቶ ደሴና መሪጌታ ስንታየሁ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 25/ 01/2011 ሊቦከምከም እና 14/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። በአጠቃላይ አካላዊ ሙቀትን በመጨመር ማተኮስ፣ ማቃጠል፣ ማንቀጥቀጥ፣ ማቃዠት፣ የልብ ምት መጨመርና ማላብ በአቃጣይ ሕመም ባሕርይ ምድብ ውስጥ እንደሚካተቱ የመስክ መረጃዎች ገልፀዋል።

### 6.2.4 አብራጅ እና አድካሚ

በአብራጅ ባሕርይ ምድብ ውስጥ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች አካልን የማድከም፣ አቅም የማሳጣት፣ የማስለምለምና የማዛል አካላዊ ምልክት እንዳላቸው መሪጌታ ሰረቀብርሃን እና ደብተራ ጥላሁን ገልጸዋል (ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት እና 03/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)። የሕመም ዓይነቶቹ በጊዜ ሂደት የሚከሰቱ፣ አብሮ አደግ እና ቁራኛ [አብሮ አደግ] በመሆን ለረጅም ጊዜ ከሕሙማን አከል ጋር ተዛምደው፤ እንደሚኖሩ ይታሰባል። የሕመም መንስኤያቸው ከቤተሰብ በውርስ እና በዘር የሚመጡ የዛር ዓይነቶች፣ በመቃብርና በወንዝ ጋኔል ቁጣና መቅሰፍት እንደሚከሰቱ ይታመናል (ከተቡው አባላት መካከል መሪጌታ ስዩም፤ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት)።

ደብተራ መልኩ ደግሞ፤ በባህል ሕክምና የሚደረጉ የምርመራ ሂደቶች እንደ ባህል ሐኪሙ ዕውቀት፣ የሃይማኖት ትምህርት ብቃት እና ተግባር እንደሚለያይ አስረድተው፤ በአብራጅና አድካሚ ማሕቀፍ ውስጥ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች በዋናነት በአጋንንት መቅሰፍት እንደሚከሰቱ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤01/03/2011 ፋርጣ)። በአጋንንት የተለከፉ ሰው የሚሸተት፣ የሚጨስ፣ የሚጠጣና "ፀሎተ-ድግምት" ሲደረግለት አንደበቱን "አንቅቶ"፤ ሕሊናውን "ሰውሮ ያናግረዋል" ተብሎ ይታሰባል።

መሪጌታ አማረ እና ቄስ አብርሃም፤ አብራጅ ከሚባሉ የሕመም ዓይነቶች መካከል፤ ስንፈተ ወሲብ፣ ኩላሊት፣ ስኳር፣ ሾተላይ [በተደጋጋሚ ፅንስ ማሶረድ]፤ ደም ግፊት፣ ደም ማነስ፤ እንደሚጠቀሱ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 27/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 01/05/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። በተመሳሳይ መልኩ መሪጌታ ባሕረጥበብ በምርመራ ሂደት የትኛው ሕመም በምን ዓይነት አጋንንት እንደሚከሰት እንደሚከተለው አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 27/02/2011 ሊቦ ከምከም)፦

> አጋንንት አካልን እያደከሙ ውስጥ ውስጡን ይበላሉ፤ ደም ይመጣሉ፣ ይጠጣሉ። …እነዚህ አጋንንት በውስጥ አካል ተሰውረው ጤና ይሰልባሉ። በተለይ በጥር፣ በግንቦት እና በሰኔ ወራት ሰውን ይለክፋሉ። …አካልን አድክመው፣ እጅና እግር አሳብጠው ይገላሉ። …መንስኤ እስኪት እና ዓይነ ጥላ በዛር፤ የስኳር ሕመም በቅድመ አያቶች መንፍስ እና ከልከሊዎስ በሚባል ጋኔል ይመጣል።

ተብሎ ይታመናል። ከዚህ በላይ የቀረቡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ አብራጅና አድካሚ የሚባሉ የሕመም ዓይነቶች አካልን ማድከምና ማዛል፤ ስሜትን መግታት፤ የእጅ እና የእግር እብጠት፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ የሕመም ምልክት ተደርገው ቢታሰቡም፤ የበሽታዎቹ መነሻ በአጋንንት ልክፍት እንደሆነ ይታመናል።

የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያ የሆኑት አቶ ፀሐዬ እና ዶ/ር አስናቀ፤ ኩላሊት፣ ደም ግፊት፣ ስኳርና መሰል ሕመሞች "ድምፅ አልባ" ገዳይ (Silent Killers) በሽታ በመባል እንደሚታወቁ ጠቁመው፤ አካልን ማድከም፣ ቶሎ ቶሎ መሽናት፣ የቆዳ ድርቀት፣ እከክና ቁስለት፤ እንቅልፍ ማጣት፣ በድንገት ክብደት መጨመር/መቀነስ፣ የዓይን ብርሃን እይታ መድከም፣ የፊት፣ የእግር ተረከዝና የእጅ አካል እብጠት፣ የሽንት ቀለም መለወጥና አረፋ ጎልቶ መታየት፤ መለያ ምልክቶች ሲሆኑ ከዘር (ከቤተሰብ) የመተላለፍ እድል እንዳላቸው ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 21/01/ 2011 ፋርጣ እና 23/04/2011 ደብረ ታቦር በቅደም ተከተል)።

በአጠቃላይ በባህል ሕክምና ልማድ አብራጅና አድካሚ የሚባሉ የሕመም ዓይነቶች መንስኤ አጋንንት እንደሆኑ ይታሰባል። አካልን በማድቀቅ እና መንፈስን በማስጨነቅ፤ ሙሉ አካልን በማድከም፣ ስሜትን በመግታት፣ ፍላጎትን በማዛባት ለስቃይና ለሞት እንደሚዳርጉ፤ ይታመናል። በዘመናዊ ሕክምናም ቢሆን አጀማመራቸው ሳይታወቅ ለጤና መቃወስ እና ለሞት ምክንያት እንደሆኑ ተጠቁሟል። ከነዚህ መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው፤ ስለበሽታዎቹ መንስኤና ምርመራ ሂደት ባህላዊና ሣይንሳዊ አተያይና እሳቤ ልዩነት ቢኖርም፤ በሕመሞቹ ምልክት፣ ውጤትና ተግባር ላይ ተቀራራቢ ግንዛቤ እንዳለ መረዳት ተችሏል።

### 6.2.5 አንቀጥቃጭ እና አርገብጋቢ

በአንቀጥቃጭ ባሕርይ ምድብ ውስጥ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች አካልን ማርገብገብ፣ ማንቀጥቀጥ፣ እረፍት አልባ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ የአዕምሮ [የነርቭ] መታወክ ምልክቶች ተደርገው ይታሰባሉ። ደብተራ መኳሪ እና ቄስ አብርሃም፤ የአዕምሮ ሕመም ዓይነቶች በድንገተኛ አደጋ በሚደርስ ጉዳት፣ ከዛፍ በመውደቅ፣ ገደል በመግባት፣ በከፍተኛ ድንጋጤ እና ግጭት እንደሚከሰቱ ገልጸዋል። በአካባቢው የሚገኙ አጋንንት የፈሰሰውን ደም "በመቅመስ እና በመላስ፤ በድንጋጤ ተዋርሰውና በሕሊና ተሰውረው ይኖራሉ"፤ በሂደት አዕምሮን በማጨናነቅ፣ በማሳት እና በመሰወር "ድንገት" እንደሚጥሉ ይታመናል። አካልን ማንቀጥቀጥ፣ እጅ እና እግርን ማርገብገብ፣ ንግግር መቆራረጥ፣ ድንገት መጨለምና መውደቅ፣ መወራጨት እና መንተባተብ ዐበይት ባሕርያት መሆናቸውን ገልጸዋል። ለአብነት ያህል፤ የዳፍንት ወይም የሚጥል በሽታ (ኤፕሌፕሲ)፣ የመርሳት እና የነርቭ ሕመም በዚህ ማሕቀፍ ውስጥ እንደሚጠቀሱ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 13/03/2011 እና 01/05/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ደግሞ የማንቀጥቀጥና የማርገብገብ ባሕርይ ያላቸው ሕመሞች በነርቭ በሽታ ማሕቀፍ ውስጥ እንደሚካተቱ ጠቁመዋል። የሕመሙ መንስኤ ውስብስብ እና ዘርፈ ብዙ መገለጫ ያለው፤ ጥርት ያለ ምክንያት ለማስቀመጥ የሚያዳግት መሆኑን ገልፀው፤ "በሆርሞን" መዛባት፣ በዘር ከቤተሰብ፣ በከባድ ግጭትና አደጋ፣ በሕመም ማስታገሻ መድኃኒቶች፣ በካንሰር እጢዎች፣ በስኳር ሕመም እና ተጓዳኝ በሆኑ በሽታዎች የነርቭ መቃወስና የሥርዓት መዛባት እንደሚያጋጥም ገልፀዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ጋሻው እና አቶ ደሳለኝ፣ ቃ.መ፤ 26/06/2011 እብናት ቡድን ሁለት)።

በአጠቃላይ በአንቀጥቃጭ እና አርገባጋቢ ምድብ ውስጥ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች ከአዕምሮ ነርቭ ሥርዓት ጋር የተገናኙ ሲሆን በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሕክምና

ባለሙያዎች አካላዊ መርገብገብን፣ በድንገት እራስን መሳትና መውደቅን፣ የአዕምሮ ጭንቀትን፣ የእጅና የእግር መንቀጥቀጥን ታሳቢ በማድረግ የበሽታ ባሕርይ ምደባ እንደሚያካሂዱ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

### 6.2.6 አደንዛዥ እና አወፋሪ

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች፤ አካልን በማወፈር፣ በማደንዘዝና በማደደር የሚለዩ፤ በአብዛኛው በእግር እና በጣት የሰውነት ክፍል ላይ የሚከሰቱ የሕመም ዓይነቶችን በአደንዛዥና አወፋሪ ባሕርይ ምድብ ውስጥ አካተዋል (*መሪጌታ ስንታየሁ፣ ቃ.መ*፤14/03/2011 እብናት)፡፡ እነዚህ ሕመሞች "በእርግማን"፣ ደንቃራ በመግባት፣ በመርዛማ እሾህ እና በአጋንንት እንደሚከሰቱ ይታሰባል፡፡ እነርሱም፤ ዝሆኔ፣ ጋንግሪን፣ ሪህ እና መሰል በሽታዎችን ይመለከታል (*መሪጌታ ፋንታሁን እና አቶ ሞላ፣ ቃ.መ*፤ 19/01/2011 እና 22/06/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)፡፡

የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ዝሆኔ፣ ሪህ እና ጋንግሪን በዋናነት በእግር የሰውነት አካል ላይ የሚከሰቱ በደም ቧንቧ ጥበት፣ በእግር ተረከዝ የሚገቡ የዐፈር ንጥረ ነገሮች፤ ከውፍረት፣ ከደም ብዛት፣ ከስኳር፣ ከኩላሊት መድከም እና በተለያዩ ምክንያቶች ሕመም እንደሚከሰት ጠቁመው፤ አካላዊ እብጠትና ውፍረትን በማስከተል ለከፋ ስቃይና ሞት እንደሚዳርጉ አስረድተዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደሳለኝ እና አቶ መንገሻ፣ *ቃ.መ*፤ 26/06/2011 እብናት ቡድን ሁለት)፡፡ በአደንዛዥ ባሕርይ ምድብ ውስጥ የሚጠቀሱ የበሽታ ዓይነቶች ምልክት በባህል እና በዘመናዊ ሕክምና ተቀራራቢ ቢሆኑም የበሽታ መንስኤ እሳቤ እና አተገባበር፤ የምርመራ ሂደት አካባቢያዊ (ልማዳዊ) እና ሣይንሳዊ ይዘት ያላቸው፤ የማይገናኙ፣ የሚጣረሱና በተቃርኖ የሚጠቀሱ ሃሳቦችን እንደሚያስተናግዱ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች አካላዊ ምርመራ ሲያካሂዱ የሕመሙን ዓይነት፣ ምልክት፣ ተግባር፣ ይዘትና ሁኔታን መነሻ በማድረግ የበሽታዎችን ባሕርይ በስድስት ዋና ዋና ክፍል መድበዋል፡፡ የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴልን መነሻ በማድረግ፤ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ የበሽታ ባሕርይ ምድቦች በሁለት ይዘት እንደሚከፈሉ፤ የመስክ መረጃዎች ገልፀዋል፡፡

እንደ ባህል ሐኪሞች እሳቤና ተግባር የበሽታ ባሕርያት በሁለት ጥቅል ማሕቀፍ እና ይዘት እንደሚከፈሉ ይታሰባል፡፡ ድንገተኛ፣ አቀጥቃጭ እና አቃጣይ የእሳትና የነፋስ ባሕርያት

እንዳላቸው ይታመናል። ከነዚህ በተቃራኒ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች ደግሞ አደንዛዥ፣ ቆንጣጭ እና አብራጅ የዉኃና የመሬት ባሕርያትን እንደሚወክሉ ገልፀዋል (መሪጌታ መኀሪ እና ደብተራ መልኩ፣ ቃ.መ፤ 27/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 01/03/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)። ለምን? ሲባል፤

"ነፋስ" የመሄድ፣ የመብረር፣ የመቅለል ተምሳሌት ሲሆን "እሳት" ደግሞ ሙቀትን ቀስቅሶ ኃይል እና ጉልበት ይሰጣል። በልኩ ሲሆን አብሳይ፣ ከልኩ ሲያልፍ አቃጣይ፤ አድራቂና አጥፊ ባሕርይ እንዳለው ይታሰባል። በነዚህ ባሕርይ ምድብ ውስጥ የሚጠቀሱ የሕመም ዓይነቶች አካልን ማተኮስ እና ማቃጠል፤ ኃይልና ጉልበት አውጥተው በፍጥነት መዛመት፣ መራባትና መሰራጨት፤ ድንገት ደርሰውና አጣድፈው ለሞት እንደሚዳርጉ ይታመናል። ድንገት ደራሽ፣ ተስፋፊ እና ቀሳፊ በመሆን አገርን የሚያዳርሱ፣ ከቦታ ቦታ የሚዛመቱ የሕመም ዓይነቶች፤ የነፋስና የእሳት ባሕርያት መገለጫ፣ ተምሳሌትና ውክልና እንዳላቸው፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል (መሪጌታ ባሕረጥበብ ቃ.መ፤ 22/01/2011 ፋርጣ)።

በአንጻሩ አካልን የመቆንጠጥ፣ የማደንዘዝ እና የማብረድ ባሕርይ ያላቸው የሕመም ዓይነቶች የዉኃና የመሬት ባሕርይ ተምሳሌት ተደርገው ይታሰባሉ። የማቆር፣ የመያዝ፣ የመቆንጠጥ፣ የማወፈር እና የማደንደን ተግባር የሚታይባቸው የሕመም ዓይነቶች፤ የዉኃና የመሬት ባሕርያትን እንደሚወክሉ፤ ጠቁመዋል (መሪጌታ ባሕረጥበብ፣ ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)።

በአጠቃላይ በሰው ልጅ አካል[75] ውስጥ፤ ድንገተኛ፣ አንቀጥቃጭና አቃጣይ ባሕርይ ያላቸው የሕመም ዓይነቶች በድንገት ተከስተው ለከፋ ጉዳት እና ለሞት የሚዳርጉ፤ የመድኃኒት ቅመማ፣

[75] አራቱ ባሕርያት፤ በሰው ልጅ አካል ውስጥ ምን ዓይነት ድርሻና ሚና አላቸው? የሰው ልጅ አካልና ነፍስ ከአራት የሥጋና ከሶስት የነፍስ ባሕርያት እንደተገኘ መሪጌታ ስንታየሁ ጠቁመዋል። የሰው ልጅ ዉኃ እና ምግብን በመጠቀም ብዙኀኑን የአካል ሥጋ "ከዉኃና መሬት" ባሕርያት እንደሚያገኝና እንደሚገነባ ገልፀው፤ ጥቂቱን ደግሞ በመተንፈስ እና አካላዊ ሙቀት በማመንጨት የነፋስ (ዐየር) እና የእሳት ባሕርያትን ተጠቅሞ [ሙቀት አካላዊ የደም ዝውውር ሥርዓትን ለማፋጠን እና ለማቀጣጠል፤ ለምግብ መፈጨት... ምክንያት በመሆን] እንደሚቀሳቀስ አስረድተዋል (መሪጌታ ስንታየሁ፣ ቃ.መ፤ 14/03/2011 እብናት)። ቄስ አብርሃም እና መሪጌታ አማረ ደግሞ፤ "እስትንፋስ" (ነፋስ) የአካልና የሕይወት መጀመሪያ ምዕራፍ እና መቋጫ ክር ተደርጋ እንደምትታሰብ ገልፀው፤ በውስጧ የእሳት እና የዉኃ ባሕርይን በመያዝ ሕልው ሆና ሥጋ ለብሳ በመወለድ ስትገኝ፤ የሕይወት እና የባሕርይ ውሕደት ሚዛን ጅማሮ መሆኑን ገልጸዋል። እስትፍስ ከሥጋዊ አካል ስትለይ እና ስትፋታ የሕይወት ፍፃሜ እና መቋጫ ተደርጎ ይታሰባል። በሂደት አራቱ የፍጥረት ባሕርያት ልካቸውን ሲያልፉ፣ መጠናቸውን ሲስቱ የጤና ኃይል ሚዛን መዛነፍ እንደሚከሰት መክረዋል (ቃ.መ፤ 01/05/2011 እብናት እና 27/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

አሰጣጥና አተገባበራቸው ቀላል፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈወሱ የሕመም ዓይነቶች ሲሆኑ በነፋስ እና በእሳት ባሕርይ ምድብ ውስጥ እንደሚካተቱ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በአንጻሩ በአደንዛዥ፣ አብራጅና ቆንጣጭ ምድብ ውስጥ የሚገኙ የሕመም ዓይነቶች፤ አካልን በመሰርሰር እና በመላመድ ቀስ በቀስ እድገታቸውን በመቀጠል፤ ጉዳትና ደረጃቸው ሳይለይ አጠቃላይ ሰውነትን ማድከም፤ ጡንቻና የደም ሥርን ተብትቦ ማሰር፤ የረጅም ጊዜ የሕመም ስሜትን በመፍጠር፤ አካልን ማሳበጥ፣ ማደንዘዝ፣ ማቁሰል፣ ዉኃ ማቆር እና ትርፍ ሥጋ ማውጣት እና ባዕድ አካል በመያዝ፤ ለከፋ ሕመም እና ስቃይ መንስኤ በመሆን ለሞት እንደሚያዳርጉ ይታሰባል፡፡ የመድኃኒት ዝግጅት፣ ቅመማ፣ አሰጣጥና አተገባበሩም የረጅም ጊዜ ዝግጅት የሚጠይቅ፤ የፈውስ ጊዜያቸው በሂደት የሚታይ፤ በሰውነት አካል ሥጋ ላይ ተለጥፈው የሚቆዩ እባጮች ዉኃና ሥጋን በማዘል፤ ሥጋና ዉኃን በሚያስገኙ ባሕርያት ተመስለውና ተወክለው ቀርበዋል፡፡ የዉኃ ተግባር አካልን ማጠጣት፣ ማለስለስ፣ ማለምልና ማራስ ሲሆን መሬት (ማዕድናት) ደግሞ የዘር አካልን ተቀብላ፤ የማብቀል፣ የመመገብ፣ የማሳደግ፣ የመጠገን፣ የመገንባት እና የማፋፋት ሚና እና ተግባር እንዳላት ይነገራል፤ ይታሰባል፡፡

## 6.3 የምርመራ ሂደት እና የተቃርኖ ሕክምና

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች አካላዊ እና መንፈሳዊ ምርመራ በማካሄድ የተቃርኖ ሕክምናን እንደሚተገብሩ መሪጌታ መንግስቴ እና ደብተራ መልኩ ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 10/03/2011 እብናት እና 01//03/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)፡፡ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች አካላዊ ምርመራ ሲያካሂዱ የሰውነት አካል ቦታዎችን በመፈተሽ እና የሕመም ባሕርይና ምልክቶችን በመለየት የሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ አንጻር፤ በምርመራ ሂደት ውስጥ የሕመም ባሕርይ እና የተቃርኖ ሕክምና እንዴት ይተገበራል?

በባህል ሕክምና ልማድ፤ የሕመም ባሕርይ እና የመድኃኒት አሰጣጥ በተቃርኖ ይዘት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ሊቀጠበብት አብረሃም ሲያስረዱ "...ለሚያቃጥል ሕመም የሚያቃጥል መድኃኒት አይሰጥም፤ ከፍተኛ ጉዳት ላይ ይጥላል፡፡ ኃይል ላለው ሕመም የሚያበርድ፤ ለሚያደክም የሚያበረታ መድኃኒት ይሰጣል፤ ...በገቢር በገቢሩ ታልሆነ ጠንቅ ላይ ይጥላል" በማለት መክረዋል፡፡ በምርመራ ሂደት የበሽታውን ባሕርይ መለየት ብቻ ሳይሆን የሚሰጠውን ሕክምና ለማወቅ፣ የመድኃኒት አመራረጥ፣ ቅመማ እና አሰጣጥን ሂደትን ለመወሰን

እንደሚያግዝ ገልፀው፤ የታማሚው ግለሰብ "ጠባይ"፣ መተዳደሪያ እና አካላዊ አቋም[76] እንደሚፈተሽ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

የአንድ አካባቢ ማኅበረሰብን የሕመም መንስኤ እሳቤን ለማወቅ፣ በሽታን ለመቆጣጠር፣ የታካሚን ሥነ ልቡና ለመረዳት፣ ልማዳዊ ተግባራትን ለመገንዘብ፣ የምርመራ ዓይነትና ስልቶችን ለመተንተን፤ ትዕምርት እና ዐውድ-ተኮር ጥናቶች ተመራጭ መሆናቸውን ምሁራን (Ben-Amos,1971;1993: Amzat and Razum, 2014; PP.128-129) ጠቁመዋል። ይህን ታሳቢ በማድረግና የመስክ መረጃዎችን በማደራጀት የደቡብ ጎንደር ዞን የባህል ሐኪሞች የምርመራ ሂደት እና የተቃርኖ ሕክምና (መድኃኒት) ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ምስል 13፡- የምርመራ ሂደት እና የተቃርኖ ሕክምና ማሕቀፍ




ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች፤ በጥናት አቅራቢው የተዘጋጀ ምስለ ማሕቀፍ፤ ግንቦት/2011 ዓ.ም

[76] በእዚህ ዐውድ አካላዊ አቋም ሲባል፤ በግለሰቡ አካል ውስጥ፤ የነፋስ፣ የእሳት፣ የዉኃ እና የመሬት ባሕርይ ምጣኔ ምን ይመስላል? የትኛው ባሕርይ በታማሚው ግለሰብ ውስጥ በዝቶ ወይም አንሶ ይገኛል? እንዴት ማመጣጠን ይቻላል? የሚሉ ጥያቄዎችን ይመልሳል (የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴልን ልብ ይሏል)።

ከዚህ በላይ የቀረበው ማሕቀፍ እንደሚያመለክተው፤ በምርመራ ሂደት እና በተቃርኖ ሕክምና ማሕቀፍ፤ ማዕከላዊ ይዘት የባህል ሐኪም ነው፡፡ የባህል ሐኪሙ ከታካሚ ጋር በአለው ግንኙነት፣ ተግባቦትና መስተጋብር የሕመሙን ዓይነት፣ ምልክት እና ባሕርይ ለይቶ የመድኃኒት ዝግጅትና ምርጫ አድርጎ፤ ቅመማ ሂደቶችን ይፈፅማል፤ ይከውናል፡፡ በሂደት የአዘጋጀውን መድኃኒት በዓይነት፣ በይዘት እና በቁስ መጥኖ፤ የመድኃኒት አሰጣጥና አተገባበር ሥርዓቱን ይወስናል፡፡ የመድኃኒት አሰጣጥ፣ ተግባርና ውሳኔውን በመከተል ለታካሚው የአዘጋጀውን መድኃኒት ቀምሞና መጥኖ ይሰጣል፡፡ ለታካሚው መድኃኒት ሲሰጥ አድርግ እና አታድርግ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፤ በሂደት መድኃኒቱ በታካሚው ላይ የሚያሳየውን ለውጥና ምልክት በመከታተል ሕክምናው ይተገበራል፡፡

በምርመራ ሂደትና በተቃርኖ ሕክምና ማሕቀፍ ውስጥ የቀረቡ መጠቁሞችና የቀስት ምልክቶች የባህል ሐኪም፣ የታካሚ እና የመድኃኒት መስተጋብርን እንዲያመላክቱ ተደርጓል፡፡ ከማዕቀፉ መሃል የሚነሱ ቀስቶች የባህል ሐኪሙን ተግባርና ግንኙነት የሚጠቁሙ ሲሆን ከግራ ወደ ቀኝ የሚነሱ ቀስቶች ደግሞ በምርመራ ሂደት የሕመሙን ዓይነትና ባሕርይን በመለየት፤ የመድኃኒት ምርጫና የቅመማ ሂደትን ይጠቁማል፡፡ በቅመማ ሂደት የተዘጋጀው መድኃኒት በዓይነትና በይዘት ተለይቶና ተመጥኖ፤ ለታካሚ እንዲሰጥ ይወሰናል፡፡ ታካሚው የሚወስደው መድኃኒት ዓይነትና ባሕርይ ከሕመሙ ስሜትና ባሕርይ ጋር በተቃርኖ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ የሕክምና ሥርዓቱ ይከወናል፡፡ በአጠቃላይ የባህል ሐኪሙና ታካሚው በሚያደርጉ መስተጋብር የታካሚው የጤና ይዘትና ደረጃ፤ የመድኃኒቱ "ፍቱንነት"፣ የባህል ሐኪሙ ውሳኔና ተግባራት፤ ጥብቅ ክትትል፣ ቁጥጥር እና ጥንቃቄ እንደሚደረግባቸው፤ የባህል ሐኪሞች አስረድተዋል (ከተቡው አባላት መካከል መሪጌታ ስንታየሁ እና አቶ ደርሶ፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት)፡፡

መሪጌታ ፍሬስብሃት፤ ርዕሰ ጉዳዩን በምሳሌ ሲያስረዱ፤ "የኪንታሮት ሕመም አካልን ሰርስሮ ከገባ በኋላ ሥሩን በመዘርጋት፤ ጡንቻን ሽምቅቆ [እየቆነጠጠ፣ እየሰበሰበ]፤ ሲንቀሳቀሱ የሚያሰቃይ፤ …ደም መጣጭ፣ ድርቀት አምጪ ሕመም ነው" ይላሉ፡፡ አካልን ሰርስሮ የገባውን ሕመም፣ ሰርስሮ በሚያወጣ መድኃኒት፤ የሚያደክመውን በሚያበረታ፤ የሚያቃጥለውን በሚያበርድ መድኃኒት እንደሚፈውሱ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ መሪጌታ አማረ ደግሞ፤ ለግብረ ወሲብ ድክመት የሚሰጡ ሕክምናዎች በሁለት መልኩ እንደሚተገበሩ ጠቁመዋል፡፡ አንድም የደከመን አካል (ብልት) የሚያጠነክር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኃይልና ስሜትን ለመቆጣጠር የሚተገበረውን ሕክምና ይመለከታል፡፡ "ብልቱ ለደከመ የሚያጠነክር፤ ቶሎ

ለሚያፈስ የሚያዘገይ፤ ሽንቱን ለሚከለክለው የሚያወርድ"[77] መድኃኒት በመስጠት የተቃርኖ ሕክምናን እንደሚተገብሩ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል ይዘት እንደተጠቀሰው፤ ምጣኔ፣ ደረጃና ልክን ጠብቆ መሄድና መከወን የጤና መሰረት የሕይወት ልክ ተደርጎ ይቆጠራል። በጤና ኃይል ሚዛን መደላድል ሂደት፤ የበዛውን ለመቀነስ፣ ያነሰውን ለመጨመር፣ የጎደለውን ለመሙላት፤ በተቃርኖ የሚከወነውን ሕክምና ይመለከታል። በተመሳሳይ መልኩ፤ መሪጌታ መኀሪ፤ የፎረፎር እና የእከክ ሕመም ባሕርይ እና የሚሰጠውን ሕክምና እንደሚከተለው ገልፀዋል (ቃ.መ፣ 28/01/ 2011 ሊቦ ከምከም)፡-

> በኩታራው [በልጆች] አናት ላይ ክብ ክብ እየሰራ እንደ ምርጊት ተለጥፎ ዱቄት መስሎ የሚወጣ ፎረፎር ነው። ... ሲበላቸው ሲያኩት እንደጤፍ እብቅ እየቦነነ ይነሳል። በትንሹ ቁርዝዝ የሚል ውኃ እያዣ፤ ሲውል ሲያድር እየሰፋ የከረመ ቁስል ይሆናል። ...መድኃኒቱ የጌሾ ቅጠልና ፍሬ፤ የባድማ ጠባቂ [ዕፀ ፋሪስ] ቅጠል ተጨቅጭቆ ሲታሰርበት፤ የሚበላው ይቆማል፤ የሚያቃጥለው ይበርዳል፤ ቁስሉ እየደረቀ ይሄዳል። በቀን ሁለት ጊዜ እየታጠበ ሲቀየርለት በሰባት ቀን ውስጥ ይረግፋል [ይድናል]። ሌላው እከክ ነው፤ ሰሞኑን እንደ ወረርሽኝ ገብቶ ትንሽ ትልቁ ይፎክታል [ማሳከክ]። በእጅ እና በእግር ጣት መሃል፣ ብሽሽት፣ ሆድ እና ጀርባን ወሮ ያሳክካል። ሰውነታችን ይጉረበረብ እና ቆዳችን ይቆጣል። በየቦታው እትር እትር ብለው ውኃ የቋጠሩ ሲፈነዱ እንደ ኑግ መልክ ጠባሳ ይፈጥራሉ። መልሰው ሲያኩት ይደማል፤ ችፍ የሚል ውኃ እየቀላቀለ ይወጣል፣ ይቆጠቁጣል። ...የሚዘጋጀው መድኃኒቱ የገበር እንቧይ እና የመቅመቆ ሥር አድርቆ፣ ወቅጦ በቫዝሊን ለውሶ መቀባት፤ የአዞ ሃረግ ቅጠል፣ የብሳና እና የገበር እንቧይ ፍሬ አድርቆ፣ ቆልቶ፣ ፈጭቶ፤ በለጋ ቅቤ ለውሶ እከክ የወረረውን ተጠንቅቆ መቀባት፤ ከቦታዉ ካለፈ ቆዳ ይልጣል። ... እከክ በያዘው መደብ [አካል] ላይ መድኃኒት ሲደረግ እሚበላው ነገር ተግ ይላል። ሲውል ሲያድር እየከሰመ፣ እየበረደ፣ የተሰነጠቀው እየገጠመ፤ የተጉረበረበው እየለሰለሰ ቅርፊት ቅርፊት እየሰራ እንደ እባብ ገላ ሙሽልቅ ብሎ ይወጣል።

በማለት ገልጸዋል። ከዚህ በላይ የቀረቡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የምርመራ ሂደት እንደተጠናቀቀ የሚሰጠው ሕክምና የሕመሙን ዓይነት፣ ባሕርይ እና የሚያደርሰውን ጉዳት

[77] የግብረ ወሲብ ድክመት (ስንፈተ ወሲብ)፡- የሕመም መንስኤ ከዛር አጋንንት እንደሚሆን ይታሰባል። ስንፈተ ወሲብ፤ ሰፊና ውስብስብ ባሕርያት እንዳሉት መሪጌታ አማረ እና መሪጌታ ባሕረጥበብ ጠቁመው፤ ሰባት ዓይነት መለያና መገለጫ ምልክት እንዳለው ገልፀዋል። እነርሱም፡- "መንስኤ እስኪት (የወንድ አካል ብልትን የሚያነሳሳ)፣ መንፅኤ እስኪት (የሚያጠነክር)፣ ዘኢያወርድ (የሚያወርድ)፣ ለመፍትሔ እስኪት (ችግሩን የሚፈታ)፣ ለፀንኤ ወሲብ (ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ጥላቻ)፣ ውኃ ሽንት ለሚከለክለው" በማለት በተለያየ ይዘት እንደሚተገበር አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 22/01/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

በመለየት፤ የታመመ አካልን ወደ ነበረበት ጤናማ አቋም ለመመለስ የተቃርኖ ሕክምና እንደሚተገበር የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡

በአጠቃላይ የሕመሙ ባሕርይ እና የሚሰጠው ሕክምና በተቃርኖ ይዘት ላይ የተመሰረተ ሲሆን በምርመራ ሂደት የተለየው ባሕርይ በመድኃኒት ምጣኔ፣ አሰጣጥ፣ ውሳኔ እና አተገባበር ላይ ጉልህ ድርሻ እንዳለው ይታሰባል፡፡ በተቃርኖ ሕክምና ልማድ፤ ለሚያቃጥል ሕመም የሚያበርድ፣ ለሚያሳብጥ የሚያሟሽሽ፣ ለሚያጠነክር የሚያላላ፣ መግል ለያዘ (ለበሰበሰ) ቁስል ማድረቂያ፣ ለተሰነጠቀ አካል መግጠሚያ፤ ስረስር ለሚገባ ሕመም ሰርስሮ የሚያወጣ፣ ለሚያደክም ማጠንከሪያ፣ ለተጨማደደ ቁስል ማፍታቻ ቅባት፣ ለሚያተኩስ ሕመም ማቀዝቀዣ መድኃኒት እንደሚሰጥ፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 6.4 የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች ምን ናቸው? እንዴት ይተገበራሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል፡፡
በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የጤና እክል ሲከሰትና ሲያጋጥም፤ ከሕመም ለመፈወስ፣ ከችግር ለመውጣት፣ ከጭንቀት ለመገላገል፣ ዕኩይ ሥራን ለመግታትና ለመቆጣጠር፣ የአራቱን ባሕርያት (የባሕርይ ሥር) "መጣላትና መዛነፍን" ለማስታረቅ እና ለማመጣጠን፤ ንስሃ፣ ፆም፣ ፀሎት፣ ስግደት፣ ምፅዋት፣ ምርቃት፣ ፀበል እና ምግብ እንደ መፍትሔ ቀርበዋል፡፡

"የሰው ልጅ አካል የእግዚአብሔር ሕንፃ ነው" ይላሉ መሪጌታ ስንታየሁ፡፡ ሕንፃውን ሲያቆም እና "ሕልው" አድርጎ ሲገነባ፤ በአራት ሥጋዊ ባሕርያት ላይ ሶስት የነፍስ (ልባዊት፣ ነባቢት እና ሕያዊት) ገቢርን ጨምሮ አካልን ከዐፈር አንጾ አቁሞታል፤ ተብሎ ይታሰባል፡፡ የሰው ልጅም ከነዚህ ባሕርያት ስለተገኘ፤ በሕይወት ዘመኑ ለሥጋ አካሉ "ምግቡን ከምድር ቡቃያ" [ከሥነ ምህዳር ውጤቶች ይመገባል] ይበላል፡፡ የሰው ልጅም፤ የዕድሜ ገደቡን ጨርሶ ወደ መጣበት ዐፈር እስከሚመለስ ድረስ፤ በሕይወት ዘመኑ የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች ለመላመድ፣ ለማለፍ እና ለመውደቅ፤ በሕመም ፈወስን፣ በሃጢያት ንስሃን፣ በሞት መውለድን፣ በርሃብ ጥጋብን፣ በብርድ ፀሐይን፣ በጨለማ ብርሃንን፣ በማጣት ማግኘትን፤ እየተካና እያፈራረቀ የዓለም ሕይወትን ተስፋ አድርጎ እንደሚኖር ገልፀዋል (ከተቡው አባላት መካከል በመሪጌታ ስንታየሁ የቀረበ፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)፡፡

መሪጌታ አዲሱ ደግሞ፤ የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ የሚያጋጥሙትን የጤና መዛነፍ እና መቃወስ ለማስተካከል፣ የጤና ኃይል ሚዛኑን ለማመጣጠን፣ የባሕርይ ሥር ምጣኔ ገቢርን ተገንዝቦ፤ ሕክምና ለመስጠት የሃይማኖት አባቶች እና የባህል ሐኪሞች[78] ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ)።

የሰው ልጅ በሥጋ ባሕርይ ፍላጎቱ ምክንያት፤ ለአካሉ ጤንነት እና ደኅንነት መሬት የአፈራችውን አዝርዕት (ዕፅዋት)፣ እንስሳት፣ ማዕድናት እና ነፍሳትን አድኖ፣ አስሶ እና "ቃርሞ፤ መናውን [ልብስና ጉርሱን] ሰብስቦ ይበላል" በማለት ደብተራ መልኩ ይገልፃሉ። ለሥጋው ምቾት፣ ማደሪያ፣ እድገት፣ ማረፊያ፣ ምግብና እና ፈውስ በአካባቢው የሚገኙ ግብዓቶችን አዘጋጅቶ ይጠቀማል። "ፍጥረት ሁሉ... ዓለም የሰጠችውን ሰብስቦ ይበላል እንጂ፤ በራሱ ፈጥሮ ለሆዱ ምግብ፣ ለሕመሙ ፈውስ አይሰራም፤...እራቁቱን እንደመጣ ባዶ እጁን ይሄዳል። አንድዬ በምድር የፈጠረለትን በሰጠው ሕሊና አስቦ፣ መጥፎና ደጉን ለይቶ፤ ...በላቡ እንዲኖር ባዘዘለት መሰረት እድሜ ልኩን ሲባትል ይኖራል" ይባላል (ደብተራ መልኩ፣ ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ)።

በተመሳሳይ መልኩ ቄስ አብርሃም፤ የሰው ልጅ ከሥነ ምህዳር የሚገኙ ግብዓቶችን ሰብስቦ ለሆዱ ምግብ፣ ለአካሉ ልብስ፣ ለሕመሙ ፈውስ የሚሆኑ መድኃኒቶችን "ፈጣሪ በምድር አዘጋጅቶ፣ በዓይነት በዓይነቱ፣ በወገን በወገኑ ለይቶ እንዳስቀመጠለት" ይገልጻሉ (ቃ.መ፤ 01/05/2011 እብናት)። የባህል ሕክምና ባለሙያዎች የአካባቢያቸውን ልማድ፣ ሃይማኖት፣ ዕውቀትና ተግባርን በማስተሳሰር፤ የሥነ ምህዳር ውጤቶችን መሰረትና መነሻ በማድረግ ለሕይወት መቅሰፍት፣ ለአካል ቁስል፣ ለመንፈስ ጭንቀት የሆኑ የሕመም ዓይነቶችን እንደሚፈውሱ፤ የመስክ መረጃዎች ገልጸዋል። የጤና ኃይል ሚዛን በምን ምክንያት ይዛነፋል? እንዴት ይስተካከላል? ሲባል፦

---

[78]እንደ መሪጌታ መንግስቱ ገለፃ፤ "የሰው ልጅ በሥጋዉ ምድራዊ አካል፤ በነፍሱ ሰማያዊ እና በመንፈሱ ሕያዊ አካል ስለሆነ፤ በሥጋው ከንቱ [በሥጋ አካሉ ምድራዊ፣ ሟችና ረጋፊ ነው]፣ በነፍሱ ክቡር፣ በመንፈሱ ከመላእክት የላቀ" መሆኑን ገልፀው፤ "የአንድዬን ሕንፃ ያፈረሰ [የሰው ሕይወት ያጠፋ]፤ በምድርም ሆነ በሰማይ ይጠየቅበታል" በማለት አስረድተዋል። የሰው ልጅ ክቡር፣ የፈጣሪ አምሳልና ስሪት ስለሆነ ለሕይወቱ ልዩ ጥንቃቄ እና ክብር እንደሚገባው ጠቁመዋል። አንድ ሰው በሕይወት ሲኖር ለአካሉና ለነፍሱ ምቾት የሚነሱ የሕመም ዓይነቶችን በመፈወስ፣ በማስተማርና በመከወን ከፈጣሪ ቀጥለው፤ የሃይማኖትና የባህል ሐኪሞች መፍትሔ እንዳላቸው ገልፀው፤ የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎችም "ሥጋዊ አካልን" በማከም የፈውስ አካል እንደሆኑ መክረዋል (ቃ.መ፤ 10/03/2011 እብናት)።

በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል እንደተጠቀሰው፤ በፍጥረት ሕይወት ውስጥ አራቱ የሥጋ ባሕርያት ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃና መሬት በተመጠነላቸው የተፈጥሮ ባሕርይ ሕግ፣ ልክ እና ሚዛን ላይ ሲገኙ የጤና መሰረት ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ የአራቱ ባሕርያት መጣላት፣ መዛነፍ፣ ቦታቸውን መልቀቅና ሚዛናቸውን መሳት ለሕመምና ለሞት መንስኤ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ የሰው ልጅ በአካሉ የነፋስ፣ የእሳት፣ የዉኃና የመሬት ባሕርይን ይዞ ስለተሰራ ከአራቱ አንዱን ባሕርይ ቢያጣ ሕይወት አልባ አካል፣ ቁስ አካል፣ "ትቢያና ዐፈር ይሆናል"፤ በማለት መሪጌታ ባሕረጥበብ ይገልጻሉ (ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)፡፡

እነዚህ ባሕርያት ተስማምተው፣ ተዋሕደው እና ሰምረው በተሰጣቸው ገደብ፣ ልክ እና ጊዜ ሲገኙ የጤና እና የሕይወት ኃይል ሚዛን ይጠበቃል፡፡ በአንጻሩ የተሰጣቸውን ገደብ፣ ልክና ደረጃ በማለፍ ዘመናቸውን ጥሰው፤ ገደባቸውን አልፈው በአካል ውስጥ ገነው ወይም አንሰው ሲገኙ፤ የጤና ኃይል ሚዛን ይዛነፋል፤ አካላዊ ሥጋ ይታመማል፤ ነፍስ ትጨነቃለች፤ ሕይወት ትናወጣለች፤ ሕመም ሲፀና "ሥጋ እና ነፍስ ውሕደታቸውን እረስተው ፍቺ ይፈፅማሉ፤ ምድራዊ ዓለም ይቋጫል" በማለት መሪጌታ ብሩህ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 18/06/2011 ፋርጣ)፡፡
በተመሳሳይ መልኩ ሠናይ ደግሞ፤ "ከአራቱም ባሕርያት ያልተፈጠረ አንድም ፍጥረት የለም፡፡ እነዚህ አራቱ ባሕርያት በፍቃደ እግዚአብሔር ይጣላሉ፣ ይሸናነፋሉ፤ [በአንዱ ገቢራቸው ይታረቃሉ፤ ይስማማሉ]፤... እግዚአብሔር... አራቱን ባሕርያት አዛምዶ፣ አዋሕዶ፣ አስማምቶ ትቷቸዋል" በማለት ገልፀዋል (2009፤ ገገ.14-16)፡፡ ልባዊት፣ ነባዊትና ሕያዊት ደግሞ "የነፍስ ባሕርያት ሥር ተምሳሌትና መሰረት ናቸው"፤ በማለት መሪጌታ አማረ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ አራቱ ባሕርያት ምን ዓይነት ተግባር እና ተምሳሌት አላቸው? በምን ይወከላሉ? ለምን? ሲባል እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል፡፡

ሊቀጠበብት አብርሃም አራቱ ባሕርያት በተፈቀደላቸው ዘመን፣ ወቅትና ቦታ ገነው እና ነግሰው በመውጣት በፍጥረተ ዓለሙ አካል ላይ ጎልተው እንደሚታዩ ጠቁመዋል፡፡ በፍጥረት ዓለም፤ በልጅነት፣ በወጣትነት፣ በጎልማሳነት እና በሽምግልና ጊዜ የተመደበላቸውን ባሕርይ በመያዝ፤ የሕይወት ዑደት ተጠንስሶ እንደሚቋጭ ይታሰባል፡፡ በሕይወት ዘመን ሂደት ባሕርያቸውን ጥሰው ሲሄዱ ወይም ሲጠፉ ሕይወት ሚዛኗን ትስታለች፤ ጠባይዋን በመቀየር "በቀውስና በጭንቀት ትናጣለች፤ መሰረቷን ታጣለች"፤ ተብሎ ይታመናል፡፡ አራቱን ባሕርያት

ለማስማማት፣ ለማስታረቅና ለማዛመድ ሶስት ሶስት ግብር ስለተሰጣቸው፤ ዞረው ዞረው "በምስጢር ይገናኛሉ፤ በተውኅቦ ይገለጻሉ" ይባላል (ቃ.መ፤ 05/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ ከዚህ አንፃር የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ምስል 14፡- የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች ማሕቀፍ




ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች፤ በጥናቱ አቅራቢ የተዘጋጀ ምስለ ማሕቀፍ ሚያዚያ/2011 ዓ.ም

የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች ማሕቀፍ ይዘት እንደሚያመለክተው፤ የሕይወት ዑደት ከመሬት ባሕርይ ተነስቶ በነፋስ እያደገ፣ በእሳት እየበሰለ፣ በወኃ እየደረጀ፣ በመሬት ይቋጫል፡፡ የቀስት ምልክቶች ከልጅነት እስከ ሽምግልና ያለውን ሂደት፣ እድገትና የዕድሜ ዘመን ለውጥን ይጠቁማሉ፤ በማዕቀፉ መሃል የሚገኘው ክብ ይዘት፤ የሰው ልጅ የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ

ስልቶች በተለያየ አቅጣጫ እና ሂደት ያላቸውን ተግባር ያመለክታል። በክብ ማሕቀፍ እና በመስመር ተሳስረው የቀረቡ ይዘቶች ደግሞ የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶችን ትስስር፣ ግንኙነትና መስተጋብርን ይገልጻሉ። በአራት ማዕዘን የቀረቡ ተግባራት የአራቱን ባሕርያት ጥቅል ይዘትና ማዕከላዊ ጭብጥ ይጠቁማሉ። የአራቱ ባሕርያት መግነንና መክሰም በሕይወት ዑደት ሂደት ውስጥ እንዴት ይገለጻል?

መሪጌታ ስንታየሁ፤ የነፋስ ባሕርይ ሲገን፤ እሳትን ያጉነዋል፣ ያበረታዋል፣ እርጥብና ደረቁን ያስበላዋል፤ ውኃን ያማተዋል፣ ይበጠብጠዋል፣ ከመሬት አንስቶ "በሰማይ" ይበትነዋል፣ ከአለት ጋር ያላትመዋል፣ ያጋጨዋል፣ ያስጮኸዋል፣ አረፋ ያስደፍቀዋል፤ መሬትን ደግሞ ያቀጠቅጣታል፣ ሆዷን በርብሮ የተሸከመችውን "ግሳግስ" ያስተፋታል፤ ተብሎ ይታሰባል (ቃ.መ ፤14/03/2011 እብናት)። ንፈስ ልጓሙን ሲስት ድንገት ደራሽ፣ ገስጋሽ እና ተራማጅ ቢሆንም በሌሎች ባሕርይ እና ገቢር ይሸነፋል። በመሬት ይከለላል፣ ይገደባል፣ ይጋርዳል፤ በዉኃ ደግሞ ይረጋጋል፣ ይሰክናል፣ እርጥበት ይሸክማል፤ ይባላል (ደብተራ ጥላሁን እና አቶ ሞገስ፣ ቃ.መ፤ 03/03/2011 እብናት እና 22/06/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

እሳት ሲበረታ፤ ዉኃን ያፈላዋል፣ ያንተከትከዋል፣ ገቢሩን አስቶ በማትነን ያደርቀዋል፤ መሬትን ይጠብሳታል፣ ውስጧን ያምሳታል፣ አብስሎ ያሳርራታል፣ ክሰል እና አመድ ያደርጋታል። ዉኃም ገደቡን ሲያልፍ፤ እሳትን ያጠፋዋል፤ ነፋስን ይጥሰዋል፤ መሬትን ይውጣታል፤ ተብሎ እንደሚታሰብ መሪጌታ አዲሱ ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 19/01/2011 ዓ.ም ፋርጣ)። መሬትም ገደቧን እና ደረጃዋን ስታልፍ እሳትን ታዳፍነዋለች፣ ታጨልመዋለች፤ ነፋስን ትገድበዋለች፤ ዉኃን ትመጠዋለች፣ ትውጠዋለች፤ በሽታ ይከሰታል፣ ሕይወት ይጠፋል፣ "ፅልመት" (ጨለማ) ይነግሳል። እነዚህ ባሕርያት በፍጥረት ዓለም ውስጥ እርስ በእርስ የሚጣሉበት፣ የሚሸናነፍበት፣ የሚከስሙበትና የሚገኑበት ወቅትና ጊዜ ቢኖርም፤ በምጣኔ እና በልክ ሰምረው ሲገኙ ለፍጥረት ዓለሙ ሰላም፣ ጤና እና የሕይወት ቤዛ፤ ልብስና ጉርስ ሆነው እንደሚያገለግሉ፤ ይታሰባል (መሪጌታ ስዩም እና አቶ ደሴ፣ ቃ.መ፤04/02/2011 እብናት እና 25/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

ከባሕርያቱ ይዘትና ተግባር በመነሳት ነፋስ እና እሳት ባላቸው ጉልበትና ኃይል፤ በመንፈስ፣ በፍጥነት እና በቀላልነት ይመሰላሉ። መሬት እና ዉኃ ደግሞ በክብደት፣ በአካለ ሥጋ፣ በሚጨበጥ ቁስና በሚዳሰስ አካል ይወክላሉ። ነፋስ እና እሳት እስትንፋስን እና መንፈስን

በመወከል በፍጥረት አካል ላይ ሕልው ሆነው ይታያሉ። ጥፋታቸው ከባድ፣ ቁጣቸው ኃይለኛ፣ ተራማጅና ተስፋፊ ቢሆኑም "ለፍጥረት አካል ጨው ናቸው። እንደ ወንድ ዘር ፍሬ በማንኛውም ፍጥረት አካል ላይ ገቢራቸውን በመጣል፤ ...በመጠን ይገኛሉ እንጂ አብዝቶ የሚሸከማቸው እና የሚጠቀማቸው የአካል ሥጋ የለም" በማለት መሪጌታ ፋንታሁን ይገልጻሉ (ቃ.መ፤ 19/01 /2011 ፋርጣ)።

መሬትና ዉኃ፤ የሕይወት መሰረት፣ ማደሪያ፣ መኖሪያ፣ ምንጭ፣ የፍጥረት አካል መነሻ እና መጠለያ፤ ምግብና መጠጥ በመሆን አገልግሎት ይሰጣሉ። በአካላቸው ተሸክመው፣ በሆዳቸው አርግዘው ከአብራካቸው "አካልና ነፍስ ሲዋሃዱ ሕይወትን" ይፈጥራሉ። የሕይወት ማደሪያ፣ የዓለም መታያ፣ ማረፊያ፣ ምግብና መጠጥ ተደርገው ይቆጠራሉ። የዓለም ፍጥረት እንደየባሕርይው "የተፈቀደለትን እየበላና እየጠጣ እድሜ ዘመኑን ጨርሶ ወደ መጣበት መሬት ይመለሳል" (ደብተራ መኀሪ፣ ቃ.መ፤ 13/03/2011 እብናት)፤ የሕይወት ዑደት እና የዓለም ምስጢር[79] ይቀጥላል። አራቱ ባሕርያት በፍጥረት አካል ውስጥ ምን ዓይነት ጠባይ፣ ዘመን፣ ተግባርና ውክልና አላቸው?

አራቱ ባሕርያት በፍጥረት አካል ውስጥ ገነው የሚወጡበት ዘመን እና ከስመው የሚታዩበት ወቅት እንዳለ፤ ከዚህ በላይ ተብራርቷል። ሕይወት በጥንስስ እና በፅንስ ይፈጠራል፤ ይበቅላል፣ ይወለዳል። በቡቃያ እና በልጅነት ማደግ ይጀመራል። በዚህ ዘመን የነፋስ ባሕርይ በአካል ውስጥ ጎልቶ ይታያል፤ ይባላል። ነፋስ የሕይወት ጥንስስ በመጀመር አካልና ሥጋ የሚዛመዱበት "የሕይወት ክብሪት ነው"፤ ወደ ሕይወት እና ሕያው አካል ያሻግራል፤ ተብሎ ይታሰባል። የሰው ልጅ፣ እንስሳት፣ ዕፅዋት እና ወቅቶች በአራቱ ባሕርያት የተለያየ መልክ፣ የሕይወት ዑደት እና ክስተት እንዳላቸው፤ ይነገራል። የሕይወት መጀመሪያ ምዕራፍ የሆነው ነፋስ፤ "በጮርቃነት"፣ በእንጪጭነት፣ በለምለምነት፣ በለጋነት፣ በልጅነት፣ በዘርና በቡቃያ ዘመን ይመሰላል (ቄስ ማስረሻ፣ እማሆይ ለተብርሃን እና ቄስ ብርሃኑ፤ ቃ.መ፤ 21-28/06/2011 ፋርጣ እና እብናት በቅደም ተከተል)።

---

[79]"ዓለም" (መሬት) ከመናፍስት እስከ ግዑዛን፣ ከደቂቅ እስከ ግዙፍ አካል የሚገኙባት የፍጥረት መኖሪያ እንደሆነች መሪጌታ መንግስቴ እና አቶ ሞላ ያስረዳሉ። ለአብነት ያህል፡- "ዕፀ ከንቱ" የምትባል ዕፅዋት በፀደይ ወራት በአንድ ቀን በቅላ፣ አድጋ፣ አብባና አፋርታ ትረግፋለች፤ ከትንኝ ነፍሳትም ጧት ተወልደው አድገው፣ እንቁላል ጥለው ማታ የሚረግፉ፤ የእበት ትል በዕለት ተፈጥረው አድገውና ኖረው እንደሚጠፉ ጠቁመዋል። ከዚህ በተቃራኒ "ከመቶና ከአምስት መቶ ዓመት በላይ" የሚኖሩ እንደ ኤሊ፣ ዝሆን እና አሳነባሪ መገኛ፣ ምግብና መጠለያ በመሆን ከጥቃቅን እስከ ግዙፍ አካል መኖሪያ እንደሆነች ያስረዳሉ። መሬት የፍጥረት ዓለሙ የሕይወት ምንጭ፣ አሳዳጊ፣ መጋቢ፣ አቃፊ፣ ተንከባካቢ፣ ማኖሪያ፣ መፈጠሪያ እና ማረፊያ በመሆን የእናትነት ሚና እንዳላት ይገልጻሉ (ቃ.መ፤10/03/2011 እብናት 22/06/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

ይህ ዘመን የፍጥረት መጀመሪያ ክፍል በመሆን፤ በጀማሪነት፣ በልጅነት፣ በድንግልና፣ በንጋት፣ በብርሃን ጮራ፣ በፀደይ ወራት፣ በሃሳብና በዕውቀት ምንጭ ይገለጻል፤ ይመሰላል፤ ይወከላል። በዚህ ወቅት የነፋስ ባሕርይ ጎልቶ ስለሚታይ፤ በአካል የመቅለል፣ የመሮጥ፣ የመብረር፣ ጎንበስ ቀና ማለት እና እረፍት አልባ እንቅስቃሴ ይታያል። በአካል የደከመን ለማጠንከር እና ለማደርጀት ምግብ ያስፈልጋል። በዚህ ወቅት "ልጅን በጡት እህልን በጥቅምት" መጠበቅ፣ መከባከብና ማሳደግ ነው፤ ይባላል። በማኅበረሰቡ ሃይማኖት፤ ልጆች እስከ ሰባት ዓመት የመጾም ግዴታ የለባቸውም፤ ሥጋዊ ባሕርይ አይታይባቸውም፤ ክፉ ደጉን አይለዩም፣ ኀጢያት አይሰሩም፣ ንጹሕ ናቸው፤ ተብሎ ይታሰባል (መሪጌታ ገብረመድኅን፣ ቃ.መ፤ 25/04/2011 ሊቦ ከምከም)። የባሕርይ መደባቸውን በመከተል የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች[80] በዋናነት በልጅነት እድሜና ዘመን የሚያስፈልጉ ባሕርያት፤ "ለአካል ሥጋ" ምግብ (መሬት እና ውኃ)፤ "ለነፍስ" ደግሞ "ምርቃት እና ምስጋና" መስጠት፤ የፈውስ ኃይል እና የሕይወት መስመር መሆኑን፤ መሪጌታ ዘላለም እና አቶ ታከለ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 20/04/2011 ፋርጣ እና 4/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

ልጆችን፤ ተንከባክቦ ማሳደግ፣ ማብላትና ማጠጣት፣ በይዘትና በዓይነት አፈራርቆ መመገብ፤ አካላቸው እንዲደረጅ፣ አዕምሯቸው እንዲዳብር እና ጤናማ እንዲሆኑ፤ በጡትና ምግብ መደገፍ ለእድገትና አዕምሯዊ ብስለት "የማይተካ ሚና" እንዳለው የጤና ባለሙያዎች ይመክራሉ (የተቡው አባላት፣ ቃ.መ፤ 26/06/2011 እብናት)። በእብናት ወረዳ የሥርዓተ ምግብና የሕጻናት ጤና ቁጥጥር ባለሙያ የሆኑት አቶ ጋሻው፤ በሰው ልጅ የእድገት ምዕራፍ ውስጥ "ከእርግዝና እስከ ሁለት ዓመት ያሉ አንድ ሺህ ቀናት፤ በተመጣጠነ ምግብና በጡት ካልተያዙ፤ አስፈላጊውን እንክብካቤ ካላገኙ፤ በቀጣይ እድገትና ሕይወታቸው ላይ ጥቁር ጠባሳ ጥለው" እንደሚያልፉ ገልጸዋል። ለሕጻናት እና ለልጆች እድገት እና አዕምሯዊ ብስለት ጡት እና የተመጣጠነ ምግብ የማይተካ ሚና እንዳላቸው አስረድተዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ጋሻው፣ ቃ.መ፤ 26/06/2011 እብናት)።

[80]የጤና ኃይል ሚዛንን ለማመጣጠንና ለማስተካከል አራቱ ባሕርያት መሰረታዊ ይዘት እንደሆኑ የመስክ መረጃዎች አስረድተዋል። ምን ዓይነት ሕመም፤ የትኛውን ባሕርይ ያሳጣል? ይጎዳል? ለሚሉ ጥያቄዎች፤ የምርመራ ሂደት እና የበሽታዎች ባሕርይ ምድብ፤ የምርመራ ሂደትና እና የተቃርኖ ሕክምና በሚሉ ይዘቶች የቀረቡ ትንታኔዎችን ልብ ይሏል።

በልጅነት (በጀማሪነት) ዘመን የሚታዩ ባሕርያት በምግብ እና መጠጥ ደርጅተው አካል እየበረታ ሲሄድ ወደ እሳት ባሕርይ መሸጋገር ይመጣል፡፡ አካል እየጠነከረ፣ እየበሰለና እየተለወጠ፣ ኃይልና ጉልበት እያገኘ፤ ከለጋ ወደ ብስል፣ ከአበባ ወደ ፍሬ፣ ከልጅነት ወደ ወጣትነት ይለወጣል፡፡ በዚህ ወቅት እሳት የለዋጭነት ባሕርይውን እያጠነከረ፣ በሂደት ንፋስ ቦታውን እየለቀቀ ከልጅነት ወደ ጉርምስና፣ ወጣትነት ባሕርይ ይሸጋገራል፡፡ "ጥሬ ሥጋ በመጠኑ እሳት ሲነካው ጣፋጭ ይሆናል፤ ልጅነትም በእንክብካቤ አድጎ፤ ወጣትነት ሲነካው፤ ...በአካል ይጠነክራል፤ በዕውቀት እና በማስተዋል ይበስላል"፤ ተብሎ ይታመናል (መሪጌታ ልሳነወርቅ፤ ቃ.መ፤ 27/04/2011 ሲቦ ከምከም)፡፡

እሳት የለዋጭነት ባሕርይውን በመጠቀም፤ ለጋውን በማጠንከር፣ ጥሬውን በማብሰል፣ ቡቃያውን ፍሬ፣ እርጥቡን ደረቅ የማድረግ፤ የኃይል፣ የጉልበት፣ የጥንካሬ፣ የብስለት ዘመን እንደሆነ ይታሰባል፡፡ እሳት፤ የበጋ፣ የቀትር፣ የሙቀት፣ የብሩህ ጊዜ፣ የኃይልና የጉልበት ምንጭና ተምሳሌት ስለሆነ ዕፅዋት እና እንስሳት "አምሳላቸውን የሚተኩበት፤ የፍሬና የዘር ወቅት ነው" ይባላል (ቄስ አብርሃም፣ ቃ.መ፤01/05/2011 እብናት)፡፡ በዚህ ወቅት አካል ይዳብራል፣ ጉልበት ይጠነክራል፣ የጠረን መለወጥ ይመጣል፡፡ ወጣትነት በእሳት ይፈተናል፣ ጉልበትና ኃይሉን በማስተባበር ይሰራል፣ ይበላል፣ ይጠጣል፤ ሥጋዊ ፍላጎቱን ለማሟላት እና ዓለማዊ ሕይወቱን ለመምራት "ሌት ተቀን ይባዝናል"፡፡ ይህ ዘመን እና እድሜ በወግና በሥርዓት ከአልተያዘ እና ከአልተገራ ገደቡን ጥሶ ሲሄድ የብዙ ፍላጎት እና ምኞት ባለቤት ይሆናል፡፡ አብዝቶ መብላት እና መጠጣት ያስደስተዋል፤ ዝሙት መስራት ያምረዋል፤ በሄደበት ማግበስበስ፣ መሰብሰብ፣ መቀማት እና የራስ ማድረግን ይመኛል፤ በአንደበቱ ያስቀይማል፤ በጉልበቱ ይገፋል፤ ይባላል (ቄስ ብርሃኑ እና ደብተራ ጥላሁን፣ ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት እና 03/03/2011 ሲቦ ከምከም በቅደም ተከተል)፡፡

የወጣትነት (እሳት ባሕርይ) እድሜን በማጤን የጤና ኃይል ሚዛን ማስታረቂያ ስልቶች የነፋስና የውኃ ባሕርያትን በማገናኘት፤ አካላዊ ቁስል እና መንፈሳዊ ጭንቀትን ለመፈወስ አማራጭ መንገድ መሆናቸውን መሪጌታ ልሳነወርቅ ገልፀዋል፡፡ ከገደብ በላይ የተሸከመውን እና የአጠራቀመውን አካላዊ ሥጋ፣ ስሜት፣ ኃይልና ጉልበት ለመቀነስ፣ ለማስወጣት እና ለማብረድ "ንስሃ" (ጾም፣ ፀሎት እና ስግደት) እና ፀበል የፈውስ አካል እንደሆኑ ጠቁመዋል፡፡ ከመጠን በላይ "የሰበሰበውን" ሐብት ደግሞ በምፅዋት ሲያካፍል "ነፍስና ሥጋው ይታረቃሉ" ተብሎ ይታሰባል፡፡

በተለይ ለመንፈሳዊ ጭንቀት ፀሎት፣ ፀበል እና ምርቃት የፈውስ ኃይልና ምንጭ ተደርገው እንደሚወሰዱ፤ መሪጌታ ልሳነወርቅ ገልጸዋል (ቃ.መ፤ 27/04/2011 ሊቦ ከምከም)።

በዚህ ወቅት የሥጋ ፍላጎት እና ምኞት በርትቶ ገደቡን ሲስት ነፍስ ትጨነቃለች፣ ማረፊያ ታጣለች፣ ከፈጣሪዋ ትጣላለች፤ ሥጋ እየደለበ፣ ሆድ እየጠገበ፣ አካል እየደረጀ የእሳት ባሕርይ ገንፍሎ ሲወጣ፤ ክፉ ደጉን መለየት፤ ነገሮችን ማመዛዘን እና ማመጣጠን ይሳነዋል (ደብተራ መልኩ፣ ቃ.መ፤01/03/2011 ፋርጣ)። ኃይልና ጉልበቱን ተመክቶ ሰውን ይበድላል፣ በአንደበቱ ያስቀይማል፤ በሄደበት ይዘርፋል፣ ይነጥቃል፣ ነፍስ ያጠፋል፣ "በስሜት ፈረስ" እየተነዳ ለፍጥረት ዓለሙ የጥፋት ኃይል ይሆናል፤ ፈጣሪውን ይረሳል። ይህን ጠባይ ለመግራት፣ ለማስከን፣ ለመቀነስ እና ለመግታት፤ "ንስሃ" የፈውስ ኃይልና "የሕይወት መድኃኒት" ሆኖ ይቀርባል። በዚህ እድሜ የአለአግባብ የተከማቸን ኃይል እና ጉልበት ለማስወጣት፣ የደለበን ሥጋ ለመቀነስ፤ በንስሃ፣ በጾም እና በስግደት ሲቀጣ ይገራል፤ ይሰክናል፤ ይበርዳል ተብሎ ይታመናል (ደብተራ መኀሪ እና አቶ ታከለ፣ ቃ.መ፤13/03/2011 እብናት እና 04/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

ወጣትነት በአግባቡ ከተያዘ የእሳት አምሳል ቢሆንም፤ ጥሬውን ወደ ብስል፤ አበባውን ወደ ፍሬ የመለወጥ ኃይል ስላለው፤ በብሩህ ዘመን እና በብርሃን ይመሰላል። ወጣትነት በሥርዓት ከተመራ፤ ኃይልና ጉልበቱን፣ "ነፍስና ሥጋውን" አስተባብሮ ከሰራ የሕይወት ዘመን መተዳደሪያውን ይሰበስባል፤ ይባላል። ሕይወቱም "በሰላም፣ በጤና፣ በፍቅር እና በፍሬ ይባረካል"፤ ተብሎ ይታመናል (መሪጌታ፣ አማረ፣ ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

በአንጻሩ ገደቡን ስቶ ሲወጣ፤ "በቀውስ እና በጥላቻ ነፍሱ ትጨነቃለች፣ በሕመም ይቀጣል፤ በሞት ይነጠቃል" ተብሎ እንደሚታሰብ መሪጌታ በረከት ገልፀዋል። ከነዚህ ፈተናዎች ለመውጣት፣ በሕይወት ለመኖር፣ በፍሬና በፀጋ ለመባረክ፤ በጉልበቱ የበደለውን፣ በአንደበቱ ያስቀየመውን "በንስሃ" ይቅር ይላል፤ ይናዘዛል። "ንስሃ" ደግሞ የሥጋን "ልጓም አልባ ጉዞ" እና ፍላጎት በመግታት፤ የበደለን አካል በመቅጣትና በማድከም፤ የሰበሰበውን ኃይልና ጠባይ በማስወጣት፣ በመቀነስና በማሳሳት ወደ ሕይወት መመለሻ መንገድ ነው፤ ይባላል። በዚህ ወቅት ሥጋ ይበደላል፣ ፍላጎት ይገደባል፤ "ማግበስበስ" ይቀንሳል፤ "ሥጋ ትበደላለች፤ ነፍስ ትደሰታለች፤ ሕይወት ትረጋጋለች" ተብሎ ይታሰባል (መሪጌታ በረከት፣ ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት)።

ደብተራ ጥላሁን፤ ወጣትነት በኃይል ስለተሞላ "የሥጋን ልጓም አልባ ፍላጎት" ለማሟላት "ይባዝናል"፤ ያገኘውን ይሰበስባል፤ ያጠራቅማል፤ ኃይልና ጉልበት እየጨመረ ይሄዳል። በዚህ ወቅት የሥጋ ፍላጎቱ አይሎ፤ "የቆመበትን መሬት እና ፈጣሪውን ይረሳል" ይባላል። በምጣኔ፣ በልክ፣ በሕግ እና በሥርዓት ማደርን ይዘነጋል። "አግበስባሽ" ጠባዩ "በምፅዋት" (በመስጠትና በማካፈል) ይገራል፤ "ሥጋ ስትበደል፤ ነፍስ በፀሎትና በምርቃት ሐሴት ታደርጋለች" ይባላል። ከሚዛን በላይ የሰበሰበው ኃይልና ጉልበት ደግሞ በፆም፣ በስግደት፣ በፀበል እና በላብ ሲወጣ "የነፍስ እና የሥጋ ጋብቻ ይሰምራል፤ በቃል እግዚአብሔር ማደር ይመጣል፤ …በጉብዝናህ ጊዜ ፈጣሪህን አትርሳ" ይባላል። በሂደት በልክ፣ በምጣኔና በሚዛን ማደርን ሲማር፤ ፈጣሪውን አስቦ፣ ነፍስና ሥጋውን አስማምቶ "ከሕይወቱ ታርቆ ይኖራል፤ የሥጋ ፍላጎት ይሰክናል" ይባላል (ደብተራ ጥላሁን፣ ቃ.መ፤ 03/03/2011 ሊቦ ከምከም)።

በአጠቃላይ በምግብ ኃይል  አይሎ የወጣውን የእሳት ባሕርይ፤ በነፋስ እና በዉኃ ኃይል አመጣጥኖ፣ አረጋግቶ እና አቀዝቅዞ፤ አካልን ከሚያደቁ እና መንፈስን ከሚያስጨንቁ አጋንንት በመፈወስ ሕይወትን ወደ ቦታዋ መመለስ እና ሚዛኗን ማስተካከል፤ በባህል ሕክምና ልማድ የዕለት ተግባር እና የሕይወት መርህ ተደርጎ ይቆጠራል። በሂደት የእሳት ባሕርይ እየቀነሰ በቦታው የዉኃ ባሕርይ ይተካል። በዚህ እድሜ በወጣትነት የደለበ አካል፣ የተከማቸ ኃይልና ጉልበት ቀስ በቀስ እየበረደ ይሄዳል። በወጣትነት ዘመን የተሰበሰበ ሐብት እና ዕውቀትን በመያዝ ወደ ዉኃ ባሕርይ ይሸጋገራል (የሕይወት ዑደት ይቀጥላል)። መሪጌታ በረከት "የዉኃ ባሕርይ በጎልማሳ እድሜ ይመሰላል" ይላሉ (መሪጌታ በረከት፣ ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት)። ዉኃ፤ የፍጥረት ዓለም "ቤዛ"፤ መጠጥ እና መጠለያ በመሆን የሕይወት ማደሪያ እና ማቆያ ተደርጎ ይታሰባል። የዉኃ ባሕርይ በንጽህና፣ በብርሃን እና ሚዛናዊ በመሆን የማኅበረሰብ ችግሮችን በመፍታት "አምድ ነው"፤ ይባላል። በእሳት ዘመኑ የአከማቸውን ዕውቀት፣ ተግባር፣ ሐብትና ንብረት ሰብስቦ በመያዝና መጥኖ በመጠቀም "የሰከነ ሕይወት" እንደሚመራ ደብተራ መልኩ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ)።

በዉኃ ባሕርይ ምድብ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በወጣትነት ዘመናቸው የመሬት (ምግብ) ኃይልን አብዝተው ወይም አሳንሰው ሲጠቀሙ የሕይወት ሚዛን ይዛነፋል፤ ሕመም ይከሰታል፤ ተብሎ በባህል ሐኪሞችና በሃይማኖት አባቶች ይታሰባል። በዚህ ጊዜ "አካል ከብዶ ወይም ደክሞ ሲገኝ ነፍስ ትበደላለች፤ …በአጋንንት ትመታለች" ይላሉ መሪጌታ መንግስቴ። ከዚህ ሕመምና ጭንቀት ለመውጣት በታካሚው አካል እና መንፈስ ውስጥ ምን ኃይል በዝቷል ወይም አንሷል? በማለት

ምርመራ ይካሄዳል። ከመጠን፣ ከሚዛን እና ከልክ ያለፈ ሐብትና ንብረት አከማችቶ ሲገኝ "ሐብት ንብረቱን አስበው አጋንንት ይቀርቡታል፤ መዋያና ማደሪያ ያደርጉታል" በሂደት አካላዊ ድቀት እና መንፈሳዊ ጭንቀት ያጋጥመዋል፤ ተብሎ ይታመናል (መሪጌታ መንግስቴ፣ ቃ.መ፤ 10/03/2011 እብናት)።

ይህን ተግባርና ሂደት ታሳቢ በማድረግ ለመንፈሳዊ ጭንቀት ፀሎት፣ ፀበል፣ ምፅዋት እና ምርቃት፤ አካሉ ቀሎት ሚዛኑን ለሳተና አቅም ላነሰው "ጎኑን በሚጠግን፣ ሥጋውን በሚያደረጅ ምግብ እና መጠጥ" ይታከማል። አካሉ ለከበደው፤ የተሸከመውን ለመቀነስ፣ ለማራገፍ፣ ለማሳሳት፣ ለማስወጣትና ለማስተካከል ደግሞ ፆም እና ስግደት የፈውስ ኃይል እና የሕይወት መንገድ መሆናቸውን፤ መሪጌታ አማረ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

የዉኃ ባሕርይ ዘመን ተጠናቆ፤ የመሬት እድሜ ሲተካ ከጎልማሳነት ወደ ሽምግልና ዘመን መሸጋገር ይመጣል። አካል እየደከመ፣ ኃይልና ጉልበት እየቀነሰ የመሬት ባሕርይ ሲጫነው መተኛትና መቀመጥን ማዘውተር የሽምግልና ባሕርይ እንደሆነ መሪጌታ አዲሱ ገልፀዋል። በሂደት ከእሳት ባሕርይ ይርቃል፤ አካሉ ይተሳሰራል፣ የፈለገውን እና የመረጠውን መብላት ይሳነዋል፤ ይባላል። በዚህ እድሜ ለሚከሰቱ ሕመሞች፤ ለመንፈስ ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ፀሎትና ፀበል የፈውስ አካል እንደሆኑ ይታመናል (መሪጌታ አዲሱ፣ ቃ.መ፤19/01/2011 ፋርጣ)።

አካልን ለሚያደቁ እና ለሚያደክሙ ሕመሞች፤ "አካልን የሚደግፉና የሚጠግኑ" ጥራ ጥሬ፣ ሥጋ እና ጎምዛዛ ጣዕም ያላቸው ምግቦች ተመራጭ መሆናቸውን፤ መሪጌታ መንግስቱ ገልፀዋል (መሪጌታ መንግስቱ፣ ቃ.መ፤11/04/2011 እብናት)። የሥነ ምግብ ባለሙያ የሆኑት አቶ ጋሻው፤ በሽምግልና እድሜ ጣፋጭ የሆኑ፤ ጮማ እና ቅባት የበዛባቸው ምግቦችን አብዝቶ መጠቀም ለሕመም መንስኤ እንደሚሆኑ ጠቁመው፤ "ማንኛውም ተመጋቢ ለስላሳና ጣፋጭ መጠጦችን፣ ስኳር፣ ጨው፣ ቅባትና ሥጋን በመቀነስ፤ ኃይል ሰጪና በሽታ ተከላካይ ምግቦችን በመጠቀም" በተወሰነ ደረጃ በሽታን መከላከል እንደሚቻል አስረድተዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ጋሻው፣ ቃ.መ፤ 26/06/2011 እብናት)።

የሽምግልና ዘመን "የሕይወት ትምህርት ቤት ነው፤ የሰፈር ዋርካ፣ የአገር አድባር ነው" ይባላል። "ክፉ ደጉን አይቷል፤ መውጣት መውረዱን ቀምሷል"፤ የወገን መከለያ፣ ማረፊያና መታሰቢያ በመሆን ማኅበራዊ አገልግሎቱን እንደሚወጣ፤ ይነገራል። ማኅበራዊ ጉዳዮችን ለመምራት፣ ለመፍታት፣ ለማስታረቅ፣ በጎ የሰራን ለመመረቅ፣ ለአካበቢ ሰላም እና ለሕይወት ማደሪያ ነው፤ ተብሎ ይታሰባል (አቶ አስማማው እና ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደመቀ፣ ቃ.መ፤ 20/01/2011 እና 19/06/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

በሌላ ፅንፍ ደግሞ፤ መሬት የምድራዊ ሕይወት መቋጫ እና የሥጋ አካል ማረፊያ ተደርጋ ትመሰላለች። በዚህ ባሕርይ፤ በብርሃን መድከም፣ መጥለቅ እና መንጠፍ፤ በክረምት ወቅት እና በጨለማ ትወከላለች። ሕይወት በእርጅና ዘመኗ፤ የእድሜ ገደብ፣ የነገሮች ማብቂያ፣ የተስፋ መቋጫ፣ የአካልና የነፍስ መዳከሚያና መፋቻ በመሆን የመጨረሻ ፅንፍ እና መዳረሻ ተደርጋ ትቆጠራለች። በፍጥረት ዓለም ውስጥ በንፋስ የተጀመረ የሕይወት ጥንስስ፣ በእሳት በስሎ፣ በውኃ ደርጅቶ፣ የሽምግልና እድሜውን ጨርሶ ወደ ዐፈር ይመለሳል። በዚህ ባሕርይ መሬት በሕይወት ዑደት ሂደት ውስጥ ሁለት ዓይነት ሚና እና ተግባር እንዳላት ይታሰባል (ደብተራ ጥላሁን እና እማሆይ ትጓደድ፣ ቃ.መ፤03/03/2011 እና 20/06/2011 ሊቦከምከም እና ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

በአጠቃላይ በጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች ይዘት ውስጥ አራቱ ባሕርያት በተገደበላቸው ዘመን ተመጥነው በልክና በሚዛን ሲገኙ የጤና መሰረት እንደሆኑ ይታመናል። የጤና መዛነፍ ሲከሰት፤ ሥጋ ለበዛበት፣ አካሉ ለከበደው፣ መንቀሳቀስ ለተሳነው፣ የሥጋ ባሕርይ ለተጫነው፤ ሸክሙን የሚቀንሱ፣ የሚያራግፉ እና የሚያራቁቱ ተግባራት ፆም፣ ስግደትና ምፅዋት እንደ ኃይል ሚዛን ማመጣጠኛ ስልት ቀርበዋል። ለአካል ቁስለት፣ ለአቅም ማነስ የሚዳርጉ የሥጋ አካል ሕመሞች ሲከሰቱ አካልን የሚያጠነክሩ እና የሚያበረቱ የመድኃኒት እና የምግብ ዓይነቶች ይሰጣሉ፤ በአንጻሩ ለመንፈስ ጭንቀት፣ ለአዕምሮ ሕመም ዓይነቶች ደግሞ፤ ፀሎት፣ ፀበል እና ምርቃት የድህነት እና የፈውስ አካል በመሆን የጤና ኃይል ሚዛንን በማደላደል ረገድ ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል።

## 6.5 የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ይዘታዊ ትንተና ቀርቧል። በትንታኔው መሰረት የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች እንደሚከተለው ተጠቁመዋል፡-

- በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ዓለማዊና መንፈሳዊ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም በአካባቢያቸው የሚከሰቱ የሕመም ዓይነቶችን መለየታቸው፤ ዓለማዊ የምርመራ ስልትና ሂደትን የሚከተሉ የባህል ሐኪሞች፤ ዕይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባዮሎጂካዊ፣ የታካሚን የሕይወት ዳራ እና መተዳደሪያ በማጥናት የሕክምና አገልግሎት መስጠታቸው፤ በመንፈሳዊ ኃይል እየታገዙ ወይም በዓለማዊ ዕውቀትና በመንፈሳዊ ኃይል ጥምረት፤ አካላዊ ቁስል እና አዕምሯዊ ጭንቀትን የሚፈውሱ የባህል ሐኪሞች እንዳሉ፤ በጥናቱ ተስተውሏል፡፡

- በሁለተኛ ደረጃ፤ በባህል ሕክምና ምርመራ ይዘት የሚተገበሩ የበሽታ ባሕርይ ምድቦች ድንገተኛና አጣዳፊ፣ ቆንጣጭና ሰርሳሪ፣ አቃጣይና አስለፍላፊ፣ አብራጅና አድካሚ፣ አንቀጥቃጭና አርገብጋቢ፣ አደንዛዥ እና አወፋሪ በማለት የበሽታ ባሕርይ ምደባዎች እንዳሏቸው፤ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

- በሶስተኛ ደረጃ፤ የበሽታ ባሕርይ እና የተቃርኖ ሕክምና ተግባራትን በማጤን፤ በምርመራ ወቅት የበሽታ ባሕርይ እና የሕክምና አሰጣጥ (የመድኃኒት) ሂደትን ፈትሸው፤ ከሕመሙ ባሕርይ፣ ስሜት እና ተግባር ጋር በተቃርኖ እንደሚከውኑ (ለሚያቃጥል ሕመም የሚያቀዘቅዝ መድኃኒት፤ ለሚያደክም በሽታ የሚያበረታ መድኃኒት እንደሚሰጡ)፤ ይስተዋላል፡፡

- በአራተኛ ደረጃ፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶችን መነሻ በማድረግ፤ የጤና ኃይል ሚዛን ሲዛነፍ አራቱን ሥጋዊ ባሕርያት ተከትለው የታካሚውን አቋም በማጤን፤ ንስሃ (ፆም፣ ፀሎት፣ ሥግደት፣ ምፅዋት)፣ ፀበል፣ ምርቃት፣ ምግብ፤ ለጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልት ሆነው መቅረባቸው፤ በጥናቱ ታይቷል፡፡

- አምስተኛ፤ የበሽታውን ባሕርይ፣ አካባቢያዊ ዐውድና ሁነትን በመገንዘብ፤ የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶችን በመተግበር፤ አካልን የሚያደቁ (ቁስለትን) እና መንፈስን የሚያስጨንቁ የሕመም ዓይነቶችን በመፈወስ፤ የሕይወት ዑደት እና አካላዊ ጠባይን በመረዳት የሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ፤ የጥናቱ ትንታኔ አረጋግጧል፡፡ በቀጥይ ምዕራፍ የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ ትንታኔ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሰባት፡- የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ ትንተና

በዚህ ንዑስ ርዕስ፤ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሥርዓተ ገቢር ዐውድ፣ የባህል መድኃኒት "ገቢር" ማስተካከያ ዐውዳዊ ስልቶች፣ የባህል መድኃኒት ቅመማ ይዘት እና ቅድመ ተግባራት፣ የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት፣ የባህል መድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ እንደሚከተለው ቀርበዋል። የመስክ መረጃዎች፤ ዐውድ-ተኮር እና የተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴሎችን በማስተሳሰር ተተንትነዋል።

## 7.1 የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ "ሥርዓተ ገቢር" ዐውድ

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ለመድኃኒት ግብዓት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ከተለያዩ የሥነ ምህዳር ቦታዎች ፈልገውና አስሰው ብዙኀኑን "ከዱር/ከጫካ" (ከወንዝ፣ ከገዳማት፣ ከተራራ፣) ጥቂቱን ደግሞ ከአካባቢያቸው (በግቢ፣ በመስኖ እና በእርሻ ማሳ) ሰብስበው፣ አዘጋጅተውና ቀምመው ለሕክምና አገልግሎት እንደሚጠቀሙ መሪጌታ ፍሬስብሃት እና መሪጌታ ሠረቀብርሃን አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 29/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 12/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሂደቱም በሥርዓተ ገቢር እንደሚመራ ገልፀዋል።

### ከቅድመ ክዋኔ በፊት የሚሟሉ ተግባራት፤

ማንኛውም የባህል ሐኪም መስክ ሄዶ ዕፀ መድኃኒት ከመሰብሰቡ በፊት የሚፈልገውን ዕፀ[81] ባሕርይ መለየት፣ የሚገኝበትን ሥነ ምህዳር ማወቅ፣ የመሰብሰቢያ ግብዓቶች ማሟላት፣ ዕፅ የሚቆረጥበትን ዐውድ መገንዘብ፤ የቅድሚያ ቅድሚያ ተግባር እንደሆነ ደብተራ መልኩ እና ሊቀጠበብት አብርሃም መክረዋል (ቃ.መ፤ 22/01/2011 ፋርጣ እና 30/01/2011 ፋርጣ እና ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

**ቅድመ ክዋኔ ተግባራት፡-** በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች፤ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሂደት፣ ሥርዓተ ገቢርና ዐውዳዊ ክዋኔ ምን ይመስላል? በአከዋወን ሂደቱ ምን ዓነት ተግባራት፣ ሥርዓትና ማሕቀፍ ይቀርባል? እንዴትና መቼ ይከወናል? ለምን ዓላማ?

[81] በዚህ ይዘት "የዕፅ ባሕርይ" ሲባል በታሳቢነት የማዕድናት፣ የነፋሳትና የእንስሳት ግብዓቶችን ባሕርይ ታሳቢ ያደርጋል።

ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት፤ በንጥል ጥናት ዘዴ የመስክ መረጃዎች ተሰብስበው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ ርዕሰ ጉዳዩን በጥልቀትና በትኩረት ለመከታተል፤ ሁለት የባህል ሕክምና ባለሙያዎች (ደብተራ መልኩ እና ሊቀጠበብት አብርሃም) ተመርጠው የመስክ ምልከታ እና ቃለመጠይቅ ተካሂዷል፡፡ የሁለቱም ባለሙያዎች የዕፀ መድኃኒት አቆራረጥ ሂደት፣ ሥርዓተ ገቢር እና ክዋኔ፤ ፀሎተ ድግምት፣ የሠዓት፣ የቀን እና የወቅት አመራረጥ፤ የቁስ አያያዝ እና አጠቃቀም፤ የቁጥሮች ልክ እና ምጣኔ፤ የአቅጣጫ አሰያየም፤ የዕፅ አቆራረጥና አቆፋፈር ሂደት ተመሳሳይ፣ ተቀራራቢ እና ወጥ የሚባል ሥርዓትን እንደሚከተሉ ከመስክ ምልከታና ቃለመጠይቅ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከደብተራ መልኩ ዘለቀ ጋር የተካሄደው የመስክ ምልከታ ዐውዳዊ ክዋኔ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## አስረጂ አንድ፤ ንጥል ጥናት ሁለት፡-

ደብተራ መልኩ ዘለቀ በፋርጣ ወረዳ በሰምናን ቀበሌ የባህል ሕክምና አገልግሎት በመስጠት በአካባቢው ማኅበረሰብ ይታወቃሉ፡፡ ደብተራ መልኩ፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ተግባርና ሥርዓት ከአያታቸው ጀምሮ ሲተገበር እና ሲተላለፍ የመጣ የቤተሰብ ልምድና ውርስ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ከአባታቸው መሪጌታ ዘለቀ ጋር በመሆን ለአካባቢው ማኅበረሰብ፤ በባህል ሕክምና ሙያ ለአስራ ሁለት ዓመት እንዳገለገሉ ጠቁመው፤ አባታቸው ካረፉ በኋላ አስራ ስድስት ዓመት እንደሰሩ አስረድተዋል፡፡ ከአያትና ከአባታቸው የወረሷቸውን የብራና መጽሐፍት (ዕፀ መድኃኒት እና መፀሐፈ ፈውስን) ዋቢ አድርገው፤ መመሪያና ደንቡን ጠብቀው፤ ለመድኃኒት አገልግሎት የሚውሉ ዕፅዋትን አንግሰው፤ ሥርዓተ ገቢሩን ፈፅመው፤ ፀሎተ ድግምት አድርሰው፤ ወቅትና ጊዜያቸውን ጠብቀው፤ የመድኃኒት ግብዓቶችን ከመስክ እንደሚሰበስቡ ተናግረዋል (ቃ.መ፤ 22/01/2011 ፋርጣ)፡፡

መስከረም ሃያ ሶስት ቀን ሁለት ሺህ አስራ አንድ ዓመት ምህረት፤ በዕለተ ረቡዕ ከንጋቱ 11፡10 ከመኝታዬ ተነስቼ ደብተራ መልኩ በአዘዙኝ መሰረት ዕፅዋትን ለመቅረብ፣ ለመቁረጥና ለማንገስ፤ የዕለት ፀሎት አድርጌ፣ ምግብና ዉኃ ሳልቀምስ፣ መፀዳጃ ቤት ሳልገባ፣ ከሰው ጋር ሳልነጋገር፤ "ምናምቴው እንዳይጣላህ" [አጋንንት] ብለው በአንገቴ አንጠልጥዬ እና በኪሴ ከትቼ እንድይዛቸው

የሰጡኝን ቋጠሮዎች ጨምሬ፤ ማስታወሻ ደብተር፣ ካሜራና ሪከርደር ይዤ 11:45 ከቤት ወጣሁ[82]::

ደብተራ መልኩ፤ በሕክምና መስጫ ቤታቸው ፀሎት አድርሰው ሲወጡ ሳይናገሩ ጎንበስ ብለው ሰላምታ ሰጥተውኝ ከአለፉ በኋላ፤ ከመኖሪያ ቤታቸው ታዛ በስተቀኝ በኩል ታስረውና ተሰቅለው ከተቀመጡ፤ የዕፀ መድኃኒት መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መካከል፤ የኮመል ዕፅ እጀታ የአለው ማጭድ፣ የቀንድ ካራ እና ከወይራ ዛቢያ የተሰራ መቆፈሪያ ይዘው 12:15 ከቤት ወጡ።

እሳቸው ከፊት እኔ ከኋላ ሆኜ አስራ አምስት ደቂቃ እንደተጓዝን ከቤታቸው ማዶ የሚገኝ "ሰሶች ቁንዲ" በሚባል ቦታና ተራራ ሥር ገባን። አካባቢው በዛፍ፣ በሃረግ፣ በቁጥቋጦና በአደይ አበባ ተሸፍኗል። ድንገት የደረስንባቸው የቆቅ፣ ዋኔስ እና መሰል አዕዋፍት እና የዱር ድመቶች (ሽለ መጥማጥ) ተንደፋድፈው ሲነሱ፣ ሲበሩ እና ሲሮጡ፤ እነሱም ደንግጠው የተጠጋቸውን አካል በማስደንገጥ፤ ቀልብ ይገፋሉ። በዚህ ሂደት የምረግጠው ድንጋይ፣ ሣርና ጤዛ አዳልጦኝ ሁለት ጊዜ ወድቄ ተነሳሁ፤ የሰጡኝን ቋጠሮ በጄ ይዤ በልቤ አማትቤ ጉዞዬን ቀጠልኩ፤ አልዞሩም፣ ጉዟቸውን ቀጠሉ። ትንሽ ከተጓዝን በኋላ በአለሁበት ቦታ እንድቆም በእጃቸው ምልክት አሳዩኝ። እኔ ከቆምኩበት በአማካይ አምስት ሜትር ራቅ ብለው፤ ለዕፅ መቁረጫ የያዟቸውን መሳሪያዎች አጠገባቸው በአለው የፅድ ዛፍ ላይ አንጠልጥለው፤ በማይነቃነቅ ጥቁር ድንጋይ ላይ ቆመው፤ ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አድርገው (አዙረው)፤ በለሆሳስ ከንፈራቸውን እያቀሳቀሱ፤ በተመስጦ ፊታቸውን ቋጠር ፈገግ እያደረጉ፤ ለሶስት ደቂቃ ፀሎተ ድግም አደረሱ።

የዕለቱ ፀሎት፤ በግዕዝ ቋንቋ የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፤ "አንቲ ዉእቱ፣ ዕፅ ብሩክ፣ ዕፀ ሕይወት፣ ዕፀ መድኃኒት ከመ ዕፀ ሕይወት፤ ዘውስተ ገነት ዘኮንኪ ዕፀ ሕይወት በዲበ ምድር ፍሬኪኒ ፍሬ ሕይወት ውእቱ ወዘበልዓ እምኔሁ ሕይወተ ዘለዓለም የሐዩ፤" የሚል ሲሆን፤ የአማርኛ ትርጉሙም፤ 'በገነት ውስጥ እንዳለችው የሕይወት ዕፅ፤ በምድር ላይ የሕይወት ዕፅ የሆንሽ፤ ሕይወትን የምትሰጪ፤ ዕፅ መድኃኒት አንቺ ነሽ። ፍሬሽም የሕይወት ፍሬ ነው። ከሱም የበላ

---

[82]የጧቱን ቅዝቃዜ ለመቋቋም ሹራብ ለብሼ ስወጣ፤ ወፎች ከማደሪያቸው ሳይወርዱ በየቦታው መጮህ ጀምረዋል። ከርቀት የቤተ ክርስቲያን ፀሎት ይሰማል። አልፎ አልፎ ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄዱ ሰዎች ነጠላ እና ፎጣ ለብሰው ሲሄዱ ይታያል። አንድ አባት በኔ ትይዩ መጥተው፤ አልፈውኝ ሲሄዱ "እንደምን አደርክ" ብለው ሰላምታ አቅርበው አለፉ። ከወገቤ ጎንበስ ብዬ ሳልናገር(በዕለቱ መናገር፣ ሰላምታ መለዋወጥና ከተለያየ ሰው ጋር ግንኙነት መፍጠር መድኃኒት ያረክሳል፤ ሥርዓተ ገቢር ያዛባል፤ ተብሎ ይታሰባል) ጉዞዬን ቀጠልኩ። 12:05 ሲሆን በደብተራ መልኩ መኖሪያ ቤት ደረስኩ።

የዘላለም ሕይወትን ያገኛል" በማለት ፀሎታቸውን ጨርሰው ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ተንቀሳቅሰው በአራቱም ማዕዘናት ተሳልመው "አምላኬ ባርክልኝ፣ ፀጋና በረከቱን አውርስልኝ፤ የፈውስና የምህረት እጅ አድርግልኝ አሜን" በማለት ከቆሙበት ጥቁር ድንጋይ ወርደው፤ ያስቀመጡትን ዕቃ አንስተው ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሄዱ (ፀሎትና ልመናው በለሆሳስ የቀረቡ ሲሆን፤ በወቅቱ የተገበሩትን በቃለመጠይቅ አስረድተዋል)፡፡

ፀሎታቸውን ጨርሰው ሲሄዱ እንድከተላቸው በእጃቸው ምልክት አሳዩኝ፡፡ አራት ሜትር አለፍ እንዳልን፤ እቃቸውን አስቀምጠው የዛፍ ቅጠል፣ አረምና ቁጥቋጦውን በእጃቸው ገለጥ፣ ገለጥ አድርገው አለፋ አለፍ እያሉ፤ የሚፈልጓቸውን ዕፅዋት ለይተውና መርጠው ለመሰበሰብ አዘጋጁ፡፡ በዕለቱ ለመድኃኒት ግብዓት የተመረጡ፤ ገበር እንቧይ፣ ልት፣ የዕባብ መድኃኒት፣ የድንጋይ ሽበት፣ የሙት አንሳ ሃረግ፣ እሬት፣ የምድር እንቧይ፣ ጥቁር ጠለንቾ እና የክትክታ ዕፅዋት ሲሆኑ፤ በዓይነትና በይዘት ለይተው፤ በቅደም ተከተል ሰበሰቡ፡፡

መጀመሪያ የድንጋይ ሽበት በእጃቸው ለቀሙ፤ ሁለተኛ የክትክታ ቅጠል ቆረጡ፤ ሶስተኛ ጥቁር ጠለንቾ አጨዱ፡፡ አራተኛ የዕባብ መድኃኒት ሥርና ግንዳቸውን ለይተው ቆፍረው አወጡ፡፡ የዕፀ መድኃኒት አቆፋፈር ሂደታቸው፤ መጀመሪያ ለመድኃኒት በተመረጡ ዕፅዋት ዙሪያ የሚገኙ ቅጠል፣ አረም፣ ሃረግና መሰል ይዘቶችን ቆርጠውና ነቅለው ካስወገዱ በኋላ፤ የዕፅዋቱ ሥር የሄደበትን አቅጣጫ ለማወቅ አራት ቦታ በያዙት "አዷማ" [መቆፈሪያ ዶማ ማለት ነው] ጫር ጫር አድርገው ዐፈሩን አነሱ፤ ጠረጉ፡፡ በሂደትም፤ በቁጥቋጦና በዛፍ ደረጃ የሚገኙትን ዕፅዋት ግማሽ ሥራቸውን ለይተውና ቆርጠው አወጡ፤ በሣር እና በሃረግ ደረጃ የአሉትን ሥርና ግንዳቸውን ሙሉ በሙሉ ነቅለው፤ ዐፈሩን አራግፈውና አስለቅቀው በያዙት ማዳበሪያ ውስጥ ከተቱ፡፡

በዚህ ሂደት፤ የዕለቱን ሥራና ተግባር ጨርሰው ሲነሱ "ተመስገን አምላኬ፤ አንተው ባርክልኝ፤ ለበረከት ካለው ይበቃል" በማለት የሰበሰቧቸውን ዕፅዋት በማዳበሪያ ይዘው፤ 3፡35 ሲሆን የእለቱን ተግባር አጠናቀው፤ ወደ ቤት ተመለስን፡፡ የዕለቱን ተግባር ከማስታወሻ ደብተር ባለፈ፤ ፈቃድ የተገኘባቸውን ይዘቶች፤ በቪዲዮና በፎቶ ግራፍ ለማስቀረት ተችሏል፡፡ ሂደቱን ለመጠቆምና ለማሳየት ያህል፤ ከዚህ በታች የቀረቡ የመስክ ናሙና ፎቶዎችን ይመልከቱ፡፡

ፎቶ ግራፍ 3፦- የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሂደትና የመስክ ተግባራት





1ኛ.ገበር እንጧይ ሲለዩ፤ 2ኛ.የምድር እንባይ ሃረግ ሲሰበስቡ፤ 3ኛ.የምድር እንጧይ ፍሬ ሲያሳዩ




4ኛ. የእባብ መድኃኒት ዕፅና አበባ ሲያሳዩ፤ 5ኛ. የእባብ መድኃኒት ዕፅ ሥር ሲቆፍሩ

ምንጭ፦- ደብተራ መልኩ፤ ከፋርጣ ወረዳ በጥናቱ አቅራቢ በቀን 23/01/2011 የተሰበሰበ፤

በዚህ ዐውድና ክዋኔ ሂደት የቀረቡ የመስክ "ገቢሮች" አንድምታ፣ ትዕምርት፣ ፍቺ እና ትንታኔ በቀጣዩ ይዘት (ንዑስ ክፍል 7.2፤ የባህል መድኃኒት "ገቢር" ማስተካከያ ዐውዳዊ ስልቶች) የቀረቡ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከመስክ ዕፀ መድኃኒት ሲቆርጡ፣ ሲለቅሙ፣ ሲቆፍሩ እና ሲሰበስቡ፤ ለሥርዓተ ገቢር መጀመሪያ "ዕፅ አንግስ" የሚባለውን ፀሎተ ድግምት "ከዕፀ ደብዳቤ እና ዐውደ ነገስት" ተምረውና ወስደው፤ መመሪያና ሥርዓቱን ጠብቀው እንደሚከውኑ ሊቀጠበብት አብርሃም እና መሪጌታ በረከት ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 12/03/2011 እብናት በተከታታይ)፡፡ በዕለቱ ለዕፅዋት ማንገሻ የሚቀርብ ሥርዓተ

ገቢርን ሊቀጠበብት አብርሃም እንደሚከተለው በግዕዝ ቋንቋ አቅርበዋል (ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡-

| <u>በግዕዝ</u> | <u>የአማርኛ ትርጉም</u> |
|---|---|
| አንቲ ውእቱ ዕፅ ብሩክ ዕፀ ሕይወት | የኮመል ዕፅ[83] የምትባይ፤ ዕፀ መድኃኒት የሆንሽ |
| ዕፀ መድኃኒት ከመ ዕፀ ኮሞል ይብሉኪ፤ | የሕይወት ዕፅ፤ አንቺ የተባረክሽ ነሽ |
| ሰንተው ቀንተው ቀርነው ቀርነለው ቀርነ | በተለያዩ መዓዛ ሽቱዎች የተሞላሽ |
| ሳሙኤል፣ ኡራኤል፣ ኢዩኤል፣ ጉሁኤል፣ | የሣሙኤል ዋንጫ፤ ኡራኤል፣ ኢዩኤል |
| አማኑኤል፣ በከመ አንገስኮ ለአዳም በውስተ | ጉሁኤል፣ አማኑኤል በሚባሉ ሕቡዕ ስሞች |
| ገነት ከማሁ አንግሣ ለዛቲ ዕፅ በእደ ገብርከ | አዳምን በገነት እንዳነገስኸው |
| እገሌ ተብሎ ፯ ጊዜ ይደገማል፡፡ | በእኔ በአገልጋይህ እጅ፤ ይህቺን ዕፀ አንግስልኝ |
| | (ፈዋሽ አድርግልኝ) በእገሌ ስም ብሎ |
| | ሰባት ጊዜ ደግሞ ይቆርጣል፡፡ |

በማለት በዕለቱ የሚከወነውን የዕፀ መድኃኒት ፀሎተ ድግምት አቅርበዋል፡፡ በሥርዓተ ገቢሩ ይዘት ምን ርዕሰ ጉዳዮች ተነሱ? ሲባል፤

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤ፤ "የኮመል ዕፅ" ወይም "የእሼ ዛፍ" በቆላ እና በወይና ደጋ አካባቢዎች እንደሚገኝ ይነገራል፡፡ ይህ ዛፍ ዓመቱን ሙሉ ለምለም የሆነ፣ በቁመቱ ረጅም፣ ቅርንጫፉ ሰፊ፣ እንደ ዋንዛ በርካታ ፍሬዎችን በመያዝ ለእንስሳት እና ለሰው ምግብ፣ ማረፊያ እና መጠለያ መሆኑን በማሰብ የዕፀ መድኃኒት ባለሙያዎች "የሕይወት ዕፅ" በማለት ይጠሩታል፡፡ ይህ ዕፅ፤ የበጋ ወቅት ሲመጣ በአካባቢው የሚገኙ ዕፅዋት ቅጠላቸውን አርግፈው፤ ፍሬያቸውን ጥለው፣ "እርቃናቸውን ቆመው" ሲታዩ የኮመል ዕፅ ለምለም ሆኖ ዓመቱን ሙሉ ይቆያል፡፡ የአካባቢው ሙቀት ሲጨምር እና ፀሐይ ሲበረታ (መጋቢት፣ ሚያዚያና ግንቦት) ቅጠሉና ግንዱ እንደጤዛ ዉኃ በማዝገት ነፍሳትን ያጠጣል፤ ይመግባል፤ ተብሎ ይታመናል

---

[83]በአካባቢው የሚገኙ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች "ዕፀ ኮሞል" በማለት በግዕዝ ይጠሩታል፡፡ በአማርኛ "የኮመል/የእሼ ዛፍ፤ ተክል፣ እንጨት" ይባላል፡፡ በግዕዝ "ዕፅ" የሚለው ቃል በአማርኛ "ተክል፣ እንጨት፣ ዛፍ" ለሚሉ ቃላት በአቻ ፍችነት ይውላል፡፡ ይህ ጥናት "ዕፅ" የሚለውን ቃል በቀጥታ የተጠቀመ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

(መሪጌታ ስዩም እና አቶ ደሴ፤ 04/02/2011 እብናት እና 23/04/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

በዚህ ባሕርይው ለሕይወት ምግብ፣ መጠለያ እና ማረፊያ በመሆን በፍሬው መመገቡን፣ በጥላው መከለሉን፣ ዓመቱን ሙሉ ለምለም ሆኖ መክረሙን ታሳቢ በማድረግ በሃይማኖት አባቶች የቅዱሳን እና የመላእክት ተምሳሌት ተደርጎ ይቆጠራል። ለቤተክርስቲያን በር፣ ግድግዳ፣ ጣራ እና ለንዋያተ ቅድሳት ቁሶች መስሪያ በመሆን ያገለግላል። ዕፁ የማይነቅዝ፣ ጠንካራ፣ ረጅም እድሜ የሚኖር፣ ቀጥ ብሎ የሚወጣ የአድባራት፣ የቤተክርስቲያን እና የገዳማት ሐብት፣ "ዉበት፣ ጥላና ሞገስ" ተደርጎ እንደሚታመን ቄስ አብርሃም ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 01/05/2011 እብናት)።

መሪጌታ አማረ ደግሞ፤ የኮመል ዕፅ ለሰው ልጅ የፈውስ ኃይል፣ ታዛዥ እና አገልጋይ መሆኑን በማሰብ፤ በማንኛውም የዕፅዋት ገቢር ውስጥ ስሙ እንደሚጠቀስ ገልፀዋል። በተወሰኑ የሃይማኖት አባቶች እና በአብነት ትምህርት ቤት የሚገኙ ሊቃውንት "የብርሃን ዕፅ" እያሉ እንደሚጠሩት ጠቁመዋል። በሃይማኖታዊ እና በዓለማይ ትምህርት ጎበዝ ሆኖ ለመገኘት፣ "ልበ ብርሃን" ለመሆን፣ የአስተሳሰብ ብስለት እና ፅናት ለማግኘት "የኮመል ዕፅ" ዋናው አካልና ገቢር እንደሆነ አስረድተው፤ ከኮመል ዕፅ የሚወጣው ዉኃ መሰል ፈሳሽ፤ የዕባጭ ቁስል፣ የሙሽሮ ነቀርሳ [ለካንሰር] እና የኪንታሮት ሕመምን፤ በመፈወስ ከፍተኛ አገልግሎት እንዳለው መክረዋል (ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም)። ከዚህ በታች የኮመል ዛፍና ፍሬ እንደሚከተለው በፍቶ ግራፍ ቀርበዋል።

ፎቶ ግራፍ 4፡- በእብናት ወረዳ በአቋሽሞች ቀበሌ የኮመል (እሼ) ዛፍና ፍሬን የሚያሳይ ፎቶ



የኮመል ዛፍ



የኮመል ዛፍ ፍሬ

ምንጭ፡- እብናት ወረዳ፤ በጥናቱ አቅራቢ በቀን 11/05/2011 ዓ.ም የተነሳ

በአጠቃላይ የዕፁን ባሕርይ፣ ታዛዥነት፣ እድሜ፣ ሙያና ገቢር በማሰብ የሕይወት ምግብ፣ መድኃኒት እና መጠለያ  ሲሆን ለሃይማኖታዊ እና ለንዋየ ቅዱሳን ቁሶች መስሪያና አገልግሎት በመዋል ተመራጭ እና "ቅዱስ ዕፅ ነው" ተብሎ በማኅበረሰቡ ይታመናል። በባህል ሕክምናም፤ የዕፁን ባሕርይ፣ እድሜ እና ከፈጣሪ የተሰጠውን ኃይል፣ ሙያና ተግባር በማጤን ለአካል ቁስል እና ለመንፈሳዊ ጭንቀት የፈውስ ምንጭና መድኃኒት እንደሆነ ይታሰባል። ይህን ቅድስና፣ ኃይል፣ ፈቃድ፣ ሙያና ተግባር አስተባብሮና አዋህዶ፤ ፈጣሪ ለባህል ሐኪሞች በማውረስ ለሚቆርጡት ቅጠል፣ ለሚለቅሙት ፍሬ እና ለሚቆፍሩት ሥር፤ ኃይልና ፀጋውን በመስጠት፤ አዘጋጅተው እና ቀምመው ለሚተገብሩት ሕክምና የሕይወት ዕፅ፣ የድኅነት መንገድ እና የፈውስ ኃይል አድርጎ እንዲባርክላቸው መለመኛና መማፀኛ እንደሆነ ይነገራል።

ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉ ዕፅዋት ከመስክ ሲሰበሰቡ፤ ለዕፅዋት ማንገሻ የሚካሄዱ ሥርዓተ ገቢሮች (ፀሎተ ድግምት) በይዘታቸው ተቀራራቢ እና ተመሳሳይ ግብ እንዳላቸው መሪጌታ ልሳነወርቅ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 27/04/2011 ሊቦ ከምከም)። ዕፅዋትን አክብሮ፣ ባሕርያቸውን አጥንቶ፣ ጊዜና ወቅታቸውን ለይቶ፣ ሥርዓተ ገቢራቸውን አሟልቶ፤ በፀሎትና በትዕግስት የዕፅዋትን ቅጠል ቆርጦ፣ ፍሬያቸውን ለቅሞ እና ሥራቸውን ምሶ ለመድኃኒት ግብዓት ማዋል፤ የዕፅዋትን የፈውስ "ኃይል እና ቅድስና" ይጨምራል ተብሎ ይታመናል። መሪጌታ ስንታየሁ፤ "እግዚአብሔር መርጦ የሾመና የሸለማቸውን ኃይሎች ስም ጠርቶ እና ገቢራቸውን ለይቶ" ዕፅዋትን ማንገስ፣ ክብርና ሞገሳቸውን መጠበቅ፣ ገቢራቸውን መፈፀም፣ ፀሎተ ድግምት ማቅረብ እና በንፅሕና መቅረብ አስፈላጊ እና መደበኛ ተግባር እንደሆነ መክረዋል (ቃ.መ፤ 14/03/2011 እብናት)።

በዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሂደት ለሥርዓተ ገቢር የሚቀርብ ፀሎተ ድግምት በግዕዝ እና በአማርኛ ቋንቋ እንደሚከወን መሪጌታ ባሕረጥበብ ገልፀዋል (ቃ.መ፤22/01/2011 ፋርጣ)። ይህን ታሳቢ በማድረግ፤ በአማርኛ ቋንቋ "ዕፅዋትን ለማገስ"[84]፣ ክብራቸውን ለመጠበቅ፣ ቅድስናቸውን ለማብሰር ሲባል የዕፀ መድኃኒት አቆራረጥ ሥርዓተ ገቢርን እንደሚከተለው አቅርበዋል፡-

[84]በዚህ ጥናት የቀረቡ የዕፅዋት ማንገሻ ፀሎተ ድግምት ይዘቶች፤ አካላዊ ሕመም እና መንፈሳዊ ጭንቀትን ለመፈወስ የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ከመስክ ለመሰብሰብ በተደጋጋሚ የሚከወኑ የዕፅ አንግስ ሥርዓተ ገቢሮች መሆናቸውን፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል (መሪጌታ አማረ፣ ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም)። ለሐብት፣ ለፍቅር፣ "ለበረድ" እና መሰል ተግባራትን ለመፈፀም የተለየ ሥርዓተ ገቢር እንዳለ ደብተራ መልኩ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ)።

አንቺ የሕይወት ዕፅ (ፍሬ)

እንደ ጳጳስ ጳጽሺ፤ እንደ ንጉስ ንገሺ

እንደ ታቦት ተቀደሺ፤ እንደ ጠቢብ ተጠበቢ

ክፉና መሰሪዎችን ደምስሺ፤ ሕሙማንን ፈውሺ፤...

የዛር ጳጳሱን፤ የጅን ንጉሱን

የአጋንንት እራሱን፤ የዛር ሰራዊቱን

የጅን መኳንንቱን፤ የቡዳ ማኅበራቱን

ለእኔ ለእገሌ (ለመሪጌታ ባሕረጥበብ)

ለእጄም ጭብጥ፤ ለእግሬም እርግጥ

አድርገሽ አሰግጅልኝ፤ ግብርሽን ይገፔ መጥቻለሁ።

በማለት ዕፅዋትን አንግሰው እና አክብረው ከመስክ እንደሚቆርጡ አስረድተዋል። ከዚህ በላይ የቀረበው ሥርዓተ ገቢር ሁለት መሰረታዊ ርዕሰ ጉዳዮችን ይጠቁማል። አንደኛ ሃይማኖታዊ አስተምህሮን፣ ቅድስና፣ ሥርዓትና ተግባርን ይመለከታል። ሁለተኛ የአጋንንትን ምድራዊ ሕይወት፣ ተግባር፣ ኃይልና ሥልጣንን ይገልፃል። በሥርዓተ ገቢር ፀሎተ ድግምት መስመር አንድ "አንቺ የሕይወት ዕፅ (ፍሬ)" የሚል ይዘት (ስንኝ)[85] ይገኛል። የሕይወት ዕፅ (ፍሬ) ማለት ምን ማለት ነው?

ደብተራ መልኩ አዳም በገነት፤ የፈጣሪውን ቃል፣ ትዕዛዝና መመሪያ አክብሮ ሲኖር "ዕፀ ሕይወትን እንዲበላ፤ ዕፀ በለስን እንዳይበላ" ክልከላና ገደብ እንደነበረበት ገልፀዋል። "ዕፀ ሕይወት" ለአዳም የሕይወት ምግብ፣ የገነት ኑሮ እና ድኅነት መንገድ እንደሆነች ይታሰባል። በአንጻሩ፤ አዳም የፈጣሪውን ትዕዛዝ ዘንግቶ፣ መመሪያና ገደቡን ረስቶ "ዕፀ በለስን በልቶ ከገነት ተባረረ፤ ... በምድር መኖር ጀመረ፣ እርቃኑን እንደቆመ አወቀ፤ በጉልበቱ ጥሮ በወዙ ማደርን ተማረ፣ በአፀደ ሥጋ ሞትን ተቀበለ" በማለት ሃይማኖታዊ ትረካውን አስረድተዋል። "ዕፅ ሕይወት"፤ የቅድስና፣ የፈውስ፣ የሕይወት ምግብ፣ የድኅነት ምሳሌ እና ትዕምርት እንደሆነች ይታመናል

[85] በሥርዓተ ገቢር ላይ የሚከወኑ ሥርዓቶች እና የሚቀርቡ ይዘቶች፤ "ቅዱስ፣ ስውር እና ክቡር ናቸው" ተብሎ ስለሚታመን በማንኛውም ዐውድና አጋጣሚ አይነገሩም፤ አይከወኑም። ከዚህ በላይ የቀረቡ ይዘቶችን እንደ ሕዝባዊ ዕውቀት (ሥነ ቃል እና ቃል ግጥም ይዘት) ማሰብና ማየት ክብርና ቅድስናቸውን ይቀንሳል፤ ተብሎ ይታሰባል።

(ቃ.መ፤ 23/01/2011 ፋርጣ)፡፡ መሪጌታ መንግስቱ ደግሞ ዕፅዋት የድኅነት እና የጥፋት ምግባር እንዳላቸው ሲያስረዱ፡-

"ዕፅ የሐዩ፤ ዕፅ ይቀትል"

ዕፅ ያድናል፤ ዕፅ ይገላል፤

ይላሉ፤ ዕፅዋትን በአግባቡ ስንጠቀም የሕይወት ፍሬ፤ በተቃራኒው ሲሆን ደግሞ የሞት ምክንያት እንደሆኑ ገልፀዋል (ቃ.መ፤11/04/2011 እብናት)፡፡ ቃልን ጠብቆ፣ መመሪያን አክብሮ፣ ሕግ እና ገደብን ለይቶ መኖር፤ የድኅነትና የቅድስና፣ የመልካም ሥራ፣ የሕይወት ፍሬና ተግባር ተደርጎ ይነገራል፡፡ በአንጻሩ፤ ቃልን ዘንግቶ ትእዛዝን መተላለፍ፣ ሕግን መጣስ፣ ገደብን ማለፍ፤ ከቅድስና ያስወጣል፣ ከሰውነት ደረጃ ያወርዳል፣ አለፍ ሲል በሞት ያስቀጣል፤ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ዕፅዋትን አክብሮ፣ ዓይነታቸውን ለይቶ፣ ገቢራቸውን አድርሶ መቁረጥ እና በአግባቡ መጠቀም፤ የድኅነት፣ የምህረት፣ የሕይወት ፍሬ እና ተምሳሌት ሲሆን፤ ከዚህ ሥርዓት፣ መመሪያና ትዕዛዝ ማለፍና መውጣት፤ "ሰይጣናዊ" ሥራ፣ ዕኩይ ተግባር እና የሞት መልዕክተኛ ተደርጎ ይታመናል (መሪጌታ መንግስቴ፣ ቃ.መ፤10/03/2011 እብናት)፡፡ ለዕፅዋት ማንገሻ የተመረጡ ስሞች ምን ኃይልና ፀጋ አላቸው ተብሎ ይታሰባል?

በሥርዓተ ገቢሩ ይዘት (ፀሎተ ድግምት)፤ "የሕይወት ዕፅ፣ ጳጳስ፣ ንጉስ፣ ጠቢብ፣ ታቦት፣ አጋንንት፣ ዛር፣ ቡዳ እና ጅን" የሚሉ ስሞች ተጠቅሰዋል፡፡ እነዚህ ስሞች ለሥርዓተ ገቢር ማስፈፀሚያነት ለምን ተመረጡ? ሲባል ደብተራ መኅሪ፤ "ከሰው መርጦ ለሹመት፤ ከእንጨት መርጦ ለታቦት" እንደሚባለው ፈጣሪ በጥበቡ አንግሶ፣ በመንበሩ አስቦ፣ ዓለምን ለማስተዳደር ኃይል፣ ጥንካሬና ቅድስናን ሰጥቶ እንደሾማቸው ይታሰባል፡፡ ስለዚህ የፈጣሪ ቃል፣ መንፈስ፣ ኃይል እና በረከት አድሮባቸዋል፤ የሚባሉ ዕፅዋት፣ መላእክት፣ ቅዱሳን የሃይማኖት አባቶች፣ የአገሪ ስብከት አስተዳዳሪ ጳጳሳት፣ የአገር መሪ መንግስት፤ "ምድራዊ ሥልጣን፣ ኃይልና ፈቃድ አላቸው" በሚባሉ አጋንንት (መናፍስት) ስም እና ተግባርን ጠርቶ ዕፅዋትን ማንገስና መቁረጥ፤ ለዕፀ መድኃኒት ግብዓቶች የኃይል፣ የብርታት፣ የቅድስና፣ "የምህረትና የፈውስ ፀጋን ያወርሳል"፤ ተብሎ በባህል ሕክምና ባለሙያዎች ይታመናል (ቃ.መ፤ 13/03/2011 እብናት)፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ከመስመር አምስት እስከ ሰባት በሥርዓተ ገቢሩ የተጠቀሱ ስሞች፤ የአጋንንት ዓይነቶችን፣ ተግባር፣ ምድራዊ ሥልጣን፣ ኃይልና ጉልበትን አመላክተዋል፡፡ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ አጋንንት (ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ የዐየር እና የምድር ጋኔል) ዓለምን ለመግዛትና

ለማስተዳደር ምድራዊ ሥልጣን እና ፈቃድ ከፈጣሪ እንደተሰጣቸው መሪጌታ መኀሪ እና ደብተራ ጥላሁን ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 27/01/2011 እና 03/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)፡፡ አጋንንት ከእይታ ተሰውረው በሰው ልጆች አኗኗር አምሳል ልክና ደረጃ አለቃና ምንዝር፤ ንጉስና አሽከር፣ የበላይና የበታች መሪና አስተዳዳሪ ሆነው ምድራዊ ሕይወት እንዳላቸው መሪጌታ መኀሪ ጠቁመው፤ "ጅኒዎች፤ ልቡሳነ ሥጋ ሆነው" ከሰው ልጆች ጋር ተጋብተውና ተዋልደው እንደሚኖሩ/ ይኖሩ እንደነበር፤ የቅርብ ጊዜ ገጠመኛቸውን በማስታወስ እንደሚከተለው ተርከዋል (ቃ.መ፤ 27/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡-

> እዚህ ማዶም አንድ ሰው አለ፤ ሴት ጂኒ 'ልቡሳነ ሥጋ ለብሳ መንገድ ላይ አግኝታው ነው' ይባላል፤ ጥሩ [ቆንጆ ማለት ነው በዚህ ዐውድ] ሚሽት አግብቶ ሲኖር ሁለት ልጆች ወለደችለት፤… 'ሌሊት ተነስታ ትሄዳለች፤ ጅብ ጋላቢ ናት' ይባላል፡፡ … አንድ ቀን ምን እንደሆነች ሳይታወቅ ተመገድ ወድቃ ደሟ ፈሶ፤… ጣረሞት ይዟት፤ ተቦታዉ የደረሱ ሰዎች አፋፍሰው ተቤቷ አስገቧት፡፡ …በማግስቱ ሊጠይቋት ሲሄዱ፤ ተቤት የለችም፤ የት ትግባ የት ትውጣ፤ ሳይታወቅ ሳይሰማ፤ ይኸው ጥላትህ ጥፍት ይበል፤ እልም ብላ ቀረች፡፡ …'ባልና ሁለት ልጆቿን ሜዳ ላይ በትና ጠፋች'፤ ተብሎ ይኸው ለታሪክ ይነገራል፡፡ …ልጆቿ ብዙም ሳይቆዩ ሞቱ፤ ባሏ አሁንም አለ፡፡ … አባቴ ጂኒ ይስባል፤ ያናግራል፤ ባገሩ የታወቀ ነው፤ በጭስ ተሰውሮ… ዳመና ጋልቦ ላሊበላ አስቀድሶ፣… ማዕድ ቀርቦ፤ ተቋድሶ ይመጣ ነበር፡፡ ይሄ ነው፤ የጂን መልክ፤ አባቴ ነው የሳለው፡፡ …ጅኒዎች ጥበበኞች ናቸው፤ የዓለም ዕውቀት በጃቸው አለ፡፡ ከነሱ የተሰወረ ምስጢር የለም፤ ለወዳጃቸው ታዛዥና አገልጋይ ናቸው፡፡

በማለት በጅን እና በሰዎች መካከል ያለውን መስተጋብርና ግንኙነት ገልፀዋል፡፡ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤ፤ "አጋንንት እንደምድር አሸዋ በዝተው፤ እንደሰማይ ከዋክብት ተበትነው" በምድር እንደሚኖሩ ይታመናል (ምዕራፍ አምስት የሕመም መንስኤ እሳቤን ልብ ይሏል)፡፡ የባህል ሕክምና ባለሙያዎችም የአጋንንትን ሥልጣን፣ ኃይልና ምድራዊ ተግባር በማሰብ፤ ፈጣሪ ለአጋንንቱ የሰጠውን ሥልጣን፣ ኃይል፣ ጉልበትና ዕውቀት "ነስቶ" (ወስዶ)፤ ለባህል ሐኪሙ አስገዝቶ ለሚቆርጡት ዕፀ በማውረስ፤ የፈውስ ዕፀ እና የሕይወት ፍሬ አድርጎ እንዲባርክላቸው፤ ፈጣሪን ለምነው፣ ፀሎተ ድግምት አድርሰው፣ ሥርዓተ ገቢሩን አሟልተው፣ ዕፅዋትን አንግሰው እንደሚቆርጡ፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በቅድመ ክዋኔ ይዘት፤ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሥርዓት፤ በፀሎት፣ በቀን፣ በሠዓት፣ በጊዜ፣ በቦታ እና በድርጊት የታጀበ እና የተገደበ፤ በሥርዓት ገቢር የሚመራ፤ አድርግ እና አታድርግ ትዕዛዝና ገደቦችን በመከተል የሚፈፀም እንደሆነ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ ሥርዓትና መመሪያውን ጠብቆ፣ ትዕዛዝ እና ገቢሩን አሟልቶ መጠቀም የፈውስ ኃይል እና

የድኅነት መንገድ ተደርጎ ይታመናል። ከዚህ በተቃራኒ መተግበር የሕመም መንስኤ፣ የመቅሰፍት አካል፣ "ሰይጣናዊ" ድርጊት እና የሞት መንገድ ተደርጎ እንደሚታሰብ፤ የመስክ መረጃዎች አስረድተዋል።

## 7.2 የባህል መድኃኒት "ገቢር" ማስተካከያ ዐውዳዊ ስልቶች

የባህል መድኃኒት አሰባሰብ ሥርዓተ ገቢር እንዲከወን አስገዳጅ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የሥርዓት መጠበቂያና ማስተካከያ ዐውዳዊ ስልቶች ምን ምን ናቸው? እንዴት ይተገበራሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች፤ ከመስክ መረጃዎች ተሰብስበው ምላሽ ተሰጥቷል። የመስክ መረጃዎች መከፋፈያ መሰረታቸው ምንድን ነው? ሲባል የክዋኔ ሥርዓተ-ገቢር ሂደትን (መመሪያና ገደብን፤ ማስተካከያና መመጠኛ ስልትን) ይመለከታል። በዚህ ንዑስ ይዘት የንጽሕና፤ የዕለት፣ የቀናትና የወቅቶች፤ የቁጥርና የአቅጣጫ እሳቤዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### ሀ) የንፅሕና እሳቤ

በባህል ሕክምና ዕውቀት የንፅሕና እሳቤ አካላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ቁሳዊና አካባቢያዊ እሴቶችን መሰረት ያደረገ ፈርጀ ብዙ መልክና ይዘት እንዳለው ከመስክ መረጃዎች፤ መገንዘብ ተችሏል። መሪጌታ ፍሬስብሃት፤ በዕፀ መድኃኒት አዘገጃጀት፣ ቅመማና አሰጣጥ ሂደት አካላዊ፣ መንፈሳዊ (ሕሊናዊ) እና ቁሳዊ ንፅሕና የሥርዓተ ገቢሩ አካል ናቸው፤ ይላሉ። ዕፅዋትን በማንኛውም ጊዜ፣ ቦታና ወቅት ቆርጦ ለመድኃኒት መጠቀም፤ "ለከፋ ጉዳት እና ለሞት ይዳርጋሉ" ተብለው ይታሰባሉ። ይህን ታሳቢ በማድረግ፤ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሂደት በከፍተኛ ጥንቃቄ፣ ትዕግስት፣ ፀሎትና ምስጋና የሚከወን፤ በሥርዓተ ገቢር የሚመራ፤ አድርግ እና አታድርግ ገደቦችን በመከተል እንደሚፈፀም፤ ይጠቁማሉ (ቃ.መ፤ 29/01/2011 ሊቦ ከምከም)። የዕፅዋቱን ባሕርይ ለይቶ፣ መገኛ ቦታቸውን አጥንቶ፣ ሥርዓተ ፀሎታቸውን አሟልቶ፣ ለፈውስ የሚበቁበትን ወቅትና ጊዜ መርጦ ቅጠላቸውን ለመቁረጥ፣ አበባና ፍሬያቸውን ለመልቀም፣ ሥራቸውን ቆፍሮ ለማውጣት "ብልሃት" እንዳለው ደብተራ መጎሪ ይመክራሉ (ቃ.መ፤ 13/03/2011 እብናት)። በምን ዓይነት ቦታ የሚገኙ ዕፅዋት ለመድኃኒት ግብዓት ይመረጣሉ? ለምን? ሲባል፤

ይህ ጥናት በሚካሄድበት አካባቢ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት ግብዓት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን በዋናነት ከገዳማት፣ ከወንዝ፣ ከተራራ፣ ከጥብቅ ደኖች፣ ከአድባራት፣ ከእዳሪ መሬት

እና ከእርሻ ማሣ ቦታዎች ሰብስበው፤ ጥቂቱን ደግሞ በግቢያቸው አልምተው እንደሚጠቀሙ፤ ገልፀዋል (ሊቀጠበብት አብርሃም እና ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደርሶ፤ ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 23/06/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። ከዚህ አንጻር፤ በማንኛውም ቦታ፣ ጊዜና ወቅት በቅለው፣ አብበውና አፍርተው የሚገኙ ዕፅዋት ለመድኃኒት አገልግሎት እንደማይውሉ፤ መሪጌታ ዘላለም ጠቁመዋል። ለምን? ሲባል፤ መገኛ ቦታቸውን፣ ጊዜና ወቅታቸውን "ስተው" ለምልመው፣ አብበውና አፍርተው የሚገኙ ዕፅዋት ተፈጥሯቸውን ዘንግተው፣ ግብራቸውን ረስተው ስለሚገኙ "የመቅሰፍት" እና የአጋንንት ማደሪያ ናቸው፤ ተብለው ይታሰባሉ (ቃ.መ፤ 20/04/2011 ፋርጣ)።

በተመሳሳይ መልኩ፤ በከተማ፣ በመኖሪያ ቤት፣ በቆሻሻ መጣያ አካባቢ፣ ፋብሪካ እና የመኪና መንገድ በሚያልፍባቸው ቦታዎች የሚገኙ ዕፅዋት፤ "አጋንንት የሰፈሩባቸው፤ የሰይጣን ፈረስ የአረፉባቸው ናቸው፤ ቢነኳቸው፣ ቢቀምሷቸው፣ ቢጠጓቸው" ለሕመም አጋልጠው፤ ለሞት እንደሚዳርጉ ደብተራ መልኩ ያስረዳሉ። ከነዚህ ቦታዎች የሚሰበሰቡ ዕፅዋት፤ በቁማቸው "እረክሰው"፣ ኃይልና ጉልበታቸውን አጥተው፣ መልክና ገቢራቸውን ስተው ስለሚገኙ "የአጋንንት መዋያ፣ ማደሪያና መስፈሪያ ናቸው" ይላሉ (ቃ.መ፤ 23/01/2011 ፋርጣ)። እነዚህን ዕፅዋትን ቆርጦ እና ቀምሞ ለሕሙማን መስጠት "ለሞት ይዳርጋል፤ በፈጣሪ ያስረግማል፤ በሕሊና ያሶቅሳል" በማለት አቶ ሞላ ይገልፃሉ (ቃ.መ፤ 22/06/2011 ፋርጣ)። በአጠቃላይ ለመድኃኒት የሚፈለጉ ዕፅዋት ከመኪና መንገድ፣ ከመኖሪያ ቤት፣ ከቆሻሻ መጣያ፣ ከፋብሪካ ቦታዎች የራቁ እና ከሰው ልጆች ንክኪ "የተገለሉ"፤ መደበኛ ሥነ ምህዳራቸውን ይዘው፣ ወቅትና ጊዜያቸውን አክብረው፣ ተፈጥሯዊ ኃይላቸውን አሟልተው፣ ንፅሕናቸውን ጠብቀው ሲገኙ በሥርዓት እና በጥንቃቄ ሰብስቦ መጠቀም የፈውስ አካልና ተግባር እንደሆኑ ይታመናል። እነዚህ ዕፅዋት በምን ዓይነት ሥርዓትና ዐውድ ይሰበሰባሉ?

መሪጌታ ሠረቀብርሃን፤ ለመድኃኒት ግብዓት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ለመሰብሰብ ሲዘጋጁ፤ ሥርዓተ ገቢር እና ዐውዳቸውን ለይተው፣ መገኛ አካባቢያቸውን፣ ባሕርይ እና የቆይታ ዘመናቸውን አጥንተው እና አሟልተው እንደሚሰበሰቡ፤ ይገልጻሉ። ዕፅዋትን ለማንገስ እና ፀሎተ ድግምት ለማቅረብ "አካላዊ እና መንፈሳዊ ንፅሕና፣ ፆም፣ ፀሎት እና ምስጋና መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው"፤ ይላሉ (ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት)። መሪጌታ ፋንታሁን ደግሞ፤ "ሆድ እንደጠገበ፣ ሕሊና እንደፈቀደ፣ እግር እንደቻለ አይኬድም፤ ለሁሉም ነገር ገደብ አለው" ይላሉ፤ "የሞት

ታናሽ ወንድም በሆነው እንቅልፍ ወድቀን ስንነሳ"፤ በነፋስ ባሕርያችን[86]፤ ሰውነት ሲታደስ፣ ሕሊና ሲረጋጋ፣ የዕለት ፀሎት አድርሶ፤ እህል ሳይበላ፣ ዓይነ ምድር ሣይወጣ፣ ሳይሸና፣ ዉኃ ሳይነካ፤ ከሰው ሳይገናኙና ሳይነጋገሩ፣ ከእይታ ተሰውሮ፣ ከጾታዊ ግንኙነት ተቆጥቦ፣ "ከሚያረክሱ" ተግባራት እራስን አርቆ፤ ወቅት፣ ዕለትና ሠዓትን ጠብቆ፤ ለፈውስ የሚያገለግሉ ዕፅዋት መሰብሰብ እንዳለባቸው፤ አፅንኦት ሰጥተው መክረዋል (ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ)። እነዚህ ዕፅዋት በምን ዓይነት መሳሪያና ግብዓት ይሰበሰባሉ? ንፅሕናን እንዴት ይጠብቃሉ? ሲባል፤

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለዕፀ መድኃኒት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ከመስክ ለመሰብሰብ የኮመል ዕፅ እጀታ ያለው ማጪድ፣ የጌሾ አንካሴ፤ የወይራ ዛቢያ እና የቀንድ ካራን አዘውትረው ይጠቀማሉ። እነዚህ ዕፅዋት (ከቀንድ ካራ በስተቀር) በባህል ሕክምና ልማድ ለምን ተመረጡ? ምን ዓይነት ተግባርና ባሕርያት አላቸው? ሲባል፤

የኮመል ዕፅ የረጅም እድሜ ባለቤት፣ ዓመቱን ሙሉ ለምለም የሆነ፣ ጠንካራ፣ የማይበሰብስና የማይነቅዝ፣ ሃይማኖታዊ ቅድስናም እንዳለው ይታሰባል። የዕፁን ታዛዥነት፣ አገልግሎትና ገቢር በማሰብ ከግብዓት ባለፈ ለሕክምና አገልግሎት እንደሚውል ከዚህ በፊት በቀረበ ይዘት፤ ተጠቁሟል። በተመሳሳይ መልኩ፤ የጌሾ ዕፅ መራራ፣ ጠንካራ እና የማይነቅዝ ዕፅ ሲሆን ፍሬው፣ ቅጠሉ፣ ቅርፊትና ሥሩ ለባህል ሕክምና እንደሚውል፤ አቶ ታከለ እና ቄስ አብረሃም ገልፀዋል። በተለይ ቅጠሉ፣ ፍሬውና ሥሩ ተጨቅጭቆና ደርቆ ዱቄቱ፤ ከተለያዩ ዕፅዋት ጋር ተቀላቅሎ ለእንጥል፣ ለሆድ ቁርጠት፣ ለቋቁቻ፣ ለፎረፍር፣ ለሆድ ትላትልና ቁስል ነክ በሽታዎች፤ ተመራጭ ዕፅ እና መድኃኒት እንደሆነ፤ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 04/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 01/05/2011 ዓ.ም እብናት በቅደም ተከተል)።

---

[86]የሰው ልጅ በሃያ አራት ሠዓት ሂደት ውስጥ፤ አራቱ ባሕርያት ሠዓትና ጊዜያቸውን ጠብቀው፤ ልክና ገደባቸውን ለይተው፤ "ይፈራረቁበታል"፤ ይባላል። ሰው፤ ከመኝታው ሲነሳ የነፋስ ባሕርይን ያስተናግዳል። "ተኝቶ መነሳት"፤ የትንሳኤ ምልክትና ተምሳሌት ተደርጎ ይታሰባል። ምግብ በልተን፣ አካባቢው ሲሞቅ፣ መንቀሳቀስ እና በየቦታው ተሰማርተን የዕለት ስራችንን ስንፈጽም፤ የአሰብነውን ስንሰራ በእሳት ባሕርያችን እንደሆነ ይታመናል። አካልና መንፈስ እየቀዘቀዘ ሲሄድና ሲደክም፣ ሲበርድ፣ ጉልበት ሲዝል የዉኃ ባሕርይ ይወከላል። የጉልበት መዛል እና መድከም ለእንቅልፍ ሠዓት አሳልፎ ይሰጣል፤ ይዳርጋል፤። በዚህ ሠዓት የመሬት ባሕርይ ይተካል። አካልና መንፈስ ይተኛል፤ ድካም በእንቅልፍ ይወጣል። ሰው በእንቅልፍ ይታከማል፤ ይታደሳል፤ የዛለውን አካሉን ያበረታል፤ በመንፈሱ ይጠነክራል፣ በየቀኑ ይታደሳል፣ "ውጣ ውረዱን ይረሳል"፤ ይላሉ መሪጌታ ባሕረጥበብ (ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)። ሰውና እንስሳት ሲደክማቸውና ሲታመሙ ለምን ይተኛሉ? ሲባል፤ የሰው ልጅ ድካም፣ ጭንቀት፣ ቁስለት፣ ሕመም እና ስቃይ "በእንቅልፍ ያልፋል"፣ ይፈወሳል፤ ተብሎ ይታመናል። "የፈጣሪ ድንቅ ሥራና መድኃኒት እንቅልፍ ነው" ይባላል (መሪጌታ ስዩም፣ ቃ.መ፤ 04/02/2011 እብናት)።

የጌሾ ዕፅ፤ መራራ ጣዕም እና የማስከር ባሕርይ ቢኖረውም፤ ጠንካራና ቀጥ ብሎ የሚወጣ፤ የማይነቅዝ፣ የማይበሰብስ፣ "አጋንንት የማይቀርቡት" እና ለረጅም ዓመት የሚቆይ ዕፅ እንደሆነ ይታመናል። ይህን እምኔታ መነሻ በማድረግ፤ "የጌሾ አንካሴን" ለዕፅዋት መቁረጫና መቆፈሪያ እንደሚጠቀሙ፤ መሪጌታ ስንታየሁ ገልፀዋል። የጌሾ ዕፅ የመምረር፣ የማስከር፣ የማዞር እና "የማስለፍለፍ ጠባይ አለው"፤ ተብሎ ቢታመንም፤ አጋንንትን ለማስወጣት፣ ለመፈወስ፣ ለማራቅና ለመከላከል ተመራጭ ዕፅ እንደሆነ፤ ይታሰባል (ቃ.መ፤14/03/2011 እብናት)።

የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያ የሆኑት ዶ/ር አስናቀ ደግሞ፤ የጌሾ ዕፅ ንጥረ ነገር የባክቴሪያና የፈንገስ ተሕዋሲያንን የማፅዳትና የመግደል ኃይል እንዳለው ጠቁመው፤ በዉኃና በጠላ ውስጥ የሚከሰቱ "ተሕዋሲያንን" እንደሚያጠፋ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 23/04/2011 ደብረ ታቦር)። ከዚህ አንጻር በባህል ሕክምና ልማድ የጌሾ ዕፅ አጋንንት የማይሰፍሩበት እና የማይኖሩበት፤ በሣይንሱም ቢሆን በባክቴሪያ፣ በፈንገስ እና መሰል ተሕዋሲያን በቀላሉ የማይጠቃ ዕፅ እንደሆነ፤ ይነገራል። በዚህ ባሕርይው፤ በሙቀትና ቅዝቃዜ፣ በአካባቢ ብክለት፣ በንፅሕና ጉድለት የሚከሰቱ ተሕዋሲያንን በማጥፋት፣ እንዳይዛመቱ እና እንዳይራቡ በማድረግ፤ የመከላከልና የማፅዳት ኃይል እንዳለው፤ ይገመታል።

በተመሳሳይ መልኩ የወይራ ዕፅ፤ በደጋና በወይና ደጋ የሚበቅል፤ ጠንካራ እና ረጅም እድሜ ከሚኖሩ ዕፅዋት መካከል እንደሚመደብ የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ መልካሙ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 17/04/2011 ፋርጣ)። ይህ ዕፅ ዓመቱን ሙሉ ለምለም፣ ጣዕሙ መራራ፣ ጠንካራ፣ የማይነቅዝና የማይበሰብስ፣ ለማጠንትና ለባህል መድኃኒት (የወይራ ሥር-ለሪህ፤ ቅጠሉ- ለቆረቆር) አገልግሎት እንዳለው ጠቁመው፤ ለቤተክርስቲያን ንዋየ ቅዱሳን መስሪያና ሥርዓት ማስፈፀሚያ እንደሚውል፤ መሪጌታ መልኩ ገልፀዋል። ከዚህ ዕፅ "የወይራ ዛቢያ" አዘጋጅቶ፤ ለዕፀ መድኃኒት መቆፈሪያ መጠቀምና ማዋል፤ የገቢር አንድ አካል ሲሆን፤ የቀንድ ካራ [ከቀንድና ከብረት የሚሰራ ቢላዋ] ደግሞ፤ ዕፅዋትን ለመቁረጥ፣ ለመከትከት፣ አጋንንትን ለማባረርና ለማራቅ፤ የፈጣሪ "ኃይል እና ቅድስና አለበት" ተብሎ እንደሚታሰብ፤ መክረዋል (ቃ.መ፤ 23/01/2011 ፋርጣ)።

በአጠቃላይ ከዕፅዋት የሚሰሩ፤ የዕፀ መድኃኒት መሰብሰቢያ ቁሶች በጣዕማቸው መራራና ጎምዛዛ፣ በቀላሉ የማይነቅዙና የማይበሰብሱ፣ ቀጥ ብለው የሚያድጉ፣ አጋንንት

የማይቀርቧቸውና የማይሰፍሩባቸው ዕፅዋት እና ቁሶች እንደሆኑ፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል። እነዚህ ቁሶች፤ በሰውና በእንስሳት ንክኪ "እንዳይረክሱ" እና ንፅሕናቸውን እንዳያጡ ሲባል ከመኖሪያ ቤት ውጪ፣ "በተገለለ እና በተሰወረ ቦታ" እንደሚቀመጡ አቶ ደርሶ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 03/02/2011 እብናት)።

"ንፅሕና" ሲባል ከሚያረክሱ፣ ከሚያጉድፉ፣ ቅድስናን ከሚያሳጡ፣ ኃይልና ጉልበትን ከሚነሱ፣ ተፈጥሯዊ ባሕርይን ከሚበርዙ፣ ጣዕምና ለዛን ከሚቀይሩ፤ ተግባራት እራስን መግታት፤ ቀልብና ሥጋን አስታርቆ በሰከነ እንደበት፣ በተረጋጋ ሕሊና ማደር እና መዳኘት፤ የንፅሕና አካልና ምግባር ተደርጎ ይታመናል (ሊቀጠበብት አብርሃም እና መሪጌታ መንግስቱ፣ ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 11/04/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። አንድ ነገር ወይም ፍጥረት ከመነሻ ባሕርይው ሲርቅ፣ አዲስ ነገር ሲለምድ፣ ከሌላ ነገር ጋር ሲቀላቀል፣ ሲዋሃድ፣ ሲዛመድና ሲገናኝ ቅድስናውን "አጣ፣ ረከሰ፣ ኃይልና ጉልበቱን ቀነሰ፣ ሌላ ጠባይ አወጣ፤ አመጣ" ተብሎ ይታሰባል። በዚህ ባሕርይው ገቢሩን ይረሳል፣ ቅድስናውን ይስታል፤ የሕመም መንስኤ ይሆናል ተብሎ ይፈራል። ስለዚህ ቅድስናን ከሚያሳጣ እና ፈውስን ከሚነሳ ተግባር፤ በመታቀብና በመለየት የዕፀ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት እንደሚተገበር መሪጌታ አዲሱ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 19/01/2011 ፋርጣ)። ለዕፀ መድኃኒት መቀመሚያ ምን ዓይነት ዉኃ ይመረጣል? ሲባል እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል።

ለዕፀ መድኃኒት መቀመሚያ የሚውል ዉኃ፤ "ወፍ ያልቀመሰው ዉኃ፣ ቤት ያልገባ፣ ሴት ያልነካው፣ የምንጭ ዉኃ" መሆን እንዳለበት ይመክራል። የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ከመስክ የሰበሰቧቸውን የመድኃኒት ግብዓቶች "ወፍ በአልቀመሰው ዉኃ" አጥበው እና ቀምመው፤ ለሕሙማን አዘጋጅተው እንደሚሰጡ ገልጸዋል (መሪጌታ ልሳነወርቅ፣ ቃ.መ፤ 27/04/2011 ሊቦ ከምከም)።

"ወፍ የአልቀመሰው ዉኃ" ሲባል፤ የአዕዋፍ ባሕርይ እና የዉኃ ብክለትን ይመለከታል። አዕዋፍ ከማደሪያ እና ከመስፈሪያ ቦታቸው እንደወረዱ መጀመሪያ ዉኃ ጠጥተው፣ ኩሳቸውን ጥለው፣ "ላባና ቅንቅናቸውን" አራግፈው፣ ሰውነታቸውን ታጥበው ሲነሱ ዉኃ "ይረክሳል" (ይበከላል) ተብሎ እንደሚታመን መሪጌታ ሠረቀብርሃን ገልፀዋል። ይህን ታሳቢ በማድረግ፤ ለመድኃኒት ቅመማ የሚውል ዉኃ አዕዋፍ ከመስፈሪያ ቦታቸው ወርደው

ሳይቀምሱ እና ሳይታጠቡበት፤ እንስሳት ሳይረግጡ እና ሳይጠጡት፤ ከምንጭ ንጹሕ ዉኃ መቀዳት እንዳለበት መክረዋል (ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ "ሴት ያልነካው እና ቤት ያልገባ የምንጭ ዉኃ" ለመድኃኒት መቀመሚያ ይመረጣል፡፡

ለምን “ሴት ያልነካው ዉኃ” ተፈለገ? ሲባል፤ ሴት የወር አበባ አይታ፣ ድንግልናዋን "አጥታ" እና ጾታዊ ግንኙነት ፈፅማ የምንጭ ዉኃ ስትቀርብና ስትቀዳ “ዉኃን/ጠበል ታረክሳለች፣ ታጎድፋለች፣ ቅድስናውን ታሳጣለች” ተብሎ ይታመናል (ከተቡው አባላት መካከል መሪጌታ መንግስቴ፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)፡፡ በዚህ ዉኃ፤ ዕፀ መድኃኒት ቢቀመም "ይረክሳል፣ ፈውስና ኃይሉን ያጣል" ይባላል፡፡ ስለዚህ ሴቶች ማልደው ሳይቀዱት እና ሳይነኩት፤ አዕዋፍ እና እንስሳት ሳይቀርቡትና ሳይቀምሱት ለመድኃኒት ግብዓት ማጠቢያና መቀመሚያ የሚውል ዉኃ "ድንግል በሆኑ ልጆች" እና በባህል ሐኪሙ (የንፅሕና ገደቦችን ሲያሟላ) ይቀዳል፡፡ እነዚህ አባላት ከሚያረክሱና ከሚያጎድፉ ነገሮች እራሳቸውን በማራቅ ንፅሕናቸውን ጠብቀዋል፤ ተፈጥሯዊ ባሕርያቸውን ይዘዋል፤ ቅድስናቸውን አክብረዋል፤ ተብለው ስለሚታመኑ ለመድኃኒት መቀመሚያ እና መስጫ የሚውል የምንጭ ዉኃ ቀድተው እንደሚያቀርቡ፤ ደብተራ ጥላሁን ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 03/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፤ "ከምንጭ የተቀዳው ዉኃና ጠበል፤ ቤት አይገባም" ይባላል፡፡ ቤት የገባ ዉኃ እና "ጠበል" ለመድኃኒትና ለመንፈሳዊ አገልግሎት አይውልም፤ "እረክሷል፤ ቅድስናውን አጥቷል" ተብሎ ይነገራል (መሪጌታ ገብረመድኃን፣ ቃ.መ፤ 25/04/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ ከነዚህ መረጃዎች በመነሳት፤ ቤት የገባ ዉኃ፤ በሙቀትና ቅዝቃዜ፣ በአቧራ፣ በሰዎች፣ በቁስና በእንስሳት ንክኪ ንፅሕናውን እንደሚያጣ እና ሊበከል እንደሚችል፤ ይታሰባል፡፡ በአጠቃላይ ለዕፀ መድኃኒት ቅመማ የሚውል ዉኃ ከምንጭ የተቀዳ፣ በእንስሳት፣ በአዕዋፍ፣ በሰውና በተለያዩ አካላት ቀድሞ ያልተነካ፣ ያልተቀመሰና ያልተቀዳ እንዲሆን ይመከራል፡፡ ይህ ተግባር፤ በዉኃ ወለድ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር፤ ወደ ሌላ አካል እንዳይዛመቱ ለማግታት፤ የመድኃኒት መቀመሚያና መስጫ ዉኃን ንጽሕና ለመጠቀም፤ ጉልህ ፋይዳ እና ተግባር እንዳለው፤ ይታመናል፡፡

### ለ) የዕለት፣ የቀናት እና የወቅቶች እሳቤ

በዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ሂደት የዕለት፣ የቀናት እና የወቅቶች ባሕርያት ልዩ ትርጉም፣ ምስጢር፣ ጊዜ እና ኃይል አላቸው እንደሚባል፤ መሪጌታ ባሕረጥበብ ይገልጻሉ። በአንድ ቀን ውስጥ አራቱ ባሕርያት የዕለት ዑደትና ገቢራቸውን ጠብቀው፤ ቦታና ገደባቸውን አክብረው፣ ኃይልና ስልጣናቸውን ለይተው በየተራ ይወጣሉ፤ ይጠልቃሉ፤ ተብሎ ይታሰባል (ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)። ስለዚህ በፅንስ፣ በመወለድ እና በልጅነት የሚጀምረው የነፋስ ባሕርይ "በጧት"[87] ይመሰላል፤ ይወከላል። በዚህ ሠዓት፤ የመሬትና የነፋስ ባሕርያት ተጋብተው[88]፤ የሕይወት ፍሬ ተጠንስሶ የተዘራበት፣ አካልና እስትንፋስ የተገናኙበት፣ ሕያው ፍጥረቶች በአካል የታዩበት፣ ከጨረቃና ከከዋክብት ወደ ፀሐይ ብርሃን መሸጋገሪያ ጊዜ [ዐውድ] እንደሆነ ይነገራል፤ ይተረጎማል። በዚህ ዐውድ እና ድባብ ለመድኃኒት የሚሰበሰቡ ዕፅዋት ቅጠላቸው ሲቆረጥ፣ ፍሬያቸው ሲለቀም፣ ሥራቸው ሲቆፈር፤ ከነሙሉ ኃይላቸው፣ መዓዛ እና ጣዕማቸው ይገኛሉ፤ ተብሎ እንደሚታሰብ መሪጌታ ፍሬ ስብሃት አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 29/01/2011 ሊቦ ከምከም)። ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ምን ሚና ዓላቸው?

አቶ ደሴ፤ ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት[89]፤ የፍጥረትን ሕይወት ዘዋሪ፣ አንቀሳቃሽና ለዋጭ ኃይሎች ናቸው፤ ተብለው እንደሚታሰቡ ገልፀዋል። በዐውደ ነገስት እና በኮከብ ቆጠራ ሂደት፤ መጠሪያ ስምን፣ የትውልድ ዘመን፣ ቦታ፣ ጊዜ፣ ወርና ዓመተ ምህረትን ለይቶ፤ የአቆጣጠር

---

[87]አራቱ ባሕርያት በአንድ  ቀን ሂደትና ዑደት ውስጥ ስልጣንና ኃይል እንዳላቸው በባህል ሕክምና ባለሙያዎች ይነገራል። ነፍስ በጠዋት፤ እሳት በቀትር/እኩለቀን፤ ዉኃ ከሠዓት፤ መሬት ደግሞ የምሽት ባሕርይን እንደሚወክሉ፤ ይታሰባል። በዚህ ሂደትና ዐውድ የአካል ሥጋና ዕስትንፋስ ሲገናኙ በፈጣሪ ጥበብ ሕይወት ይፈጠራል። የአካል ሥጋ የመሬትን፤ ዕስትንፋስ ደግሞ የነፋስን ገቢር በመያዝ መሬትና ነፋስ "በኅልዮ" ሲገናኙ የፍጥረት ምንጭ እንደሆኑ ይታመናል (መሪጌታ ባሕረጥበብ እና መሪጌታ መንግስቴ፣ ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ እና 10/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

[88]በሥነ ፍጥረት፤ አካልና ሥጋ "የመሬት"፤ ነፋስና ሕይወት "የነፋስ" ተምሳሌት ተደርገው እንደሚታሰቡ  መሪጌታ ፍሬስብሃት ይገልጻሉ (ቃ.መ፤ 29/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

[89]ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት፤ ከመሬትና ከተፈጥሮ ጋር የአላቸው መስተጋብር ምን ይሆን? ምን ዓይነት ምስጢርና ቃል ኪዳን አላቸው? ከዋክብት፣ ሥነ ምህዳር እና ጤና እንዴት ይገናኛሉ? ሲባል የሥነ ከዋክብት፣ "ሜዲካል አስትሮሎጂ" እና የሥነ ፈለግ ሣይንስ ምርምሮች ምላሽ የሚሰጡት ርዕሰ ጉዳይ ቢሆንም በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች (ኮከብ ቆጣሪዎች)፤ አካባቢያቸውን አንብበው፣ ዘመኑን ለይተው፣ ሥነ ምህዳሩን አጥንተው፣ የኮከብ ባሕርያትን ዑደት ተከትለው፤ ዓመቱን ቆጥረው፤ ወቅቱን ጠብቀው፤ ዕለቱን አክብረው ለመድኃኒት የሚውሉ ዕፅዋትን ከመስክ እንደሚሰበስቡ አስረድተዋል (አቶ ደሴና መሪጌታ ዘላለም፣ ቃ.መ፤ 25/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 20/04/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)። Alemayehu (1982) ኢትዮጵያ የምትገኝበት መልክዓ ምድር፣ የሥነ ምህዳር ስብጥር፣ የዕፅዋት ዓይነትና ባሕርይ፣ የበሽታ እና የፈውስ አማራጮች መብዛት ከሌላው ዓለም እንደሚለያት መክረዋል። ከዚህ አንጻር የሕዋ ሣይንስን ተጠቅሞ፤ የሥነ ከዋክብት እና የሥነ ምህዳር ትስስርን በማጤን በጤና፣ በባሕርይ እና በዕድሜ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ መገንዘብ እንደሚቻል፤ ይታመናል።

ልማድና ተግባራትን አሟልቶ የግለሰብ ባሕርይ፣ ዕጣ ፈንታ፣ ይነገራል፤ ይቆጠራል፣ ይጠቆማል፣ ይተነበያል፣ ይገለጻል፤ በማለት አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 23/04/2011 ሊቦ ከምከም)። በሥነ ከዋክብት አቆጣጠር ሂደት የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት አቀማመጥ፣ መውጫና መጥለቂያ ጊዜ፣ መገኛ ቦታና የቆይታ ቀን፤ የፍጥረትን ዕጣ ፈንታ፣ እድሜና ተፈጥሯዊ ባሕርይን ለመመርመር እና ለመተንበይ ዐበይት ርዕሰ ጉዳዮች እንደሆኑ፤ መሪጌታ ፋንታሁን መክረዋል (ቃ.መ፤ 20/06/2011 ፋርጣ)።

ፀሐይ፤ ጧት ስትወጣ "በብርሃኗ አድምቃ፣ በሙቀቷ አብስላ፤ ፍጥረትን መግባ የዕለት ተግባሯን አጠናቃ በስተ ምዕራብ ትጠልቃለች" ይላሉ ሊቀጠበብት አብርሃም። ጨረቃና ከዋክብትም ጊዜና ሠዓታቸውን ጠብቀው በምሽቱ ይሰለጥናሉ። ፍጥረትን፤ በነፋስና በዉኃ ባሕርያቸው አብርደው፣ አስክነው እና አቀዝቅዘው የዕለት ዑደታቸውን አጠናቀው ከመሄዳቸው በፊት፤ የጨለማ እና የብርሃን፤ "የሰማይ" እና የመሬትን "መፋቻ"፣ መሸጋገሪያ እና መጋጠሚያ የንጋት ሠዓትና ድባብን ጠብቆ ዕፅዋትን መቅረብ እና መቁረጥ ቅድስናቸውን ይጠብቃል፤ የፈውስ ኃይላቸውን ይጨምራል፤ ተብሎ ይታመናል (ሊቀጠበብት አብርሃም፣ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም)። ይህን እሳቤ፣ እምነት እና ዐውድ መነሻ አድርጎ የዕፅዋትን ገቢር አሟልቶ ዕፀ መድኃኒት መሰብሰብ ጥራቱን ለማረጋገጥ፣ ልክና ደረጃውን ለማወቅ፣ ገደብና ፍቃዱን ለመለየት፣ ማስተካከያና ማስፈፀሚያ ስልቶችን ለመገንዘብ፤ ጉልህ ፋይዳ እንዳለው፤ ይታሰባል።

ከዚህ ተግባርና ሥርዓት በተለየ ዕፅዋትን በማንኛውም ሠዓት ወይም "በቀትር ፀሐይ" ቆርጦ፣ ፍሬያቸውን ለቅሞና ቆፍሮ ለመድኃኒት መጠቀም፤ ሁለት ዓይነት ጉዳት እንዳለው መሪጌታ ስዩም ገልፀዋል። አንድም ዕፅዋትን አላግባብ መቅረብ የባህል ሐኪሙን "ያስቀስፋል፤ በአጋንንት ያስመታል፤ ጤናን ጠንቅ ላይ ይጥላል" ተብሎ ይታሰባል። በሌላ በኩል ደግሞ ለታካሚው "መርዝ በጥብጦ እንደመስጠት ይቆጠራል፤ ለሞት ምክንያት ይሆናል" ይባላል (ቃ.መ፤04/02/2011 እብናት)። ይህን ጉዳት ታሳቢ በማድረግ የንጋት ዐውድን ጠብቀው፤ ዕለትን አክብረው እና ቀናትን ቆጥረው፣ ወቅትን ለይተው ለፈውስ የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ከመስክ እንደሚሰበስቡ መገንዘብ ተችሏል። ዕፀ መድኃኒት መሰብሰቢያ ቀናት እነማን ናቸው? ለምን ተመረጡ? ምን ዓይነት ትዕምርት/ውክልና አላቸው ተብሎ ይታሰባል?

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች፤ ዕፀ መድኃኒት ለመሰብሰብ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ሐሙስ እና ዓርብ ቀናትን ይመርጣሉ። በአንጻሩ ቅዳሜ፣ እሁድና ሰኞ ዕፀ መድኃኒት የማይሰበሰብባቸው ቀናት እንደሆኑ ደብተራ ጥላሁን እና መሪጌታ መንግስቴ

ይገልጻሉ። እነዚህ ቀናት ለምን አልተመረጡም? ሲባል እግዚአብሔር ከእሁድ እስከ ዓርብ በዚህ ዓለም የሚገኙ አራቱን ባሕርያት፣ "ጠፍር" እና መሬትን፣ ዕፅዋትን፣ ከዋክብትን፣ እንስሳትን እና ሰውን ፈጥሮ ሲያበቃ፤ የአረፈበት ዕለት "ቅዳሜ፤ የሰንበት ቀን ነው"፤ ተብሎ ይታመናል። እሁድ አራቱን ባሕርያት፣ መላእክት እና ጨለማን የፈጠረበት፤ "በዕለተ ሰኑይ" [ሰኞ] ደግሞ መሬትና ጠፈርን የለየበት፤ በቃሉ አፅንቶ የአቆመበትና የአረጋበት ቀናትን ታሳቢ በማድረግ፤ በነዚህ ቀናት ዕፅዋትን "መቅረብና መቁረጥ አይገባም፤ ለድግምት ካልሆነ ለፈውስ መድኃኒት አይውሉም"፤ በማለት ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 03/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 10/03/ 2011 እብናት)። ፈጣሪ ጠፈርና እና ምድርን ከለየ በኂላ በዕለተ ሰሉስ ማክሰኞ ቀን ዕፅዋትን እንደፈጠረ፤ መሪጌታ ሠረቀብርሃን ገልፀዋል። የማክሰኞ ፍጥረት (ዕፅዋት) ለአካል ሥጋ እና መንፈስ ምግብ እና መድኃኒት በመሆን የሕይወት ፍሬ (ዕፅ) ናቸው፤ ተብሎ ይታሰባል። ስለዚህ በዕለተ ማክሰኞ ከመስክ የመሰብሰባቸው ምስጢር፤ አንድም የተፈጠሩበትን ቀን ለማስታወስ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሕይወት ምግብ እና መድኃኒት እንደሆኑ በማሰብ ነው፤ ይባላል (ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት)።

መሪጌታ ልሳነወርቅ፤ እግዚአብሔር በዕለተ ረቡዕ፤ "ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብትን ፈጠረ፤ ፀሐይን ከእሳት፤ ጨረቃ እና ከዋክብትን ከነፋስና ከዉኃ ባሕርያት ሰራቸው" በማለት ገልፀዋል። ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት የተፈጥሮ ዓለምን (መሬትን) የመቀየር እና የመለወጥ ኃይልና ጉልበት እንዳላቸው፤ ስለሚታሰብ፤ የፍጥረትን ባሕርይ፣ ዕድሜ፣ ገጠመኝ እና ዕጣ ፈንታ ይወስናሉ፤ ይባላል። በዚህ ዕለት ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት ከመስክ ሲቆረጡ፣ ሲለቀሙና ሲቆፈሩ የክዋክብትን ገቢር፣ ስም፣ ኃይል እና ሥልጣን ጠርቶ ዕፅዋትን አንግሶ መሰብሰብ የተለመደ ተግባር መሆኑን ገልፀዋል። በተለይ "ለእርኩስ መንፈስ፣ ለሾተላይ፣ ለድግምት እና ለግርማ ሞገስ" ሥርዓተ ገቢር የሚቆረጡ ዕፅዋት በዕለተ ረቡዕ ከመስክ ቢሰበሰቡ መልካም መሆኑን ጠቁመው፤ "ለግርማ ሞገስ" የሚውሉ ዕፅዋት በሚከተለው አግባብ ተደግሞ እንደሚቆረጡ አስረድተዋል ።

እንተ ውእቱ ዕፀ ጥበብ
የፀሐይን ኃይል፤ የንጉስን ሥልጣን
የጨረቃን ብርሃን፤ የኮከብን ድምቀት
ኃይልና ሥልጣን ሽረሽ፤
ለእኔ እገሌ አሰግጅልኝ፤

በማለት ፀሎተ ድግምት እንደሚቀርብ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 27/04/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ ከዚህ ይዘት እንደምንረዳው፤ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ለፍጥረት ዓለም የኃይል፣ የብርሃን እና የለዋጭነት ሚና እንዳላቸው፤ ይታሰባል፡፡ ንጉስም በሥልጣኑ፣ በዙፋኑ፣ በግርማ ሞገሱና በድባቡ የበላይ አለቃ፣ አስተዳዳሪ፤ የሚከበርና የሚፈራ፤ ሰው የሚሰግድለትና የሚታዘዝለት፤ የወደደና የፈቀደውን የሚያደርግ ኃይልና ሥልጣን በእጁ እንዳለ ይታመናል፡፡ በዚህ አግባብ እና ትይዩ "ለግርማ ሞገስ" የሚሰበሰቡ ዕፅዋት ተደግመው ሲቆረጡና ሲሰጡ፤ ለግለሰቡ ሞገስን፣ ድምቀትን፣ ግዝፈትን፣ ብርታትን፣ ኃይልና ሥልጣንን ይሰጣሉ፤ ያወርሳሉ፤ ያገዝፋሉ፤ ተብሎ ይታሰባል (ሊቀጠበብት አብርሃም፣ ቃ.መ፤ 30/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

መሪጌታ መኀሪ ደግሞ፤ በዕለተ ሐሙስ፤ ፈጣሪ በውኃ እና በየብስ የሚኖሩ እንስሳትን እንደፈጠረ ጠቁመው፤ በዚህ ዕለት ለመድኃኒት የሚውሉ ዕፅዋትን እና እንስሳትን ዓይነትና ባሕርያቸውን ለይቶ ለምግብና ለሕመም ፈውስ የሚሆኑትን መጠቀም፤ የፈጣሪ ፈቃድ እንደሆነ፤ ገልፀዋል፡፡ የሰው ልጅ ለምግብና ለፈውሱ ተለይተው የተሰጡትን ዕፅዋትና እንስሳት ሲመገብና ሲጠቀም ድኅነትን እንደሚያገኝ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 27/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ "እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን በዕለተ ዓርብ፤ በአምሳሉና በመልኩ አንጾ አዳምን ፈጠረ" ይላሉ መሪጌታ አዲሱ፡፡ አዳም በተፈጠረበት ዕለት የሚሰበሰቡ ዕፅዋት ለአዳም የታዘዙ እና የተገዙ፤ ለአዳም ዘር መሰልጠኛ፤ ለአዳም ልብስ፣ "ጉርስ" (ምግብ)፣ መጠለያ እና የሕይወት ፍሬ በመሆን እንዲገዙለት የፈጣሪ ፈቃድና "ቃል ኪዳን አለ"፤ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ዕለት የመድኃኒት ግብዓቶችን መሰብሰብ አጋንንትን ለመዋጋት፤ በጾምና በፀሎት[90] ዕፅዋትን ለመቅረብ እና አንግሶ ለመቁረጥ ተመራጭ ቀን እንደሚሆን ገልፀዋል (ቃ.መ፤19/01/2011 ፋርጣ)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዕፅዋትን ከመስክ ለመልቀምና ለመሰብሰብ የወቅቶች ዐውድ፣ ገደብ እና ፈቃድ እንዳለ በባሕል ሕክምና

[90] በክርስትና ሃይማኖት ረቡዕ እና ዓርብ የጾም ቀናት ናቸው፡፡ በባህል ሕክምና ልማድም ረቡዕ እና ዓርብን ታሳቢ በማድረግ የመድኃኒት ግብዓቶች ከመስክ ይሰበስባሉ፡፡ እነዚህ ቀናት ከሌሎች ቀናት በተለየ ለምን ተመረጡ? ሲባል ከእየሱስ ክርስቶስ መያዝና መሰቀል ዕለት ጋር አገናኝተው ይገልጻሉ፡፡ "አይሁዶች ረቡዕ እየሱስ ክርስቶስን ይዘው ዓርብ የሰቀሉበት ዕለት ነው" ይላሉ መሪጌታ ስዩም፡፡ በነዚህ ቀናት የአጋንንት ሥራ እና ተንኮል የታየበት፤ ዕቅዳቸው የሰመረበትና የተፈፀመበት፤ እየሱስ ክርስቶስ የተያዘበት፣ የታሰረበት፣ የተገረፈበት እና "ደሙ የፈሰሰበት ነው" ይባላል (ቃ.መ፤04/02/2011 እብናት)፡፡ የእየሱስ ክርስቶስ መንገላታት እና ደም መፍሰስ፤ ለዓለም ድኅነት እና ብርሃን በመሆን፤ "አጋንንትን ድል ነስቶ የረከሰውን ማንነት በቅድስና፣ የወደቀውን ሰብዕና በሕይወት፤ የሞተውን አካል በትንሳኤ አድሶታል" በማለት ደብተራ መልኩ ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፤ የተሰቀለበት ዕፅ፣ የተገረፈበት ገመድ፣ የረገጠው መሬት የምኅረትና የድኅነት ምሳሌ፤ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ረቡዕና ዓርብ ዕለትን፤ በጾም እና በፀሎት አስቦ፤ በተረጋጋ አዕምሮ እና በሰከነ አንደበት አጋንንትን መዋጋት እና ክፉ ስራቸውን ማርከስ፤ እንደ ቅድስና ይታሰባል፡፡ በነዚህ ቀናት ዕፅዋትን አመስግኖ፣ "ባርኮ"ና ቀድሶ መቅረብና መቁረጥ ለፈውስ ያበቃል፤ ለድኅነት ያደርሳል፤ ተብሎ ይታመናል (ቃ.መ፤23/01/2011 ፋርጣ)፡፡

ባለሙያዎች ይታሰባል። ከዚህ አንጻር፤ ዕፀ መድኃኒት ከመስክ ለመሰብሰብ የትኛው ወቅት እና ዐውድ ይመረጣል? ለምን?

መሪጌታ በረከት እና ደብተራ መልኩ፤ ለባህል ሕክምና የሚውሉ ዕፅዋት ዓመትን ጠብቆ፣ ወቅትና ጊዜን አስቦ፣ ወር እና ዕለትን አክብሮ መሰብሰብ እንዳለባቸው ይመክራሉ። በዓመት ውስጥ አራት ወቅቶች እንዳሉ ጠቁመው፤ የራሳቸው ገቢር፣ ዘመን፣ መገለጫ፣ ኃይልና ጉልበት እንዳላቸው ይገልፃሉ። የዓመት ሂደትና ዘመናቸውን በመተካካት ፈጽመው፤ ዑደታቸውን ጨርሰው ሲገኙ አንድ ዓመት ይባላል። በዚህ ሂደት በነፋስ ባሕርይ (ፀደይ) የተወለደውና የተጀመረው ዓመት፤ በእሳት (በጋ) ዘመን በስሎና ጠንክሮ፤ የዉኃ (በልግ) ጊዜውን ጨርሶ፤ በመሬት (በክረምት) ባሕርይው ይጠናቀቃል። ወቅቶችም በፀደይ ተወልደው፤ በክረምት አርጅተው የዓመት ፈቃድና ገቢራቸውን ፈፅመው፤ ሲሰናበቱ ዓመት ይቆጠራል (ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት እና 23/01/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

በዚህ ሂደት ለዕፀ መድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት በክረምት በቅለውና አድገው፤ ነባር ዕፅዋትም ለምልመው በፀደይ ወቅት ጠንክረው፣ አብበውና አፍርተው እንደሚገኙ መሪጌታ መኀሪ ገልፀዋል። የፀደይ ወቅት (በንፋስ ባሕርያቸው) "የነፋስ፣ የአበባና የፍሬ ወቅት ነው" ይባላል (ቃ.መ፤27/01/2011 ሊቦ ከምከም)። በዚህ ወቅት ዕፅዋት ጠንክረው፣ አብበውና አፍርተው፤ በመልካም መዓዛቸው፣ በተፈጥሯዊ ባሕርያቸው፣ በሙሉ ኃይልና ጉልበታቸው የሚገኙበት ወቅት ነው፤ ተብሎ ይታሰባል። ይህ ወቅት እና ዐውድ ለባህል ሕክምና ባለሙያዎች "የዕለትና የዓመት መድኃኒት መሰብሰቢያ ጊዜ፤ የአዝመራ ወቅት ነው" ይላሉ፤ መሪጌታ ስንታየሁ (14/03/2011 እብናት)። ለመድኃኒት የሚውሉ ግብዓቶችን በሥፋትና በብዛት ሥራቸውን፣ ቅጠላቸውን፣ አበባቸውን፣ ቅርፊታቸውን እንደልብ ለማግኘት አመቺ ጊዜ መሆኑን ጠቁመው፤ “የጮርቃ እና የለጋ” እድሜያቸውን አሳልፈው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሳይደርቁ፣ ሳይጠነክሩ፣ “ሳይቆረፍዱ”፣ ሳያረጁ፤ ጣዕምና መዓዛቸውን ሳያጡ፤ በመካከለኛ ዕድሜና ዐውድ ዘመናቸው፤ ለመሰብሰብ አመቺ ወራቶች እንደሆኑ፤ መረጃ ሰጪዎች አስረድተዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደርሶ የሰጡት ሃሳብ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)።

በፀደይ ወቅት (መስከረም፣ ጥቅምትና ኅዳር)፤ ዕፅዋት አብበውና አፍርተው፣ ትኩስ ኃይላቸውን እንደያዙ "በወጣትነት ዘመናቸው የሚገኙበት እድሜ ነው" ይላሉ ደብተራ መልኩ (ቃ.መ፤ 23/01/2011 ፋርጣ)። ይህ ወቅት የአዲስ ዓመት መጀመሪያ፣ ሌቱና ቀኑ እኩል የሚሆኑበት፣

ፀሐይ ሚዛኗን ጠብቃ በምድር ወገብ የምትገኝበት፣ ጨረቃ የምትወጣበትና ከዋክብት የሚደምቁበት፣ የተፈጥሮ ፀጋ የሚታይበት፤ ሰው፣ እንስሳትና ዕፅዋት ሚዛናቸውን ጠብቀው በልተውና ጠግበው የሚያድሩበት፤ "ልዩ ወቅት እና የተፈጥሮ ገፀ በረከት ነው" ይባላል። ይህ ወቅት ሲያልፍ በጋ ሲተካ፤ የሣር፣ የአረም፣ የሃረግ እና የቁጥቋጦ ዘሮች አበባቸውን አክስመው፣ ዘራቸውን አርግፈው፣ ግንዳቸውን አድርቀው ይጠፋሉ፤ ነባር ዕፅዋትም ቅጠላቸው ደርቆ፣ ግንዳቸው ጠውልጎ ከጥቅም ውጪ በመሆን ለመድኃኒት[91] ግብዓት እንደማያገለግሉ፤ አቶ ደርሶ መክረዋል (ቃ.መ፤03/02/2011 እብናት)።

በአጠቃላይ ለድኃኒት አገልግሎት የሚውሉ ዕፅዋት ከመስክ ሲሰበሰቡ፤ የዕለት፣ የቀን እና የወቅት ዐውድን ጠብቆ፣ ሥነ ምህዳራዊ መገኛ ቦታቸውን ለይቶ፣ ሥርዓትና ገቢራቸውን አሟልቶ፣ ማስፈፀሚያና ማስተካከያ ስልቶችን ተግብሮ መልቀምና መሰብሰብ እንደሚገባ፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል።

### ሐ) የቁጥርና የአቅጣጫ እሳቤ

አንድ ባሕርይ (ሥርዓተ ገቢር) ልክ እና ገደቡ ስንት ነው? ባሕርይ ሲዛባ ማስተካከያ መጠኑ እስከምን ድረስ ነው? ሲባል ልክን፣ ገደብን፣ መጠንን፣ ብዛትን፣ ደንብን፣ ሃሳብና ድርጊትን ገላጭ፤ መስፈሪያ እና ማስፈፀሚያ አሃድ በመሆን ቁጥር እና አቅጣጫዎች ይቀርባሉ። የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እና የባህል ሐኪሞች በተደጋጋሚ ለሥርዓተ ገቢር ማስተካከያ የሚጠቀሟቸው ቁጥርና አቅጣጫዎች እነማን ናቸው? ምን ዓይነት ተግባርና ውክልና አላቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል።

---

[91]በፀደይ ወቅት የሚቆረጥ ማር፤ በተለይ የአቡነ አረጋዊ (ጥቅምት 14 ቀን) እና የእስጢፋኖስ ማር ለምግብና ለመድኃኒት እንደሚያገለግል አቶ ጌጡ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 24/01/2011 ፋርጣ)። የደብረ ዳሞ ገዳም መስራች አቡነ አረጋዊ "ዓለምን ዞረው ሕሙማንን ፈውሰው፣ ዓይን አብርተው፤ ከዚህ ዓለም የተለዩባትን ዕለት አስቦ ማር ቆርጦ መጠቀም" [ጥቅምት 14 ቀን/መታሰቢያ ዕለት]፤ መድኃኒት እንደሆነ ይታመናል። በተመሳሳይ መልኩ ጥቅምት 17 ቀን በእስጢፋኖስ ዕለት ታስቦ የሚቆረጥ ማር ፍቱን መድኃኒት እንደሆነ፤ መሪጌታ ሠረቀብርሃን እና ሊቀጠበብት አብርሃም ገልፀዋል። በባህል ሕክምና ማር ምን ፋይዳ አለው? ለምን የፀደይ ወቅት ተመረጠ? ሲባል፤ በፀደይ ወቅት ዕፅዋት በዓይነትና በብዛት የሚገኙበት፤ በየቦታው አብበው እና አፍርተው የሚታዩበት፤ ንቦች እንደልባቸው አበባ ቀስመው ማር የሚሰሩበት ወቅት ሲሆን፤ ከመስክ የሚሰበሰበው የንብ፣ የጣዝማ እና የትንኝ ማር በዓይነቱ እና በግብዓቱ የጨመረ፤ ከሌላው ጊዜ በተለየ ለመድኃኒት መቀመሚያ እና ለምግብ እንደሚውል ገልፀዋል። የጣዝማ ማር ከመሬት ተቆፍሮ የሚገኝ ሲሆን የትንኝ ማር ደግሞ ከዛፍ ግንድ ውስጥ ተፈልፍሎ እንደሚወጣ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት እና 30/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብና በባህል ሐኪሞች እሳቤ ልማዳዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ሲከውኑ ልክና ገደባቸውን ለመግለጽ፤ መስፈርትና መጠናቸውን ለመጠቆም፣ ደንብና ሥርዓታቸውን ለመተግበር፣ ለተፈጥሮ ያላቸውን እሳቤ ለመገንዘብ፤ ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት፣ የተዛባን ባሕርይ ለማስተካከል እና የጎደለን ለመሙላት፤ ሰባት ቁጥር ልዩና ፍጹም ቁጥር በመሆን ለሥርዓተ ገቢር ማስተካከያ እንደምታገለግል፤ ይታመናል[92] (መሪጌታ ዘላለም እና መሪጌታ መንግስቱ፣ ቃ.መ፤ 20/04/2011 ፋርጣ እና 10/03/2011 እብናት በቅደም ከተል)። አንድ ድርጊት በምን ያህል ብዛት ቢዘጋጅና ቢፈፀም ይበቃል? መጠኑ ስንት ነው? በሃሳብና በድርጊት መካከል ፍጹም የሆነ ስምረትና ጥምረት፤ መስማማት እና መዋሃድ እንዴት ይመጣል? ሲባል፤

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ እሳቤ፤ ሰባት ቁጥር በሰው ልጅ አኗኗር፣ ልማድ፣ ሃይማኖትና ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የምትገባበት፣ የምትጠራበት፣ የምትጠቀስበት ርዕሰ ጉዳይ በርካታ ቢሆንም፤ "በድርጊቷ ፍጹም ቁጥር ናት" ይላሉ መሪጌታ ፍሬስብሃት። ሰባት ቁጥር ከመደበኛ አገልግሎቷ በተለየ፤ "ሥነ ፍጥረትን" በማስገኘት፣ የተዛባን ባሕርይን በማስተካከል፣ ወደ ቀድሞ ባሕርይ በመመለስ፣ ሥርዓተ ገቢርን በማስተካከል ሂደት "መለኮታዊ ኃይል አላት" ተብሎ ይታመናል (ቃ.መ፤ 29/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

መሪጌታ ባሕረጥበብ፤ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት አስተምህሮ፤ እግዚአብሔር በኀልዮ [በአርምሞ] ዓለምን ሲፈጥር መጀመሪያ አራቱን ባሕርያት (ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃ እና መሬትን)፣ ሰማያት፣ ጨለማን እና መላእክትን በመፍጠር፤ የሌለውን ዓለም እንዳለ፤ የማይታየውን እንዲታይ፣ የማይታወቀውን እንዲታወቅ አድርጎ ሰባቱን ተግባራት አሟልቶ በዕለት እሁድ በቅደም ተከተል እንደፈጠራቸው፤ ገልፀዋል። የሰው ልጅም አራት ሥጋዊ እና ሶስት የነፍስ ባሕርያትን አዋህዶና አስተባብሮ የሚኖር፤ ከሰባት ባሕርያት እንደተገኘ እና እንደተሰራ ይታሰባል። ይህም የፍጥረት ሥር መሰረት ከሚባሉት አራቱ ባሕርያት ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃ እና መሬት አካላዊ ፍጥረቱን፤ የነፍሱን ገቢር ደግሞ ከሶስቱ ባሕርያት ልባዊት፣ ነባዊት እና ሕያዊት እንዳገኘ ይታመናል (ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)።

[92]በዚህ ጥናት ከቁጥር ይዘቶች መካከል ሰባት ጎልታ በመውጣት በተደጋጋሚ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ውክልናን በመያዝ የባሕርይ ማስተካከያና የድርጊት ማስፈፀሚያ ቀመር ሆና ቀርባለች። ከአቅጣጫ ምሥራቅና ምዕራብ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ፍቺን በመያዝ ተገልፀዋል፤ ከቁጥር ሰባትን ከአቅጣጫ ምሥራቅና ምዕራብን በማሳያነት በማቅረብ ይዘቱ የታለፈ መሆኑን ልብ ይሏል።

ሠናይ ደግሞ፤ በእብራዊያን "ሳብእ" ሲባል "ሰባት" ማለት ሲሆን "ፍጹም ቁጥር ማለት ነው"፤ በግዕዝ፤ "ሰብእ" ሲባል "ሰው" ማለት ሲሆን ሰባት ባሕርያት የአሉበት፤ "አዳም ነውርና ነቀፋ የሌለበት፣ ...ሥግው እመሬት" የሆነ [ከመሬት የተገኘ ሰው]፣ "ፍጹምና መልካም" ፍጥረት ማለት ነው፤ ይላሉ (2009፤ ገ.151)። በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች እሳቤ፤ ሰባት ቁጥር በሥነ ፍጥረት ሂደት ውስጥ "ዓለም" እና "ሰውን" በማስገኘት፤ መለኮታዊ ኃይል እና ፀጋ እንዳላት ይታሰባል። እግዚአብሔር በዕለተ እሁድ ከፈጠራቸው ባሕርያት ብርሃንን "ነስቶ" [ወስዶ] ሰባቱን ሰማያት እንደፈጠራቸው መሪጌታ ስንታየሁ ገልፀዋል። ሰባቱ ሰማያትም፤ "ሰማይ ውዱድ፣ መንበረ ስብሃት፣ ጽርሐ አርያም፣ ኢዮር፣ ራማ፣ ኤረርና እየሩሳሌም ሰማያዊት ናቸው" በማለት ጠቅሰዋል። ከሰባቱ ሰማያት መካከል፤ መንበረ ስብሐት፣ ኢዮር፣ ራማ እና ኤረርን ፈጥሮ ሲያበቃ በሰባት የእሳት መጋረጃ ጋረዳቸው፤ በሰባት የእሳት አጥር አጠራቸው፤ ተብሎ እንደሚታመን አስረድተዋል (ቃ.መ፤14/03/2011 እብናት)።

ከሰባቱ ሰማያት ሶስቱ "ኢዮር፣ ራማ እና ኤረር የመላእክት መገኛና መኖሪያ ከተሞች ናቸው" ይላሉ መሪጌታ መንግስቱ። ከነዚህ ከተሞች መካከል የፍጥረት መኖሪያ እና የሕይወት መገኛ የሆነችው፤ ኢዮር ክልል (መሬት) "የሰባቱ ሊቃነ መላእክት ከዋክብት[93] መገኛ ናት" ተብሎ ይታመናል። ሰባቱ ከዋክብት ደግሞ ለሰባቱ (ለሳምንቱ) ቀናት ተምሳሌት፣ ተወካይ፣ ጠባቂ እና ተጠሪ በመሆን እንደተሾሙ፤ ገልፀዋል (ቃ.መ፤11/04/2011 እብናት)።

በዚህ እሳቤ፤ በሥነ ፍጥረት ሂደትና ሕይወት ውስጥ ሰባት ቁጥር መለኮታዊ ኃይል፣ የፈጣሪ "ምስጢርና ፀጋ አላት" ተብሎ ይታመናል። ሰባት ቁጥር "ፍጹም የሆነውን አዳም በአካልና በመንፈስ የአስገኘች"፤ ፈጣሪ ይህን ዓለም ሲሰራ እና ሲፈጥር ስድስቱን ቀናት ሰርቶ በሰባተኛው ቀን ሥራውን አጠናቆ የአረፈበት (ዕለተ ሰንበት ቅዳሜ)፤ "ቅዱስ ቀን" ትባላለች። የሰው ልጆችም አምስቱን ቀን ሰርተው ሰንበትን እንዲያርፉ፤ በሰንበት እንዳይሰሩ "የሰንበት ዉኃን" [ዓርብ የተቀዳ ዉኃ] እንዲጠቀሙ፣ የታመመን እንዲጠይቁ፣ የተራበን እንዲያጎርሱ፣ የታረዘን እንዲያለብሱ፤ ለሥጋቸው እረፍትን፣ ለመንፈሳቸው ምስጋናን፣ ለሕይወታቸው ጣዕምን ለማግኘት ዕለተ

---

[93] መሪጌታ መንግስቱ እና ደብተራ ማኅሪ፤ በሰባቱ ከዋክብት የተወከሉት ሊቃነ መልእክት፤ ሚካኤል (ምህረት የሚያመጣ)፣ ገብርኤል (የምሥጋና ዜና አብሳሪ)፣ ሩፋኤል (ፈዋሽ ፈጥኖ ደራሽ)፣ ፋኑኤል (ከአደጋ የሚሰውር)፣ ኡራኤል (ለመብረቅና ለነጎድጓድ የተሾመ)፣ ራጉኤል (አጋንንት የሚያሳድድ) እና ሣቁኤል (ለተቸገሩ ፈጥኖ ደራሽና የሚያጽናና) የሚሉ ናቸው። እነዚህ መላእክት ለሥርዓተ ገቢር ፀሎት ማስፈፀሚያ፤ ለዕፅዋት ማንገሻ፣ ለአጋንንት ማስለፍለፊያ፣ ለቁም ጽሕፈት፣ ለክታብ እና መሰል ተግባራት ሲጻፍና ሲነገር፤ የመላእክቱ ሥም እንደሚጠቀስና እንደሚጠራ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 11/04/2011 እብናት እና 27/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

ሰንበትን በመልካም ሥራና ምግባር አክብረውና አስበው እንደሚውሉ፤ ደብተራ መልኩ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፤ የሰው ልጅ ምሳሌ የሆነው "አዳም" በገነት ሰባት ዓመት ብቻውን ሲኖር፤ ፈጣሪ "ብቸኝነቱን ዓይቶ በከፍተኛ እንቅልፍ ሰመመን ውስጥ ጥሎት" የሕይወት አጋርና አምሳሉን ሄዋን ከግራ ጎኑ አጥንት፣ ሥጋ፣ ደምና ነፍስ "ነስቶ" ሰራት፤ አዳምም በሰባት ዓመቱ ከሰመመን እንቅልፍ ሲነሳ በፈጣሪ መለኮት ኃይልና ምስጢር አምሳሉ እንደሆነች አወቃት፡፡ ከዚህ በኋላ፤ አዳምና ሄዋን በገነት ዓለም አብረው ሲኖሩ፤ የፈጣሪን ቃል ዘንግተውና ተላልፈው፤ ዕፀ በለስን በልተው አዳም በአስራ አራት ዓመቱ፤ ሄዋን ደግሞ በሰባት ዓመቷ ከገነት ተባረው እንደወጡ መሪጌታ ገብረመድኅን ሃይማኖታዊ ትረካውን ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 25/04/2011 ሊቦ ከምከም)

በዚህ ዐውድ፤ በሰው ልጆች የእድሜ ገደብ ሂደት ውስጥ ሰባት ዓመት ክፉ ደጉን መለያ፣ የዓለምን ምስጢር ማወቂያ፣ ከነገሮችና ከድርጊቶች መማሪያ፣ አካባቢን መፈተሻና መጠየቂያ፣ እራስን ወደ መቻል፣ ከለጋነት ወደ ብስል፣ ከደካማ አካላዊ ይዘት ወደ ጥንካሬ መሸጋገሪያ እና መተላለፊያ ዓመት እንደሆነች ይታሰባል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ልጆች ሰባት ዓመት ሲሞላቸው መጾም እንዲጀምሩ ይደረጋል፤ ይመከራል፡፡ ለምን? ሲባል ሰባት ዓመት እራስን መቻያ፣ አካልና መንፈስን መግዣና መቆጣጠሪያ፣ ፍላጎት እና ጉልበትን መግቻ፣ መግሪያ እና መማሪያ ደረጃ እንደሆነ ይታመናል (ቄስ ብርሃኑ፣ ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት)፡፡ ሰባት ቁጥር በባህል ሕክምና ይዘት ምን ዓይነት ሚና አላት? ሲባል፤

በባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ልማድ፣ ድርጊትና ገቢር ውስጥ ተደጋግማ የምትመጣ ልክን፣ ገደብን፣ መጠንና ብዛትን አስረጅ በመሆን "ሰባት" ቁጥር ትጠቀሳለች፡፡ መሪጌታ ፍሬስብሃት፤ ሰባት ቁጥር "ዕፅዋት ማንገሻ፣ ፀሎተ ድግምት ማድረሻ ልዩ ቁጥር ናት" ይላሉ፡፡ በዚህ አግባብ፤ "የዕፅ አንግስ" ፀሎትን ለማድረስ፤ በሽታን ለመፈወስ፣ የተዛባ ባሕርይን ለማስተካከል፣ የመድኃኒት ግብዓት መጥኖ ለመስጠት፣ ልክና ገደብን ለማወቅ፤ ወደ ትክክለኛ መንገድ፣ ምጣኔ፣ ስኬትና ደረጃ ታደርሳለች፤ ወደ መታደስ ታመጣለች ተብሎ ይታሰባል (ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ ይህም ስለሆነ፤ "ለመፍትሔ ሥራይ እና ለአጋንንት" ፈውስ የሚደረግ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት ሲከወን፤ ሰባት ቁጥር የመጠን እና የገደብ ልክ መሆኗን፤ መሪጌታ ባሕረጥበብ እንደሚከተለው ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)፡-

> አጋንንት ለተፀናወተው [ለያዘው]፤ ገቢር[94] የቀጋ ሰባት ፍሬ፣ የሎሚ ሰባት ቀንበጥ፣ የቀጠጥና ሰባት ቅጠል፣ የወገርት ሥር፣ የአምጃ እና የፅጌረዳ አበባ፣ የአቱች ሥር አድርቆ፣ በአንድነት ደባልቆ፣ ወቅጦ፣ አሰሩን ለይቶ፣ የተወቀጠውን አልሞ ፈጭቶ፤ ጥቅምት አስራ አራት ቀን በተቆረጠ በአቡነ አረጋይ ነጭ ማር ለውሶ፣ ከአለት በፈለቀ ጠበል በጥብጦ በገንቦ [ከሸክላ የተሰራች በመጠኗ አነስተኛ የጠላና የጠጅ መጠጥ ማቅረቢያ] አሽጎ እንዲበስል [እንዲብላላ] ሰባት ቀን መሬት ውስጥ ይቀብራል፡፡ በሰባተኛው ቀን ጧት በጧት ተነስቶ፤ ፀሐይ ሳትወጣ እና ጮራዋን ሳትፈነጥቅ ከመሬት የተቀበረውን ገንቦ አውጥቶ፣ ጥላ ቦታ አስቀምጦ፣ በኮመል እንጨት አማስሎ፤ ውኃ ባልነካው ፈትል (በንፁሕ ጨርቅ) አሰሩን አጥሎ፣ የተጣራውን በጠርሙስ ሹሞ [ሞልቶና አሽጎ] ለሰባት ቀን ይቀመጣል፡፡ ከሰባት ቀን በኂላ ለመፍትሔ ሥራይ እና አጋንንት ለተፀናወተው፤ በአዋቂ ሰው ልክ በባዶ ሆዱ አንድ መለኪያ ለሰባት ቀን እየወሰደ ይቆያል፡፡ ከሆዱ የተጣለበትን ሥራይ ይሽራል፤ የተፀናወተውን አጋንንት ነቅሎ ያወጣል፡፡

በማለት አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው፤ ሰባት ቁጥር፤ ከዕፅዋት መረጣ እስከ አሰጣጥ ሂደት በአለው ሥርዓተ ገቢር ውስጥ ተደጋግማ እንደምትመጣ ይጠቁማል፡፡ የቁጥሯ ገቢርና ምጣኔ ከፀሎተ ድግምት፣ ከዕፅዋት ዓይነት፣ ምርጫ፣ ብዛት፣ ልክ፣ የመድኃኒት ክፍል እና ምጣኔ ይጀምራል፡፡ የቅመማ ሂደትና የቆይታ ጊዜን በማመላከት፤ የአሰጣጥ ሂደት፣ ድግግሞሽና ብዛትን በመወሰን ጉልህ ድርሻና ሚና እንዳላት ይገልፃል፡፡ በዚህ ሂደት እና እሳቤ፤ ሰባት ቁጥር፤ የልኬት ሚዛን እና መመጠኛ ኃይል በመሆን፤ የመብሰልና የመብቃት ደረጃን በመያዝ "ምሉዕ ቁጥር ናት"፤ ይባላል፡፡ ቁጥሯ ወደ ትክክለኛ መንገድ፣ ቦታ፣ ጣዕም፣ ስሜት፣ ብስለትና ደረጃ ታደርሳለች፤ "መለኮታዊ ኃይል አላት" ተብሎ ይታሰባል፡፡

ደብተራ መልኩ እና መሪጌታ ስዩም ደግሞ፤ "ለቡዳና ለዛር ቂም"፣ ለመንፈሳዊ ጭንቀት (ለባሕርይ መዛባት) "ፀበል፣ ፆምና ስግደት ይታዘዛል"፤ ይላሉ፡፡ የትእዛዙ ልኬትና መስፈርት "አንድ ሰንበት [ሰባት ቀን]፣ ሁለት ሰንበት..." እየተባለ ፀበል ለመጠመቅ፣ ለመፆምና ለመስገድ መመሪያ እንደሚሰጥ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ እና 14/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡ በዚህ ይዘት ደግሞ መንፈሳዊ ጭንቀትን፣ "የረከሰና የጎደፈን" ሰብዕና፣ የጠባይ

[94]በባህል ሕክምና ልማድ እና አተገባበር፤ "በነቢብ" እና "በገቢር" የሚባሉ ሁለት መሰረታዊ ይዘቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ በነቢብ ሲባል ርዕሰ ጉዳዩን፣ ይዘቱን፣ ፀሎቱን፣ ድግምቱን የሚያስረዳ መጽሐፍ ሲሆን፤ አተገባበሩን፣ ቅደም ተከተላዊ ሂደቱን፣ ሥርዓቱን እና ድርጊቱን የሚገልፅ ርዕሰ ጉዳይ "ገቢር" ይባላል፡፡ በነቢብ የሚጠቀሱ ይዘቶች፣ የሚቀርቡ ፀሎትና ድግምቶች ሳይሟሉ፤ ሥርዓተ ገቢሩን ተከትሎ መድኃኒት ማዘጋጀትና መስጠት ይዘቱን ያጓድላል፤ "የፈውስ ኃይሉን ይቀንሳል፤ ገቢሩን ይስታል፤ መድኃኒቱ ይረክሳል"፤ ተብሎ ይታሰባል (መሪጌታ መንግስቱ እና መሪጌታ ፋንታሁን፣ ቃ.መ፤ 11/04/2011 እብናት እና 19/01/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)፡፡

መቀያየርን ለማስተካከል፣ አጋንትን ለማስወጣትና ለማስለቀቅ ሰባት ቀን ፀበል መጠጣትና መጠመቅ፣ መስገድና መፆም የልኬቱና የመስፈርቱ አንድ አካል ተደርጎ ይታመናል።

መሪጌታ ፍሬስብሃት ደግሞ፤ ሰባት ቁጥር፤ ከፀሎተ ድግምት እስከ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት የሚዘልቅ ገቢርና መገለጫ እንዳላት ይመክራሉ። በተለይ "ለአንደርቢ፣ ለሕልመ ሌሊት፣ ለመንስኤ እስኪት (ብልቱ ለደከመ)፣ ለቡዳ፣ ለሸተላይ" የሚቆረጡ ዕፀ መድኃኒቶች ሰባት ጊዜ ተደግመው፣ ሰባት ፍሬ፣ ሰባት ቅጠል፣ ሰባት ዓይነት ሥር፣ ሰባት ድንጋይ ተራምደው (ረግጠው)፣ ሰባት ዕፅዋት ቀምመው፣ መጥነው፣ ልክና ሚዛኑን ጠብቀው፤ ሰባት ቀን ሲሰጡ "ድግምት ይፈታል፣ ፀሎት ይሰምራል፣ አጋንንት እና የሆድ ሥራይ ይወጣሉ" ተብሎ ይታሰባል (ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም)። በዚህ እሳቤ፤ የተዛባን ጠባይና ጤና በማስተካከል፣ የደከመን አካል በማበርታት፣ ወደ ቀድሞ አቋምና ባሕርይ መላሽ በመሆን፣ አካላዊና መንፈሳዊ ሚዛንን በመጠበቅ፣ የጎደለን በመሙላትና የበዛን በመቀነስ፤ ሰባት ቁጥር የመመለስ፣ የማመጣጠን እና የማስተካከል ገቢር እንዳላት ይታመናል። ከዚህ ይዘት በመቀጠል የባህል ሕክምና ሥርዓተ ገቢርን ለማስፈፀም አቅጣጫዎች (ምሥራቅና ምዕራብ) ምን ዓይነት ትዕምርት፣ ትርጓሜና ፍቺ እንዳላቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

መሪጌታ መኅሪ እና ሊቀጠበብት አብርሃም፤ ዕፀ መድኃኒት ከመሰብሰባቸው በፊት በማይነቃነቅ ጥቁር አለት (በተፈጥሮ በሚገኝ) ድንጋይ ላይ በመቆም፤ ፊትን ወደ ምሥራቅ በማዞር "የዕፀ አንግስ" ፀሎተ ድግምት እንደሚቀርብ ገልፀዋል። በማይነቃነቅ ጥቁር ድንጋይ ላይ ቆሞ የመፀለይ ምስጢር፤ ለፈውስ የሚቆረጡ ዕፅዋት ኃይል፣ ባሕርይ፣ ቅድስና፣ ተግባርና መሰረታቸውን ጠብቀው፤ በዕውነተኛ "ጠባያቸው" እና በፅኑ ባሕርያቸው ተገኝተው ፈውስ እንዲሰጡ፤ ገቢራቸው እንዲሰምር እና ፀሎታቸው እንዲሳካ፤ አጋንንትን ለማስወጣትና ለማራቅ፤ የዓለምን ኃይል፣ ጥበብና ዕውቀት ለመውረስ፤ ፀጋና በረከትን ለማግኘት ተብሎ እንደሚከወን መክረዋል (ቃ.መ፤23/01/2011 ፋርጣ እና 05/03/2011 ሊቦ ከምከም)።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ ምሥራቅ የተስፋ፣ የብርሃን፣ የኃይል፣ የትንሳኤ መንገድ ተደርጎ፤ እንደሚታመን ሊቀጠበብት አብርሃም ይገልፃሉ። በተለይ ለዕፀ መድኃኒት መቀመሚያ የሚውሉ የምንጭ "ጠበል" ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ የሚፈሱ እና በሩፋኤል እለት ጿጉሜ ሶስት ቀን የሚቀዱ "ጠበሎች በጠጅና በማር ተለውሰው፣ የቃለ እግዚአብሔር ስም ተደግሞባቸው፤ ለመንፈስ ጭንቀት፣ ልቡን ለሚስትና ሃሳቡን ለሚረሳ በጥብጠው ቢረጩት እና ቢያጠጡ" ጭንቀቱን ይፈወሳል፣ "የልቡ ብርሃን" ይመለሳል፣ የተደገመበትን ይፈታል፣ "ዓይነ ጥላን"

ያርቃል፣ ድግምትን ያፈርሳል፣ እድልን ያቃናል፤ ተስፋን ያለመልማል፣ "ከመቅሰፍት" ይሰውራል፣ አካልና መንፈስን በቅድስና ይባርካል፤ "የረከሰውን" ማንነት በቅድስና፣ የወደቀውን ስብዕና በንስሃ ያድሳል፤ የደከመውን ሥጋ "በፀጋ" ለማበርታት፤ ከገቢርና ከሥርዓት የወጣን ጠባይ ለማስተካከል፤ ወደ ምሥራቅ ከሚፈስ "ጠበል" መጠጣትና መጠመቅ "ስሙርና ፍቱን" እንደሆነ ይታመናል (ቃ.መ፤05/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

መሪጌታ ሠረቀብርሃን፤ "የዘወትር ፀሎተ እና የዕፅ አንግስ ድግምት" ለማቅረብና ለማድረስ ምሥራቅ አቅጣጫ ይመረጣል፤ ይላሉ፡፡ ለምን? ሲባል ምሥራቅ[95] የተስፋ ስንቅ መቋጠሪያ፣ የብርሃን መውጫ፣ የሕይወት መጀመሪያ፣ የመታደስ፣ የዳግም ትንሳኤ እና የእየሱስ ክርስቶስን መምጫ በማሰብ እንደሚከወን፤ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት)፡፡ በአጠቃላይ የባህል መድኃኒት ሥርዓተ ገቢርን በማስተካከል፣ በማስታረቅና በማስተግበር ረገድ ቁጥርና አቅጫዎች ጉልህ ሚና፣ ተግባርና ይዘት እንዳላቸው፤ መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 7.3 የባህል መድኃኒት ቅመማ ይዘት እና ቅድመ ተግባራት

**የግብዓቶችን ዓይነት እና ባሕርያት መለየት፡-** በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን[96] በዋናነት ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚያገኙ ሲሆን ጥቂቱን ደግሞ ከነፍሳት ዓይነቶች እንደሚያዘጋጁ ጠቁመው፤ ከዕፀ መድኃኒት ቅመማ በፊት የዕፅዋትን ዓይነት፣ ባሕርይና ጣዕም መለየት ቅድመ ተግባር መሆኑን መሪጌታ

---

[95]ከነዚህም መካከል አዲስ ቤት "ሲተለም"ና ሲሰራ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ፤ "በሩ በፀሐይ መውጫ"፣ መስኮቱ ደግሞ በምዕራብ አቅጣጫ ይሰራል፤ "መተኛ" አልጋ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ይዘረጋል፤ የአስክሬን ማረፉያ ጉድጓድ ሲቆፈር ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ይደረጋል፤ አስክሬን ተገንዞ ሲቀበር "ትራሱን" ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ በማሳረፍ የቀብር ሥርዓት እንደሚፈፀም አስረድተዋል፡፡ በዚህ ተግባርና ሂደት ውስጥ ምን ዓይነት አንድምታ፣ ትዕምርትና እሳቤ አለ? ሲባል፤ የንጋት፣ የብርሃን፣ የተስፋ፣ የዳግም ትንሳኤ መንገድና መምጫ ምሥራቅ እንደሆነ ይታመናል፤ የአስክሬን ማረፊያና ትራስ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ መደረጉ፤ "በዳግም ትንሳኤ" በምሥራቅ አቅጣጫ ለመነሳት፣ ተስፋና ብርሃን ለማየት፣ ዳግም ትንሳኤን ለማብሰር ሲባል እንደሚከወን፤ መክረዋል (ቃ.መ፤19-21/06/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል ቡድን ሶስት)፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ምዕራብ፤ የአንድ ነገር ተግባርና ድርጊት፤ ማብቂያ፣ ማሳረጊያ፣ መቋጫና መሰናበቻ፤ የፀሐይ መጥለቂያ፣ "የዕልመት" ቦታ፣ የተስፋ እና የሕይወት ፍጻሜ፤ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ምሥራቅ ለፀሎት፣ ለምስጋና፣ ለተስፋና ለሠናይ ተግባር፤ ምዕራብ ደግሞ "ለዕልመት እና ለዕኩይ" ምግባር ይገለጻል፤ ይታሰባል፡፡ ይህን ተግባርና እሳቤ በመፍራት ፀሎት ሲደረግ፣ የቤት በር ሲሰራ፣ መኝታ፣ አስክሬን ሲቀበር አቅጣጫን አስቦና ጠብቆ እንደሚከወን አስረድተዋል (ከተቡው አባላት አቶ ውለታው፣ ቃ.መ፤19/06/2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት)፡፡

[96]ለባህል መድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ ግብዓቶች፤ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት ውጤቶች ተሰብስበው እንደሚዘጋጁ፤ በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት (ንዑስ ርዕስ 2.1.8) የቀረቡ ጽንሰ ሃሳቦችን ልብ ይሏል፡፡

ብሩህ እና ደብተራ ጥላሁን ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 18/06/2011 ፋርጣ እና 03/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

የዕፀ መድኃኒት ግብዓቶች የሚገኙበትን ሥነ ምህዳር (የዐየር ንብረትና መገኛ ቦታን)፣ ለመድኃኒት ግብዓት የሚደርሱበትን ወቅት፣ ዕድሜ፣ የዕድገት ደረጃ፣ የግብዓቶቹን ባሕርያት እና የመድኃኒት ክፍል ለይተው እና አጥንተው የባህል መድኃኒት እንደሚያዘጋጁ ደብተራ መኀሪ ገልፀዋል። የመድኃኒት ልየታ፣ አዘገጃጀት፣ ቅመማ እና አሰጣጥ ሂደት የመድኃኒት ግብዓቶችን ጣዕም እና ባሕርያትን መነሻ በማድረግ እንደሚከወን ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 27/01/2011 ሊቦ ከምከም)። የባህል መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች፣ የመድኃኒት ክፍል እና ባሕርያት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 7.3.1. የዕፅዋት ግብዓት ባሕርያት

አቶ ጌጡ እና ሊቀጠበብት አብርሃም (ቃ.መ፤ 24/01/2011 ፋርጣ እና 30/01/2011 ሊቦ ከምከም)፤ በባህል ሕክምና ዕውቀትና ክዋኔ ሂደት፤ ለባህል መድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ይዘት፣ ዓይነት፣ ጣዕም እና ባሕርይ መለየት የመጀመሪያው ተግባርና ሙያ እንደሆነ ጠቁመዋል። ከዕፅዋት ግብዓት የምግብ ሰብሎች፣ የዛፍ፣ የቁጥቋጦ፣ የአትክልት (ሥራ ሥር እና ፍራፍሬ)፣ የሃረግ፣ የሣር እና የአረም ዓይነቶችን በመለየት ዕፀ መድኃኒት አዘጋጅተው እንደሚሰጡ ገልፀዋል። ከነዚህ ይዘቶች መካከል፤ ቅጠል፣ ቀንበጥ፣ አበባ፣ ፍሬ፣ ሥር፣ ግንድ፣ ተቀፅላ፣ ተገድራ፣ ሙጫ፣ ልጣጭ፣ ቅርፊት፣ ሽበት እና መሰል ይዘቶችን ለቅመው፣ ቆርጠው፣ ነቅለው እና ሰብስበው፤ የዕፅዋትን ጣዕምና ባሕርያት ለይተው የቅመማ ሂደቱን እንደሚከውኑ አስረድተዋል። በባህል ሕክምና ዕውቀት መሰረታዊ የዕፅዋት ጣዕም ዓይነቶች በስንት ይመደባሉ? ሲባል እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል።

በባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ሥርዓትና ተግባር የዕፅዋት ተፈጥሯዊ ጣዕምና መዓዛን ለመለየት በምላስ መቅመስን፣ በአፍንጫ ማሽተትን፣ በዓይን ማየትን እና በዕጅ መዳሰስን እንደሚጠይቅ መሪጌታ መኀሪ ገልፀዋል። ዐበይት የሚባሉ የዕፅዋት ጣዕም[97] ይዘቶች፤ መራራ (እሬት፣ ጌሾ፣ ግራዋ፣ ወይራ)፣ ጣፋጭ (የሾላ ፍሬ፣ የማንጎ ፍሬ፣ ሸንኮራ፣ ሙዝ)፣ አቃጣይ/ ኮምጣጣ/ ጨዋማ (በርበሬ፣ ኮሽም፣ እምቧጮ፣ ዝንጅብል) እና ዉኃማ/ ለስላሳ (ጎመን፣ "ወፍ አንቁር"፣ "ዉኃ አክርም"፣ ድንች) በመባል እንደሚመደቡ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 27/01/2011 ሊቦ

[97]የዕፅዋት ተፈጥሯዊ ጣዕምና መዓዛ በአራት መሰረታዊ ምድብ የተከፈሉ ቢሆንም፤ ጎልቶ በሚታይ ዝርያቸው፣ ጣዕማቸውና ባሕርያቸው የተመደቡ እንጂ፤ ከነዚህ የተለየ ጣዕም የለም ማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል።

ከምከም)። ይህን ታሳቢ በማድረግ፤ መሰረታዊ የዕፅዋት ጣዕም ዓይነቶች ይዘት ምደባ ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ምስል 15፡- መሰረታዊ የዕፅዋት ጣዕም ዓይነቶች ይዘት ምደባ




ሀ) መሰረታዊ የዕፅዋት ጣዕም ምድብ ለ) የዕፅዋት ጣዕምን በተለየ ሁኔታ አካቶ የሚገኝ ዕፀ

ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች ምድብ፤ በጥናቱ አቅራቢ ተዘጋጅቶ የቀረበ፤ መስከረም 2012 ዓ.ም

ደብተራ ጥላሁን ደግሞ፤ አንዳንድ ዕፅዋት መሰረታዊ የሚባሉ የዕፅዋት ጣዕም ዓይነቶች በአንድ ዕፅ ቅጠል፣ ፍሬ፣ ሥር፣ ግንድ፣ ልጣጭ/ቆዳ እና መሰል ይዘት ላይ በተለያየ ጣዕም እና ይዘት አካተው እንደሚገኙ ጠቁመዋል። ለምሳሌ፡-ፓፓዬ በቅጠሉ እና በሥሩ መራራ፣ በሚበላው ፍሬ ጣፋጭ፣ በዘር ፍሬው መራራና አቃጣይ፣ በወተቱ ለስላሳና መራራ፣ በፍሬው ዉኃ ጣፍጭና ለስላሳ፣ በግንዱ ዉኃ መራራና ለስላሳ ጣዕምና ይዘትን በማስተናገድ የተለያየ ተግባር እንዳለው፤ ገልፀዋል። በዚህ ባሕርይው የተለያየ ተግባር፣ ጣዕም፣ ሚና እና ይዘት እንዳለው፤ መክረዋል (ቃ.መ፤ 03/03/2011 ሊቦ ከምከም)።

የፓፓዬ ዕፅ በባህል ሕክምና አገልግሎት፣ ዕውቀትና ተግባር ሂደት ግንባር ቀደም ከሚባሉ የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች ውስጥ እንደሚመደብ መሪጌታ መጎሪ ጠቁመዋል። የፓፓዬ ቅጠል

ለወባ ሕመም፣ ወተቱ ለችፌ፣ የዘር ፍሬው ለሆድ ውስጥ ጥገኛ ትላትል፣ የሚበላው ፍሬና ቆዳ ለውስጥና ለውጭ አካል ቁስል መድኃኒት በመሆን የተለያዩ የበሽታ ዓይነቶችን እንደሚፈውስ፤ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 27/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

ደብተራ መልኩ ደግሞ፤ የዕፅዋት ጣዕም እና ይዘት፤ የዕፅዋትን ባሕርይ ምድብ፣ ተግባር፣ የቅመማ ሂደት፣ የመድኃኒት አሰጣጥና ምጣኔን ልክ እንደሚወስን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንጻር፤ የዕፅዋትን ባሕርይ፣ ምድብና ይዘት ለመለየት የዕፅዋትን ጣዕም መነሻ በማድረግ ምደባ እንደሚያካሂዱ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ)፡፡ በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል ትግበራ፤ የባህል ሐኪሞች ምን ዓይነት ጣዕም የአላቸውን ዕፅዋት በየትኛው የተፈጥሮ ባሕርይ ምድብ ይዘት ውስጥ ይገልፃሉ? ለምን? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ቀርቧል፡፡

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የዕፅዋትን ባሕርያት ሲመድቡ፣ ሲለዩና ሲያደራጁ፤ የማቃጠል፣ የመምረር፣ የመለብለብ፣ የማንገብገብ፣ የማተኮስ፣ የመኮምጠጥ፣ የማስነጠስ፣ የማስለፍለፍ፣ "የማንገሽገሽ" እና መሰል ይዘት የአላቸውን የዕፅዋት ዓይነቶች በእሳት ባሕርይ ምድብ፤ የቅባት፣ "የማላጠቅ"፣ የማጣበቅ፣ "የማሙለጭለጭ"፣ የመለስለስ፣ የመስፋፋት፣ "የማረስረስ" እና መሰል ይዘት የአላቸውን ዕፅዋት በነፋስ ባሕርይ፤ ዉኃን የማዘል፣ የማቆር፣ የመሰብሰብ፣ የመለስለስ እና ጣፍጭ ይዘት የአላቸው ዕፅዋት በዉኃ ባሕርይ፤ ክብደት በመጨመር፣ በማወፈር፣ ሥጋን በማደለብ ሰውነትና አካልን የሚገነቡ ዕፅዋትን በመሬት ባሕርይ ምድብ ማሕቀፍ ውስጥ እንደሚካተቱ አስረድተዋል (ሊቀጠበብት አብርሃም፣ መሪጌታ ስዩም እና አቶ ጌጡ፣ ቃ.መ፤ 05/03/2011 ሊቦ ከምከም፤ 04/02/2011 እብናት እና 20/06/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)፡፡ ከዚህ አንፃር፤ የዕፅዋት ባሕርያት ምድብ ማሕቀፍ፤ በምግብ ሰብሎች ማሳያነት ይዘት በምስል 16 እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

ምስለ 16-፡- የዕፅዋት ባሕርያት ምድብ ማሕቀፍ በምግብ ሰብሎች ማሳያነት




ምንጭ፡-የባህል ሐኪሞች፤ በጥናቱ አቅራቢ ተዘጋጅቶ የቀረበ ምስለ መዋቅር፤ ጥቅምት/2012፤

ከዚህ በላይ የቀረቡ የዕፅዋት ባሕርያት ምድብ ማሕቀፍ[98] በምግብ ሰብሎች ማሳያነት፤ የዕፅዋትን ባሕርያት ለማመላከት ተሞክሯል፡፡ በንፋስ ባሕርይ ምድብ የቅባት ሰብሎች (ኑግ፣ ተልባ፣ ለውዝ፣ ሰሊጥ፣ ሱፍ)፤ በእሳት ባሕርይ የቅመማ ቅመም ዓይነቶች (ድንብላል፣ ጥቁር አዝሙድ፣ ዝንጅብል፣ ኮረሪማ፣ ቅርንፉድ፣ ኮሰረት)፤ በዉኃ ባሕርይ ምድብ፤ የአትክልት፣ የሥራ ሥር እና

[98]በዕፅዋት ባሕርይ ምድብ ማሕቀፍ የቀረቡ ይዘቶች ጎልተው በታዩበት ዝርያ፣ ዓይነትና ባሕርይ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከመደበኛ ዝርያ እና ዓይነታቸው በተለየ ጣዕምና ባሕርይ ያላቸው የዕፅዋት ዓይነቶች እንዳሉ፤ በባህል ሕክምና ባለሙያዎች ይታሰባል፡፡ ይህ እሳቤ፤ በእንስሳት፣ በነፍሳትና በመዓድናት ይዘቶች ላይም ይሰራል፡፡ ለዓብነት ያህል፡- የጫቅማ ፍሬ [የጉሎ ፍሬ]- አቃጣይ/መራራ፤ ነጭ ሽንኩርት እና የወርቅ በሜዳ ሥር [የዕፅ መጠሪያ ስም ሲሆን፤ ከሣር ወገን ሚመደብ እንደ ካሮት በሥሩ የሚያድግ ለብላቢና አቃጣይ ባሕርይ ያለው ዕፅ ነው] ለብላቢና ሰርሳሪ፤… ከመደበኛ ይዘታቸው በተለየ ጣዕም እንዳላቸው፤ ይታሰባል፡፡ የምደባ ሂደቱ ዋና ዋና ተግባራትን መሰረት በማድረግ የቀረበ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

የፍራፍሬ ዕፅዋት (ጎመን፣ ካሮት፣ ድንች፣ ቀይ ሥር፣ ሙዝ፣ ብርቱካን)፤ በመሬት ባሕርይ ምድብ ይዘት ደግሞ የጥራ ጥሬ፣ የብዕር እና የአገዳ እህሎች (ባቄላ፣ አተር፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ ማሽላ፣ በቆሎ) እንደሚካተቱ፤ ይገልጻል። እነዚህ ባሕርያት ከተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል እይታ አንፃር እንዴት ይተገበራሉ? ምን ዓይነት ባሕርይ ያላቸው ዕፅዋት ለሕመም መንስኤና ፈውስ ይሆናሉ?

በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል ዕይታና ትግበራ፤ የዉኃና የመሬት ባሕርይ ያላቸው ዕፅዋት ጣፍጭ እና ዉኃማ ይዘትን በመሸከም ለምግብና መጠጥ አገልግሎት በመዋል ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ። እነዚህ ግብዓቶች ለአጋንንት መራቢያ፣ መገኛ፣ መኖሪያና መነሻ በመሆን የበሽታ መንስኤ እንደሚሆኑ ይታሰባል። በአንጻሩ የእሳትና የነፋስ ባሕርይ ያላቸው ዕፅዋት አቃጣይ፣ መራራ፣ ጎምዛዛ፣ ኮምጣጣ በመሆን የማጣፈጥና የማዋሃድ ሚና አላቸው፤ የቅባት ይዘት ያላቸው ደግሞ የዘይት ባሕርይን በመውረስ የማርጠብ፣ የማራስ፣ የማለስለስ ተግባር እንዳላቸው ይታመናል። እነዚህ ዕፅዋት፤ ለምግብና መጠጥ በአነስተኛ መጠን የሚወሰዱ ሲሆን በብዛት ለመድኃኒት አገልግሎት እንደሚውሉ፤ ሊቀጠበብት አብርሃም እና መሪጌታ ዘላለም ገልፀዋል (ቃ.መ፤05/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 20/04/2011 ፋርጣ)። በዚህ እሳቤ ሰውነትን ለሚያቃጥሉ እና ለሚያንገበግቡ የሕመም ዓይነቶች አካልን የሚያቀዘቅዙ እና የሚያረጋጉ፤ ጉልበትን ለሚያዝሉ እና ጥንካሬን ለሚያሳጡ የሕመም ዓይነቶች፤ አካልን የሚገነቡ፣ የሚያጠነክሩ እና የሚያደረጁ የዕፀ መድኃኒት ግብዓቶችን ለይተውና አዘጋጅተው እንደሚሰጡ፤ ከባህል ሐኪሞች መገንዘብ ተችሏል (ምዕራፍ ሰባት፤ የምርመራ ሂደትና የተቃርኖ ሕክምና ይዘትን ልብ ይሏል)።

በአጠቃላይ በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች፤ ለባህል መድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ጣዕም፣ መዓዛና ይዘት መርምረውና አጢነው፤ የዕፅዋትን ባሕርይ ፈትሸው የባህል ሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ፤ መገንዘብ ተችሏል። እነዚህ ዕፅዋት ምን ዓይነት ተግባር፣ ጠቀሜታ እና ይዘት እንዳላቸው ባሕርያቸውን ፈትሸው፤ የበሽታውን መንስኤ፣ ዓይነት፣ ባሕርይና ይዘት ተገንዝበው፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዐውድን ለይተው፤ የፈውስ አማራጭ መሆን/አለመሆናቸውን መርምረው፤ የሕክምና ሥርዓቱን እንደሚከውኑ የመስክ መረጃዎች አመላክተዋል።

### 7.3.2 የእንስሳት እና የነፍሳት ግብዓት ባሕርያት

ለባህል መድኃኒት ቅመማ አገልግሎት የሚውሉ የእንስሳት ግብዓት ዓይነቶች ሣር በል፣ ሥጋ በል፣ ሣርና ሥጋ በል፣ ጥንብ አንሳ እንስሳትን ይመለከታል። ከእነዚህ እንስሳት ሥጋ፣ ደም፣ ሞራ፣ ወተት፣ ፀጉር፣ ቀንድ፣ ጥፍር እና መሰል ግብዓቶችን በመውሰድ መድኃኒት አዘጋጅተው እንደሚጠቀሙ አቶ ደሴ እና ደብተራ መኀሪ ገልፀዋል። ከእንስሳት የሚሰበሰበው የመድኃኒት ግብዓት ዓይነት የእንስሳትን የምግብ ምርጫ እና ባሕርይን መነሻ በማድረግ እንደሚከወን ጠቁመዋል (ቃ.መ፤23/04/2011 እና 13/03/2011 ሊቦ ከምከም እና እብናት በቅደም ተከተል)። በተመሳሳይ መልኩ በየብስና በውኃ የሚኖሩ እንስሳትና ነፍሳትን ከተለያዩ የሥነ ምህዳር መዳረሻ ቦታዎች ሰብስበው የባህል መድኃኒት አዘጋጅተው እንደሚሰጡ መሪጌታ መኀሪ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 28/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

አቶ ሞላ ደግሞ፤ ከእንስሳት የሚገኙ ግብዓቶችን ባሕርያት ለመለየት የእንስሳትን የምግብ ምርጫ እና ዝርያን መሰረት እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል። ከዚህ አንፃር፤ ሣር በል የሆኑ እንስሳት በዝርያቸው የቀንድና የጋማ እንስሳት ቢሆኑም፤ በመድኃኒት መረጣና ቅመማ ሂደት ላይ ልዩነት እንዳላቸው ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 22/06/2011 ፋርጣ)። ከተቡው አባላት መካከል አቶ ውለታው፤ ሣር ተመጋቢ ሆነው፤ ሳያደቁ የሚውጡ፣ በምራቃቸው አርሰው የሚከቱ፣ "የሚያመሰኩ" (የሚያመነዥጉ)፣ ገደብ ያላቸውና የሚጠግቡ፣ የእግር "ሸኾናቸው" ክፍት የሆኑ፣ ከላይኛው የፊት ድዳቸው ጥርስ የሌላቸው፤ "የዳልጋ እና የቀንድ ከብቶች ቅዱስ ናቸው" ተብሎ በማኅበረሰቡ ይታመናል። በዚሁ ትይዩ እና ገቢር፤ ሣር ተመጋቢ ቢሆኑም፤ አድቀውና አጣርተው የሚመገቡ፣ የማያመነዥጉ፣ ሲበሉ የሚውሉና የሚያድሩ፣ "እንብርት" አልባ እና የማይጠግቡ የጋማ እንስሳት ደግሞ በገቢራቸው "እርኩስ ናቸው" ይባላል። በዚህ አግባብ "ቅዱስ" የሚሏቸውን እንስሳት ለምግብ አገልግሎት በማዋልና በማቅረብ፤ "እርኩስ" የሚሏቸውን ደግሞ ከምግብ ይዘት በማስወጣትና በማራቅ ለማኅበራዊ ጉዳይ መከወኛ እንደሚጠቀሟቸው፤ አስረድተዋል (ቃ.መ፤19/06/2011 ፋርጣ ቡድን ሶስት)።

በዚህ እሳቤ፤ ሣር፣ ሥጋ፣ ጥንብ አንሳ፣ ሳርና ሥጋ በል የሆኑ እንስሳትን ባሕርይና ዝርያ በመለየት፤ ከሰውነት አካላቸው የትኛው ይዘት ለመድኃኒት ግብዓት እንደሚውል ምርጫ ይካሄዳል። ይህን ታሳቢ በማድረግ መሪጌታ ፍሬስብሃት እና ደብተራ መልኩ ከእንስሳት፤ የበግ ላት ሞራ፣ የዓሣ ቋንጣ፣ የከብት ቅልጥም፣ የግመል እና የአህያ ወተትና ፋንድያ፣ የእስስት እና

የለሊት ወፍ ሥጋ፣ የፈረስ ሸኾና፣ የፍየል ወተት እና ሥጋ፣ "የእማምሳይ ላም ቅቤ" [በቆዳ ቀለማቸው ተመሳሳይ የሆኑ ላም እና ጥጃ]፤ የጅብ ቆዳ፣ የጥቁር ሙጨጭላ ቆዳ፤ የዘንዶ ቆዳና ሞራ፤ የሸኮኮ፣ የቆቅ እና የሶረኔ ሥጋ እና መሰል ግብዓቶችን ለይተው፣ አዘጋጅተው እና ቀምመው ለመድኃኒት ግብዓት እንደሚጠቀሙ፤ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦከምከም እና 23/01/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)፡፡

ከነዚህ መረጃዎች በተጨማሪ በውኃና በየብስ የሚገኙ በራሪና ተሳቢ፤ ተናዳፊና ደም መጣጭ፣ መርዛማና መርዝ አልባ ነፍሳትን ከመስክ ሰብስበው፤ የመድኃኒት ግብዓት ዓይነቶችን አዘጋጅተው እንደሚሰጡ ደብተራ በረከት ገልፀዋል፡፡ "ለቁመኛ" (በቁሙ ለሚከሳ ሕጻን) የሸኮኮ ሥጋ ማብላትና እና መረቁን ማጠጣት፤ የዓሣ መረቅና ቋንጣ ማብላት፤ አጋንንት ለማስወጣት በጅብ ቆዳ ላይ አስቀምጦ ማናገር፤ ዐበይት ተግባራት እንደሆኑ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት)፡፡ በአጠቃላይ ከእንስሳት እና ከነፍሳት የሚገኙ የመድኃኒት ግብዓት ዓይነቶችን ይዘት እና ገቢር ለይተው፤ የእንስሳት እና የነፍሳትን ባሕርይ ተገንዝበው፤ የሕመሙን ዓይነት አጥንተው ለፈውስ የሚያገለግሉ መድኃኒቶችን ከተለያዩ የሥነ ምህዳር ቦታዎች ሰብስበው፣ ቀምመው እና መጥነው እንደሚሰጡ፤ የመስክ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡

### 7.3.3 የማዕድናት ግብዓት ባሕርያት

ለባህል መድኃኒት ቅመማ ከሚያገለግሉ ይዘቶች መካከል ማዕድናት[99] ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው፤ ደብተራ መልኩ እና ሊቀጠበብት አብርሃም ጠቁመዋል፡፡ ከነዚህ ግብዓቶች መካከል፤ ፀበል፣ ጨው፣ ዲኚ፣ የድንጋይ ሽበት፣ ብር፣ መዳብ፣ ጥቁር ዐፈር፣ ወርቅ፣ የምስጥ ኩይሳ፣ ቀይ እና ነጭ መሰል የድንጋይ ዓይነቶችን ሰብስበው፤ መድኃኒት ቀምመው እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡ ማዕድናት በዓይነት፣ በቀለም፣ በገቢር እና በባሕርይ የተለያየ ሙያ እና ተግባር እንዳላቸው በባህል ሕክምና ባለሙያዎች ይታሰባል፡፡ የማዕድናትን ኃይል፣ ተግባርና ባሕርይ ለማወቅ፤ በመቅመስ፣ በማሽተት፣ በማየት እና በመንካት እንደሚለዩ አስረድተው፤ ማዕድናት ጣፍጭ፣ መራራ፣ አቃጣይና አብራጅ ባሕርያትን አካተው እንደያዙ መክረዋል (ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ እና 30/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

---

[99] የደቡብ ጎንደር ዞን መልክዓ ምድር ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ የሚባሉ የሥነ ምህዳር ዓይነቶችን በማካተት የተፈጥሮ ፀበል፣ ፍል ውኃ እና "የማዕድን አምቦ ጠበል" ማዕድናት በብዛት እንደሚገኙ፤ በአካባቢው "የተፈጥሮ ሕክምና ቱሪዝም" (Natural Medical Tourism) እንደሚካሄድ፤ በምዕራፍ አራት የደቡብ ጎንደር ዞን መልክዓ ምድራዊና ማኅበረ-ባህላዊ ዳራ በሚል ይዘት የቀረበውን ርዕሰ ጉዳይ ልብ ይሏል፡፡

የድንጋይ፣ የብረት፣ የብር፣ የዐፈር እና የፀበል ዓይነቶችን ባሕርያት ለይቶ፣ መገኛ ቦታቸውን አጥንቶ "በገቢራቸው ልክ መጥኖ ማዘጋጀትና መስጠት"፤ አጋንንትን ለመከላከል፣ ለማስወጣት፣ ለመፈወስ፤ ለመፍትሔ ሥራይ፣ ለእጀ ሰብ፣ ድግምት ለመጣልና ለመፍታት፣ ለቆዳ ቁስል፣ ለራስ ምታት እና ለሆድ ሕመም፤ "ፍቱን" መድኃኒት እንደሆኑ አቶ ጌጡ ጠቁመው፤ ከዕፅዋት እኩል ተግባርና ጠቀሜታ እንዳላቸው ገልፀዋል (24/01/2011 ፋርጣ)።

መሪጌታ ፍሬስብሃት ደግሞ፤ ማዕድናት በቀለም፣ በጣዕም እና በባሕርይ እንደሚለያዩ ጠቁመው፤ አገልግሎትና ተግባራቸው እንደ ጣዕምና ባሕርያቸው የተለያየ ሚና እንዳላቸው መክረዋል። ይህን ርዕሰ ጉዳይ ሲያስረዱ፤ "የወንዝ ሙዳይ የሚባል ድንጋይ፤ ቅርጹ ጠፍጣፋ፣ መልኩ ሰማያዊና ነጣ ያለ አሞሌ ጨው ይመስላል" ይላሉ። ይህ "ድንጋይ" የደፈረሰ ዉኃን የሚያጠራ፣ የዉኃውን ጣዕም የሚቀይር፣ ከአለት ድንጋይ በሚፈልቅ ፀበል፤ በወራጅ ወንዝና በምንጭ ቦታዎች አልፎ አልፎ እንደሚገኝ፤ ገልፀዋል። "ይህን ድንጋይ፤ በእንስራ ዉኃ ውስጥ ቢከቱት፤ የቆሸሸ ዉኃን ያጠራል፣ ሲጠጡት ጣዕሙ ለምላስ ይከብዳል/ይመራል፤ በሆድ ውስጥ የአለውን ደዌ እና ነፍሳት በተቅማጥና በትውከት ጠራርጎ ያስወጣል፣ ለመድኃኒት መቀመሚያ እና መጋቻ[መስጫ፤ በጥብጦ ማጠጫ] ይጠቅማል" በማለት የሚሰጠውን ጥቅምና ተግባር አስረድተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ለረጅም ጊዜ ተቀምመው የሚቀመጡ መድኃኒቶች ጣዕማቸውን እንዳያጡና ኃይላቸውን እንዳይቀንሱ "የወንዝ ሙዳይ ድንጋይ" በተነከረበት ዉኃ (ፀበል) ተቀምመው፤ መቀመጥ እንዳላቸው መክረዋል (ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም)።

ደብተራ መኀሪ እና ሊቀጠበብት አብርሃም ደግሞ፤ ማዕድናት የዕፅዋት ዝርያና ጣዕም በማብዛትና በመለየት፤ የእንስሳትን ሥጋና ወተት[100] ጣዕም በመለወጥ፤ የዉኃን ቃና፣ ለዛና መዓዛ በመቀየር፤ ኃይልና ጉልበት በመጨመርና በመቀነስ፤ አካላዊ አቋማቸውን በማሳደግና በማሳነስ፤ የለዋጭነት ኃይል እንዳላቸው፤ ይመክራሉ (ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ እና 05/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

---

[100]አቶ ጌጡ፤ በደጋና በቆላ የሚገኝ ወተትና ቅቤ ዘርና መልኩ አንድ ዓይነት ቢሆንም፤ በጣዕሙ እንደሚለያይ፤ ገልፀዋል። የደጋ ወተት እና ቅቤ በቅባትና በጣዕሙ ከቆላው የተለየና የተሻለ እንደሆነ መክረዋል። ለምን? ሲባል የደጋ ዐፈር የአበቀለው ሣር እና ዉኃ ከቆላ ቦታ የተለየ እንደሆነ፤ አስረድተዋል። ለመድኃኒት ቅመማና መስጫ የደጋ ቅቤና ወተት ተመራጭ እንደሆነ ጠቁመዋል። ከዚህም በተጨማሪ የማዕድናት መገኛ ቦታዎች በፀበል፣ በወንዝ፣ በገደልና በዋሻ አካባቢ ሲሆን ነፍሳት የሰፈሩባቸው ድንጋዮች፤ የጨው ጣዕም የአላቸው፤ በፍየልና በከብት የሚላሱና የሚቀመሱ ማዕድናትን ሰብስቦ ለአካል ቁስል በጥብጠው ቢቀቡት፤ ለሆድ ሕመም ቢጠጡት፤ ገላን ቢታጠቡበት መልካም እንደሆነ ይታሰባል (ቃ.መ፤ 24/01/2011 ፋርጣ)።

በተመሳሳይ መልኩ አቶ ጌጡ፤ ዕፅዋት አንድ ዓይነት መልክ እና ዝርያ ቢኖራቸውም የሚያበቅላቸው ዐፈርና ዉኃ የመድኃኒት ኃይልና ይዘታቸው እንደሚለያይ ጠቁመዋል፡፡ ለምን? ሲባል፤ "የተመገቡት ዐፈር እና የጠጡት ዉኃ ሲለያይ፤ በደጋ እና በቆላ በቅለው ሲገኙ" ጣዕማቸው የተለያየ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ለአብነት ያህል፤- "ዕፀ ፋሪስ ሶስት ዓይነት ዝርያ አለው" ይላሉ፡፡ በደጋ አካባቢ በቅሎ የሚገኘው "ዕፀ ፋሪስ አገዳው ወፍራም፤ ፍሬው ትልቅ፣ መልኩ ጥቁር፣ ቅጠሉ ሰፊ ሲሆን ለፎረፎርና ለቁስል መድኃኒት ይውላል"፡፡ በቆላ የምትገኘው ዕፀ ፋሪስ ደግሞ፤ "አገዳዋ ቀጭን፣ ፍሬዋ ደቃቃና ጤፍ የምታክል፣ መልኳ ነጭና ቀይ፣ ቅጠሏ ሹል፣ ለስላሳ እና ቀጭን" እንደሆነች አስረድተዋል፡፡ ገቢሯ፤ "አርባ ዘጠኝ ፍሬ ተቆጥራ፣ በኮመል ዕፅ ፈሳሽ እና በምስጥ ዐፈር ተድቦልቡላ፤ ሰባት ዓመት ላልሞላው ልጅ፤ በቀን አንድ ፍሬ እያዋጡ፤ ለሰባት ቀን መክስተ አእምሮን እየደገሙ ቢሰጡ፤ ልበ ብርሃን ታደርጋለች" ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያት አንድ ዓይነት ዘር እና ተፈጥሮ ቢኖራቸውም፤ የበቀሉበት ቦታና ማዕድን ሲለያይ ገቢራቸው አብሮ እንደሚለወጥ መክረዋል (ቃ.መ፤ 20/06/2011 ፋርጣ)፡፡ ፡፡

መሪጌታ ልሳነወርቅ ደግሞ፤ የፀበል ቦታዎች "የእግዚአብሔር መንፈስ አድሮባቸዋል፣ የቅዱሳን አባቶች ረድኤት፣ ምርቃትና ምስጋና አርፎባቸዋል" ተብሎ ስለሚታመን፤ አካላዊ ቁስል፣ የሆድ ሕመምን፣ የራስ ምታትን፣ የአጋንንት ዓይነቶችን የማስወጣትና የመፈወስ ኃይል እንዳላቸው፤ ገልፀዋል፡፡ በምርመራ ሂደት፤ መድኃኒት ቀምመው ለሕሙማን ሲሰጡ፤ የበሽታውን ዓይነት እና የታማሚውን ግለሰብ ባሕርይ አጥንተው፤ ኮከቡን ቆጥረው "ግጥሙና ግንባሩ ነው" የሚባለውን "ጠበል" ለይተው እንደሚያዙ ጠቁመው፤ "ሁሉም ጠበል አንድ ዓይነት ጣዕም እና ፈውስ የላቸውም" ይላሉ፡፡ ለምን? ሲባል በገቢራቸው፤ የአዕምሮ ጭንቀትን የሚፈውሱ፣ አጋንንትን የሚያባርሩ፣ የአካል ቁስልን የሚያረግፉ፣ የሆድ ትልን የሚያስወጡ እንዳሉ አትተው፤ በጣዕማቸው፣ በባሕርያቸውና "በቅድስናቸው ልክ" የተለያየ ተግባር እንዳላቸው መክረዋል (ቃ.መ፤ 27/04/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

መሪጌታ ስንታየሁ፤ የዐፈር እና የድንጋይ ማዕድናት፤ ተዓምር፣ ኃይልና ጉልበት "ተነግሮ አያልቅም፤ መሬት በሆዷ ብዙ ምስጢርና ጥበብ ተሸክማለች" ይላሉ፡፡ ለዓብነት ያህል፡- "እሳተ ከላ" የሚባል ድንጋይ መልኩ ጥቁር፣ እንደብረት ከባድ እና ቀዝቃዛ ሲሆን "እሱ በደረሰበት ቦታ እሳት ያጠፋል፤ ...በድንጋዩ ላይ የጤፍ ጭድ ቆልለህ እሳት ብትለኩስ አይነድም፤ እሳት ይከላል [ይከላከላል]" በማለት ገልፀዋል፡፡ በዚህ ባሕርይ እና ተግባሩ "እሳተ ከላ" እንደተባለ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 14/03/2011 እብናት)፡፡ አቶ ደሴ እና መሪጌታ ዘላለም፤ የብር ቀለበትና የማር ትሬዛ

ሳንቲም ዉኃ ውስጥ ጨምረው ዕፅዋትን ቢቀምሙ ዉኃን ያጠራል፤ ቁስል ቢያጥቡበት ቶሎ ያደርቃል፣ ብርና መዳብ የተነከረበትን ዉኃ "ከከረቤና ከነጭ" ዕጣን ጋር ደባልቀው በባዶ ሆድ ቢጠጡ "የሆድ ሥራይን ይፈታል"፤ ብር የተነከረበትን ውኃ ከአመድ፣ ከገል [የሸክላ] እና ከጥቁር ዐፈር ጋር ለውሰው ለማንኛውም የቆዳ ቁስል ቢጠቀሚቸው፤ መድኃኒት እንደሚሆኑ መክረዋል (ቃ.መ፤ 25/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 20/04/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

መሪጌታ አማረ ደግሞ፤ የማዕድናትን ይዘት፣ ተግባር፣ ቀለም እና የሚፈውሱትን የሕመም ዓይነት እንደሚከተለው አቅርበዋል (ቃ.መ፤ 26/01/2011 ሊቦ ከምከም)፡-

> በወንዝና በገደል የሚገኙ ቀይ፣ ነጭ እና አርጓዴ ቀለም ያላቸው ድንጋዮች፤ ለተለያዩ በሽታዎች መድኃኒት ናቸው። በገደልና በዋሻ የሚፈስ ዉኃ፤ በዚያ አካባቢ የሚገኘውን የድንጋይ ዓይነት [ማዕድን] ይጠቁማል። ደም የሚተፋ፣ የአህያ ሽንት የሚመስል፣ ጨው የመሰለ ቀለም የሚረጭ ድንጋይ አለ። በዚህ ቦታ የሚፈስ ዉኃን ቢቀምሱት ይመራል፤ ብረት ብረት እና ጨው ጨው ይላል። …ዉኃን የሚያጠራ፣ የሚያመር እና የሚያደርቅ ድንጋይ አለ። ለምሳሌ፡- ብሃ የሚባል ድንጋይ መልኩ ቡላ፤ ዓመቱን ሙሉ እርጥብና ዉኃ በማዥት ይለያል፤ ነፍሳት ይወሩታል። በክረምት ወቅት፤ የድንጋይ ሙጫ በመያዝ ወለላ የመሰለ ልጋግ ይተፋል። ሙጫው ቢጫ እና አርንጓዴ ከሆነ መርዛማ ነው፤ መድኃኒት አይሆንም፤ ሰማያዊ፣ ቀይና ነጭ ከሆነ ለቆዳ ቁስልና ለሆድ ደዌ በዉኃ በጥብጦ ቢጠጡት፣ ቁስሉን ቢቀቡ እና ቢያስሩበት ፈውስ ይሆናል። ለነቀርሳ፣ ለብጉንጅ እና ለእባጭ ቁስል ልጋጉን ቀብቶ ማዋልና ማሳደር፤ በማግስቱ መግልና ደሙን አፍሶ ሰንኮፉን አውጥቶ ዲኚ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቅርንፉድ፣ የጥድ ፍሬ ደባልቆና ሰልቆ፤ በጥቁር ማር ለውሶ በቀን ሁለት ጊዜ ቁስሉን እያጠቡ ቢቀቡት ቶሎ ይሽራል።

በማለት አስረድተዋል። ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ማዕድናት በዓይነት፣ በገቢር፣ በጣዕም እና በባሕርይ የተለያየ ሙያና ተግባር ቢኖራቸውም፤ ለመድኃኒት አገልግሎት የሚመረጡ ማዕድናት ምን ዓይነት ይዘት፣ ቀለምና ባሕርይ እንዳላቸው አጥንተው፤ የትኛውን የበሽታ ዓይነት እንደሚፈውሱ ለይተው፤ ተደጋጋሚ ተግባር፣ ልምድ እና ምልከታን መነሻ አድርገው የባህል ሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ፤ ከቀረበው ይዘት መገንዘብ ተችሏል። በአጠቃላይ የዕፅዋት፣ የማዕድናት፣ የእንስሳት እና የነፍሳት ግብዓት ዓይነቶች እንደ ዝርያቸው፣ ጣዕማቸው፣ ዓይነትና ባሕርያቸው፤ የተለያየ ተግባርና አገልግሎት እንዳላቸው፤ በባህል ሕክምና ባለሙያዎች ይታሰባል፤ ይታመናል።

## 7.4 የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት

የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት[101] በቅደም ተከተል የሚከወን፤ ደረጃ በደረጃ (Phase by Phase) የሚፈፀም፤ የቅመማ ስልትና ሥርዓትን ተከትሎ የሚቀርብ፤ የባህል ሐኪሙን ዕውቀት፣ ክህሎት እና ልምድን አቀናጅቶ የሚተገበር ሙያ እንደሆነ፤ ይታመናል፡፡ መሪጌታ ባሕረጥበብ እና አቶ ደርሶ፤ የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት አጭርና ረጅም ይዘት እንዳለው ጠቁመው፤ በዓይነት፣ በመልክ፣ በጣዕም፣ በቀለም፣ በገቢር የተለያየ ተግባር እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ የመድኃኒት ግብዓት መለያየት የቅመማ ዓይነት፣ ቅደም ተከተል፣ ሥርዓትና ተግባሩን እንደሚቀይረው፤ መክረዋል (ቃ.መ፤ 22/01/2011 ፋርጣ እና 03/02/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡

ሊቀጠበብት አብርሃም እና አቶ ሞገስ፤ የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት፤ ከማጠብ እስከ ማሸግ የሚደርሰውን ረጅም ተግባር እንደሚያካትት ገልፀው፤ በማጠብ፣ በማድረቅ፣ በመልቀም፣ በመከትከት፣ በመቀጥቀጥ፣ በመውቀጥ፣ በመንፋት፣ በመፍጨት፣ በመሰለቅ፣ በመዘፍዘፍ፣ በመቀቀል፣ በማንጠር እና መሰል ተግባራትን በመከወን፤ መድኃኒት ቀምመው እንደሚሰጡ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 05/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 22/06/2011 ፋርጣ)፡፡

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደታቸው ተመሳሳይ፣ ተወራራሽ እና ተቀራራቢ ይዘትና ተግባር እንዳለው የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ ለመድኃኒት የተመረጡ ግብዓቶች በዓይነትና በመልክ ተለይተው ሲዘጋጁ፣ ሲቀመሙ እና ሲታሸጉ፤ በዋናነት አምስት ዓይነት ደረጃና ሂደቶችን እንደሚያልፉ የባህል ሐኪሞች ገልፀዋል (መሪጌታ ፍሬ ስብሃት እና መሪጌታ ባሕረጥበብ፣ ቃ.መ፤ 29/01/2011 እና 22/01/2011 ፋርጣ)፡፡ ይህን ተግባር ታሳቢ በማድረግ፤ የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

[101] የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት በውስጡ ዝርዝርና ውስብስብ ተግባራት የሚፈፀሙበት ይዘት ቢሆንም፤ የቅመማ ሂደቱን ማሕቀፍ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ ይህ ተግባር በባህል ሐኪሙ ዕውቀት፤ በመልክዓ ምድር ሁነት፤ በዕፅዋት ዓይነት፣ በሕመም ባሕርይ እና በወቅቶች መፈራረቅ ክዋኔው ይለያያል፡፡ ለአንድ ሕመም የሚዘጋጀው እና የሚቀመመው የመድኃኒት ዓይነት እና ክዋኔ እንዲለያይ መንስኤ ይሆናል (አባሪ ስድስትን ልብ ይሏል)፡፡

ምስል 17፤ የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት ማሕቀፍ




ምንጭ፦ የባህል ሐኪሞች፤ በጥናት አቅራቢው የተዘጋጀ ማሕቀፍ፤ ጥቅምት 2012 ዓ.ም

ከዚህ በላይ የቀረበው ማሕቀፍ እንደሚያስረዳው፤ የባህል መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች እና ምንጭ ዕፅዋት[102]፣ እንስሳት፣ ማዕድናት እና ነፍሳት እንደሆኑ ተጠቁሟል። ከነዚህ ግብዓቶች

[102]ከባህል መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች መካከል፤ በአማካይ ከ90% በላይ የዕፅዋት ግብዓት ዓይነቶች፤ ለባህል መድኃኒት ምንጭና መሰረት እንደሆኑ ምሁራን (Wondwoson,1999: Fekadu,2001) እና በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች አስረድተዋል (ደብተራ መልኩ እና የተቡው አባላት፣ 01/03/2011 ፋርጣ እና 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ በቅደም ተከተል)። በዚህ ጥናት፤ ለባህል መድኃኒት ግብዓት ዐበይት "ምንጭና መሰረት ናቸው"፤ የሚባሉ "የዕፅዋት" ግብዓት ዓይነቶችን በመለየት፤ የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደትና ተግባርን ለማሳየትና ለመግለፅ ተችሏል። የእንስሳት፣ የማዕድናት እና የነፍሳት ግብዓቶች እንዴት ተዘጋጅተው፣ ተቀምመው፣ ተመጥነውና ታሽገው ይቀርባሉ? የክዋኔ ሂደታቸው ምን ይመስላል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ አይሰጥም።

የተሰበሰቡ የመድኃኒት ውጤቶች በዓይነትና በይዘት ተለይተው፤ የባህል መድኃኒት ቅመማ[103] ይከሄዳል፡፡ ይህ ተግባር፤ ከማጠብ እስከ ማሸግ በአለው ሂደት ውስጥ አምስት መሰረታዊ ደረጃዎችን እንደሚያልፉ ይታሰባል፡፡ ሂደቱን የደቡብ ጎንደር ዞን የባህል ሐኪሞች እንደሚከተለው አስረድተዋል፡-

በመጀመሪያ ደረጃ፡- የባህል መድኃኒት ግብዓት ምንጭ፣ ዓይነት፣ ይዘትና ባሕርይ ይለያል፡፡ በዚህ መሰረት ከዕፅዋት የተሰበሰቡ ግብዓቶች፤ ፍሬ፣ አበባ፣ የዕፅዋት ፈሳሽ/ "ልቡጫ" (ዕጣን)፣ ቅጠል፣ ቅርፊት፣ ግንድና ሥር በቅደም ተከተል ይዘጋጃሉ፡፡ የተዘጋጁት ግብዓቶች "አሞሌ ጨው በላሰና በነካው" ንጹህ ዉኃ ይዘፈዘፋሉ፡፡ "አሞሌ ጨው የነካው ዉኃ" ለምን አስፈለገ? ሲባል ዕፅዋት በቁማቸው ነፍሳት እና እንስሳት ይጠጓቸዋል፣ ይልሷቸዋል፣ ይበሏቸዋል፤ ቤት ሰርተው፣ እንቁላል ጥለው፣ መርዝ ተፍተው፤ "የተሸከሟቸውን አጋንንት አራግፈውባቸው ይሄዳሉ፤ አቧራ ተሸክመው ይኖራሉ" ተብሎ ስለሚታመን፤ "አሞሌ ጨው" [ለክብት የሚሰጥ ጨው] በተነከረበት፤ ንጹህ ዉኃ ተዘፍዝፈው ይታጠባሉ (አቶ ደሴ እና መሪጌታ ፋንታሁን፣ ቃ.መ፤ 25/01/2011 ሊቦ ከምከም እና 19/01/2011 ፋርጣ)፡፡

በዚህ ሂደት፤ አጋንንት "አሞሌ ጨው፣ ብረት እና ነጭ ሽንኩርት ባሉበት አካባቢ አይቀርቡም" በማለት መሪጌታ ባሕረጥበብ ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ሂደት የተሸከሙትን ቆሻሻ እና አቧራ በማራገፍ፣ በማስወገድና በማጣራት "ንጹህ ናቸው" ተብሎ ሲታመን፤ የያዙትን ዉኃ በማንጠፍጠፍ ወደ ማስጫ ቦታ ይወሰዳሉ (ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)፡፡ ከዚህ በታች ከመስክ የተሰበሰቡ የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች፣ አሞሌ ጨውና ካራን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

---

[103] ማሳሰቢያ፡- የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት እንደ ግብዓቱ ዓይነትና ተግባር አጭርና እረጅም ጊዜ የሚወስዱ ግብዓቶች እንዳሉ፤ ይታመናል፡፡ ለአብነት ያህል፤ በጭስ መልክ የሚዘጋጁ፤ የዕፅዋት ግብዓቶች ሥር፣ ቅጠልና ግንዳቸው ደርቆ፤ በአጭሩ ታጥበውና ደርቀው ለመድኃኒት ግብዓት ይውላሉ፡፡ ከነዚህ መካከል፤ ዕጣን፣ ፀመና፣ ወገርት፣ ጥንዡት፣ ቀበርቾ እና ወይራን፤ በማጨስና በማጠን ሕክምና ይሰጣሉ፡፡ ተበጥብጠው የሚጠጡ፣ በዱቄት መልክ የሚዘጋጁ፣ በመቀቀልና በማፍላት የሚነጠሩ የዕፅዋት ግብዓት ዓይነቶች፤ እርጅም ሂደትና ጊዜን ይወስዳሉ፤ ይታጠባሉ፣ ይደርቃሉ፣ ይለቀማሉ፣ ይጨቀጨቃሉ፣ ይወቀጣሉ፣ በድጋሚ ይደርቃሉ፣ ተመልሰው ይወቀጣሉ፣ ይነፋሉ (አሰርና ዱቄት ይለያል)፤ በፈላ ውኃ ላይ ተጨምረው ይንተከተካሉ፤ ይነጠራሉ፤ ተፈላጊውን ፈሳሽ በመለየትና በማጣራት በፈሳሽ መልክ ይዘጋጃሉ፡፡ ይህ ሂደት ልምድና ጥንቃቄን የሚፈልግ፣ እረጅም ጊዜ፣ ጉልበት፣ ወጪና ገንዘብ የሚጠይቅ ተግባር እንደሆነ ይታሰባል፡፡

ፎቶ ግራፍ 5፡- ከመስክ የተሰበሰቡ የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች፣ አሞሌ ጨውና ካራ





1ኛ. ከመስክ የተሰበሰቡ የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች፤ 2ኛ. አሞሌ ጨውና ካራ

ምንጭ፡- ከሊቦ ከምከም ወረዳ፤ በጥናቱ አቅራቢ በቀን 25/01/2011 ዓ.ም የተነሳ ፎቶ

በሁለተኛ ደረጃ፡- ለማስጫ በተዘጋጀ "የቆጥ መደብ" ላይ ከስር ሰሌንና ማዳበሪያ ተነጥፎ "ከተዘረሩና ከተሰጡ" በኋላ፤ ከላይ በንጹሕ ነጠላ ጨርቅ ይሸፈናሉ፡፡ በተሰጡበት መደብ ላይ በእኩል መጠን ከታችና ከላይ ነፋስ እያገኙ፤ በእንስሳት፣ በነፍሳት እና በሰው እንዳይረገጡና እንዳይቀመሱ፤ አቧራ እና መሰል ቆሻሻ እንዳይበክላቸው ልዩ ጥበቃና ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ሂደት፤ የያዙትን ውኃ አንጠፍጥፈው ሲጨርሱ፤ መምጠጥ እና መድረቅ ሲጀምሩ፤ ዕርጥበቱን በማስለቀቅና በማራገፍ የለቀማና የማጣራት ሂደት እንደሚጀመር ሊቀጠበብት አብርሃም ያስረዳሉ (ቃ.መ፤ 05/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

በሶስተኛ ደረጃ፡- "የለቀማና የማጣሪያ" ሂደት ሲከወን፤ ለመድኃኒት የሚፈለገው ግብዓት ተለይቶ፤ ዕንቡጥ እና ቀንበጥ ይቆረጣል፤ አበባ እና ፍሬ ይራገፋል፣ ይለቀማል፤ ቅጠል ይለመለማል፣ ይሸመጠጣል፤ የደረቀ ቅርፊት ይራገፋል፤ "ልጥ" ይወጣል፤ የዕፅዋት ግንድ ሽበት እና ፈሳሽ እዥ "ልቡጫ" እና እጣን ይላቀቃል፣ ይራገፋል፣ ይጣራል፤ ተፈላጊውን የዕፅዋት ግንድ፣ ፍልጥና ሥር በመለየት፤ በመጠን በመጠኑ ይቆረጣል፣ ይሸነሸናል፣ ይከተፋል፡፡ በዚህ ደረጃ የተለየውና የተጣራው የመድኃኒት ግብዓት ወደ ቅመማ እና ማንጠር ሂደት ይሸጋገራል (መሪጌታ ባሕረጥበብ፣ ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)፡፡ ከዚህ በታች ታጥቦ፣ ተለቅሞና ተጨቅጭቆ የተሰጣ የዕፀ መድኃኒት ቅጠልን የሚያሳይ ፎቶ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ፎቶ ግራፍ 6፡- ታጥቦ፣ ተለቅሞና ተጨቅጭቆ የተሰጣ የዕፀ መድኃኒት ቅጠል





1ኛ. ታጥቦና ተለቅሞ የተሰጣ የዕፅዋት ቅጠል 2ኛ.ተጨቅጭቆ የተሰጣ የዕፅዋት ቅጠል

ምንጭ፡- ከፋርጣ ወረዳ፤ በጥናቱ አቅራቢ በቀን 27/02/2011 ዓ.ም የተነሳ ፎቶ

በአራተኛ ደረጃ፡- የመድኃኒት ግብዓት "ቅመማ (ጨቅጭቆ ማድረቅ) እና ማንጠር" ሂደት ይጀመራል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚዘጋጁ የመድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች ልዩ ሙያ፣ ተግባርና ክህሎትን ስለሚጠይቁ፤ እንደ ግብዓቶቹ ዓይነት፣ ይዘትና ተግባር የቅመማ ሂደታቸው አጭርና እረጅም ጊዜና ጉልበት እንደሚወስድ፤ ይታመናል፡፡ የዕፅዋት ዕንቡጥ፣ ቀንበጥ፣ አበባ እና ቅጠል ተወቅጠውና ተጨቅጭቀው ይሰጣሉ፡፡ የዕፅዋት ፍሬ በመጠኑ ሲቆላ፣ ሲፈለፈል፣ ሲቀጠቀጥ፣ ሲከሰከስ እና ሲሸከሸክ ቆይቶ፤ ሽፋኑ ሲነሳና ሲለቅ በግርድፉ ይወቀጡና ይደርቃሉ፡፡ የዕፅዋት ቅጠል፣ ሽበት፣ ልቡጫ እና ዕጣን በሙቀጫ ተወቅጠው፣ "ተደልዘው"ና ተጠፍጥፈው ሲወጡ፤ በንፋስና በመጠነኛ የፀሐይ ሙቀት የያዙትን ዉኃ ይመጣሉ፡፡ የዕፅዋት ቅርፊት፣ ግንድ፣ ሥር እና መሰል ይዘቶች ተከትፈው፣ ተቀጥቅጠው፣ ተከትክተው በአሉበት ደረጃ እንዲደርቁ ይደረጋል (ሊቀጠበብት አብርሃም፣ ቃ.መ፤ 05/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡

በዚህ ሂደት ተጨቅጭቀው፣ ተቀጥቅጠው፣ ተወቅጠው፣ ተገርድፈው፣ ተደልዘው እና ተጠፍጥፈው፤ የተዘጋጁ የዕፅዋት ግብዓት ዓይነቶች በጥንቃቄ እና በንጽሕና ተይዘው፤ በእኩል መጠንና ይዘት እንዲደርቁ ይደረጋል፡፡ ለመድኃኒት ግብዓት ማስጫ በተዘጋጀ "የቆጥ መደብ" ላይ የሰሌን ምንጣፍ ተዘርግቶ ማዳበሪያ ተነጥፎ፤ በዓይነትና በመጠን ተለይተው፣ ተወቅጠው፣ ተከትፈው እና ተቀምመው ሲያበቁ በተመሳሳይ ሂደት እንዲደርቁ ይደረጋል፡፡ በሂደት በመታፈን፣ በመታመቅ፣ በመታጀልና በመጣበቅ ዕርጥበትና "ሻጋታ" እንዳይፈጥሩ፤ በየሁለት ሠዓቱ

በማገላበጥ፤ "የማዳረቅ" ሥራ ይካሄዳል (አቶ ደርሶ፣ ቃ.መ፤ 03/02/2011 እብናት)፡፡ ከዚህ በታች ዕፅዋትን ለቅሞ፣ ቀጥቅጦና አድርቆ የማስቀመጥ ሂደትን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ፎቶ ግራፍ 7፡- ዕፅዋትን ለቅሞ፣ ቀጥቅጦና አድርቆ የማስቀመጥ ሂደት



1ኛ. የግመሮ ሥር 2ኛ. የዕፀ ሣቤቅ ሥር 3ኛ. የዕፀ ልቡና ቅጠል እና ሥር

ምንጭ፡- ከሊቦ ከምከም ወረዳ፤ በጥናቱ አቅራቢ በቀን 05/03/2011 ዓ.ም የተነሳ ፎቶ

የመድኃኒት ግብዓቶች በሚሰጡበት አካባቢ ከፍተኛ ሙቀት፣ የፀሐይ ጨረር፣ አቧራ እና ቆሻሻ እንዳይገባቸው፤ በስስ እና ዉኃ ባልነካው [የአልተለበሰ፤ የሰው ወዝና ላብ ያልነካው] ንጹህ ነጠላ ጨርቅ ተሸፍነው ይሰጣሉ፡፡ ሰው፣ እንስሳት እና ነፍሳት በተሰጡበት ቦታ ላይ ሄደው እንዳይረግጡ፣ እንዳይቀምሱ፣ እንዳያርፉበት እና እንዳያረክሱት ሲባል፤ ልዩ ጥበቃና ክትትል ይደረጋል፡፡ በዚህ ተግባር እና ሂደት ውስጥ አልፈው ሙሉ በሙሉ ደርቀው ሲያበቁ፤ የዕፅዋት ዓይነትና ባሕርያት ተለይቶ ጣፋጭ፣ ጎምዛዛ፣ ለስላሳ፣ አቃጣይ እና መራራ ጣዕም የአላቸውን ይዘቶች በቅደም ተከተል ተወቅጠው፣ ተነፍተው፣ አሰርና ዱቄታቸው ተለይቶ፤ ከደቀቁና ከተደቆሱ በኋላ፤ ለመድኃኒት የተፈለገው ግብዓት በዱቄት እና በፈሳሽ መልክ ተመጥኖ ይታሻጋል (መሪጌታ ፍሬስብሃት እና አቶ ሞላ፣ ቃ.መ፤ 07/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 22/06/2011 ፋርጣ)፡፡ ከዚህ በታች በዱቄትና በፈሳሽ መልክ የተዘጋጁ ግብዓቶች ፎቶ ግራፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ፎቶ ግራፍ 8፡- በዱቄትና በፈሳሽ መልክ የታሸጉ ዕፀ መድኃኒቶች



1ኛ. የዕፅዋት ዱቄት 2ኛ. በዱቄት መልክ የታሸጉ 3ኛ. በፈሳሽ መልክ የተዘጋጁ

ምንጭ፡- ደቡብ ጎንደር ዞን፤ በጥናቱ አቅራቢ በቀን 05/03/2011 (1ኛ እና 2ኛ ፎቶ) ሊቦ ከምከም እና 27/02/2011 ፋርጣ በቅደም ተከተል የተነሳ ፎቶ፤

በአምስተኛ ደረጃ፡- በመድኃኒት ቅመማ ሂደት ታጥበው፣ ደርቀው፣ ተለቅመው፣ ተወቅጠው፣ ተነፍተው፣ አሰርና ዱቄታቸው ተለይቶ የተቀመሙ ግብዓቶች፤ በዱቄት፣ በፍሬ፣ በጥፍጥፍ ቂጣ፣ በፈሳሽ እና መሰል ይዘት ታሽገው፤ በዓይነትና በስም ተለይተው፤ የቆይታ ጊዜያቸው ተገምቶ በመጠኑ ተዘጋጅተው እንዲቀመሙ ይደረጋል፡፡ በባህል መድኃኒት ቅመማ እና አስተሻሸግ ሂደት የዓመት ግብዓት እና መድኃኒት በአንድ ጊዜ ተሰርቶና ተመጥኖ እንደማይታሸግ ደብተራ መልኩ ገልፀዋል፡፡ ለምን? ሲባል በዱቄት መልክ ታሽገው ዓመት የሚቆዩ መድኃኒቶች "ኃይላቸው ይቀንሳል፤ አቅማቸው ይደክማል፣ ይነቅዛሉ"፤ ተብሎ ስለሚታመን፤ ለመድኃኒት የተመረጡ፣ የተለቀሙና የተጣሩ የዕፅዋት ግብዓት ዓይነቶች ደርቀው፤ ፀሐይና ዕርጥበት በማይደርሱበት ቦታ በማዳበሪያ፣ በካርቶን፣ በጠርሙስና በፕላስቲክ ታሽገው እረጅም ጊዜ ማቆየትና ማስቀመጥ እንደሚቻል አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 23/01/2011 ፋርጣ)፡፡

በዚህ ሂደት በዱቄትና በፈሳሽ መልክ ተቀምመውና ተመጥነው የተቀመጡ ይዘቶች ሲያልቁ፤ ደርቀው የተዘጋጁ ግብዓቶችን በመቀመም በየጊዜው መድኃኒት ማዘጋጀት እንደሚቻል ቄስ አብርሃም ይጠቁማሉ፡፡ በተለይ ተቆርጠው፣ ተወቅጠውና ደርቀው በዱቄት መልክ የተዘጋጁ ግብዓቶች ዓመቱን ሲያልፉ፤ በቀላሉ የማይገኙ ሲሆን ጷጉሜ አምስት/ስድስት በተቀመሙበት "እቃ መሬት ውስጥ ተቀብረው፤ በማግስቱ በቅዱስ ዮሐንስ መባቻ [አዲስ ዓመት መጀመሪያ] ተቆፍረው ይወጣሉ"፡፡ ለምን? ሲባል፤ ተቀብረው ሲወጡ ኃይላቸው ይታደሳል፤ አቅማቸው ይጨምራል፤ ፈውሳቸው ይሰምራል፤ ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ሂደት በቀላሉ የማይገኙ ዕፀ

መድኃኒት ዓመትና ዘመን ሲሻገሩ፤ መቀበር እንዳለባቸው ገልፀዋል። በየዓመቱ የሚገኙና የሚበቅሉ ግብዓቶች ከሆኑ እንደገና "ማንገስ"፣ መልቀም፣ ማዘጋጀት እና መቀመም እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥተው፤ መክረዋል። ለዚህ ዐብይ ምክንያት የዕፅዋት ኃይልና ጉልበት፤ ዘመን ይሽረዋል፤ ወቅት ያደክመዋል፤ ዓመት ሲቀየር "ይነጥፋል"፤ ፈውሱን በመሳት "ይረክሳል"፤ ተብሎ ይታሰባል። በዚህ እሳቤ፤ ዕፀ መድኃኒት በየዓመቱ መዘጋጀትና መቀመም እንዳለባቸው አስረድተዋል (ቃ.መ፤01/05/2011 እብናት)። ከዚህ በታች፤ ከዕፅዋት ቅጠል የሚዘጋጅ መድኃኒት ቅመማ ሂደት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

አስረጂ አንድ፡- ከዕፅዋት ቅጠል የሚዘጋጅ መድኃኒት ቅመማ ሂደት፡-

ለመድኃኒት ቅመማ የሚመረጡ ዕፅዋት፤ በቅጠል፤ በሥር፣ በግንድ፣ በዘር፣ በቅርፊት፣ በአበባ፣ በልቡጫ (ዕጣን) እና መሰል ይዘቶችን የሚያካትቱ ናቸው። ከነዚህ ግብዓቶች መካከል ከዕፅዋት ቅጠል የሚዘጋጅ መድኃኒት ቅመማ ሂደትን መሪጌታ ስዩም እና አቶ ደሴ እንደሚከተለው አቅርበዋል (ቃ.መ፤ 04/02/2011 እና 03/07/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

**የዕፅዋት ቅጠል ቅመማ ሂደት፡-** ለባህል መድኃኒት ቅመማ የሚሰበሰቡ የዕፅዋት ቅጠል ግብዓት ዓይነቶች በዋናነት "ከመስከረም እስከ ኅዳር በአሉት ወራት ውስጥ የሚቆረጡና የሚለቀሙ ናቸው"፤ ይላሉ መሪጌታ ስዩም። እነዚህ ቅጠሎች ለመድኃኒት ግብዓት የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ፣ ወቅት፣ ዐውድ እና ይዘት በመለየት፤ በነፍሳት፣ በተባይና በእንስሳት ያልተበሉ፤ ያልደረቁና በቆሻሻ ያልተበከሉ፣ ያልተበሳሱና የብልሽት ምልክት የማይታይባቸው፤ በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ በጣም "ለጋ" ወይም ያልደረቁ መሆን እንዳለባቸው፤ ገልፀዋል። ይህን ይዘት በመለየት፤ ከመስክ ተሰብስበው፣ ታጥበው፣ ጠፈፍ ሲሉና እና ሲደርቁ፤ በዕርጥብ ይዘታቸው ተለቅመውና ተጣርተው፤ ተወቅጠው እና ተጨቅጭቀው በግርድፉ ደርቀው ወይም በዱቄት መልክ ተቀምመው መቀመጥ እንዳለባቸው፤ ይመክራሉ(ቃ.መ፤14/03/2011 እብናት)።

መሪጌታ መኅሪ፤ ከአቶ ደሴና መሪጌታ ስዩም በተለየ፤ ቅጠልና ተቀጽላ ከመስክ ተሰብስበውና ታጥበው ባሉበት ይዘት ደርቀው ቢቀመጡ፤ ኃይልና ጉልበታቸው አይቀንስም በማለት ይሞግታሉ (ቃ.መ፤ 28/01/2011)። በዚህ ሃሳብ ብዙኅኑ የባህል ሐኪሞች አይስማሙም፤ ዕፅዋት በዕርጥብ ይዘታቸው መጨቅጨቅ፣ መድረቅና መቀመም እንዳለባቸው ይመክራሉ (የተቡው አባላት፤ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)።

የዕፅዋት ቅጠል፤ በእርጥብ ይዘቱ ተጨቅጭቆ ወዲያው ሲሰጣ፤ የተሻለ ኃይል፣ ጥቅም እና አገልግሎት እንደሚሰጥ መረጌታ ስዩም ገልፀዋል፡፡ በዚህ ሂደትና ተግባር የዕፅዋት መድኃኒት ይዘት፣ ኃይልና ጉልበት ተጠብቆ፤ የቆይታ ጊዜያቸው እንደሚራዘም፤ ይታመናል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ፤ የዕፅዋትን ቅጠል ሳይወቅጡና ሳይጨቀጨቁ አድርቆ ማስቀመጥና ቀምሞ መጠቀም፤ የፈውስ ኃይልና ጉልበታቸውን እንደሚቀንስና እንደሚያሳጣ፤ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ ዓመቱን ሙሉ የማይገኙ የዕፅዋት ቅጠሎች ተለቅመው፤ ታጥበውና ተጨቅጭቀው በግርድፉ ደርቀው፤ በንጹህ ማዳበሪያ፣ ካርቶን እና መሰል ግብዓት ታሽገው መቀመጥ እንዳለባቸው መክረዋል (ቃ.መ፤ 04/02/2011 እብናት)፡፡

ለመድኃኒት ቅመማ ሲፈለግ፤ በግርድፉ ደርቆ የተቀመጠው ግብዓት፤ በሙቀጫ ተወቅጦ፤ አሰሩና ዱቄቱ በወንፊት ተለይቶና ተጣርቶ፤ መድቀቅና መላሙ ተፈትሾ በዱቄት መልክ ተዘጋጅቶ ይታሸጋል፡፡ ከዚህ ተግባር በኋል፤ ተበጥብጠው የሚጠጡ፣ በቁስል ላይ የሚነሰነሱ፣ በአፍንጫ የሚሸተቱ፤ በፈላ ዉኃ ላይ ተጨምረው፣ "ተንተክትከው" እና ተጣርተው የሚጠጡ እና መሰል ይዘትን በመተግበር የሚቀመሙና የሚሰጡ ግብዓቶች እንዳሉ፤ አቶ ደሴ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 03/07/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ ለምሳሌ፡- የዓይጥ ሃረግ ቅጠል ለልፌ ቁስል፤ የእምቧጮ ቅጠል ለዓይን ሕመም በጠብታ መልክ፣ የሳማ ቅጠል በእሳት ለተበላ አካልና ለጨንራ፣ የሽፈራው ቅጠል [ሞሪንጋ ነጩ] ለስኳር ሕመም፤ ቀምመው እንደሚሰጡ፤ የመስክ መረጃዎች ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በታች ከዕፅዋት ቅጠል የሚዘጋጁ የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች ፎቶ ግራፍ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ፎቶ ግራፍ 9፡- ከዕፅዋት ቅጠል የሚዘጋጁ የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች





1ኛ. የዓይጥ ሃረግ ቅጠል 2ኛ. የእምቧጮ ቅጠል 3ኛ. የሽፈራው ቅጠል

ምንጭ፡- ደቡብ ጎንደር ዞን፤ በጥናቱ አቅራቢ በቀን 19/01/2011 ፋርጣ እና 03/02/2011 (2ኛ እና 3ኛ ፎቶ) እብናት በቅደም ተከተል የተነሳ ፎቶ፤

በአጠቃላይ የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የማዕድን እና የነፍሳት ግብዓት ዓይነቶችን ይዘትና ባሕርይ በመለየት የሚከወን ሲሆን፤ ጊዜ፣ ወቅት እና ዐውድን ጠብቀውና ተከትለው እንደሚሰበሰቡ፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ የመድኃኒት ግብዓት አሰባሰብ እና ቅመማ ሂደቱም፤ ከመስክ በመሰብሰብ፣ በመዘፍዘፍ፣ በማጠብ፣ በማድረቅ፣ በመልቀም፣ በመቀጥቀጥ፣ በመከትከት፣ በመክተፍ፣ በመውቀጥ፣ በመፍጨት እና በመንፋት፤ አሰርና ገለባው ተጣርቶ ለመድኃኒት የሚያገለግለው ዱቄት ተለይቶ፤ ይዘጋጃል፡፡

በዚህ ተግባርና ሂደት ውስጥ ሲታለፍ ልዩ ሙያ፣ ተግባር፣ ዕውቀት፣ ጥንቃቄ እና ትኩረት በመስጠት የመድኃኒት ቅመማ ይካሄዳል፡፡ በመድኃኒት ቅመማ ወቅት፤ የመቀመሚያ ግብዓት ንጽሕናን፣ የመድኃኒት ግብዓት አያያዝ እና አስተሻሸግ ሂደትን፣ የቅመማ ጊዜን፣ ጉልበትን፣ ገንዘብን፣ ዕውቀትን እና ተሰጥኦን አስተባብሮና አቀናጅቶ ይከወናል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ፤ ሂደቱ ቢዛነፍ፣ ሥርዓቱ ቢዛባ፣ ንጽሕናው ቢጓደል፤ የሕመም መንስኤና የሞት ምክንያት ተደርጎ፤ ይታመናል፡፡

## 7.5 የባህል መድኃኒት አሰጣጥ ሥርዓት

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች፤ የሕመሙን ዓይነትና ባሕርይ ለይተው፤ መድኃኒት ቀምመው ሲሰጡ፤ በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚታጠን፣ በሚጨስ፣ በሚቀባ፣ በሚነሰነስ፣ በሚታሰር፣ በሚታኘክ፣ በሚቆረጠም፣ በሚመጠጥ እና መሰል ተግባራትን በመፈፀም፤ አዘጋጅተው እንደሚሰጡ የመስክ መረጃዎች ገልፀዋል፡፡ የባህል መድኃኒት አሰጣጥ፣ ምጣኔ፣ ሥርዓትና አተገባበር፤ እንደ ሕመሙ ዓይነት፣ መገኛ ቦታ፣ የጉዳት መጠን፣ የመድኃኒት ባሕርይ፣ የታካሚ ሁኔታ (ፆታ፣ ዕድሜ፣ አቅም)፣ የጊዜ ገደብ፣ አወሳሰድ፣ የምግብ ምርጫና ክልከላ (ብላ አትብላ)፣ አድርግና አታድርግ የሚባሉ ገደቦችን በመፈፀም እንደሚከወን መሪጌታ ስንታየሁ እና መሪጌታ ፍሬስብሃት ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 14/03/2011 ዕብናት እና

07/03/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ ከዚህ በታች "ለወፍ/ለጉበት እና ለውሻ" በሽታ የመድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ ክዋኔ ማሳያ (ናሙና) ይዘቶች[104] እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**አስረጂ አንድ፡- የ"ወፍ"/የጉበት በሽታ መድኃኒት አሰጣጥ**

የባህል ሐኪም፡- አቶ ጌጡ[105] (ከምዕራፍ ስድስት፤ ንዑስ ክፍል 6.1.1 ከአይታዊ የምርመራ ዘዴ የቀጠለ)

ታካሚ፡-ሀ

የባህል ሐኪም፡-"አይዞህ የኔልጅ! ደርሰሃል! አሁን ትገላገላለህ" በማለት ለታካሚያቸው ተስፋ በመስጠት አበረታቱት፡፡ እጃቸውን ጠራርገው ወደ መኖሪያ ቤታቸው ሄደው በጠፍር የተለበጠች አገልግል ይዘው መጡ፤ አገልግሏን ከፍተው የተፈተለ ጥጥ፣ ቤሣ [ምላጭ]፣ አንድ የተላጠች የነጭ ሽንኩርት ፍሬ አወጡ፤ አገልግሏን መልሰው ከድነው፤ ቤት ወስደው አስቀመጡ፡፡

የባህል ሐኪም፡- ከቤት ሲመለሱ በእሳት መያዣ/መጫሪያ ገል አመድ ይዘው፤ "ና አብዬ!" በማለት ወደ ጓሮ ይዘውት ሄዱ፡፡ ከቤታቸው ጀርባ በአማካይ ሃምሳ ሳንቲ ሜትር በሚያህል ስፋት እና ጥልቀት አመድና ደም የተቀላቀለበት ጉድጓድ ይታያል፤ ከጉድጓዱ አናት ላይ የነጭ ባህር ዛፍ ቅጠል እና የብሳና ቅጠል ዝንጣፊ [ቁራጭ] ተጥሎበታል/ለብሷል፡፡ የባህር ዛፍና የብሳናውን ቅጠል አንስተው ወደ ጎን አስቀመጡ፡፡ ታካሚያቸውን "ና ወዲህ!" በማለት ጉድጓዱ ዳር አስቀመጡት፤ ከመቀመጫቸው ሳይነሱ ከታካሚው ዕይታ ዘውር ብለው፤ ሶስት ቀዳዳ ያላትን ቤሳ [ምላጭ፤ ሌዘር ምላጭ ለዚህ ዓይነት ሕክምና አገልግሎት አይመረጥም] በሁለት እጃቸው አውራ ጣት መሃል አስገብተው ወደ ጎን ዘንበል በማለት፤ በሰያፉ አስተካክለው ሶስት ቦታ ሰብረው ሁለቱን በጃኬት ኪሳቸው ከተው፤ ወደ ታካሚያቸው ዞረው፤ "ቀና በል፤ ምላስህን አውጣልኝ!" በማለት፤ የታካሚውን ምላስ በጠመጠመው ሻርፐ ወደ ጎን ገልብጠው ከያዙ በኋላ "አይዞህ እንዳትፈራ! ስትንቀሳቀስ ስሩን ታስተኛለህ!" በማለት ኮስተር ብለው አዘዙ፤ "እስቲ አንተ፤ ትከሻውን ደገፍ አድርገህ ያዝልኝ!" ብለው፤ የጥናቱን አቅራቢ ጠየቁ፤ "ደም ሲፈስ ትክ ብለህ አትየው እህል አያስበላህም፤ ተመሬት ተፈናጥሮ ደም እንዳይነካህ፤ ወደ

---

[104]የዕፀ መድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ እንደ ባህል ሐኪሙ ዕውቀት፤ እንደ መልክዓ ምድሩ ሁነት፤ እንደ ዕፅዋቱ ዓይነት፤ እንደ ሥነ ምህዳሩ ይዘት፤ ቅመማ፣ አሰጣትና መመሪያዎች ይለያያሉ፡፡ ለአብነት ያህል፡- የዚህ ጥናት አቅራቢ "ለኮሶ ትል እና ለእከክ በሽታ" ብቻ አስራ ሶስት ክዋኔዎችን ከመስክ ምልከታው መዝግቧል፡፡ ይህ ልዩነትና ብዛት ከየት መጣ ቢባል? አንደኛ ከሥነ ምህዳር ልዩነት፤ ሁለተኛ ከመድኃኒቱ ግብዓት ዓይነት (በፍሬ፣ በቅጠል፣ በሥር)፤ በማዕድን እና በመሳሰሉት መፈወስ መቻላቸው ልዩነቱን ያጎላዋል፡፡ የዚህ ንዑስ ይዘት ትኩረትም የመድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ ይዘትን ፈትሾ፤ ወጥ የሆነ የጋራ ዕውቀት ማሕቀፍን ማሳየት ላይ አተኩሯል፡፡

[105]ፋርጣ ወረዳ በክምር ድንጋይ ከተማ፤ 03 ቀበሌ በቀን 20/06/2011 ዓ.ም፤ ከጧቱ 2፡50፣ ጀምሮ፤ ከባህል ሐኪም አቶ ጌጡ ነጋሽ እና ከታካሚ (ሀ) ጋር የተካሄደ የመድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ ክዋኔ ይዘት፡፡

እዚህ ሰብሰብ ብለህ ቁም" አሉ፤ ጥናት አቅራቢውን፡፡ ጥናት አቅራቢውም የታካሚውን ሁለት ትከሻ ጠንከር አድርጎ እንደያዘ፤ የታካሚውን ምላስ ወደ ጎን ገልበጥ አድርገው፤ ጥቁሩን የምላስ ሰንበር ለይተው በጡት!

ታካሚ፡- ሰውነቱ ደንገጥ/ ሽምቀቅ ሲል እንደ መቀሳቀስ ሞከር ሲያደርግ፤

የባህል ሐኪም፡- "ተው! ጠንከር በል!...፤ ስለቅህ ነው! ምላስህ የምትመልሰው፤ አይዞህ ልጄ! ጭክን በል!... ተገላገልህ፤ ይኸው ወጣችልህ!" በማለት ታካሚያቸውን አፅናኑ፤ የምላሱን ደም መቀየርና ንጹህ ደም መምጣቱን ሲያዩ፤ በጥጥ አፍነው ይዘው፤ የተላጠችውን ነጭ ሽንኩርት በእሳቷ ፍም ሞቅ፤ ሞቅ፤ አድርገው፤ በተበጣው ቦታ ላይ ተኮስ! ተኮስ! አደረጉ፡፡

ታካሚ፡-ትንፋሹ እየተቆራረጠ፤ ዓይኑን እየጨፈነ ማቃሰት ሲጀምር፤ "ጨርሷል ልቀቀው" በማለት ጥናት አቅራቢውን አዘዙ፡፡ ታካሚው በአፉ ውስጥ ተጠራቅሞ የነበረውን ምራቅና ደም ጠራርጎ ወደ ጉድጓዱ ተፋ!

የባህል ሐኪም፡- የፈሰሰውን ደም አመድ አልብሰው፤ ጉድጓዱን በብሳና እና በባህር ዛፉ ቅጠል መልሰው ከደኑት [ብሳና እና ባህር ዛፍ መራራ፣ አቃጣይ፤ ሽታና ጠረን አጥፊ መሆናቸውን ልብ ይሏል]፡፡ ከአምስት ደቂቃ ቆይታ በኋላ፤ ሕክምናውን ጨርሰው ወደ ነበርንበት ቦታ ተመለስን፡፡ ታካሚውን ጠርተው፤... በቀን አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ቀንሰህ፤ በአንድ ጣሳ/ጆክ ዉኃ በጥብጠህ፤ በሻይ ማፍያ አፍልተህ፤ ሲበርድ ዉኃ ባልነካው ቁጢት [በአዲስ ነጠላ ቁርጭ] ጨርቅ አጥለህ፤ አንድ ብርጭቆ በባዶ ሆድህ ጠጣ፤ ለአንድ ሠዓት ያህል ምግብ አትብላ፤ ከምትጠጣው የተረፈውን ወደ ጓሮ ወስደህ ድፋው፡፡... ለአንድ ወር ወተት፣ ሥጋ፣ ቅቤ፣ እንቁላልና ዘይት ያለው ነገር እንዳትበላ፡፡ በሽታው ተመልሶ ያገረሻል፤ እሚያዳግም ከሆነ አይድንም፡፡... በዚህ ምትክ ሽሮ ወጥ፣ ክትፎ ድንች፣ ምስር፣ አተር፣ ባቄላ፣ ጎመን እና ፍራፍሬ ብላ! ጣፍጭ ነገር የደረሰበት ቦታ እንዳትደርስ፤ መዳኒቱን ወስደህ ትውከትና ማስቀመጥ ካለው አንድ ፍንጃል [ስኒ] አቦል ቡና ጠጣበት፤ የገብስ ጠላ አለፍ አለፍ እያልክ ጠጣ፤ ሰውነትህ ይመለሳል [ትድናለህ]፡፡ ሁለት ሶስት ቀን ቆይተህ፤ ካልተሻለህ ተመልሰህ ና! ድጋሚ ትታያለህ፡፡

በማለት ታካሚያቸውን መክረው፤ ከተለያዩ ዕፅዋት ቀምመው በዱቄት መልክ መጥነው ከአዘጋጁት መድኃኒት፤ ሰባት የሾርባ ማንኪያ የዕፀ መድኃኒት ዱቄት ለክተው፤ ዱቄቱን በጥቁር ላስቲክ አስረው፤ "እግዚአብሔር ምህረቱን ይላክልህ፤ ሰላም ግባ ልጄ!" በማለት አንድ መቶ ብር ተቀብለ ታካሚያቸውን አሰናበቱ፡፡ ክዋኔ ሁለት፡- "የዉሻ ከለባት" መድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ ክዋኔ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## አስረጂ ሁለት፡- የዉሻ ከለባት መድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ

የባህል ሐኪም፡-መሪጌታ ስንታየሁ[106]

ታካሚ፡- ለ፤ "እዚህ ቤት! ደህና አረፈዳችሁ" በማለት ገርበብ ብሎ የቆመውን የግቢ በር ከፍተው ወደ ውስጥ ገቡ።

የባህል ሐኪም፡- "አቤት!... እንደምን አረፈዳችሁ!" በማለት ከተቀመጡበት ተነሱ፤ "ምነው! ምን ሆናችሁ!" በተደናገጠ ስሜት ታካሚያቸውን እያዩ፤ አብረው የመጡ ሰዎችንም ጠየቁ፤

ታካሚ፡- ዉሻ! ዉሻ ለክፎኝ [ነክሶኝ] ነው! (በግምት የሰላሳ ዓመት ወጣት ይሆናል)

የባህል ሐኪም፡- መቼ ነው የለከፈህ?

ታካሚ፡- የስላሴ ለታ/ ዐርብ ለት ነው፤

የባህል ሐኪም፡- ከኪሳቸው ክብና የፊት መስተዋት የምትመስል (አዕጋረ ፀሐይ) መመርመሪያ መሳሪያ አውጥተው፤ "እስኪ አፍክን ከፈት አርገው" አሉ፤

ታካሚ፡- አፉን ከፈት አርጎ፤ ምላሱን አሳየ፤

የባህል ሐኪም፡- አፉን፣ ምላሱን፣ ዓይንና ደረቱን በመስታወቷ አዩ፤ "በሽታው ለክፎሃል፤ ወደ ሰውነትህ ገና አልተሰራጨም፤ ሆድህ ውስጥ የዕንቁላል ዕጭ ጀምሯል" በማለት ከታካሚው አለፍ ብለው ሄደው፤ አንድ የብሳና ቅጠል በጠስ አድርገው ተመለሱ፤ "እስቲ እዚህ ላይ ምራቅህን አስቀምጥ" በማለት ለታካሚው ቅጠሏን ሰጡ፤

ታካሚ፡- በተሰጠው ቅጠል ላይ ትንሽ ምራቅ ጠብ አድርጎ መለሰላቸው፤

የባህል ሐኪም፡- ከታካሚው በቅጠል የተቀበሉትን ምራቅ በግራ እጃቸው መዳፍ ይዘው፤ በቀኝ እጃቸው ከተፈለጠ እንጨት ላይ ንፁህ ስንጥር አላቀው ካነሱ በኋላ፤ ምራቁን ደጋግመው ወደ ግራ ወደ ቀኝ፤ ብድግ፤ ጣል፤ እያደረጉ መወፈርና መቅጠኑን አረጋገጡ፤ ከአንገታቸው ጎንበስ፤ ከድምጻቸው ቀነስ አድርገው "በሎህሳስ" "በሽታው ሲብስ ምራቁ ይወፍርና እንደ ተልባ ይዝለገለጋል" በማለት ለጥናቱ አቅራቢ ጠቆሙ፤

[106]መሪጌታ ስንታየሁ፤ በእብናት ወረዳ፤ በኒቋራ 01 ቀበሌ በቀን 14/03/2011 ዓ.ም፤ ከጧቱ 2፡10፣ በሕክምና መስጫ ጣቢያቸው ደረስኩ፤ በዕለቱ በእብድ ውሻ በሽታ ለተለከፈ ታካሚያቸው (ለ) መድኃኒት ቀምመው ሲሰጡ፤ እንዴት ይከዉኑ እንደነበር የቀረበ ይዘት።

የባህል ሐኪም፦ ማነህ ልጄ! መዳኒት ለመጠጣት ተዘጋጅተሃል፤ ቁርስ አልበላህም መቼም፤

ታካሚ፦ አልበላሁም አባቴ! አሁን እወስዳለሁ፤

የባህል ሐኪም፦ "በሉ እዛች መደቧ ላይ አረፍ ብላችሁ ጠብቁኝ"፤ በማለት ትእዛዝ ካስተላለፉ በኋላ፤ ባለቤታቸውን ጠርተው በፌርሜሎ [በክሰል ማንደጃ] የተቀጣጠለ እሳት እንዲሰጧቸው አዘዙ፤ በፍጥነት ክሰሉ ከነፍሙ ተቀጣጥሎ መጣ፤ አንድ ብርጭቆ ዉኃ እና አንድ የሻይ ማንኪያ የተቀመመ የዕፀ መድኃኒት ዱቄት ቀላቅለው፤ በሻይ ማፍያ ጨምረው፤ ለአምስት ደቂቃ አፍልተውና አንተክትከው አወጡ፤ ወደ ሕክምና መስጫ ቤታቸው ገባ ብለው፤ በሻይ ቅጠል ማጥለያ አጣርተው፤ አንድ ስኒ አጥለውና አንጠፍጥፈው አስቀመጡ፤ በረድ ሲል፤ አንድ የሻይ ማንኪያ ነጭ ማር ቀንጠር አድርገው ጨመሩ፤ "ና! ወደ እዚህ" በማለት ታካሚያቸውን ጠሩ፤

ታካሚ፦ ከተቀመጠበት ተነስቶ አጠገባቸው ቆመ፤

የባህል ሐኪም፦ ወደ ጓሮ ይዘውት ሄደው፤ "እዚህ ላይ አረፍ በል" በማለት እህል በሚወቀጥበት ሙቀጫ ላይ አስቀምጠው፤ በስኒ ይዘውት የሄዱትን፤ "ዓይንህን ጨፍነህ ዥው! አርገህ ጠጣ! መሬት ጠብ እንዳትል!" በማለት አዘዙት፤ [በሙቀጫ የማስቀመጣቸው ምስጢር፤ የሰጡት መድኃኒት እንዲሰራ፤ በሆዱ ውስጥ ያለው በሽታ እንዲመክን፤ ሕይወቱና አካሉ እንዲጠፋ፣ እንቁላሉ እንዲፈርስ፤ የታለመ መሆኑን ልብ ይሏል፤ ሙቀጫ ፍሬን አምካኝ፣ ሕይወትን አጥፊ፣ ባሕርይን ቀያሪ፣ ዕውቀትን ደምሳሽና ለዋጭ ኃይል ነው፤ ተብሎ ይታመናል።]

ታካሚው፦ ትንሽ ካቅማማ በኋላ፤ ከአንገቱ ቀና ብሎ፤ ምራቁን ዋጥ አድርጎ፤ በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርጎ ጠጣ፤ የጠጣበትን ስኒ ሲመልስ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ፤ አክታው እየበዛ ሄደ፤

የባህል ሐኪም፦ "እዛ ጥላው ስር አረፍ በል፤ የማዞር፣ የማስመለስ ጠባይ አለው! ያስቀምጥሃል! እንዳትደነግጥ"፤ በማለት የመድኃኒቱን ባሕርይ አስረድተው፤ "ወደታች ካለህ ወረድ ብለህ ተናፈስ [የዓይነ ምድር መውጫ]" በማለት አቅጣጫ አሳይተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፤

ታካሚ፦ ከሁለት ሠዓት ቆይታ በኋላ ትውከትና ተቅማጥ ጀመረው፤

የባህል ሐኪም፦ "ነፋስ ይምታህ! አትተኛ ሙቀት ነው። አይዞህ በርታ!" በማለት እስከ ዘጠኝ ሠዓት ተኩል አቆዩት፤

ታካሚ፦ "ኧረ!... ወይኔ! አልቻልኩ መሪጌታ፤ ኧረ ልሞት ነው! ሰውነቴ ተቃጠለ!...፤" በማለት "ይንቆራጠጣል" [ይነሳል፤ ይቀመጣል፤ ይተኛል፤..]፤

የባህል ሐኪም፡- ሠዓቱ ደርሷል፤ ጠንከር በል!፤ ማርከሻውን እየሰራሁልህ ነው፤

ታካሚ፡- እሺ አባቴ!

የባህል ሐኪም፡- "ና! እስቲ" በማለት መጀመሪያ አንድ ፍንጃል [ስኒ] አቦል ቡና አጠጡት፤ "ከቤትህ ስትደርስ፤ የዶሮ ጉበት ጠብሰህ ብላ፤ ወተት እና የዶሮ መረቅ ጠጣበት፤ የገብስ ጠላ ካገኘህ ጥሩ ነው፤ አንድ ሰንበት [ሰባት ቀን] ፀበል ጠጣ"

በማለት ታካሚያቸውን ከቀኑ ዘጠኝ ሠዓት ከአርባ አሰናበቱ። በባህል ሕክምና ልማድ፤ የመድኃኒት እና የሕክምና አገልግሎት መስጫ ዐውዳዊ ሠዓት ከጧቱ አስራ ሁለት ሠዓት እስከ ረፋዱ አራት ሠዓት፤ ከሠዓት ፀሐይ በረድ ሲል ከዘጠኝ ሠዓት በኋላ ይከወናል። ከአምስት እስከ ዘጠኝ ሠዓት ያለው ጊዜ "ቀትር ነው!፤ አጋንንት የሚቀሳቀሱበት ሠዓት ነው፤... የባህል ሐኪሙን ሃሳብ እና የሕመሙን ባሕርይ ይለውጣሉ!" ተብሎ ይታሰባል (መሪጌታ ስንታየሁ፣ ቃ.መ፤14/03/2011 እብናት)።

ከዚህ በላይ የቀረቡ የመድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ ክዋኔዎች እንደሚያስረዱት፤ በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች፤ ለታካሚ መድኃኒት ሲሰጡ የበሽታውን ዓይነትና ባሕርይ ተገንዝበው፤ የታካሚውን ወቅታዊ ሁኔታ፣ የበሽታውን ጉዳትና መጠን መርምረው፤ ከአረጋገጡ በኋላ ቀምመውና መጥነው ያዘጋጁቸውን መድኃኒቶች እንዴት እንደሚወሰዱ፣ መቼ እንደሚወሰዱ፣ በምን እንደሚወሰዱ፣ ምን ዓይነት ምግብ መብላት እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው፣ ከምን ዓይነት ድርጊት መቆጠብ እና ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንደሚችሉ፤ የሚወስዱት መድኃኒት "ማርከሻ/ መሻሪያ" ምን እንደሆነ በማስረዳት፤ ገቢሩን፣ ሥርዓቱን፣ ፈቃድና ገደቡን ገልፀው፤ መመሪያና ማስጠንቀቂያ ሰጥተው እንደሚተገብሩ አቶ ጌጡ እና መሪጌታ ስንታየሁ መክረዋል (ቃ.መ፤20/06/2011 ፋርጣ እና 14/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

ሊቀጠበብት አብርሃምና መሪጌታ በረከት፤ የባህል መድኃኒት አሰጣጥና ቅመማ አራት መሰረታዊ ስሌቶችን በመተግበር እንደሚፈፀም ጠቁመው፤ እንደ መድኃኒቱ ባሕርይ/ጣዕም (አቃጣይ፣ መራራ፣ ጣፍጭና ለስላሳ)፤ "የማባረዝና የማዋኀድ"፣ "የማብረድና የማተኮስ"፣ የማላላትና የማጠንከር፣ የማቅጠንና የማወፈር ስልትና ሂደቶች ሲከውኑ፤ የመደመርና የመቀነስ፤ የማባዛትና የማካፍል ቀመሮችን ተከትለው፤ የመድኃኒት ይዘት፣ ኃይልና ጉልበት ተመጥኖ እና ተቀምሞ እንደሚሰጥ ገልፀዋል። በዚህ ሂደት የማቃጠልና የማተኮስ ባሕርይና ጣዕም ያላቸው ግብዓቶች፤ የዉኃ ይዘት ባላቸው፤ መራራና መርዛማ መድኃኒቶች ደግሞ ጣፋጭ ከሆኑ ግብዓቶች ጋር

ተለውሰው፣ ተቀላቅለው፣ ተበርዘውና ተዋኀደው እንደሚሰጡ፤ መክረዋል (ቃ.መ፤ 05/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 12/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)። ከዚህ በታች የመድኃኒት ቅመማና ምጣኔ፤ ማባረዝና ማዋኀድን የሚጠቁም ፎቶ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ፎቶ ግራፍ 10፡- የመድኃኒት ቅመማና ምጣኔ፤ ማባረዝና ማዋኀድ ይዘት





የጥናቱ አቅራቢና መሪጌታ በረከት፤ የመድኃኒት ግብዓት፣ ቅመማ፣ ምጣኔና ማዋኀድ

ምንጭ፡- ከእብናት ወረዳ፤ በጥናቱ አቅራቢ 12/03/2011 የተነሳ ፎቶ

በተመሳሳይ መልኩ፤ መሪጌታ መኀሪ፤ መራራ ጣዕምና ባሕርይ ያላቸው መድኃኒቶች ተቀምመው በተቀመጡበት ይዘትና ጣዕም "በቀጥታ ለታካሚ አይሰጡም" ይላሉ። እነዚህ መድኃኒቶች "መከለሻ፣ ማባረጃና ማዋሃጃ ያስፈልጋቸዋል" በማለት ይመክራሉ። ለምን? ሲባል፤ አካልን የማቁሰል፣ የማቃጠል፣ የመላጥና የማድከም ባሕርይ እንዳላቸው፤ ይገልፃሉ (ቃ.መ፤ 28/01/2011 ሊቦ ከምከም)።

መሪጌታ ባሕረጥበብ ደግሞ፤ "የአዞ ሃረግ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ 'ወርቅ በሜዳ'፣ ጨው፣ እሬት፣..." የመሳሰሉ ግብዓቶችን በቀጥታ ለታካሚ መስጠትና ማጠጣት "ከመግደል አይተናነስም" ይላሉ። ለዚህ ብልኃቱ ኃይልና ጉልበታቸውን በሚቀንሱና በሚያሳሱ ተጨማሪ ግብዓቶች "ተከልሰውና ተበርዘው" [ተቀላቀልው] ሲሰጡ፤ የሚደመሩና የሚቀነሱ፤ የሚካፈሉና የሚባዙ ግብዓቶችን በመቀላቀል ተገቢና "ልከኛ" ደረጃ ላይ ሲደርሱ የማመጣጠን እና የማቻቻል ስልቶች እንደሚከተሉ ገልፀዋል። ለአብነት ያህል፡- አንድ የሻይ ማንኪያ "የዕፀ እስራኤል" [የአህያ ጆሮ] ቅጠል ዱቄት፤ በሁለት የሻይ ማንኪያ የሽፈራው ቅጠል ዱቄት በርዞና ቀላቅሎ በአራት ብርጭቆ ዉኃ አፍልቶና አብርዶ፤ በሻይ ማጠንፈፊያ ወይም በንጹሕ ነጠላ ጨርቅ አጥሎ አሰርና ዝቃጩን በመጣል፤ ሁለት ብርጭቆ መድኃኒት "ተጠሎ" ይገኛል። ይህን መድኃኒት በሁለት ማንኪያ ጥቁር ማር

ለውሶና በጥብጦ በባዶ ሆድ/ ከምግብ በፊት ጧትና ማታ አንድ ስኒ መጥኖ ለተከታታይ ሶስት ቀን መጠጣት፤ የወገብ፣ የእጅና የእግር ቁርጥማትን በማስቆም ዘላቂ ፈውስ እንደሚያስገኝ መክረዋል (ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)። ይህ ተግባር በሥነ ዕውቀት ንድፈ ሃሳብ እና በተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል እሳቤ እንዴት ይደራጃል?

በሥነ ዕውቀት ንድፈ ሃሳብ፤ የባህል መድኃኒት አሰጣጥ ሂደት፣ አደረጃጀት እና ተግባር በሥርዓትና በዕውቀት እንደሚተገበር ይታሰባል። ይህን ተግባር ታሳቢ በማድረግ፤ የባህል መድኃኒት አሰጣጥ ሂደት ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ምስል 18፡- የባህል መድኃኒት አሰጣጥ ሂደት ማሕቀፍ




ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች፤ በጥናት አቅራቢው የተዘጋጀ ማሕቀፍ ኅዳር/2012 ዓ.ም

ከዚህ በላይ የቀረበው ማሕቀፍ እንደሚያስረዳው፤ የባህል መድኃኒት አሰጣጥ ሂደት እንደበሽታው ዓይነትና ባሕርይ የሚለያይ፤ ከመድኃኒት ግብዓት ዓይነትና ባሕርይ ይዘት ጋር በተቃርኖ

እንደሚተገበር፤ ይገልፃል። ከዚህ አንፃር የበሽታው ዓይነት፤ የመድኃኒት አሰጣጥ ሂደትን፣ ተግባርን፣ ምጣኔ እና አጠቃላይ ሥርዓትን እንደሚወስን፤ ይነገራል። ይህ ተግባር፤ በአፍ የሚጠጡ (ለውስጥ አካል ሕመም)፣ በቆዳ ላይ የሚቀቡ (ለውጭ አካል ሕመም)፤ በአፍንጫ የሚሸተቱ፤ በዓይን እና በጆሮ ላይ በጠብታና በመጥረግ የሚሰጡ፤ በፊንጢጣ የሚቀበሩ እና የሚጨሱ ይዘቶችን በማካተት፤ አምስት መሰረታዊ የባህል መድኃኒት አሰጣጥ፣ አወሳሰድና አተገባበር ስልቶች እንዳሉ፤ የመስክ መረጃዎች ገልፀዋል። እነዚህ ስልቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ለውስጥ አካል ሕመም የሚሰጡ መድኃኒቶች በዋናነት በአፍ የሚወሰዱ ሲሆን ለጨጓራ፣ ለስኳር፣ ለሆድ ጥገኛ ትላትል፣ ለኩላሊት፣ "ለወፍ" (ለጉበት)፣ ለደም ማነስ፣ ለተቅማጥ እና መስል በሽታዎች፤ በሚጠጣ፣ በሚበላ፣ በሚዋጥ፣ በሚታኘክ፣ በሚመጠጥ መልክ አዘጋጅተው እንደሚሰጡ መሪጌታ በረከት እና አቶ ደሴ ገልፀዋል (ቃ.መ፤12/03/2011 እና 03/07/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)። ይህን ተግባር ታሳቢ በማድረግ፤ መሪጌታ ባሕረጥበብ "የወስፋትና የኮሶ ትል ሲጣባ"፤ የመድኃኒት አሰጣጥና አወሳሰድ ሂደትን እንደሚከተለው ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 27/02/2011 ፋርጣ)።

> ያበሻ መዳኒት ሲሰጥ መልኩ ብዙ ነው፤ መውሰጃው ለየቅል [የተለያየ] ነው። የበሽታው ዓይነት ሲለያይ መዳኒቱም አብሮ ይለያያል።... ሕመሙ ሲታወቅ፤ በታማሚው አቅም ልክ መዳኒት ይዘጋጃል።... ልጅ፣ ነፍሰጡር፣ አዋቂ፣ ሽማግሌ ሲሆኑ እንዳቅማቸው ተሰፍሮ [ተመጥኖ] ይሰጣል። ...ኮሶ ሲጣባቸው [ሲይዛቸው]፤ ለልጆች የወገርት ዱቄት በንጹህ ውኃ ተፈልቶ፤ በሻይ ማጥለያ ተጣርቶ ሶስት የሻይ ማንኪያ ለክቶ በማር ለውሶ ማጠጣት። ለነፍሰጡር ሴቶች የዱባ ፍሬ በምጣድ ታምሶ፤ በጥሬ ጨው ታሽቶ ሁለት እፍኝ ዘግነው፤ በባዶ ሆዳቸው እንደቆሎ ለሶስት ቀን ማብላት። ለአዋቂ የመተሬ ፍሬ፣ የኮሶ እና የወገርት ሥር በአንድ ላይ ደባልቆ ወቅጦ፤ ሁለት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ለክቶ፤ በቀይ ጤፍ ዱቄት ለውሶ እና ጋግሮ በባዶ ሆድ ቂጣውን ማብላት፤ ለአቅመ ደካሞች ግማሽ ቂጣ ሰጥቶ እስከ ግማሽ ቀን ምግብ ሳይበሉ፤ ማዋል ነው። መዳኒቱ ሲጣላ የማስመለስና የማስቀመጥ ጠባይ አለው፤... መሻሪያው የዶሮ መረቅ ማጠጣት እና ጉበት ማብላት ነው። በማግስቱ ዓይነ ምድር ሲወጡ እንደ ሰርዶ ተጠቅሎ ዝርግፍ ብሎ ይወጣል።

በማለት ገልፀዋል። እንደ መሪጌታ ባሕረጥበብ መረጃ የባህል መድኃኒት አሰጣጥና አወሳሰድ ሂደት እንደ በሽታው ዓይነት እና ታካሚው አካላዊ ሁነት የሚለያይ ሲሆን፤ አተገባበሩም

በሚበላ፣ በሚጠጣ፣ በሚታኘክ እና መሰል ተግባራትን በመፈፀም እንደሚከወን ገልፀዋል። መሪጌታ መኀሪ፤ ለአንድ በሽታ የተለያየ ዓይነት መድኃኒት፣ ቅመማ፣ አሰጣጥና አወሳሰድ ሂደት እንዳለ ጠቁመው፤ ለሆድ ጥገኛ ተሕዋሲያን (ወስፋትና የኮሶ ትል) ተቀምመው የሚሰጡ መድኃኒቶች እንደ ታካሚው እድሜ፣ ፆታ፣ ደረጃና ይዘት ተመጥነው፤ ጎምዛዛና አቃጣይ ይዘት የሌላቸውን በማር ተለውሰው፤ መራራ የሆኑትን ደግሞ በቀይ ጤፍ ቂጣ እና ጣፍጭ ይዘት በአላቸው ግብዓቶች ተዘጋጅተው እንደሚሰጡ፤ መክረዋል (ቃ.መ፤ 28/01/2011 ሊቦ ከምከም)። ደብተራ ጥላሁን ደግሞ፤ ለሆድ ሕመም እና ጥገኛ ተኀዋሲያን የሚሰጥ መድኃኒት "በባዶ ሆድ" (ከምግብ በፊት) መሰጠት እንዳለበት ጠቁመው፤ "ምግብ ተበልቶ እና ውኃ ተጠጥቶ ቢሰጥ፤ መድኃኒቱ ይረክሳል፤ ኃይል ያጣል፤ አቅሙ ይደክማል፤ በሽታውን ሳያገኝ እና አገልግሎት ሳይሰጥ መክኖ ይቀራል" ተብሎ እንደሚታመን አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 03/03/2011 ሊቦ ከምከም)።

የባህል መድኃኒት አሰጣጥ፣ አወሳሰድና አተገባበር ሂደት፤ በዐውድ እና "በገቢር" የተገደበ፤ የተለያዩ እና ዘርፈ ብዙ ሂደቶችን በማለፍ፤ በሚነሰነስ፣ በሚቀባ፣ በሚጨስ፣ በሚቀበር እና መሰል ተግባራትን በመፈፀም፤ እንደሚከወን የባህል ሐኪሞች ገልፀዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደርሶ እና መሪጌታ መንግስቴ፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት)። አቶ ጌጡና መሪጌታ ሠረቀብርሃን ደግሞ፤ የባህል መድኃኒት አሰጣጥና አወሳሰድ በዋናነት፤ በአፍ የሚጠጡ (ለሆድ ሕመም)፣ በቆዳ ላይ የሚቀቡ (ለነቀርሳ ቁስል)፣ በአፍንጫ የሚሸተቱ (ለቡዳና ለአዕምሮ ሕመም)፣ ለዓይንና ለጆሮ ሕመም "በጠብታና በመጥረግ" የሚሰጡ፣ በፊንጢጣ የሚቀበሩና የሚጨሱ የመድኃኒት ዓይነቶች እንዳሉ፤ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 20/06/2011 ፋርጣ እና 12/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

እነዚህ መድኃኒቶች ሲሰጡ በተለያየ ግብዓት ተመጥነው፣ "ተሰፍረው"ና ተለክተው እንደሚሰጡ አቶ ታከለ እና መሪጌታ አማረ ጠቁመዋል። የመድኃኒት መለኪያ፤ ምጣኔና አሰጣጥ ሂደት እንደመድኃኒቱና በሽታው ባሕርይ የሚወሰን ሲሆን፤ በስኒ፣ በኩባያ፣ በመለኪያ፣ በሻይ ብርጭቆ፣ በማንኪያ፣ "በአፅቅና በኃት" [በትንሿ ጣት ክርክር ልክና በእጅ እፍኝ መጠን] እንደሚለኩ ገልፀዋል። በመድኃኒት አሰጣጥ ሂደት ወቅት አቃጣይ፣ ጎምዛዛ፣ ጨዋማ እና ኮምጣጣ የሆኑ መድኃኒቶችን በሚያለሰልሱ፣ በሚያቀዘቅዙ እና ኃይላቸውን በሚያበርዱ ግብዓቶች፤ መራራ እና አደገኛ የሚባሉ መድኃኒቶችን ደግሞ ጣፍጭ ይዘት በአላቸው፤ ማር፣ ሙዝና ፓፓዬ ቀምመውና ደባልቀው እንደሚሰጡ መክረዋል። ለታካሚ የሚሰጡት መድኃኒት የፈውስ ኃይልና

ይዘቱን ጠብቆ ሲተገበር፤ የማቃጠል፣ የማስታወክና የማስቀመጥ ኃይሉ ጎልቶ ከወጣ፤ የመድኃኒት "ማርከሻ" (ቡና፣ ወተት፣ የዶሮ መረቅና ጉበት፣ ጠላ፣...) ግብዓቶችን እንደሚጠቀሙ አስረድተዋል (ቃ.መ፤04/03 እና 26/01/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)፡፡

መሪጌታ መኅሪ እና መሪጌታ ልሳነወርቅ፤ ውጫዊ አካልን የሚያቆስሉ፣ ቆዳና መሰል የሰውነት ክፍልን የሚያጠቁ የሕመም ዓይነቶች፤ የቆላ ቁስል፣ ኪንታሮት፣ ፎረፎር፣ እከክ፣ ቋቁቻ፣ ልፌ፣ ብጉንጅና መሰል በሽታዎች ሲከሰቱ፤ ተቀምመው የተዘጋጁ መድኃኒቶች በመቀባት፣ በመነስነስ፣ በመተኮስ፣ በመብጣት እና በማጀል ሕክምና እንደሚሰጡ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 28/01/2011 እና 27/04/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)፡፡ የባህል መድኃኒት አሰጣጥና አወሳሰድ ሂደት ዐውዱን ለይቶ፤ መመሪያና ትእዛዝን አክብሮ፣ የበሽታውን ዓይነት መነሻ አድርጎ እንደሚተገበር ደብተራ መኅሪ ጠቁመው፤ ሂደቱን እንደሚከተለው ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 13/03/2011 እብናት)፡፡

> በሰውነት ቆዳ ላይ የሚከሰቱ በሽታዎች "በዉኃ ልክፍት"፣ በመውደቅ፣ በእንስሳት ንክሻ እና በተለያየ ነገር ይመጣሉ፡፡ ...ከውሻ ከለባት [ልክፍት] ዉጪ፤ ምግብ ቢበላም ባይበላም ችግር የለውም፡፡ ቁስሉ ከባድ እና በልክፍት የመጣ ከሆነ፤ ከፀሐይ ከልሎ፤ ከጥላ ጠብቆ ጧትና ማታ እያጠቡ መቀባት፣ መነስነስና ማሰር ነው፡፡ እንደ ሕመሙ ጠባይ አንድ ጊዜ፣ ሁለት ሶስት ጊዜ ሊቀባና ሊታሰር ይችላል፡፡ ...ለሙሽሮ ነቀርሳ፣ ለኪንታሮት፣ ለልፌ ቁስል መዳኒት ከሰጠሁ፤ የአገዳ እህል [ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ በቆሎ] እንዳይበሉ እከለክላለሁ፡፡ የአገዳ እህል፤ ቁስል ያመረቅዛል፤ ቶሎ አይድንም፡፡ ከስንዴና ባቄላ በስተቀር ጤፍ፣ ገብስና አጃ እንዲበሉ እመክራለሁ፡፡ ..መድኃኒት ከወሰዱ በኋላ ከጥላ እንዲጠበቁ፤ አስጠነቅቃለሁ፡፡ ...ፀሐይ የነካው፣ ቀብር፣ ለቅሶ እና ገበያ ውለው የሚመጡ ሰዎች፤ ዶሮ እና እንስሳት፤ ለታካሚ ጥላ ናቸው፡፡ ሕመሙን ያባብሳሉ፤ መድኃኒት ያረክሳሉ፡፡

በማለት ገልፀዋል፡፡ እንደ ደብተራ መኅሪ መረጃ፤ ለአካላዊ ቁስል በሚቀባ፣ በሚነሰነስ፣ በሚታሰር እና መሰል ይዘቶችን በመፈፀም፤ ምግብ ተበልቶና ሳይበላ የሚወሰዱ መድኃኒቶች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ምግብ ተበልቶ የሚወሰዱ መድኃኒቶች በአብዛኛው ለአካላዊ ቁስል ሲሆን፤ "በባዶ ሆድ" የሚወሰዱ መድኃኒቶች ደግሞ ለውስጥ አካል ሕመሞች ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡ አቶ ደርሶ እና መሪጌታ በረከት፤ በመድኃኒት አሰጣጥና አወሳሰድ ሂደት ውስጥ መድኃኒት ከተሰጠ በኋላ ለቁስል ሕመሞች "የአገዳ እህልና ነቀዝ የሚደፍራቸው" የእህል ዓይነቶች[107]፤ ቁስልን የማባባስ፣ የማመርቀዝ፣ የማላላት ፀባይ እንዳላቸው መክረዋል፡፡ ከዚህ

[107] በባህል ሕክምና ዕውቀትና ተግባር፤ ከመድኃኒት አሰጣጥና አጠቃቀም ሥርዓት ጋር በተገናኘ የሚበሉና የማይበሉ የምግብ ዓይነቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ለምሳሌ፤ ለወፍ/ ለጉበት በሽታ ጣፋጭና የቅባት ዘሮች (ቅባት፣ ስኳር፣ ጮማ ሥጋ) ይከለከላሉ፤ በአንጻሩ ፍራፍሬ፣ ቅጠላ ቅጠል እና ገብስ፣ ምስር፣ አተር፣ ጤፍ ይፈቀዳሉ (አቶ ጌጡ፤

በተጓዳኝ የገብስ፣ የአጃና የጤፍ እህል ዓይነቶችን መጠቀም ተመራጭ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ከሚበላውና ከሚጠጣው ምግብና ዉኃ በተጨማሪ "አድርግና አታድርግ" የሚባሉ ትእዛዝና ገደቦች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ መድኃኒት የወሰደና የተቀባ ሰው፤ ከፀሐይ ጨረር፣ ከጾታዊ ግንኙነት እና "ከጥላ" [ከዶሮ፣ ገበያ፣ ቀብር እና ፀሐይ ላይ ውሉ ከመጣ ሰውና እንስሳት] ተጠብቆ፤ ሕመሙ እስከሚድን ድረስ መቆየት እንዳለበት ይነገራል (ቃ.መ፤ 03/02/2011 እብናት እና 12/03/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡ ይህ ካልሆነ ቁስሉ አመርቅዞ በማገርሸት እንደሚባባስ፤ ይታመናል፡፡

በአጠቃላይ በመድኃኒት አሰጣጥ ሂደት፤ የመድኃኒቱ ባሕርይና የባህል ሐኪሞች "ማባረዣና ማዋኀጃ" ቀመሮች፤ የሕመሙ ዓይነት፤ የታካሚው ወቅታዊ ሁኔታ፣ የመድኃኒት መጠንና የሚሰጥበትን ዐውድ፣ የበሽታና የመድኃኒት ባሕርይ፣ ከምግብ በፊትና በኋላ የሚሰጥ መሆን አለመሆኑ፤ መድኃኒት እንደተሰጠ የሚበሉ (የሚጠጡ) እና የማይበሉ (የማይጠጡ) የምግብና መጠጥ ዓይነቶችን በመለየት፤ የመድኃኒት ማርከሻ ግብዓቶችን በመግለጽ፤ ከምን ዓይነት ድርጊትና ተግባር መቆጠብ እንዳለባቸው በመምከር፤ መመሪያና ትእዛዝ በመስጠት፤ የሕክምና ሥርዓቱን እንደሚከውኑ መገንዘብ ተችሏል (አባሪ ስድስትን ልብ ይሏል)፡፡

## 7.6 የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣር ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔን ለማሳየት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ዋቢ በማድረግ በዓይነትና በይዘት ተዘጋጅተው ትንታኔ ቀርቧል፡፡ በትንታኔው መሰረት ጎልተው የወጡና የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ ከባህል መድኃኒት ግብዓት አሰባሰብ እስከ መድኃኒት አሰጣጥ፣ መመሪያና አጠቃቀም ድረስ በሥርዓተ ገቢር እና በፀሎት የሚመራ፣ በዐውድ (በቀን፣ በሠዓት፣ በጊዜ፣ በቦታና በሁነት) የተወሰነ፣ በድርጊት የታጀበና የተገደበ፣ ብላ/አትብላ፣ አድርግ/አታድርግ መመሪያና ገደቦችን በመጠቀም ይፈፀማል፡፡

20/06/2011 ፋርጣ)፡፡ የበሽታዎች ባሕርያት እና የምግብ ንጥረ ነገሮች ይዘት ምን ዓይነት ዝምድና ወይም ተቃርኖ አላቸው? በሽታን እንዴት ይፈውሳሉ ወይም ያባብሳሉ? የምግብ ንጥረ ነገሮች በሕክምና ሥርዓት ላይ ምን ተፅእኖ/ አበርክቶ አላቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች የሥነ ምግብ፣ የጤና እና የባህል ባለሙያዎች ተቀናጅተው ምን ዓይነት ውጤትና ተግባር እንዳላቸው ቢፈትሹ፤ የባህል ሕክምና አሰጣጥና አጠቃቀም፤ የምግብ ፍቃድና ክልከላ ይዘት በምን ተግባር ላይ ተመስርቶ እንደሚከወን ቢመረመር፤ በር ከፋች ጥናት እንደሚሆን ይታመናል፡፡

- የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት "የገቢር" ማስተካከያ ዐውዳዊ ስልቶች የንፅሕና፤ የዕለት፣ የቀናትና የወቅቶች፤ የቁጥርና የአቅጣጫ እሳቤዎችን በማካተት ይተገበራል፡፡
- የባህል መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶች ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ ማዕድንና ነፋሳት ሲሆኑ አብዛኛው ግብዓት ከዕፅዋት ዓይነቶች ተሰብስቦ ይቀመማል፡፡ እነዚህ ግብዓቶች ሲሰበሰቡ መገኛ ቦታ (ሥነ ምህዳር)፣ የዕድገት ደረጃ፣ መሰብሰቢያ ወቅት፣ ዕድሜ፣ ዐውድ፣ የመድኃኒት ክፍል፣ ጣዕምና ባሕርይ ተለይቶ ወደ መድኃኒት ቅመማ ይገባል፡፡ የመድኃኒት ቅመማ ይዘትና ምድብ በግብዓት ዓይነት፣ ጣዕምና ባሕርይ ላይ ይወሰናል፡፡ የግብዓቶቹ ጣዕም በዋናነት ጣፍጭ፣ መራራ፣ አቃጣይና ለስላሳ ሲሆኑ፤ በአራት ዋና ዋና ባሕርያት (ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃና መሬት) ተመድበውና ተለይተው የቅመማ ሥርዓት ይካሄዳል፡፡
- የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት ደግሞ ከማጠብ እስከ ማሸግ የሚደርሰውን ረጅም ክዋኔን በመከተል ይፈፀማል፡፡ የክዋኔ ሂደቱም፤ ከመስክ የተሰበሰቡ ግብዓቶችን በማጠብ፣ በማድረቅ፣ በመልቀም፣ በመከትከት፣ በመቀጥቀጥ፣ በመውቀጥ፣ በመንፋት፣ በመፍጨት፣ በመሰለቅ፣ በመዘፍዘፍ፣ በመቀቀል፣ በማንጠር እና በማሸግ ተዘጋጅቶ ወደ መድኃኒት አሰጣጥ ሥርዓት ይሸጋገራል፡፡
- የባህል መድኃኒት አሰጣጥ ሥርዓት፣ መመሪያና ተግባር፤ በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚታጠን፣ በሚጨስ፣ በሚቀባ፣ በሚነሰነስ፣ በሚታሰር፣ በሚታኘክ፣ በሚቆረጠም፣ በሚመጠጥ እና መሰል ተግባራትን በመፈፀም የሚከወን ሲሆን፤ በአፍ የሚወሰዱ፣ በአካል ላይ የሚቀቡ፤ በአፍንጫ የሚሸተቱ፣ በዓይንና በጆሮ በጠብታ መልክ የሚሰጡ፣ በፊንጥጣ የሚቀበሩና የሚጨሱ መድኃኒቶችን በመውሰድ ይተገበራል፡፡
- የመድኃኒት አሰጣጥ፣ ትግበራና ሂደት ደግሞ የበሽታው ዓይነት፣ ያደረሰው ጉዳትና ደረጃ ተለይቶ፤ የታካሚው ወቅታዊ አቋምና ዐውዳዊ ሁኔታ፣ የመድኃኒት ባሕርይ፣ አወሳሰድና ምጣኔ፤ መስጫና ማርከሻ፤ የምግብ ፈቃድና ክልከላን ታሳቢ በማድረግ ይፈፀማል/ ይከወናል፡፡ በቀጣይ ምዕራፍ፤ የባህል ሕክምና ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው አስተዋፅኦ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ስምንት፡- የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው አስተዋፅኦ ይዘታዊ ትንተና

ይህ ምዕራፍ የባህል ሕክምና ዕውቀት (የማኅበረሰብ ልማድ) ለሥነ ምህዳር[108] ጥበቃ ያለውን አስተዋፅኦ (አበርክቶና ተግዳሮት) መርምሯል፡፡ በዚህ ይዘት ከሥነ ምህዳር ውጤትና ይዘቶች መካከል ዕፅዋትና እንስሳትን ብቻ በመለየት የጥናቱ አካልና ትኩረት አድርጓል፡፡ የባህል ሐኪሞች ዕውቀትና የማኅበረሰብ ልማድ፤ ዕፅዋትና እንስሳትን በመጠበቅና በማጥፋት፤ በማቅረብና በማራቅ ሂደት አካባቢያዊ ሥነ ምህዳር እንዴት ተጠበቀ፤ ተራቆተ ወይም ተዛነፈ? በሰው፣ በሥነ ሕይወትና በአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር መካከል ምን ዓይነት ትስስር እንዳለ ይገልፃል፡፡ በባህላዊ ሥነ ምህዳር (Cultural Ecology) ጥናት፤ የሰው ልጆች ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር፣ እሴት፣ ተግባር፣ እምነት፣ ግንኙነት፤… ይመረምራል፡፡ የባህል ሥነ ምህዳር ቀዳሚ ግብ የማኅበረሰቡ መተዳደሪያ ዕውቀት፣ ልማድና እምነት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አበርክቶ እንዳለው፤ ይፈትሻል፡፡ ከዚህ አንፃር የሰው ልጅ ከአካባቢው ሥነ ምህዳር ጋር ምን ዓይነት ግንኙነትና ዝምድና አለው? ማኅበረሰቡ ምን ዓይነት ሐብት አለው? ኢኮኖሚያዊ መሰረቱ፣ ገደቡና ተግዳሮቱ ምንድን ነው? ኃብቱን በምን መንገድ ያገኙታል? ምን ዓይነት ዕፅዋትና እንስሳትን ያቀርባሉ/ያርቃሉ? ለምን? የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች መታየትና መመርመር እንዳለባቸው ምሁራን መክረዋል (Sutton and Anderson, 2010; PP.8-9: Steward, 2006; PP.5-6)፡፡

## 8.1 የባህል ሕክምና ዕውቀት (የማኅበረሰብ ልማድ) ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው አስተዋፅኦ

በዚህ ንዑስ ይዘት ሥር የባህል ሐኪሞች እምነትና ተግባር፤ የማኅበረሰብ ልማድ ለአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር ጥበቃ ያላቸው አበርክቶ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

---

[108]በዚህ ጥናት ሥነ ምህዳር የምርምሩ አካልና አምድ በመሆን በሕመም መንስኤ፣ በምርመራ ዘዴ፣ በመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ ይዘት ምን ዓይነት ሚና፣ ተግባርና እሳቤ እንዳለው፤ በተለያየ መልኩ ቀርቧል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የባህል ሕክምና ዕውቀትና የማኅበረሰብ ልማድ ለአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር መጠበቅና መራቆት ምን ዓይነት አስተዋፅኦ አላቸው? የሚለውን ንዑስ ይዘት ፈትሾ ለማሳየት የቀረበ ነው፡፡ ይህም ስለሆነ፤ ይዘቱ በሕመም መንስኤ እና በመድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ሂደትና ተግባር በተለያየ ዐውድና ይዘት የተገለፀ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ለምሳሌ፡- ዕፅዋትና እንስሳትን ሲተክሉና ሲነቅሉ፤ ሲያቀርቡና ሲያርቁ፤ የመንፈስ ማደሪያ፣ የአጋንንት መኖሪያ የሕመም መንስኤ፣ የፈውስ አካል መሆን/ አለመሆናቸውን በማሰብና በመለየት ይከውናሉ፡፡ ይህ ተግባር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሥነ ምህዳር መጠበቅና መራቆት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ በዚህ ሂደት ጎልተው የታዩ እሳቤዎችና ተግባራትን ለማሳየት፤ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳትና በአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር መካከል የሚታየውን ትስስር ለመግለጽ፤ አድባራት፣ ገዳማት፣ የሃይማኖት ተቋማት ለአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር መጠበቅ ያላቸውን አበርክቶ ለመጠቆም፤ የመስክ መረጃዎችና ዋቢ ጽሑፎችን በማስተሳሰር ትንተና ቀርቧል፡፡

### 8.1.1 የባህል ሐኪሞች እምነትና ተግባር ለአካባቢ ሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው አበርክቶ

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለባህል መድኃኒት የሚጠቀሟቸውን ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ አዕዋፍ እና ነፍሳትን ከመስክ ሲሰበስቡ መገኛ ቦታቸውን፣ ዓይነትና ዝርያቸውን፣ ጣዕምና ባሕርያቸውን፣ ጥቅምና ጉዳታቸውን ለይተው ሲቀርቡና ሲርቁ፤ ሲተክሉና ሲነቅሉ፤ ሲመርቁና ሲረግሙ ዐውድንና ወቅትን ተከትለው፤ ምልከታና ዝግጅት አድርገው፤ ሥርዓተ ገቢር አሟልተውና አክብረው ዕፅዋት እና እንስሳትን ለባህል መድኃኒት ሲጠቀሙ ዓይነትና ዘራቸው እንዳይጠፉ፤ አገልግሎታቸው እንዳይቋረጥ፤ በማባዛት፣ በማራባት፣ በማሰራጨትና በመከባከብ ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ ልዩ ጥንቃቄ እንደሚደረጉ ሊቀጠበብት አብርሃም እና መሪጌታ ስዩም ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 05/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 04/02/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

ይህን እሳቤ፤ መሪጌታ ስዩም ሲያስረዱ "ዕፅዋትን ለመቅረብና ለመቁረጥ ፀሎት ያስፈልጋል። በእርጋታ አመስግነህና አንግሰህ፤ ቀናቸውን ቆጥረህ፣ የመድኃኒት ጊዜያቸውን ጠብቀህ፤ ቀንበጥና ፍሬያቸውን ብትለቅም፤ ሥራቸውን ቀንሰህ ብትቆርጥ፣ ቅርጫፋቸውን ብትገነጥል አይደርቁም፤ ተመልሰው ያቀጠቅጣሉ [ማቆጥቆጥ]፣ ይስፋፋሉ" ይላሉ። በዚህ ሂደት የዕፅዋት ዓይነትና ዝርያዎች እንዳይጠፉ ጥንቃቄና እንክብካቤ በማድረግ፤ የመሰብሰቢያ፣ የመቁረጫና የመልቀሚያ ዐውዳቸውን በመለየት ዕፅዋትን አክብረውና አንግሰው ከመስክ እንደሚሰበስቡ አስረድተዋል። ከዚህ በተቃራኒ በማንኛውም ወቅት፣ ዐውድ፣ ቀን፣ ዕለትና በጠራራ ፀሐይ ዕፅዋትን መቅረብ፣ መጠጋት፣ መቁረጥና መልቀም በቁማቸው ያደርቃል፤ ዝርያቸውን ያጠፋል፤ በአጋንንት ያስመታል፤ ተብሎ ይታሰባል (ከተቡው አባላት መካከል መሪጌታ ስዩም ያቀረቡት ሃሳብ፤ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን ሁለት)።

መሪጌታ መኅሪና ደብተራ ጥላሁን ደግሞ፤ ዕፅዋት ከሚሰጡት ጥቅምና አገልግሎት አንፃር ልዩ ጥበቃና ጥንቃቄ ሊደረግላቸው እንደሚገባ መክረዋል። በተለይ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ከሌላ ቦታ (ከበረሃ፣ ከወንዝ፣ ከተራራ፣ ከገዳማትና ከችግኝ ጣቢያዎች...) ፍሬና ችግኞቻቸውን ገዝተው፣ ነቅለውና ተውሰው በማምጣት፤ በግቢያቸው፣ በእርሻና በመስኖ ማሳቸው፣ በአካባቢያቸው በሚገኙ አድባራት፣ ገዳማት፣ በሃይማኖታዊ ደብሮች ተክለው፣ በማፅደቅ፤ በማራባትና በማባዛት ዓይነትና ዝርያቸው እንዲቀጥል፤ የሚሰጡት ጥቅምና አገልግሎት እንዳይቋረጥ፤ በማድረግ ዕፅዋት እና እንስሳትን የመጠበቅና የማባዛት፣ የማራባትና የማልማት፣

የማሳደግና የመንከባከብ ዕውቀት፣ ልምድና ተግባር እንዳላቸው ጠቁመዋል (ቃ.መ፤28/01/ 2011 እና 03/03/2011 ሊቦ ከምከም በቅደም ተከተል)።

መሪጌታ አማረ ደግሞ፤ "ጺም የሌለው ቄስ እና ዛፍ የሌለው ቤተክርስቲያን አንድ ናቸው" ይላሉ። የአድባራት፣ የገዳማት፣ የፀበልና የአቢያተ ክርስቲያን ደብር ድምቀት፣ ድባብና ግርማ ሞገስ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳት እንደሆኑ ይመክራሉ። እነዚህ ዕፅዋትና እንስሳት ከሰውና ከቤት እንስሳት ንክኪ ነፃ ሲሆኑ፤ ለመባዛትና ለመራባት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጠርላቸው ጠቁመው፤ ለአካል ቁስልና ለመንፈስ ጭንቀት ፈውስ የሚሆኑ የባህል መድኃኒት ግብዓቶችን ለማግኘት ተመራጭ ቦታዎች እንደሆኑ፤ ይገልፃሉ (ቃ.መ፤26/01/2011 ሊቦ ከምከም)። ቄስ አብርሃም፤ ዕፅዋትን በገዳማት፣ በአድባራት፣ በቤተ ክርስቲያን ደብር መትከል፣ ማሳደግ፣ ማባዛትና ማራባት ሁለት ዓይነት ጥቅም እንዳለው ይመክራሉ። አንድም የፈጣሪ "ፍጥረት" ማደሪያ፣ ማረፊያ፣ ምግብና መጠጥ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ለሕይወት ፍሬና "ለደዌ" ፈውስ የሚሆኑ ዕፅዋትና እንስሳትን አቅፈው መያዛቸው፤ የፈጣሪን ኃይል፣ ቃልና ትእዛዝ ጠብቀው ከሕመም፣ ከስቃይና ከሞት እንደሚታደጓቸው ገልፀዋል (ቃ.መ፤01/05/2011 እብናት)።

በተለይ በአድባራት፣ በገዳማት፣ በፀበል ቦታዎችና በአቢያተ ክርስቲያን ደብር አካባቢ የሚገኙ "እንስሳትን መግደል፤ ዕፅዋትን መቁረጥ አይቻልም ግዝት አለ?፤ በመንፈስ ያስመታሉ፤ ጠባቂ ኃይልና ጦር ሰራዊት አላቸው?" ይላሉ መሪጌታ ፍሬስብሃት። ጠባቂ ኃይል፣ መንፈስና አጋንንትን ለማራቅ ጦር ሰራዊታቸውን ለማስለቀቅ "ግብርና ምሳቸውን" አሟልቶና አቅርቦ፤ ፀሎትና ድግምት አድርሶ፣ የደም ግብር መስዋዕት "ጪዳ" ተብሎ፤ ለምኖና አመስግኖ ዕፅዋት ሲቆርጡና ሲነቀሉ ጠባቂ ኃይልና አጋንንት ይነሳሉ፤ ይርቃሉ፤ ግብራቸው ካልተሟላና ገቢራቸው ካልሰመረ "መናፍስት ቁጡና ቀናተኛ ናቸው፤ ሕሊናን ሰውረው፤ አካልን ሰንክለው፤ ለአደጋና ለመቅሰፍት ይዳርጋሉ" ይላሉ። በዚህ ሂደት ማንኛውም ሰው ዕፅዋት እና እንስሳት የሚገኙበትን ቅጥርና አካባቢ ለይቶ፣ አክብሮ፣ ከቦታው ተጠብቆ ሲኖር፤ ተናካሽና ተናዳፊ እንስሳት ቅጥራቸውን አልፈው፤ ተግባራቸውን ዘንግተው፣ ቦታቸውን ረስተው ሰው እንዳይበሉ፣ እንዳይነክሱ፣ እንዳይነድፉ የቅዱሳን አባቶች ቃልና ግዝት እንዳለባቸው፤ ይመክራሉ። "ዕፅዋትና እንስሳት አመስጋኝና አክባሪያቸውን አይነኩም፤ ካልሄዱባቸው አይመጡም፤ መኖሪያቸውን ስተው አይውጡም" በማለት በዕፅዋት፣ በእንስሳትና በሰው መካከል ያለውን መስተጋብርና ግንኙነት አስረድተዋል (ቃ.መ፤07/03/2011 ሊቦ ከምከም)። ይህ ተግባር የሰው ልጅ የአካባቢውን ሥነ

ምህዳር ጠብቆና አክብሮ እንዴት ተግባብቶና ተስማምቶ መኖር እና መቅረብ እንዳለበት ይመክራል/ ያስረዳል።

መሪጌታ ልሳነወርቅ ደግሞ፤ "ሁሉም ፍጥረት የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ፣ የተዓምሩና የጥበቡ መገለጫ ናቸው፤ ...ያለ ምክንያት የተፈጠረ ነገር የለም" ይላሉ። በተለይ ሴት እንስሳት እርጉዝ እና አጥቢ፣ ግልገልና ጫጩት የመሳሰሉትን መግደል "በሥጋም ሆነ በነፍስ ያስጠይቃል፤ የሰማይ ቤትን ያሳጣል፤... በእድሜ ገፋ ያለውን መርጦ መጠቀም ተገቢ ነው" በማለት ገልፀዋል። ለምሳሌ፡- "ምን ቢቸግር፤ ክበድ [ነፍሰ ጡር] ላም አትታረድም፤ ሁለት ነፍስ ናት" ይላሉ። ግለሰቡ እርጉዝ መሆኗን ሳያውቅ በስህተት እንኳ እርድ ፈጽሞ ሁለት ነፍስ ቢያጠፋ፤ ለነፍስ አባቱ ሄዶ ተናዞና ንስሃ ገብቶ "ፈጣሪ ማረኝ፤ ይቅር በለኝ" በማለት ለሶስት ቀን ሰግዶ "የረከሰ አካልና መንፈሱን" በፀሎትና በፀበል አድሶ፤ ወደ ቀደመ ተግባርና መንፈሱ እንደሚመለስ መክረዋል። ይህ ካልሆነ ባርኮ የሚበላውና ቀድሶ የሚጠጣው ዉኃና ምግብ "የነፍስ አባላ ነው" [የነፍስ ዋጋ ነው፤ የሃጢያት ሥራ ነው] በማለት፤ ጤና እና ሐብት እንደሚያሳጣው ጠቁመዋል። በዚህ ትይዩ ሆን ብሎ በዱር የሚገኙ እንስሳትን መግደል እና ዕፅዋትን መቁረጥ በፈጣሪና አካባቢውን በሚጠብቁ "መናፍስት ያስመታል፤ በቅዱሳን አባቶች ያስረግማል"፤ ተብሎ ይታሰባል (ቃ.መ፤27/04/2011 ሊቦ ከምከም)። ይህ ተግባርና እሳቤ፤ ለሰው ልጅ ሕልውና፣ ለኑሮ ዋስትና፣ ለአካልና ለመንፈሱ ማደሪያ፣ ምግብና መጠጥ የሆኑ፤ ዕፅዋትና እንስሳትን በአግባቡ ለመጠቀም፤ ገደብና ልክን ለይቶ ለመኖር፤ ዕፅዋት ተገቢ ባልሆነ መንገድ "እንዳይጨፈጨፉ"፤ እንስሳት እንዳይገደሉ ለመከላከል፤ የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ሚዛን ለመጠበቅ ጉልህ ድርሻ እንዳለው፤ ይታመናል።

በተመሳሳይ መልኩ መሪጌታ ፋንታሁን (ቃ.መ፤19/01/2011 ፋርጣ)፤ በአካባቢያቸው የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳት "አፍ አውጥተው እንደሰው ባይናገሩ" የፈጣሪን ቃልና ኃይል ተሸክመው፤ ግብራቸውን ጠብቀው፣ ተፈጥሯቸውን አክብረው፣ "በፀሐይና በብርድ ተንገላተው፤ ሕይወት ተሸክመው እንደሰው ይኖራሉ" ይላሉ። የባህል ሐኪሞች ሥራና ምግባር፤ የዕፅዋትና የእንስሳትን አካል አጉድሎ፣ ሕይወት አጥፍቶ መድኃኒት ቀምሞ ለሰው ፈውስ መስጠት ቢሆንም፤ በፀሎትና በልመና፤ በፈጣሪ ኃይልና መንፈስ በመታገዝ ቁስልን የማዳን፣ አጋንንትን የማስወጣትና የማባረር ፀጋ ከፈጣሪ እንደተሰጣቸው፤ ገልፀዋል። "እግዚአብሔር በዕለተ ሰሉስ [በሶስተኛው ቀን ማክሰኞ] ዕፅዋትን ፈጠረ፤ ለምን ቢሉ፤ ለመሬት ልብስ፣ ለእንስሳት ጉርስ [ምግብ] እና መጠለያ ይሁን ብሎ ነው" ይላሉ። ዕፅዋት ለእንስሳት፣ ለአዕዋፍ፣ ለሰውና መሰል ፍጥረት ምግብ፣ መጠለያ

በመሆን የፈጣሪን ፈቃድ ይፈፅማሉ፤ ፍጥረቱን ይቀልባሉ፤ ይመግባሉ፤ ተብሎ ይታመናል። በዚህ እሳቤና እምነት ዕፅዋት በአግባቡ ሲያዙ፤ የፈውስ፣ የኃይል፣ የምግብና የፍጥረት መሰረት እንደሆኑ ይታሰባል። በአንፃሩ በደረሱበት አካባቢ እንስሳትን መግደል፤ ዕፅዋትን መቁረጥ፣ መንቀልና መጣል፤ በጠባቂያቸው አጋንንትና በፈጣሪ ኃይል ያስመታል፤ ያስቀስፋል፤ ተብሎ መታመኑ፤ የአካባቢው ሥነ ምህዳር እንዲጠበቅና እንዲከበር ምክንያት እንደሚሆን ይታሰባል።

መሪጌታ ብሩህ፤ ዕፅዋትን አላግባብ መቁረጥ፣ መንቀልና ማድረቅ፤ ጥብቅ ቦታቸውን ማለፍና መንካት በቅዱሳን አባቶች ያስረግማል፣ በጠባቂ አጋንንት ያስመታል፤ ለከፋ ጉዳት፣ ለሞትና ለስደት ይዳርጋል፤ በማለት የቅርብ ጊዜ ገጠመኛቸውን እንደሚከተለው ዋቢ በማድረግ ገልፀዋል (ቃ.መ፤18/06/2011 ፋርጣ)።

> የዛሬ ዓመት አካባቢ ይሆናል፤ አንድ ጉበዝ፤ እዚህ ማዶ ከሚገኘው አለም ሳጋ ተራራ ሥር ይገባና የክትክታ ዱላ ቆርጦ ይወጣል። ...ይህ ጎበዝ በሕልሙ እንደ ዝንጀሮ እየተመሰለ፣ እንደባብ እየተከተለ፣ እንደውሻ እያባረረ ሲያሮጠው ያድራል። በማግስቱም ሁለት ሶስት ቀን እየመጣ ያስደነግጠዋል። ለአንድ አባት [መንፈሳዊ] ሕልሙን ሲናገር 'ምን ሰርተሃል፤ መንፈስ አድሮብሃል፣ እንደ ዓይነጥላ ይከተልሃል፤ ለሩፋኤል ተሳል' ይሉታል። ...ሁሉንም ነገር ረስቶ ዱላዋ መጠጥ ስትል በሳት ለብልቦ፤ በሞራ አሽቶ ስሙር [ጥሩ/ቆንጆ] ስትሆን፤ ገበያ ይዟት ይወጣል። እህል አቅቶ [ሸጦ] ገበያ ውሎ ሸምቶ ሲመለስ፤ የገነነ [የደነገጠ] በሬ ተኟላው ደርሶ ባስጢሙ ሲተክለው። የሞት ሽረቱን ይነሳና በዛች ዱላ መሃል ግንባሩን ሲመታው፤ ያ በሬ ረብ ይላል።... ሰውዬው ታሽቶ በመከራ ይድናል። የበሬው ባለቤት አማላጅ ልኮ በሽማግሌ ታርቀው ችግሩ ይፈታል።... አፍታም ሳይቆይ የወንድሙ ልጅ ተሰዎች ተጣልቶ ሊገላግል ሲገባ፤ ተደርብሃል ብለው በሽመል ሲጠምዱት፤ ...በእጁ የሰው ነፍስ ጠፋ። አሁን በሕግ ተይዞ ተፈርዶበት እስር ቤት ይገኛል። ...ቤተሰብ ተበተነ፤... ዘመዶቹ አንድ አይናማ [ጠንቋይ] ቤት ሄደው ሲያስጠይቁ። 'በያዘው ዱላ ላይ ደም የጠማው ጋኔል ሰፍሯል። ወደ ቦታው ይመልስ።... መመለሻው [ግብሩ] በጥር ሚካኤል ዕለት ነጭ ጫጩት እና ጥቁር ጠቦት ፍየል አርዶ ጭዳ ይበል። ማሩኝ ብሎ ለሩፋኤል ስለት ያስገባ' ተብሎ ተነገረ። ...አገር ተሚፈራው አድባርና ተራራ ዕፅ ቆርጦ መያዝ ምን ይሉታል። ተራሱ አልፎ ለቤተሰቡ መከራ ሁነ።

በማለት መሪጌታ ብሩህ ገልፀዋል። ከዚህ መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው፤ ማኅበረሰቡ በአካባቢው የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳትን አክብሮ ለመኖር፤ ለመቅረብና ለመጠቀም ፈቃድና ክልከላ እንዳለ ይገልፃል። ይህን ተግባርና ገደብ ማለፍ ደግሞ ለችግር፣ ለጉዳት፣ ለቅጣት፣ ለሕመም፣ ለስቃይና ለሞት እንደሚዳረግ ይተርካል። በዚህ ገለፃና መረጃ ማኅበረሰቡ የአካባቢውን ሥነ ምህዳር እንዴት አክብሮና ጠብቆ መያዝ እንዳለበት፤ "ከዚህ ነገር ተጠበቁ፤ ይህን ነገር አድርጉ" በማለት፣

"በመርገም/በመገዘት" ሰው ከአካባቢው ሥነ ምህዳር ጋር ተስማምቶ እንዲኖር፤ ፈቃድና ገደቡን፤ ፈውስና "መቅሰፍቱን"፣ "ሰናይና ዕኩይ ምግባሩን" ለይቶ፤ የአካባቢውን ፍጥረት አክብሮ፣ ጠብቆ፣ ተግባብቶና ተናቦ (ወቅትና ጊዜን ጠብቆ መንቀሳቀስ) የመኖር ብልኀትን፤ ይገልፃል/ ይመክራል።

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች፤ የአካባቢያቸውን ሥነ ምህዳር ለመጠበቅና ለመጠቀም፤ ከዕፅዋትና እንስሳት የሚያገኙት ግብዓት፣ አግልግሎትና ጥቅም እንዳይቋረጥ፤ ዓይነትና ዝርያቸው እንዳይጠፋ፤ በግቢያቸው፣ በእርሻና በመስኖ ማሳቸው ዕፅዋትን በመትከል በማባዛት፣ በማሰራጨት፣ በመከባከብና በማሳደግ ጉልህ ሚና እንዳላቸው፤ ከመስክ ምልከታና ገለጻ መገንዘብ ተችሏል። በተለይ ልማዳዊ፣ አምልኳዊ፣ ሃይማኖታዊና መሰል ሁነቶችን በመጥራትና በመፍራት፤ ለሥርዓተ ገቢሩ፣ ለፈቃድና "ግዝቱ" ታዛዥና ተገዢ በመሆን በልዩ ጥንቃቄ፣ ተግባር፣ ዕውቀትና ሥርዓት በመመራት ዕፅዋትና እንስሳትን እንዴት መቅረብና መራቅ፤ መጠቀምና መንከባከብ እንዳለባቸው፤ መክረዋል (ከተቡው አባላት መካከል መሪጌታ ስዩም፣ ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)።

ይህን ተግባር፤ ከሃይማኖቱና ከእምነቱ መመሪያ በተለየ መልኩ ሲታይ፤ ዕፅዋት እና እንስሳት ሙያ በሌላቸው ግለሰቦች እንዳይሰበሰቡ፣ እንዳይቆረጡ፣ እንዳይነቀሉ፣ ከአካባቢው እንዳይጠፉና ጉዳት እንዳይደርስባቸው፤ ሥርዓተ ገቢሩ ለዕፅዋት ጥበቃ፤ ለአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር ደህንነት፣ ትስስርና አበርክቶ እንዳለው፤ መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ሥርዓትና መመሪያ ማኅበረሰቡ የአካባቢውን ሁነትና ሥነ ምህዳር ይጠብቃል፣ ይማራል። ልማድና ገደቡን ቢጥስ፤ እምነታዊና ሃይማኖታዊ ተግባራት ቢቀሩ ዕፅዋት ይጠፋሉ፤ እንስሳትና አዕዋፍ ይሞታሉ፤ ይሰደዳሉ። በሂደት የአካባቢው ሥነ ምህዳር ይመናመናል፣ ይረበሻል፣ ይዛባል፣ ይራቆታል ተብሎ ይታመናል።

ደብተራ መልኩ እና አቶ ደርሶ፤ በአካባቢያቸው ጥብቅ የደን ቦታዎች፣ በአድባራትና ገዳማት ውስጥ የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳት ባልታወቁ ሰዎች እንዳይቆረጡና እንዳይገደሉ ክልከላና ጥበቃ በማድረግ፤ ከተፈጥሮ ጥበቃ ባለሙያዎች ጋር አብረው እንደሚሰሩ ገልፀዋል። ዕፅዋትን በብዛት ቆርጠው ከቦታ ቦታ የሚያንቀሳቅሱ ሰዎች የመንግስት ፈቃድ ከሌላቸው በሕግ ተይዘው እንደሚጠየቁ ጠቁመዋል። የባህል ሐኪሞች በየደብራቸው የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳትን ጠብቀው በመያዝ እና መርጠው በመጠቀም፤ ለባህል መድኃኒት ተፈላጊ ዕፅዋትን ከሌላ ቦታ ከሚገኙ የባህል ሐኪሞች ገዝተውና ተውሰው፤ ከበረሃ፣ ከተራራ፣ ከአድባራትና ከገዳማት ቦታዎች

ሰብስበው ጥብቅ በሚባሉ አካባቢዎች ዘርተው፣ ተክለውና አፅድቀው እንደሚጠቀሙ አስረድተዋል፡፡ ለባህል ሕክምና የሚያገለግሉ ዕፅዋት በብዛት የሚበቅሉበት ቦታ ከሰውና ከቤት እንስሳት የተለየና የተሰወረ ድንግል መሬት መሆን እንዳለበት መክረዋል (ቃ.መ፤ 01/03/2011 ፋርጣ እና 03/02/2011 እብናት)፡፡

የደቡብ ጎንደር ዞን የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ መልካሙ፤ በዞኑ የተፈጥሮ ሐብት በብዛት የሚገኙባቸው አካባቢዎች፤ ከእርሻ፣ ከሰውና ከቤት እንስሳት ንክኪ የተከለሉ ጥብቅ ፓርኮች፣ ገዳማት፣ አድባራት፣ የሃይማኖት እና የፀበል ቦታዎች፣ ታሪካዊ የመስሕብ መዳረሻዎች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ በነዚህ አካባቢ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች አካባቢውን በመጠበቅ፣ ዕፅዋትን በመትከልና በማልማት ከማኅበረሰቡ በተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው ጠቁመው፤ ከችግኝ ጣቢያዎች አገር በቀል የሚባሉ ዕፅዋትን ወስደው በግላቸው እንደሚያለሙ መክረዋል፡፡ እነዚህ ሐኪሞች በአካባቢው የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳትን ከጥብቅ ፓርኮችና ገዳማት ሰብስበው ጉዳት በማያደርስ መልኩ እንደሚጠቀሙ፤ ፓርኮችን ከሚጠብቁ የአካባቢው ሚኒሻዎችና የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች ጋር ግንኙነት ፈጥረውና ተባብረው አካባቢውን እንደሚጠብቁ፤ አስረድተዋል (ቃ.መ፤17/04/2011 ደብረ ታቦር)፡፡

በፋርጣ ወረዳ የባህል ሐኪሞች ማኅበር ሊቀመንበር የሆኑት መሪጌታ ፋንታሁን ከረጅም ጊዜ ጥያቄ፣ ጉትጎታና እንግልት በኋላ ከሁለት ዓመት ወዲህ ከወረዳው አስተዳደር መሬት ተረክበው፤ የማኅበሩ አባላት ለባህል መድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ከተለያየ አካባቢ ሰብስበው መትከልና ማልማት መጀመራቸውን ገልፀዋል፡፡ ዕፅዋት ከቤት እንስሳትና ከሰው ተጠብቀውና ተለይተው ካልተያዙ ልፋቱ ከንቱ መሆኑን ጠቁመው፤ ለማኅበሩ የተሰጠውን መሬት ከልሎና አጥሮ ጥቅም ላይ ለማዋል ጅምር ሥራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በማንኛውም ቦታና አካባቢ የማይገኙ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዕፅዋትን በገዳማት፣ በተራራና በጥብቅ ደኖች፣ በአድባራት አካባቢ ከሰው ተሰውረው እንደሚተክሉና እንደሚያፀድቁ ገልፀዋል፡፡ በዚህ ዘመን የባህል ሐኪሞች ፈቃድ አውጥተው ዕፅዋትን አልምተው፣ አሳድገውና ተንከባክበው በጋራ የሚጠቀሙበት አመራጭ የተሰጠ ቢሆንም፤ የማኅበሩ አቅም እስከሚጠናከር፤ ከመንግስት ድጋፍ፣ ክትትልና ጥበቃ ከሌለው ቦታ መውሰድ ብቻውን ዋስትና አለመሆኑን አሳስበዋል፡፡ አሁን ባለው ሂደትና ሁነት ከአድባራት፣ ከገዳማት፣ ከችግኝ ጣቢያ የሰበሰቧቸውን ከሃምሳ በላይ ዕፅዋት ተክለውና አጥረው እያለሙና እያሳደጉ እንደሚገኙ አስረድተዋል (ቃ.መ፤19/01/2011 ፋርጣ)፡፡

በእብናት ወረዳ የሚገኙት መሪጌታ ስዩም ሁለት መቶ የሚሆኑ ዕፅዋትን ከተለያዩ ቦታዎች ሰብስበው ለማልማት ከሃያ ዓመት በፊት ወረዳውን መሬት ጠይቀው እንደነበር በማስታወስ፤ "ሰሚና ተቀባይ" ሲያጡ በግቢያቸው፣ በመስኖ ማሳቸው፣ በአድባራትና በደብር ቦታዎች ቋሚ ዕፅዋትን ተክለው፤ ፍሬና ዘራቸውን በትነው እንደሚጠቀሙ፤ ገልፀዋል። በመስክ ምልከታና ቃለ ምልልስ ወቅት ከሰው ተውሰው፣ ከበረሃ፣ ከወንዝና ከገዳማት የሚገኙ የዛፍና የሃረግ ዕፅ ዓይነቶችን አሰባስበው፤ በግቢያቸው ተክለው፣ አሳድገውና ተንከባክበው ያለሟቸውን ዕፅዋት፤ ለጥናት አቅራቢው አስጎብኚተዋል (የመስክ ምልከታ፤04/02/2011 እብናት)። እነዚህ ዕፅዋት በወቅት፣ በዓመትና በዘመን ሂደት ዓይነታቸው እየጠፉ፤ ቁጥራቸው እየቀነሰ መሄዱን ጠቁመው፤ በግቢያቸው የሚገኙ ዕፅዋት ከአካባቢው የተለዩ መሆኑን ለማጤን ተችሏል (ቃ.መ፤04/02/2011 እብናት)። በእብናት ወረዳ የባህል ሐኪሞች ተወካይና ሊቀመንበር አቶ ደርሶ፤ በቅርቡ ከወረዳው አስተዳደር መሬት ወስደው በአካባቢያቸው የማይገኙ ዕፅዋትን አልምተው፣ አሳድገውና አባዝተው ለመጠቀም እቅድና ዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል (ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደርሶ ያቀረቡት ሃሳብ፣ ቃ.መ፤23/06/2011 እብናት)።

በአጠቃላይ የባህል ሐኪሞች፤ የዕፅዋትን ባሕርይ ለይተው፣ ወቅትን ጠብቀው፣ ዐውድን መነሻ አድርገው፣ ዕለትን አክብረው፣ ቦታና ጊዜን መርጠው፣ ፀሎት አድርሰው፣ ከሰው ተሰውረው በምስጢር ዕፅዋት እና እንስሳትን ለመድኃኒት መጠቀማቸው፤ ዕፅዋትን በግቢያቸው፣ በእርሻ፣ በአካባቢያቸውና በመስኖ ማሳቸው፣ በገዳማት፣ በደብርና መሰል ጥብቅ ቦታዎች በመዝራት፣ በመትከል፣ በማፅደቅ፣ በመጠበቅና በማራባት ለአገልግሎት ማዋላቸው፤ ዕፅዋት ለመድኃኒት አገልግሎት ሲደርሱ ቅጠል፣ ፍሬ፣ አበባ፣ ቅርንጫፍ፣ ሥር እና መሰል አካላቸውን ሲጠቀሙ እንዴት መቆፈር፣ መቁረጥ፣ መልቀም እንዳለባቸው፤ ለቀጣይ አገልግሎት የማዘጋጀት ብልኀትን መጠቀማቸውና መተግበራቸው፤ ዕፅዋትና እንስሳት "ጠባቂ ኃይልና መንፈስ አላቸው" የሚሉ እምነታዊና ሚታዊ ተረኮችን ማመናቸው፤ በአድባራት፣ በገዳማት፣ በፀበልና በሃይማኖት ደብሮች፣ በመንግስት ፓርኮች የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳት ከሌላ አካባቢ በሚመጡ ሰዎች እንዳይቆረጡና እንዳይገደሉ ከተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎችና ከአካባቢው ጠባቂ ሚኒሻዎች ጋር ተባብረው መስራታቸው፤ የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ለመጠበቅና ለመንከባከብ ጉልህ አበርክቶ እንዳላቸው፤ የመስክ መረጃዎችና ምሁራን ጠቁመዋል (Brady, 2001: Wondwosen, 2006: Bodeker, 2010)።

ከዚህ አንፃር የባህል ሐኪሞች እምነትና ተግባር፣ ሚታዊ ተረኮች፣ የማኅበረሰብ ልማድ፤ ሰውን ከአካባቢው ሁነት ጋር ለማስታረቅ፣ ለማስማማት፣ ለማግባባት፣ ለማገናኘትና ለመነጠል፤ ሥርዓት ለመትከልና ለመንቀል፤ ሚታዊ ተረኮችና አምልኳዊ ሥርዓቶች ሚና እንዳላቸው ምሁራን ይጠቁማሉ (Sims and Stephens, 2005; Steward; 2006, PP.5-6)። “ሚት” ደግሞ፤ በእንቆቅልሽ ለተሞላው ዓለም፤ በአይ-አዎ መሀል ለሚዋልለው፣ ተፈጥሮን ከባህሉ፣ ደመነፍሱን ከህሊናው… አስታርቆና አስማምቶ ማኖር ለተሳነው የሰው ልጅ ልቡና ማስታረቂያ መንገድና የ“ሕክምና” ይዘት እንዳላቸው ቴዎድሮስ ይገልፃሉ (2001፣ ገገ.74-75)። በዚህ ሁነት ሰው ከአካባቢው ሥነ ምህዳር ጋር ተላምዶና ተግባብቶ ለመኖር፤ ልማዳዊ ተግባራት፣ የባህል ሐኪሞች እምነት፣ ዕውቀትና ተግባር አስተዋፅኦና አበርክቶ እንዳላቸው፤ ይታሰባል።

### 8.1.2 የማኅበረሰብ ልማድ ለአካባቢ ሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው አበርክቶ

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ ልማድ ጥብቅ ደንኖች (ፓርኮች)፤ አድባራትና ገዳማት፤ ተራራ እና የፀበል ቦታ፣ የመቃብር ስፍራ እና የቤተክርስቲያን ደብር፤ ለዕፅዋትና ለእንስሳት መገኛ፣ መራቢያ፣ መጠለያ፣ ምንጭ ተደርገው እንደሚታሰቡ በማኅበረሰቡና በምሁራን ጥናቶች ተዘግቧል (Pankhurst, 1976: Fassil, 2001)።

**አድባራት (ቆሌ)፡-** የአካባቢው ማኅበረሰብ የእለት እንቅስቃሴያቸውን ከአድባር ጋር በማገናኘት "አድባር ትጠብቅህ! በሰላም አድርሳ ትመልስህ! ጤናውን ትስጥህ!" በማለት ይመርቃሉ። በማኅበረሰቡ እምነት “አድባራት/ቆሌዎች” በሴት መንፈስና ጾታ ቢጠሩም፤ አልፎ አልፎ በወንድ መንፈስ የሚጠሩ ቦታዎች እንዳሉ ወ/ሮ ጠጂ ገልፀዋል (ቃ.መ፤28/06/2011 እብናት)። የሰፈር አድባር የሰው እና የእንስሳት ጠባቂ፣ ለሕሙማን ፈውስ፣ ለነፍሰጡር እናቶች አማላጅ፣ ለአካባቢው ሰላም እና ደህንነት፣ ለሐብት ንብረት መጠበቅ፣ ከድንገተኛ ተውሳክና በሽታ ለመሰወር፣ ምህረት ለማውረድ መንፈሳዊ/መለኮታዊ ኃይል እንዳላት ይታመናል። ከዚህ አንጻር የሰፈር አድባር/ቆሌ ማደሪያ፣ መቆያና ማረፊያ በዋናነት ዛፍ፣ ወንዝ፣ ተራራ፣ ዋሻ ቦታዎች እንደሆኑ ይጠቀሳል። በአድባር ቦታና ክልል ውስጥ የሚገኙ ዕፅዋት አይቆረጡም፣ እንስሳት፣ አዕዋፍና ነፍሳት አይገደሉም፤ ለምን? ሲባል "የመንፈስ ማደሪያ ናቸው" ይባላል፤ ዕፅዋት ቢቆረጡ፣ እንስሳት ቢገደሉ፤ የሰፈር አድባር/ቆሌ ተቆጥታ በሽታ ታወርዳለች፤ መቅሰፍት ትልካለች፤ ሐብትና ንብረት ታወድማለች፤ ሰላምና ጤና ትነሳለች ብለው እንደሚያስቡ (ከተቡው

አባላት መካከል እማሆይ ማርሸት ፣ቃ.መ፤ 19/06/2011 ፋርጣ ቡድን አራት) መረጃ ሰጪዎች ጠቁመዋል፡፡

አድባር ወይም "ቆሌ" የቤት እና የሰፈር ጠባቂ ተደርገው ይታመናሉ (ወ/ሮ ጀማነሽ፣ ቃ.መ፤ 21/06/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላትም "አድባር" የሚለውን ቃል "ብዙን ጊዜ በሴት የምትጠራ የመንፈስ አይነት ወይም ቆሌ፤ የአካባቢው ቆሌ ወይም መንፈስ የሚኖርበት ነው በሚል እምነት ሰዎች ቅቤ በመቀባት፣ ቡና በማፍላት፣... የሚያከብሩትና አምልኮ የሚያደርጉበት ዛፍ፣ ድንጋይ፣..." ነው (1993፤ ገ.464) በማለት ተተርጉሚል፡፡

የአድባር ሥርዓት የሚከበርባቸው ቦታዎች በዋናነት የዉኃ ምንጭ፣ ዛፍ እና ተራራማ ቦታዎች ሲሆኑ የመንፈሱ/ዋ ማረፍያና ማደሪያ ዛፎች፤ ዋርካ፣ ሾላ፣ ዋንዛ፣ ግራር፣ አስታ፣ ቀረሮ፣ ጽድ፤... ያሉባቸው ቦታዎች ይመረጣሉ፡፡ እነዚህ ዛፎች በሌሉበት ቦታ ወይም ባህር ዛፍ ፣ ብሣና፣ ኮሶ እና ቁጥቋጦ ቦታዎች ለአድባር መውጫና ማረፊያ ቦታ አይመረጡም፤ አይከለሉም፡፡ ለምን? ሲባል አንድም ባህር ዛፍ (መጤ እና የባሕር ማዶ ዛፍ መሆኑን በማሰብ)፤ ብሣና እና ኮሶ፤ ጠረናቸው፣ ሽታና ጣዕማቸው፤ የማቃጠል፤ የመለብለብ፣ የማንገብገብ እና የመሰንፈጥ ባሕርይን አላቸው፡፡ እነዚህ ዕፅዋት የአጋንንት ማናገሪያ፣ ማስለፍለፊያ፣ ማስወጫ እና ማባረሪያ ዕፀ ስለሆኑ ለአድባር ቦታና ማረፊያ አይመረጡም፤ በማለት ያስረዳሉ (መሪጌታ ልሳነ ወርቅ፣ ቃ.መ፤ 27/04/2011 ሊቦ ከምከም)፡፡ ለምን? ሲባል አድባር ጥሩ ሽታ፣ ጠረንና መዓዛ ያላቸውን "እረጃጅም" ዛፎችን መርጠው መስፈሪያና መኖሪያ እንደሚያደርጉ ይታመናል፡፡

አድባር ሲባል ከቤት ቆሌ ጀምሮ፣ በግቢ፣ በሰፈር/በቀጣና፣ በቀበሌ፣ በወረዳና በዞን ደረጃ የሚደርስ የግዛት ቦታ እና የማስተዳደር ሥልጣን እንዳላቸው የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት ይጠቁማሉ፡፡ የቤት፣ የግቢ፣ የሰፈር፣ የወንዝ እና የቀበሌ ቦታና ክልሎች በዋናነት በሴት መናፍስት ወይም ቆሌዎች እንደሚጠበቁ (እንደሚተዳደሩ)፤ የወረዳ እና ዞን ክልል ቦታዎች ደግሞ በወንድ ጾታ የሚጠሩ መናፍስት "በትላልቅ ኮረብታ ቦታዎች፣ ተራራ፣ ደን፣ በርሃ እና ወንዞችን፤ ያስተዳድራሉ" ተብሎ ይታሰባል፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ቦታው ላይ በመሰባሰብ ሥርዓቱን እንደሚፈጽሙ ያስረዳሉ (ደብተራ መኳሪ፣ቃ.መ፤ 13/03/2011 እብናት)፡፡ ለአድባር የተመረጡ ቦታዎች፤ ከቤት እንስሳት ንክኪ የራቁ፣ ከፍተኛ ጥበቃ፣ ጥንቃቄና እንክብካቤ በአካባቢው ማኅበረሰብ ይደረግላቸዋል፡፡ ከዚህ ቦታና አካባቢ፤ እንጨት መልቀም፣ ዛፍ መቁረጥ፣ ሣር ማጨድ፣ ከብት ማሰማራት፣ የወደቁ ዛፎችን ለቅሞ

መሄድና መሸጥ፣ ዓይነ ምድር መውጣት/መጣል፣ በአድባር መቀለድ… ለመቅሰፍትና ለከፋ ሕመም ይዳርጋሉ፤ ተብሎ ይታመናል (ከተቡው አባላት መካከል ግራጌታ ወንድማገኝ፣ቃ.መ፤ 19/06/2011 ፋርጣ) ፡፡

ወ/ሮ ጠጁ፤ ለቤት ቆሌ ወይም ለሰፈር አድባር በቀን አንድ ጊዜ ቡና ማፍላት፣ እጣን ማጨስ፣ ቁርስና "ሰደቃ" ማዘጋጀትና "መፈንጠቅ" [ከተዘጋጀው ቡና ቁርስ ቆንጥሮ መጣል]፣ አቦል ቡና በመውጫ በር "ደፍ" [መረማመጃ ቦታ] ላይ "ጠብ" ማድረግና መርጨት፤ ከጎኑ እጣን ማጨስን፤ ጤና፣ ሐብት፣ በረከት እንድትሰጣቸው መለመን፤ ከብት፣ ልጅ፣ "አባወራ"፣ እንስሳት በሰላም ወጥተው፤ በደህና እንዲመለሱ፤ መማፀንና መለማመን የዕለት ተግባርና የሰፈር ቆሌን እንደሚመለከት ገልፀዋል፡፡ በእብናት ወረዳ "አባ ዝንጀር" በሚባል ተራራ (በመንፈሱ ስም የሚጠራ ተራራ) እና በሊቦ ከምከም ደግሞ በርብ ወንዝ "አባ ወርቄ" የሚባሉ ሁለት መናፍስት ወረዳውን ያስተዳድራሉ ተብሎ ይታሰባል (ወ/ሮ ጠጁ፣ቃ.መ፤ 28/06/2011 እብናት)፡፡ ይህን ሃሳብ ለማጠናከር የሚከተለውን አስረጂና ትረካ ልብ ይሏል፡፡

## አስረጅ አንድ፡- የዋርካ ዛፍ (አድባር) እና መናፍስትን የማገናኘት ልማድ

"ዋርካን እስከ ሥሩ መንቀል ዘር ይነቅላል፤ በዋርካ ሥር መተኛት ጋኔል ያስመታል፤ ነባር ዋርካ ሲወድቅ በአካባቢው ትልቅ ሰው ይሞታል፣ መንግስት ይገለበጣል፣ ሹም ሽር ይመጣል" ተብሎ ይፈራል፡፡ በእብናት ወረዳ ደጋ መልዛ ቀበሌ፤ "አባ ዝንጀር" በሚባል ተራራ ላይ ትልቅ ዋርካ ይገኛል፡፡ "አባ ዝንጀር" በወረዳው ከሚገኙ ተራራማ ቦታዎች ትልቁ ተራራ ሲሆን፤ "የአባ ዝንጀር መንፈስ መኖሪያ ነው" ተብሎ በአካባቢው ማኅበረሰብ ይታመናል (ወ/ሮ ጠጁ፣ ቃ.መ፤ 28/06/2011 እብናት)፡፡ በዚህ ቦታ በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ጥር ወይም ሰኔ ሚካኤል፤ ለአድባር ሰደቃ የሚሆን ምግብና መጠጥ ሰርተውና አዘጋጅተው፤ ይወጣሉ፡፡ አባ ዝንጀር "ለመስዋዕት የሚፈልጋትን ጊደር በራዕይ ወይም በሕልም ለሽማግሌዎች መርጦ ያሳያል"፤ የተመረጠችውን  ጊደር ዋጋ አገር አዋጥቶ ግምትና ገንዘቡ ለባለቤቱ ተከፍሎ እንዳበቃ "መንፈሱ ይዟት ይመጣል…" ተብሎ እንደሚታመን አቶ ደርሶ ገልጸዋል (03/02/2011 እብናት)፡፡

መሪጌታ ስዩም፤ በዕርዱ እለት፤ ለመስዋዕት የቀረበችው ጊደር "መንፈሱ በዋርካው ሥር እግሯን ቆልፎ፣ አንገቷን ዘርግታ እንድትተኛ ያደርጋታል" ይላሉ፡፡ የጊደሯ እግር በገመድ አይታሰርም፣ ቀንድና እግሯ በሰው አይያዝም፤ በተኛችበት እንደ እንቅልፍ ስታሸልብ፤ መንፈሱን የሚያናግሩና

የሚያቋድሱ ሶስት ሰዎች ባርከው፤ ደሙን አቋድሰው፤ ቡና አፍልተው፣ አረቄ፣ ቂጣ፣ ኑግ፣ ቆሎና ንፍሮ ጨምረው፤... የዕለቱን ሥርዓት በዋርካው ዙሪያ ይፈጽማሉ (መሪጌታ ስዩም፣ ቃ.መ፤ 04/02/2011 እብናት[109])።

ለአድባር የወጣው ሰው፤ የቀረበውን ሥጋ እዛው ጠብሶና በልቶ፤ ቡና አፍልቶና ጠጥቶ፤ ዛር ያለበት አጉርቶ፣ ተለምኖ፤... አገር፣ ወገንና ሰፈር ተመርቆ፤ "...ለልጆች ጤና ለከብቶች አማን አድርግልን፣ ዕፅዋትና እንስሳቱን ጠብቅልን፣ ዝናቡን ከደጃችን፤... ምርቱን ከጎተራ አታሳጣን፤... ከበሽታና ከመከራ ጠብቀን..." እየተባለ (አቶ ደርሶ፣ ቃ.መ፤03/02/2011 እብናት) ፀሎት ተደርጎ ሥርዓቱ ሲጠናቀቅ፤ ለአድባር የወጣው ሰው ወደ ቤቱ ይመለሳል። በአድባር ቦታ የሚተርፍ ምግብና መጠጥ ወደ ቤት "አይሄድም፣ አይገባም፤ ቢተርፍ እንኳ እዛው ይደፋል፤ ይቀበራል"፤ በስህተት የአድባር ምግብ ወደ ቤት ቢመጣና ቢገባ "በሽታና መቅሰፍት ይዞ ይገባል"፤ ተብሎ ይፈራል (ወ/ሮ ጠጂ፣ ቃ.መ፤ 28/06 /2011 እብናት)።

አቶ መኮንን ደግሞ፤ "በአባ ዝንጀር የተከበረ ቦታ ነው" ይላሉ። በዚህ አካባቢ የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳት ከሰውና ከቤት እንስሳት የራቁ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ዕፅዋት እንዳይቆረጡ፤ እንስሳት እንዳይገደሉ የአባ ዝንጀር መንፈስ ይጠብቃቸዋል፤ ተብሎ እንደሚታሰብ አስረድተዋል። እንስሳቱም፤ ከሚኖሩበት አካባቢ ወጥተው የገበሬውን ከብትና ፍየሎች እንዳይበሉ፤ "ግዝት አለባቸው" ተብሎ እንደሚነገር ገልፀዋል (ቃ.መ፤20/04/2011 እብናት)።

መሪጌታ ስዩም፤ በ2009 ዓ.ም ከጎንደር ሃገረ ስብከት የተላኩ አባት "አባ ዝንጀር እና አባ ወርቄን" አታምልኩ፤ ብለው ሰውና ደብሩን ገዝተው እንደሄዱ ይገልፃሉ። በዚህ ዓመት ግብርና ሰደቃው ሲቋረጥ አባ ዝንጀር ከብቱን በርሃብና በወረርሽኝ ፈጀው፤ በአገር ላይ መከራ ወረደ፤ አዝመራውን በቁሙ ተባይ በላው፤ "በረድ" [በረዶ] መታው፤ የሚታፈስና የሚቀመስ ሲጠፋ ሕዝቡ "እግዚኦ ምህረት አውርድልን" እያለ በየደብሩ መለመን ጀመረ፤ የአካባቢው አባቶችና ትንቢት ተናጋሪዎች "አባ ዝንጀር ተቆጥቶ ነው፤ ሰደቃና ዕርዱ ከቀረ፤ ሕዝቡ እርስ በርሱ ይባላል፤ ርሃብ ይገባል፤...እንስሳት ያልቃሉ፤ ዕፅዋት ይደርቃሉ" ተብሎ ሲነገር ሕዝቡ ለሁለት ሃሳብ ተከፈለ፤ ይላሉ መሪጌታ ስዩም (ቃ.መ፤04/02/2011 እብናት)።

---

[109]መሪጌታ ስዩም የወንዝ ጅን በመጥራት፣ በመሳብ፣ ባሕር ጠልቀው በመውጣትና በማናገር፤ የአድባር መናፍስትን በማቋደስና በመለመን፤ ጭዳ በመስጠት እና በባህል ሕክምና ተግባር፤ በአካባቢውና በአገሩ የታወቁ፤ የተከበሩ፣ የአግር ሽማግሌና አስታራቂ አባት፤ እንደሆኑ በተቡው አባላት ተደጋግሞ ተጠቁሟል (ከተቡው አባላት የአቶ ደርሶና የቄስ አብርሃም ሃሳብ፤ ቃ.መ፤23/06/2011 እብናት ቡድን አንድ)። ለዚህ ጥናት መሪጌታ ስዩም ቁልፍ መረጃ ሰጪ መሆናቸውን ልብ ይሏል።

የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሰዎች ሕዝቡ እንዳይወጣ በየደብሩ መገዘታቸውን ቢቀጥሉም፤ በ2010 ዓ.ም በሰኔ ሚካኤል ዕለት የተወሰኑ ሰዎች ተሰባስበው ቦታው ላይ ደርሰው ሥርዓቱን ሲያከብሩ፤ በአካባቢው የሚገኝ የደብር አስተዳዳሪ ቄስ ሄዶ ሥርዓቱን እንዲያቆሙ "ገዘቶ" ሲመለስ "ልቡነ ነስቶ፤ እራሱን አዙሮ ገደል ሰደደው፤ እግሩ ተሰብሮ ለሶስት ወር ሲማቅቅ ቆይቶ አንደበቱ ተዘግቶ በቅርቡ ዐረፈ፤ ከብትና ፍየሎቹ እያበዱ አገር አምሰው ሲሞቱ… ቤተሰቡ ፈራ፡፡ …ወዳኛ ግባልነ፣ አስታርቀነ፣ ለምንልነ ብለው ይዘውኛል" በማለት መሪጌታ ስዩም ገልፀዋል (ቃ.መ፤04/02/2011 እብናት)፡፡ የአባ ዝንጀር ቁጣና ቅጣት "ክፉ ነው፤ ምህረት የለውም" ተብሎ ይፈራል፡፡ ከዚህ በታች የዕርድ መስዋዕት የሚቀርብበት ዋርካና አድባር እንደሚከተለው በፎቶ ግራፍ ቀርቧል፡፡

ፎቶ ግራፍ 11፡- የዕርድ መስዋዕት የሚቀርብበት የዋርካ ዛፍ ፎቶ



ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ በቀን 24/06/2011 ዓ.ም የተነሳ

ይህ ዋርካ፣ "አራት ትውልድ ያሳለፈ፣ አካባቢውን የሚጠብቅ መንፈስ መኖሪያ ቦታ ነው"፣ ተብሎ ይታመናል፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ በዛፉ አካባቢ ሲያልፍ “በደህና አድርሰህ፤ በሰላም መልሰኝ” በማለት ትንሽ ድንጋይና የቁጥቋጦ ይዘት ያላቸውን ዕፅዋት በመቁረጥ በዛፉ

ስር አስቀምጠውና ድንጋይ ጭነው ያልፋሉ። በዚህ ዛፍ ስር እንቅልፍ መተኛት፣ ዓይነ ምድር መውጣት፣ ሩካቤ ሥጋ መፈፀም... ያስቀስፋል፤ በአጋንንት ያስመታል፤ ይባላል (መሪጌታ መንግስቴ፣ ቃ.መ፤10/03/2011 እብናት)፡፡ በዛፉ አካባቢ በቀንም ሆነ በማታ "ሴት ልጅ ብቻዋን አታልፍም፤ መንፈሱ ያስደነግጣታል" ተብሎ ይፈራል፡፡ በወረዳው፤ ወረርሽን ሲከሰት፤ ዝናብ ሲጠፋና ድርቅ ሲመጣ፣ ተባይ ሲፈጠር የአካባቢው ማኀበረሰብ በአንድነት ተሰብስበው "ምህረቱን አውርድልን" በማለት ይማፀናሉ፡፡ ምህረቱንም እንደሚያወርድላቸው ያምናሉ፡፡ የዋርካዉ አንድ አካል ወይም ዝንጣፊ ቢወድቅ/ቢገነጠል፤ ትልቅ ሰው ይሞታል ተብሎ እንደሚታመን የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ አቶ አዲሱ ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 25/06/2011 እብናት)፡፡

በማኅበረሰብ ልማድ አስተዳደር መዋቅር እና ሥርዓት "አድባር እና ቆሌ" ለአካባቢ ሥነ ምህዳር ጥበቃ፣ ለማኅበራዊ መረጋጋት፤ ለሥነ ልቡናዊ እርካታ፣ ለመቀራረብና ማኅበራዊ ችግርን ለመፍታት፤ ተቀራራቢ አመለካከትና አኗኗር ልማድን ለመጋራት፤ ለሥነ ተፈጥሮ የአለን እሳቤ ለመጠቀም፤ ለዓለም እና ለሕይወት የአለን አመለካከት ለመገንዘብ፤ የጋራ እሴት ለመቅረጽ፤ የአካባቢ ሥነ ምህዳር ተፅእኖዎችን ለመቋቋም እና ለመላመድ፤ የግለሰብ፣ የቡድንና የማኅበረሰብ የጤና እክሎችን ለመፍታት እና መፍትሔ ለመሻት ሲባል መለኮታዊ ተግባራትን እንደሚፈጽሙ፤ ምሁራን ይጠቁማሉ (Pereira and Dein,1995፡ Sims and Stephens, 2005; Winkelman, 2009)። ይህ ተግባርና እሳቤ ሰው ከአካባቢው ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ መልክዓ ምድር እና የዐየር ንብረት ጋር እንዴት ተግባብቶና ተዛምዶ መኖር እንዳለበት፤ መቼ መቅረብና መራቅ እንደሚገባው ይገልፃል።

### አስረጂ ሁለት፡-ተራራ፣ ጥብቅ ደኖችንና መናፍስትን የማገናኘት ልማድ

ተራራና ጥብቅ ደኖች፡- በእብናት ወረዳ "ድንግል ፋፎ" የሚባል ተራራ እና "ጥቅጥቅ" ደን ይገኛል። ይህ ተራራ በተለያዩ ዕፅዋት የተሸፈነ፤ ለእንስሳት፣ ለአዕዋፍና ለነፍሳት መጠለያ፣ መራቢያና የምግብ ምንጭ በመሆን ዘመናትን እንዳስቆጠረ በእብናት ወረዳ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ አበባው ገልፀዋል (ቃ.መ/02/05/ 2011 እብናት)። ደብተራ መኀሪ እና መሪጌታ መንግስቱ፤ በድንግል ፋፎ ደንና ተራራ "እሳት ባፉ"ና "ሻንቂት" የሚባሉ ሁለት የዛር መንፈሶች ይኖራሉ፤ ተብሎ እንደሚታመን ጠቁመዋል። የዛር መንፈሶች ወደ አካባቢው የሚመጣ የሰው ልጅን መንፈስ በመዋረስ፣ "ዓይነ ጥላ ይሆናሉ፤ መንፈስና ጤናን ይሰልባሉ"

በማለት፤ በአካባቢው ማኅበረሰብ ይፈራሉ። እነዚህ ሁለት የዛር መንፈሶች በኃይለስላሴ ዘመን ከተራራ ተራራ እየተዘዋወሩ የሰው ልጆችን እያስጨነቁ እና እያሳበዱ ብዙ ሰው ይሞት እንደነበር መሪጌታ ስንታየሁ እና መሪጌታ መንግስቱ አስታውሰዋል። በዚህ ምክንያት፤ በአካባቢው የሚያደርሱትን አደጋና የሚጥሉትን መቅሰፍት ለመከላከል የፋኑኤል [ከአደጋ የሚሰውር] ቤተክርስቲያን ከተሰራ በኋላ፤ ከዚያ አካባቢ እንዳይቀሳቀሱ ተገዝተው፣ መኖሪያ ቦታቸውን አክብረውና ጠብቀው እንደሚኖሩ፤ በዚህ አካባቢ የሚገኙ ተናካሽ፣ ተናዳፊና ሥጋ በል የዱር እንስሳት በሰውና በቤት እንስሳት ላይ ጥቃት እንዳያደርሱ፤ "ግዝት አለባቸው" ተብሎ ይታሰባል (መሪጌታ ስንታየሁና መሪጌታ መንግስቱቃ.መ፤ 14/03/2011 እና 11/04/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

መሪጌታ መንግስቱ፤ እነዚህ የዛር መንፈሶች "የአካባቢው ዕፅዋትና እንስሳት ጠባቂ ናቸው፤... በዕፅዋቱ ላይ ሰፍረው፤ በእንስሳቱ ላይ አድረው ይኖራሉ" ተብሎ ይታመናል። ከዚህ ቦታ ዕፅዋት የቆረጠ እና እንስሳት የገደለ ሰው በዛር መንፈስ "ይመታል፤ ይቀሰፋል" ወይም "ማደሪያ ይሆናል" ተብሎ ይፈራል። በዚህ ምክንያት፤ ከአካባቢው ምንም ዓይነት የማገዶ እንጨት ወደ ቤት አይሄድም፤ በአሞራ የተጣለ እንጨት እና አጥንት እንኳ በድንገት ወደ ቤት ቢገባ የዛር መንፈሶቹ፤ በቤቱ ጣራና ግድግዳ በመስፈር ገቢና ወጭውን ሰው ይቀስፋሉ ተብሎ ይታሰባል። ሰውም ወደ ተራራው እንዳይወጣ፣ ዛፍ እንዳይቆረጥ፣ እንስሳት እንዳይገድል፤ ግዝትና እርግማን መኖሩን በማስታወስ "ዕፅ ብነቅል፤ ዛፍ ብቆርጥ አድባር ትጣላኝ! ነፍስ ባጠፋ አናብስቱ ያጥፉኝ፤ እባብና ጊንጡ ይንደፉኝ፤..." በማለት መሃላ እንዳለ፤ መሪጌታ መንግስቱ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 11/04/2011 እብናት)። ይህ እሳቤ (የማኅበረሰብ አምልኳዊ ሥርዓትና እምነት) የአካባቢውን ብዝሐ-ሕይወት ለመንከባከብ፤ የተፈጥሮ ሚዛንን ለመጠበቅ፣ የዐየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም፣ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን፣ ነፋሳትና አዕዋፍን ለማግኘት መዳረሻና ማዕከል ቦታዎች እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል።

## አስረጂ ሶስት፡- በመቃብር ቦታዎች ዛፍ የመትከል ልማድ

**በመቃብር ቦታ ዛፍ መትከል፡-** የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ፤ ሰው ሲሞት በመቃብር ቦታ ላይ ዛፍ ይተክላሉ። የባህል ሕክምና ባለሙያዎች እና የአካባቢው ማኅበረሰብ ዓመቱን ሙሉ ለምለም ሆነው የሚከርሙ ቁጥቋጦ እና የዛፍ ይዘት ያላቸውን ዕፅዋት በመቃብሩ ዙሪያ የመትከል ልማድ እንዳላቸው መሪጌታ ገብረመድኅን ይገልፃሉ። በመቃብር ቦታና አካባቢ የሚተከሉ ዕፅዋት ክረምት

ከበጋ ለምለም ሆነው የሚከርሙ፤ ወይራ፣ ዝግባ፣ ችብሃ፣ ቁልቋል፣ ቅንጭብ፣ ባንቡላ፤... በመትከል የሙታንን ፅድቅ፣ ነፍስና ሥራን ማሰብ እንደሚቻል ይጠቁማሉ። በተለይ የወይራና የዝግባ ዛፎች ፀድቀው፣ አድገውና ለምልመው አካባቢውን ጥላ አልብሰው፤ "ወፌ ሰማያትን" [እንስሳትና አዕዋፍን] በፍሬና በቅጠላቸው መግበውና አስጠልለው ሲኖሩ፤ በዚህ ዓለም መልካም ሥራ ሰርተው፣ አብልተውና አጠጥተው፣ አልብሰውና አስጠግተው፤ በኑሯቸው ሁሉ ተደስተው፣ የረጅም ዕድሜ ባለቤትና የጻድቃን ምሳሌ ተደርገው፤ እንደሚታሰቡ፤ ይመክራሉ። በተለይ የሃይማኖት መሪና ቅዱሳን አባቶች ባረፉበት ቦታ ለቅድስናቸው፣ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ፤ "አባት" ዛፎችን የመትከልና ቦታውን የማስታወስ ልማድ እንዳለ አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 25/04/2011 ሊቦ ከምከም)።

እነዚህ ዕፅዋት፤ ድርቅን በመቋቋም፣ ረጅም ዓመት በመቆየት፣ ወደጎን እራሳቸውን በማስፋትና በማራባት የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ልምላሜ በመጠበቅ፤ ለአዕዋፍ እና ለእንስሳት ምግብና መጠለያ በመሆን አገልግሎት እንደሚሰጡ ይታሰባል። ቄስ ማስረሻ እና ቄስ ዐቢይ ደግሞ፤ በመቃብር ቦታ ላይ የሚገኙ፤ ቁጥቋጦና ዛፎች ሲፀድቁ፤ የድህነት፣ የትንሳኤ፣ የምህረት፣ የፈውስ ተምሳሌት እንደሆኑ ጠቁመዋል። ከዚህ በተቃራኒ፤ ምንም ዓይነት ነገር በመቃብር ቦታው ላይ ዕፀ ባይተከል፤ በቅርብ ቤተሰቡ፣ ዘመዶቹ እና ቀብሩን በፈፀሙ ሰዎች ላይ መከራና ችግር ይደርሳል፤ ተብሎ ይፈራል። በአካባቢው ማኅበረሰብ ላይ ድርቅ፣ ርሃብና መቅሰፍት ይወርዳል፤ ይባላል። የቀብር ቦታን ባዶ መተው፤ የመጥፋት፣ የመረሳት፣ ወገን አልባ መሆንን፤ የመድረቅ፣ የመጠውለግ ምልክት እና ተምሳሌትን እንደሚወክል አስረድተዋል (ቃ.መ፤21/06/2011 ፋርጣ እና ከተቡው አባላት መካከል ቄስ ዐቢይ ያቀረቡት ሃሳብ፤ ቡድን ሶስት በቅደም ተከተለል)።

መሪጌታ በረከት "በመቃብር ቦታ ላይ የሚተከሉ ዕፅዋት የሙት መንፈስ ማደሪያና መኖሪያ ናቸው" ይላሉ። እነዚህ ዕፅዋት መራራና አቃጣይ ባሕርይ ስላላቸው፤ አጋንንትን ለመዋጋት፣ ድግምትን ለመፍታትና ለማርከስ፣ ሕሙማንን ለመፈወስ፤ በመቃብሩ ዙሪያ የተተከሉ ዕፅዋት ፍቱን መድኃኒት እንደሆኑ ይታመናል። የመቃብሩ ጠባቂ መንፈስ በቁጥቋጦዎቹ ቅጠል ላይ ያርፋል፣ ይውላል፣ ያድራል፣ ይኖራል፤ ተብሎ ይታሰባል። በዚህ አካባቢ የበቀሉና የፀደቁ ዕፅዋት ከባህል ሕክምና ባለሙያ ውጪ ቢቆረጡ፤ ለእለት መቅሰፍት፣ ለዓመት ቁራኛ ይዳርጋሉ ተብሎ ይታመናል። ዕፅዋቱ ፀድቀው፣ ለምልመው አድገው ከታዩ የሟች ነፍስ ፀድቋል፤ በአንፃሩ ዛፎች

ከደረቁ የሚች ነፍስ ተኮንኗል፤ የሲኦል ቦታ ተቀላቅሏል፤ ነፍሱ አልተባረከችም ተብሎ ይገመታል (ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት)፡፡ በአጠቃላይ በመቃብር ቦታ ላይ የሚተከሉ ዕፅዋት የልምላሜ፣ የማደግ፣ የመባረክ፣ የመብዛት፣ የመፅደቅ… ትዕምርትና ተምሳሌትን በመወከል የሚታሰቡ ቢሆኑም፤ የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ለመጠበቅ፤ ድርቅን ለመከላከል፤ የአገር በቀል ዕፅዋትን እና እንስሳትን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ዋስትና እንደሚሆኑ፤ ይታሰባል፡፡

በፋርጣና በእብናት ወረዳ የሚገኙ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች አቶ ሰሎሞን እና አቶ አበባው፤ በዞኑ የተፈጥሮ ኃብቶች በብዛት ከሚገኙባቸው ቦታዎች መካከል ጣራ ገዳም ደን፣ ጉና ተራራ፣ አለም ሳጋ፣ "ቋላ" ዩሐንስ፤ አባ መርዓዊ ደን፣ "ፈረዴ" ደን፣ አብርሐም ደን፣ "ዉሻ ጥርስ" ደን፣ ገላውዴዎስ ደን፣ ድንግል "ፋፎ" ደን፣ "እፍ በይኝ" እና "ዠፍ" ንጉስ ደን እንደሚጠቀሱ ገልፀዋል፡፡ እነዚህ ቦታዎች ጥንታዊ ገዳማት፣ አድባራት፣ ታሪካዊ መስሕቦች፣ የፀበልና የአቢያተ ክርስቲያን ደብር መገኛዎች፤ በመንግስት የተከለሉ ጥብቅ ፓርኮች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ የዞኑን የተፈጥሮ ሐብት በብዛትና በስፋት በመያዝ ተጠቃሽ ቦታዎች መሆናቸውን አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 18/04/2011 ፋርጣ እና 02/05/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡

እነዚህ ቦታዎች፤ የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ለመጠበቅ፤ የአገር በቀል ዕፅዋትን ዝርያን ለማባዛት፣ የአዕዋፍ መጠለያ፣ የእንስሳት ምግብና መኖሪያ፣ የነፍሳት መራቢያና መከማቻ፣ የዘር ኃይል ምንጭ ወይም የዘረ መል ማፍለቂያ (Seed power house) ተፈጥሯዊ ማዕከል መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ የማኅበረሰቡ አባላትም ከአካባቢው ሥነ ምህዳር ሥርዓት ጋር ተግባብቶና ተስማምቶ በመኖር፤ ንፁሕ ዐየር፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ መንፈሳዊ እርካታና ጥቅም እንደሚያገኝ አስረድተዋል፡፡ ለምሳሌ በአበባቸው፤ በዘራቸው፣ በግንዳቸው የሚራቡና የሚበቅሉ ዕፅዋት ወደ ሌላ ቦታ በነፋስ፣ በእንስሳትና በአዕዋፍ ይዛመታሉ፤ ይሰራጫሉ፤ ይራባሉ፤ አገር በቀል ዕፅዋትን በቀላሉ ለማግኘት፣ ለማላመድና ለማፅደቅ የአካባቢያቸውን ሥነ ምህዳር ሂደትና ዑደት ለመጠበቅ አበርክቶ እንዳላቸው መክረዋል (አቶ ሰሎሞን እና አቶ አበባው፤ ቃ.መ፤ 18/04/2011 ፋርጣ እና 02/05/2011 እብናት በቅደም ተከተል)፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ የደቡብ ጎንደር ዞን የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ መልካሙ፣ የተፈጥሮ ጥብቅ ደኖች፣ ለንብ ማነብ፣ ለጣዉላ ምርት አገልግሎት (ተመርጠው በባለሙያ የሚቆረጡ)፣ ለዕፅዋት ዘርና ዝርያ ምንጭ፣ ለእንስሳት እና ለአዕዋፍ ምግብ፣ መኖሪያ እና መራቢያ አካባቢ በመሆን የተፈጥሮን ሚዛን በመጠበቅ (ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ አዕዋፍ እና ነፍሳት እንዳይጠፉ በማድረግ)፣ የምግብ ሰንሰለት ሥርዓትን (Food chain system) እንዳይቋረጥ በማስተሳሰር፣ የሥነ ምህዳር ዐየር ንብረት ይዘትን ለማስተካከል እና ለመጠበቅ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳላቸው፣ ገልጸዋል። ይህ ተግባርና ድርጊት የአካባቢን ሥነ ምህዳር ሚዛን ለመጠበቅ፣ የተፈጥሮ ሐብትን ለመከባከብ፣ የአካባቢው ዐፈር በጎርፍ እንዳይጠረግ፣ የከርሰ ምድር ዉኃና ምንጮች እንዳይደርቁ፣ የዕፅዋት እና የእንስሳት ዝርያ እንዳይጠፋ፣ እንዳይሞቱና እንዳይሰደዱ፣ ማኅበረሰቡም ከጥብቅ ደኑ የሚገኙ ግብዓቶችን ለባህል መድኃኒት፣ ለጣውላ ምርት፣ ለንብ ማነብ፣ ለከብት መኖ በማዋል ተጠቃሚ እንደሆኑ አስረድተዋል (ቃ.መ፤17/04/2011 ደብረ ታቦር)። በመስክ ቆይታዬ እንዳረጋገጥኩት አድባራት፣ ገዳማት፣ የመቃብርና የፀበል ቦታዎች፣ የቤተክርስቲያን ደብር፤ በደን የተሸፈኑ ሲሆን፤ እነዚህ አካባቢዎች ለባህል ሕክምና ባለሙያዎች የባህል መድኃኒት ምንጭ እና ማዕከል፤ እንደሆኑ መገንዘብ ተችሏል።

## አስረጂ አራት፡- ዕፅዋትና እንስሳትን የማቅረብና የማራቅ ልማድ

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞችና የማኅበረሰብ አባላት ዕፅዋትና እንስሳትን የማቅረብና የማራቅ ልማድ እንዳላቸው የመስክ ምልከታና መረጃዎች ገልፀዋል (የመስክ ምልከታ፤ ከመስከረም እስከ የካቲት 2011 ዓ.ም)። መሪጌታ ገብረመድኅን፤ "መሬት የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብላ" ሁሉንም ዕፅዋትና እንስሳት በዓይነት፣ በባሕርይ፣ በጣዕምና በገቢር ለይታ፤ መልካምና መጥፎውን፣ ጣፍጭና መራራውን በአንድነት አብቅላ እንደምትገኝ፤ ገልፀዋል (ቃ.መ፤25/04/2011 ሊቦ ከምከም)።

ይህን ጉዳይ ሊቀጠበብት አብርሃም ከሃይማኖት ምግባርና አስተምህሮ አንፃር በማየት "በጻድቃንና በኀጥዓን" መስለው ይገልጻሉ። "መሬት እሬትና ሙዝን፤ ወይንና መርዝን፤ በርበሬና ጎመንን" በአንድነት አብቅላ ትገኛለች ይላሉ። እነዚህ ዕፅዋት ከአንድ መሬት ተገኝተው በጣዕም እና በባሕርይ መለያየታቸው፤ ከአንድ የአዳም ዘር የተገኙ የሰው ልጆችም፤ በበጎነትና በክፋት፤ በሰናይና በእኩይ፤ በእምነትና በክህደት፤ በደግነትና በተንኮል ምግባራቸው ተለያይተው እንደሚኖሩ ይመክራሉ። እንደ ወይን፣ እንደሙዝ መልካምና ጣፋጭ የሆኑ ዕፅዋት፤ የመልካም፣ የበጎ ሰውና የፃድቅ ምሳሌና ተምሳሌት በመሆን በፍሬያቸው፣ በቅጠላቸውና በአካላቸው

እንስሳትን፣ አዕዋፍና ነፍሳት ሳይሰለቹ መግበውና አጠጥተው፤ የሕይወትን ፍሬን ይሰጣሉ፤ ተብለው ይመሰገናሉ። በአንፃሩ እንደ ሬት፣ እንደግራዋ፣ እንደ በርበሬ የሚመሩና የሚያቃጥሉ መርዝነት ያላቸው ዕፅዋት፤ የክፉ፣ የከንዲ፣ የተንኮለኛና "የጎጥዓን" አምሳል በመሆን በፍሬያቸው፣ በቅጠላቸው፣ በሥራቸውና በመላ አካላቸው መርዝ ተሸክመው እንስሳት፣ አዕዋፍ እና ሰዎች አብዝተው ቢበሏቸውና ቢጠጧቸው፤ አካልን አድክመው፣ መንፈስን ሰውረው፣ አንደበትን ዘግተው፣ ነፍስና ሥጋን ነጥለው ለሞት ይዳርጋሉ፤ ተብሎ ይታሰባል (ቃ.መ፤ 05/03/2011 ሊቦ ከምከም)።

መሪጌታ መኅሪና አቶ ደሴ፤ የዕፅዋቱን ጣፍጭነት፣ መጋቢነት፣ አጠጪነት፣ ሰብሳቢነት፣ ለስላሳነት፣ መልካምነት እና የሕይወት ፍሬ መሆናቸውን በማሰብ "አጋንንት ይቀርቧቸዋል፤ ማደሪያ ያደርጓቸዋል፤ ሰፍረው ይኖሩባቸዋል" ተብለው ስለሚታሰቡ ከግቢና ከመኖሪያ ቦታቸው በማራቅ እንደሚተክሏቸው ገልፀዋል። በዚሁ ትይዩ፤ የመምረር፣ የማቃጠል፣ የመኮምጠጥ፣ የማስነጠስ ባሕርይ ያላቸው ዕፅዋት "አጋንንት ያርቃሉ፤ እርኩስ መንፈስ ያስወጣሉ፤ ይከላከላሉ፤ ይጠብቃሉ" በማለት በመኖሪያ ግቢና አጥራቸው ተክለውና አቅርበው እንደሚኖሩ አስረድተዋል። ከዚህ እሳቤና ተግባር በመነሳት፤ ጣፋጭና ለስላሳ ጣዕም ያላቸው የሕመም መንስኤ፤ መራራና አቃጣይ ይዘት ያላቸው የፈውስ ምክንያት እንደሆኑ ይታመናል[110]።

መሪጌታ ባሕረጥበብ እና ወ/ሮ ብርቄ፤ የዕፅዋትንና የእንስሳትን ባሕርይ፣ ጣዕምና ተግባር መነሻ በማድረግ የማቅረብና የማራቅ ልማድ እንዳለ ይመክራሉ። የማቃጠል፣ የመጎምዘዝና የመምረር ጣዕም እና ባሕርይ ያላቸውን ዕፅዋት፤ ጌሾ፣ ሬት፣ ቃጫ፣ ግራዋ፣ ጤና አዳም፣ ብሳና፣ ሎሚ፣ ሰንሰል፣ ቅንጭብ፣ ቁልቋልን፤ በማቅረብ በአቅራቢያቸውና በአካባቢያቸው ይተክላሉ። በአንጻሩ ጣፋጭ፣ ለስላሳና የዉኃ ጣዕም ያላቸውን ዕፅዋት፤ ከሚኖሩበት ግቢና አካባቢ በማራቅ፤ ከዕለታዊ የሰውና የቤት እንስሳት ንክኪ በመነጠል የመትከል፣ የማራባትና የማባዛት ልማድ እንዳላቸው ይመክራሉ። ይህን ታሳቢ በማድረግ፤ ሾላ፣ ዋንዛ፣ ዋርካ፣ ዶቅማ፣ ኮመል፣ አቮካዶ፣ ማንጎ እና መሰል ዕፅዋትን ከግቢያቸው አርቀው ይተክላሉ። እነዚህ ዛፎች የአጋንንት ማረፊያ፣ የሰፈር ቆሌ መዋያ፣ የዛር መንፈስ መስፈሪያ እንደሆኑ ይታመናል። በተለይ በአበባና በፍሬ ዘመናቸው፤ ዝናብ ሲጥል እና "በጠራራ ፀሐይ"፤ በነዚህ ዛፎች ስር መቀመጥ፣ መጠለልና መተኛት "በአጋንንት ያስለክፋሉ፤ በመብረቅ ያስመታሉ" ተብለው ይፈራሉ (ቃ.መ፤27/02/2011 እና

[110] ምዕራፍ አምስት የሕመም መንስኤ እና ምዕራፍ ሰባት የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ይዘትን ልብ ይሏል።

19/06/2011 ፋርጣ ከተቡው አባላት መካከል ወ/ሮ ብርቂ የሰጡት ሃሳብ ቡድን አራት በቅደም ተከተል)፡፡

በመስክ ምልከታ ወቅት የማኅበረሰቡ አባላት ግቢያቸውን በሰንሰል፣ በግራዋ፣ በቃጫ፣ በቅንጭብ፣ በቁልቋልና መሰል ዕፅዋት በማጠር ቦታና ክልላቸውን አስከብረው ይታያሉ፡፡ በግቢያቸውና በዙሪያቸው፤ ጌሾ፣ ሎሚ እና የቅመማ ቅመም ዘሮችን በማጽደቅ የማቃጠል፣ የመምረር፣ የመኮምጠጥ ባሕርይ ያላቸውን ዕፅዋት አቅርበው እንደሚኖሩ፤ ጣፍጭና ለስላሳ ባሕርይ ያላቸውን ዕፅዋት ከአካባቢያቸው በማራቅ ግንኙነታቸውን ገድበውና አክብረው እንደሚኖሩ፤ የምልከታ መከታተያ ቅጾች ይገልጻሉ (የመስክ ምልከታ፤ ጥቅምት/2011)፡፡ የዕፅዋቱ ባሕርይ፣ ሚና፣ ተግባርና አገልግሎት ምንድን ነው? ለምግብ ሰንሰለት (Food Chain) ሥርዓት መቀጠልና መቋረጥ ምን ዓይነት ሚና አላቸው? የማኅበረሰብ እምነት፤ ለሥነ ሕይወታዊ ሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አበርክቶ አላቸው? ሲባል፤

ይህን ርዕሰ ጉዳይ ለመተንተን፤ የዕፅዋቱን ተግባርና አገልግሎት በውል ማጤንና መለየት ይገባል፡፡ ጣፍጭ ጣዕምና ባሕርይ ያላቸው ትልቅና ግዙፉ የሆኑ የዛፍ ዓይነቶች በጣፋጭ አበባቸው፣ ፍሬና ቅጠል በራሪ ነፍሳት፣ ትላትል እና አዕዋፍን ይሰባሰባሉ፡፡ በራሪ ነፍሳትን፣ ትላትል እና አዕዋፍን የሚመገቡ ሥጋ በል (Carnivores) እንስሳት ወደ አካባቢው ይመጣሉ፡፡ ሥጋ በሉን ተሳቢና በራሪ እንስሳት ለመብላት አሞራ፣ ጭልፊት፣ ድመት… ወደ ቦታው ይገባሉ፡፡ አንዱ አንዱን በመብላት የሕይወት ዑደት ይቀጥላል፡፡ ይህ ሂደት ቀጣይነት ባለው መልኩ አንዱ ለሌላው የሕይወት መሰረት እና ሰንሰለት በመሆን የአካባቢው ሥነ ምህዳር ሚዛን እንዲጠበቅ አበርክቶ እንዳለው፤ በፋርጣ ወረዳ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ ታደሰ ገልፀዋል (ቃ.መ፤23/04/2011 ፋርጣ)፡፡

እነዚህ ዛፎች ለእንስሳት፣ ለአዕዋፍና ነፍሳት የሕልውና መሰረት፣ "የሕይወት ዑደት ማስቀጠያ፣ የምግብና የመጠለያ ቦታ ናቸው" በማለት የደቡብ ጎንደር ዞን የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ መልካሙ ገልፀዋል፡፡ የሰው ልጅ በነዚህ ዛፎች አቅራቢያና ሥር ቢኖርና ቢቀመጥ የአካባቢው ሥነ ምህዳር ይረበሻል፡፡ የዛፎቹ ፍሬ በወፍና በነፍሳት ካልተበላ፤ የዕፅዋቱም ቀጣይነትና መራባት ተግዳሮት ይገጥመዋል፡፡ የአካባቢው አዕዋፍና ነፍሳት፤ ተሳቢ፣ ተናካሽ፣ ሥጋ በል እና ቅጠል በል እንስሳት "ከሰው ልጅ ጋር ፀብ ፈጥረው፤ ለስደትና ለሞት ይዳረጋሉ፤ ጤናማ ሕይወታቸው ይረበሻል"፤ ተብሎ ይታመናል (ቃ.መ፤17/04/2011 ደብረ ታቦር)፡፡ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ

እምነት፤ ጣፍጭ ፍሬ፣ መልካም ጠረን፣ "ሽቱ"፣ ጣዕምና ባሕርይ የሚታዩባቸው ዕፅዋት "አጋንንት ይቀርቧቸዋል" ተብለው መፈራታቸው፤ የአካባቢው ሥነ ምህዳር ሂደትና ዑደት እንዳይቋረጥ ምክንያትና አበርክቶ እንዳላቸው ይታመናል።

ለምን ይፈራሉ? ሰው ቢቀርባቸው ምን ጉዳት ይደርሳል? ሲባል፤ በዛፎቹ መኖር ምክንያት ሕይወታቸውን የመሰረቱ ነፍሳትና እንስሳት፤ ምግብና መጠጣቸው፤ መስፈሪያና ማደሪያቸው፤ ከዝናብና ከፀሐይ መከለያቸው፤ መሆኑን ልብ ይሏል። የፋራጣ ወረዳ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ ሰሎሞን፤ የምግብ ትስስር ሥርዓትን ሲያስረዱ፤ የዉኃ መኖር ሣር እንዲበቅል ያደርጋል። ሣር ደግሞ ዕፅዋት በል (Herbivores) እንስሳትን ይስባል። ዕፅ በል እንስሳትን ለመብላት ደግሞ ሥጋ በል፤ ዕፅ እና ስጋ በል እንስሳት ይሰበሰባሉ። ይህ የምግብ ሰንሰለት (Food Chain) እና ሂደት የአካባቢው ሥነ ምህዳር ተፈጥሯዊ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ እንዲቀጥል ምክንያት ይሆናል፤ ይላሉ (ቃ.መ፤18/04/2011 ፋርጣ)።

በሊቦ ከምከም ወረዳ የእርሻና ተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ ታደሰ (ቃ.መ፤23/04/ 2011)፤ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ዕፅዋት የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለመጠበቅ አበርክቶ እንዳላቸው ጠቁመዋል። ለአካባቢው ሥነ ምህዳር መጠበቅ የዕፅዋት መኖር ብቻ ሳይሆን እንስሳት፣ ነፍሳት፣ አዕዋፍም፤ የራሳቸው ሚና እና ድርሻ እንዳላቸው ገልፀዋል። ከሌሎች ዛፎች በተለየ ጽድ እና ዋንዛ የዓይረን ንጥረ ነገር በውስጣቸው እንደያዙ በሣይንሱ የሚታመን መሆኑን ጠቁመው፤ "አልፎ አልፎ መብረቅ የመሳብ ኃይል እንዳላቸው"፤ መክረዋል። በአጠቃላይ ለእንስሳት ምግብና መጠለያ በመሆን ከፍተኛ አገልግሎት ያላቸው ዕፅዋት ከማኅበረሰቡ እንቅስቃሴ እርቀው፣ ተከልለውና ተጠብቀው መኖራቸው፤ ለሥነ ምህዳር ጥበቃና ደኅንነት አበርክቶ እንዳለው ይታመናል።

ግራጌታ ወንድማገኝ እና ወ/ሮ ትጓደድ፤ በደቡብ ጎንደር ማኅበረሰብ ልማድ ሣር በል እንስሳትን በማቅረብ፤ ሥጋ ተመጋቢዎችን የማራቅ ልማድ እንዳለ ገልፀዋል። ከሣር በል ሥጋቸው የሚበላና ወተታቸው የሚጠጣ፤ ከላይ የፊት ጥርስ የሌላቸው፤ "ቅዱስ ናቸው" ተብሎ በይበልጥ የማቅረብ ተግባር እንዳለ ገልፀዋል። በአንጻሩ ሥጋ በል፣ ደም መጣጭና ቆርጣሚ የሆኑ ነፍሳትና እንስሳትን በማራቅ ግንኙነታቸውን እንደሚገድቡ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤19/06/ 2011 ፋርጣ፤ ከተቡው አባላት መካከል ግራጌታ ወንድማገኝ ቡድን ሦስት እና ከቡድን አራት ወ/ሮ ትጓደድ የአቀረቡት ሃሳብ)። ለምን? ሲባል አጋንንት ተሸክመው ይዞራሉ ተብለው ይፈራሉ።

በአጠቃላይ ዕፅዋትና እንስሳትን በማቅረብና በማራቅ፤ የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ለመጠበቅ የማኅበረሰብ ልማድና ተመክሮ ጉልህ አበርክቶ እንዳለው ይታመናል። ከዚህ ይዘት በመቀጠል የባህል ሕክምና ዕውቀትና የማኅበረሰብ ልማድ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አበርክቶ እንዳለው የምሁራን ጥናቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የባህል ሕክምና ዕውቀትና ተግባር፣ ጥንታዊ ገዳማት፣ አድባራት፣ የፀበልና የሃይማኖት መገኛ ደብሮች ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አስተዋጽኦ አላቸው? ሲባል ምሁራን (Fekadu, 2001፣ Fassil, 2001 እና Pankhurst, 1976) የሚከተለውን ሃሳብ ገልፀዋል።

Fekadu (2001; P.22)፤ የኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ጥበብ ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ሲሆን ዕውቀቱና ጥበቡ ከመካከለኛው አቢሲኒያ ተነስቶ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ምሥራቁ ክፍል እንደተስፋፋ፤ ይጠቁማሉ። ለባህል ሕክምና ጥበብ፣ ዕውቀትና እድገት፤ ገዳማት፣ አድባራት፣ የሃይማኖት መጻሕፍት፣ የአብነት ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ፤ የአካባቢውን የሥነ ምህዳር ሥብጥር ዓይነት (Ecology Types/diversity) በማካተትና በመጠበቅ፤ ለዐየር ንብረት እና ለመልክዓ ምድር ጥበቃ፣ ለተፈጥሮ ሐብት ምንጭ፤ ለብዝሐ ሕይወት ትስስር ምክንያት መሆናቸውን ገልፀዋል (Pankhurst, 1976;P.10: Alemayehu, 1984; P.119)። ይህን ታሳቢ በማድረግ፤ ጥንታዊ ገዳማት፣ አድባራት፤ የሃይማኖት እና የአብነት ትምህርት ቤቶች በሚገኙባቸው ቦታዎች ዕፅዋት የማይቆረጡበት፣ እንስሳት የማይገደሉበት ጥብቅ የመስሕብ ሐብት መገኛ መሆናቸውን በማሰብ፤ ለባህል ሕክምና ዕውቀት ምንጭና እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከታቸውን ምሁራን አስረድተዋል (Fassil, 2001; PP.36-37: አሰፋ፣ 2008)።

በአጠቃላይ የባህል ሕክምና ባለሙያዎችም ከአካባቢያቸው ሥነ ምህዳር ጋር በመላመድና በመግባባት የዕፅዋትና እንስሳትን ባሕርይ በማጥናት እንዴት መቅረብና መራቅ እንዳለባቸው፤ ዘርና ዓይነታቸው እንዳይጠፋ የሚያደርጉትን እንክብካቤ፤ የማባዛትና የማራባት ዕውቀት፣ ልማድና ተግባር ለሥነ ምህዳር ጥበቃ አስተዋፅኦ እንዳላቸው፤ ይታመናል። Young የባህል ሕክምና ዕውቀት፤ የማኅበረሰቡን ሃይማኖት፣ ልማድ፣ ልምድና ተግባር መሰረት ያደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ለዓለምና ለተፈጥሮ የአለን እሳቤ፣ አመለካከት፣ ፍልስፍና እና ፅንሰ ሃሳባዊ ሥርዓት ከእምነቱ አንፃር መቃኘት እንዳለባቸው ይመክራሉ (1979; P.288)።

## 8.2 የባህል ሕክምና ዕውቀት (የማኅበረሰብ ልማድ) ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለው ተግዳሮት

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞችና የማኅበረሰቡ አባላት በአካባቢያቸው የሚገኙ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ አዕዋፍ እና የነፍሳትን ዓይነት፣ ዘርና ባሕርይ በማጥናት፤ "ገስጋሽ፣ አፍላሽ፣ ደም ላሽና ዕርኩስ" የሚሏቸውን ዕፅዋትና እንስሳት የመንቀልና የማጥፋት፤ የማራቅና የመግደል፤ ልማድ እንዳላቸው የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል (የተቡው አባላት ቡድን ሁለትና ሶስት)። ከማኅበረሰብ ልማድ በተለየ ዕፅዋትና እንስሳትን ለባህል መድኃኒትና ለገቢ ምንጭ አብዝቶ በመጠቀም፤ ለንግድ አገልግሎት በማዋል፣ የከተማ መስፋፋት፣ የሕዝብ ቁጥር እና የተፈጥሮ ሐብት ፍላጎት መጨመር፤ የእርሻ መሬት ጥበት፤ ለሥነ ምህዳር መዛባት፣ ለድርቅ መከሰት፣ ለዐየር ንብረት ለውጥና ለብዝሐ ሕይወት መመናመን መንስኤ መሆኑን፤ አቶ ታከለ እና በእብናት ወረዳ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ አበባው ገልፀዋል (ቃ.መ፤ 04/03/2011 ሊቦ ከምከም እና 02/05/2011 እብናት በቅደም ተከተል)።

### ከዕፅዋት ባሕርይ አንፃር፡-

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ ልማድ፤ እራሳቸውን የማይችሉ፣ ድንገት ታይተው የሚጠፉ፤ ወቅትና ዘመን ጠብቀው የሚከሰቱ፤ አገሩን አዳርሰውና አልብሰው የሚታዩ፤ ባገኙት መሬት ላይ በቅለው፣ ከዕፅዋት ተጠግተው፣ ተጠምጥመው፣ ተለጥፈውና ተንጠላጥለው የሚኖሩ የሣረግና የዐረም ዓይነቶች "ገፊና አጥፊ ናቸው" ይላሉ ቄስ ማስረሻ (ቃ.መ፤21/06/2011 ፋርጣ)። እነዚህ ዕፅዋት በድንገት በቅለው አካባቢውን ወረው፣ ሸፍነውና አዳርሰው የተጠጉትን ዛፍና ድንጋይ አልብሰው፣ ቤትና አጥር አፍርሰው የሚደርቁ ተስፋፊ እና "ገስጋሽ ባሕርይ አላቸው" ይላሉ፤ አቶ ደመቀና ብላታ ጓዴ። ይህም ስለሆነ፤ ድንገት ደርሰው በእርሻ ማሳ ውስጥ በቅለው ሲታዩ፤ በዛፍ እና በአጥር ላይ ተንጠላጥለው ሲገኙ አጥፊና እንግዳ ነገር ወደ ሰፈራቸው እንደገባ ይታሰባል። በዚህ ሂደት የእህል ሰብልና ነባር ዕፅዋትን የሚያደርቁ፣ የሚያደክሙ፣ የሚያነግሉና የሚያጠፉ "ደራሽ፣ ባዕድ፣ አጥፊ እና እንግዳ ናቸው" በማለት፤ ከመኖሪያ ግቢያቸው ለማራቅ ተከታትለው የማረም፣ የመንቀልና የማጥፋት ልማድ እንዳላቸው፤ ገልፀዋል (19/06/2011 ፋርጣ ከተቡው አባላት መካከል አቶ ደመቀና ብላታ ጓዴ ያቀረቡት ሃሳብ ቡድን ሶስት)።

እነዚህ ዕፅዋት ከትንሽ ቦታ ተነስተው በአገኙት አቅጣጫ በመሄድ የደረሱበትን ዕፅዋት ከበውና አስረው በመያዝ ምግብና መጠጡን እየተሻሙ፤ እያደከሙና እያደረቁ፤ በአፍላሽነት ባሕርያቸው

አካባቢውን ወረው፤ ተባዝተውና ተስፋፍተው የመኖር "ጠባይ አለባቸው" ይላሉ ወ/ሮ ጀማነሽ። በተለይ አቀንጭራ፣ ኩርንቺት፣ ሃረግ እሬሳ፣ ዕፀ ደብተራ፣ የእረኛ ቆሎ አካባቢና ሰፈሩን አልብሰው ከያዙ አዝመራ ይጠፋል፤ የከብት መኖ [ሣር] ይቸግራል፤ ተብሎ ይፈራል (ቃ.መ፤02/07/2011 ሊቦ ከምከም)።

የአካባቢው ማኅበረሰብ የዐረምና የሃረግ ዓይነቶችን በእርሻ ማሣና በግቢው በቅለው ሲያገኛቸው ይፋራል። ዐረሞች ከየት መጡ ሳይባል ድንገት ደርሰውና ተስፋፍተው የማሳውን አዝርዕት (ዕፅዋት) ወረው እድገቱን ሲገቱት፣ ምግቡን ሲሻሙት፣ ሲያደክሙትና ሲያደርቁት፤ ቦታውን አፈናቅለው በዝተውና ተስፋፍተው ሲያገኝ፤ ጥረትና ልፋቱ ከንቱ እንደሆነ ያስባል። ይህን ታሳቢ በማድረግ፤ ወፍ ዘራሽና ድንገት ደራሽ የሆኑ ዕፅዋትን ተከታትሎ በመንቀልና በማረም፤ ከአካባቢውና ከማሳው በማጥፋትና በማራቅ ቦታውን አስከብሮ ይኖራል (ወ/ሮ ቃልኪዳን እና ግራጌታ ወንድማገኝ፣ ቃ.መ፤ 21/04/2011 እና 19/06/2011 ፋርጣ ከተቡው አባላት መካከል ቡድን ሶስት በቅደም ተከተል)።

**ከእንስሳት ባሕርይ አንፃር፦** በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ ልማድ ከእንስሳት ደም መጣጭ፣ ቆንጣጭ፣ "ላሽ"፣ ቆርጣሚና ሥጋ በል እንስሳትን አድነው የመግደል፣ እንዳይባዙና እንዳይራቡ የማድረግ፤ እንዳይጠጓቸው የመከላከል፣ የማባረርና የማራቅ ልማድ እንዳላቸው አቶ መኮንን ገልፀዋል (ቃ.መ፤19/06/2011 ፋርጣ)። እነዚህ እንስሳት አጋንንት (ሰይጣን) ተሸክመው፣ ተጠግተውና ታግለው ደም ይልሳሉ፣ ይጠጣሉ፤ ሥጋ ይበላሉ፤ የአጋንንት ማደሪያ ናቸው፤ በማለት ሰው በሚኖርበት ቤትና አካባቢ ሲገቡ ታድነው እንደሚገደሉ መሪጌታ በረከት ገልፀዋል። ከነዚህ እንስሳት መካከል፤ እባብ፣ ዘንዶ፣ ቀበሮ፣ እንቃቅላ፣ ገበሎ፣ አዞ፣ ጅብ የሚጠቀሱ ሲሆን፤ በዕፅዋት ቅጠልና ቅርንጫፍ ላይ ተለጥፈው እንደ ቅጫም የሚልሱ፤ በእንስሳት አካል፣ ፀጉርና "ጉያ" ተጣብቀውና ተደብቀው እንደ መዥገር ደም የሚመጡ ነፍሳት በተገኙበት አካባቢ እንደሚገደሉ አስረድተዋል (ቃ.መ፤12/03/2011 እብናት)።

እነዚህ ሥጋ በል እንስሳት፤ ለሰውና ለእንስሳት "ጥላትና አጥፊ፣ ለካፊና ነዳፊ ናቸው"፤ በማለት በማንኛውም ጊዜና ቦታ መግደልና ማጥፋት ተገቢ እንደሆነ ይታመናል። ነፍስ አጥፍተው እና ደም አፍሰው ሥጋ የሚበሉ፤ ከእንስሳት ተለጥፈው ደም የሚመጡ፤ ከሰውና ከእንስሳት ተጠግተው ኑሯቸውን የሚገፉ፤ "ቀሳፊና ዕኩይ" ናቸው፤ በማለት ይገደላሉ። በአጠቃላይ ሥጋ በል እና ደም መጣጭ እንስሳትና ነፋሳትን ማራቅ፣ ማባረር፣ መከላከልና መግደል "ኩነኔ"

[በፈጣሪ አያስከስስም/አያስጠይቅም] የለበትም ተብሎ እንደሚታሰብ አቶ አስማማው ገልፀዋል (ቃ.መ፤14/03/2011 እብናት)፡፡

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከእንስሳት፤ ጅብ፣ አነር፣ ጥቁር ሙጨጭላ (የድመት ዘር)፣ ገበሎ፣ እባብ፤ ዘንዶ፣ አዞ፣ ጉማሬ፣ እስስት፤ ለባህል ሕክምና ተፈላጊ እንደሆኑ መሪጌታ መንግስቴ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ 23/06/2011 እብናት የተቡው አባላት ቡድን አንድ)፡፡ እነዚህ እንስሳት በማኅበረሰቡ የሚጠሉ፣ የሚፈሩና የሚገደሉ ቢሆንም ለባህል ሕክምና ከፍተኛ ጥቅምና አገልግሎት እንዳላቸው፤ መሪጌታ ባሕረጥበብ ገልፀዋል፡፡ ሥጋ በል እንስሳት በተገኙበት ቦታ በማኅበረሰቡ አባላት "መሳደዳቸውና መገደላቸው"፤ ለባህል ሕክምና ተግባር በብዛት መዋላቸው፤ ቁጥራቸው እንዲቀንስና እንዲጠፋ መንስኤ መሆኑን አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 22/07/2011 ፋርጣ)፡፡ ከዚህ በታች የጅብ፣ የአነር፣ የጥቁር ሙጨጭላ እና የገበሎ እንስሳት ቆዳዎችን የሚያሳይ ፎቶ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ፎቶ ግራፍ 12፡- በባህል ሕክምና ቦታ የሚገኙ የጅብ፣ የአነር፣ የጥቁር ሙጨጭላና የገበሎ ቆዳዎችን የሚያሳይ ፎቶ



ምንጭ፡- ፋርጣ ወረዳ፤ በጥናቱ አቅራቢ በቀን 27/02/2011 ዓ.ም የተነሳ

በእብናት ወረዳ የዱር እንስሳት እና የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ የሆኑት አቶ አበባው ደግሞ፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ ሥጋ በል እንስሳት እንዳይገደሉ በተደጋጋሚ ትምህርት ቢሰጥም፤ ጅብ፣

አነር፣ ቀበሮ፣ እባብ፣ ዘንዶ እና መሰል እንስሳትን የመግደሉ ሂደት እንዳላቆመ ጠቁመዋል። ይህ ተግባር፤ "ለጅብ፣ ለአነርና ለቀበሮ እንስሳት ቁጥር መቀነስና መመናመን መንስኤ ነው" ይላሉ። ሥጋ በል እንስሳት የአካባቢን ሥነ ምህዳር ሚዛን እንዳይዛባ፣ የምግብ ሰንሰለት ሂደት እንዳይቋረጥ፤ የሥነ ምህዳር ሥርዓት (Ecosystem) እንዲጠበቅና እንዲመጣጠን ለማድረግ ከፍተኛ አበርክቶ እንዳላቸው ገልጸዋል። እነዚህ እንስሳት አካባቢን በማጽዳት፣ "ሞተው" የወደቁ እንስሳትና ቆሻሻዎችን በማንሳት፤ ለአካባቢ ንጽሕና መጠበቅ እና ለተፈጥሮ ሚዛን መደላድል ምክንያት መሆናቸውን፤ መክረዋል (02/05/2011 እብናት)።

በአጠቃላይ ሥጋ በል እንስሳት በማኅበረሰቡ የሚፈሩ፣ የሚጠሉና የሚገደሉ፤ በባህል ሕክምና ባለሙያዎች በጥብቅ የሚፈለጉና ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉ ሲሆን በተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች ደግሞ የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስና ንጽሕናን ለመጠበቅ፤ በየቦታው ሞተው የወደቁ የቤትና የዱር እንስሳትን ብስባሽና ቆሻሻ ለማንሳት፤ የሥነ ምህዳር ሚዛን ለማመጣጠን ጉልህ ተግባርና ሚና እንዳላቸው፤ ይታመናል። ከዚህ በታች ከማኅበረሰብ ልማድ በተለየ ለሥነ ምህዳር ተግዳሮት ናቸው፤ የሚባሉ ርዕሰ ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

መሪጌታ በረከት እና ደብተራ መልኩ፤ አብዛኛው የባህል መድኃኒት ግብዓት ከዕፅዋት ሥር ተሰብስቦ የሚቀመም መሆኑን ገልፀው፤ "አንድ እግር በቀል" የሆኑ ዕፅዋት ዓይነትና ዘራቸው እየጠፋ መሄዱን አስረድተዋል። ለዚህ ተግባር ሁለት ምክንያቶችን ጠቁመዋል፤ አንደኛ "አንድ እግር በቀል" ዕፅዋት አንድ ጊዜ ከተነቀሉ በኋላ በነበሩበት ቦታ መልሶ ማግኘት አለመቻሉ፤ ሁለተኛ በሌላ ቦታ ዘርና ተክላቸውን ወስዶ ለማሳደግ፣ ለማራባትና ለማባዛት ከባድና አስቸጋሪ መሆናቸውን ገልፀዋል። እነዚህ ዕፅዋት እንደቡና ተክል፤ በጥቅጥቅ ደንና ዛፍ ሥር ተጠግተው ከፀሐይ፣ ከሰውና ከቤት እንስሳት ተከልለው በገዳማት፣ በአድባራት፣ በወንዝና በጥብቅ ደኖች መሃል አልፎ አልፎ በቅለው የሚገኙ ቢሆንም፤ ከሚሰጡት ጥቅም አንፃር አይቶ የሚያልፋቸው የባህል ሐኪም እንደሌለ ጠቁመዋል (ቃ.መ፤ ቃ.መ፤ 12/03/2011 እብናት እና 01/03/2011 ፋርጣ አቅደም ተከተል)።

መሪጌታ መኅሪ ደግሞ፤ ከመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ምትክ የሌላቸው የቁጥቋጦ፣ የሃረግና የሥራ ሥራ ዕፅዋት ሥራቸው እየተነቀለ፣ ፍሬያቸው እየተለቀመ፣ ግንዳቸው እየተቆረጠ፣ ዘራቸው እየጠፋ መሄዱን ጠቁመው፤ "በዱር በገደሉ፤ በአድባራትና በወንዙ" ፈልጎ ለማግኘት አዳጋች መሆናቸውን አስረድተዋል (ቃ.መ፤ 28/01/2011 ሲቦ

ከምከም)። በተመሳሳይ መልኩ መሪጌታ ዘላለም፤ በዚህ ዘመን ለባህል ሕክምና አገልግሎት ተፈላጊ በመሆናቸው ምክንያት እየጠፉ የሄዱ ዕፅዋትን እንደሚከተለው ዘርዝረዋል (ቃ.መ፤ 20/04/2011 ፋርጣ)፡-

> በአሁኑ ወቅት ዕፀ ልባዊት፣ የምድር እምቧይ፣ ፍላጹት፣ የአይጥ አተር፣ ሞይደር፣ ወርቅ በሜዳ ዕፆች ተፈልገው አይገኙም። አንጼ ተነቅለው ተሄዱ ምትክ የላቸውም። ከአስር፤ ከአስራ አምስት ዓመት በፊት በቀላሉ በተራራው፣ በመንገዱ፣ በወንዙ፣ በአድባርና በገዳሙ የምናገኛቸው ዕፆች አሁነ የሉም። ደኑ እያለቀ ሄደ፤… የዶቅማ፣ የእንኳይ፣ የጥንዥት፣ የእንቧጮ ተቀፅላ ማግኘት ዘበት ነው። በየቦታው ብንማስነ [ብንፈልግ] አናገኝም፤ በርሃ ሄደነ፣ ገዳማት ገብተነ፤ ስንት ፈተና ታይቶ ባዶ እጅ እንመለሳለነ።… ችግር ውስጥ ነው ያለነው። ዕፅ ካልተገኘ ምን ትሰጣለሁ።

በማለት ገልፀዋል። ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ለባህል መድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት በጊዜ ሂደት እየጠፉ፤ የደን ሽፋን እየቀነሰ፣ አካባቢው እየተራቆተ መሄዱ፤ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን በቀላሉ ማግኘት እንዳልተቻለ ይጠቁማል። የአካባቢው ሥነ ምህዳር እየሳሳ፣ እየተጎዳ፣ እየተመናመነ ሲሄድ፤ የባህል መድኃኒት ዕፅዋትን መፈለግና ማግኘት የዘመኑ ፈተና እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል።

ሊቀጠበብት አብርሃም እና ደብተራ መልኩ ደግሞ፤ የዕፅዋት እና የእንስሳት ንግድ እየተስፋፋ እና እየጨመረ መሄድ ለዕፅዋትና እንስሳት መጥፋት ዋና ምክንያት እንደሆነ ገልፀዋል። በገዳም ውስጥ የሚኖሩ መነኮሳትና አባቶች፤ የባህል ሐኪሞች ዕፅዋትን ነቅለው፣ ቆርጠውና ሰብስበው፤ ከተማ ውስጥ ለሚገኙ የባህል ሐኪሞች ማስረከባቸው፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ ወጣት ገንዘብ ለማግኘት በወንዝና በተራራ የሚገኙ ዕፅዋትን እየቆረጡ ለክሰል፣ ለጣውላ፣ ለቤት መስሪያ፣ ለማገዶ ከተማ ወስደው መሸጣቸው፤ እንስሳትን እያደኑና እየገደሉ ሥጋ፣ ቆዳና ሞራቸውን ለባህል ሐኪሞችና ለከተማ ማኅበረሰብ ሸጠው የገንዘብ ምንጭ ማድረጋቸው፤ የአካባቢው ዕፅዋት ሽፋንና የእንስሳት ቁጥር እንዲቀንስ ዐቢይ ጉዳይ መሆናቸውን መክረዋል (ቃ.መ፤ 05/03/2011 እና 01/03/2011 ሊቦ ከምከም እና ፋርጣ በቅደም ተከተል)።

በሊቦ ከምከም ወረዳ የእርሻና የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ አቶ ታደሰ (ቃ.መ፤23/04/2011 ሊቦ ከምከም)፤ ለአካባቢ ሥነ ምህዳር መዛባት እና ለተፈጥሮ ሐብት መመናመን፣ መራቆትና መቀነስ፤ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የእርሻ መስፋፋትና የደን መመንጠር፣ የዕፅዋትና የእንስሳት ንግድ (በግልጽ የተከለከለ ቢሆንም በድብቅ መካሄዱ)፣ የከተማ መስፋፋት እና የተፈጥሮ ሐብት

ፍላጎት ማደግና አቅርቦት ማነስ፤ ለዕፅዋትና ለእንስሳት ብቻ ሳይሆን ለመሬት ለምነት፣ ለዐየር ንብረት ለውጥ፣ ለአካባቢ ብክለት፣ ለመሬት ጥበትና ለተፈጥሮ ሐብት እጥረት ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል። የአካባቢው ሥነ ምህዳር "እየተራቆተ" እና እየተመናመነ መሄዱ ለዕፅዋት፣ ለእንስሳት፣ ለአዕዋፍ መቀነስ፣ መሰደድና መጥፋት መንስኤ ነው፤ በማለት አስረድተዋል። በዞኑ የደን ሽፋን እና የዱር እንስሳት በብዛት ተጠብቀው የሚገኙባቸው ቦታዎች፤ መንግስት የከለላቸው ጥብቅ ፓርኮች፣ ገዳማት፣ የአቢያተ ክርስቲያን ደብር፣ አድባራትና የፀበል መፍለቂያ አካባቢዎች እንደሆኑ ዘርዝረዋል። በአጠቃላይ የዕፅዋትና የእንስሳት ንግድ፣ የሕዝብ ቁርጥ መጨመር፣ የመሬት ጥበትና የተፈጥሮ ሐብት እጥረት፣ የከተማ መስፋፋት፤ ለአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር መለወጥ፤ ለዕፅዋትና ለእንስሳት መመናመንና መጥፋት መንስኤ እንደሆኑ መገንዘብ ተችሏል።

## 8.3 የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የማኅበረሰብ ልማድ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ የነበራቸውን አበርክቶና ተግዳሮት ለማሳየት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ዋቢ በማድረግ ትንታኔ ቀርቧል። በትንታኔው ሂደት ጎልተው የወጡና የምዕራፉ ዐበይት ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- በጥናቱ ተተኳሪ ማኀበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች እምነት፣ ዕውቀትና ተግባር የዕፅዋትና እንስሳትን ቀጣይነት እና ሕልውናን ለማረጋገጥ፤ መኖሪያ አካባቢዎችን (ግቢ፣ የእርሻና የመስኖ ቦታዎችን)፣ ገዳማትን፣ አድባራትን፣ የአቢያተ ክርስቲያን ደብሮችን፣ የፀበል ቦታዎችን እና ጥብቅ ፓርኮችን ምርጫቸው በማድረግ እንስሳትን የመጠበቅና የማራባት፤ ዕፅዋትን የመትከል፣ የመዝራት፣ የማስፋፋትና የማባዛት ልምድ ማዳበራቸውን፤ ጥናቱ አረጋግጧል።
- የባህል ሐኪሞች በዘመን ሂደት የቀሰሙትን ዕውቀትና ተግባር ተጠቅመው፤ የአካባቢያቸውን ሁነትና ዐውድ ለይተው ለባህል መድኃኒት የሚጠቀሟቸውን ዕፅዋት ቀጣይነት ለማረጋገጥ፤ የመድረሻ ወቅታቸውን፣ ጊዜና ቦታቸውን ጠብቀውና መርጠው፤ ሥርዓተ ገቢር አድርሰው በመጠኑ የመቁረጥ፣ የመልቀምና የመቆፈር ክህሎት ማዳበራቸው፤ ከአካባቢው የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች፤ ከፓርክ ጠባቂ ሚኒሻች ጋር

በመተባበር ተገቢ ባልሆነ አካል ዕፅዋት እንዳይቆረጡና እንስሳት እንዳይገደሉ ጥበቃ ማድረጋቸው፤ በጥናቱ ተስተውሏል፡፡

- በአካባቢያቸው ለሚገኙ እንስሳት ጥበቃ በማድረግ ግልገልና ጫጩት የሆኑ፣ እርጉዝና የሚያጠቡ ሴት እንስሳትን በመለየት፤ ለባህል መድኃኒት አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ በእድሜያቸው የገፉ ወንድ እንስሳትን መርጠዉ በመግደል ግብዓቱን ለረጅም ጊዜ የመጠቀም ልማድ እንዳላቸው፤ በጥናቱ ታይቷል፡፡
- በአካባቢው ማኅበረሰብ ልማድ በአድባራት፣ በገዳማት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በፀበል እና በመቃብር ቦታዎች የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳት እንዳይገደሉና እንዳይቆረጡ "የመንፈስ ማረፊያና ማደሪያ (ጠባቂ ኃይል) ናቸው፤ የቅዱሳን አባቶች ግዝትና ቃል ኪዳን አሉባቸው"፤ ተብሎ መታመኑ፤
- የአካባቢው ማኅበረሰብ ልማድ፤ የዕፅዋት እና እንስሳትን ዓይነትና ባሕርይ በመለየት፤ ከዕፅዋት መራራና አቃጣይ፤ ከእንስሳት ደግሞ ሣር በል ተመጋቢዎችን በማቅረብ፤ ጣፍጭና ለስላሳ ባሕርይ ያላቸውን ዕፅዋት እና ሥጋ በል እንስሳትን በማራቅ፤ ለምግብ ሰንሰለት ሥርዓት መቀጠልና ለሥነ ምህዳር ሚዛን መጠበቅ አስተዋጽኦ ማድረጉ፤
- የባህል ሐኪሞች የዕፅዋትን ሥር ነቅለው ለባህል መድኃኒት አገልግሎት አዘውትረው መጠቀማቸው፤ ሥጋ በል እንስሳትን አድነው በብዛት ለባህል ሕክምና ተግባር ማዋላቸው ለዕፅዋት ዝርያ መጥፋት እና ለእንስሳት ቁጥር መቀነስ መንስኤ መሆኑ፤
- የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላትና የባህል ሐኪሞች በዕፅዋትና እንስሳት ንግድ ላይ መሳተፍና የገቢ ምንጭ ማድረጋቸው፤ የከተማ መስፋፋት፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የእርሻ መሬት ጥበት፣ የተፈጥሮ ሐብት እና የፍላጎት አለመመጣጠን፤ ለደን ሽፋን መቀነስ፤ ለእንስሳት ቁጥር ማነስና መጥፋት፣ የምግብ ሰንሰለት ሥርዓት መዛከምና መቋረጥ፤ ለሥነ ምህዳር ሥርዓት መዛባት፤ ጉልህ ተግዳሮት መሆናቸውን፤ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ማጠቃለያና ይሁንታ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሃሳቦች ይዘት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 9.1 ማጠቃለያ (መደምደሚያ)

ይህ ጥናት "የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ፤ ጥናት ለማካሄድ ካነሳሱኝ ዐበይት ምክንያቶች መካከል የባህል ሕክምና እና የሥነ ምህዳር መስተጋብር፤ የአጥኚው ልምድና የመስክ ተመክሮ፤ በቀደምት ጥናቶች ያልተዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች መነሻ በማድረግ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ በተመረጡ ወረዳዎች የሚካሄደውን የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብርን ተንትኖ ማሳየት ማዕከላዊ ጉዳይ ነበር፡፡ የጥናቱን ማዕከላዊ ጉዳይ ከግብ ለማድረስ አራት መሰረታዊ የምርምር ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ እነርሱም፤ የባህል ሐኪሞች/ማኅበረሰቡ ለበሽታና ለሕመም መንስኤ ምን ዓይነት እሳቤና አተገባበር አላቸው? የባህል ሕክምና ባለሙያዎች የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው? የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ ምን ይመስላል? የባህል ሕክምና ዕውቀት (የማኅበረሰብ ልማድ) ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አበርክቶ እና ተግዳሮት አለው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

እነዚህን የምርምር ጥያቄዎች ከግብ ለማድረስ፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤን መግለጽ፤ የበሽታ መለያና መመርመሪያ ዘዴዎችን ማብራራት፤ የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔን በማሳየት መተንተን፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን አበርክቶ እና ተግዳሮት መለየት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎች ተነስተዋል፡፡ የጥናቱን ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ኢትኖግራፊያዊ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን ታሳቢ በማድረግ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ በተተኳሪ ቡድን ውይይት እና በንጥል ጥናት ዘዴዎች ተሰብስበው፤ በማስታወሻ፣ በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ ተሰንደዋል፡፡

የመስክ መረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ፤ በዓላማ ተኮር (Purposive Sampling) እና በአጋዥ ጠቋሚ ናሙና (Network or snowball sampling) ስልት የተካሄደ ሲሆን፤ ጥናቱ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ብቻ ታላሚ አድርጓል፡፡ እነዚህ መረጃ ሰጪዎች የሚኖሩበትን (የደቡብ

ጎንደር ዞን)፣ አካባቢያዊ መልክዓ ምድር (ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ ቦታዎችን) መነሻ በማድረግ ሶስት ወረዳዎች (ፋርጣ 5፣ ሊቦ ከምከም 6፣ እብናት 5፤ በድምሩ 16 ቀበሌዎች) ተለይተዋል። ከነዚህ ሶስቱ የወረዳ ቀበሌዎች፤ የባህል ሐኪሞችን፤ የባህል መድኃኒት ተጠቃሚና ተጠቅመው የማያውቁ ግለሰቦችን፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሽማግሌና እናቶች፤ የዘመናዊ ሕክምና፣ የደን እና የተፈጥሮ ሐብት፣ የባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎችን ታላሚ በማድረግ፤ በድምሩ 76 (56 ወንድና 20 ሴት) መረጃ ሰጪዎች ተሳትፈዋል።

ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ይዘትን በመከተል የትርጓሜ ንድፈ ሃሳብ (Interpretive theory) አካል በሆኑት፤ በሥነ ዕውቀት (Epistemology) እና ማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ (Social Constructionist Theory)፣ በዐውድ-ተኮር ክዋኔ (Contextual-centered Performance theory) እና ሕዝባዊ የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦችን (Lay theories of illness Causation) መሰረት በማድረግ፤ የመስክ መረጃዎችን ከባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል (Culture-Centered Explanatory Model)፣ ከዐውድ-ተኮር ክዋኔ ሞዴል እና ከተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል ምልከታና አንፃር በማደራጀት ፈትሿል። እነዚህ መረጃዎች በገላጭ፣ በይዘት እና ትርጓሜ (Interpretation) ስልት ተተንትነው ቀርበዋል። የጥናቱን ዝርዝር ዓላማዎችና ትንታኔ መነሻ በማድረግ ከሚከተሉት ማጠቃለያ ነጥቦች ላይ ለመድረስ ተችሏል።

እንደ ደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ (የባህል ሐኪሞች) እሳቤ የሕመም መንስኤ አጋንንት እንደሆኑ ይታመናል። እነዚህ አጋንንት በዋናነት፤ ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ የመሬትና የዐየር ጋኔል በመባል የሚጠሩ ሲሆን፤ መከሰቻ ዐውዳቸው፤ መቅረቢያ መንገዳቸው፤ የሚያጠቁት የሰውነት አካል እና መተላለፊያ አጋጣሚያቸው፤ እንደ ባሕርይና ግብራቸው የተለያየ ዐውድ እንዳላቸው፤ ጥናቱ ጠቁሟል። በዚህ መሰረት፤ ጅን በወንዝ እና በውኃ መገኛ አካባቢዎች የሚኖር የወንዝ እና የባሕር አስተዳዳሪ "ጌታ ነው" ይባላል። የባሕር ጅን በዕኩለ ቀን ሲቀርቡት "ሰውና እንስሳትን ይመታል"፤ ለአካል ቁስለት እና ለሆድ ሕመም ይዳርጋል፤ ተብሎ ይታሰባል። ዛር፤ ከሰው (በዘር) እና ከአድባር ቦታዎች (ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት፣ ከበረሃና ከዋሻ) ዐውድና አጋጣሚ በመነሳት የሰውን አዕምሮ በመቆጣጠር፤ የመራቢያ አካልን በማድከም ለስንፈተ ወሲብ፣ "ለሾተላይ"፣ ለአዕምሮ ጭንቀት በሽታ ይዳርጋል፤ ተብሎ እንደሚፈራ ጥናቱ ይገልፃል።

የቡዳ ሕመም ደግሞ፤ በደም መፍሰስ፣ በምግብና መጠጥ ላይ በማረፍ፣ በደም ግባትና ቁንጅና፤ ለዕይታ አጋላጭ በሆኑ መሰብሰቢያ ቦታዎች በመገኘትና በመመገብ እንደሚከሰት፤ ይታሰባል።

የቡዳ ሕመም፤ አካልን በማድከም፣ ሰውነትን በማዛል፣ በማስለፍለፍና በማንቀጥቀጥ "ልብን ይሰውራል" ተብሎ ይታመናል። የዐየር ጋኔል፤ በፀሐይ ጨረር "ዉጋት" ይከሰታል በማለት ለአዕምሮ ሕመም፣ ለድንገተኛ አካል ጉዳት፣ ለዓይን ስውርነት፣ "ለዳፍንት" (ድንገት በቁም ለሚጥል) በሽታ መንስኤ እንደሆነ፤ ይገመታል። በተመሳሳይ መልኩ የመሬት ጋኔል፤ ከመኖሪያ ቤትና ቆሻሻ አካባቢዎች በመነሳት፤ በር በመክፈትና በመዝጋት፣ በሞቃትና ቀዝቃዛ ዐየር መጋጨት፤ ከቤት ጥራጊ መጣያ ቆሻሻ፤ ከዐመድና አተላ ማፍሰሻ ቦታዎች በመነሳት፤ የሰውነት አካልን የማቃጠልና የማሽማቀቅ፤ አፍና አፍንጫን የማፈን፣ እራስ የማዞር፣ የፊት አካልን የማጣመም፣ የዓይን ክፍልን "የማንሸዋረር"፣ የምች እና "የብርድ ሕመም" መነሻ ተደርጎ እንደሚታሰብ፤ ጥናቱ አረጋግጧል።

እንደ ደቡብ ጎንደር ዞን በማኅበረሰብ እሳቤ፤ ሕይወት በጤና እና በሕመም፣ በሰናይ እና በዕኩይ መናፍስት ኃይል ስበት መሃል እንደምትገኝ ይታሰባል። በዚህ እሳቤ፤ ፈጣሪ የሕይወት ምንጭ፤ አጋንንት (ዲያቢሎስ) ደግሞ የሞት ምክንያት ተደርገው ይታመናሉ። በሁለቱ ተቃራኒ ኃይሎች ስበት፤ የሕይወት ዑደት (መውለድ-ማደግና መሞት)፣ ጥሪን እና የለውጥ ሂደት፣ ለፍጥረተ-ዓለሙ የተሰጠ ባሕርይና ፀጋ ተደርጎ እንደሚታሰብ፤ ጥናቱ ይጠቁማል። ማኅበረሰቡ በጣዕማቸው ጣፋጭና ለስላሳ ይዘትና ፍሬ ያላቸውን ዕፅዋት (ሾላ፣ ዋንዛ፣ ዋርካ፣ ማንጎ፤...) ለሕመም መንስኤ መሆናቸውን በማመን፤ "የዛር ማደሪያ እና የቆሌ መስፈሪያ ናቸው" በማለት ከግቢና ከአካባቢያቸው አርቀው ይተክላሉ። በአንጻሩ፤ መራራ፣ አቃጣይና ለብላቢ ጣዕምና ይዘት ያላቸውን ዕፅዋት (ጌሾ፣ ጤና አዳም፣ ሰንሰል፣ ቅንጭብ፤...) በማቅረብ በግቢያቸው ተክለውና አጥረው ይታያሉ። በተመሳሳይ መልኩ ሣር በል እንስሳትን በማቅረብና በመጠቀም፤ ሥጋ በል እንስሳትን በማራቅ ጤናቸውን እንደሚጠብቁ፤ ጥናቱ አስረድቷል። በመጨረሻም ዓመት፣ ወቅትና ወራትን ጠብቀው፤ መከሰቻ ዐውድን ለይተው የሚነሱ በሽታዎችን በማሰብ እና የኮከብ ቆጠራ በማካሄድ የሕመም መንስኤና ባሕርያትን በመለየት፤ አካልን ለሚያደቁ እና መንፈስን ለሚያስጨንቁ በሽታዎች የሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ፤ ጥናቱ አረጋግጧል።

በሁለተኛ ደረጃ የዚህ ጥናት ትኩረት፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ምን ዓይነት ተግባርና ይዘት እንዳላቸው ማብራራት ነበር። በጥናቱ ትንታኔ ይዘት በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ዓለማዊና መንፈሳዊ የምርመራ ዘዴዎችን በተናጠልና በቅይጥ በመጠቀም በአካባቢያቸው የሚከሰቱ የሕመም ዓይነቶችን እንደሚለዩ፤ ጥናቱ አሳይቷል። ዓለማዊ ምርመራን የሚከተሉ የባህል ሐኪሞች እይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባዮሎጂካዊ፣

የታካሚን የሕይወት ዳራ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስተጋብሩን በማጤን የበሽታ ዓይነቶችን እንደሚለዩ፤ ከዓለማዊ ዕይታና ትግበራ በተጨማሪ በመንፈስ እየተመሩና እየታገዙ ምርመራ የሚያካሂዱ የባህል ሐኪሞች እንዳሉ፤ ጥናቱ አመላክቷል።

እነዚህ የባህል ሐኪሞች፤ "ድንገት ደራሽ" የሕመም ዓይነቶችን በመለየት፤ የማተኮስ፣ የማቃጠልና የማስለፍለፍ፤ በፍጥነት የመዛመትና የመስፋፋት ባሕርይ ያላቸውን በሽታዎች በእሳትና በነፋስ ባሕርይ ምድብ ውስጥ በማካተት፤ ድንገተኛና አጣዳፊ፣ አንቀጥቃጭና አርገብጋቢ፣  አቃጣይና አስለፍላፊ በማለት ይመድባሉ። ከዚህ በተቃራኒ አካልን ቆንጥጠው፣ ሥር ሰደው፣ ቀስ በቀስ እያደጉና ሕመማቸው እየጠነከረ፣ ለረጅም ጊዜ ቆይተው ለሞት የሚዳርጉ፤ በአካል ክፍል ላይ አብጠውና ከብደት ጨምረው የሚታዩ የመሬትና የውኃ ባሕርይ ያላቸው፤ ቆንጣጭና ሰርሳሪ፣ አብራጅና አድካሚ፣ አደንዛዥ እና አወፋሪ የበሽታ ዓይነቶች እንዳሉ፤ በጥናቱ ተጠቁሟል። ከዚህ ይዘት በተጓዳኝ፤ የበሽታ ባሕርይን በመለየት እና የተቃርኖ ሕክምናን በመተግበር፤ ለሚያቃጥል ሕመም የሚያበርድ፤ ለሚያደክም በሽታ የሚያበረታ፤ ሰርስሮ ለሚገባ፣ ሰርስሮ የሚያወጣ መድኃኒት በመስጠት ሕክምና እንደሚያካሂዱ፤ ጥናቱ አመላክቷል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች፤ በሕሙማን አካልና መንፈስ ላይ የጤና ኃይል ሚዛን መዛነፍ ሲያጋጥማቸው፤ የታካሚውን አቋም በማጤን፤ አራቱን ሥጋዊ ባሕርያትን (ነፋስ፣ እሳት፣ ውኃና መሬት) ተከትለው፤ ንስሃ (ፆም፣ ፀሎት፣ ሥግደት፣ ምፅዋት)፣ ፀበል፣ ምርቃት እና የምግብ ዓይነቶችን በማዘዝና በመስጠት፤ የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶችን በመተግበር ሕክምና እንደሚሰጡ፤ ጥናቱ አረጋግጧል።

በሶስተኛ ደረጃ የዚህ ጥናት ትኩረትና ዓላማ በባህል ሕክምና ዕውቀት፤ የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ ምን ዓይነት ተግባርና ይዘት እንዳለው ተንትኖ ማሳየት ነበር። በጥናቱ ትንታኔ ይዘት፤ የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ ከባህል መድኃኒት ግብዓት አሰባሰብ እስከ መድኃኒት አሰጣጥ ድረስ ረጅም ሂደቶችን ሲያልፍ፤ በሥርዓተ ገቢር እና በፀሎት የሚመራ፣ በዐውድ (በቀን፣ በሠዓት፣ በጊዜ፣ በቦታና በሁነት) የተወሰነ፣ በድርጊት የታጀበና የተገደበ፣ ብላ/አትብላ፣ አድርግ/አታድርግ መመሪያና ገደቦችን በማካተትና በመተግበር እንደሚከወን፤ ጥናቱ አረጋግጧል።

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች፤ በመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት፤ የሥርዓተ-ገቢር ማስተካከያ ዐውዳዊ ስልቶችን በመከተል የንፅሕና፤ የዕለት፣ የቀናትና

የወቅቶች፤ የቁጥርና የአቅጣጫ እሳቤዎችን በመተግበር ሥርዓቱን እንደሚፈፅሙ፤ ጥናቱ ጠቁሟል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች፤ ለመድኃኒት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናትና ከነፋሳት የሚያገኙ ሲሆኑ አብዛኛውን ይዘት ከዕፅዋት ዓይነቶች እንደሚሰበስቡ፤ ጥናቱ ገልጿል።

በመድኃኒት አሰባሰብ ሂደት፤ የዕፅ (የግብዓት) መገኛ ቦታዎች (ሥነ ምህዳር)፣ የዕድገት ደረጃ፣ መሰብሰቢያ ወቅት፣ ዕድሜ፣ ዐውድ፣ የመድኃኒት ክፍል፣ ጣዕምና ባሕርይ ተለይቶ ወደ መድኃኒት ቅመማ ይገባል። የመድኃኒት ቅመማ ይዘትና ምድብ ደግሞ በግብዓት ዓይነትና ባሕርይ ላይ ተመስርቶ አራት ዋና ዋና የጣዕም ዓይነቶችን በመለየት ይከወናል። የክወና ሂደቱ በግብዓቶቹ ባሕርይ የሚወሰን ሲሆን፤ ሰውነትን የማለስለስ፣ የማወርዛት፣ የማዳረስ፣ የማላላትና የማዳለጥ ባሕርይ ያላቸው የቅባት ዘሮች በነፋስ፤ የማቃጠል፣ የመለብለብ፣ የማስነጠስና የማስለፍለፍ ባሕርይ ያላቸው የቅመማ ቅመም ዘሮች በእሳት፤ ዉኃን ተሸክመውና አቁረው የሚይዙ፣ አጠራቅመው የሚገኙ ለስላሳና ቀዝቃዛ የአትክልትና ሥራ ሥር ዘሮች በዉኃ፤ አካልን የመጠገን፣ የመገንባት፣ የማሳደግ፣ የማወፈር፣ የማክበድና የማደርጀት ይዘት ያላቸው የእህል ዘሮች በመሬት ባሕርይ ምድብ ውስጥ እንደሚካተቱ፤ ጥናቱ አረጋግጧል።

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የመድኃኒት ቅመማ ሲያካሂዱ ከማጠብ እስከ ማሸግ የሚደርስ ረጅም የክዋኔ ሂደትን እንደሚያልፉ፤ ጥናቱ ጠቁሟል። የክዋኔ ሂደቱም፤ ከመስክ የተሰበሰቡ ግብዓቶችን በማጠብ፣ በማድረቅ፣ በመልቀም፣ በመከትከት፣ በመቀጥቀጥ፣ በመውቀጥ፣ በመንፋት፣ በመፍጨት፣ በመሰለቅ፣ በመዘፍዘፍ፣ በመቀቀል፣ በማንጠር እና በማሸግ በቅደም ተከተል ይከወናል። ይህ ክዋኔና ተግባር ሲጠናቀቅ ወደ መድኃኒት አሰጣጥ ሥርዓት ይሸጋገራል። በመድኃኒት አሰጣጥ ሥርዓትና መመሪያ ደግሞ ተቀምመው የተዘጋጁ ግብዓቶች፤ በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚታጠን፣ በሚጨስ፣ በሚቀባ፣ በሚነሰነስ፣ በሚታሰር፣ በሚታኘክ፣ በሚቀረጠም፣ በሚመጠጥ እና መሰል ተግባራትን በመፈፀም፤ በአፍ የሚወሰዱ፣ በአካል ላይ የሚቀቡ፤ በአፍንጫ የሚሸተቱ፣ በዓይንና በጆሮ በጠብታ መልክ የሚሰጡ፣ በፊንጥጣ የሚቀበሩና የሚጨሱ መድኃኒቶችን በመስጠት ይፈፀማል። በመድኃኒት አሰጣጥ ሂደት፤ የበሽታው ዓይነት፣ የጉዳት መጠንና ደረጃ ተለይቶ፤ የታካሚው ወቅታዊ አቋም፣ የመድኃኒት ባሕርይ፣ አወሳሰድና ምጣኔ፤ መስጫና ማርከሻ፤ የምግብ ፈቃድና ክልከላን ታሳቢ በማድረግ እንደሚከወን፤ ጥናቱ አረጋግጧል።

በመጨረሻም የዚህ ጥናት ዐቢይ ትኩረት፣ የባህል ሕክምና ዕውቀት (የማኅበረሰብ ልማድ) ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን አስተዋፅኦ ለይቶና ተንትኖ ማቅረብ ነበር። በትንታኔው መሰረት በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች እምነት፣ ዕውቀትና ተግባር፣ ለዕፅዋትና እንስሳት ቀጣይነት፣ ለአካባቢ ሥነ ምህዳር ጥበቃ አበርክቶ እንዳላቸው፣ ጥናቱ ጠቁሟል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች የሕክምና አገልግሎታቸው እንዳይቋረጥ፣ ለሕይወትና ለፍጥረት ያላቸው እሳቤና እምነት፣ በአካባቢያቸው የሚገኙ ጥብቅ ቦታዎችን ታሳቢና ታላሚ በማድረግ፣ በመኖሪያ አካባቢያቸው (ግቢ፣ የእርሻና የመስኖ ቦታዎችን)፣ ገዳማት፣ አድባራት፣ አቢያተ ክርስቲያን ደብሮች፣ የመቃብር ስፍራዎች፣ የፀበል ቦታዎችን እና ጥብቅ ፓርኮችን ምርጫቸው በማድረግ እንስሳትን የመጠበቅና የማራባት፣ ዕፅዋትን የመትከል፣ የመዝራት፣ የማስፋፋትና የማባዛት ልምድ እና ዕውቀትን ማዳበራቸው፣ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ አስተዋፅኦ እንደነበረው፣ ጥናቱ አስረድቷል። እነዚህ ቦታዎች ለምን ተመረጡ ሲባል፣ "ዕፅዋትና እንስሳትን ጠበቂ ኃይልና መንፈስ አላቸው" ተብሎ በባህል ሐኪሞችና በአካባቢው ማኅበረሰብ ይታመናል (የሕመም መንስኤን ልብ ይሏል)። የባህል ሐኪሞች ከአድባራት፣ ከገዳማትና ከመሰል ቦታዎች ፀሎት ፈፅመው፣ ሥርዓተ ገቢር አድርሰው ዕፅዋትን የመቁረጥ፣ የመልቀምና የመንቀል እምነታዊና ማኅበራዊ ፈቃድ እንዳላቸው፣ ጥናቱ ጠቁሟል።

ከዚህም በተጨማሪ ዕፅዋትና እንስሳትን ለባህል መድኃኒት ሲጠቀሙ በዓመታት ሂደት ያዳበሩትን ዕውቀት፣ ክህሎትና ተግባር መነሻ በማድረግ፣ ዕፅዋት እንዳይደርቁና እንዳይጠፉ የመቅረቢያ ወቅትና ዐውዶችን በመለየት፣ መጥነውና ቀንሰው በመጠቀም፣ ቀጣይነታቸውን በማረጋገጥ መተግበራቸው፣ እንስሳት ዘራቸው እንዳይጠፋና እንዳይሰደዱ በዕድሜ ትልቅ እና ወንድ የሆኑትን መርጠው መጠቀማቸው፣ ለዕፅዋትና እንስሳት ጥበቃና ቀጣይነት ጉልህ ፋይዳ እንዳላቸው፣ ጥናቱ አስረድቷል።

በአካባቢው ማኅበረሰብ ልማድ፣ "የዕፅዋትና እንስሳት ጠባቂ መንፈስና ኃይል አለ" ተብሎ መታመኑ፣ በአድባራት፣ በገዳማት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በፀበል እና በመቃብር ቦታዎች የሚገኙ ዕፅዋት እንዳይቆረጡና እንስሳት እንዳይገደሉ ላቅ ያለ አበርክቶ እንዳላቸው፣ ጥናቱ አረጋግጧል። ይህም፣ የአካባቢው ሥነ ምህዳር በተወሰኑ ቦታዎች ተጠብቆ እና ተለይቶ እንዲኖር ምክንያት ሆኗል። እነዚህ ቦታዎች ለዕፅዋት፣ ለእንስሳት፣ ለአዕዋፍና ለነፍሳት ትስስር፣ የምግብ ሰንሰለት ሥርዓት (Food chain System) እንዳይቋረጥ ዋስትና በመሆን፣ የአካባቢን ሥነ ምህዳር

ለመጠበቅ፣ የተፈጥሮ ሚዛንን ለማደላደል፣ የዘር ምንጭና መራቢያ (Seed source/power house) አካባቢ በመሆን፤ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው፤ ጥናቱ አስረድቷል። ከነዚህ አበርክቶዎች በተጨማሪ የአካባቢው ማኅበረሰብ የዕፅዋት እና እንስሳትን ዓይነትና ባሕርይ በመለየት፤ ከዕፅዋት መራራና አቃጣይ፤ ከእንስሳት ደግሞ ሣር በል የሆኑትን የማቅረብ፤ ጣፍጭና ለስላሳ ባሕርይ ያላቸውን ዕፅዋት እና ሥጋ በል እንስሳትን የማራቅ ልማድ፤ ለምግብ ሰንሰለት ሥርዓት መቀጠልና ለሥነ ምህዳር ሚዛን መጠበቅ አስተዋጽኦ ማድረጉን፤ ጥናቱ ጠቁሟል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ርዕሰ ጉዳዮች ለሥነ ምህዳር ጥበቃ አበርክቶ ቢኖራቸውም፤ በአካባቢው ማኅበረሰብ ሥጋ በል እንስሳትን በተገኙበት የመግደል ልማድ፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት፣ በገዳም፣ በፀበልና በደብር ቦታዎች የሚገኙ አባቶችና የባህል ሐኪሞች በዕፅዋትና እንስሳት ንግድ ላይ መሳተፋቸው፤ የከተማ መስፋፋት፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የእርሻ መሬት ጥበት፣ የተፈጥሮ ሐብት እና የፍላጎት አለመመጣጠን፤ ለደን ሽፋን መቀነስ፤ ለእንስሳት ቁጥር ማነስና መጥፋት፣ ለምግብ ሰንሰለት ሥርዓት መዳከምና መቋረጥ፤ ለአካባቢ ሥነ ምህዳር ሥርዓት መዛባት፤ ዐበይት ተግዳሮት እንደነበሩ፤ ጥናቱ አረጋግጧል።

በዚህ ጥናት የሰውና የሥነ ምህዳር መስተጋብር ምን ሆኖ ተገኘ? ሲባል፤ የሰው ልጅ ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ ደህንነቱን ለማረጋገጥ፤ ከሥነ ምህዳር ሁነት ጋር ለመግባባት፣ ለመላመድና ለመስማማት፤ እሳቤው፣ ዕውቀቱና ተግባሩ በፈቀደለት መጠን አካባቢውን ይፈትሻል፣ ይመረምራል፤ ይጠይቃል። ሥነ ምህዳሩን እንዴት እና መቼ መቅረብና መራቅ እንዳለበት፤ ከዕለታዊ ሕይወቱ፣ ተግባርና ልምምዱ በመነሳት አካባቢያዊ ዕውቀቱን ይቀነብባል፤ መተዳደሪያ ሥርዓቱን ይገነባል። አካባቢያዊ ልምዱ (የሕይወት ተመክሮው)፤ ዕውቀትና ሥርዓቱ ደግሞ ከሥነ ምህዳር ጋር ተግባብቶና ተላምዶ እንዲኖር እድል ይፈጥርለታል። በሂደትም ለአካሉ ምግብ፣ ለመንፈሱ ደስታ፤ ለጤናው ምቾት፤ ለሕመሙ ፈውስ የሚላቸውን፤ የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የማዕድናት፣ የነፍሳት፣ የመልክዓ ምድር ሁነትን፤ ባሕርይና ተፈጥሮን ይመረምራል፤ ይለያል። የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብም፤ አካባቢያዊ መስተጋብሩን በማጤን፣ ዕውቀትና ተግባሩን በማስተባበር በቀጣይነት እንዴት ሊጠቀምባቸውና ሊኖርባቸው እንደሚችል የዕውቀት ማዕቀፉን (ልማዱን)፤ ሥርዓትና መዳረሻውን ይዘረጋል። በዚህ ተግባሩ ከሥነ ምህዳር (ከተፈጥሮ) ጋር ለመተዋወቅ፣ ዐውዳዊ መስተጋብሩን ጠብቆ ለመንቀሳቀስ፤ ከባህሉ፣ ከጤናው፣

ከሕመሙና ከሥነ ምህዳሩ ጋር ለመግባባትና አብሮ ለመኖር ምቹ አጋጣሚዎችን እንደፈጠረለት፤ ከምርምሩ ውጤት መገንዘብ ተችሏል፡፡

ሰው፤ የሥነ ምህዳር አካል እና አባል እንደመሆኑ መጠን በአካባቢው ተፈጥሮ ተፅዕኖ ይደርስበታል፡፡ እሳቤው፣ መኖሪያው፣ ልብስና ጉርሱ በሥነ ምህዳር ውጤቶች ሊገደብ ይችላል፡፡ በዚህ ሁነት ሰው ለተፈጥሮ ተገዢ ይሆናል (ሰው ተፈጥሮን ይለውጣል፣ ይቀይራል፣ ይገዛል፤ ይሰለጥንበታል፤ የሚለውንም መከራከሪያ ልብ ይሏል)፡፡ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብም የሥነ ምህዳር ግብዓቶችን፤ ዓይነታቸውን፣ ባሕርያቸውን፣ ተግባራቸውን በመለየት ሲቀርብና ሲርቃቸው፤ ሲተክልና ሲነቅላቸው፤ ሲበላና ሲተዋቸው፤ ሲፈራና ሲያከብራቸው ከአካላዊ፣ ከመንፈሳዊ እና ከሥነ ልቡናዊ ጤንነቱ ጋር በማስተሳሰር ዕለታዊ ተግባሩን ሲከውን መኖሩን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በሂደትም እኔነቱን፣ ማንነቱን፣ እሴቱን፣ ተላምዷዊና ባህላዊ መስተጋብሩን ለመቅረፅና ለመከወን መንስኤ እንደሆኑት፤ ከጥናቱ ይዘት መደምደም ተችሏል፡፡ የባህል ሕክምና ዕውቀቱም [ከመንፈሳዊ/ከመለኮታዊ ኃይል በስተቀር] በአካባቢያዊ ልማድ (ዕውቀትን) እንዲከውን፣ በሥነ ምህዳር ግብዓቶች እንዲወሰንና እንዲመራ ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ ተፈጥሮን ሲጠብቅ እና በአግባቡ ሲጠቀም የሕልውናው መሰረት፤ የደኅንነቱ ምክንያትና ውጤት ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በአንፃሩ፤ የተፈጥሮን ሐብት ሲያጠፉ እና ሲያራቁት ለአካሉ ምግብ፤ ለመንፈሱ ሰላም፤ ለሕይወቱ ቀጣይነት እና ለሕመሙ ፈውስን እንደሚያጣ፤ ከምርምሩ ውጤት በመነሳት መደምደም ተችሏል፡፡

## 9.2 ይሁንታ

ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ የሚካሄደውን የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ይዘትን ተንትኖ አቅርቧል፡፡ ከምርምሩ ይዘት፤ በመስክ ቆይታ ከተገኘ ልምድና መረጃ በመነሳት፤ በዘርፉ የታዩ ክፍተቶችን በማጤን፤ የይሁንታ ሃሳቦች እና ቀጣይ የምርምር አቅጣጫዎችን እንደሚከተለው ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

- ❖ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ የበሽታ እሳቤ፤ የሕመም መንስኤዎች በዋናነት ጅን፣ ቡዳ፣ ዛር፣ የዐየርና የመሬት ኃኔል እንደሆኑ ይታመናል፡፡ በዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ደግሞ የሕመም መንስኤዎች (ቫይረስ፣ ፈንገስ፣ ባክቴሪያ፣ አሜባ፣ ጥገኛ ትላትል እና ተሕዋሲያን) የአካባቢ ብክለት፣ የግል እና የምግብ ንፅሕና ጉድለት፣ የዐየር

ንብረት ለውጥና የሥነ ምህዳር መዛባት፣ ድንገተኛ አደጋ ዐበይት ምክንያት እንደሆኑ ይነገራል፡፡ በሁለቱ ሙያዎች መካከል የማይታረቁና ተቃራኒ ሃሳቦች ይነሳሉ፤ ዓላማና ግባቸው ደግሞ አካላዊ ቁስልና መንፈሳዊ ጭንቀትን መፈወስና ማስታገስ ነው፡፡ የተጠኚው አካባቢ ማኅበረሰብ ደግሞ በመርፌና በቀዶ ጥገና የሚሰጡ የዘመናዊ ሕክምና አገልግሎትን በመፍራትና በመግፋት "ደም አፍሰው ለአጋንንት ይዳርጋሉ፤ ቡዳ ያስበላሉ፤ ለሰራቂያን ያጋልጣሉ" በማለት በባህል ሕክምና ሞክረው ካልተሳካ፤ ሕመማቸው ተባብሶ ለከፋ ጉዳትና ችግል ሲጋለጡ ይታያል፡፡ እነዚህ ሁለት የሕክምና ዘርፎች የዕውቀት ምንጭና መሰረታቸው፤ እሳቤና ፍልስፍናቸው መንፈሳዊና ዓለማዊ ሆኖ ቢለያይም፤ ባለሙያዎቹ ተቀራርበው ቢወያዩና በጋራ እሳቤዎች ላይ ተመስርተው ማኅበረሰቡን በማስተማር ችግሩን ለመፍታት ጥረት ቢያደረጉ መልካም እንደሆነ አጥኚው ያምናል፡፡

- የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ፤ በማኅበረሰብ ልማድና በሥነ ምህዳር ግብዓቶች እንደሚወሰን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ ይህን ተግባር ታሳቢ በማድረግ፤ የአካባቢው ባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች፤ በባህልና በጤና ላይ ምርምር የሚያካሂዱ አባላትና ተቋማት፤ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞችን ዕውቀት፣ ተግባርና ልማድ እየተከታተሉ መመዝገብ፣ ማደራጀትና ማጥናት ቢቻል፤ ለአካላዊ ቁስልና ለመንፈሳዊ ጭንቀት ፈውስ የሚባሉ ተግባራትን ለይቶ፤ ዕውቀቱን ለማሻሻል፤ ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ፤ የማኅበረሰቡን የጤና ችግሮች በአካባቢው ግብዓት፣ ዕውቀትና ሥርዓት ለመፍታት መልካም አጋጣሚን እንደሚፈጥር ይታሰባል፡፡

- የጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ልማድና የባህል ሕክምና ዕውቀት፤ ከባህል፣ ከጤና፣ ከሕመም መንስኤ እና ከሥነ ምህዳር ጋር ጥብቅ ትስስርና መስተጋብር እንዳላቸው በጥናቱ ውስጥ በግልፅ ታይቷል፡፡ ከባህል፣ ከጤና እና ከሥነ ምህዳር ጋር የተገናኙ የፎክሎር ክዋኔዎች (ሚታዊ ተረኮች፣ ቃል ግጥሞች፣ ልማዳዊ ሥርዓቶች፣ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ሐብቶች) በባለሙያ ተሰብስበው ቢጠኑ፣ ቢተነተኑ እና ቢሰነዱ የማኅበረሰቡን ዕውቀት፣ ተግባር፣ የዕለት ሕይወትና ፍልስፍናን ከማስረዳታቸው ባለፈ፤ ተጨባጭ ዕውቀትና ጥበብን ከማኅበረሰቡ ልማድ ለማውጣትና ለማግኘት፤ ማኅበራዊ ችግሮችን (የጤና፣ የሰላም፣…) ለመፍታት አማራጭ ሳይሆን ብቸኛ መፍትሔ ሆነው የሚመጡበት አጋጣሚ እንደሚኖር ይታሰባል፡፡ ስለዚህ በአካባቢው የሚገኙ የባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች የማኅበረሰብን ፎክሎር ከሥነ ምህዳር መስተጋብር ጋር በማስተሳሰር

ልማዱን፣ ዕውቀትና ተግባሩን ተከታትለው ቢሰበስቡ፣ ቢያጠኑና ቢሰንዱ፤ ለቀጣይ ምርምር ግብዓት በመሆን፤ የማኅበረሰቡን ዕውቀት፣ የኑሮ መሰረት እና የሥነ ምህዳርን ይዘት ለመረዳት፤ ከጤና ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት አበርክቶ እንዳላቸው፤ ይታመናል፡፡

❖ የማኅበረሰብ ጤና እና የባህል ሕክምና ተግባር (ዕውቀት) በሥነ ምህዳር ይዘት ተፅእኖ እንደሚደርስበት፤ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ለባህላዊ መድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት እና እንስሳት በሰው ሰራሽ እና በሥነ ምህዳር መዛባት ምክንያት ከእለት ወደ እለት እየተመናመኑ መሄዳቸው ደግሞ ለሕክምና ዘርፉ ተግዳሮት እንደሆኑ በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት እና የሥነ ምህዳር ሚዛንን ለመጠበቅ፤ የባህል ሐኪሞች፣ የአካባቢው ማኅበረሰብ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች፣ የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች፤ በጉዳዩ አሳሳቢነት እና ቀጣይነት ላይ ቢወያዩ፤ ችግሩ የሚቃለልበትን የመፍትሔ ሃሳቦች ቢያቀርቡና የጋራ መፍትሔ ቢፈልጉ መልካም ነው ተብሎ በአጥኚው ይታሰባል፡፡ በቀጣይ ጥናት ቢተኮሩባቸው መልካም ነው፤ የሚባሉ ርዕሰ ጉዳዮች እንደሚከትለው ቀርበዋል፡-

- በማዕድንና በፀበል ቦታዎች፤ በፍል ዉኃና በጭስ የሚሰጡ ሕክምናዎችን ታሳቢ በማድረግ ምርምር ቢደረግ፤
- በባህል ሕክምና ዕውቀት የሚተገበረው የበሽታ መለያና መመርመሪያ ዘዴዎች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ በዘመናዊ ሕክምና ሣይንስ በንፅፅር ቢጠኑ፤
- በመድኃኒት አሰጣጥ ሂደት የበሽታ ዓይነትና ባሕርይ፤ ብላ/አትብላ፤ የምግብ ምርጫና ክልከላ ከምግብ ንጥረ ነገር ይዘት፤ ከበሽታው ዓይነት ጋር ምን ዓይነት ተዛምዶ እና ተቃርኖ እንዳላቸው በንፅፅር ቢጠኑ፤ የዘርፉን ክፍተት ለመሙላት አበርክቶ እንዳላቸው ይታሰባል፡፡

Notes: Reference work, According to The APA 6th Style (Bookman Old Style).

## ማጣቀሻ ምንጮች


መስፍን ፍቃዱ (2002)፤ "የሃገረሰባዊ መድኃኒቶች ቅመማና ባህላዊ አጠቃቀም በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ማኅሌት ዘነበ (2011)፤ "ሃገረሰባዊ ሕክምና፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ"፤ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ የፎክሎር (የባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

<u>ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት</u> (1978)፤ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (የታተመ)፡፡

ምህረት ዳኘው (2000)፤ "በአዲስ አበባ ከተማ የባህላዊ መድኃኒት አዘገጃጀት፣ አሰጣጥና አጠቃቀም"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ሠናይ ምስክር (2009)፤ <u>መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ</u>፤4ኛ እትም፣ ባሕር ዳር፣ አፍሪካ ፕሪንቲንግ፡፡

ተመስገን በየነ (2003)፤ "በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በግሼ ወረዳ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ (2001)፤ <u>በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ</u>፤ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

አሰፋ ባልቻ (2008)፤ <u>የኢትዮጵያ ባሕላዊ መድኃኒትና ሕክምና የምዕተ ዓመት ጉዞ፤</u> አዲስ አበባ፣ (ማተሚያ ቦታ አልተገለፀም)፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948)፤ <u>መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤</u> አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ዋልተንጉስ መኮንን (2007)፤ "ተፈጥሮን መናቅ ሥጋን ማክበር፤ ለክፉ ዐይን አጋላጭ ክስተት በምስራቅ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማህበረሰብ እምነት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪ ጥናት ማሟያ የቀረበ፡፡

ዐቢዩ አስማማው (2010)፤ "የቦሮ ሽናሻ ብሔረሰብ ሃገረሰባዊ መድኃኒት ምንጩ፤ ተስተላልፎውና ገቢሩ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪ ጥናት ማሟያ የቀረበ፡፡

ዓለማየሁ ዘሪሁን (2000)፤ "የኑዌር ማኅበረሰብ የባህል ህክምና እውቀት አመለካከት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (1980)፤ <u>መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት</u>፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993)፤ <u>አማርኛ መዝገበ ቃላት</u>፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፣ 2010፡፡

የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረ-ኢኮኖሚ መረጃ፤ 2006፡፡

የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤ 2007፡፡

የፋርጣ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት፤ 2010፡፡

ይሁኔ አየለ፤ (2010)፤ <u>ሙሉ ጤናን ፍለጋ</u>፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ደስታ ተክለወልድ (1962)፤ <u>ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት</u>፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ጠና ደዎ (2009)፤ <u>ሰው ግብረገብና ሥነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች</u>፤ ሁለተኛ እትም፤ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ፈቃደ አዘዘ (1991)፤ የስነ-ቃል መምሪያ፤ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት።

…………(2004)፤"ቁዘማ፡-ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ"፤ በሺፈራው በቀለ፣ የአርታኦት መድበል ውስጥ፤ ባህልና ልማት በኢትዮጵያ። አዲስ አበባ፣ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ ከገፅ 97-136።

ፈቃዱ ፋሳስ (2002)፤ የኢትዮጵያ የባህል መድኃኒት በሳይንሳዊ አቀራረብ፤ የመድኃኒት ዕፅዋት፤ አሜሪካ፣ (አሳታሚ አልተገለፀም)።

ፍቅርተ ማቴዎስ (2009)፤ "ከዕፅዋት የሚገኙ ሃገረሰባዊ መድኃኒቶች ዕውቀት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ በከምባታ ብሔረሰብ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት።

Abraraw, T.(1993).“Traditional Medicine in an Urban Center, Belief and Practices (The Case of Dessie Town, North Ethiopia)” M.A Thesis, Department of Social Anthropology; Addis Ababa University.

Agonafir, E.(2004). “Vision and Mission of Traditional Health Practitioners in Ethiopia.”In Urga. K, Assefa. A, and Guta. M, (eds). Traditional Medicine in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: Addis Ababa: PP. 48-51.

Alemayehu, M.(1984). “Traditional Ethiopian Medicines.” Institute of Ethiopian Studies; Eighth International Conferences of Ethiopian Studies: Addis Ababa University.

Allen, D. and Hatfield, G.(2004). Medicinal Plants in Folk Tradition: An Ethnobotany of Britain & Ireland. China; Timber Press, Inc.

Amazat, J. and, Razum, O.(2014). Medical Sociology in Africa. New York; Springer International Publishing Switzerland.

Assefa, B.(1992). “Traditional Medicine in Wollo Nature and History.” M.A Thesis, Department of History: Addis Ababa University.

Baer, H, Singer, M, and Susser, I. (2003). Medical Anthropology and the World System.2nd ed; United States of America; Greenwood Publishing Group Inc.

Baquar, S.(1995). "The Role of Traditional Medicine in a Rural Environment." Traditional Medicine in Africa; PP.56-79.

Barsh, R.(1997). "The Epistemology of Traditional Healing Systems". Society for Applied Anthropology; Vol.56.No. 1;PP.28-37.

Bascom, W.(1954). "Folklore and Anthropology." The Journal of American Folklore, *66* (262); PP. 283-290.

Bauman, R.(1975). "Verbal Art as Performance."Journal of American Folklore; University of Texas at Austin, PP.290-311.

Bauman, R.(1977).Verbal Art as Performance. Prospect Heights. IL: Waveland Press.

Bauman, R.(1983).“The Field Study of Folklore in Context.” Handbook of American Folklore. Ed. Richard M. Dorson. Bloomington: Indiana University Press, PP.362-368.

Bauman, R.(1986).Story, Performance, and Event; Contextual Studies of Oral Narratives. New York: Cambridge University Press.

Bauman, R.(1992).Folklore, Cultural Performance, and Popular Entertainments: A Communication-Centered Handbook. (Ed.) New York: Oxford University Press.

Benally, S (2010)."Health, Illness, and Healing". In Cultural Foundation. England; Open University Press.

Ben-Amos, D.(1971). “Toward a Definition of Folklore in Context.”Journal of American Folklore. 84:PP. 3-15.

Ben-Amos, D.(1975). “Folklore in African Society”. Research in African Literature. Vol 6.2: PP.165-198.

Ben-Amos, D.(1976). Folklore Genres. (Ed). Austin: University of Texas Press.

Ben-Amos, D.(1977). “The Context of Folklore: Implications and prospects”. The Forms of Folklore. Ed. William R. Bascom. Boulder: West view Press.

Ben-Amos, D.(1993). “'Context', in context”. Western Folklore. Vol. 52:PP. 209 – 226.

Ben-Amos, D.(1997). "The Context of Folklore: Implications and prospects". The Forms of Folklore. Ed. William R. Bascom. Boulder: Westview Press.

Berger, P. and Luckman, N.(1966). The Social Construction of Reality. USA; New York.

Berger, A.(2010). The Objects of Affection Semiotics and Consumer Culture. USA, Palgrave Macmillan.

Black, W. (1883). Folk Medicine: A Chapter in the History of Culture. London: Folklore Society.

Blaxter,L, Hughes,c, and Tight, M.(2006). How to Research. 3rd ed: England; Open University Press.

Bodeker, G and Burford, G (2007).Traditional, Complementary and Alternative Medicine: Policy and Public Health Perspectives. (Ed) UK; Oxford University Imperial College Press.

Bodeker, G.(2010). "Traditional Knowledge and Health". In Suneetha M. Subramanian and Balakrishna Pisupati .Traditional Knowledge in Policy and Practice: Approaches to Development and Human Well-being. New York; United Nations University Press.

Brady, E.(2001). Healing Logics: Culture and Medicine in Modern Health Belief Systems. Edited Logan, Utah: Utah State University Press.

Busenbark, E.(1949). Symbols, Sex, and The Stars: In Popular Beliefs. California- San Diego; Truth Seeker,Co.,Inc.

Chappell, B.(1999). Folklore Semiotic; Charles Peirce and the Experience of Signs. Folklore Forum.

Chavunduka, G. (1994). Traditional Medicine in Modern Zimbabwe. Zimbabwe: University of Zimbabwe Publications 115p. ISBN, 908307403.

Chokevivat, V. and Chuthaputt,A (2005). "The Role of Thai Traditional Medicine in Health Promotion" Thailand; Department for the Development of Thai Traditional and Alternative Medicine, Ministry of Public Health.

Creswell, J.(2014). Research Design: Qualitative, Quantitative, and Mixed Methods Approach. 4th ed. Thousand Oaks, CA: SAGE.

Danesi, M.(2004). Message, Sign and Meanings A Basic Textbook in Semiotics and Communication. (3rd ed.) Volume 1 in the Series Studies in Linguistic and Cultural Anthropology; University of Toronto.

Dawit, A. (1986). "Traditional Medicine in Ethiopia: The Attempts Being Made to Promote it for Effective and Better Utilization." In SINET; 9(suppl.); PP.61-69.

Dawson, C.(2009). Introduction to Research Methods: A Practical Guide for any one Understanding a Research Project. Hachetter UK.

Denzin, N., and Lincoln, Y.(2000). "The Discipline and Practice of Qualitative Research." Handbook of Qualitative Research; *2*.PP: 1-28.

Desta B.(2004). ''Review of Traditional Medicine Research in Ethiopia" Proceedings of a National Workshop: Addis Ababa, 30 June-2July, 2004.

Destro, A. (2010). "Cosmology and Mythology". In James Brix (Ed). 21st Century Anthropology; A Reference Handbook. Canisivs College and State University of New York; SAGA Publication, PP.227-234.

Dorson, R.(1972). Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago; University of Chicago Press.

Dundes, A (1980). Interpreting Folklore. India; Indiana University Press.

Dundes, A. (1965). The Study of Folklore. Upper Saddle River, NJ, Prentice Hall.

Ember, C, and Ember, M. (2004). Encyclopedia of Medical Anthropology: Health and Illness in the World's Cultures. Edited New York; Kluwer Academic/Plenum Publishers. Logan, Utah

Fekadu, F. (2001). Ethiopian Traditional Medicine: Common Medicinal Plants in Perspective. Sioux City Lowa: St. Luke's Regional Medical Center.

Feraraho, G, and Andreatta, S.(2010). Cultural Anthropology; An Applied Perspective.(8th Ed). United State of America; Wadsworth print.

Geertz, C. (1973). The Interpretation of Culture: Selected Essays By Clifford Geertz. USA, Basic Books Publishing.

Good, C.(1987). Ethno-Medical System in Africa: Patterns of Traditional Medicine in Rural and Urban Kenya. New York: The Guilford Press.

Greco, J.(2001). "Vertues and Rules in Epistemology." In Abrol Fairweather and Linda Zagzebski (eds). Vertue Epistemology: Essays on Epistemic Vertue and Responsibility. New York; Oxford University Press.

Gumede, M.(1990). Traditional Healers: A Medical Practitioner's Perspective. Jahannesbarg: Skotaville Publisher, 1990.

Hammersley, M, and Atkinson, P.(2007). Ethnography Principles in Practice. 3rd ed, London: Routledge.

Heindel, M and Heindel, F.(2011). Astro-Diagnosis A Guide to Healing. 10th ed.; USA, California.

Helman, C.(1984). Culture, Health and Illness.An Introduction for Health Professionals. Bristol-London-Boston; wrighit PSG.

Higgs, J, Trede, F and Rothwell, L. (2007). Practice, Education, Work and Society. New York; Springer publisher.

Hufford, J. (1986). "Folk Healers" In Richard Dorson M (ed). Handbook of American Folklore. India: Indian University Press: P306-313.

Hurreize, S.(2006). Studies in African Applied Folklore. Khartoum: The Occasions of African Universities Congress.

Jackson, B.(1987). Fieldwork. Urbana and Chicago: University of Illinois Press.

Janes,C., Stall, R. and Gifford, S. (eds.). (1986). Anthropology and Epidemology. USA. Reidel Publishing Company.

Kannon, B.(2004). "Integration of Traditional Medicine with Modern Medicine." In Urga. K, Assefa. A, and Guta. M (eds). Traditional Medicine in Ethiopia.

Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: Addis Ababa, (2004): PP.32-38.

Kapchan, D.(1995). "Performance" Journal of American Folklore, Vol.108. No.430;PP.479-508.

Kayne, S.(2010). Traditional Medicine: A global Perspective. London; Pharmaceutical Press.

Kleinman, A.(1980). Patients and Healers in the Context of Culture: An Exploration of the Borderland between Anthropology, Medicine, and Psychiatry. Berkeley: University of California.

Kleinman, A.(1984). "Indigenous Systems of Healing: Questions for Professional, Popular, and Folk Care". In Journal of Alternative Medicines. J.W. Salmon, ed. 138-164. London: Tavistock Publications.

Kloos, H. and Zein, A. (1993). (eds.). The Ecology of Health and Disease in Ethiopia. Boulder, Sanfrancisco and Oxford, Westview Press.

Kloos, J.(1973). "A Historical Overview of Traditional Medicine Practices and Policy in Ethiopia." Ethiopian Journal of Health Development, *20*(2), 127-134.

Kokwaro, O.(1976). Medicinal Plants of East Africa. East Africa Press.

Konadu, K.(2007). Indigenous Medicine and Knowledge in African Society. New York and London: Taylor and Francis Group PLC.

Kothari, C.(2004). Research Methodology: Methods and Techniques. India; New Age International Limited Publisher.

Leung, L.(2010). "Traditional Chinese Medicine a Beginner's Guide." University of Ottawa; Oxford University Press: InnovAiT,Vol;N0.1: PP 1-7.

Lewis, J.(2003). The Astrology Book. 2nd Ed; USA: Visible ink Press.

Lindstorm, V.(1997). "Melting in to Great Waters". Journals of Finnish form Nine Province, Papers from Finnforum V.PP.11-19.

Lopatin, A.(1960). “Origin of the Native American Steam Bath” American Anthropologist; University of Southern California New Series, PP;977-993.

Mack, N, Woodsong, C, MacQueen, K, Greg Guest, G, and Namay, E.(2005). Qualitative Research Methods: A data Collector’s Field Guide. USA, Family Health International.

Maclachlan, M.(2006). Culture and Health: A Critical Perspective Towards Global Health. (2nd Ed) England; John Wiley & Sons Ltd.

Martin, D. (2003). Traditional Medicine in Contemporary Contexts: Protecting and Respecting Indigenous Knowledge and Medicine. Aborigina; National Aboriginal Health Organization.

McElroy, A. and Patricia K.(2004). Medical Anthropology in Ecological Perspective. (4th ed). Westview Press.

McElroy, A. and Townsend, P.(2009). Medical Anthropology in Ecological Perspective. (5thEd.) United States of America; Westview Press.

Mekonen, B. (1988). "Integrating Indigenous and Cosmopolitan Medicine in Ethiopia." UMI Dissertation Information Service.

Mekonen, M.(2010). “Indigenous Medicine, Beliefs and Practices Among; The Kunama In Sheraro, Tigray” Addis Ababa University, M.A. Thesis; Department of Ethiopian Study.

Mekonen, W.(2008). “The Attitude of Traditional Practitioners, Biomedical Workers and the Public to Wards Traditional Medicines with Particular Reference to Rabies Healers in West Gojjam.” Addis Ababa University, MA Thesis, Department of Ethiopian Studies.

Messeret, S.(1996). “The Role of Health Professionals in the Development of Traditional Medicine in Ethiopia.” In Dawit Abebe (ed). Development and Utilization of Herbal Remedies in Ethiopia. Addis Ababa, Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: PP. 15-19.

Milton, K.(1996). Environmentalism and Cultural Theory; Exploring the Role of Anthropology in Environmental Discourse. London and New York Routledge.

Mirgissa, K.(1993). "Indigenous Medical Beliefs and Practices Among the Oromo of Illubabor" Addis Ababa University, MA thesis in Social Anthropology.

Mishra, S, Yadlapalli,S, and Kusuma, B.(2013). "Concepts of Health and Illness: Continuity and Change A mong Migrant Tribal Community in An Eastern Indian City". Slovene Anthropological Society; Anthropological Notebook 19 (3): PP. 61–69. ISSN 1408-032X.

Molvaer, R. K.(1987). "Medical Anthropology: Topics of Relevance for Health Workers and Students of Health in Ethiopia." Addis Ababa: UNICEF/ Ministry of Health.

Murdock, G. P.(1980). Theories of Illness: A World Survey. Pittsburgh; University of Pittsburgh Press.

Napier, D. Ancarno, C, Butler, B, and Calabrese, J. (2014). "Culture and Health". The Lancet Commissions; Vol.384: PP.1607-1639.

O'reilly, K.(2012). Ethnographic Methods. Country (ud), Routledge,plc.

Oring, E.(1986). Folk Groups and Folk Genres: An Introduction. (Ed) Logan: Utah State University Press.

Pankhurst, R.(1965). "An Historical Examination of Traditional Ethiopian Medicine and Surgery." Publisher not identified.

Pankhurst, R.(1976). "Historical Reflections on the Traditional Ethiopian Pharmacopoeia". Journal of Ethiopian Pharm; *Vol. 2*, 29-33.

Pankhurst, R. (1990). An Introduction to the Medical History of Ethiopia; with a Post Script by Asrat Woldeyes. Red Sea. New Jeresy.

Pankhurst, R.(2005). "Traditional Ethiopian Knowledge of Medicine and Surgery: An Introduction to Sources." Indigenous Knowledge Systems in Ethiopia:

Proceedings of the first national workshop of the Ethiopia chapter of OSSREA, Image printing Press.

Payyappallimana, U.(2006). "Role of Traditional Medicine in Primary Health Care: An Overview of Perspectives and Challenges". World Health Report 2006—http://www.who.int/whr/2006/en/ accessed on 28th August 2009.

Pehkonen, E, and Pietilä, R.(2003). "On Relationships between Beliefs and Knowledge in Mathematics Education." Proceedings of the CERME-3 (Bellaria) Meeting.

Pereira, S, and Dein, S. (1995). "Making Sense of Possession States Psychopathology and Differential-Diagnosis". Medical Journal of British Hospital: Vol.53; PP.582-598.

Pool, R. and Geissler, W.(2005). Medical Anthropology. England; London School of Hygiene and Tropical Medicine: Open University Press.

Posner, R.(2004). "Basic Tasks of Cultural Semiotics." In Gloria Withalm and Josef Wallmannsberger(eds). Signs of Power- Power of Signs. Vienna; INST, PP.56-89.

Radley, A.(1993). Worlds of Illness; Biographical and Cultural Perspectives on Health and Disease. London and New York; A Tavistock/Routledge Publication.

Read, M.(1966). Culture, Health and Disease. London: Tavistock Plc.

Richter, M.(2004). "Traditional Medicine and Traditional Healers in South Africa." AIDS Law Project; Discussion paper prepared for the Treatment Action Campaign and AIDS Law Project.

Riddle, J. (2013). "Folk Tradition and Folk Medicine: Recognition of Drugs in Classical Antiquity". Pharmacy in History; American Institute of the History of Pharmacy, Vol. 55, No. 2/3, pp. 64-87.

Schechner, R.(2003). Performance Theory. London and New York; Taylor and Francis Group Plc.

Schensul, J, Lecompte, M, Nastasi, B, and Borgatti, S. (1999). Enhanced Ethnographic Methods. New York, Altamira Press.

Schoemaker, G.(1990). The Emergence of Folklore in Everyday Life: A Field Guide and Source Book. (Ed).Trickster Press.

Sebeok, T.(2001). Signs; An Introduction to Semiotics. 2nd ed; Toronto, University of Toronto Press.

Short, T.(2007). Peirce's Theory of Signs. United States os America; Cambridge University Press.

Sims, M, and Stephens, M.(2005). Living Folklore; An Introduction to the Study of People and their Traditions. The Ohio State University.

Sindiga,I., Chacha, C., & Kanunah, M.(1995).Traditional Medicine in Africa. East African Publishers.

Sosa, E. (2007). A Vertue Epistemology; Apt Belief and Reflective Knowledge. Vol.I: New York; Oxford University Press.

Sofowora, A.(1982). Medicinal Plants and Traditional Medicine in Africa. John Wiley and Sons LTD.

Steiner, R. P.(1986). Folk Medicine: the Art and the Science. Publisher not identified.

Steward, J.(2006). "The Concept and Method of Cultural Ecology" In Nora Haenn and Richard R.Wilk (eds). The Environment in Anthropology. New York and London Press; www.nyu press.org.

Storey, J.(2016). Cultural Theory and Popular Culture An Introduction.5th(ed.) University of Sunderland; www.pearsoned.co.uk/storey.

Strinati, D.(2004). An Introduction to Theories of Popular Culture. 2nd (ed.). London and New York; Routledge press.

Sutton, M. and Anderson, E.(2010). Introduction to Cultural Ecology. 2nd (ed); New York.Published by AltaMira Press.

Tebaber, C. (2015). “Indigenous Medical Knowledge and Practices: Cultural and Environmental Values of Medicinal Plants Used by the Konso People of South Western Ethiopia.” Unpublished Dissertation Submitted to the Department of Social Anthropology; Addis Ababa University.

Tesfaye, A.(1998). "Traditional Medicine in An Urban Centre: Beliefs and Practices: the Case of Dessie Town, Northern Ethiopia" (MA thesis in Social Anthropology, Addis Ababa University).

Teshome, B. (2000). "Initiation of Healers in Ethiopia: A Case Study". Journal of Anthropology. Department of Ethno medicine, University of Vienna, Austria, Coll. Antropol. 24. 2: PP. 555–563.

Ingold, T. (2012). "Toward an Ecology of Materials." Annual Review of Anthropology. (2012.41); PP. 427-442. Downloaded from www. annual reviews. org.

Toelken, B.(1996). The Dynamics of Folklore. Logan, Utah State University Press.

Trostle, J.(2005). Epidemiology and Culture. New York; University of Massachusett: Cambridge Studies in Medical Anthropology, Cambridge University Press.

UNDEP (2008). Indigenous Knowledge in Disaster Management in Africa. Kenya Nairobi; United Nations Environment Programme.

Vanderstoep, S. and Johnston, D.(2009). Research Methods for Everyday Life. John Willey Press.

WHO (2002). WHO Traditional Medicine Strategy 2002-2005. Geneva; World Health Organization.

WHO (2007). WHO International Standard Terminologies on Traditional Medicine in the Western Pacific Region. Geneva; World Health Organization.

WHO (2015). Connecting Global Priorities: Biodiversity and Human Health: A State of Knowledge Review. WHO; WHO web site, (http://www.who.int/about/licensing/copyright form/en/index.html) .

WHO-AFRO. (2010)."African Traditional Medicine Day". The African Health Monitor Special Issues; WHO Regional Office for Africa: Brazzaville Republic of Congo.

Waldram, J.(2000). "The Efficacy of Traditional Medicine: Current Theoretical and Methodological issues." Medical Anthropology Quarterly: Blackwell Publishing on Behalf of the American Anthropological Association; New series, Vol.14, No 4 (2000): pp 603-625.

Wilbrit, W.(1988). Black Folk Medicine: The Therapeutic Significance of Faith and Trust. (Ed.) Transaction Publishers.

Williams, L.(2006)."Ethno Medicine". India. West Indian Med. 55 (4): 215.

Winkelman, M.(2009). Culture and Health Applying Medical Anthropology. San Francisco; John Wiley and Sons Imprint.

Wondwoson, T.(1999). "Indigenous Medicinal Plants Used in Ethiopia". Viennese Ethno medicine News Letter; vol.9,No.2:PP.28-32.

Wondwosen, T.(2006).Medical Pluralism in Ethiopia. German: Shaker Verlag Gmb.

Yoder, D.(1972). "Folk Medicine" In Richard Dorson (ed).Folklore and Folk life; An Introduction. Chicago: University of Chicago Press;PP.190-214.

Young, A.(1970). Medical Beliefs and Practices of Begemder Amhara. Published PhD Dissertation in Philadelphia: University of Pensylvania.

Young, A.(1976). "Internalizing and Externalizing Medical Belief System; An Ethiopian Example." Journal of Social Science and Medicine Department of Anthropology, USA Case Western Reserve University, 1976, Vol.10. PP.147-156.

Young, A.(1980). "An Anthropological Perspective on Medical Knowledge". The Journal of Medicine and Philosophy. (1980); vol. 5, no. 2.PP.102-116.

Zerihun, D.(2001). “Culture, Belief and Mental Illness among the Zay”. Addis Ababa University, M.A Thesis, Department of Social Anthropology.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡- <u>የምልከታ መከታተያ ቅፅ</u>፤

የዚህ ምልከታ ዓላማ የባህል ሐኪሞች እና የታካሚዎችን ግንኙነት፣ መስተጋብር፣ ተግባር እና አካባቢያዊ ሁነትን ለመገንዘብ የታለመ ነው፡፡ በምርምሩ ሂደት የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

1. በባህል ሕክምና መስጫ ቦታ/ቤት በውስጥና በውጭ ግድግዳ ምን ተሰቅሎ/ተለጥፎ ይታያል?
   ..........................................................................................................................
   ..........................................................................................................................
   ....................................................................................................
2. በቤት ውስጥ የመድኃኒት ግብዓቶች በምን መልክና ይዘት ተሰድረው ተቀምጠዋል?.
   ..........................................................................................................................
   ..........................................................................................................................
   ....................................................................................................
3. በባህል ሐኪሙ እና በመታካሚው/ዋ መካከል ምን ዓይነት ንግግር፣ ግንኙነትና ትእዛዝ/ መመሪያ ነበር?
   ..........................................................................................................................
   ....................................................................................................
4. በባህል ሐኪሙ መኖሪያ ቤት ግቢ እና ጓሮ ምን ዓይነት ዕፅዋት ይገኛሉ?
   ..........................................................................................................................
   ............................................................................................................
5. በመድኃኒት መቀመሚያ ቦታ ምን ዓይነት መቀመሚያ መሳሪያዎች ይገኛሉ?
   ..........................................................................................................................
   ............................................................................................................
6. ለመድኃኒት ቅመማ የተዘጋጁ ግብዓቶች ምን ምን ናቸው?
   ..........................................................................................................................
   ............................................................................................................
7. ዕፀ መድኃኒት ከመስክ ለመሰብሰብ ምን ዓይነት መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ይዘው ይሄዳሉ?
   ..........................................................................................................................
   ............................................................................................................
8. የመድኃኒት ግብዓት የሰበሰቡበት ቦታ፡-......................... ዕለት፡-.............................
   ቀን፡-........................ ሠዓት፡-...................
9. ከመስክ ዕፀ መድኃኒት ሲሰበስቡ ምን አይነት ሥርዓት/ ቅደም ተከተልን ተገበሩ?
   ..........................................................................................................................
   ....................................................................................................................

10. በዕፅ አቆራረጥ፣ አቆፋፈር፣ አያያዝ፣ አሰባሰብ፣... አቅጣጫና ጥንቃቄ ምን ሥርዓት ይታያል?

..........................................................................................................................................

......................................................................................................................

11. የመድኃኒት ግብዓት ከመስክ ሰብስበው ሲመለሱ በየት ቦታ አስቀመጡ? የቦታው ሁነት?

..........................................................................................................................................

......................................................................................................................

12. በመድኃኒት ቅመማ ወቅት ምን ምን ሂደቶች ይታያሉ?

..........................................................................................................................................

..................................................................................................................

13. በባህል ሕክምና መስጫ ቦታ ምን ያህል ታካሚዎች ይገኛሉ?............................

14. በዕለቱ የነበሩ ታካሚዎች ማኅበራዊ ደረጃ (ሕጻናት፣ ወጣት፣ ሽማግሌ፣ ወንድ/ሴት፣...)

................................................................................................................................

15. የባህል ሐኪሙ ምን ዓይነት አልባሳትና ጌጣጌጦችን ለብሰው/ አድርገው ይታያሉ?

................................................................................................................................

16. ታካሚዎች ምን ዓይነት አልባሳትና ጌጣጌጦችን ለብሰው/ አድርገው ይታያሉ?

................................................................................................................................

17. በሕክምና መስጫ ቦታው ምን ዓይነት ድምፅ እና ሁነት ይሰማል/ ይካሄዳል?

................................................................................................................................

................................................................................................................................

18. የባህል ሐኪሙ የምርመራ ሂደትና ድርጊት ቅደም ተከተል ምን ይመስላል?
(ለመረጃ ሰብሳቢው ግልጽና ምስጢር ምርመራዎች/ እይታዎች ምን ምን ናቸው)

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

.........................................................................................................

19. የባህል ሐኪሙ አጋንንት/ እርኩስ መናፍስት ከሕሙማን ሲያስወጡ ይሰሙ የነበሩ፡-
ድምፆች፡-.....................................................................................................................
የባህል ሐኪሙ ቅደም ተከተላዊ ድርጊቶች፡.........................................................................

..........................................................................................................................................

የታካሚዎች ሁነትና ስሜት፡-...................................................................................
በምልከታው ዕለት የነበሩ አስታማሚዎችና የሌሎች ሕሙማን ስሜት፡-

..........................................................................................................................................

..........................................................................................................................................

20. ለታካሚዎች የተሰጡ መድኃኒቶች ይዘት ምን ዓይነት ነው? (በሚጠጣ፣ በሚቀባ፣ በሚጨስ፣ በሚታሰር)

..................................................................................................................................................

...........................................................................................................................

አባሪ ሁለት፡- ለባህል ሐኪሞች፤ ለዘመናዊ ሐኪሞች፣ ለአካባቢው ማኅበረሰብ፣ ለተፈጥሮ ሐብት፣ ለባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች የቀረቡ ቃለመጠይቆች፤

2.1 ቃለመጠይቅ፡- ለባህል ሐኪሞች

የዚህ ቃለመጠይቅ ዓላማ "የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ" በሚል ርዕስ ለ3ኛ ዲግሪ (PhD) ማሟያ ለሚሰራ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፤ ለጥናቱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የታለመ ነው፡፡ የጥያቄዎቹ ዐቢይ ትኩረት በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መንስኤ እና የምርመራ ዘዴን ለመግለጽ፣ የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ ሂደትን ለመዘርዘር፣ እንዲሁም የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን አበርክቶና ተግዳሮት ለመለየት ነው፡፡ እርሰዎ የሚሰጡት መረጃ ምስጢራዊነቱ ተጠብቆ፤ ለትምህርታዊ ዓላማ እና ተግባር ብቻ ይውላል፡፡ እርሰዎ ፈቅደው የሚሰጡኝን መረጃ በማስታወሻ ደብተር፣ በመቅረፀ ድምፅ፣ በፎቶ ግራፍ እና በቪዲዮ ካሜራ እንድቀርፅ መልካም ፈቃድዎን እየጠየቅሁ፤ ለሚያደርጉልኝ ትብብር ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

ሀ/ የቃለመጠይቅ መረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃ

I. ሙሉ ስም፡-................................
II. ዕድሜ፡-.......................................
III. ጾታ፡-.........................................
IV. ሃይማኖት፡-..................................
V. የጋብቻ ሁኔታ፡-.............................
VI. ሥራ/መተዳደሪያ፡-..........................
VII. የትምህርት ደረጃ፡-..........................
VIII. መኖሪያ አድራሻ፡-
   ዞን፡-............... ወረዳ፡-.................
   ቀበሌ፡-............. ጎጥ፡..................
IX. ቃለመጠይቅ የተካሄደበት ቦታ፡---------------------
X. ቃለመጠይቅ የተካሄደበት ቀን፡-----------------------
   ዕለት፡-................ ሠዓት፡------------------

XI. የጠያቂው ሙሉ ስም:--------------------------------

1. በአካባቢያችሁ የሕመም መንስኤ የሚባሉ ምን ምን ናቸው? (መናፍስት፣ ሰው፣ እንስሳት፣...)
2. መናፍስት ከሆኑ፤ ምን ዓይነት ባሕርይ አላቸው?
3. ምን ዓይነት ሕመም በየትኛው አጋንንት ይመጣል ተብሎ ይታመናል? (ለምሳሌ፤ ሾተላይ፣ ሥንፈተ ወሲብ፣ የወፍ በሽታ፣ የስኳር በሽታ፣...)
4. በአካባቢያችሁ ወቅትን ጠብቀው የሚነሱ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?
5. በአካባቢያችሁ ለሕመም መንስኤ አጋላጭ ሁነት/ድርጊት ምንድን ነው?
6. በአካባቢያችሁ ከበሽታ ለመጠበቅ/ለመፈወስ ምን ዓይነት እምነታዊ ሥርዓቶች ይፈፀማሉ?
7. ማኅበረሰቡ ስለበሽታ መንስኤና ፈውስ በሥነ ቃል (ተረት/አፈታሪክ/ቃል ግጥም) ምን ይላል?
8. ከሕመምተኛ በሽታን እንዴት ይለያሉ? (በማየት፣ በመጠየቅ፣ ኮከብ በመቁጠር...)
9. ምን ዓይነት የምርመራ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ? በመንፈሳዊ/በተዋርሶ (አዕጋረ ፀሐይ፣ አሾክሿኪ፣ ቆጵሪያኖስ፣ ሞርሞሪዮን፣ ከልከሊዎስ፣ ህልመ ዮሴፍ፣...) እና በዓለማዊ ተግባራት (በዕይታ፣ አካልን በመዳበስ፣...)
10. የጤና (የኃይል ሚዛን) መዛነፍ ሲያጋጥም ማስተካከያ ስልቶችምንድን ናቸው?
11. በምርመራ ሂደት የበሽታ ባሕርያትን እንዴት ይለያሉ?
12. ውስጣዊ ሕመምን ከውጫዊ የሰውነት አካል ምልክት እንዴት መለየት ይቻላል?
13. ውስጣዊና ውጫዊ ሕመምን ለመለየት ምን ዓይነት ፍተሻ/ሙከራ ያካሂዳሉ? (ለምሳሌ፤ ስኳር፣ ቁስል፣ ጉበት፣ ኪንታሮት፣ ስንፈተ-ወሲብ፣ ነቀርሳ...)
14. ዕፀ መድኃኒት ለመሰብሰብ ምን ዓይነት ቅድመ ዝግጅት ያደርጋሉ?
15. ዕፀ መድኃኒት ለመሰብሰብ የትኛውን ዐውድ (ቦታ፣ ወቅት፣ ቀን፣ ዕለት፣ ሠዓት...) ይመረጣሉ? ለምን?
16. በዕፀ መድኃኒት አቆራረጥና አሰባሰብ ሂደት ምን ዓይነት ሥርዓት-ገቢር ይፈፅማሉ? (ዕፀ መድኃኒትን ለማንገስ፤ ዕኩይ መናፍስትን ለመከላከል/ለመዋረስ)
17. በአካባቢያችሁ የዕፀ መድኃኒት ቅመማ እንዴት ይከወናል?
18. በአካባቢያችሁ የዕፅዋት ጣዕም፣ ባሕርያትና ምድብ አለ?
19. በአካባቢያችሁ የመድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ ሂደት እንዴት ይከወናል?

20. አዘጋጅተው ያስቀመጧቸውን መድኃኒቶች እንዴት ቀላቅለው ይጠቀማሉ? ለምን? (ማቀላቀል/መበረዝ)
21. ቀምመውና መጥነው የአዘጋጁትን መድኃኒት በምን ዓይነት መልክና ይዘት ለክተው፤ ለሕመምተኛ ይሰጣሉ?
22. በአካባቢያችሁ በመድኃኒት አሰጣጥ ሂደት "አድርግ/አታድርግ፤ብላ/አትብላ" የሚባሉ ትዕዛዞች ምን ምን ናቸው?
23. በአካባቢያችሁ ለመድኃት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን በየት ቦታ አልምተው ይጠቀማሉ?
24. በአካባቢያችሁ ዕፅዋትና እንስሳትን እንዳይጠፉ ምን ዓይነት ጥበቃና ጥንቃቄ ያደርጋሉ?
25. በአካባቢያችሁ ዕፅዋት የማይቆረጡበትና እንስሳት የማይገደሉበት ጥብቅ ቦታዎች ምን ምን ናቸው? ለምን?
26. በአካባቢያችሁ ምን ዓይነት ዕፅዋትና እንስሳትን ታቀርባላችሁ/ታርቃላችሁ? ለምን?
27. በአካባቢያችሁ በመጥፋት ላይ ያሉ ዕፅዋትና እንስሳት ምን ምን ናቸው? ለምን?
28. በአካባቢያችሁ ለዕፅዋትና ለእንስሳት መጥፋት ምክንያቱ ምንድን ነው ብለው ያምናሉ?

2.2 ቃለመጠይቅ፡- <u>ለዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች</u>

1. በአካባቢያችሁ የሕመም መንስኤ የሚባሉ ምን ምን ናቸው?
2. በአካባቢያችሁ ወቅት ለይተው፤ ዓመት ጠብቀው የሚከሰቱ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?
3. የሥነ ምህዳር ልዩነት ለምን ዓይነት  በሽታዎች መንስኤ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል?
4. ማኅበረሰቡ የበሽታ መንስኤ መናፍስት እንደሆኑ ያምናል፤ ይህ እሳቤ በዘመናዊ ሕክምና እንዴት ይታያል?
5. የአካባቢውን ማኅበረሰብ ለበሽታ የሚዳርጉ ሁነት/ድርጊት ምን ምን ናቸው?
6. የባህል ሐኪሞች የምርመራ ዘዴ መንፈሳዊና ዓለማዊ ተግባራትን ያካትታል፤ ይህ ተግባር በዘመናዊ ሕክምና እንዴት ይታሰባል?
7. ውስጣዊ ሕመምን፤ ዉጫዊ የሰውነት አካል ላይ በሚታይ ምልክት መለየት ይቻላል? ከተቻለ፤ በምሳሌ ቢያስረዱ፤
8. ማኅበረሰቡ ከሕመም ለመፈወስ/ለመጠበቅ እምነታዊ ሥርዓትን ይፈጽማል፤ ከጤና፣ ከሕመምና ከበሽታ አንጻር እንዴት ይታያል?
9. ምን ዓይነት በሽታዎች በባህል ሕክምና ይድናሉ/ጉዳት ይደርሳል ተብሎ ይታሰባል?
10. ለባህል ሕክምና ሥርዓትና ተግባር ምን አስተያየት አሎዎት?

2.3 ቃለመጠይቅ፡- <u>ለማኅበረሰቡ አባላት</u>

- ለባህል ሕክምና ተጠቃሚዎች/ታካሚዎች፣
- ለሃይማኖት አባቶች፤ ለአካባቢው ሽማግሌዎች/እናቶች
- ለአካባቢው ወጣቶች/ የባህል ሕክምና ተጠቅመው ለማያውቁ ግለሰቦች

1. በአካባቢያችሁ የሕመም መንስኤ ምን ምን ናቸው ተብሎ ይታሰባል?
2. በአካባቢያችሁ ከሕመም ለመፈወስ /ለመጠበቅ ምን ዓይነት እምነታዊ ሥርዓት ይፈጸማል?
3. በአካባቢያችሁ ቦታ፣ ወቅትና ዓመትን ጠብቀው የሚነሱ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?
4. የአካባቢያችሁ ማኅበረሰብ ሕመም ሲያጋጥማቸው የት ቦታ ይሄዳሉ?
5. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለምን ዓይነት ሕመም ተመራጭ ናቸው ይባላል?
6. በአካባቢያች ማኅበረሰብ በሽታ/"መቅሰፍት" ያመጣሉ ተብሎ የሚፈሩ ተግባራት ምን ምን ናቸው? (ሃይማኖታዊ በዓላትን መሻር፣ በአጉል ሠዓት መንቀሳቀስ፣ ልማዳዊ እምነቶችን አለማክበር፣ የምግብ ዓይነቶች፣ እንስሳት፣ ዕፅዋት...)
7. የአካባቢያችሁ ማኅበረሰብ ምን ዓይነት እንስሳት እና ዕፅዋትን... ይፈራል/ያቀርባል?
8. በአካባቢያችሁ ማኅበረሰብ "የበሽታ" ሽኝት ልማድ ካለ ቢያስረዱኝ?
9. በአካባቢያችሁ "የሐበሻ መድኃኒት" ከተሰጠ በኋላ ምን አድርግ/አታድርግ ይባላል?
10. ስለ"ሐበሻ መድኃኒት" ተግባር ማኅበረሰቡ በሥነ ቃል (በቃል ግጥም/ተረት/አፈታሪክ...) ምን ይላል?

2.4 ቃለመጠይቅ፡- <u>ለተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች</u>

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሐብቶች ምን ምን ናቸው?
2. በአካባቢያችሁ የተፈጥሮ ሐብት በብዛት የሚገኙባቸው ቦታዎች ምን ምን ናቸው?
3. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለሥነ ምህዳር ደህንነት ምን አበርክቶ አላቸው?
4. ማኅበረሰቡ ምን ዓይነት ቦታዎችን፣ እንስሳትንና ዕፅዋትን ያቀርባል/ያርቃል? ለምን?
5. የማኅበረሰቡ እምነት/አምልኮ፤ ገዳማትና የሃይማኖት ቦታዎች የተፈጥሮ ሐብትን ለመጠበቅ ምን ዓይነት ሚና አላቸው?
6. በአካባቢያችሁ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣... ከሥነ ምህዳር ጋር ምን ዓይነት ትስስር አላቸው?

7. የትስስሩ ሂደት የተፈጥሮ ሚዛንን በመጠበቅ/ በማዛባት ምን ዓይነት ተግባር አለው?
8. በአካባቢያችሁ በመጥፋት ላይ ያሉ የተፈጥሮ ሐብቶች ምን ምን ናቸው? ለምን?
9. በአካባቢያችሁ የሥነ ምህዳር መዛባት ምን ዓይነት ተፅእኖ ያሳድራል?

2.5 ቃለመጠይቅ፡- <u>ለባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች</u>

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ዋና ዋና የመስኅብ ሐብቶች (ተፈጥሯዊ/ሰው ሰራሽ) ምን ምን ናቸው? ምን ዓይነት አገልግሎት አላቸው?
2. በአካባቢያችሁ ለሕክምና/ለፈውስ አገልግሎት (Medical Tourism) የሚውሉ የተፈጥሮ መስሕቦች ካሉ ቢጠቅሱ? (ፀበል፣ ፍል ውኃ፣ ተፈጥሯዊ "ጋዝ" ያላቸው የማዕድን ውኃ)
3. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ የባህል ሐኪሞች ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት አላችሁ?
4. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከዘመናዊ ሐኪሞች ጋር ተቀራርበው እንዲሰሩ ምን ተግባራትን ታከናውናላችሁ?
5. በአካባቢያችሁ ማኅበረሰብ "ለሕመም መንስኤ ናቸው" የሚባሉ ምን ምን ናቸው?
6. በአካባቢያችሁ ማኅበረሰብ ምን ምን ልማዳዊ እምነቶች ይፈፀማሉ? ተግባራቸውን ቢያስረዱኝ?
7. ማኅበረሰቡ ምን ዓይነት ዕፅዋትን፣ እንስሳትን... ያቀርባል/ያርቃል?
8. በአካባቢያችሁ ማኅበረሰብ ከባህል መድኃኒት፣ ሐኪም እና በሽታ ጋር በተገናኘ የሚነገሩ ሥነ ቃሎችን ቢገልፁ?

2.6 የመወያያ ጭብጥ፡- <u>ለተተኳሪ ቡድን ተወያይ አባላት የቀረቡ ይዘቶች</u>

**ቡድን አንድ፡- ለባህል ሕክምና ባለሙያዎች**

የሕመም መንስኤ፤ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ፣ ሥነ ምህዳር

**ቡድን ሁለት፡- ለዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች**

የበሽታ መንስኤ፣ ሥነ ምህዳርና የበሽታ ሥርጭት፣ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ሚና

**ቡድን ሶስት/አራት፡- ለአካባቢው ማኅበረሰብ አባቶች/እናቶች አባላት**

ባህላዊ እምነት፣ የሕመም መንስኤ፣ የባህል ሕክምና አጠቃቀም ልማድ፤ ሥነ ምህዳር፣

አባሪ ሶስት፡- <u>የውል ስምምነት</u>

እኔ ተማሪ ተመስገን በየነ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተማሪ ስሆን "የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ" በሚል ርዕስ ለ3ኛ ዲግሪ (PhD) ማሟያ የሚቀርብ ጥናት እየሰራሁ እገኛለሁ፡፡ የዚህ ጥናት ዐቢይ ትኩረት በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መንስኤ እና የምርመራ ዘዴን መግለጽ፣ የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ ሂደትን ማስረዳት፣ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ያለውን አበርክቶና ተግዳሮት መተንተን ነው፡፡ እርሶ የሚሰጡት መረጃ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ፤ ለትምህርታዊ ዓላማ እና ተግባር ብቻ የሚውል ነው፡፡ ይህም ስለሆነ እርሶ ፈቅደው የሚሰጡኝን መረጃ በማስታወሻ ደብተር፣ በመቅረፀ ድምፅ፣ በፎቶ ግራፍ እና በቪዲዮ ካሜራ እንድይዝ መልካም ፈቃድዎን እየጠየቅሁ፤ ለሚያደርጉልኝ ትብብር ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል እርሶ የሚስማሙበትን መርጠዉ ስምና ፊርማዎን በመጻፍ ፈቃድዎን እንዲያረጋግጡልኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ ለሚካሄደው ጥናት፡-

1. ሙሉ ስሜን፣ አድራሻዬን፣ በቃለመጠይቅ የሰጠሁትን መረጃ፣ የፎቶ ምስሌን... እንዲጠቀም፤ ሙሉ ፍቃዴን ሰጥቻለሁ፡፡
   ሙሉ ስም፡-................................ ቀን፡-.............. ፊርማ፡-.............. ቦታ፡-...........
2. ሙሉ ስሜን ቀይሮ በምስጢር እንዲጠቀም፣ በቃለመጠይቅ የሰጠሁትን መረጃ፣ የፎቶ ምስሌን፣... በቀጥታ እንዲጠቀም፤ ሙሉ ፍቃዴን ሰጥቻለሁ፡፡ ስም
   ሙሉ ስም፡-................................ ቀን፡-.............. ፊርማ፡-.............. ቦታ፡-...........
3. ሙሉ ስሜን፣ አድራሻዬን፣ በቃለመጠይቅ የሰጠሁትን መረጃ በምስጢር (ስም በመለወጥ) ይዞ እንዲጠቀም፤ ሙሉ ፍቃዴን ሰጥቻለሁ፡፡
   ሙሉ ስም፡-................................ ቀን፡-.............. ፊርማ፡-.............. ቦታ፡-...........

እኔ…………………………………. የተባልኩ መረጃ ሰጪ፤ በተራ ቁጥር…………. በተጠቀሰው ይዘትና አማራጭ የተስማማሁ መሆኔን በስሜና በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የተመራማሪው ስምና አድራሻ፡-

ተመስገን በየነ                    አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ                    2011 ዓ.ም

ስልክ ቁጥር፡ 0947089170

# አባሪ አራት፡- የመስክ መረጃ ሰጪዎች ዳራ

## ሀ. ዐቢይ መረጃ ሰጪዎች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | የመስክ መረጃ ሰጪዎች ስም | ፆታ[111] | ዕድሜ | መኖሪያ አካባቢ ወረዳ/ቀበሌ | መተዳደሪያ/ ሙያ | ቃለመጠይቅ የተከወነበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መሪጌታ ዘላለም ባየህ | ወ | 51 | ፋርጣ፤ስምና | የባህል ሐኪም | 20/04/2011 |
| | መሪጌታ ፋንታሁን ታዬ | ወ | 80 | ፋርጣ፤ወዋን መገራ | የባህል ሐኪም | 19/01/2011 |
| 3 | አቶ ጌጡ ነጋሽ | ወ | 56 | ፋርጣ፤ ክምር ድንጋይ ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 24/01/2011<br>20/06/2011 |
| 4 | መሪጌታ ባሕረጥበብ ደጀኔ | ወ | 48 | ፋርጣ፤ ጋሣይ ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 22/01/2011<br>27/02/2011 |
| 5 | ደብተራ መልኩ ዘለቀ | ወ | 53 | ፋርጣ፤ ስምና ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 22/01/2011<br>23/01/2011<br>01/03/2011 |
| 6 | አቶ ደሴ ገብሩ | ወ | 61 | ሊቦ ከምከም፤ አዲስ ዘመን 01 ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 25/01/2011<br>23/04/2011<br>03/07/2011 |
| 7 | መሪጌታ መኳሪ መስፍን | ወ | 54 | ሊቦ ከምከም፤ ሽና ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 27/01/2011<br>28/01/2011 |
| 8 | መሪጌታ አማረ አስፋው | ወ | 91 | ሊቦ ከምከም፤ ጣራ ገዳም | የባህል ሐኪም | 26/01/2011 |
| 9 | መሪጌታ ፍሬስብሃት ወንድይራድ | ወ | 52 | ሊቦ ከምከም፤ ይፋግ | የባህል ሐኪም | 29/01/2011<br>07/03/2011 |
| 10 | ሊቀጠበብት አብርሃም ዓለምነህ | ወ | 49 | ሊቦ ከምከም፤ ብራ አቦ | የባህል ሐኪም | 30/01/2011<br>05/03/2011 |

[111] ፆታ፡- ወንድ (ወ)፤ ሴት (ሴ) የሚሉ ፊደላትን ይወክላል፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | አቶ ደርሶ ገዜ | ወ | 59 | እብናት፣ እብናት 01 ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 03/02/2011<br><br>23/06/2011 ተቡው[112] |
| 12 | መሪጌታ ስዩም ዓለሙ | ወ | 77 | እብናት፣ ጀማን ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 04/02/2011<br><br>23/06/2011 ተቡው |
| 13 | መሪጌታ ስንታየሁ ሰሎሞን | ወ | 60 | እብናት፣ ኒቋራ ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 14/03/2011<br><br>23/06/2011 ተቡው |
| 14 | መሪጌታ መንግስቱ ጫቅሌ | ወ | 94 | እብናት፣ አቋሽሞች | የባህል ሐኪም | 11/04/2011 |
| 15 | ቄስ አብርሃም አክሊሉ | ወ | 39 | እብናት፣ እብናት 02 ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 01/05/2011<br><br>23/06/2011 ተቡው |

ማሣሰቢያ፡- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 በፋርጣ ወረዳ፣ ከ6-10 በሊቦ ከምከም ወረዳ፣ ከ11-15 በእብናት ወረዳ የሚገኙ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎችን (የባህል ሐኪሞች) ዝርዝር መግለጫ ይመለከታል፡፡

### ለ. አጋዥ መረጃ ሰጪዎች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | የመስክ መረጃ ሰጪዎች ስም | ፆታ | ዕድሜ | መኖሪያ አካባቢ ወረዳ/ቀበሌ | መተዳደሪያ/ ሙያ | ቃለመጠይቅ የተከወነበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መሪጌታ ብሩህ ዘላለም | ወ | 48 | ፋርጣ፣ ሰምና | የባህል ሐኪም እና የመንግሥት ሰራተኛ | 18/01/2011<br><br>18/06/2011 |
| 2 | መሪጌታ አዲሱ ጥላሁን | ወ | 56 | ፋርጣ፣ ክምር ድንጋይ ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 19/01/2011 |
| 3 | አቶ ሞላ ገብሬ | ወ | 48 | ፋርጣ፣ ጋሣይ ቀበሌ | የባህል ሐኪም እና የመንግሥት ሰራተኛ | 22/06/2011 |
| 4 | አቶ ሞገስ አየለ | ወ | 37 | ፋርጣ፣ ጋሣይ ቀበሌ | የባህል ሐኪም እና የመንግሥት ሰራተኛ | 22/06/2011 |
| 5 | መሪጌታ ልሳነወርቅ ገብሬ | ወ | 62 | ሊቦ ከምከም፣ ጣራ ገዳም | የባህል ሐኪም | 27/04/2011 |
| 6 | ወ/ሮ አበበች አሸናፊ | ሴ | 49 | ሊቦ ከምከም፣ ይፋግ | የባህል ሐኪም እና ግብርና | 26/04/2011 |
| 7 | ደብተራ ጥላሁን | ወ | 45 | ሊቦ ከምከም፣ አግታ | የባህል ሐኪም | 03/03/2011 |

[112] ተቡው፡- ተተኳሪ ቡድን ውይይት

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አስማማው | | | ቀበሌ | | |
| 8 | አቶ ታከለ ኅበዜ | ወ | 41 | ሊቦ ከምከም፤ ሽና ቀበሌ | የባህል ሐኪም እና ግብርና | 04/03/2011 |
| 9 | መሪጌታ መንግስቴ ተዘራ | ወ | 36 | እብናት፤ 01 ቀበሌ | የባህል ሐኪም፤ የአቋቋም መምህር | 10/03/2011 23/06/2011 ተቡው |
| 10 | መሪጌታ ሰረቀብርሃን ክንዴ | ወ | 72 | እብናት፤ ኒቋራ ቀበሌ | የባህል ሐኪምና ግብርና | 12/03/2011 |
| 11 | ደብተራ መኅሪ ተካልኝ | ወ | 38 | እብናት፤ አቋሽሞች | የባህል ሐኪም | 13/03/2011 |
| 12 | መሪጌታ በረከት መስፍን | ወ | 53 | እብናት፤ ኒቋራ ቀበሌ | የባህል ሐኪም እና ግብርና | 12/03/2011 |
| ለአካባቢው ማኅበረሰብ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ፤ ጤና መኮንኖች/ ባለሙያዎች | | | | | | |
| 13 | አቶ ፀሐዬ አሻግሬ | ወ | 30 | ፋርጣ፤ ጋሣይ ቀበሌ | የጋሣይ ጤና ጣቢያ አስተዳደር፤ የጤና መኮንን | 21/01/2011 |
| 14 | አቶ ግርማ ማናዬ | ወ | 32 | ፋርጣ፤ ክምር ድንጋይ ቀበሌ | የክምር ድንጋይ ጤና ጣቢያ አስተዳደር፤ የጤና መኮንን | 21/01/2011 |
| 15 | አቶ እሸቱ አማረ | ወ | 37 | ሊቦ ከምከም፤ አዲስ ዘመን ከተማ | በአዲስ ዘመን ጤና ጣቢያ፤ የጤና መኮንን/ባለሙያ | 22/04/2011 |
| 16 | ዶ/ር አስናቀ ግርማ | ወ | 42 | ደብረ ታቦር | ደብረ ታቦር የጤና ባለሙያ | 18/04/2011 |
| 17 | አቶ ዐባይ መላክ | ወ | 28 | እብናት፤ እብናት ከተማ | በእብናት ወረዳ ጤና ጣቢያ፤ የሥነ ተዋልዶ ቁጥጥር ባለሙያ | 30/05/2011 26/06/2011 ተቡው |
| ከአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት የባህል ሕክምና ተጠቃሚዎች | | | | | | |
| 18 | አቶ አስማማው ተሻገር | ወ | 69 | ፋርጣ፤ መገንዲ ቀበሌ | ግብርና | 20/06/2011 |
| 19 | እማሆይ ትኅደድ አስረስ | ሴ | 58 | ፋርጣ፤ አምኟዬ ቀበሌ | ግብርና | 20/06/2011 |
| 20 | ወ/ሮ ዳሣሽ ትዛዙ | ሴ | 30 | ሊቦ ከምከም፤ ደሪጣ ቀበሌ | ግብርና | 03/07/2011 |
| 21 | አቶ አረጋ ጋሹ | ወ | 45 | ሊቦ ከምከም፤ ሽና ቀበሌ | ግብርና | 23/04/2011 |
| 22 | ወ/ሮ ዉዲቱ ዐብዩ | ሴ | 25 | ሊቦ ከምከም፤ ውሻጥርስ ቀበሌ | ነጋዴ | 03/07/2011 |
| 23 | አቶ ምትኩ ሙጩ- | ወ | 42 | ሊቦ ከምከም፤ ሽና ቀበሌ | ግብርና | 28/01/2011 |
| 24 | ወ/ሮ ቅድስት ከተማ | ሴ | 26 | እብናት፤ እብናት 02 ቀበሌ | የኮሌጅ ተማሪ | 03/02/2011 |
| 24 | ወ/ሮ ምህረት ገበየሁ | ሴ | 41 | ሊቦ ከምከም አገላ ማንቶራ ቀበሌ | ግብርና | 08/03/2011 |
| 25 | አቶ አስማማው ተሻገር | ወ | 41 | እብናት፤ ኒቋራ ቀበሌ | ግብርና | 14/03/2011 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት የሃይማኖት አባቶች፣ ሽማግሌና እናቶች | | | | | | |
| 26 | እማሆይ ለተብርሃን ተሸመ | ሴ | 64 | ፋርጣ፤ ገንተኛ ቀበሌ | ግብርና | 21/06/2011 |
| 27 | ቄስ ማስረሻ አይተንፍሱ | ወ | 51 | ፋርጣ፤ ፋርጣ ቁስቋም ቀበሌ | ግብርና | 21/06/2011 |
| 28 | ወ/ሮ ጀማነሽ ሀብታሙ | ሴ | 46 | ሊቦ ከምከም፤ ውሻጥርስ ቀበሌ | ነጋዴ | 02/07/2011 |
| 29 | መሪጌታ ገብረመድኅን ኃይሉ | ወ | 42 | ሊቦ ከምከም፤ ዉሻጥርስ ቀበሌ | የቤተክርስቲያን ደብር አስተዳዳሪ | 25/04/2011 |
| 30 | ወ/ሮ ጠጁ ተዘራ | ሴ | 48 | እብናት፤ እብናት 02 ቀበሌ | ነጋዴ | 28/06/2011 |
| 31 | ቄስ ብርሃኑ አይቼው | ወ | 43 | እብናት፤ ኒቋራ ቀበሌ | ግብርና | 12/03/2011 |
| ከአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት የባህል ሕክምና ተጠቅመው የማያውቁ | | | | | | |
| 32 | ወ/ሮ ቃልኪዳን ተጫኔ | ሴ | 31 | ፋርጣ፤ ጋሣይ ቀበሌ | የመንግሥት ሰራተኛ | 21/04/2011 |
| 33 | ወ/ት ሽታዬ አላምረው | ሴ | 24 | ሊቦከምከም፤ ብር አቦ ቀበሌ | የኮሌጅ ተማሪ | 27/04/211 |
| 34 | አቶ መኮንን ማስረሻ | ወ | 26 | እብናት፤ እብናት 01 ቀበሌ | የመንግሥት | 29/04/2011 |
| ለአካባቢው ማኅበረሰብ የግብርና እና ተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ በመሆን የሚያገለግሉ | | | | | | |
| 35 | አቶ መልካሙ ቸርነት | ወ | 46 | ደብረ ታቦር | የደ.ጎ.ዞ. የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ | 17/04/2011 |
| 36 | አቶ ሰሎሞን ሹመት | ወ | 37 | ፋርጣ፤ ደብረታቦር | የዱር እንስሣትና ተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ | 18/04/2011 |
| 37 | አቶ ታደሰ አራጌ | ወ | 32 | ሊቦ ከምከም፤ አዲስ ዘመን ከተማ | የእርሻና ተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ | 23/04/2011 |
| 38 | አቶ አበባው ዋለ | ወ | 30 | እብናት፤ እብናት ከተማ | የዱር እንስሣትና ተፈጥሮ ሐብት ባለሙያ | 02/05/2011 |
| ለአካባቢው ማኅበረሰብ የባህልና ቱሪዝም ባለሙያ በመሆን የሚያገለግሉ | | | | | | |
| 39 | አቶ ሰሎሞን ካሣ | ወ | 34 | ደብረ ታቦር | የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ | 16/04/2011 |
| 40 | ወ/ሮ ሙሉ ክፍሌ | ሴ | 32 | ፋርጣ፤ ደብረታቦር | የፋርጣ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ | 16/04/2011 |
| 41 | አቶ አራጋው ዘውዴ | ወ | 26 | ሊቦ ከምከም፤ አዲስ ዘመን ከተማ | የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም /የፎክሎር/ ባለሙያ | 22/04/2011 |
| 42 | አቶ አዲሱ አዝመራ | ወ | 29 | እብናት፤ እብናት 01 | የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ | 25/06/2011 |

## ሐ. የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ዝርዝር መግለጫ

### ቡድን አንድ፡- የባህል ሕክምና ባለሙያዎች

### የመወያያ ርዕሰ ጉዳይ፡- የሕመም መንስኤ፤ የምርመራ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ፣ ሥነ ምህዳር

| ተ.ቁ | የመስክ መረጃ ሰጪዎች ስም | ፆታ | ዕድሜ | መኖሪያ አካባቢ ወረዳ/ቀበሌ | መተዳደሪያ/ ሙያ | ቃለመጠይቅ የተከወነበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መሪጌታ ስዩም ዓለሙ | ወ | 77 | እብናት፤ ጀማን ቀበሌ | የባህል ሐኪም | 23/06/2011 |
| 2 | መሪጌታ ስንታየሁ ሰሎሞን | ወ | 60 | እብናት፤ ኒቋራ ቀበሌ | የባህል ሐኪም | |
| 3 | አቶ ደርሶ ገዜ | ወ | 56 | እብናት፤ እብናት 01 ቀበሌ | የባህል ሐኪም | |
| 4 | ቄስ አብርሃም አክሊሉ | ወ | 39 | እብናት፤ እብናት 02 ቀበሌ | የባህል ሐኪም | |
| 5 | መሪጌታ መንግስቴ ተዘራ | ወ | 36 | እብናት፤ 01 ቀበሌ | የባህል ሐኪም፤የአቋቋም መምህር | |
| 6 | መሪጌታ ታደሰ ካሣሁን | ወ | 37 | እብናት፤ 02 ቀበሌ | የደብር አስተዳዳሪ፤ የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ | |

### ቡድን ሁለት፡- የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች

### የመወያያ ጭብጥ፡- የሕመም መንስኤ፣ሥነ ምህዳር እና የበሽታ ስርጭት፣ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ሚና

| ተ.ቁ | የመስክ መረጃ ሰጪዎች ስም | ፆታ | ዕድሜ | መኖሪያ አካባቢ ወረዳ/ቀበሌ | መተዳደሪያ/ ሙያ | ቃለመጠይቅ የተከወነበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አግንቼው ብርሃኑ | ወ | 33 | እብናት እብናት ከተማ | በእብናት ወረዳ ጤና ጣቢያ፤የፈቃድና ጤና ድርጅት ክትትል ኃላፊ | 26/06/2011 |
| 2 | አቶ ዐባይ መላክ | ወ | 29 | እብናት፤ እብናት ከተማ | በእብናት ወረዳ ጤና ጣቢያ፤ የሥነተዋልዶ ቁጥጥር ባለሙያ | |
| 3 | አቶ ኃሻው ጌቱ | ወ | 42 | እብናት፤ እብናት ከተማ | በእብናት ወረዳ የሥርዓተ ምግብና የሕፃናት ጤና ቁጥጥር ባለሙያ | |
| 4 | አቶ ደሳለኝ መንበር | ወ | 34 | እብናት፤ እብናት ከተማ | የእብናት ወረዳ ጤና ጣቢያ ምክትል ኃላፊ የጤና መኮንን | |
| 5 | አቶ መንገሻ አየለ | ወ | 48 | እብናት፤ እብናት ከተማ | በእብናት ወረዳ የማኅበረሰብ ጤና መረጃ ክትትል ባለሙያ | |

## ቡድን ሶስት:- የማኅበረሰብ አባላት

## የመወያያ ጭብጥ:- ባህላዊ እምነት፣ ሥነ ምህዳር፣ የሕመም መንስኤ፣ የባህል ሕክምና አጠቃቀም ልማድ፤

| ተ.ቁ | የመስክ መረጃ ሰጪዎች ስም | ፆታ | ዕድሜ | መኖሪያ አካባቢ ወረዳ/ቀበሌ | መተዳደሪያ/ ሙያ | ቃለመጠይቅ የተከወነበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቄስ ዐቢይ ዳመና | ወ | 48 | ፋርጣ፤ ወዋ ማገራ ቀበሌ | ግብርና | 19/06/2011 |
| 2 | አቶ ውለታው ዘገዬ | ወ | 65 | ፋርጣ፤ ወዋ ማገራ ቀበሌ | ግብርና | |
| 3 | ቄስ ካሳ ባዬ | ወ | 37 | ፋርጣ፤ ወዋ ማገራ ቀበሌ | ግብርና | |
| 4 | ግራጌታ ወንድማገኝ ኃይሉ | ወ | 63 | ፋርጣ፤ ወዋ ማገራ ቀበሌ | ግብርና | |
| 5 | አቶ ደመቀ ያለው | ወ | 70 | ፋርጣ፤ ወዋ ማገራ ቀበሌ | ግብርና | |
| 6 | ብላታ ጓዴ ዘገዬ | ወ | 76 | ፋርጣ፤ ወዋ ማገራ ቀበሌ | ግብርና | |
| ቡድን አራት:- ከእናቶችን ጋር የተካሄደ ውይይት | | | | | | |
| 1 | ወ/ሮ እታገኝ መኮንን | ሴ | 42 | ፋርጣ፤ ሰምና ቀበሌ | ግብርና | 19/06/2011 |
| 2 | ወ/ሮ የዛብ ወንዴ | ሴ | 45 | ፋርጣ፤ ሰምና ቀበሌ | ግብርና | |
| 3 | ወ/ሮ ብርቂ ሞላ | ሴ | 36 | ፋርጣ፤ ሰምና ቀበሌ | ግብርና | |
| 4 | እማሆይ ማርሸት በቀለ | ሴ | 58 | ፋርጣ፤ ሰምና ቀበሌ | ግብርና | |
| 5 | ወ/ሮ ብሬ ጎበዜ | ሴ | 50 | ፋርጣ፤ ሰምና ቀበሌ | ግብርና | |
| 6 | ወ/ሮ እመቤት አማረ | ሴ | 32 | ፋርጣ፤ ሰምና ቀበሌ | ግብርና | |
| 7 | ወ/ሮ ትጓደድ ይፍሩ | ሴ | 47 | ፋርጣ፤ ሰምና ቀበሌ | ግብርና | |

መረጃ ሰጪዎች፤ ወንድ 56፤ ሴት 20 በድምሩ 76።

አባሪ- አምስት:- በደቡብ ጎንደር ዞን፤ በባህላዊ እና በዘመናዊ ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና በሽታዎች (Top Ten Diseases)

1. በባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና በሽታዎች (Top Ten Diseases)፤ በባህል ሐኪሞች ምርጫ

ሀ/ በፋርጣ ወረዳ (ደ.ጋ):- የባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች (Top Ten Diseases) ዝርዝር፤

| ተ.ቁ | መሪጌታ ዘላለም ባየህ | መሪጌታ ፋንታሁን ታዬ | አቶ ጌጡ ነጋሽ | መሪጌታ ባሕረጥበብ ደጀኔ | ደብተራ መልኩ ዘለቀ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለእከክ (ለልክፍት) | ለቁርጥማት | ለወፍ (ጉበት) | ለመንስኤ እስኪት | ለወፍ (ጉበት) |
| 2 | ለወፍ (ለጉበት) | ለመንስኤ እስኪት | ለእከክ | ለወፍ (ጉበት) | ለጨጓራ |
| 3 | ለአስም በሽታ | ለእከክ (ልክፍት) | ለኮሶ ትል | ለስኳር በሽት | ለእከክ |
| 4 | ለመንስኤ እስኪት | ለጡት ነቀርሳ | ለቁርጥማት | ለእንግዴ ልጅ ማስወረጃ | ለአጥንት ስብራት |
| 5 | ለቁርጥማት | ለወፍ (ለጉበት) | ለሽንት ማጥ | ለቁርጥት | ለቁመኛ |
| 6 | ለስኳር | ለሆድ ሥራይ | ለኮሶ ትል | ለሾተላይ | ለአስም |
| 7 | ለነቀርሳ | ለስኳር | ለቁንጭር | ለአስም | ለከይሲ ቁስል (ነቀርሳ) |
| 8 | ለወስፋትና የኮሶ ትል | ለቁመኛ (በቁሙ የሚያከሳ) | ለመንስኤ እስኪት | ለነቀርሳ | ለጆሮ መግል |
| 9 | ለእጥልና ለጉንፋን፣ | ለፎረፎር፣ ለቋቁቻ | ለእንጥልና ለጉፋን | ለሽረሪት (አልማዝ ባለጭራ) | ለእባጭ (ብጉጅ) |
| 10 | ለዛር ውላጅ | ለእንጥል | ለጨጓራ | ለሚጥል በሽታ | ለእንጥል |

ምንጭ:- የፋርጣ ወረዳ የባህል ሐኪሞች፤ ኅዳር 2011 ዓ.ም።

ለ) በሊቦ ከምከም ወረዳ (ወይና ደጋ)፤ የባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች (Top Ten Diseases) ዝርዝር፤

| ተ.ቁ | አቶ ደሴ ገብሩ | መሪጌታ መኅሪ መስፍን | መሪጌታ አማረ አስፋው | መሪጌታ ፍሬስብሃት ወንድይራድ | ሊቀጠበብት አብርሃም ዓለምነህ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለዉሻ ከለባት | ለሸረሪት (ለአልማዝ ባለጭራ) | ለስንፈተ ወሲብ | ለኪንታሮት | ለኪንታሮት |
| 2 | ለችፌ ቁስል | ለወባ በሽታ | ለፎረፎር | ለወፍ (ለጉበት) | ለወፍ (ጉበት) |
| 3 | ለወር አበባ መዛባት | ለጎርምጥ | ለቆረቆር | ለሾተላይ | ለስንፈተ ወሲብ |
| 4 | ለወፍ (ለጉበት) | ለውሻ ከለባት | ለእጅ ሰብ | ለጨጓራ ሕመም | ለሪህ/ ለቁርጥማት |
| 5 | ለቁርጥማት (ሪህ) | ለወፍ (ለጉበት) | ለዓይን ጥላ | ለመፍትሔ ሥራይ | ለጎርምጥ ቁስል |
| 6 | ለራስ ፍልጠት | ለጅን ልክፍት (በወንዝ) | ለልፌ ቁስል | ለስንፈተ ወሲብ | ለድንገተኛ |
| 7 | ለእከክ (ለልክፍት) | ለስንፈተ ወሲብ | ለቁርጥማት | ለውሻ ከለባት | ለወባ በሽታ |
| 8 | ለጎርምጥ | ለችፌ ቁስል | ለሚጥል በሽታ | ለእንቅርት | ለውሻ ከለባት |
| 9 | ለመንስኤ እስኪት | ለቁርጥማት (ሪህ) | ለእንጥል | ለስኳር | ለኩላሊት |
| 10 | ለስኳር | ለራስ ፍልጠት | ለእከክ | ለደም ግፊት | ለልፌ |

ምንጭ፡- የሊቦ ከምከም ወረዳ የባህል ሐኪሞች፤ ኅዳር 2011 ዓ.ም፡፡

ሐ) በእብናት ወረዳ (ቆላ)፤ የባህል ሕክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች (Top Ten Diseases) ዝርዝር፤

| ተ.ቁ | አቶ ደርሶ ገዜ | መሪጌታ ስዩም ዓለሙ | መሪጌታ ስንታየሁ ሰሎሞን | መሪጌታ መንግስቱ ጫቅሌ | ቄስ አብርሃም አክሊሉ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለወፍ (ጉበት) | ለኪንታሮት | ለቁመኛ (ለሚከሳ) | ለወባ በሽታ | ለቡዳ ቂም |
| 2 | ለጎርምጥ ቁስል | ለሞኝ ባገኝ | ለከይሲ ቁስል (ነቀርሳ) | ለስፈተ ወሲብ | ለወፍ (ለጉበት) |
| 3 | ለወባ በሽታ | ለወፍ (ለጉበት) | ለጎርምጥ | ለጡት ነቀርሳ | ለስንፈተ ወሲብ |
| 4 | ለወስፋትና ለኮሶ ትል | ለዛር ዉላጅ | ለወባ በሽታ | ለችፌ ቁስል | ለጨጓራ ሕመም |
| 5 | ለሽንት ማጥ በሽታ | ለኩላሊት | ለፎረፎር | በዉኃ ለሚነሳ ልክፍት | ለወባ በሽታ |
| 6 | ለልክፍት (እከክ) | ለአእምሮ ጭንቀት | ለቡዳ ቂም | ለኩላሊት | ለእከክ |
| 7 | ለኪንታሮት | ለውሻ ከለባት | ለውሻ ከለባት | ለሞኝ ባገኝ | ለሞኝ ባገኝ (ማንጅራት ገትር) |
| 8 | ለስኳር በሽታ | ለወንዝ ልክፍት (ለዉኃ) | ለኩላሊት | ለወስፋት | ለቋቁቻ |
| 9 | ለቆላ ቁስል | ለወባ በሽታ | ለድንገተኛ | ለባሩሌ (የእግር) ቁስል | ለፎረፎር |
| 10 | ለተቀማጥ በሽታ | ለሽንት ማጥ በሽታ | ለቆላ ቁስል | ለጎርምጥ ቁስል | ለደም ግፊት |

ምንጭ፡- የእብናት ወረዳ የባህል ሐኪሞች፤ ኅዳር 2011 ዓ.ም፡፡

2. በዘመናዊ ሕክምና፤ በ2010 ዓ.ም ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች (Top Ten Diseases) ዝርዝር፤

ሀ/ በፋርጣ ወረዳ ጤና ጥበቃ (ክምር ድንጋይ) ጽ/ቤት፤ በ2010 ዓ.ም ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች (Top Ten Diseases) ዝርዝር፤

| ተ.ቁ | የበሽታው አይነት | ጎልተው የታዩ በሽታዎች በቁጥር | ጎልተው የታዩ በሽታዎች በፐርሰንት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ የትኩሳት ሕመም/Acute febrile illness(AFI) | 532 | 18.44 | |
| 2 | የሣንባ ምች/Pneumonia | 364 | 12.62 | |
| 3 | ከፍተኛ የላይኛው መተንፈሻ አካል ብክለት/ Acute upper respiratory infections | 363 | 12.58 | |
| 4 | የላይኛው የጨጓራ ክፍል መላጥ/መፋቅ ሕመም/Dyspepsia | 354 | 12.27 | |
| 5 | የላይኛው የቆዳ ክፍል ብክለት (እከክ፣ ጭርትና ችፌ...)/ Infections of the skin and subcutaneous tissue | 324 | 11.23 | |
| 6 | ስብራት/መመታት (ጉዳትና መሰንጠቅ)/ Trauma (injury, Fracture) | 246 | 8.53 | |
| 7 | የአጥንት መጋጠሚያ እና የጡንቻ መገናኛ ሕመም/ Diseases of the musculoskeletal system and connective tissue | 236 | 8.18 | |
| 8 | ከፍተኛ የሳንባ (መተንፈሻ አካል) ሕመም/Acute Bronchitis | 192 | 6.6 | |
| 9 | ሌሎች ያልታወቁ እና ያልተገለጹ የዓይን ብክለቶች/Others or unspecified of eye infectious | 146 | 5.06 | |
| 10 | ጥገኛ የሆድ ውስጥ ተሕዋሲያን ትላትል/Helminthiasis | 128 | 4.44 | |

በፋርጣ ወረዳ ክምር ድንጋይ ጤና ጣቢያ ጽ/ቤት ከተረገጠ ማኅተም ሰነድ ጋር የተመሳከረ መረጃ፤ 2010 ዓ.ም።

ለ/ በሊቦ ከምከም ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት፤ በ2010 ዓ.ም ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች (Top Ten Diseases) ዝርዝር

| ተ.ቁ | የበሽታው አይነት | ጎልተው የታዩ በሽታዎች በቁጥር | ጎልተው የታዩ በሽታዎች በፐርሰንት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ የላይኛው መተንፈሻ አካል ብክለት/ Acute upper respiratory infections | 12098 | 18.21 | |
| 2 | ከፍተኛ የትኩሳት ሕመም/Acute febrile illness(AFI) | 9111 | 13.71 | |
| 3 | የላይኛው የጨጓራ ክፍል መላጥ/መፋቅ ሕመም/Dyspepsia | 7848 | 11.81 | |
| 4 | ጥገኛ የሆድ ውስጥ ተሕዋሲያን ትላትል/Helminthiasis | 6763 | 10.18 | |
| 5 | የሣንባ ምች/Pneumonia | 5899 | 8.88 | |
| 6 | ስብራት/መመታት (ጉዳትና መሰንጠቅ)/Trauma (injury, Fracture) | 5801 | 8.73 | |
| 7 | የላይኛው የቆዳ ክፍል ብክለት (እከክ፣ ጭርትና ችፌ...)/Infections of the skin and subcutaneous tissue | 5778 | 8.69 | |
| 8 | ሌሎች ያልታወቁ እና ያልተገለጹ ብክለቶችና ጥገኛ ተሕዋሲያን ሕመሞች/ Others or Unspecified infectious and parasitic diseases | 5352 | 8.05 | |
| 9 | የአጥንት መጋጠሚያ እና የጡንቻ መገናኛ ሕመም/ Diseases of the musculoskeletal system and connective tissue | 4538 | 6.83 | |
| 10 | የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን/Urinary tract infection | 3267 | 4.92 | |

በሊቦ ከምከም ወረዳ ጤና ጥበቃ ዋና ጽ/ቤት ከተረገጠ ማኅተም ሰነድ ጋር የተመሳከረ መረጃ፤ 2010 ዓ.ም።

ሐ/ በእብናት ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት፤ በ2010 ዓ.ም ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች (Top Ten Diseases) ዝርዝር፤

| ተ.ቁ | የበሽታው አይነት | ጎልተው የታዩ በሽታዎች በቁጥር | ጎልተው የታዩ በሽታዎች በፐርሰንት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የሣንባ ምች/Pneumonia | 3693 | 15.63 | |
| 2 | ከፍተኛ የትኩሳት ሕመም/Acute febrile illness(AFI) | 3492 | 14.78 | |
| 3 | ከፍተኛ የላይኛው መተንፈሻ አካል ብክለት/Acute upper respiratory infections | 3147 | 13.32 | |
| 4 | የላይኛው የጨጓራ ክፍል መላጥ/መፋቅ ሕመም/Dyspepsia | 3030 | 12.82 | |
| 5 | የላይኛው የቆዳ ክፍል ብክለት (እከክ፣ ጭርትና ችፌ...)/Infections of the skin and subcutaneous tissue | 2235 | 9.47 | |
| 6 | የአጥንት መጋጠሚያ እና የጡንቻ መገናኛ ሕመም/Diseases of the musculoskeletal system and connective tissue | 1803 | 7.63 | |
| 7 | የጭንቅላት ወባ/Malaria P. Falciparum | 1758 | 7.44 | |
| 8 | ጥገኛ የሆድ ውስጥ ተሕዋሲያን ትላትል/Helminthiasis | 1755 | 7.43 | |
| 9 | ስብራት/መመታት (ጉዳትና መሰንጠቅ)/Trauma (injury, Fracture) | 1569 | 6.64 | |
| 10 | የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን/Urinary tract infection | 1146 | 4.85 | |

በእብናት ወረዳ ጤና ጥበቃ ዋና ጽ/ቤት ከተረገጠ ማኅተም ሰነድ ጋር የተመሳከረ መረጃ፤ 2010 ዓ.ም፡፡

## አባሪ ስድስት፡- በባህል ሕክምና የበሽታ መለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት ናሙና

### በባህል ሕክምና የበሽታ መለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደትን የሚያሳይ ሰጠረዥ

| ተ.ቁ | የበሽታው ዓይነት | የበሽታ መለያ ዘዴዎች | የባህል መድኃኒት ግብዓት | | ለመድኃኒት ግብዓት የሚውል የዕፅዋት ክፍል፣ የእንስሳት አካል፣ የማዕድናት ዓይነት | የባህል መድኃኒት ቅመማ፣ ምጣኔ እና አሰጣጥ በአዋቂ ሰው[11] መጠን ልክ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለእከክ ቁስል[114] (ልክፍት) | ➢ ሰውነትን እየበላ ጣት፣ ብብትና ክንድን ማሳከክ፤<br>➢ ቆዳን መሰነጣጠቅና ዱቄት የመሰለ ብናኝ ማውጣት፤<br>➢ እትር እትር እያለ ዉኃ ማዘል፤ የቆዳ መሰንጠቅና መድማት፤<br>➢ የኑግ ፍሬ የሚመስል ጠባሳ መፍጠር፤ | ሀ | የገበር እንቧ | ፍሬና ሥር | የገበር እንቧይ ፍሬ እና ሥር አድርቆ፣ ወቅጦና ደቁሶ፤ ሶስት የሻይ ማንኪያ ዱቄት መጥኖ በቫዝሊን/በለጋ ቅቤ እየለወሱ እከክ በወጣበት ቆዳ ላይ ለአንድ ሳምንት ከፀሐይ ተከልሎ ጧትና ማታ መቀባት፤ |
| | | | ለ | የእንዶድ | ፍሬ እና ሥር | የእንዶድ ፍሬና ሥር አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ ሁለት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በለጋ ቅቤ ለውሶ ጧትና ማታ እያጠቡ መቀባት፤ ወይም እርጥቡን ጨቅጭቆ የቆሰለውን ቦታ እያጠቡ በቀን ሁለት ጊዜ እስከሚድን መቀባት |
| | | | ሐ | የጊዜዋ እና<br>የነጭ ሽንኩርት | ፍሬ | የጊዜዋና የነጭ ሽንኩርት ፍሬ አድርቆ፣ ወቅጦ፣ ሰልቆ፤ ሁለት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ለአምስት ቀን በለጋ ቅቤ/ ቫዝሊን ለውሶ ጧትና ማታ እያጠቡ መቀባት |
| | | | መ | ዲኚ እና ጨው | ዲኚና ጨው | ሁለት የሻይ ማንኪያ ዲኚ ዱቄት፤ ከግማሽ የሻይ ማንኪያ ጨው ጋር ቀላቅሎ በቫዝሊን ወይም በቅልጥም ስብ ደባልቆ ማታ ማታ እየታጠበ እስከሚድን መቀባት |
| | | | ሠ | የመቅመቆ | የመቅመቆ ሥር | የመቅመቆ ሥር አድርቆ፣ ወቅጦና ደቁሶ፤ ሁለት የሾርባ ማንኪያያ ዱቄት ላይ አንድ ፍሬ ነጭ ሽንኩርት ጨምሮ፤ መውቀጥና ማድረቅ በለጋ ቅቤ/ ቫዝሊን ለውሶ ከፀሐይ ተከልሎ ለአንድ ሳምንት ጧትና ማታ መቀባት |

113 ማሳሰቢያ፡- ከሚመለከታቸው (የባህል ሐኪሞች) ባለሙያዎች ውጪ፤ ይህ የባህል መድኃኒት ቅመማ፣ ምጣኔና አሰጣጥን ሥርዓት ተከትሎ በራስና በሰው ላይ መተግበር እና መፈተሽ ለአደጋ ያጋልጣል፡፡ የመድኃኒት ምጣኔና አሰጣጥ በአዋቂ ሰው ልክ ተመጥኖ የቀረበ ሲሆን፤ በደቡብ ጎንደር ዞን ከሚገኙ የባህል ሐኪሞች (ዐበይት መረጃ ሰጪዎች) ተሰብስቦና ተደራጅቶ የቀረበ ይዘት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

114 ይህ መረጃ ሲሰበሰብ (በ2011 ዓ.ም) የእከክ ወረርሽኝ በዞኑ ተከስቶ፤ በወረርሽኙ የተጠቁ ሰዎች በባህል ሕክምና ጣቢያ ተገኝተው ሕክምና ሲከታተሉ፤ በምልከታና በቃለ መጠይቅ መገንዘብ ተችሏል፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ረ | የል[ድ]ግጣ | ፍሬ፣ ቅጠል፣ ቅርፊት እና ሥር | የድግጣ ፍሬ፣ ቅርፊት፣ ሥርና ቅጠል አድርቆ፣ ወቅጦና ደቁሶ፤ ሶስት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በለጋ ቅቤ/ቫዝሊን ለውሶ ለአንድ ሳምንት ጧትና ማታ መቀባት |
| | | | ሰ | የአዞ ሃረግ፤<br>የዕፀ እየሱስና<br>የጤና አዳም | ቅጠላቸውን | ቅጠላቸውን አድርቆ ወቅጦና ደቁሶ ሁለት የሻይ ማንኪያ ዱቄት በለጋ ቅቤ/ቫዝሊን ለውሶ ጧትና ማታ ቁስሉን እያጠቡ ለአምስት ቀን መቀባትና ተጠንቅቆ ማሰር፤ ጤነኛ አካልን ይጎዳል፤ |
| | | | ሸ | የብሳና | ፍሬ እና ቅጠል | የብሳና ፍሬና ቅጠል አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ፤ ሶስት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ላይ አንድ ነጭ ሽንኩርት ጨምሮ በለጋ ቅቤ ለውሶ ጧትና ማታ መቀባት፤ ከፀሐይ መከለል። |
| | | | ቀ | የቀበርቾና<br>የገበር እንቧይ<br>የአባሎና<br>የድግጣ ፍሬ | ሥር<br>ፍሬ | የቀበርቾና የገበር እንቧይ ሥር አድርቆ፣ ወቅጦና ደቁሶ አንድ የሻርባ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ የአባሎና የድግጣ ፍሬ ቆልቶና አሳርሮ፤ ወቅጦና ሰልቆ ሁለት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ ሁለቱን ዱቄት ቀላቅሎ፤ በለጋ ቅቤ እየለወሱ ጧትና ማታ ለአምስት ቀን መቀባትና ከፀሐይ መከለል፤ |
| | | | በ | የአቱች፣ የአዞ ሃረግ፣ የበለስ<br>የፌጦ እና<br>የጎመን ዘር | ቅጠላቸውን<br>ፍሬ | ከአቱች፣ ከአዞ ሃረግ እና ከበለስ ቅጠል ዱቄት አንድ አንድ የሻይ ማንኪያ በማዋጣት፤ ከፌጦና ከጎመን ዘር ዱቄት ግማሽ ግማሽ የሻይ ማንኪያ በማዋጣት መደባለቅ፤ በቫዝሊን/በለጋ ቅቤ ከፀሐይ ተከልሎ እስከሚድን ጧትና ማታ መቀባት፤ |
| 2 | ለኪንታሮት | በእጅ፣ በውስጥ እግር፣ በእራስ ቅል፣ በፊት ገፅ፣ በፊንጢጣ እና በተለያዩ የሰውነት ቦታዎች ላይ በመውጣት እብጠት ይፈጥራል፤ ሰውነትን ሰርስሮ ይገባል፤ እየባሰ ሲሄድ የደም ሥርን ይሰበስባል፤ ሰውነት ያደርቃል፤ | ሀ | የሞይደር፣<br>የሃረግ ሬሳ፣<br>የአዞ ሃረግ<br>እና<br>የሴት ቀስት | ቅጠላቸውን | ቅጠላቸውን አድርቆ፣ ደቁሶ አንድ የሻርባ ማንኪያ ዱቄት በለጋ ቅቤ/ዘይት/ቫዝሊን ለውሶ ለሁለት ቀን ማሰር/ማሸግ፤ ቦታው ሲላላ በቤሳ ሰንጥቆ ማውጣት፤ በነጭ ሽንኩርት፣ በጨውና በድኝ ቁስሉን ማጠብና ዱቄቱን ነስንሶ ማሰር፤ ክትትል ያስፈልጋል፤ |
| | | | ለ | የዕፀ ሳቤቅ፤ የሞይደር ሃረግ፣የቁራ ሃረግ | ቅጠላቸውን | ቅጠላቸውን አድርቆና ወቅጦ፤ ሁለት የሻይ ማንኪያ ዱቄት አዘጋጅቶ የበግ ላት ስብ አንጥሮ ከዱቄቱ ጋር ቀላቅሎ መቀባት/ ማሰር እስከሚረግፍ ድረስ ሳያቋርጡ መቀባት፤ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሐ | የልት፣<br>የጎርጠብ፣<br>የሰንሰልና<br>የጉሎ | ቅጠላቸውን | ቅጠላቸውን አድርቆ ወቅጦና ሰልቆ በለጋ ቅቤ/ በዶሮ ሥብ/በዘይት ለውሶ ማሰር እና መተኮስ ለቀላል ኪንታሮት እስከሚድን፤ |
| | | | መ | የምድር<br>እንባይ | ፍሬ | በእሳት ጠብሶ ማሰር ለቀላል ኪንታሮት |
| | | | ሠ | የልት | ሥርና ቅጠል | ዱቄት በለጋ ቅቤ/በወይራ ዘይት ተለውሶ እስከሚድን መቀባት |
| | | | ረ | የእሬት እና የቆለቆል | ልብ ፈሳሽ እና ወተት | አዋህዶ በኪንታሮት ላይ እስከሚድን መቀባት/ማሰር |
| | | | ሰ | በአዞ ሃረግ እና የጠለንዥ | ቅጠላቸውን | አድርቆና ወቅጦ ዱቄቱን በበግ ላት ሞራ ለውሶ መቀባት |
| 3 | ለጉበት "ወፍ" በሽታ | ➢ ዓይንና ጥፍር ቢጫ ማድረግ<br>➢ ማቅለሽለሽና ማስታወክ<br>➢ ምራቅና አክታ ማብዛት<br>➢ የምላስ ሰንበር መጥቆር<br>➢ የሽንት ቀለም መለወጥ<br>➢ የምላስ መንጣት<br>➢ መድከምና | ሀ | የምስርች፣<br>የድግጣ፣<br>የአዛምር | ቅጠላቸውን | ቅጠላቸውን አድርቆና ደቁሶ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ጣሳ ዉኃ አፍልቶና አጥሎ ሲቀዘቅዝ አንድ ብርጭቆ በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | ለ | የአቱች፣<br>የአህያ<br>ኮሽስሌ፣ ብሳና | ፍሬያቸውን | ፍሬያቸውን ወቅጦና ሰልቆ ሁለት የሻይ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ጣሳ ዉኃ ላይ ጨምሮ ማፍላትና ማተክተክ፤ ሲበርድ አንድ ብርጭቆ አጥልሎ ከአንድ ማንኪያ ማር ጋር ለውሶ ማጠጣት |
| | | | ሐ | እሬት | የእሬት ልብ ፈሳሽ | የእሬት ልብ ፈሳሽ አልቦና አጠራቅሞ ሁለት የሾርባ ማንኪያ ፈሳሽ ከአንድ የሾርባ ማንኪያ ነጭ ማር ጋር ለውሶ በአንድ ብርጭቆ ዉኃ በጥብጦ በባዶ ሆድ መጠጣት |
| | | | መ | የፍላጹትና<br>የሰንሰል | ቅጠል | የፍላጹትና የሰንሰል ቅጠልን ጨቅጭቆ በአንድ ጣሳ ዉኃ አፍልቶ ሲቀዘቅዝ አንድ ብርጭቆ ዉኃ አጥሎ፤ አንድ ማንኪያ ማር ለውሶ ለሶስት ቀን በባዶ ሆድ ማጠጣት፤ ተቅማጥና ትውከት ካመጣና ከተጣላ የዶሮ መረቅና ጉበት ማብላት |
| 4 | ለኮሶ ትል | ➢ ሆድ መንፋትና ማቅለሽለሽ<br>➢ የከንፈር መንጣት<br>➢ ከዓይነ ምድር ጋር የኮሶ ትል መውጣት | ሀ | የወገርት፣<br>የመተሬና<br>የደድሆ | ሥራቸውን | ሥራቸውን አድርቆና ወቅጦ ሁለት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከቀይ ጤፍ ቂጣ ጋር ደባልቆ መውቀጥ፤ ጭብጦውን በባዶ ሆድ ማብላት እስከ ስድስት ሠዓት ምግብ አይበላም፤ ሆድ ከተጣላ ማርከሻ ቡና መጠጣት፤ |
| | | | ለ | የኮሶ ዛፍ | ፍሬና ሥር | የኮሶ ዛፍ ፍሬና ሥር አድርቆና ወቅጦ ሁለት የሾርባ ማንኪያ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ➢ ክብደት መቀነስ/የሆድ መቆዘር<br>➢ ፊንጢጣን በማሳከክ ብቻውን መውጣት<br>➢ እየባሰና እየበዛ ሲሄድ በአፍንጫ መውጣት ይከሰታል | | | | ዱቄት በድፍድፍ ለውሶ ማጠጣት፤ በሽሮ ፈትፍቶ መስጠት፤ |
| | | | ሐ | የእንዳሁላ | ቅጠልና ሥር | የእንደሁላ ቅጠልና ሥር አድርቆና ወቅጦ አንድ የሻይ ማንኪያ ዱቄት በቀይ ጤፍ ቂጣና ኑግ ደባልቆ መውቀጥና ለውሶ መብላት |
| 5 | ለስኳር በሽታ | ➢ የመራብ ስሜትና ምግብ መብላት<br>➢ የጥፍር መውለቅና የዓይን መፍዘዝ<br>➢ የስኳር ጣዕም በታማሚው ሽንት ውስጥ መገኘት<br>➢ ክብደት መቀነስና መድከም<br>➢ ማላብና መጨነቅ<br>➢ ታካሚው ሰውነቱን ሲጠባ/ ሲመጥ የስኳር ጣዕም ማግኘት<br>➢ ታካሚው በጥቁር ድንጋይ ላይ ሽንቱን ማሸናት፤ ሲደርቅ ዱቄት/ ጨው የመሰለ ነጭ ምልክት በድንጋዩ ላይ መታየት፤ ንብ፣ ጉንዳን፣ ዝንብና የተለያዩ ነፍሳት ድንጋዩን ወረው መታየት፤ | ሀ | የእሬት<br>የቁልቋል | የእሬት ልብ<br><br>ጠፍጣፋ ግንድ | የእሬት ልብና እና የቁልቋል ጠፍጣፋ ግንድን ቀላቅሎ መጨቅጨቅ፤ በአንድ ጣሣ ዉኃ መበጥበጥና በንጹሕ ጨርቅ ማጥለል፤ በባዶ ሆድ በቀን አንድ ስኒ ለአስራ አምስት ቀን ጧት ጧት ማጠጣት፤ |
| | | | ለ | የምድር እንቧይ፣<br>የአቱች፣<br>ጊዜዋና ወይና ግፍት | ሥራቸውን | ሥራቸውን አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ አንድ የሻይ ማንኪያ ዱቄት፤ በአንድ ብርጭቆ ዉኃ አፍልቶ፤ አንድ የሾርባ ማንኪያ ነጭ ማር ጨምሮና አጥልሎ፤ በቀን አንድ ስኒ በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | ሐ | የመተሬ፣<br>የወይና ግፍት<br>የዶቅማ | ፍሬያቸውን | የመተሬ፣ የወይና ግፍት እና የዶቅማ ፍሬን አድርቆና ወቅጦ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በሁለት ብርጭቆ ዉኃ በጥብጦ ማፍላትና ማጥለል፤ በሁለት ሾርባ ማንኪያ ቀይ ማር ለውሶ በባዶ ሆድ አንድ ብርጭቆ ማጠጣት፤ |
| | | | መ | የአሚራ፣<br>የፍላጹት፣<br>የመቅመቆ | ሥራቸውን | ሥራቸውን አድርቆና ወቅጦ ሁለት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ጣሳ ዉኃ አፍልቶ፣ አብርዶና አጥልሎ፤ አንድ ብርጭቆ ጧት ጧት በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | ሠ | የስሚዛ፣<br>የፓፓያ፣<br>የጎርጠብ፣ | ቅጠላቸውን | የስሚዛ፣ የፓፓዬ እና የጎርጠብ ቅጠላቸውን አድርቆና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከሁለት ስኒ ወለላ ማር ጋር ደባልቆ በቀይ ጤፍ ቂጣ እና የኑግ ልጥልጥ ጋር ደብልቆ ጭብጦውን ማብላት፤ |
| 6 | ለሆድ ቁርጠት | ሆድ ቁርጠት | ሀ | የአቱች<br><br>የምድር እንቧይ | ሥር | የአቱች እና የምድር እንቧይ ሥር አድርቆ፣ ወቅጦና ደቁሶ አንድ የሻይ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ስኒ ቡና በጥብጦ ማጠታት |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለ | የወርቅ በሜዳ | ሥር | የወርቅ በሜዳ ሥር አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ፤ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ዱቅት፤ በአንድ ጣሳ ዉኃ አፍልቶና አጥልሎ አንድ ብርጭቆ ማጠጣት፤ ተቅማጥና ትውከት ከበዛ፤ በአቦል ቡና ማርከስ ነው፤ |
| 7 | ለመንስኤ እስኪት | ብልቱ ለደከመ እና አልታዘዝ ለሚለው | ሀ | የግመሮ፤ የጋንቤሎ፣ የሙት አንሳ ሃረግ እና የዳማ ከሴ | ሥራቸውን | የግመሮ፣ የጋንቤሎ፣ የሙት አንሳ ሃረግ እና የዳማ ከሴ ሥራቸውን አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ፤ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ ከአንድ ብርጭቆ ብርዝ ጋር ቀላቅሎ ማጠጣት፤ ትውከትና ተቅማጥ ካለው የዶሮ መረቅ ማጠጣት፤ |
| 8 | ለጨንራ | ደረት መፋቅ፤ የሆድ መለብለብ፣ ድርቀት እና በእንቅልፍ ሠዓት ማቃጠል፤ ቃር<br>የምግብ አለመፍጨት | ሀ | የፓፓዬ<br>የዱባ<br>የተልባ | ፍሬያቸውን | የፓፓዬና የዱባ ፍሬ ጭማቂ አንድ ብርጭቆ፤ ሁለት ሾርባ ማንኪያ የተልባ ዱቄት፤ በአንድ ላይ ለውሶና ደባልቆ ለሶስት ቀን በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | ለ | የሳማ | ቅጠል | የሳማ ቅጠል ቀቅሎ እንደ ወጥ ሰርቶ በእንጀራ ማብላት |
| | | | ሐ | የእሬት<br>የአልቴት<br>የከረቤ | ልብ<br>ፍሬ<br>ልቡጫ(እጣን) | የእሬት ልብ አውጥቶ ጨቅጭቆ፤ አንድ የሻይ ማንኪያ የአልቴትና ከረቤ ዱቄት ጨምሮ አዋህዶ በአንድ ብርጭቆ ዉኃ በጥብጦ በባዶ ሆድ በቀን አንድ ግዜ ማጠጣት |
| 9 | ለቡዳ | ድካም፤ እራስን ስቶ መውደቅና መደፋደፍ፤ መጮህ፤ አእምሮ መናወጥ፤ መረጋጋትን መንሳት | ሀ | የግመሮ፤ የግዜዋ፣ የጅባራ፣የጥን ዡት፣የምድር እንቧይ፤ የጅብና የሙጨጭላ | ሥራቸውን<br>የጅብ ጉበት፣ ቆዳ<br>የሚጨጭላ ሥጋ | ሥራቸውን አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ፤ አንድ የሻይ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ የጅብ ቆዳ፤ የጥቁር ሙጨጭላ ሥጋን አድርቆ፣ ወቅጦ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ ሁለቱን ደባልቆ ማጠንና ማሸተት፤ |
| | | | ለ | ጤና አዳም፣ ነጭ ሽንኩርት፣ የምድር እንቧይ ወርቅ በሜዳ | ፍሬ/ፍሬ<br>ሥር<br>ሥር | የጤና አዳም እና የነጭ ሽንኩርት ፍሬ አድርቆ፣ ፈጭቶና ሰልቆ አንድ የሻይ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ የምድር እንቧይና የወርቅ በሜዳ ሥር አድርቆ፣ ወቅጦና ፈጭቶ፤ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ ሁለቱን ቀምሞ በአፍንጫ ማሸተት፤ ወይም አንድ የሻይ ማንኪያ ዱቄት በማር ለውሶ አንድ ስኒ ማጠጣት፤ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ለእጀ ሰብ | በሰው እጅ የተጣሉ፤ በእርኩሳን መናፍስት የሚነሳ፤ | ሀ | ጤና አዳም<br>ፌጦና ጊዜዋ፤<br>አልቴትና ነጭ ሽንኩርት፤ዲኚ | ፍሬያቸውን<br>ማዕድን | ፍሬያቸውን አድርቆ፣ ወቅጦና ደቁሶ፤ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት እና ግማሽ የሻይ ማንኪያ ዲኚ በማዘጋጀት፤ ሁለቱን ቀላቅሎ በለጋ ቅቤ ለውሶ ማታ ማታ ተቀብቶ ማደር፤ ዱቄቱን ማጨስ፤ |
| 11 | ለወባ በሽታ | ብርድ ብርድ ማለትና ማተኮስ<br>ማቃዠትና ማንቀጥቀጥ<br>ምግብ መከልከልና ማቅለሽለሽ | ሀ | የፓፓዬ | ቅጠል | የፓፓዬ ቅጠል ጭቅጭቆ፤ በአንድ ጣሳ ዉኃ በጥብጦና አጥሎ፤ አንድ ማንኪያ ማር ጨምሮ፤ አንድ ስኒ ጭማቂ ለሶስት ቀን ጧት ጧት በባዶ ሆድ ማጠጣት፤ ወይም ቅጠሉን ጨቅጭቆና ቀቅሎ አጥሎ፤ በተመሳሳይ መልኩ ማጠጣት፤ |
| | | | ለ | የስሚዛ፤የምድ ር እንቧይ፤ የመካን፤ እንዶድ | ሥራቸውን | ሥራቸውን አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ፤ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት፤ ከሁለት ማንኪያ ማር ጋር ደባልቆ፤ በአንድ ብርጭቆ ዉኃ በጥብጦ በባዶ ሆድ ማጠጣት፤ ተቅማጥና ትውከት ከበዛ ማርከሻ አቦል ቡና ማጠጣት፤ |
| 12 | ለሾተላይ | በተደጋጋሚ ጽንስ ማሶረድ<br>አጥንት ሆኖ በሆድ መክረም | ሀ | የጥንዡት፤<br>የሎሚ፤<br>የእቧጮ | ተቀጽላ | የሶስቱን ተቀጽላ አድርቆ፣ ወቅጦና ደቁሶ፤ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ማንኪያ ነጭ ማር ለውሶና አድቦልቦሎ በየወሩ ለሶስት ቀን ሶስት ፍሬ ማዋጥ፤ የመርበብተ ሰሎሞንን ጸሎት ማድረስ፤ |
| | | | ለ | የሙጨጭላ<br>የእስስት<br>የዘረጭ እንቧይ | ቆዳና ሥጋ<br>ሥጋና ቆዳ<br>ሥር | የሙጨጭላ እና የእስስት ቆዳና ሥጋ አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ አንድ የሻይ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ የዘረጭ እንቧይ ሥር አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ ሁለቱን ቀላቅሎ በኮመል ዕፅ ዉኃ ለውሶ በክታብ ሰፍቶ በአንገት ማሰር፤ |
| 13 | ለሙሸሮ ነቀርሳ (አንገት ላይ ለሚወጣ) | በቆዳ ላይ እንደ ችፌ እና እከክ በማሳከክ ይጀምራል፤ እየቆየ ሲሄድ አካልን እያሳበጠ፤ ቆዳን እየበላና እያሳሳ ወደ ውስጥ ይገባል፤ | ሀ | የእሬት<br>የወገርት፣<br>የመቅመቆ፣<br>ጥቁር አዝሙድ | ልብና ፈሳሽ<br>ሥር<br>ሥር<br>ዘይት | አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ዱቄት ማዘጋጀት፤ ከአንድ የሻይ ማንኪያ ጥቁር አዝሙድ ዘይት ጋር ለውሶ በቁስሉ ላይ ማሰር፤ ወይም በበግ ላት ሞራ ዘይት ለውሶ ቁስሉን ማሰር፤ ሲፈነዳ አንድ የሻይ ማንኪያ ዱቄትና የጥቁር አዝሙድ ዘይት ቀላቅሎ፤ በሁለት ማንኪያ ጣዝማ ማር ለውሶና በዉኃ በጥብጦ፤ በቀን አንድ ብርጭቆ ማጠጣት፤ |
| 14 | ለተቅማጥ | አጣዳፉና የሚያስምጥ እንደ ዉኃ የሚፈስ፤ ንፍጥና ደም ለቀላቀለ ተቅማጥ፤ | ሀ | የከረቤ<br>የፌጦ | ሙጫ/እጣን<br>ፍሬ | የከረቤ ሙጫ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ዱቄት፤ የፌጦ ፍሬ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ዱቆት ማዘጋጀት፤ እሩዝ የተቀቀለበትን ዉኃ አጠንፍፎ፤ አንድ ብርጭቆ ዉኃ በማዘጋጀት ዱቄቱን ጨምሮ መበጥበጥና ማጠጣት፤ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የእሩዝ | የእሩዝ ውኃ | |
| 15 | ለቁርጥማት | ወገብ፧ እጅና እግርን መቆርጠም፧ ጅማትና የመገጣጠሚያ አካል ሕለም | ሀ | የእንዳሁላ<br>ፍየለፈጅ<br>ጦስኝ | ቅጠላቸውን | የእንዳሁላ፣ የፍየለፈጅና የጦስኝ ቅጠላቸውን አድርቆ፣ ወቅጦና ሰልቆ፧ አንድ የሻይ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ማንኪያ ነጭ ማር ለውሶ፧ በአንድ ብርጭቆ ውኃ በጥብጦ ማጠጣት፧ ትዉከትና ማስመለስ ካለው፧ ማርከሻው ቡና ማጠጣት ወይም የዶሮ ጉበት ማብላት፧ |

ምንጭ፡- በደቡብ ጎንደር ዞን ከሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከነሐሴ 2010 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ በተካሄደ የመስክ ስምሪት ወቅት፧ በጥናት አቅራቢው (የመስክ ስምሪት ወቅት) ተሰብስበውና ተደራጅተው ለናሙና የቀረቡ ይዘቶች ናቸው። እነዚህ መረጃዎች ሲሰበሰቡ (ፋርጣ፣ ሊቦከምከምና እብናት)፧ ለአንድ በሽታ (ለእከክ፣ ለኮሶ ትል፣ ለነቀርሳ፣…) ከሰላሳ በላይ የዕፅዋት፣ የእንስሳትና የማዕድናት ግብዓት ዓይነቶችን በመጠቀም የባህል ሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ፧ ለማጤን ተችሏል።

## አባሪ ሰባት፡- የባህል ሐኪሞች እና የዕፀ መድኃኒት "ናሙና" ማሳያ ፎቶዎች

### 6.1 የባህል ሐኪሞች እና የጥናት አቅራቢውን የመስክ ቆይታ የሚጠቁሙ ፎቶዎች ናሙና



መሪጌታ ማኅሪ የዕፀ መድኃኒት ዓይነቶችን ለጥናቱ አቅራቢ ሲያስረዱ፤ (28/01/2011 ሊቦ ከምከም)



ሊቀጠበብት አብርሃም የዕፀ መድኃኒት ግብዓቶችን ከመስክ ሲሰበስቡና ለጥናቱ አቅራቢ ሲያስረዱ (30/01/2011 ሊቦ ከምከም)



አቶ ደሴ የዕፀ መድኃኒት ግብዓት ዓይነቶችን ለጥናቱ አቅራቢ ሲያስረዱ (25/01/2011 ሊቦ ከምከም)



መሪጌታ ፋንታሁን ለጥናቱ አቅራቢ የቃል መረጃ ሲሰጡ (19/01/2011 ፋርጣ)

## ማረጋገጫ (Declaration)

“የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር፤ በፎክሎር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት፤ ይህ ጥናት፤ ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ እና የራሴ ወጥ ስራ ሲሆን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ሕጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ተመስገን በየነ

ፊርማ፡- __________________

ቀን፡- ____________________